# የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች የህዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት

(የመጨረሻ ሪፖርት)

የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን

ታህሳስ 19 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE

## ማውጫ

**ምህፃረ-ቃላት** (Acronyms) 7

**መፍቻ** (Glossary) 8

**አጽህሮተ ሪፖርት** (Executive Summary) 11

**ክፍል አንድ፥ አጠቃላይ መግለጫ**

1.1. መግቢያ 20
1.2. የሪፖርቱ ዓላማ 22
1.3. የሪፖርቱ አደረጃጀት 22

**ክፍል ሁለት፥ የሽግግር ፍትህ ታሪካዊ ዳራ እና አስፈላጊነት**

2.1. የሽግግር ፍትህ ሂደት ዓለም-አቀፋዊ ተሞክሮ አጭር ምልከታ 24
2.2. የሽግግር ፍትህ ሂደት ተሞክሮ በኢትዮጵያ 24
2.3. በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት መተግበር አስፈላጊነት እና ወቅታዊነት 25
2.4. የሽግግር ፍትህ ሥርዓት አስፈላጊነትን የሚያጠናክሩ ተጨማሪ ወቅታዊ ኩነቶች 26
2.5. የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አስፈላጊነት 27

**ክፍል ሶስት፥ የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን መቋቋም**

3.1. የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን አሰያየም 28
3.2. የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን የስራ ኃላፊነት 28
3.3. የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን እና ፖሊሲ የማዘጋጀት ስራዎች የተመሩባቸው ሰነዶች 29

**ክፍል አራት፥ የሽግግር ፍትህ ምክክር አስፈላጊነት፣ የምክክሩ ሂደት እና ምክክሩ የተመራባቸው መርሆዎች አፈፃፀም**

4.1. የምክክር ሂደቱ አስፈላጊነት 31
4.1.1. ምክክር እንደ መብት 31
4.1.2. በሽግግር ፍትህ አውድ የሚኖረው ተጨማሪ ፋይዳ 32
4.1.3. የምክክር ሂደቱ በኢትዮጵያ ስር-ነቀል የፖሊሲ አወጣጥ ዘይቤን ስለማስተዋወቁ 33
4.2. ምክክር/ግብዓት የማሰበባሰብ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች፣ ምክክር የተካሄደባቸው ቦታዎች፣ የተሳተፉ ሰዎች እና የጊዜ ሰሌዳ 33
4.2.1. የቅድመ-ረቂቅ ፖሊሲ የምክክር እና የግብዓት ማሰባሰብ ሂደት ዋና ዋና ስራዎች 33
4.2.2. ምክክር/ግብዓት የማሰበባሰብ ስራ የተካሄደባቸው ቦታዎች የተመረጡበት መስፈርት 35
4.2.3. የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ መርሀ-ግብሮች እና የእለት ፕሮግራሞች ጊዜ ምጣኔ 39
4.3. የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ የተመራባቸው መርሆዎች ይዘት እና ዝርዝር አፈፃፀም 40
4.3.1. የሂደቱ አካታችነት፡ የተሳታፊ ሰዎች/ባለድርሻ አካላት ልየታ፡ መረጣ፡ ብዛት እና ስብጥር 40
4.3.1.1. የትኞቹ ሰዎች/የማህበረሰብ ክፍሎች ተለዩ? 41
4.3.1.2. የተሳታፊዎች ልየታና መረጣ ስነ-ዘዴ ምን ይመስል ነበር? 41
4.3.1.3. በየምክክር መድረኩ ላይ ምን ያህል ተሳታፊዎች እንዲኖሩ ተደረገ? 42

4.3.1.4. የምክክር መድረክ ተሳታፊዎች ስብጥር 46
4.3.1.5. በክልሎች ከሚገኙ ዩኒቨሲቲዎች የተመረጡ አስተባባሪዎች መረጣ፣ ሚና እና ስልጠና 46
4.3.1.6. በምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቶች ያጋጠሙ ውስንነቶች 48
4.3.1.7. በመድረኮቹ የተስተዋለው የማህበረሰቡ ከፍተኛ ቁጥር ተሳትፎ ልዩ እንደምታ 49
4.3.2. በምክክር ሂደቱ ላይ በነፃ ፈቃድ ስለመሳተፍ 49
4.3.3. የምክክር እና ግብአት ማሰባሰብ ሂደቱ ተጎጂ-ተኮር እይታን በማረጋገጥ ረገድ የተከተለው አሰራር 50
4.3.4. የምክክር እና ግብአት ማሰባሰብ ሂደቱ የፆታ እይታን በማረጋገጥ ረገድ የተከተለው ልዩ አሰራር 51
4.3.4.1. መርህ 51
4.3.4.2. ተመዛዛኝነት ያለው የፆታ ውክልና ለማረጋገጥ የተከናወነ የዝግጅት ስራ 51
4.3.4.3. ያጋጠሙ ውስንነቶች 51
4.3.5. የተሳታፊዎችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማረጋገጥ 52
4.3.5.1. መርህ 52
4.3.5.2. ተሳታፊዎችን በሽግግር ፍትህ ይዘት ላይ የማንቃት/ማሳወቅ ስራ 52
4.3.5.3. ተለዋዋጭ/አማራጭ የቋንቋ እና ትርጉም አገልግሎት አቅርቦት 54
4.3.5.4. የተሳታፊዎች የፕሌናሪ ውይይት እና የትኩረት ቡድኖች ውይይት መድረኮች ዝግጅት 55
4.3.5.5. ያጋጠሙ ውስንነቶች 55
4.3.6. ከጉዳት የመጠበቅ መብት 56
4.3.6.1. መርሁ ተፈፃሚ የሆነበት አግባብ 56
4.3.6.2. ያጋጠሙ ውስንነቶች 56
4.3.7. ደህንነት 57
4.3.7.1. የተደረጉ የጥንቃቄ ዝግጅቶች እና መርሆው ተፈፃሚ የሆነበት አግባብ 57
4.3.7.2. ከደህንነት ሁኔታ ጋር በተያያዘ ያጋጠሙ እክሎች 57
4.3.8. ግልፀኝነትን ስለማስፈን 58
4.3.8.1. ግልፀኝነትን ለማስፈን የተከናወኑ ዝግጅቶች እና የተፈፀሙ ሥራዎች 58
4.3.8.2. ያጋጠሙ ውስንነቶች 59
4.3.9. የሕዝብ ምክክር ግብዓቶችን በትክክል ስለመያዝ 59
4.3.9.1. የተከናወኑ የሰነዳ ስራዎች 59
4.3.9.2. ሰነዳን በተመለከተ አስተባባሪዎች የነበራቸው ሚና 60
4.3.10. የሂደቱ ገለልተኝነት፣ ነፃነት እና ተአማኒነት 60
4.3.10.1. መርህ 60
4.3.10.2. ገለልተኝነት፣ ነፃነት እና ተአማኒነትን ለማረጋገጥ የተከወኑ ሥራዎች 60
4.3.10.3. ሂደቱ ከፖለቲካ ጣልቃገብነት የተጠበቀበት ሁኔታ 61
4.3.11. የሀገር መሪነት/የህዝብ ባለቤትነት መርህ ተፈፃሚ የሆነበት አግባብ 61
4.3.11.1. የመርሆው አፈፃፀም 62
4.3.11.2. የአጋር አካላት ተሳትፎ እና ትብብር 63
4.3.11.3. የምክክር ሂደቶቹን የተከታተሉ አካላት እና የቀረቡ ምልከታዎች 63

## ክፍል አምስት: ከህዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቶች የተገኙ ግብአቶች የተሰበሰቡበት፣ የተደራጁበት እና የተተነተኑበት ሥነ ዘዴ


5.1. ከምክክር መድረኮችና ከባለድርሻ አካላት ግብዓት የተሰበሰበበት ስነ-ዘዴ 64
5.2. ከምክክር መድረኮች እና ባለድርሻ አካላት የተገኙ ግብዓቶች የተደራጁበት ስነ-ዘዴ 66
5.3. ከምክክር መድረኮች እና ባለድርሻ አካላት የተገኙ ግብዓቶች የተተነተኑበት ስነ-ዘዴ 68


## ክፍል ስድስት፡ ዋና ዋና ግኝቶች


6.1. በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ የተንፀባረቁ ዝርዝር ግኝቶች ይዘት 70
6.2. የወንጀል ተጠያቂነት፥ ክስ፡ ምርመራ እና የፍርድ ሂደትን በተመለከተ 70
6.2.1. የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል? 70
6.2.1.1. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 70
6.2.1.2. 'የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 77
6.2.1.3. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 80
6.2.1.4. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 81
6.2.2. በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል? 82
6.2.2.1. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 83
6.2.2.2. 'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' - አገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 92
6.2.2.3. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 97
6.2.2.4. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 97
6.2.3. የፍርድ ሂደትን ማን ያከናውነው? 98
6.2.3.1. መግቢያ 98
6.2.3.2. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 99
6.2.3.3. 'የፍርድ ሂደትን ማን ያከናውነው' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 108
6.2.3.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 113
6.2.3.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 114
6.2.4. የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው? 115
6.2.4.1. መግቢያ 115
6.2.4.2. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 116
6.2.4.3. 'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' – ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 124
6.2.4.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 129
6.2.4.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 130
6.3. እውነትን ማፈላለግ እና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት 130
6.3.1. መግቢያ 130
6.3.2. እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች ሊተገበሩ ይገባል? 130

6.3.2.1. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 131
6.3.2.2. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 139
6.3.2.3. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 143
6.3.2.4. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 143
6.3.3. እውነት የማፈላለግና እርቅ የሚመለከቱ ተግባራት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል? 144
6.3.3.1. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 144
6.3.3.2. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 155
6.3.3.3. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ ምክክሮች ማጠቃለያ 157
6.3.3.4. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 157
6.4. በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ምህረት 157
6.4.1. መግቢያ 158
6.4.2. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ መስፈርቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ? 158
6.4.2.1. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 158
6.4.2.2. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 161
6.4.2.3. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 163
6.4.2.4. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 163
6.4.3. ምህረት የመስጠት ሂደትን ማን ያከናውነው? 164
6.4.3.1. መግቢያ 164
6.4.3.2. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 164
6.4.3.3. የምህረት ሂደቱ በማን ሊከናወን ይገባል? - አገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 171
6.4.3.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ ምክክሮች ማጠቃለያ 175
6.4.3.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 176
6.5. ማካካሻ 176
6.5.1. መግቢያ 176
6.5.2. የማካካሻ ሂደት የትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል? 176
6.5.2.1. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 176
6.5.2.2. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 178
6.5.2.3. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 179
6.5.2.4. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 179
6.5.3. በማካካሻ ስርአት የትኞቹ የማካካሻ ዓይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው/ሊተገበሩ ይገባል? 179
6.5.3.1. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 180
6.5.3.2. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 182
6.5.3.3. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 182
6.5.4. የማካካሻ ሥርዓትን ማን ሊመራው ይገባል? 182
6.5.4.1. መግቢያ 183
6.5.4.2. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 183

6.5.4.3. 'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይምራው?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 189
6.5.4.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 193
6.5.4.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 193
6.6. ተቋማዊ ማሻሻያ 193
6.6.1. መግቢያ 192
6.6.2. 'በየትኞቹ ተቋማት ላይ ቅድሚያ በመስጠት የመለየት/የማጥራት ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል?' 194
6.6.2.1. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 194
6.6.2.2. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ ምክክሮች ማጠቃለያ 195
6.6.2.3. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 195
6.6.3. ተመሳሳይ ወንጀሎች/ጥሰቶች እንዳይደገሙ ምን እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል? 196
6.6.4. የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ? 197
6.6.4.1. መግቢያ 197
6.6.4.2. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 198
6.6.4.3. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 202
6.6.4.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ ምክክሮች ማጠቃለያ 206
6.6.4.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 206
6.7. የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር? 206
6.7.1. መግቢያ 206
6.7.2. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 207
6.7.3. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 218
6.7.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 223
6.7.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 224
6.8. በሽግግር ፍትህ ሂደት የባህላዊ ፍትህ ሥርአቶች ሚና ምን ይሁን? 224
6.8.1. አካባቢያዊ ወይም ሀገራዊ ሚና መጫወት የሚችሉ ተለይተው ሊጠቀሱ የሚችሉ ባህላዊ አሰራሮች 225
6.8.2. ባህላዊ አሰራሮች የትኞቹን ጉዳዮች ለመፍታት ሊተገበሩ ይችላሉ? 225
6.8.3. ባህላዊ ዘዴዎች እና እሴቶችን ለመጠቀም መደረግ የሚገባቸው ለውጦች/ማሻሻያዎች? 226
6.8.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ 228
6.8.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 229
6.9. በሽግግር ፍትህ ሂደት የክልሎች/ከተማ መስተዳደሮች ሚና ምን ይሁን? 230
6.9.1. መግቢያ 230
6.9.2. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ 230
6.9.3. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ 236
6.9.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ ምክክሮች ማጠቃለያ 238
6.9.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ 239
**ክፍል ሰባት፤ ማጠቃለያ** 240
**ክፍል ስምንት፤ የባለሙያዎች ቡድን ዋና ዋና ምልከታዎች እና ምክረ ሀሳቦች**

8.1. የወንጀል ተጠያቂነትን በሚመለከት 249
8.1.1. የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል? 249
8.1.2. የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል? 250
8.1.3. ክሶችን የሚመለከቱ ፍርድ ቤቶችን በሚመለከት 251
8.1.4. የምርመራና የክስ ተግባር ተቋማዊ አደረጃጀት 253
8.2. እውነት ማፈላለግ እና የእርቅ ተግባርን በተመለከተ 254
8.2.1. እውነትን የማፈላለግና የእርቅ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች/ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል? 254
8.2.2. የእውነት የማፈላለግ እና እርቅ ተግባር ተቋማዊ አደረጃጀት 255
8.3. በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት 256
8.3.1. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ መስፈርቶች 256
8.3.2. የምህረት መስጠቱ ሂደት ተቋማዊ አደረጃጀት 258
8.4. ማካካሻ 259
8.4.1. ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተጎጂዎች እና የማካካሻ ዓይነቶች 259
8.4.2. የማካካሻ ሥርዓት ተቋማዊ አደረጃጀት 260
8.5. ተቋማዊ ማሻሻያ 261
8.5.1. ቅድሚያ በመስጠት የመለየት እና ማጥራት ተግባራት የሚከናወንባቸው ተቋማት 261
8.5.2. የማሻሻያ ስራ ተቋማዊ አደረጃጀት 262
8.6. የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን 263
8.7. ባህላዊ የፍትህ ስርአቶች ሚና 263
8.8. የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ሚና 265
8.9. የፖሊሲ አፀዳደቅ እና የመንግስትና የባለድርሻ አካላት ሚናን በተመለከተ የቀረቡ ተጨማሪ ምክረ-ሀሳቦች 267

## ምህፃረ-ቃላት

| | |
|---|---|
| ተ.መ.ድ | የተባበሩት መንግስታት ድርጅት |
| ኢ.ሰ.መ.ኮ | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን |
| ኢ.ፌ.ዲ.ሪ | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ |
| ደ/ምዕራብ | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል |
| ደ/ብ/ብ/ሕ | ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል |
| አ.ኅ | የአፍሪካ ኅብረት |
| ሽ.ፍ.ፖ | የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ |
| CEHRO | Consortium of Ethiopian Human Rights Organization (የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ድርጅት ህብረት) |
| ECSOC | Ethiopian Civil Society Organizations Council (የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት) |
| IGAD | Inter-Governmental Authority on Development (የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ክልላዊ የልማት በይነ መንግሥታት ባለሥልጣን) |
| UNHCR | United Nation High Commission for Refugees (በተ.መ.ድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን) |
| UN WOMEN | The United Nations Entity for Gender Equality and Empowerment of Women |
| UNICEF | United Nations Children's Fund (በተ.መ.ድ የህጻናት መርጃ ድርጅት) |

## መፍቻ

| | |
|---|---|
| **ዓላባ፡-** | በሽግግር ፍትህ ሂደት ማእቀፍ ተግባራዊ የሚደረጉ ስልቶችን ወይም አምዶችን ማለትም የወንጀል ተጠያቂነት፣ እውነት ማፈላለግ፣ በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ምህረት፣ ማካካሻ፣ የሕግ እና ተቋማዊ ማሻሻያ፣ እና ከዚህ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ሀሳቦችን ለማመላከት ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው፤ |
| **ምህረት፡-** | ማለት በሕግ በግልጽ በሚደነገጉ ቅድመ-ሁኔታዎች ላይ ተመሥርቶ ለተወሰኑ አጥፊዎች የወንጀል ተጠያቂነትን በሚያስቀር አግባብ የሚሰጥ የሽግግር ፍትህ ዓላባ ነው፤ |
| **ማካካሻ፡-** | ማለት ወደነበረበት መመለስ እና መልሶ ማቋቋም፣ ካሳ፣ የማገገሚያ እርምጃዎች፣ ፈውስ፣ የመታሰቢያ ወይም የማስታወሻ ክንዋኔዎችን እና የአለመደገም ዋስትና ለማረጋገጥ የሚረዱ እርምጃዎችን የሚያካትት ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮችን የያዘ የሽግግር ፍትህ አምድ ነው፤ |
| **የፖሊሲ አማራጮች፡-** | ማለት የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን 'የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች' በሚል ርእስ ባዘጋጀው ሰነድ መሰረት በሀገር-አቀፍ ደረጃ ግብዓት ለማሰባሰብ እንዲረዱ የቀረቡ የተለያዩ የፖሊሲ አማራጮችን የሚያመላክት ነው፤ |
| **ግብዓት፡-** | ማለት በቀረቡት የፖሊሲ አማራጮች ላይ በሀገራዊ የውይይት መድረኮች ሂደት እና በፅሁፍ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተሰጠ ሀሳብ፣ አስተያየት፣ ምልከታ ወይም አማራጭን የሚያመላክት ነው፤ |
| **እውነት ማፈላለግ፡-** | ማለት የጉልህ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ በደሎች እና ኢ-ፍትሐዊነቶች መሠረታዊ ምክንያት፣ ሁነት፣ መጠን እና ዓይነት ተጎጂ-ተኮር እና እርቅን በሚያበረታታ መልኩ ለማፈላለግ፣ ለመለየት እና ይፋ ለማውጣት የሚረዳ የሽግግር ፍትህ ዓላባ ነው፤ |
| **ተጎጂ፡-** | ማለት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ስልታዊ፣ መጠነ-ሰፊ ወይም ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሰለባ የሆነ በተለይም የሕይወት፣ የአካል፣ የህሊና፣ የሥነ-ልቦና፣ የንብረት ወይም ሌላ ዓይነት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው ወይም ማህበረሰብን የሚመለከት ነው፤ |
| **ተፈናቃይ፡-** | ማለት በግጭት፣ በሰብዓዊ መብቶች ጥሰት፣ በሌሎች አውዶች ወይም በሚያስከትሏቸው ውጤቶች የተነሳ የኢትዮጵያን የግዛት ወሰን ሳያልፍ ከሚኖርበት ቤት ወይም ከመደበኛ የመኖሪያ ቦታው ከህግ አግባብ ውጪ ተገዶ እንዲሸሽ፣ እንዲለቅ ወይም ለቆ እንዲወጣ የተደረገ ማንኛውም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሰለባ ሰው ወይም ቡድንን የሚመለከት ነው፤ |
| **አጥፊ፡-** | ማለት የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ስልታዊ፣ መጠነ-ሰፊ ወይም ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የፈጸመ፣ ያስፈራራ፣ የጠነሰሰ፣ ያበረ ወይም በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም አድርጓል ተብሎ የሚጠረጠር ማንኛውም ሰው ነው፣ |
| **እርቅ፡-** | ማለት በግጭት ወይም በሌላ አውድ ማእቀፍ በተፈጸሙ በደሎች፣ ጥሰቶች እና ኢ-ፍትሀዊነቶች ምክንያት የተጎዱ ወይም የላሉ ማህበረሰባዊ ግንኙነቶች እና እሴቶችን፣ የተፈጠሩ አለመተማመኖችን፣ ጥላቻ እና ቅራኔዎችን፣ እንዲሁም ቁርሾዎች እና |

መገፋቶች የተሟላ መፍትሔ እንዲሰጣቸው በማድረግ ግንኙነቶቹ እና እሴቶቹ የሚጠገኑበትን፤ ጥላቻ፣ አለመተማመን እና መከፋፈል በአብሮነት፣ በመተባበር፣ በመተማመን፣ እና በመቻቻል እሴት የሚተካበትን ሂደት እና ሁኔታ በመፍጠር ማህበረሰባዊ ውህደት፣ የሕግ የበላይነት እና ዘላቂ ሠላም እንዲመጣ የሚያልም የሽግግር ፍትህ ሂደትና ግብን የሚያመላክት ፅንሰ-ሀሳብ ነው፤

**ፈውስ/እርካታ፡-** ማለት በማካካሻ ስርአት ማእቀፍ ተጎጂዎች ለደረሰባቸው ጉዳት ወይም የሰብዓዊ መብት ጥሰት በተገቢ መልክ ይፋ የማውጣት፣ ለደረሱ ጥሰቶት እውቅና የመስጠት እና በይፋ ይቅርታ የመጠየቅ፣ ተገቢ የመታሰቢያ እና ማስታወሻ ክንዋኔዎችን የማድረግ እና የቀጠሉ ተመሣሣይ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን የማስቆም እርምጃዎችን የሚያካትት ተግባር ነው፤

**ማገገሚያ፡-** ማለት ተጎጂዎች ከደረሰባቸው አካላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ጉዳት እና በደል የሚያገግሙበት፣ የሚጠገኑበት፣ የሕክምና፡ የሥነ-ልቦና ወይም የህግ ድጋፍ እና ሌሎች ለዚህ አላማ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሚያካትት የማካካሻ ዓይነት ነው፤

**አብዞኛው ቡድን/**
**ተሳታፊዎች፡-** ማለት ውይይት ካደረጉ ቡድኖች/ተሳታፊዎች በአንጻራዊነት 'ብዛት' ያለው ቁጥር የያዘ ቡድን/ተሳታፊዎችን የሚያመለክት ነው፤

**የተወሰኑ ቡድኖች/**
**ተሳታፊዎች፡-** ማለት ውይይት ካደረጉ ቡድኖች ውስጥ በአንጻራዊነት ከአብዛኛው ቡድን 'ያነሰ' ቁጥር የያዘ ቡድን ወይም ተሳታፊን የሚያመለክት ነው፤

**በጣም ጥቂት ቡድኖች/**
**ተሳታፊዎች፡-** ማለት በአንጻራዊነት ከተወሰኑ ቡድኖች ያነሰ ቁጥርን የያዘ ቡድን/ተሳታፊዎችን የሚያመለክት ነው፤

**የቅልቅል ቡድን፡-** ማለት ግብአቶችን በማሰባሰብ ማእቀፍ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እንዲይዝ ተደርጎ የተዋቀረ የትኩረት ቡድን ሆኖ በተለይም ከሴት እና ከወንድ ተጎጂ ቡድኖች ውጭ ያለ ቡድንን የሚመለከት ነው፤

**ጉልህ የሰብዓዊ መብት**
**ጥሰት፡-** ማለት መጠነ-ሰፊ፣ ስልታዊ ወይም ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የኢፌድሪ ሕገ-መንግስት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕጎች እና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ሕግ ማዕቀፍ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕግጋትን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች/ጥሰቶች ናቸው፤

**ከፍተኛ የወንጀል ተሳትፎ፡** ማለት ወንጀልን በመጠንሰስ፣ በማቀድ፣ በመምራት እና ወንጀሉ ከግብ እንዲደርስ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ማንኛውንም ድርጊት የሚፈጽም ከፍተኛ ተጠያቂነት ያለበት ጥፋት አድራጊን የሚያመላክት ነው፣

**ተቋማዊ ማሻሻያ፡-** ማለት ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲፈጸም ያደረጉ ወይም አስቻይ ሁኔታን የፈጠሩ ተቋማት፣ ሠራተኞቻቸው እና አሠራራቸው በተገቢ መንገድ በልየታ የማጥራት እና የማሻሻያ ተግባር በማከናወን ተመሣሣይ በደል እንዳይደገም የሚረዳ የሽግግር ፍትህ አምድ ነው፤

**ልዩ ትኩረት የሚሹ**

**የሕብረተሰብ ክፍሎች፡-** ማለት ሕጻናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እና ተፈናቃዮችን የሚያመለክት ነው፤

**ጾታዊ ጥቃት፡-** ማለት ጾታን መሠረት ያደረገ በተጠቂው ላይ ወሲባዊ፣ አካላዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ እና/ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያደርስ ወይም መሠረታዊ መብቶችን የሚገድብ ስልታዊ ወይም ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የሚፈጸም ወይም የተፈጸመ ጥሰት/ወንጀል ነው፤

**ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓት፡-** ከመደበኛው የፍትህ ሥርዓት የተለዩ እድሜ-ጠገብ እና ሀገር-በቀል በሆኑ ባህሎች፣ ትውፊቶች ወይም የእምነት እሳቤዎች ላይ በመመርኮዝ እና እውነትን፣ እርቅን ወይም ካሳን መሠረት በማድረግ ግጭቶችን እና አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚተገበሩ ሥርዓቶችን የሚመለከት ነው፤

**እውነትን (ቃልን) እንደ ማስረጃ አለመጠቀም**
(Use Immunity):- ማለት አጥፊ እውነት በማፈላለግ ሂደት እንዲሳተፍ ለማበረታታት ለእውነት ማፈላለግ አላማ አጥፊው የገለፀው ቃል እንደ ማስረጃ ጥቅም ላይ እንዳይውልበት የሚከለክል ጽንሰ-ሀሳብን የሚመለከት ነው፤

**ክልል፡-** ማለት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 47(1)(2) መሠረት የተቋቋሙ ክልሎችና የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

## አጽህሮተ ሪፖርት

### መግቢያ

በሀገራችን የተለያዩ ሀይሎች እርስ በርስ እና ከመንግስት ጋር ባደረጉት እና በሚያደርጉት ግጭት መነሻነት - እንዲሁም ከግጭት አውድ ውጭ በነበሩ ኩነቶች - በርካታ ዜጎች ሰፊና ተከታታይነት ላለው ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ መፈናቀል እና እንግልት መዳረጋቸውን የሚያመላክቱ በርካታ ሪፖርቶች ወጥተዋል።[1] በመሆኑም የሀገረ-መንግስቱን ግንባታ ከማሳለጥ፣ ዘላቂነቱን ከማረጋገጥ እና በሰብአዊ መብቶች እና የሕግ የበላይነት መሠረታዊ መርሆዎች ላይ የተዋቀረ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ማህበረሰብ ግንባታና ሽግግር እውን ከማድረግ አንጻር - የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን መቅረፅ እና ተግባራዊ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በኢትዮጵያ ተግባራዊ የሚደረገው የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ቀደም ሲል የተሰራ ጥናት ግኝትን፣[2] የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) እና የተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን ፅህፈት ቤት ጣምራ ምርመራ ውጤት ምክረ-ሀሳቦችን፣[3] እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት እና በህወሓት መካከል የተፈረመውን የሰላም

---

[1] የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፡ 'የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ አመታዊ ሪፖርት፡ ከሰኔ 2014-ሰኔ 2015 ዓ.ም'፡ ለኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ፡ አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

Ethiopian Human Rights Commission. 'Annual Report on the Human Rights Situation of Internally Displaced Persons in Ethiopia'. June 2021-June 2022. Addis Ababa. Ethiopia.

Human Rights Watch. 'Human Rights Watch World Report. Ethiopia.' 1995.

Amnesty International. 'Amnesty International Report. Ethiopia.' 1 January 1996.

ልዩ አቃቤ ህግ ጽፈት ቤት 'ደም ያዝለ ዶሴ : በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ወይም መንግስት አባላት በንፁሃን ዜጎች ላይ የተፈፀመ ወንጀል ዘገባ'. 2010.

Human Rights Watch. 'Collective Punishment War Crimes and Crimes against Humanity in the Ogaden area of Ethiopia's Somali Regional State'. 2008.

Human Rights Watch. 'Targeting the Anuak: Human Rights Violations and Crimes against Humanity in Ethiopia's Gambella Region'. Vol.17, No.3(A). March 2005.

Human Rights Watch. 'Suppressing Dissent: Human Rights Abuses and Political Repression in Ethiopia's Oromia Region'. Vol.17, No.7(A). 2005.

Human Rights Watch. 'Such a Brutal Crackdown: Killings and Arrests in Response to Ethiopia's Oromo Protests'. 2016.

Ethiopian Human Rights Commission/Office of the United Nations High Commissioner. Report on 'Human Rights Joint Investigation into Alleged Violations of International Human Rights, Humanitarian and Refugee Law Committed by all Parties to the Conflict in the Tigray Region of the Federal Democratic Republic of Ethiopia'. 2021.

Human Rights Watch and Amnesty International. 'We Will Erase You From This Land: Crimes Against Humanity and Ethnic Cleansing in Ethiopia's Western Tigray Zone'. 2022.

[2] የፍትህ ሚኒስቴር፡ የሽግግር ፍትህ በኢትዮጵያ: አሁናዊ ሁኔታ እና ቀጣይ አቅጣጫ (2014 ዓ.ም.)፡ ኢትዮጵያ

[3] የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት፡ 'በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትግራይ ክልል ውስጥ በተፈጠረው ግጭት ወቅት በሁሉም የግጭቱ ተሳታፊ አካላት ተፈጽመዋል የተባሉትን የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች፣ የሰብአዊነት እና የስደተኞች ሕግጋት ጥሰቶች በተመለከተ በጋራ ያካሄዱት የምርመራ ሪፖርት'፡ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም

*ሪፖርቱ በትግራይ ግጭት ወቅት ለተፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂነት ማስፈንን ጨምሮ የተሟላ እና ተበዳይ-ተኮር የሆነ የሽግግር ወቅት የፍትህ እና የሰብአዊ መብት አቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት ለመፍጠር ሀገሪቱ እንድትሰራ ምክረ-ሀሳብ አቅርቧል።*

ስምምነት[4] ይዘት መሰረት የሚያደርግ ሆኖ - ቀደም ሲል በተሞከሩ ሀገራዊ የሽግግር ፍትሕ ስራዎች ሂደት የታየውን ክፍተት የሚያርም፣ ተሳታፊዎችን ማዕከል የሚያደርግ፡ ከዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎችና ድንጋጌዎች ጋር የተሰናሰለ እና ለሀገራችን ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አውድ በሚስማማ መልኩ የሚቀረፅ መሆን አለበት። በተጨማሪም የሚዘረጋው የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ሁሉንም የሽግግር ፍትሕ ስልቶች በተናበበ እና በተቀናጀ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል።

## I. የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን መደራጀት

ከዚህ ዓላማ እና ሀገራዊ ፍላጎት በመነሳት 'የቅድመ ረቂቅ ፖሊሲ ሕዝባዊ ምክክሮች እና ግብዓት ማሰባሰብ' ሥራዎችን፣ 'የረቂቅ ፖሊሲ' እና 'የድህረ-ረቂቅ ፖሊሲ' ዝግጅት ተግባራትን የማከናወን ሙሉ ኃላፊነት የተሰጠው የሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን ህዳር 2015 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር እንዲደራጅ ተደርጓል። የባለሙያዎች ቡድኑ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በሽግግር ፍትህ እና ሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ላይ ምርምር ከሚያደርጉ ምሁራን፣ ከሰብአዊ መብት ተከላካይ ባለሙያዎች፣ ከጥብቅና እና ምክር አገልግሎት ዘርፍ፣ ከሲቪል ማህበረሰብ እና ከፖሊሲና እና ሕግ ማርቀቅ ባለሙያዎች የተውጣጡ 13 አባላትን ያካተተ ነፃ እና ገለልተኛ የሙያተኞች ስብስብ ነው።[5]

## II. 'የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች የሕዝብ ምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት' ዓላማ

ይህ 'የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች የሕዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት' ሁለት መሠረታዊ ዓላማዎች አሉት።

የመጀመሪያው ዓላማ - በሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ላይ በክልላዊ እና ሀገር-አቀፍ መድረኮች፣ እንዲሁም በፅሁፍ የተሰበሰቡ ግብዓቶችን በአግባቡ በማደራጀት እና በመተንተን ለሚዘጋጀው የሽግግር ፍትሕ ሀገራዊ ፖሊሲ ይዘት ግብዓት ሊሆኑ በሚችሉበት አግባብ መሰነድ ነው።

ሁለተኛው ዓላማ - በፖሊሲ አማራጮቹ ላይ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶችን፣ ማጠቃለያዎችን እና ምክረ-ሀሳቦችን ዝርዝር ለሕዝብ ይፋ በማድረግ - የሂደቱ ባለቤት የሆኑት የኢትዮጵያ ህዝብ፣ መንግስት፣ ባለድርሻ አካላት እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የአለም-አቀፉ ማህበረሰብ አባላት ሙሉ መረጃ እንዲኖራቸው ማስቻልና በዚህም የሂደቱን ግልፅነት፣ ተዓማኒነት እና ተቀባይነት ማረጋገጥ ነው።

## III. የሕዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሥራ ሂደት

በሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድኑ ከተከናወኑ የቅድመ ረቂቅ ፖሊሲ ተግባራት አንዱ እና ዋናው - በህዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ምዕራፍ የተሰሩ ሥራዎችን የሚመለከት ነው። የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ከመውጣቱ በፊት የሚከናወን የቅድመ-ፖሊሲ ማርቀቅ ሕዝባዊ ምክክር እና ግብዓት የማሰባሰብ ሥራ - የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱን እና ይህን ተከትሎ የሚወጣውን የሽግግር ፍትህ ሀገራዊ ፖሊሲ የህዝቡን የፍትህ፣ እውነት እና እርቅ ፍላጎት ያማከለ እና አውድ-ተኮር እንዲሆን ያደርጋል። የፖሊሲውን ተቀባይነት፣ ተአማኒነት፣ አሳታፊነት፣ አካታችነት እና ህዝባዊ ባለቤትነት ለማረጋገጥም አይነተኛ ሚና ይኖረዋል።

የባለሙያዎች ቡድኑ የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ስራውን በይፋ ከጀመረበት ከየካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ሁሉንም ክልሎች እና ሁለቱን የከተማ መስተዳድሮች ያሳተፈ

[4] Agreement for Lasting Peace Through a Permanent Cessation of Hostilities Between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Tigray Peoples Liberation Front (TPLF)
ይህ ስምምነት በአንቀጽ 10(3) ላይ የኢትዮጵያ መንግስት የተሟላ እና ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ፍትህ መተግበር እንዳለበት ያስቀምጣል።

[5] የሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን አባላት የሚከተሉት ናቸው፦ ዶ/ር ታደሰ ካሳ (ሰብሳቢ)፡ ዶ/ር ማርሸት ታደሰ፡ ዶ/ር ደመላሽ ሺፈራው፡ በላይሁን ይርጋ፡ ቃልኪዳን ደረጀ፡ ተጓዳ አለባቸው፡ እንቁ አሰናቀ፡ አዲስ ጌትነት፡ አዲ ደቀቦ፡ ምስጋናው ሙልጌታ፡ ሲሳይ አሰፋው፡ ቸርነት ተገኑ፡ ጠገነኝ ትርፌ፡

ክልላዊ እና ሀገር-አቀፍ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮችን አካሂዷል። እንዲሁም በልዩ ሁኔታ በተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ብቻ ያተኮሩ ተጨማሪ መድረኮችን አዘጋጅቷል። በሁለቱም ሂደቶች ከፍተኛ መጠን ያለው ግብዓት ለማሰባሰብ ችሏል።

በዚህ ሂደት በክልሎች እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በጥቅሉ 47 ህዝባዊ የምክክር መድረኮች፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ 11 የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተዋል። በተጨማሪም 22 የምክክር መድረኮች በባለሙያዎች ቡድኑ እና የውስን ማህበረሰብ ክፍል ድምፅን በሚወክሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና አጋር ተቋማት ቅንጅት ተካሂደዋል።

በነዚህ የምክክር ሂደቶች - የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የሽግግር ፍትህ ኤክስፐርቶች፣ ከሽግግር ፍትህ አላባዎች ጋር የተያያዘ የቀደመ ተሞክሮ ያላቸው ተቋማት/ባለሙያዎች፣ የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ተቋማት/ተወካዮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ የሚዲያ ባለሙያዎች፣ ሴቶች እና የሴቶች ማህበራት፣ አካል ጉዳተኞች፣ ህፃናት እና የህፃናት መብት አስጠባቂ ድርጅቶች፣ ወጣቶች እና የወጣት ማህበራት፣ የሠራተኞች እና የንግድ ማህበረሰብ ተወካዮች፣ የፍትህ አካላት እና የፀጥታ ዘርፍ ባለሙያዎች/ኃላፊዎች፣ የፌዴራል እና ክልል መንግስት ተቋማት ኃላፊዎች፣ እና አለም-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።

በተጨማሪም የግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱን ተጎጂ-ተኮርነት እና ጾታዊ ምልከታ ለማጠናከር ከተ.መ.ድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (UNHCR Ethiopia) እና ከUNWOMEN ጋር በመተባበር በተፈናቃዮች እና ሴቶች ላይ ብቻ ያተኮሩ የተለያዩ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ተዘጋጅተዋል።

ከምክክር መድረኮቹ የሚገኙ ግብዓቶችን ይበልጥ ለማጠናከርም በፍትሕ ሚኒስቴር የማህበራዊ ትስስር ገጽ፣ በባለሙያዎች ቡድኑ የኢ-ሜይል አድራሻ እና በባለሙያዎች ቡድኑ አባላት የኢ-ሜይል አድራሻ አማካኝነት ከግለሰቦች እና ከተለያዩ ተቋማት በርካታ የፅሁፍ አስተያየቶችን ለማሰባሰብ ተችሏል።

## IV. የሕዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሥራ የተከናወነባቸው ቦታዎች እና ተሳታፊዎች አመራረጥ

የሕዝብ ምክክር እና የግብዓት ማሰባሰብ መድረኮቹ በክልሎች እና በሁለቱ የከተማ መስተዳድሮች የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን ተግባራዊ በማድረግ እንዲከናወኑ ተደርገዋል። ምክክር የተካሄደባቸው ቦታዎች መረጣ - የክልሎቹን እና በየክልሉ የሚገኙ የዞን ከተሞችን ልዩ ሁኔታ፣ የሕዝብ ብዛት፣ ያለፉ ግጭቶችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ባህሪና መጠን፣ እንዲሁም ተደራሽነትን መሰረት በማድረግ - አስቀድሞ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ማሳያ/ቴምፕሌት መሰረት ተከናውኗል።

በተመሳሳይ የተሳታፊዎች ልየታ እና መረጣ የአካታችነት መርህን ተከትሎ - ተጎጂዎችን ማዕከል በማድረግ እና ሰብዓዊ መብት ተኮር በሆነ የአሠራር ሥርዓት - ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቴምፕሌት መሠረት ተካሂዷል። በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ ላይ ከሚሳተፉ ሰዎች ውስጥ ቢያንስ 50% የሚሆኑት ሴቶች እንዲሆኑ፡ እንዲሁም ከየመድረኩ አጠቃላይ ተሳታፊዎች ቢያንስ 60% የሚሆኑት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች እንዲሆኑ በማቀድ አንድ ወጥ የዝግጅት ሥራ ተሰርቷል። በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ ላይም 60 ሰዎች እንዲሳተፉ ጥሪ ተደርጓል።

በምክክር መድረኮቹ ላይ የሚገኙ ተሳታፊዎች - በምክክር እና በግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ ላይ ነጻ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና ሂደቱም ገለልተኛ እና ተአማኒ እንዲሆን ለማስቻል - በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ ላይ በሽግግር ፍትሕ ጽንሰ-ሀሳብ ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለጻ ተደርጓል። ገለፃውም በተቻለ መጠን አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ሊረዱት በሚችል ቋንቋ እንዲቀርብ ተደርጓል።

በየክልሎቹ በተከናወኑ የምክክር መድረኮች ተሳታፊዎችን የመምረጥ እና የውይይት ሂደቱን የማስተባበር ስራ - ምክክሮቹ በተከናወኑበት አካባቢ በሚገኙ የዩኒቨርሲቲ መምሕራን እና የተወሰኑ ተመራቂ ተማሪዎች አማካኝነት ተሳልጧል። የምክክር መድረኮቹ ተሳታፊዎች ያለምንም ፍርሃትና መሸማቀቅ ሃሳባቸውን በነፃነት መግለጽ እንዲችሉ ለማድረግ - የሚካሄዱባቸው ቦታዎች (የተሳታፊዎች ማረፊያ እና መድረኮቹ) ከመንግስት ይዞታና መዋቅር ውጭ በሆኑ የግል ሆቴሎች ብቻ እንዲከናወኑ በማድረግ አስፈላጊ የጥንቃቄ እና የዝግጅት ሥራዎች ተሰርተዋል።

## V. ግብዓቶችን ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀት እና ለመተንተን የተተገበሩ ስነ-ዘዴዎች

በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ላይ - በክልል እና በሀገር-አቀፍ ደረጃ በተደረጉ የምክክር መድረኮች ግብዓት ለማሰባሰብ የተመረጠው ዋነኛው ስነ-ዘዴ አይነታዊ ዘዴ (Qualitative Method) የተሰኘው የግብዓት/መረጃ አሰባሰብ ስነ-ዘዴ ነው። በዚህ ስነ-ዘዴ አማካኝነት ዝርዝር ግብዓት ለማሰባሰብ እንዲቻልም በዋናነት የትኩረት ቡድን ውይይት (Focus Group Discussion) ስልት በሰፊው ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህም ተሳታፊዎች በሁሉም የፖሊሲ አማራጮች ላይ ዝርዝር ምልከታዎቻቸውን የሚያጋሩበት ሰፊ ጊዜ እና እድል አግኝተዋል። በተጨማሪም በየውይይት ቦታዎቹ የፕሌናሪ መድረኮች ላይ - ተሳታፊዎች ጥቅል ሀሳቦችን እንዲሰጡ ውስን ጊዜ ተመቻችቷል።

በሌላ በኩል በርካታ የሲቪል ማህበረሰብ እና ባለድርሻ አካላት በፖሊሲ አማራጮች ሰነዱ ላይ አስተያየቶቻቸውን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ተደርጓል።

በሁሉም የውይይት መድረኮች ላይ የተነሱ ሃሳቦች፣ አስተያቶች እና በመወያያ ጥያቄዎቹ ላይ የተሰጡ ምላሾች በቃለ-ጉባኤ እንዲመዘገቡ ተደርጓል። እንዲሁም በተሳታፊዎች ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ በመመስረት በሁሉም የውይይት መድረኮች የተነሱ ሃሳቦችና አስተያየቶች በመቅረጸ-ድምጽ ተይዘዋል። በዚህ አግባብ የተያዙ መረጃዎች በተለያዩ ባለሙያዎች አማካኝነት ምንም ለውጥ ሳይደረግባቸው ወደ ፅሁፍ እንዲቀየሩ ተደርገዋል።

ከላይ በተገለጸው መንገድ የተሰበሰበው ከፍተኛ መጠን ያለው ግብዓት - ዓለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብት እና የሽግግር ፍትህ መርሆዎችን በተከተለ መልኩ - በባለሙያዎች ቡድኑ እንዲደራጅ ተደርጓል። በዚህ ረገድ ሂደቱ - በተለይም በሽግግር ፍትህ ምክክር ዝግጅት ማእቀፍ የመረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት እና ሪፖርት አፃፃፍን አስመልክቶ የተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት ያወጣውን ሰነድ ይዘት ግምት ውስጥ አስገብቷል።[6] በዚህም የተሳታፊዎች መሰረታዊ ሃሳብ ምንም ለውጥ ሳይደረግበት ሙሉ ይዘቱን ጠብቆ እንዲደራጅ ተደርጓል።

በተጨማሪም የመረጃ ማደራጀት ሂደቱ የሽግግር ፍትህ ዓላማን ታሳቢ ባደረገ መልኩ - የተሳታፊዎች ማንነት እና ግላዊ ምልከታ ሚስጥራዊነትን በጠበቀ፣ እንዲሁም የተጎጂዎችን እና ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን (ሴቶች፣ ህጻናት፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች፣ አረጋውያን፣ ተፈናቃዮች እና ስደተኞች) ሃሳብና እይታን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ እንዲከናወን ተደርጓል።

የተሰበሰበው ግብዓት - በእያንዳንዱ መድረክ፣ በክልል/ከተማ መስተዳድር፣ እንዲሁም በሀገር-አቀፍ ደረጃ በትኩረት ቡድኖች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እይታ ላይ ተመስርቶ እንዲደራጅ ተደርጓል። በሁሉም የመረጃ ማደራጀት ሂደቶች - በብዙሃኑም ሆነ በጥቂት ተሳታፊዎች የተነሱ ሃሳቦችን ከነዝርዝር ምክንያቶቻቸው የመሰነድ ሥራም ተከናውኗል። በልዩነት የተነሱ ሀሳቦች የብዙሃኑን ይሁንታ ባያገኙም እንኳ ባሉበት ደረጃ እንዲመዘገቡ ተደርጓል። በተጨማሪም ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ አስተያየቶች ተካተዋል።

[6] The United Nations Security Council. 'The Rule of Law and Transitional Justice in Conflict and Post-conflict Societies.' Report of the Secretary-General. S/2004/616. 2004.

በሌላ በኩል ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮች ጋር በተደረጉ ጉዳይ-ተኮር የምክክር መድረኮች (thematic consultations) የተሰባሰበው ከፍተኛ መጠን ያለው ግብዓት ራሱን ችሎ የተደራጀ ሲሆን - በተቻለ መጠን በመረጃ ትንተና ወቅት - ከክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች ከተሰበሰበው ግብዓት ጋር ተጠቃሎ እንዲቀርብ እና ተያይዞ እንዲተነተን ተደርጓል። በተመሳሳይ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በፅሁፍ የቀረቡ ግብዓቶች (ለምሳሌ የፖሊሲ መነሻዎች፣ ምክረ-ሃሳቦችና በፖሊሲ አማራጮቹ ላይ የተሰጡ ምልከታዎች) በመረጃ ትንተናው ምዕራፍ እንዲካተቱ ተደርጓል።

በተለያዩ ስልቶች የተሰበሰበውን መረጃ በማደራጀት እና በመተንተን ረገድ ሰፋ ያለ አሀዛዊ አቀራረብ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

የሪፖርቱ አጻጻፍ ዘዴ ገላጭ እና ሃተታዊ አቀራረብ (Descriptive and Narrative Approach) ስልትን የተከተለ ነው። ይህ ስልት የአብዛኛዎቹን ተሳታፊዎች እና ቡድኖች ድጋፍ ያገኘውን የፖሊሲ አማራጭ ከነምክንያቶቹ በቁጥር መረጃ አስደግፎ የሚያስቀምጥና የሚተነትን ነው። በዚህ አካሄድ - መግለጫዎችን እና ሃተታዎችን ከአሀዞች ጋር በማስተሳሰር - የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የሚጠይቀውን ከፍተኛ ጥንቃቄ ታሳቢ ያደረገ እና የተሳታፊዎች ሃሳብ በደፈናው እንዳይጠቃለል ወይም እንዳይጨፈለቅ ያስቻለ አሠራር ተግባራዊ ተደርጓል።

በመሆኑም መረጃዎች በሀገር-አቀፍ ደረጃ፣ በክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ደረጃ፣ እንዲሁም በሁሉም የትኩረት ቡድኖች ደረጃ በቁጥር ተደግፈው እንዲደራጁ - እንዲሁም በሁሉም ደረጃ በፖሊሲ አማራጮቹ ላይ የቀረቡ የጋራ እና የልዩነት ሀሳቦች ከትንተና ጋር ተቀራኝተው እንዲቀርቡ ተደርጓል። በተጨማሪም በእያንዳንዱ የፖሊሲ አማራጭ ስር አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ተሳታፊዎች ወይም ቡድኖች የተነሱ አቋሞችን ከነማብራሪያቸው ተመላክተዋል። በጥቂት ድምፆችም ቢሆን - በተለየ መልኩ የቀረቡ ተጨማሪ አማራጮችና ልዩ ሀሳቦችም በሪፖርቱ ተካተዋል።

## VI. ዋና ዋና ግኝቶች

ከላይ የተመለከተውን የመረጃ ማሰባሰብ፣ ማደራጀት እና ትንተና ዘዴን በመጠቀም በእያንዳንዱ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጭ ላይ - አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የደገፏቸው እና አቋም የወሰዱባቸው ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**ከወንጀል ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ፡** 'በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?'፣ 'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ሊመሠረት ይገባል?'፣ 'የፍርድ ሂደቱን ማን ያከናውነው?'፣ እና 'የወንጀል ምርመራና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚሉ መሰረታዊ የፖሊሲ ጥያቄዎችን በተመለከተ የተለያዩ አማራጮች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

**'በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል**?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ በተደረጉት ውይይቶች - አብዛኞቹ ተሳታፊዎች 'ጉልህ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል። ሆኖም ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎች 'የክስ ሂደቱ ሁሉንም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ያካተተ መሆን አለበት' የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል።

**'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል**?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የአብዛኛውን ተሳታፊ ድጋፍ ያገኘው ሀሳብ 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' የሚለው ነው። በሌላ በኩል ውስን ተሳታፊዎች ሁሉም አጥፊዎች እንደየተሳትፎ ደረጃቸው ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል።

**'የፍርድ ሂደትን ማን ያከናውነው?'** በሚለው የፖሊሲ ጥያቄ ላይ ተመስርተው ከቀረቡ አማራጮች ውስጥ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች 'አዲስ/ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክስ የመስማት እና ውሳኔ የመስጠት ተግባር ማከናወን ይገባል' የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል። ውስን ተሳታፊዎች ደግሞ በፌዴራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ልዩ ችሎት በማቋቋም፡ ብቁ የሆኑና ልምድ ያላቸው ዳኞችን በመመደብ እና ነፃና ገለልተኛ ሆነው እንዲሰሩ በማድረግ ተጠያቂነት ማስፈን ይገባል ብለዋል። አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎች ደግሞ ክሶቹ መታየት ያለባቸው አዲስና ገለልተኛ በሆነ ቅይጥ (የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ባለሙያዎችን ያካተተ) ፍርድ ቤት ወይም በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት አማካኝነት መሆን አለበት የሚል አዲስ አማራጭ አቅርበዋል።

**'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?'** በሚለው ጥያቄ ላይ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች 'አሁን ካለው የምርመራና የዓቃቤ ሕግ ተቋም ውጭ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር ልዩ፣ ነጻና ገለልተኛ የምርመራ እና የክስ ስራ የሚሰራ ተቋም በማቋቋም፡ እንዲሁም የተሻለ እውቀትና ልምድ ያላቸውን የምርመራ ባለሙያዎችና ዐቃቤያነ-ሕግ በመመደብ' ስራው መከናወን አለበት የሚል አቋም ይዘዋል። ውስን ተሳታፊዎች ደግሞ አሁን ባለው የፖሊስ እና የዐቃቤ ሕግ ተቋም ውስጥ ተገቢ ልየታ በማድረግ እና የተለየ ቡድን በመመስረት መስራት ያስፈልጋል ያሉ ሲሆን - ሌሎች ውስን ተሳታፊዎች ደግሞ ስራው የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሙያዎችን ባካተተ ወይም በአለም አቀፍ ተቋም አማካኝነት ሊከናወን ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል።

**እውነት የማፈላለግ እና እርቅን በተመለከተ፡** 'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች ሊተገበሩ ይገባል?' እና 'እውነት የማፈላለግና እርቅን የማውረድ ሂደቱ በየትኛው ተቋም ሊከናወን ይገባል?' በሚሉ የፖሊሲ ጥያቄዎች ዙሪያ ተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት እና ክርክር አድርገዋል።

የመጀመሪያውን ጥያቄ በተመለከተ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች 'ጉልህ የሆኑ እና ጉልህ ያልሆኑ ጥሰቶች የትኞቹ ናቸው?' በሚለው ነጥብ ላይ በመመርኮዝ የእውነት ማፈላለግና የእርቅ ተግባራትን ለማስኬድ መሞከር በህብረተሰቡ ውስጥ ሰፊ ቅሬታን ይፈጥራል፤ ስለሆነም ተገቢውን ጊዜ፣ ሀብት እና የሰው ሀይል በመመደብ እውነትን የማፈላለግና ይፋ የማውጣቱ ሥራ ሁሉንም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እና ለግጭቶች ምክንያት የነበሩ ተቀዳሚ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶችን ጥሰት መሸፈን አለበት' የሚል ሀሳብ ደግፈው ሞግተዋል። ሌሎች ተሳታፊዎች ደግም እውነት የማፈላለጉ እና የእርቅ ተግባር 'በተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ያተኮረ' ሊሆን ይገባል የሚል አቋም ይዘዋል።

**'እውነት የማፈላለግና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት በየትኛው ተቋም ሊከናወኑ ይገባል?'** በሚለው ጥያቄ ላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች 'እውነትን የማፈላለግና የእርቅ ሥራ/ሂደት የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ውክልና እና ተሳትፎ ባረጋገጠ መልኩ በሚመሠረት አዲስ የእውነት አፈላላጊ ተቋም አማካኝነት መከናወን አለበት' የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል። ውስን ተሳታፊዎች - እውነት የማፈላለጉ እና የእርቅ ተግባር በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ወይም በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ሊሰራ ይገባል ያሉ ሲሆን፤ የተወሰኑ ሌሎች ተሳታፊዎች ደግሞ ስራው ኢትዮጵያውያን በሚሳተፉበት ቅይጥ አለም-አቀፋዊ ተቋም ሊመራ ይገባል ብለዋል።

**በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረትን እንደ አንድ የሽግግር ፍትሕ ስልት ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር፡** 'ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ መስፈርቶች ምን ሊሆኑ ይገባል?' እንዲሁም 'ምህረት የመስጠት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚሉ መሰረታዊ የፖሊሲ ጥያቄዎች ለውይይት ቀርበዋል።

ምህረትን ለመተግበር የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎችን በተመለከተ አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች 'የምህረት ቅድመ-ሁኔታዎች በግልፅ ሊቀመጡና እና ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 28 ጋር እንዲሁም ከዓለም-አቀፍ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ ሊሆኑ ይገባል' የሚል ሀሳብ አንስተዋል። ለምህረት ብቁ የማያደርጉ መስፈርቶችን በተመለከተ -

አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ወይም ከባድ ወንጀሎችን የፈፀሙ አጥፊዎች ለምህረት ብቁ ሊሆኑ አይገባም ብለዋል። ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶችን በተመለከተም የተለያዩ ዝርዝር መለኪያዎችን በቅድመ-ሁኔታነት አቅርበዋል።

**'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው**?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ምህረት የመስጠት ሥራው 'አዲስ በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ሊከናወን ይገባል' የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። ውስን ተሳታፊዎች - አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ መጠቀም ይገባል ያሉ ሲሆን፤ ሌሎች ጥቂት ተሳታፊዎች ደግሞ የስራ ሂደቱ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ወይም በሀገር ሽማግሌዎች ቢሰራ ይበልጥ ተመራጭ ነው የሚል ሀሳብ አንስተዋል።

**በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት ማካካሻ** - ተጎጂዎች የተሟላ መፍትሄ እንዲያገኙ የሚያስችል አንኳር የሽግግር ፍትህ አምድ ነው። በዚህ ረገድ ለተሳታፊዎች ሶስት ተያያዥ የፖሊሲ ጥያቄዎች ቀርበዋል። እነዚህም 'የማካካሻ ሂደቱ በየትኛዎቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል?'፣ 'የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ አግኝተው ሊተገበሩ ይገባል?'፣ እና 'የማካካሻ ሥርዓቱን ማን ሊተገብረው ይገባል?' የሚሉ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥያቄዎችን በተመለከተ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ አማራጮች ሳይቀርቡ - ተሳታፊዎች ምልከታዎቻቸውን እንዲያጋሩ ተደርጓል። ሶስተኛውን ጥያቄ በተመለከተ አማራጮች ቀርበው ሰፊ ግብዓት ተሰብስቧል።

**'የማካካሻ ሂደቱ በየትኛዎቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል**?' የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ብዙዎቹ ተሳታፊዎች በሰፊው ያንፀባረቁት ሀሳብ 'በመርህ ደረጃ ለሁሉም ተጎጂዎች እንደየጉዳቱ አይነትና መጠን ማካካሻ መስጠት ተገቢ ነው' የሚል ይዘት ያለው ነው። አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች - በማካካሻ ትግበራ ሂደቱ ለተወሰኑ ተጎጂዎች ቅድሚያ መስጠት ካለበት በሚከተሉት ዝርዝሮች ላይ ማተኮር ይገባል ብለዋል። በማካካሻ ትግበራ ሂደቱ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል በሚል ካነሷቸው መካከልም ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው፣ የስነ-ልቦና እና የአዕምሮ ቀውስ ያጋጠማቸው፣ ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው እና የጤና እክል ያለባቸው፣ ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው፤ ተፈናቃዮች፣ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ መጠለያዎች የሚገኙ፣ የንብረት ጉዳት የደረሰባቸው፣ ንብረታቸው በህገወጥ መንገድ የተነጠቀ፣ የማስቃየት ድርጊት ሰለባ የሆኑ፣ ከደረሰባቸው ጉዳት ያላገገሙ፣ ቤተሰቦቻቸውን ያጡ፣ የቤተሰብ አባላቸው ደብዛ የጠፋባቸው፣ ያለ ሕግ ለረጅም ጊዜ በእስር የቆዩ፣ አቅመ-ደካማዎች፣ እና ቤተሰባቸውን ያጡ ህጻናት ይገኙበታል።

በተጨማሪም የማካካሻ ሂደቱ ጉዳት የደረሰባቸው ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች (ሴቶች፣ ህጻናት፣ በጦርነት ወላጅ ያጡ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን) ልዩ ሁኔታን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ አግባብ ሊተገበር ይገባል ብለዋል።

**'በማካካሻ ሥርዓት ምን የማካካሻ አይነቶች ሊተገበሩ ይገባል**?' የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ - አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የማካካሻው ዓይነት እንደየጉዳቱ አይነት የተለያየ ሊሆን ይገባል የሚል አቋም አንጸባርቀዋል። የማካካሻው ዓይነት ለጥሰት/ጉዳት እውቅና መስጠትን፣ መልሶ ማቋቋምን፣ የማገገሚያ አገልግሎት ማቅረብን፣ ቁሳዊ ወይም የገንዘብ ካሳ መስጠትን፣ የወደመ ሐብት መልሶ መገንባትን እንዲሁም የስራ እድል እና የጡረታ መብት ማመቻቸትን ሊያጠቃልል እንደሚገባ ገልፀዋል። እንዲሁም የስነ-ልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የምክር አገልግሎትና የማገገሚያ ስርዓቶችን መዘርጋት ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ አንስተዋል።

በዚህ ረገድ - አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች አጽንኦት በመስጠት ለተፈናቀሉ እና ንብረታቸውን ላጡ ሰዎች ሰላማዊ ኑሯቸውን መኖር የሚችሉበት ሁኔታ መፍጠር፣ መልሶ ማቋቋምና ወደ ነበሩበት ህይወት መመለስ፣ የህክምና እና የሥነ-ልቦና አገልግሎት፣ የምግብና መጠለያ ድጋፍ፣ ጉዳቱ ዳግም እንደማይፈፀም ዋስትና የመስጠት፣ ተፈናቃዮችን

ቀድሞ ወደነበሩበት ቦታ የመመለስ፣ የማይቻል ከሆነም ከጊዜያዊ መጠለያ ወጥተው በዘላቂነት የሚኖሩበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል።

በተጨማሪም የማካካሻ ሥርዓቱ እንዳስፈላጊነቱ ምሳሌያዊ (ለምሳሌ ጅምላ ግድያ በተፈፀመባቸው ቦታዎች ላይ ሃውልት/ማስታወሻ ወይም ሙዝየም በማቆም) እና የገንዘብ ካሳን በሚያካትት አግባብ ሊከናወን እንደሚገባ አንስተዋል።

በሌላ በኩል ጥቂት የማይባሉ ተሳታፊዎች ለእያንዳንዱ ጥሰት - በግለሰብ ደረጃ ማካካሻን ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ ስለሚሆን - ሥርዓቱ በዋናነት በማህበረሰብ ደረጃ ሊተገበር ይገባል፤ ትኩረቱም ሰዎች በጋራ የሚገለገሉባቸው ተቋማትን በመገንባት ላይ መሆን አለበት የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።

ሌላው ከማካካሻ ጋር በተገናኘ ግብዓት የተሰበሰበበት ጉዳይ '**የማካካሻ ሥርዓቱን ማን ይምራው**?' የሚለው ጥያቄ ነው። በዚህ ረገድ አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች - የማካካሻ ሥርዓቱ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን' አማካኝነት ሊመራ ይገባል የሚል ሀሳብ ሰጥተዋል። ውስን ተሳታፊዎች ደግሞ የማካካሻ ተግባሩ መከናወን ያለበት በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ወይም በባህላዊ የፍትህ ተቋማት አማካኝነት መሆን አለበት የሚሉ የተለያዩ አማራጮችን ደግፈዋል። ጥቂት ተሳታፊዎች ደግሞ የግል ካሳ ሥርዓትን በመደበኛው ፍርድ ቤት አማካኝነት መተግበር ይገባል ብለዋል።

የሽግግር ፍትህ ሂደትን ከመተግበር ጋር ተያይዞ በቀዳሚነት የሚነሳ ሌላው ጥያቄ '**የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር**' የሚለው ነው። ስኬታማ በሆኑ የሽግግር ፍትህ ተሞክሮዎች የታየው አንዱ ጠቃሚ አካሄድ በሂደቱ የሚሸፈነውን ጊዜ መነሻ እና መዳረሻ አስቀድሞ መወሰን ፍፁም ተገቢ መሆኑን የሚያመላክት ነው። በአንድ በኩል ሂደቱ እጅግ የራቀ የመነሻ ጊዜ ኖሮት - ወሰኑ እጅግ እንዲሰፋ እና ማስረጃ እና ምስክሮች በማይገኙበት ጊዜ እንዲጀምር ማድረግ ሥራው ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በጣም የቀረበ የመነሻ ጊዜ ኖሮት ዋና ዋና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተከሰቱበትን ጊዜ የማያካትት ከሆነ - የታሰበውን ዓላማ ማሳካት አይችልም። ስለሆነም በሀገራችን ለመተግበር በሚታሰበው ሂደት - የሽግግር ፍትሕ ሀገራዊ አውዱን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የጊዜ ወሰን ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ ለተሳታፊዎች አምስት መነሻ አማራጮች ቀርበዋል።

ከቀረቡት አማራጮች ሁሉ የሽግግር ፍትህ የጊዜ ማእቀፍ '**ለክስ ጉዳይ** ከ1987 **ጀምሮ እና ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ ማስፈንና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ**' ድረስ ሊዘረጋ ይገባል የሚለው አማራጭ የአብዛኛዎቹን ተሳታፊዎች ድጋፍ አግኝቷል። በመቀጠልም በቅደም-ተከተል በተለያየ ቁጥር የተሳታፊዎችን ድጋፍ ያገኙት አማራጮች - የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ከ1983 ዓ.ም በፊት ጀምሮ ባለው የጊዜ ማእቀፍ ላይ ይተግበር'፣ 'ከ2010 ጀምሮ ባለው የጊዜ ማእቀፍ ላይ ይተግበር'፣ 'ከ1983 ጀምሮ ባለው የጊዜ ማእቀፍ ላይ ይተግበር'፣ እና 'ከ1987 ጀምሮ ባለው የጊዜ ማእቀፍ ላይ ይተግበር' የሚሉት ናቸው።

**ተቋማዊ ማሻሻያ** ከዚህ ቀደም ሲፈጸሙ የነበሩ ጥሰቶች እና ኢፍትሀዊ ኩነቶች ድጋሚ እንዳይፈጸሙ ዋስትና ለመስጠት የሚያስችል የሽግግር ፍትሕ ስልት ነው። በዚህ ረገድ '**ቅድሚያ ተሰጥቶ የመለየት እና የማጥራት ተግባራት ሊደረግባቸው የሚገቡ ተቋማት የትኞቹ ሊሆኑ ይገባል**?' እንዲሁም '**የተቋማት የመለየት እና የማጥራት ተግባሩ በማን ይከናወን**?' የሚሉ መሰረታዊ የፖሊሲ ጥያቄዎች ከአማራጭ ሀሳቦች ጋር ሆነው ለውይይት ቀርበዋል።

'ቅድሚያ ተሰጥቶ የመለየት እና የማጥራት ተግባራት ሊደረግባቸው የሚገቡ ተቋማት የትኞቹ ሊሆኑ ይገባል' የሚለውን በተመለከተ - አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች የፍትህ ተቋማት፣ የጸጥታ እና የደህንነት አካላት፣ ሚዲያ፣ እንዲሁም በተወሰኑ ህጎች ላይ የመለየት፣ የማጥራት እና የማሻሻያ ተግባራት ሊከናወን ይገባል ብለዋል።

**'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ'** የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ለውይይት ሁለት አማራጮች ቀርበዋል። እነዚህም 'አዲስ ተቋም በማቋቋም የተቋማት ማሻሻያ ተግባር ማከናወን' ወይም 'በሁሉም ተቋማት ውስጥ የልየታ፡ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ሀላፊነት ያላቸው ቡድኖችን በማዋቀር ተግባራቶቹን ማከናወን' የሚሉ ናቸው። በዚህ ረገድ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ገለልተኛ እና ነጻ የሆነ አዲስ ተቋም በማቋቋም ተቋማትን የማጥራትና የማሻሻል ተግባር ሊከናወን ይገባል ብለዋል። በአንጻሩ የተወሰኑ ተሳታፊዎች በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር ተቋማት የማጥራትና የማሻሻያ ተግባራትን ማከናወን ይመረጣል የሚል ሀሳብ አንፀባርቀዋል።

በሀገራዊ ምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት ተሳታፊዎች ሃሳብ እንዲሰጡበት የተደረገው ሌላው ጉዳይ **በሽግግር ፍትሕ ሒደት ባህላዊ የፍትህ ሥርዐቶች የሚኖራቸውን ሚና እና ቅንጅት** የሚመለከት ነው። ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎች ቀርበው ሰፊ ውይይት ተካሂዶባቸዋል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በርካታ የተለያዩ እና ረዥም እድሜ ያስቆጠሩ የባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ባለቤት በሆኑ ሀገራት - ለሽግግር ፍትህ ዓላማ ባህላዊ የፍትሕ ስርዓቶችን በአግባቡ መለየት እና ለየትኞቹ ጉዳዮች ጥቅም ላይ ሊውሉ እንደሚገባ መወሰን ለሽግግር ፍትሕ ውጤታማነት መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

በዚህ ረገድ ከተሳታፊዎች የተሰጡ ግብዓቶች - በመላው ሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሽግግር ፍትህ ሂደቱን የማገዝ እና የመደገፍ ሚና ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚያመላክቱ ናቸው። 'ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶችን ከሌሎች መደበኛ የፍትሕ ተቋማት ጋር በማቀናጀት እውነትን በማፈላለግ፣ ተጠያቂዎች ለፍትህ እንዲቀርቡ በማድረግ፣ በእርቅ ጉዳይ፣ እና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር በሚያስችሉ ስራዎች ወሳኝ የድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን ይችላሉ፤ ይገባቸዋልም፤' የሚሉ ሀሳቦች በስፋት ተንጸባርቀዋል። ይሁን እንጂ 'ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት ማሻሻያ ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለይቶ ማስቀመጥ - እንዲሁም አሰራሮቻቸው እንደየሁኔታው ውስጣዊ እና ውጫዊ ይዘት ያላቸው ማሻሻያዎች ሊደረጉባቸው ይገባል' የሚል ምልከታም ተያይዞ ተነስቷል።

በመጨረሻም ኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓትን የምትከተል ሀገር እንደመሆኗ መጠን **በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የሚኖራቸውን ሚና በግልጽ መወሰን** አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ በተካሄዱት የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ላይ ሁሉም ተሳታፊዎች ሊባል በሚችል መልኩ በሀገር-አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሊቀረጽ እንደሚገባ አንስተዋል። በፖሊሲ ትግበራ ሂደቱ ክልሎች አስፈላጊ ድጋፍና ትብብር ማድረግ እንዳለባቸው፣ እንዲሁም የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሊቀርፁም ሆነ ሊተገብሩ እንደማይገባ በስፋት ተንጸባርቋል። ለዚህም በዋናነት የተሰጡት ምክንያቶች 'የሽግግር ፍትሕ ስራ በአጠቃላይ ዜጋ-ተኮርና ሀገራዊ ይዘት ያለው ነው'፣ 'ብዙ ክልሎችን ባንድ ጊዜ ያቅፋል'፣ እንዲሁም 'በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ተግባራዊ የሚደረጉ ብዙዎቹ ሕጎች በፌዴራል መንግስት ሥልጣን ማዕቀፍ ስር የሚወድቁና ሀገራዊ የተፈጻሚነት ወሰን ያላቸው ናቸው' የሚሉ ናቸው። ሆኖም ክልሎች የሀገራዊ ችግሮቹ አካል እንደመሆናቸው መጠን - ዝርዝሮቹ በጥንቃቄ እየተለዩ - የመፍትሄው አካል መሆን እንደሚኖርባቸው፣ ለዚህም የሚያመች አሳታፊ ሥርዓት ሊቀረፅ እንደሚገባ ተሳታፊዎች በአጽንኦት አንስተዋል።

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ መግለጫ

### 1.1. መግቢያ

በአፍሪካ ሕብረት የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ ማዕቀፍ መሠረት **የሽግግር ፍትህ** ማለት 'ማኅበረሰቦች የትላንት ጥሰቶችን፣ መከፋፈሎችን እና የእኩልነት ዕጦትን ለማሸነፍ፣ ለደኅንነት እንዲሁም ለዴሞራሲያዊ ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሲሉ አካታች በሆነ የምክክር ሒደት የሚያጸድቋቸው የተለያዩ መደበኛና ባሕላዊ ወይም መደበኛ ያልሆኑ የፖሊሲ እርምጃዎችና ተቋማዊ ዘዴዎች ናቸው።'[7]

የሽግግር ፍትህ አጠቃላይ ዓላማ ላለፉ በደሎች እና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተገቢ ምላሽ በመስጠት ዘላቂ ሰላም፣ ፍትህ እና እርቅ ማምጣት ነው። የሽግግር ፍትህ እርስ በእርስ የተያያዘ በአንድነት ወደ ኋላ እና ወደፊት የሚመለከት ዓላማ ያለው ሂደት ነው። የሽግግር ፍትህ ሂደት በተጎጂዎች እና በማህበረሰብ ላይ ለደረሱ ጥፋቶች ምላሽ መስጠት፣ አጥፊዎችን ተጠያቂ ማድረግ፣ እውነትን ማረጋገጥ፣ የተጎዱትን መጠገን ወይም መካስ፣ ለተጠቂዎች ክብር መስጠት፣ ተመሳሳይ በደሎችን መከላከል እና ብሄራዊ መግባባትን ማሳለጥን የሚያጠቃልሉ ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።[8]

ከላይ የተጠቀሱትን የሽግግር ፍትሕ ዓላማዎችን በተሟላ መንገድ ለማሳካት - በተ.መ.ድ እና በአፍሪካ ሕብረት የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ የተጠቀሱትን የሽግግር ፍትህ ስልቶችን በተቀናጀ እና በተሰናሰለ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህ ስልቶች የወንጀል ተጠያቂነት፣ እውነትን ማፈላለግ፣ ማካካሻ፣ በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ምህረት፣ እና የሕግና የተቋማት ማሻሻያ ናቸው።

በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት ተፈፅመዋል የተባሉ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ቁርሾዎች - አግባብነት ባለው፣ አሳታፊ በሆነ እና በተቀናጀ አካሄድ የተሟላ ምላሽ ሳይሰጣቸው ቆይተዋል። ስለሆነም በደሎች እንዲሽሩ፣ ቁርሾዎች እንዲጠገኑ፣ ወደ ዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚደረገው ሽግግር እንዲሳካ - እንዲሁም ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ እንዲቻል - የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ ነው።[9]

በሀገራችን ከዚህ ቀደም - ከደርግ መንግስት መውደቅ በኋላ (ድህረ-ደርግ) እና ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ (ድህረ-ኢህአዴግ) የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ሙከራዎች ተካሂደዋል። እነዚህ ሙከራዎች እንደ መልካም ጅማሮ ቢወሰዱም - የሽግግር ፍትህ መርሆዎችንና ስልቶችን ከመተግበር አንጻር ሰፊ ክፍተቶች የነበሩባቸው በመሆኑ በተለያዩ ጊዜያት ለተፈጸሙ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት አልቻሉም።

በአሁኑ ጊዜ በተጨባጭ ያለውን ሀገራዊ አውድ ስንመለከት - በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለያዩ ሀይሎች መካከል በተከሰቱ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ምክንያት አለመረጋጋት፣ መጠነ-ሰፊ እና ተከታታይ መፈናቀል እና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሲፈፀሙ ይስተዋላሉ። የእነዚህ ችግሮች መነሻ የተለያየ ቢሆንም - በዋናነት ግን በተለያዩ ጊዜያት በተሟላ መልኩ ምላሽ ሳያገኙ ሲንከባለሉ የመጡ ጥያቄዎች ድምር ውጤት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

---

[7] African Union. 'African Union Transitional Justice Policy'. February 2019.
The United Nations Security Council. 'The Rule of Law and Transitional Justice in Conflict and Post-conflict Societies'. Report of the Secretary-General. S/2004/616. 2004.

[8] The United Nations Security Council. 'The Rule of Law and Transitional Justice in Conflict and Post-conflict Societies'. Report of the Secretary-General. S/2004/616. 2004. p.4.

[9] የፍትህ ሚኒስቴር፡ የሽግግር ፍትህ በኢትዮጵያ - አሁናዊ ሁኔታ እና ቀጣይ አቅጣጫ (2014 ዓ.ም.)፡ ኢትዮጵያ፡ ገፅ 59

ከዚህ አንጻር በተሟላና በተቀናጀ መልኩ የሚዘረጋ፣ አሳታፊ፣ ተጎጂዎችን ማዕከል ያደረገ፣ ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን ያከበረ፣ የሀገራችንን ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አውድ መሰረት ያደረገ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት መቀመር እና ተግባራዊ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን መተግበር ለሰብዓዊ መብቶች መከበር እና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።[10]

በዚህ ረገድ - ሀገራዊ አውዱን መነሻ ያደረገና በዋናነትም ቀደም ሲል የተከወነ ጥናትን፣ ህዳር 2014 ዓ.ም ይፋ የተደረገው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የጋራ ምርመራ ውጤት ምክረ-ሀሳብን፣ እንዲሁም ጥቅምት 2015 ዓ.ም በተፈረመው የፕሪቶርያ የሰላም ስምምነት መሰረት የሽግግር ፍትሕን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል - የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የሚያዘጋጅ የባለሙያዎች ቡድን ጥቅምት 2015 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ተቋቁሟል።

የባለሙያዎች ቡድኑ ሀገራዊ ፖሊሲ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። ከነዚህም መካከል ለሚዘጋጀው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ሰነድ መነሻ የሚሆነውና - በሀገራችን ከሚገኙ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለመሰብሰብ የተዘጋጀው 'የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ሰነድ'[11] አንዱ ነው።

ሰብዓዊ መብት-ተኮር የሽግግር ፍትሕ ሥራ በበርካታ መርሆዎች ላይ ተዋቅሮ የሚመሠረት ነው። በተለያዩ ጊዜያት እና ኩነቶች በተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተጎጂ የሆኑ አካላት - እንዲሁም ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ምሁራን እና ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች - በሽግግር ፍትሕ ሒደት የተለያዩ ምእራፎች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል። በዚህ ረገድ የተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ያወጣው ምክረ ሀሳብ ቁጥር 2005/70 - በሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ላይ በተለየ ሁኔታ ትኩረት ያደረገ እና የእያንዳንዱን አካባቢያዊ አውድ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ሁሉን-አቀፍ ብሔራዊ የምክክር ሂደት ማካሄድ አስፈላጊ እንደሆነ በአጽንኦት ገልጿል።[12]

በዚህ መሠረት የባለሙያዎች ቡድኑ በሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ላይ በመመስረት ግብዓት ማሰባሰብ እንዲቻል - በሁሉም አካባቢ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ፣ በሰብዓዊ መብቶች መርህ ላይ የተመሠረተ፣ ተጎጂ-ተኮር የሆነ - ሁሉን ክልሎች እና ሁለቱን የከተማ አስተዳደሮች ያሳተፈ የግብዓት ማሰባሰቢያ የምክክር መድረኮችን አዘጋጅቷል። የምክክር ሂደቶቹም በአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፖሊሲ፣ በ1988፣ በ1996፣ በ2008 እና በ2016 ዓ.ም በወጡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፀሃፊ ሪፖርቶች፣ እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ባወጣው የሕግ የበላይነት ሰነዶች ላይ በሰፈሩ እሴቶች እና መርሆዎች እንዲመሩ ተደርገዋል።

በተጨማሪም የባለሙያዎች ቡድኑ በልዩ ሁኔታ በተለዩ እና በተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮሩ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮችን ከተ.መ.ድ የተለያዩ ቢሮዎች፣ ከኢ.ጋድ እና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በቅንጅት አከናውኗል።

---

[10] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች፡ ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለመሰብሰብ የተዘጋጀ'፡ ጥር 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ፡ ገጽ 10-11

[11] 'የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ሰነድ' ማለት ወደፊት ለሚቀረፀው ፖሊሲ ከህብረተሰቡ እና ባለድርሻ አካላት ቅርፅ ያለው ግብአት ለማሰባሰብ እንዲቻል በሁሉም የሽግግር ፍትህ አምዶች ላይ የተለያዩ አማራጮችን እንዲሁም እያንዳንዱ አማራጭ ያለውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን በማስቀመጥ የተዘጋጀ ሰነድ ነው።

[12] UN Commission on Human Rights. 'Human Rights Resolution 2005/70. Human Rights and Transitional Justice'. E/CN.4/RES/2005/70. April 20, 2005.

*Also refer* to 'The Rule of Law and Transitional Justice in Conflict and Post-conflict Societies'. Note 8 above.

ከእነዚህ የግብዓት ማሰባሰቢያ የምክክር መድረኮች በተጨማሪ በፍትሕ ሚኒስቴር የማህበራዊ ትስስር ገጽ፣ በባለሙያዎች ቡድኑ የኢ-ሜይል አድራሻ እና በባለሙያዎች ቡድኑ አባላት የግል የኢ-ሜይል አድራሻዎች አማካኝነት በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ላይ ከግለሰቦች እና ከተለያዩ ተቋማት በፅሁፍ የተሰጡ ግብዓቶችን ለማሰባሰብ ተችሏል።

## 1.2. የሪፖርቱ ዓላማ

ይህ ሪፖርት ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት። የመጀመሪያው ዓላማ በሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጭ ላይ በክልላዊ እና ሀገር-አቀፍ መድረኮች አማካኝነት እንዲሁም በፅሁፍ የተሰባሰቡ ግብዓቶችን በአግባቡ በማደራጀት እና በመተንተን - ለሚዘጋጀው የሽግግር ፍትሕ አገራዊ ፖሊሲ ግብዓት ሊሆኑ በሚችሉበት አግባብ ማስቀመጥ ነው።

ሁለተኛው ዓላማ ከሽግግር ፍትሕ ዋና ዋና መርሆዎች መካከል አንዱ የሆነው የግልጸኝነት አሠራርን ከመከተል አንፃር፥

- በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የተለያዩ ምእራፎች የተከናወኑ ተግባራትን፣ በተለይም በሕዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰበባሰብ ሥራዎች ሂደቱ የተገኙ መረጃዎች የተሰበሰቡበት፣ የተደራጁበት እና የተተነተኑበትን መንገድ ማሳየት፣
- ከግብዓቶቹ ይዘት በመነሳት በፖሊሲ አማራጮቹ ላይ የተንፀባረቁ ዋና ዋና ግኝቶች እና ማጠቃለያዎችን ዝርዝር ይፋ ማድረግ፣
- በዚህም የሂደቱ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የኢትዮጵያ መንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እና የሂደቱ አጋር አለም-አቀፍ አካላት ተገቢ መረጃ እንዲኖራቸው በማስቻል - የሂደቱን ግልፅነት፣ ተአማኒነት እና ተቀባይነት ማረጋገጥ ነው።

## 1.3. የሪፖርቱ አደረጃጀት

ይህ ሪፖርት በስምንት ዋና ዋና ክፍሎች ተደራጅቷል።

ክፍል አንድ የሪፖርቱን ዓላማ የሚያብራራ ሲሆን፣ ክፍል ሁለት የሽግግር ፍትህን ታሪካዊ ዳራ እና አስፈላጊነት ከዓለም-አቀፋዊ እና ሀገራዊ ተሞክሮ ጋር በማሰናሰል ይዳስሳል። በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማውጣትና መተግበር አስፈላጊ ያደረጉ ምክንያቶችንም ይዘረዝራል።

ክፍል ሶስት የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን መቋቋም፣ ዝርዝር የስራ ኃላፊነት፣ እና የቡድኑን እና የፖሊሲ ዝግጅት ስራዎች የተመሩበት በቅድመ-ዝግጅት ምዕራፍ የተዘጋጁ ሰነዶችን ይዘት ማብራሪያ ያስቀምጣል።

ክፍል አራት የህዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰበባሰብ ስራዎች በማከናወን ሂደት ምክክር እንደ መብት ሊታይ የሚገባበትን አግባብ፣ መብቱን መተግበር በሽግግር ፍትህ አውድ የሚኖረው ልዩ ፋይዳ፣ ግብዓት ለማሰበባሰብ የተከወኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች፣ ምክክር የተካሄደባቸው ቦታዎች፣ የተሳተፉ ሰዎች እና የጊዜ ሰሌዳ፣ እንዲሁም የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ የተመራባቸው ዋና ዋና መርሆዎች ይዘት እና ተግባራዊ አፈፃፀምን በዝርዝር ያቀርባል።

ክፍል አምስት ከህዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰበባሰብ ሂደቶች የተገኙ ግብአቶች የተሰበሰቡበት፣ የተደራጁበት እና የተተነተኑበትን ሥነ ዘዴ ያብራራል።

ክፍል ስድስት በሁሉም የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ ተሳታፊዎች እና ባለድርሻ አካላት የሰጧቸው ግብአቶች ማጠቃለያ እና ከግብአቶቹ የሚቀዱ ዋና ዋና ግኝቶችን የሚያቀርብ ሲሆን፣ ክፍል ሰባት የሪፖርቱን ማጠቃለያ ያስቀምጣል።

በክፍል ስምንት ስር በሁሉም የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ ከህዝቡ እና ከባለድርሻ አካላት በተሰበሰበው መረጃ እና ከተሳታፊዎች የተለያዩ ምርጫዎች በመነሳት - የባለሙያዎች ቡድኑ ያጋራቸው እይታዎች እና በዝርዝር ምክንያቶች ላይ ተንተርሶ የሰጣቸው ምክረ-ሀሳቦች ተደራጅተው እንዲቀርቡ ተደርጓል።

## ክፍል ሁለት

## የሽግግር ፍትህ ታሪካዊ ዳራ እና አስፈላጊነት

### 2.1. የሽግግር ፍትህ ሂደት ዓለም-አቀፋዊ ተሞክሮ አጭር ምልከታ

በዓለማችን በግጭት፣ በጦርነት ወይም በጨቋኝ ሥርዓት ውስጥ ያለፉ በርካታ ሀገራት ወደ ሰላም እና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለመሸጋገር የየራሳቸውን አውድ መሠረት ያደረገ የሽግግር ፍትሕን ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ የተለያዩ የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ተሞክሮዎች ተስተውለዋል፡፡

በዚህ ረገድ የተወሰኑ ሀገራት ጊዜያዊ ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም አጥፊዎችን በመቅጣት ላይ ትኩረት ያደረጉ ሲሆን፣ ሌሎች ጊዜያዊ ዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤቶች በመመስረት፡ አጥፊዎችን በዓለም-አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት በማቅረብ ወይም በሀገር ውስጥ ልዩ ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም ፍትህ የመስጠት አሰራሮችን ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ መጠነ-ሰፊ እና ውስብስብ ጥሰቶች በነበሩባቸው አገራዊ አውዶች አጥፊዎችን በመቅጣት ላይ ብቻ ያተኮሩ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች መሠረታዊ ጉድለቶች እንደነበሩባቸውም ማየት ተችሏል፡፡

ስለሆነም በወንጀል ክስ ላይ ብቻ የተመሰረቱ የሽግግር ፍትህ ሂደቶችን ክፍተት በመሙላት - ለዘላቂ ሰላም አስተዋፅኦ የሚያደርግ እና ሁለንተናዊ ጠቀሜታን የሚሰጥ የሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ - አዳዲስ ዘዴዎች እና መንገዶችን ይዞ ብቅ ብሏል፡፡ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ለጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ክስን እንደ አንድ የሽግግር ፍትህ ስልት በመጠቀም ተጠያቂነትን ከማስፈን በተጨማሪ - እውነትን ማጣራት እና ይፋ ማውጣት፣ እርቅ ማስፈን፣ የማካካሻ እርምጃዎች መውሰድ እና የተቋማትን ለውጥ ማሳለጥ - አንኳር የሽግግር ፍትህ ስልቶች ሆነው በስራ ላይ እየዋሉ ነው፡፡

ከዚህ ተሞክሮ በመነሳት - የሽግግር ፍትህ ስርአት በአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና በተ.መ.ድ የሽግግር ፍትህ ሰነዶች ላይ በተመላከተው አግባብ - የዳኝነት እና የዳኝነት ያልሆኑ ምሰሶዎችን በጣምራ በመያዝ፣ የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስልቶችን ሁለንተናዊነት እና ተመጋጋቢነትን በሚያረጋግጥ መንገድ፣ አሳታፊ እና አካታች በሆነ ሂደት፣ ሀገራዊ ባለቤትነትን እና አውድን ባማከለ፣ ተገቢ ቅንጅት እና ቅደም ተከተል በማስጠበቅ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

### 2.2. የሽግግር ፍትህ ሂደት ተሞክሮ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ በተለያዩ የመንግስት ሥርዓቶች የስልጣን ዘመን - በዜጎች ላይ መጠነ-ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ጭቆናዎች ሲፈጸሙ እንደቆዩ የተለያዩ መረጃዎች እና ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡[13] ለእነዚህ ጥሰቶች በሽግግር ፍትሕ አማካኝነት ምላሽ ለመስጠትም ውስን ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡ በዚህ ረገድ ከተተገበሩ የሽግግር ፍትሕ ሥራዎች ውስጥ - ከደርግ መንግስት መውደቅ በኋላ በሽግግር መንግስቱ የተከናወነው በክስ ላይ ትኩረት ያደረገው የሽግግር ፍትሕ ሂደት እና ከ2010 በኋላ ተግባራዊ የተደረገው የሽግግር ፍትሕ ተመክሮ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በ1983 ዓ.ም ኢህአዴግ በትረ-መንግስቱን በመቆጣጠር የሽግግር መንግስት ካቋቋመ በኋላ - በደርግ መንግስት የሥልጣን ዘመን ለተፈጸሙ ጥሰቶች ምላሽ ከመስጠት አንፃር የወንጀል ክስን እንደ ዋነኛ የፍትህ ማሳለጫ መንገድ ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 22/1985 መሰረት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሆነ የልዩ ዓቃቤ ሕግ ፅህፈት ቤት የተቋቋመ ሲሆን - የፅህፈት ቤቱ ዋና ስራም የደርግ ዘመን ባለስልጣናት የፈጸሟቸውን

[13] የፍትህ ሚኒስቴር፡ 'የሽግግር ፍትህ በኢትዮጵያ: አሁናዊ ሁኔታ እና ቀጣይ አቅጣጫ' (2014)፡ ኢትዮጵያ

ወንጀሎች መመርመር፣ ክስ መመስረት እና ማስቀጣት ነበር። በዚህ መሠረት የቀድሞ የሀገሪቱ ርእሰ-ብሔር ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ጨምሮ - በበርካታ ተጠርጣሪዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ ተላልፏል። በሂደቱ በርካታ ምስክሮችን የመስማት፣ የሰነድ ማስረጃዎችን የማደራጀት እና ክስ የመመስረት ሥራ ራሱን በቻለ ተቋም እንዲሠራ መደረጉ[14] በጥንካሬ ሊወሰድ የሚገባው አፈፃፀም ነው። በተጨማሪም - በኢህአዴግ ቀጣይ የሥልጣን አመታት አዲስ ሕገ-መንግስት የማውጣት፣ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የማቋቋም ሥራዎች ተሠርተዋል።

ይሁን እንጂ በኢህአዴግ የስልጣን ዘመን ተግባራዊ የተደረገው የሽግግር ፍትሕ ሥራ - ከተገቢ ከሽግግር ፍትሕ መርሆዎች እና አላባዎች አንፃር ሲታይ በዋናነት በክስ ላይ ያተኮረ፣ ሌሎች የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ማለትም እውነት ማፈላለግ እና የእርቅ ተግባራትን፣ እንዲሁም ማካካሻ እና ተቋማዊ ማሻሻያን በአግባቡ እና በተሟላ መንገድ ተግባራዊ ያደረገ አልነበረም። ሂደቱ አሳታፊና አውድ-ተኮር ያልነበረ ከመሆኑም በላይ - የክስ ሂደቱም ቢሆን በሁሉም ወገን በኩል ሊጠየቁ የሚገባቸውን አካላት ያላካተተ፣ ረዥም ጊዜ የወሰደ እና የተጠያቂነት ደረጃን ሳይለይ የቀረበ በመሆኑ በውጤታማነቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል።

ከ2010 ዓ.ም ወዲህ በኢትዮጵያ የተፈጠረውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ - መንግስት ያለፉትን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና በደሎች በእውነት፣ በእርቅ እና በፍትህ ላይ ተመስርቶ ለመፍታት እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መንገዱን ለማመቻቸት የተለያዩ የሽግግር ፍትህ እርምጃዎችን ወስዷል። ከነዚህም ውስጥ ለተፈጠሩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችና በደሎች እንደመንግስት በይፋ ህዝብን ይቅርታ መጠየቅ፣ የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋም፣ ክስ፣ ምህረት እና ለሽግግር ፍትህ ሂደት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የሕግ እና የተቋማት ማሻሻያዎችን ማከናወን በጥንካሬ የሚጠቀሱ ሥራዎች ናቸው።

ሆኖም በወቅቱ የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በተሟላ እና ወጥነት ባለው መልኩ በማቀናጀት ለመተግበር የሚያስችል የፖሊሲ እሳቤ ያልነበረ መሆኑ፣ አንዱ እርምጃ ከሌላው ጋር ያለው መስተጋብር በግልፅ አለመደንገጉ፣ ሂደቱ በአሳታፊነት መርህ ላይ ተመስርቶ የተመራ አለመሆኑ፣ እንዲሁም የተወሰዱ እርምጃዎችም ቢሆኑ ከአወቃቀር፣ ከአሰራር እና ከህግ ክፍተቶች ጋር የተያያዙ ጉድለቶች የነበረባቸው መሆኑ - የሽግግር ፍትህ ዓላማዎችን በሚፈለገው መጠን ወይም አግባብ ማሳካት አልተቻለም።[15]

## 2.3. በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት መተግበር አስፈላጊነት እና ወቅታዊነት

ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ የተሞከሩ ስራዎች ውስን የሽግግር ፍትሕ አላባዎችን በተሟላ እና በተቀናጀ መልኩ ባለመተግበራቸው የሽግግር ፍትህ ዓላማን ማሳካት አልቻሉም።

ስለሆነም በተሟላ እና በተቀናጀ መልኩ የሚዘረጋ፣ አሳታፊ፣ ተጎጂዎችን ማዕከል ያደረገ፣ ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎችን የሚያከብር፣ ከሌሎች ሀገራት እና ከሀገራችን ልምምዶች ትምህርት የሚቀምር፣ በሀገራችን ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አውድ ላይ የተመሰረተ እና በግልፅ የፖሊሲ ማዕቀፍ የሚመራ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ ነው። የሽግግር ፍትሕ ለኢትዮጵያ ካለው አስፈላጊነትና ወቅታዊነት ጋር በተያያዘ - የሚከተሉትን ማሳያ ምክንያቶች መጥቀስ ይቻላል።

### I. ያለው ሀገራዊ አውድ የሽግግር ፍትሕ ትግበራን የሚሻ መሆኑ

[14] የልዩ አቃቤ ህግ ጽህፈት ቤት፡ 'ደም ያዘለ ዶሴ፡ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ/መንግስት አባላት በንፁሃን ዜጎች ላይ የተፈፀመ ወንጀል ዘገባ'፡ 2002 ዓ.ም አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

[15] የፍትህ ሚኒስቴር፡ 'የሽግግር ፍትህ በኢትዮጵያ፡ አሁናዊ ሁኔታ እና ቀጣይ አቅጣጫ' (2014)፡ ኢትዮጵያ
የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች፡ ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለመሰብሰብ የተዘጋጀ'፡ ጥር 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች - ጥያቄዎችን የሚያነሱ ሀይሎች እርስ በርስ እና ከመንግስት ጋር ባደረጉት እና በሚያደርጉት ግጭት - በርካታ ዜጎች ሰፊና ተከታታይነት ላለው የመብት ጥሰት፣ መፈናቀል እና እንግልት ተዳርገዋል፤ እየተዳረጉም ይገኛሉ። ከዚህ ባለፈም በተለያዩ ስርዐቶች የተፈጸሙ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና የተሳሳቱ የታሪክ አረዳዶች በአግባቡ ተዳሰው እና ተፈትሸው ምላሽ እንዲሰጣቸው ባለመደረጉ አሁን ላይ እየተስተዋለ ላለው ግጭት፣ መፈናቀልና አለመረጋጋት መነሻ ሲሆኑ ይስተዋላል።

በመሆኑም የሀገሪቱን አሁናዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ፣ ያለፈውን በአግባቡ የሚያስተናግድ፣ የሀገሪቱን ሰላም፣ መረጋጋት፣ የሕግ የበላይነት፣ እና የዜጎች ሰብአዊ መብቶችን የሚያረጋግጥ፣ በአጠቃላይም ሀገሪቱ ከምትገኝበት ውስብስብ የችግሮች አዙሪት እንድትወጣና በቀጣይም ጠንካራ መሠረት ለመጣል የሚያስችል የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር ወሳኝና ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ነው።

### II. ከሀገረ-መንግስት ግንባታና ቀጣይነት አንጻር ሲታይ

ይቅር መባባልና እርቅ ማውረድ ለሀገሪቱ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። የነበሩና የቀጠሉ ውስብስብ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ካልተበጀላቸው ታሪካዊ ኢፍትሃዊነትን የሚያሳዩ ተፃራሪ ትርክቶች እየሰፉ ሄደው ለባሰ ግጭትና ብጥብጥ ምክንያት ሆነው ሊቀጥሉ ይችላሉ።

በመሆኑም በተለያዩ ምክንያቶች በብዙ የአገሪቱ አካባቢዎች በሚገኙ ህዝቦች መካከል ያለውን መለያየት ለማስተካከል እና ለማቀራረብ፣ የሻከረውን ግንኙነት ለመጠገን፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና እርቅ ለመፍጠር - የሽግግር ፍትህ ስልቶችን በአግባቡ በመተግበር መፍትሔ ማበጀት - የህዝብን ሰላምና አንድነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

በተጨማሪም ውጤታማ የሽግግር ፍትሕ ሥርዓትን መተግበር የዲሞክራሲ ሽግግርን ለማሳለጥ፣ ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ፣ ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት እንደመሆኑ መጠን - እነዚህ እሴቶች ተግባራዊ የሚደረጉበት የሽግግር ፍትህ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ይሆናል።

## 2.4. የሽግግር ፍትህ ሥርዓት አስፈላጊነትን የሚያጠናክሩ ተጨማሪ ወቅታዊ ኩነቶች

ከላይ ከተገለጹት ምክንያቶች በተጨማሪ - የሽግግር ፍትህ ሥርዓት መዘርጋትን አስፈላጊነት የሚያጎሉ ሌሎች ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታዎችም አሉ።

ባለፉት ጥቂት አመታት በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው ግጭት ማእቀፍ ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መፈፀሙ በተደጋጋሚ ሲነሳ የቆየ ጉዳይ ነው። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ተፈናቅለዋል፤ ንብረቶች ወድመዋል፤ ብዙዎቹ ጉዳቶች በሕገ-መንግስቱ እና በዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት እና ሌሎች ህጎች ላይ የተጠበቁ መሠረታዊ መብቶችን እና ጥበቃዎችን በመጣስ የተፈፀሙ ወንጀሎች ናቸው።[16] ይህን ተከትሎ በተለይ በትግራይ፣ በአማራ

[16] The Federal Democratic Republic of Ethiopia Inter-Ministerial Taskforce on Accountability and Redress. 'Investigation and Prosecutions Committee Criminal Investigation Preliminary Report (Phase I) - On Allegations of War crimes, Crimes Against Humanity and Other Violations of International Human Rights Law, International Humanitarian Law, and Domestic Criminal Law Committed by the Parties to the Conflict in Northern Ethiopia'. 19 September 2022. Addis Ababa, Ethiopia.

*See also* የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት፡ 'በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትግራይ ክልል ውስጥ በተፈጠረው ግጭት ወቅት በሁሉም የግጭቱ ተሳታፊ አካላት ተፈጽመዋል የተባሉትን የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች፣ የሰብአዊነት እና የስደተኞች ሕግጋት ጥሰቶች በተመለከተ በጋራ ያካሄዱት የምርመራ ሪፖርት'፡ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፡ 'በኢትዮጵያ የአፋር እና የአማራ ክልሎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ የተደረገ ምርመራ ሪፖርት'፡ 2014 ዓ.ም ኢትዮጵያ

እና በአፋር ክልሎች ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እና ወንጀሎችን በመመርመር እና መረጃዎችን በማደራጀት ረገድ መንግስት ባቋቋመው የሚኒስትሮች ግብረ-ሀይል አማካኝነት በርካታ የምርመራ እና ውስን የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች ተከናውነዋል።[17] ሆኖም ከጉዳዮቹ ግዝፈት እና ውስብስብነት አንፃር በመደበኛው የሕግ ሥርዓት የተሟላ ፍትህ ማስፈን የሚቻልበት እድል አነስተኛ ሆኖ በመገኘቱ - የክስ መመስረት እና ተጠያቂነትን የማስፈን ሥራዎች ለጊዜው እንዳይቀጥሉ ተደርጓል።

ይሁን እንጂ የወንጀል ተጠያቂነትን የማረጋገጡን ሂደት ለተራዘመ ጊዜ ማቆየት በራሱ ኢፍትሀዊነትን የሚያስከትል በመሆኑ - የተሟላ ፍትህን ለማስፈን በሚያስችል ማዕቀፍ ስር የወንጀል ተጠያቂነትን ማረጋገጥ እንዲቻል የሽግግር ፍትህ ሂደትን በአፋጣኝ መዘርጋት - የሽግግር ፍትህን አስፈላጊነት ካጎሉ ተጨማሪ ገፊ ምክንያቶች አንዱ ሆኖ ተገኝቷል።

በሌላ በኩል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት እና በህወሓት መካከል ጥቅምት 2015 ዓ.ም የተፈረመው የሰላም ስምምነት ተጨማሪ ገፊ ክስተት ነው። ለሁለት አመታት በፌዴራል መንግስት እና በህወሓት መካከል ሲደረግ የነበረውን ደም አፋሳሽ ግጭት የቋጨው ይህ ስምምነት - የግጭት ኩነትን ከማስቀም ባለፈ ሀገር-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት መዘርጋትን እንደ አስገዳጅ ሁኔታ ያስቀምጣል። በተለይም የስምምነቱ አንቀጽ 10(3) - በቀጣይ ዘላቂ ሰላም እና መረጋጋት ለማምጣት የሚያስችል፣ ከሕገ-መንግስቱና ከአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ ማዕቀፍ ጋር የተጣጣመ፣ ተጠያቂነትን፣ እውነት ማፈላለግን፣ እርቅንና ተጎጂዎችን የመካስ ዓላማ የያዘ እና በዝግጅት ሂደቱ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚሳተፉበት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ እንዲዘጋጅ ይጠይቃል። ስለሆነም ይህ ወቅታዊ ኩነት የሽግግር ፍትህን አስፈላጊነት ካጎሉ ተጨማሪ ምክንያቶች አንዱ ነው ማለት ይቻላል።

### 2.5. የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አስፈላጊነት

የሽግግር ፍትሕን ተግባራዊ ያደረጉ ሀገራት - ሂደታቸውን ለመምራት የተለያዩ መንገዶችን ተከትለዋል። በሰፊው የተለመደ ባይሆንም - ከእነዚህ አካሄዶች አንዱ ሁሉን-አቀፍ የሆነ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አስቀድሞ መቅረጽና ሂደቱን በፖሊሲ መምራት ነው። በሀገራችን ተግባራዊ ለማድረግ የታሰበውን የሽግግር ፍትሕ ሂደት - የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በመቅረጽ በዚሁ ማእቀፍ እንዲመራና እንዲተገበር ማድረግ - የሽግግር ፍትሕ ሂደቱን ቀላልና ውጤታማ የማድረግ እድል ይፈጥራል።

ውጤታማ የሽግግር ፍትሕ ሂደት - ሁሉንም የሽግግር ፍትሕ ስልቶች በተናበበ እና በተቀናጀ መልኩ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል። በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት ውስን የሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የተሞከረ ቢሆንም - ሂደቶቹ የሽግግር ፍትህ ስልቶችን ዓላማ፣ ግብ እና የሚኖራቸውን መስተጋብር በሚያንሰላስል የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሰላልተመሩ - አማራጮቹ በተንጠባጠበ እና በማይመጋገብ መልኩ እንዲተገበሩ ሆኗል። ይህም የሽግግር ፍትሕ ስልቶቹ በሚፈለገው መጠን ውጤታማ እንዳይሆኑ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በመሆኑም የሽግግር ፍትሕ አጠቃላይ ሂደት እና ይዘትን የሚመራ ፖሊሲ ማዘጋጀት - የሽግግር ፍትሕ አንኳር ስልቶችን በተሰናሰለ እና በተመጋገበ መንገድ ለማስኬድና የሽግግር ፍትሕ ስልቶች የሆኑትን የወንጀል ፍትሕን ማስፈን፣ እውነትን መፈለግ እና ይፋ ማውጣት፣ የእርቅ ተግባራት፣ ማካካሻ እና ተቋማዊ ማሻሻያዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ያስችላል።

[17] The Federal Democratic Republic of Ethiopia Inter-Ministerial Taskforce on Accountability and Redress. Note 16.

## ክፍል ሶስት

## የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን መቋቋም

### 3.1. የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን አሰያየም

የሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በሽግግር ፍትህ እና ሰብአዊ መብት ጉዳዮች ላይ ጥናት እና ምርምር ከሚያደርጉ ምሁራን፣ ከሰብአዊ መብት ባለሙያዎች፣ ከጠበቆች፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እንዲሁም ከፖሊሲ እና ሕግ ማርቀቅ ባለሙያዎች የተውጣጡ 13 ከፍተኛ ባለሙያዎችን በማካተት ህዳር 2015 ዓ.ም በፍትሕ ሚኒስቴር እንዲቋቋም ተደርጓል። ከኮሚቴው አባላት መካከል አስሩ ወንዶች ሲሆኑ ሶስቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው።[18]

### 3.2. የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን የስራ ሀላፊነት

የባለሙያዎች ቡድኑ የስራ ሀላፊነት በዋናነት በሶስት ዋና ዋና ምእራፎች የተከፈለ ነው። እነዚህም የቅድመ-ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ፣ የረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ፣ እና የድህረ-ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ ናቸው።

#### I. የቅድመ-ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ

ይህ ምዕራፍ በዋናነት የሚከተሉት ተግባራት የተከናወኑበት ነው።

- የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ፅሁፍ እና ሌሎች ሰነዶችን ማዘጋጀት፤
- በሀገር-አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የፖሊሲ ግብዓት ማሰባሰቢያ የህዝብ ምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጮች ሰነድ ላይ የተመሰረተ የግብዓት ማሰባሰብ ሥራ ማከናወን፤
- የሕዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቶችን አፈፃፀም፣ ግኝቶችን፣ ማጠቃለያዎችን እና ምክረ-ሀሳቦችን የሚመለከት ዝርዝር ሪፖርት ማዘጋጀት፣ እና የተዘጋጀውን ሪፖርት ለመንግስት፣ ለህዝብ እና ለባለድርሻ አካላት ይፋ ማድረግ።

#### II. የረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ

ይህ ምዕራፍ ከሕዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት የተገኙ መረጃዎችን ከመሰረታዊ የሽግግር ፍትሕ መርሆዎች ጋር በማገናዘብ እና በማሰናሰል - ሀገራዊ የሽግግር ፍትሕ ረቂቅ የፖሊሲ ሰነድ የማዘጋጀት ሥራ የሚከናወንበት ምዕራፍ ነው።

#### III. የድህረ-ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ

ይህ ምዕራፍ የባለሙያዎች ቡድኑ የሚከተሉትን ተግባራት የሚያከናውንበት ነው።

- በተዘጋጀው የሽግግር ፍትሕ ረቂቅ የፖሊሲ ሰነድ ላይ ውስን ሀገር-አቀፍ እና ክልላዊ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ተጨማሪ ግብዐት የማሰባሰብ ሥራ ማከናወን፤
- በተሰበሰቡ ግብዓቶች መሠረት የረቂቅ ፖሊሲውን ይዘት አዳብሮ የመጨረሻ የሽግግር ፍትሕ ረቂቅ የፖሊሲ ሰነድ ማዘጋጀት፤ እና
- የተዘጋጀውን ረቂቅ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ሰነድ ከነአባሪዎቹ እና የዶክሜንቴሽን ሥራዎች ለሚመለከተው የመንግስት አካል ማስረከብ።

[18] ማጣቀሻ ቁጥር 5.

## 3.3. የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን እና ፖሊሲ የማዘጋጀት ስራዎች የተመሩባቸው ሰነዶች

የሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እንዲችል የተለያዩ ይዘት እና ዓላማ ያላቸውን ስድስት ሰነዶችን ያዘጋጀ ሲሆን - የሰነዶቹ ምንነት፣ ዓላማና የዝግጅት ሂደት እንደሚከተለው ተዳሷል።

### I. ብሔራዊ የምክክር መድረኮች እና የሽግግር ፍትሕ ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ፍኖተ-ካርታ[19]

ይህ ሰነድ በአጠቃላይ ስድስት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን በውስጡ ከብሔራዊ የምክክር መድረኮች እና የሽግግር ፍትሕ ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ጋር የተገናኙ የተለያዩ ጉዳዮች ተካተዋል። ሰነዱ - የቅድመ-ረቂቅ ፖሊሲ ብሔራዊ የምክክር መድረኮችን የሚመለከቱ ክፍሎች ያሉት ሲሆን - በዚህም የሕዝብ ምክክር አስፈላጊነት፣ በዓለም አቀፍ ሕጎች ያለው ቦታ፣ የምክክር መድረኮች ዓላማ፣ የሚመሩበት መርሆ፣ በምክክሩ መሳተፍ የሚኖርባቸው ሰዎች እና የሚመረጡበት መስፈርት፣ እና ምክክሮቹ የሚካሄዱባቸውን ስነ-ዘዴዎች በዝርዝር ተመላክተዋል።

በተጨማሪም ሰነዱ - የምክክር መድረኮች የሚካሄዱባቸውን ቦታዎች እና ጊዜያት፣ የምክክር መድረክ እና ግብዓት የማሰባሰብ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ግብዓቶች የሚጠናቀሩበትን የሪፖርት ዝግጅት ጊዜ እና የሰው ኃይል፣ እንዲሁም የረቂቅ ፖሊሲ እና የድህረ-ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቶችን ዳሰሷል። የመጨረሻው ክፍል አጠቃላይ የበጀት ማዕቀፍን እንዲያመላክት ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

### II. የሥራ ሒደት ካርታ እና የአፈጻጸም እቅድ[20]

ይህ ሰነድ በዋናነት የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን አባላት በተለያዩ የፖሊሲው ዝግጅት ሂደቶች የሚኖራቸውን ሚና እና ሀላፊነት የሚያስቀምጥ እና የምክክር እና የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች የሚከናወኑበትን የጊዜ ማዕቀፍ በዝርዝር የሚገልጽ ነው።

### III. በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የአጋር አካላት ተሳትፎ ማንዋል[21]

ይህ ማንዋል በሶስት ክፍሎች እና በአስራ አንድ አንቀፆች የተዋቀረ ሲሆን - በተለይ በማኑዋሉ ክፍል ሁለት ሥር ድጋፍ ማድረግ ስለሚችሉ አካላትና ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ፣ የድጋፍ አድራጊ (አጋር አካል) ሚና፣ ወሰን እና የግንኙነት አግባቦችን ደንግጓል።

### IV. የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የህዝብ የግንኙነት/ኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ[22]

የህዝብ ግንኙነት/ኮምዩኒኬሽን ስትራቴጂ ሰነዱ ዓላማ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አስፈላጊነት፣ ሂደት እና ተግባራትን አስመልክቶ ለሕዝብ እና ለሚመለከታቸው አካላት ወቅታዊ መረጃ መስጠትና ግልጽ ማድረግ የሚቻልበትን አሰራር ማመላከት፣ ተገቢ መረጃ በየጊዜው በማቅረብ ሕዝቡ የሚጠበቅበትን ተሳትፎ እና ድጋፍ በአግባቡ እንዲወጣ ማስቻል፣ እንዲሁም በሕዝብ ተሳትፎ የዳበረና የህዝብ አመኔታን ያተረፈ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የሚቀረጽበትን እድል ማስፋት ነው።

ስትራቴጂው በሁለት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን - የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የማዘጋጀት ስራ ሂደትን በተመለከተ ለሚቀርብ የመረጃ ጥያቄ መልስ የሚሰጥበትን አግባብ፣ መረጃ የሚሰጡ አካላትን፣ መረጃ ሊሰጣቸው ስለሚችሉ

---

[19] Transitional Justice Working Group of Experts. 'Roadmap for National Consultations and Preparation of a Draft Transitional Justice Policy'. January 2023. Addis Ababa Ethiopia.

[20] Transitional Justice Working Group of Experts. Process Map and Execution Plan. 2023.

[21] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የአጋር አካላት ተሳትፎ ማንዋል'፡ ጥር 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

[22] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ'፡ ጥር 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

አካላት፣ የመረጃ/የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት፣ የመረጃ/የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት፣ ከመንግስት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተቋም ጋር ስለሚኖር ግንኙነት፣ በከፍተኛ አመራሩ እና በስራ ቡድኑ መካከል ስለሚኖር ግንኙነት፣ በመረጃ አሰጣጥ ሂደት መከተል ስለሚገባ ሥነ-ምግባር፣ እና የህዝብ አስተያየትና ሃሳብ የመገምገምና የማካተት ሥርዓትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቷል።

## V. የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ሰነድ ማደራጀት እና ቴምፕሌት[23]

የዚህ ሰነድ ዋና ዓላማ በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት - በተለያየ የዝግጅቱ ደረጃዎች የተሰሩ ሥራዎች እና ከዝግጅት ሂደቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ውይይቶች ተሰንደው የሚያዙበትን አሠራር ማመላከት ነው። የሚሰነዱ መረጃዎች - ለሚዘጋጀው ፖሊሲ ዋና ግብዓት ሆነው ከማገልገል ባለፈ - ወደፊት የፖሊሲው ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላም - የፖሊሲውን አጠቃላይ የዝግጅት ሂደት አስመልክቶ ማንኛውም አካል የተደራጀ እና በቀላሉ ጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎችን የሚያገኝባቸው ታሪካዊ ሰነዶች እንዲሆኑ ታስበው የሚዘጋጁ ናቸው።

በዚህ ረገድ ሰነዱ በሶስት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን - የመጀመሪያው ክፍል የሚሰነዱ ሰነዶችን አይነት ይመለከታል። ክፍል ሁለት የሰነዳ አስተዳደርን እና ሀላፊነትን የሚዳስስ ሲሆን፣ ክፍል ሶስት የሰነዳ ደረጃዎች እና ፎርማት (Standardization and Format) የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ነው።

## VI. የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት የባለሙያዎች ቡድን አባላት የአሰራርና የስነ-ምግባር መመሪያ

የዚህ መመሪያ ዓላማ - የባለሙያዎች ቡድኑ አባላት በፖሊሲ ዝግጅት ሂደቶች በሚዘጋጁ የምክክር መድረኮች፣ ከሚዲያ አጠቃቀም እና ከሚዲያ አካላት ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት፣ እና መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በሚመሰርቱት ግንኙነት ማእቀፍ የሚከተሏቸውን የስነ-ምግባር መርሆዎች ዝርዝሮ ማስቀመጥ ነው። መመሪያው በሶስት ክፍሎች እና ዘጠኝ አንቀፆች የተዋቀረ ነው።

[23] Transitional Justice Working Group of Experts. 'Transitional Justice Policy Documentation Process and Templates'. January 2023. Addis Ababa. Ethiopia.

## ክፍል አራት

## የሽግግር ፍትህ ምክክር አስፈላጊነት፣ የምክክሩ ሂደት እና ምክክሩ የተመራባቸው መርሆዎች አፈፃፀም

### 4.1. የምክክር ሂደቱ አስፈላጊነት

የሽግግር ፍትህን የሚመለከት ማናቸውም የሥራ ሂደት በዓለም-አቀፍ ደረጃ ሰፊ ተቀባይነት ባገኙ የሰብአዊ መብት ሕጎች እና መርሆች ላይ የተመሰረተ መሆን ይጠበቅበታል። ሰብዓዊ መብት ተኮር እና የመብት ጥሰት ሰለባዎችን ማዕከል ያደረገ የሽግግር ፍትህ ምክክር ስራ ለማከናወንም ሆነ ተያያዥ የፖሊሲ ማዕቀፎችን ከማደራጀት አንፃር - ሂደቶቹን የሚመሩ ዓለም-አቀፍ እና አህጉራዊ ሕጎችና መርሆዎች በተለያዩ ጊዜያት ወጥተዋል። የእነዚህ መርሆዎች መኖር - የአለማቀፉ ማህበረሰብ እና የሀገራት ተሞክሮ በየጊዜው እንዲሻሻል እና ተግባራዊ የተደረጉ የሽግግር ፍትህ-ነክ ስራዎችም በጠሩ አካሄዶች ላይ ተመስርተው እንዲከናወኑ ሰፊ እድል ፈጥሯል።

የባለሙያዎች ቡድኑም - የምክክር እና ግብዓት የማሰባሰብ ሥራዎቹ ከነዚህ ዓለም-አቀፍ ሰነዶች ይዘት እና ተጠባቂ ግዴታዎች ጋር በተጣጣመ እና የአገራዊ አውዱን ልዩ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ እንዲከናወኑ አድርጓል።[24]

#### 4.1.1. ምክክር እንደ መብት

በኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት[25] እና በርካታ አለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች ላይ[26] ሀገራዊ ወይም ሕዝባዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ በሚደረጉ ውይይቶች ሰዎች የሚኖራቸውን ለምክክር የመጠየቅ እና የመሳተፍ መብት በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ መንገድ ተካተው ይገኛሉ። ይህ መብት ሰዎች በተለይ ጥቅማቸውን በሚመለከቱ የሕዝብ

---

[24] በዚህ ረገድ በሰፊው ጥቅም ላይ የዋሉ ዋና ዋና ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው።

International Covenant on Civil and Political Rights (1966); International Covenant on Social, Economic and Cultural Rights (1966); *Convention against Torture* and Other Cruel, Inhuman or Degrading Treatment or Punishment (1984)፡ Convention on the Prevention and Punishment of the Crime of Genocide (1948); International Convention on the Elimination of Racial Discrimination (1965); Intentional Convention on the Elimination of all Forms of Discrimination Against Women (1979); Convention on the Rights of the Child (1989); Convention on the Rights of Persons with Disabilities (2006); General Assembly Resolution 60/147 - Basic Principles and Guidelines on Right to Remedy/Reparation for Victims of Gross Violations (2005); Commission on Human Rights - Principles for protection/promotion of HRs through action to combat impunity 1997, 2005; The rule of law and transitional justice in conflict and post-conflict societies : Report of the Secretary-General (2004, 2011); Guidance Note of the Secretary-General - United Nations Approach to Transitional Justice (2010); OHCHR Rule of law tools for post-conflict societies (2006); African Charter on Human and Peoples Rights (1981); African Charter on Rights and Welfare of the Child (1990); Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Women in Africa (2003); African Union Convention for the Protection and Assistance of Internally Displaced Persons in Africa (*Kampala Convention*) (2009); Protocol Relating to the Establishment of the Peace and Security Council of the African Union (2002); AU Post-Conflict Reconstruction and Development Policy of 2006AU Transitional Justice Policy 2019.

[25] The Constitution of the Federal Democractic Republic Ethiopia. Proclamation No.1/1995. Article 35(6) and 43(2).

[26] ለአብነት ያህል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

Art. 21 and 27 of UDHR; Art. 25 of ICCPR; Art. 13 (1) and 15 (1) of ICESCR; Arts 7, 8, 13 (c) and 14 (2) of CEDAW; Art. 5 (e) (vi) of CERD; Arts 12 and 31 of the CRC; Arts. 3(c), 4)(3), 9, 29 and 30 CRPD; Arts. 41 and 42 (2) International Convention on the Rights of All Migrant Workers and Members of their Families; Arts. 1(1), 2 and 8(2) United Nations Declaration on the Right to Development; Arts. 5, 18, 19 and 21 of United Nations Declaration on the Rights of Indigenous Peoples.

አስተዳደር፣ የሕግ እና የፖሊሲ ጉዳዮች ዝግጅት እና አተገባበር ላይ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት እና በውሳኔዎች ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩበትን እድል የሚፈጥር ነው።

በባለሙያዎች ቡድኑ የስራ ሂደት - የሽግግር ፍትህ የሕዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ - በልዩነት ከታች ወደ ላይ በሚፈስ የሕዝብ እና ወሳኝ ባለድርሻ አካላት የመጠየቅ፣ የመሳተፍ እና እይታቸውን የማካፈል መብት ላይ ተመርኩዞ እንዲደራጅ እና እንዲመራ የተደረገውም ለዚህ መሠረታዊ የዜጎች መብት ሙሉ እውቅና ለመስጠት ነው።

## 4.1.2. በሽግግር ፍትህ አውድ የሚኖረው ተጨማሪ ፋይዳ

በሽግግር ፍትህ ሥራ ልዩ አውድ - ከምክክር ጋር የሚያያዙ የሰዎችን መብት ተግባራዊ ማድረግን የግድ የሚያሰኙ በርካታ ኩነቶች አሉ። መብቱን አጠናክረው የመሰረቱ፣ ይበልጥ ያብራሩ እና በተግባር የሚፈፀምበትን አግባብ ያመላከቱ የተለያዩ ሰነዶችም ተዘጋጅተዋል። መሰረታዊ መልእክታቸው - የሽግግር ፍትህን የሚመለከቱ የምክክር፣ የፖሊሲ ቀረፃ እና ትግበራ ስራዎች ሁሉ ሰብአዊ መብት-ተኮር መሆን እንዳለባቸው፣ በተለይም ሰዎች በሽግግር ፍትህ ፕሮግራም ቀረፃ ምዕራፍ ያለመድልዎ ይሳተፉ ዘንድ ሊጠየቁ እና ጥልቅ ውይይት ሊያካሂዱ የሚገባ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው። በርግጥም በተ.መ.ድ ዋና ፀሃፊ ሪፖርት ላይ በግልፅ እንደተመለከተው - የአንድ የሽግግር ፍትህ ተሞክሮ ስኬት በዋናነት የሚመሰረተው ሂደቱ ባሳለፈው የህዝብ እና ተጎጂ-ተኮር ምክክር ጥራት እና ብዛት ነው።[27]

የባለሙያዎች ቡድኑ - በኢትዮጵያ የሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ተሞክሮ በሀገር-አቀፍ ደረጃ በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች በሚካሄዱ የህዝብ ምክክርና ተሳትፎ እንዲጀመርና ከታች ወደላይ በሚደራጅ ሂደት እንዲያልፍ ማድረጉ - ምክክር እና ተሳትፎ የሽግግር ፍትህ ስራ መሰረታዊ አውድ መሆናቸውን ከመገንዘብና ለዚህ ተገቢ እውቅና ከመስጠት የሚነጭ ነው።

በምክክር መድረኮች እና በፖሊሲ ማርቀቅ ሂደቶች ላይ የመሳተፍ መብት የተረጋገጠና በሕግና በምርጥ የአገራት ተመክሮ ሰፊ እውቅና የተሰጠው መሆኑ አንድ ነገር ሆኖ - በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የህዝባዊ ምክክሮችና ተሳትፎ መከናወን አስፈላጊነትን የሚያጎሉ ተጨማሪ ምክንያቶችም አሉ። እነዚህ ገፊ ምክንያቶች በባለሙያዎች ቡድኑ ከሶስት ማእዘናት አንፃር ታይተዋል።

**የመጀመሪያው የባለሙያዎች ቡድኑ ምልከታ** - የቅድመ-ፖሊሲ ህዝባዊ ምክክሮች እና የግብዓት ማሰባሰብ ስራዎችን ማካሄድ በራሱ - በኋላ ላይ በፖሊሲው ይዘት ላይ ተፅእኖ ማሳደር የሚችሉ መሬት የረገጡ እይታዎችንና ሀሳቦችን ከጉዳዩ ባለቤት ከሆነው ህዝብ መስማት የሚቻልበትን ሰፊ እድል ይሰጣል የሚል ነው።

በርጥም በተግባር እንደተስተዋለው ሂደቱ በዚህ አግባብ በመመራቱ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል በተካሄዱ መድረኮች ላይ የተሳተፉ ሰዎች - ከሽግግር ፍትህ ጋር የተያያዘ ሀሳባቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ምርጫቸውን እና ተስፋቸውን በነፃነት እና ደህንነታቸውን በጠበቀ አውድ ማንሸራሸር የቻሉበትን ምቹ መድረክ እንዲፈጠር አድርጓል። ይህም በበኩሉ በዚህ ሪፖርት ክፍል 8 ላይ እንደተመለከተው ህዝቡ በገለፀው ሀሳብ እና ወደፊት በፖሊሲው ውስጥ በሚካተቱ የሽግግር ፍትህ አሰራር ሀሳቦች መካከል እጅጉን የተቀራረበ ይዘት እንዲንፀባረቅ አስችሏል። ይህ አካሄድ በቀጣይ የፖሊሲው የትግበራ ምእራፎች ላይ ከኢትዮጵያውያን የሚጠበቁ የባለቤትነት ጥያቄዎችን በአግባቡ ለመመለስ፣ እንዲሁም ሁሉንም የሽግግር ፍትህ አላባዎች በተሳካ መንገድ ለመተግበር የሚቻልበትን እድል ይፈጥራል።

[27] The United Nations Security Council. 'The Rule of Law and Transitional Justice in Conflict and Post-conflict Societies'. Report of the Secretary-General. S/2004/616. 2004. p.7

***ሁለተኛው የባለሙያዎች ቡድኑ ምልከታ*** - *የቅድመ-ፖሊሲ ህዝባዊ ምክክሮች እና የግብዓት ማሰባሰብ ስራዎችን ማካሄድ - ተሳታፊዎች በተለይም የመብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች - ለደረሰባቸው ጉዳት እውቅና የመስጠት እና በፖሊሲው ይዘት ላይ አሻራቸውን እንዲያሳርፉ እድል ይሰጣቸዋል ከሚል የሚነሳ ነው። በሀገር-አቀፍ ደረጃ በተካሄዱ ምክክሮች በተግባር እንደተስተዋለው - ምክክሮቹ ህዝባዊ ተሳትፎንና የተጎጂዎችን ድምፅ ባማከለ መልኩ መከናወናቸው የተሳታፊዎች በራስ መተማመን ከፍ እንዲል፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የተሰጣቸው ቦታ ወይም ግምት እንዲሻሻል እና ግለሰባዊ አቅማቸው እንዲጠናከር አስተዋጽኦ አድርጓል።*

***ሶስተኛው የባለሙያዎች ቡድኑ ምልከታ*** - *የቅድመ-ፖሊሲ ህዝባዊ ምክክሮች እና የግብዓት ማሰባሰብ ስራዎችን ማካሄድ በአጠቃላይ የምክክር ሂደቱ እና በሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት ተአማኒነት፣ ተቀባይነት እና ዘላቂነት ላይ ቀጥተኛ አዎንታዊ ተፅእኖ የሚያሳድር መሆኑ ነው። ሕዝብን በዚህ የተሳትፎ ደረጃ የጉዳይ ባለቤት ማድረግ፣ ተሳታፊውም በሀገሩ ጉዳይ ስሜቱ ሳይደፈርስ ወይም ተስፋ ሳይቆርጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያሰማበት መድረክ በራሱ - ከሽግግር ፍትህ ግቦች አንፃር ሲታይ ትልቅ እርምጃ ነው።*

### 4.1.3. ***የምክክር ሂደቱ በኢትዮጵያ ሥር-ነቀል የፖሊሲ አወጣጥ ዘይቤን ስለማስተዋወቁ***

*የሽግግር ፍትህ መሠረታዊ መርሆዎችን በመከተል በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ላይ የተካሄደው ሀገር-አቀፍ የሕዝብ ምክክር እና ግብዓት የማሰባሰብ ሂደት በኢትዮጵያ የሕግ እና ፖሊሲ አወጣጥ ታሪክ አዲስ እና ስር-ነቀል የታሪክ ክዋኔ ሆኖ አልፏል።*

*በምክክር እና በፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ላይ የመሳተፍ መብት ህገ-መንግስታዊ ሽፋን የተሰጠው መብት ከመሆኑም በላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃም የፖሊሲ አረቃቀቅ እና አወጣጥ ሂደትን የሚገዙ ዝርዝር አሠራሮች ዳብረዋል። እንዲያም ሆኖ - በኢትዮጵያ ታሪክ አንድን ሀገራዊ የፖሊሲ ማዕቀፍ በማውጣት ሂደት - በዚህ ደረጃ በተለይ ለመብት ጥሰት ሰለባዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆነውን ሕዝብ እና ባለድርሻ አካላትን በቀጥታ በነፃ የልየታ እና አመራረጥ ሂደት እንዲያልፉ እና እንዲሳተፉ በማድረግ - ህዝብ በስፋት የተሳተፈበት እና ከፍተኛ ሀብት የፈሰሰበት የቅድመ-ፖሊሲ ማርቀቅ ህዝባዊ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ስራ ከአሁን በፊት በሀገራችን አልነበረም ብሎ መናገር ይቻላል።*

*በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ እንዲፈቱ ከሚታሰቡ ውስብስብ ሀገራዊ ችግሮች እና በሽግግር ፍትህ ላይ ከቀረቡ ተወዳዳሪ/ተነፃፃሪ አማራጮች አንፃር ሲታይ - በሀገር-አቀፍ ደረጃ ህዝብን በምክክር መድረኮች ላይ በስፋት የማሳተፍ አዲስ አሠራር ተግባራዊ መደረጉ - የሚወጡ ፖሊሲዎች ህዝባዊ ባለቤት እና ድጋፍ እንዲኖራቸው ከማድረግ አንፃር ታላቅ ጅማሮ ነው።*

*ከላይ እንደተመለከተው - በበርካታ ሀገራት ተሞክሮ የሽግግር ፍትህ ስኬትን ከሚወስኑ ትላልቅ ኩነቶች አንዱ እና ዋናው ህዝቡ እና የመብት ጥሰት ተጎጂዎች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ - በተለይም በምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ምዕራፍ ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ መጠንና ጥራት ነው። በርግጥም በሕዝብ ሰፊ ተሳትፎ ላይ በተመሠረተ የምክክር ሂደት ያላለፈ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አወጣጥ እና ትግበራ ሥራ በብዙ ተግዳሮቶች ለመፈተን እና ውጤታማ ላለመሆን የሚኖረው እድል ከፍተኛ ነው።*

## 4.2. ***ምክክር/ግብዓት የማሰበባሰብ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች፣ ምክክር የተካሄደባቸው ቦታዎች፣ የተሳተፉ ሰዎች እና የጊዜ ሰሌዳ***

### 4.2.1. ***የቅድመ-ረቂቅ ፖሊሲ የምክክር እና የግብዓት ማሰባሰብ ሂደት ዋና ዋና ስራዎች***

*በሀገር-አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎች እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የቅድመ-ፖሊሲ ማርቀቅ የሕዝብ ምክክር እና የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች እንዲዘጋጁ በማድረግ - ከፍተኛ መጠን ያለው የህዝብ ምልከታ እና ግብዓት*

ተሰብስቧል። እነዚህ የምክክር መድረኮች በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቁ ከማድረግ አንፃር የሚከተሉት አምስት ዋና ዋና የቅድመ-ምክክር ተግባራት ተከናውነዋል።

### I. የውይይት ሰነዶች እና ቅጾች ዝግጅት

የባለሙያዎች ቡድኑ ለህዝባዊ ምክክሮቹ መነሻ የሚሆኑ እና በውይይት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ የተለያዩ ሰነዶችን ያዘጋጀ ሲሆን ከነዚህ መካከል፡-

- በግብዓት ማሰባሰቢያ የምክክር መድረኮች ላይ ለሚሳተፉ ሰዎች የሽግግር ፍትህን ጽንሰ ሀሳብ እና ሀገራዊ ተሞክሮን በተመለከተ አጠር ባለ መልኩ የሚያብራራ ሰነድ፤[28]
- በምክክር እና ግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ላይ የሚሳተፉ ሰዎች የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጮችን በውል ተረድተው ሀሳብ እንዲሰጡ የሚያግዝ - የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጮች ሰነድን አጠር ባለ መልኩ የሚያብራራ ሰነድ፤[29] እና
- በግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ አስተባባሪዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ መርሆዎችን፣ እንዲሁም የፖሊሲ አማራጮቹን ይዘት ተከትለው የተዘጋጁ የመወያያ ጥያቄዎችን የያዘ ሰነድ ይገኙበታል።[30]

እነዚህ ሰነዶች በሁሉም ውይይቶች ላይ በባለሙያዎች ቡድን አባላት አማካኝነት እንዲቀርቡ ተደርጓል።

ከላይ ከተገለጹት ሰነዶች ባሻገር - አሠራሮችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመተግበር የሚያስችሉ የተለያዩ ቅጾች ተዘጋጅተዋል። የመጀመሪያው የትኩረት ቡድን ውይይት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ሲሆን - ዓላማውም በቡድን ውይይት ጊዜ ማስታወሻ እንዲይዙ የሚመደቡ አስተባባሪዎች በእጅ ጽሁፍ የያዙትን የውይይት ሃሳብ ወጥነት ባለው መልኩ በቅፁ መሰረት በኮምፒዩተር ላይ በመሙላት የሚያስረክቡበት ቅጽ ነው። ሌላው ቅጽ የምክክር እና የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረክ ተሳታፊዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመምረጥ የሚያስችሉ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘ ሰነድ ነው።

### II. የዩኒቨርሲቲ አስተባባሪዎች መረጣ እና ሥልጠና

በክልሎች የተካሄዱ የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮችን በተመለከተ - ለየምክክር ማዕከላቱ ከተመደቡ የባለሙያዎች ቡድኑ አባላት ጋር በመቀናጀት የማስተባበር ስራ የሚሠሩ የዩኒቨርሲቲ መምህራን እንዲመለመሉ ተደርጓል። የዩኒቨርሲቲ አስተባባሪዎቹ በሽግግር ፍትሕ እና በፖሊሲ አማራጮች ዙሪያ እንዲሁም በምክክር መድረኮቹ አጠቃላይ ዓላማ፣ ሂደት እና በሚኖራቸው ተግባርና ኃላፊነት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። በዚህ ረገድ አስተባባሪዎች ካከናወኗቸው ተግባራት መካከል - ህዝባዊ ምክክር የሚከናወንባቸውን ሆቴሎች የመምረጥ፣ በባለሙያዎች ቡድኑ በሚሰጡ መስፈርቶች መሠረት የምክክር እጩ ተሳታፊዎችን የመለየት፣ ተሳታፊዎች በውይይት መድረኮች ላይ በሰዓቱ እንዲገኙ የማድረግ፣ የየእለት የውይይት ሂደቶችን የማስተባበር እና በቡድን ውይይቶች ጊዜ የሚነሱ ሀሳቦችን በጽሁፍ በመያዝ ለባለሙያዎች ቡድኑ ሪፖርት ማድረግን ያካትታል።

### III. የምክክር መድረክ የሚከናወንባቸው ማዕከላት እና የተሳታፊዎች መረጣ

የምክክር እና የግብዓት ማሰባሰብ ስራ የሚከናወንባቸውን ማዕከላት እና በመድረኮቹ ሊሳተፉ የሚገባቸውን ሰዎች በአግባቡ እና በሚታወቅ መመዘኛ መሰረት መለየት - የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱን ተአማኒነት፣ አሳታፊነት፣ አካታችነትና የሀገር ባለቤትነትን ከማረጋገጥ አንፃር  ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል።

---

[28] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'የሽግግር ፍትህ ምንነት፣ አላማ፣ አላባዎች እና መርሆች፤ የሽግግር ፍትህ ተሞክሮ በኢትዮጵያ ከድህረ ደርግ እስከ ድህረ-ኢህአዴግ'፡ 2015 አዲስ አበባ

[29] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ሰነድ'፡ 2015 አዲስ አበባ

[30] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለመሰብሰብ የተዘጋጀ የውይይት መድረክ የቡድን ውይይት አላማ፣ መርሆዎችና የመወያያ ጥያቄዎች'፡ 2015 አዲስ አበባ

በመሆኑም የክልሎቹን እና በክልሎች የሚገኙ የዞን ከተሞችን ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የሕዝብ ብዛትን፣ ያለፉ ግጭቶችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ባህሪ እና መጠን፣ እንዲሁም ተደራሽነትን መሠረት በማድረግ መረጣውን ለማካሄድ የሚያግዝ ቅጽ/ቴምፕሌት ተዘጋጅቷል።

በተመሳሳይ ተሳታፊዎችን አካታች በሆነ፣ ተጎጂዎችን ማዕከል ባደረገ እና ሰብዓዊ መብት ተኮር በሆነ መንገድ ለመለየት እና ለመምረጥ የሚያስችል ቴምፕሌት በቅድመ-ረቂቅ ፖሊሲ የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት እንዲዘጋጅ እና ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

### IV. የፋይናንስና ሎጂስቲክስ ተግባራት

የምክክር እና የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ከፍተኛ የፋይናንስ እና የሎጂስቲክስ አቅርቦትን ይጠይቃል። ከሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ጋር በተያያዘ በተለይ በክልሎች ለሚከናወኑ መድረኮች መጠነ ሰፊ እና የተቀናጀ ቅድመ-ዝግጅትን የሚጠይቅ የፋይናንስና የሎጅስቲክስ ተግባራትን ማከናወን የግድ ይላል።

በዚህ ረገድ ሁሉም መድረኮች በታቀደላቸው ጊዜ እና ቦታ በአግባቡ እንዲከናወኑ ለማድረግ የግዥ ሂደቶችን የማመቻቸት፣ ቢጋሮችን የማዘጋጀት፣ የትራንስፖርት የፋይናንስ እና የካሜራ ባለሙያዎችን ለሁሉም መድረኮች በቋሚነት የመመደብ፣ በየመድረኩ የሚካሄዱ የፕሌናሪ እና የትኩረት ቡድኖች ውይይቶችን በምስል እና መቅረጸ-ድምጽ መያዝ የሚያስችሉ መሣሪያዎችን ግዢ የመፈጸም እና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች በቅድመ ረቂቅ ፖሊሲ ምክክር ሂደት የተከወኑ አበይት የዝግጅት ተግባራት ናቸው።

### V. የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጮች ሀገራዊ ምክክር ማስጀመሪያ መርሀ-ግብር ዝግጅት

በሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጮች ሰነዱ ላይ የግብዓት ማሳባሰቢያ መድረኮች በይፋ ከመጀመራቸው በፊት - በምክክር መድረኮቹ ዓላማ እና አስፈላጊነት ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር ተገቢ ነው። ይህን ለማድረግ እንዲቻል እና መድረኮቹ የሚዘጋጁባቸው አካባቢዎችም የሂደቱ ባለቤት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ስራ መሥራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ - 'የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጮች ሀገራዊ ምክክር ማስጀመሪያ መርሀ-ግብር' የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣ የክልል ርዕሳነ-መስተዳድሮች፣ የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ኮሚሽነሮች፣ የጸጥታ ዘርፍ ሀላፊዎች፣ የፍትህ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ አምባሳደሮችና አግባብነት ያላቸው የተ.መ.ድ ኢትዮጵያ ጽህፈት ቤት ሀላፊዎች በተገኙበት - የካቲት 27/2015 ዓ.ም በሸራተን አዲስ ሆቴል ተከናውኗል።

## 4.2.2. ምክክር/ግብዓት የማሰበባሰብ ስራ የተካሄደባቸው ቦታዎች የተመረጡበት መስፈርት

ምክክር እና ግብዓት የማሰባሰብ ሥራዎች የሚከናወኑባቸውን ቦታዎች ግልፅ መመዘኛ አውጥቶ መለየት እና መምረጥ ቀላል ተግባር አይደለም። የምክክር ቦታዎችን ልየታ እና መረጣን ከሚወስኑ መሰረታዊ መርሆዎች እና ኩነቶች ውስጥ አንዱ እና ዋናው 'የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ስራው የሚካሄደው ምን ዓላማ ለማሳካት ነው' የሚለው ነው።

በሀገር-አቀፍ ደረጃ በተደረጉ ህዝባዊ ምክክሮች - ከሕዝብ የሚገኙ ሃሳቦች እና አስተያየቶች የሚቀረፀውን ሀገራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ይዘት የሚወስኑ እንደመሆናቸው መጠን - የምክክር መድረኮቹ በሀገር-አቀፍ ደረጃ በስፋት እንዲዘጋጁ ማድረግ እና በተቻለ መጠንም እስከታችኛው የአደረጃጀት እርከን ድረስ መውረድ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ አካሄድ በግጭት እና ከግጭት አውድ ውጭ የመብቶች ጥሰት ሰለባ የሆኑ ሰዎችን እና በገጠራማ አካባቢዎች የሚገኙ ማህበረሰቦችን በመድረስ - ከሁሉም ባለድርሻ አካላት የተለያዩ ሀሳቦች እና አስተያቶችን ማሰባሰብ የሚቻልበትን እድል ይፈጥራል።

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ህዝባዊ ምክክሮችን ለማድረግ በተደረገው ዝግጅት አንዱና ትልቁ ተግዳሮት ምክክሮቹ በየትኞቹ የተመረጡ ቦታዎች ይካሄዱ የሚለው ነው። በዚህ ረገድ የቦታዎቹ ልየታ እና መረጣ የሚመራበት ግልፅ መስፈርት ማዘጋጀት አስፈላጊ ስለነበር የባለሙያዎች ቡድኑ ባዘጋጀው ፍኖተ-ካርታ ላይ በግልጽ እንዲመላከት ተደርጓል። በተግባርም በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች የሚካሄዱ ሕዝባዊ ምክክሮች የሚደረጉባቸውን ከተሞች ልየታ እና መረጣ - ልዩ ክልላዊ ሁኔታን፣ የሕዝብ ቁጥርን፣ ተደራሽነትን፣ የኩነቶችን አመቺነትን፣ ደህንነትን እና የቀደመ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ታሪካዊ ኩነቶችን መሰረት በማድረግ ተከናውኗል። ይህን ዓላማ ለማገዝ የግጭቶች እና የመብቶችን ጥሰት አጠቃላይ ስእል እና ከባቢያዊ ስርጭት የሚያሳይ መለስተኛ ዳሰሳ ተደርጓል።

በዚህ መነሻነት የባለሙያዎች ቡድኑ በቀዳሚ እቅድ ደረጃ ምክክር የሚካሄድባቸው ሀምሳ-ዘጠኝ የክልል ከተሞችን መርጧል። የከተሞቹ አመራረጥም በከተሞቹ በራሳቸው እና በአጎራባች ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የሚገኙ ተሳታፊዎችን በሚያካትት መልኩ ተለይቷል። ይህ እቅድ በአዲስ አበባ ከተማ በብሄራዊ ደረጃ የተካሄዱትን 9 የምክክር መድረኮች፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ እና አቅራቢያ ከተሞች ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የተዘጋጁ 22 ተጨማሪ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮችን አያካትትም።

ሰንጠረዥ 1፥ በባለሙያዎች ቡድኑ በክልልና ሀገር-አቀፍ ደረጃ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ስራ የተከናወነባቸው ከተሞች

| | ምክክር የተካሄደበት ክልል | ምክክር የተካሄደበት ከተማ | ምክክር የተካሄደበት ቀን | ጠቅላላ ቁጥር (በክልል ደረጃ) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | **አፋር** | ሰመራ | ሐምሌ 11 2015 | 1 |
| 2 | **አማራ** | ባህር ዳር | ሐምሌ 17 2015 | |
| | | ደብረታቦር | ሐምሌ 17 2015 | 7 |
| | | ጎንደር | ሐምሌ 22 2015 | |
| | | እንጅባራ | ሐምሌ 20 2015 | |
| | | ደሴ | ሐምሌ 24 2015 | |
| | | ወልዲያ | ሐምሌ 26 2015 | |
| | | ደብረብርሀን | ሐምሌ 27 2015 | |
| 3 | **ትግራይ** | መቀሌ | ነሀሴ 3 2015 | 5 |
| | | አዲግራት | ነሀሴ 5 2015 | |
| | | ሽሬ | ነሀሴ 3 2015 | |
| | | አድዋ/አክሱም | ነሀሴ 1 2015 | |
| | | ማይጨው | ነሀሴ 1 2015 | |
| 4 | **ቤኒሻንጉል ጉሙዝ** | አሶሳ | ሰኔ 19 2015 | 2 |
| | | ግልገል-በለስ | ሰኔ 22 2015 | |
| 5 | **ኦሮሚያ** | አዳማ | ሚያዝያ 16 2015 | 14 |
| | | አሰላ | ሚያዝያ 18 2015 | |
| | | ጭሮ | ሚያዝያ 21 2015 | |
| | | ሻሸመኔ | ሚያዝያ 26 2015 | |
| | | ባሌ ሮቤ | ሚያዝያ 24 2015 | |
| | | ቡሌ ሆራ | ሚያዝያ 26 2015 | |
| | | አዶላ/ጉጂ | ሚያዝያ 24 2015 | |
| | | ወሊሶ | ሚያዝያ 30 2015 | |
| | | አምቦ | ግንቦት 2 2015 | |
| | | ጅማ | ግንቦት 3 2015 | |
| | | መቱ | ግንቦት 5 2015 | |
| | | ነቀምት | ግንቦት 4 2015 | |
| | | ፍቼ/ሰላሌ | ሰኔ 10 2015 | |
| | | ምስራቅ ሀረርጌ | ሐምሌ 13 2015 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6 | **ጋምቤላ** | ጋምቤላ | ሐምሌ 6 2015 | 1 |
| 7 | **ደ/ምእራብ ኢትዮጵያ** | ሚዛን አማን | ሰኔ 9 2015 | 2 |
| | | ቦንጋ | ሰኔ 7 2015 | |
| 8 | **ደቡብ ህ/ብ/ብ** | ጂንካ | ሰኔ 9 2015 | 4 |
| | | ዲላ | ግንቦት 26 2015 | |
| | | አርባምንጭ | ግንቦት 24 2015 | |
| | | ኮንሶ/አማሮ | ግንቦት 26 2015 | |
| 9 | **ማእከላዊ ኢትዮጵያ** | ሆሳእና | ሰኔ 3 2015 | 5 |
| | | ወልቂጤ | ሰኔ 3 2015 | |
| | | ቡታጅራ | ግንቦት 30 2015 | |
| | | ወራቤ | ግንቦት 28 2015 | |
| | | ወላይታ ሶዶ | ሰኔ 1 2015 | |
| 10 | **ሲዳማ** | ሀዋሳ | ግንቦት 24 2015 | 1 |
| 11 | **ሶማሌ** | ጅግጅጋ | ሐምሌ 11 2015 | 3 |
| | | ጎዴ | ሐምሌ 15 2015 | |
| | | ደገሀቡር | ሐምሌ 10 2015 | |
| 12 | **ሀረሪ** | ሀረር | ሐምሌ 10 2015 | 1 |
| 13 | **ድሬዳዋ** | ድሬዳዋ | ሐምሌ 15 2015 | 1 |
| 14 | **አዲስ አበባ** | አዲስ አበባ - መክፈቻ፡ የመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች፡ ታዋቂ ሰዎች፡ የክልል ተወካዮች፡ የዩኒቨርሲቲ/ፍትህ ተቋማት ሀላፊዎች | የካቲት 27 2015 | 11 |
| | | አዲስ አበባ - ሚዲያ፡ ሲቪል ማህበረሰብ፡ እና ዲሞክራቲክ ተቋማት | የካቲት 29 2015 | |
| | | አዲስ አበባ - የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች/ሀላፊዎች | መጋቢት 1 2015 | |
| | | አዲስ አበባ - የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች፡ ተፅእኖ ፈጣሪዎች | መጋቢት 5 2015 | |
| | | አዲስ አበባ - የሽግግር ፍትህ ሀገር-አቀፍ ባለሙያዎች | ህዳር 28 2015 | |
| | | ከዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ምክክር | ህዳር 29 2015 | |
| | | አዲስ አበባ - በቀይ ሽብር ፍርድ ሂደት የተሳተፉ የቀድሞ ባለሙያዎች፡ የእርቀሰላም ኮሚሽን አባላት | መጋቢት 6 2015 | |
| | | አዲስ አበባ - የሽግግር ፍትህ አለማቀፍ ኤክስፐርቶች ምክክር | መጋቢት 7-8 2015 | |
| | | አዲስ አበባ - የሽግግር ፍትህ አለማቀፍ ኤክስፐርቶች - ጥልቅ ዎርክሾፕ | ነሃሴ 26-27 2015 | |
| | | አዲስ አበባ - የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች | መስከረም 4 2016 | |
| | | አዲስ አበባ - የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች | መስከረም 4 2016 | |
| | | | | 58 |

**በአጠቃላይ - የሀገራዊ ምክክሩ የመክፈቻ ሥነ-ስርዓት ከተካሄደበት ከየካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ መስከረም 30/2016 ዓ.ም ድረስ በሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድኑ 47 የምክክር መድረኮች በተለያዩ የክልል ከተሞች፣ እንዲሁም 11 የምክክር መድረኮች በአዲስ አበባ ከተማ ተካሂደዋል። በተጨማሪም 22 የምክክር መድረኮች በባለሙያዎች ቡድኑ እና የውስን ማህበረሰብ ክፍል ድምፅን በሚወክሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች/አጋር ተቋማት ትብብር ተከናውነዋል።**

*ሰንጠረዥ 2፥ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የሽግግር ፍትህ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ስራ የተከናወነባቸው መድረኮች*

| | የምክክሩ ርእስ | የተካሄደበት ቦታ | ቀን | ምክክሩን በቅንጅት ያዘጋጁ ተቋማት |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 'በሽግግር ፍትህ ዙሪያ የሲቪል ማህበረሰብ እይታ እና ሚና' | አዲስ አበባ | ጥር 4 2015 | የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ድርጅት ህብረት (CEHRO) ከሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ጋር በመተባበር፡ |
| 2 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከሀገር-አቀፍ እና ክልላዊ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ምክክር' | አዲስ አበባ | መጋቢት 21 2015 | Institute for Security Studies እና የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት (ECSOC) ከሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ጋር በመተባበር፡ |
| 3-6 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከተመረጡ ምሁራን፣ ሲቪል ማህበረሰቦች ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች' (4) | አዲስ አበባ<br>አዲስ አበባ<br>ደሴ<br>ሰመራ | ሚያዝያ 18 2015<br>ግንቦት 1 2015<br>ግንቦት 7 2015<br>ግንቦት 7 2015 | የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት እና የአሜሪካ ዓለም-አቀፍ ልማት ፍትህ ፕሮጀክት ከሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ጋር በመተባበር፡ |
| 7 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከሴቶች ጋር ብቻ' የተካሄደ ምክክር | ቢሾፍቱ | ግንቦት 22-23 2015 | UN-WOMEN ከሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ጋር በመተባበር |
| 8-9 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከጥቃት ሰለባ ሴቶች ጋር ብቻ' የተካሄዱ የምክክር መድረኮች' (2) | መቀሌ<br>ባህር ዳር | ሀምሌ 24-26 2015<br>ሀምሌ 24-26 2015 | UN-WOMEN ከሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ጋር በመተባበር |
| 10 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከፌዴራል ጸጥታ አካላት ጋር የተደረገ ምክክር' | ቢሾፍቱ | ነሀሴ 17-19 2015 | በIGAD Security Sector Program (IGAD SSP) እና የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ትብብር |
| 11 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከፌዴራል እና ክልል ከፍተኛ አመራሮች ጋር የተደረገ ምክክር' | ቢሾፍቱ | መስከረም 3-4 2015 | በIGAD Security Sector Program እና የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ትብብር |
| 12-15 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ስደተኞች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች' (5)[31] | አሶሳ<br>አሶሳ<br>መቀሌ<br>ጭሮ<br>አዲስ አበባ | ሰኔ 27 2015<br>ሰኔ 27 2015<br>መስከረም 11 2016<br>ጥቅምት 27 2016<br>መስከረም 29 2016 | በተ.መ.ድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) እና የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ትብብር |
| 16 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከህፃናትና ከህፃናት መብት ተጣባቂ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ምክክር' | አዳማ | መስከረም 21 2016 | በUNICEF፣ የፍትህ ሚኒስቴር እና የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ትብብር |
| 17 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከዩኒቨርሲቲ ምሁራን ጋር የተደረገ ምክክር' | አዲስ አበባ | መስከረም 21-22 2015 | የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሰብዓዊ መብቶች ማዕከል ከሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ጋር በመተባበር፡ |
| 18 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከአካል ጉዳተኞች አረጋውያን ጋር የተደረገ ምክክር' | አዲስ አበባ | መስከረም 19 2016 | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ከሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ጋር በመተባበር፡ |
| 19 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከንግድ ማህበረሰብ አባላት ጋር የተደረገ ምክክር' | አዲስ አበባ | መስከረም 05 2016 | - |
| 20 | 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች፡ የፖሊሲ | መቀሌ | ሐምሌ 22 2015 | በሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች |

[31] ሰኔ 28 2015 በአሶሳ ከተማ፣ መስከረም 29 2016 በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄዱት መድረኮች ከስደተኞች ጋር ሲሆን፣ የቀሩት ሶስት መድረኮች ደግሞ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጋር የተደረጉ ናቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አማራጮች እና አካሄዶች ላይ በትግራይ ክልል ከሚገኙ አካዳሚክ ማህበረሰብ አባላት ጋር የተደረገ ምክክር'[32] | | | ቡድን እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት ትብብር |
| 21 | 'የሽግግር ፍትህ ሀገር-አቀፍ ባለሙያዎች' ጋር የተደረገ ምክክር | አዲስ አበባ | ህዳር 28 2015 | በተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር እና በሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን |
| 22 | 'ከዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ምክክር' | አዲስ አበባ | ህዳር 29 2015 | በተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር እና በሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን |
| | | | | |

### 4.2.3. የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ መርሀ-ግብሮች እና የዕለት ፕሮግራሞች ጊዜ ምጣኔ

የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ስራ የሚፈፀምበትን የጊዜ ሰሌዳ በምናባዊ ስሌት ይህን ያህል ጊዜ መሆን አለበት ብሎ ለመደምደም የሚያስችል መርህ የለም። ሆኖም የምክክር መድረኮች - በተለይም በሽግግር ፍትህ ጉዳዮች ላይ የሚካሄዱ የህዝብ የምክክር መድረኮች - በባህሪያቸው ሰፊ አካባቢን የሚሸፍኑ፣ ብዙ ባለድርሻዎች የሚሳተፉባቸው እና ረጅም ጊዜ የሚወስዱ መሆናቸው የማይቀር ነው።

በኢትዮጵያም ምክክር እና ግብዓት ማሰባብሰብ የሚጀመርበት እና የሚጠናቀቅበት የጊዜ ማዕቀፍ የሂደቱን አጠቃላይ ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የጊዜ ሰሌዳ ሊኖረው እንደሚገባ እሙን ነው። በዚህ ረገድ የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድኑ ተግባራዊ ያደረገው ስነ-ዘዴ ሁለት ገፅታዎች አሉት።

**የመጀመሪያው ገጽታ** - የተደራሽነት እና የሰላም ሁኔታ በፈቀደ መጠን - ገዢ መርሆዎችን የተከተሉ የምክክር መድረኮች በማካሄድ ጥራት ያለው ግብዓት በርከት ካሉ ባለድርሻ አካላት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መሰብሰብ የሚቻልበትን እድል ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው። የምክክር መርሀ-ግብሩ እጅጉን ተጣድፎ የይስሙላ ሂደት የሚያስመስል ስእል እንዳይፈጠር - በሌላም በኩል ደግሞ ከመጠን በላይ ተንዛዝቶ ትኩረት እንዳያጣ እና የተሳታፊዎች እና የተጎጂዎችን ስሜት እንዳይነካ ወይም በቀጣይ የሚታሰብ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ትልምን እንዳያዘገይ - በቡድኑ በኩል ልዩ ጥንቃቄ ተደርጓል።

በተጨማሪም የጉዳዩ ባለቤት የሆነው መንግስት - ቀደም ሲል በፍትህ ሚኒስቴር የውስጥ ጥናት ግምገማ፣ ቀጥሎም በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን ጥምር ምርመራ፣ በመጨረሻም በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ማዕቀፍ የገለፃቸው ጠንካራ የፖለቲካ ፍላጎቶች የፈጠሩትን የመነቃቃት ድባብ መከተል እና መጠቀም - የምክክር መርሀ-ግብሩ የጊዜ ሰሌዳ አወጣጥ ግንዛቤ ውስጥ ካስገባቸው ኩነቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

በመሆኑም በእነዚህ እይታዎች መሠረት - የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ መርሀ-ግብር የጊዜ ሰሌዳ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። ሶስት ወር የፈጀውን የቅድመ-ዝግጅት ሥራ ሳያካትት - በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተደረገው የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ስራ - የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በይፋ ከተከፈተ በኋላ ለተከታታይ 8 ወራት ሲካሄድ ቆይቶ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ተጠናቋል። በአጠቃላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ 80 የምክክር መድረኮችን በተሳካ ሁኔታ ለማዘጋጀት ተችሏል።

እንዲህ ያለ ሰፊ የምክክር ጊዜ ማዕቀፍ መዘጋጀቱ - ከአጠቃላይ ስነ-ዘዴ አንፃር ተቀባይነት ያለው ምክንያታዊ ማዕቀፍ ከመሆኑም በላይ - ምክክሮቹ እንዳይጣደፉና በይምሰል አሠራር እንዳይከናወኑ ትልቅ ዋስትና ሰጥቷል።

[32] Transitional Justice Working Group of Experts/Mekelle University - School of Law. Intellectual Discourse/Consultation on transitional justice notions and the transitional justice policy options for Ethiopia document. July 2023. Mekelle. Ethiopia.

በርግጥም ለሂደቱ የተሰጠው ረጅም ጊዜ - በሽግግር ፍትህ እና በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦቹ ላይ የቀረቡ ውስብስብ ሀሳቦችን በጥልቀት ለማስረፅና በጉዳዩ ላይ የሕዝብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እይታን ለማጠናከር ተጨባጭ እድልን ፈጥሯል።

***ሁለተኛው ጊዜን በተመለከተ በጥንቃቄ ተግባራዊ የተደረገው የስነ-ዘዴ ገፅታ*** - ለእያንዳንዱ የምክክር መድረክ የተመደበው ቀን እና ለዝርዝር እለታዊ ፕሮግራሞች የተመደበውን ሰአት የሚመለከት ነው። በክልል ደረጃ ተግባራዊ ለተደረጉ ሁሉም የምክክር መርሀ-ግብሮች - የቅድመ-ዝግጅት እና ሎጂስቲክስ ሥራዎችን ሳያካትት እንደየከተሞቹ ርቀት ከ3-4 ቀናት እንዲመደብ ተደርጓል። ሁለቱ ቀናት የባለሙያ ቡድኑ አባላትና የሂደት አስተባባሪዎች የምክክር መድረክ ወደሚገኝበት እያንዳንዱ ከተማ ለሚያደርጉት ጉዞ የተመደበ ሲሆን፡ ከ2-3 ሰዓት የሚሆነው ጊዜ ደግሞ ከአስተባባሪ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ጋር በፖሊሲ አማራጮች ላይ ለሚካሄድ የትኩረት ቡድን ውይይት የተመደበ ነው።

የሚቀረው አንድ ሙሉ ቀን - ከተመረጡት ተሳታፊዎች ጋር ሶስት ተያያዥ መርሀ-ግብሮች የተተገበረበት ነበር። በመሆኑም በእያንዳንዱ ከተማ የምክክር መድረክ የጠዋት መርሀ-ግብር ላይ ሁለት ፅሁፎች እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን፡[33] ይህ መድረክ ሁሉም ተሳታፊዎች ባንድነት ያለገደብ ነፃ ውይይት የሚያደርጉበት ነው። ሁለተኛው እና ከሰአት በኋላ የተመደበው ሙሉ ጊዜ - የመድረኩን ተሳታፊዎች ለአራት የትኩረት ቡድኖች በመክፈል[34] በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦቹ ላይ ዝርዝር ውይይት ያደረጉበት እና የየራሳቸውን እይታ ያጋሩበት ነው።

በጥቅሉ ሲታይ የተመደበው የአንድ ሙሉ ቀን የውይይት መድረክ ጊዜ - ተሳታፊዎች ረዘም ያለ ጊዜ በመውሰድ ጥራት ያለው ውይይት ለማድረግና ዝርዝር ምልከታቸውን በግብዓት መልክ ለማጋራት በቂ ጊዜ የሰጠ ነበር። በአንዳንድ መድረኮች ላይ የቡድን ውይይቶቹ የተሟሟቀ ክርክርን በማስነሳታቸው እስከ ምሽቱ ሁለት ሰአት ድረስ የተገፉባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ። በተለምዶ በአማካይ ከ1-2 ሰአት ብቻ ከሚጠይቁ እና እስካሁን በተለዩ የምርጥ ልምዶች ቀመራ እና የማህበራዊ ሳይንስ አሰራሮች አንፃር ሲታይ - በባለሙያዎች ቡድኑ በተለይ ለትኩረት ቡድን ውይይቶች የተሰጠው ጊዜ ከበቂ በላይ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። በዚህ ረገድ በባለሙያዎች ቡድኑ ተግባራዊ የተደረገው ስነ-ዘዴ ዓለም-አቀፍ ደረጃዎች ከሚጠይቁት አነስተኛ መጠን እጅጉን ያለፈ ነው። በእርግጥም አሁን ላይ ከሂደቱ የድምፅ ቅጂዎች እና የድምፅ ውይይት ትርጉሞች ይዘት መረዳት የተቻለው - በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ መጠን እና ጥራት ያለው ግብዓት መሰብሰብ መቻሉን ነው።

## 4.3. የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ የተመራባቸው መርሆዎች ይዘት እና ዝርዝር አፈፃፀም

### 4.3.1. የሂደቱ አካታችነት፣ የተሳታፊዎች/ባለድርሻ አካላት ልየታ፣ መረጣ፣ ብዛት እና ስብጥር

በምክክር እና ግብዓት ማሰበባሰቢያ መድረኮች ላይ የሚሳተፉ ሰዎች ልየታ፣ መረጣ፣ ብዛት እና ስብጥር በጥንቃቄ መከወን ያለበት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሥራ ሂደት አንኳር ተግባር ነው። የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ባዘጋጀው ፍኖተ-ካርታ ላይ እንደተመለከተው - የትኛውም የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የማውጣት ሥራ ሂደት አካታች እና አሳታፊ በሆነ ምክክር ማለፍ ይኖርበታል።

ከዚህ አንፃር የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ስራ በዘር፣ በፆታ፣ በእምነት፣ በትምህርት ሁኔታ፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ ሁኔታ ላይ ሳይመሰረት - ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ እና

---

[33] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'የሽግግር ፍትህ ምንነት፣ አላማ፣ አላባዎች እና መርሆች፤ የሽግግር ፍትህ ተሞክሮ በኢትዮጵያ ከድህረ ደርግ እስከ ድህረ-ኢህአዴግ'፡ 2015 አዲስ አበባ

የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ሰነድ'፡ 2015 አዲስ አበባ

[34] የሴት የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ቡድን፡ የወንድ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ቡድን፡ ቅልቅል ቡድኖች (2)፡ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን፡

በሀገሪቱ ያለውን ብዝሀነት ባንፀባረቀ መልኩ እንዲተገበር ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል። በሰንጠረዥ 1 እና 2 ላይ እንደተመለከተው ይህ የተከናወነበት ዝርዝር የአሰራር ዘዴ አስቀድሞ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

### 4.3.1.1.የትኞቹ ሰዎች/የማህበረሰብ ክፍሎች ተለዩ?

በመሠረቱ ሕዝባዊ የምክክር መድረኮች እና ግብዓት የማሰባሰብ ሥራዎች - በሽግግር ፍትህ ጉዳይ ላይ እንደሚካሄዱ ሕዝበ ውሳኔ ወይም የሕዝቡን ጥቅል ምልከታ ለመለካት በማሰብ ብቻ እንደሚቀረፁ መርሀ-ግብሮች የሚታዩ አይደሉም። የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ ዓላማ ግልፅ ነው፤ ብዙሀኑን በማሳተፍ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ይዘትን የሚወስኑ የሕዝብ እና የባለድርሻ አካላት እይታዎችን ማሰባበሰብ፡ እንዲሁም ህዝቡን የሂደቱ አካል እንዲሆን በማድረግ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖር ማድረግ ነው።

ከዚህ አንፃር በምክክሮቹ ላይ ለመሳተፍ የሚለዩ እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚመረጡ ሰዎች - ከሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች የሚወከሉ፣ በተቻለ መጠንም የተገለሉ እና በተለያዩ ጊዜያት የከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ቀጥተኛ ሰለባ የሆኑ ግለሰቦችን ያካተተ እንዲሆን ማድረግ የግድ ይላል። በዚህ ረገድ በተለይ የመብት ጥሰቶችን በተመለከተ - የግለሰቦች ልየታ ሥራው - ሰዎች በተለያዩ አገራዊ ኩነቶች ተበዳይ የሆኑባቸውን አጋጣሚዎች ለማየት ሙከራ አድርጓል።

ሰብዓዊ መብት-ተኮር የሆነ የሽግግር ፍትህ ሂደት የሁሉንም ሀገራዊ እና ዓለም-አቀፋዊ ተዋንያን እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ትብብር እና ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃል። ከዚህ በመነሳትም በምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ የሚሳተፉ ሰዎች ከሚከተሉት የማህበረሰብ ክፍሎች የተውጣጡ እንዲሆኑ ተደርጓል፡-

- የእምነት አባቶች እና የማህበረሰብ መሪዎች፣
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ምሁራን/የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ እና የሽግግር ፍትህ ኤክስፐርቶች፣
- ከሽግግር ፍትህ አላባዎች ጋር የተያያዘ የቀደመ ተሞክሮ ያላቸው ተቋማት/ባለሙያዎች፣
- የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ተቋማት/ተወካዮች፣
- የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች እና የሚዲያ ባለሙያዎች፣
- ሴቶች እና የሴቶች ማህበራት፣
- አካል ጉዳተኞች፣ ህፃናትና የህፃናት መብት አስጠባቂ ድርጅቶች፣
- ወጣቶች እና የወጣት ማህበራት፣
- የከባድ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ቀጥተኛ ሰለባ የሆኑ ሴቶችና ወንዶች
- የሠራተኞች እና ንግድ ማህበረሰብ ተወካዮች፣
- የዳኝነት፣ የፍትህ እና የፀጥታ ዘርፍ ባለሙያዎች/ሀላፊዎች፣
- የፌዴራል እና ክልል መንግስት ተቋማት ሀላፊዎች፣ እና
- የሽግግር ፍትህ ዓለም-አቀፍ ባለሙያዎች።

### 4.3.1.2.የተሳታፊዎች ልየታና መረጣ ስነ-ዘዴ ምን ይመስል ነበር?

የግለሰቦች እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎን የሚመለከት ማናቸውም ውሳኔ በተቻለ መጠን ግልፅ እና ፍትሀዊ መሆን አለበት። አስቀድሞ በሚታወቅ እና አካታችነትን በሚያረጋግጥ መለኪያ መመራት ይኖርበታል። በተለምዶ ሕዝባዊ የምክክር መድረኮች ሲካሄዱ የተገለሉ እና የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ ሰዎችን የማሳተፍ ሁኔታ ብዙም አይስተዋልም።

በሽግግር ፍትህ ሂደት የተገለሉ እና የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ ሰዎችን ያገለለ የምክክር እና የግብዓት ማሰባሰብ ሂደት መከተል - ለማሳካት በታሰበው የሽግግር ፍትሕ ዓላማ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ለማድረግ ተሞክሯል። በመሆኑም የተሳታፊዎች ልየታን የሚመራበት ፕሮቶኮል ሲዘጋጅ -

በተለያየ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የተገለሉ እና የሰብዓዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው ሰዎች ሙሉ ተሳታፊነትን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲቀረፅ ተደርጓል። ለዚህ የሚያገለግል መለስተኛ የልየታ ዳሰሳ ጥናትም ተካሂዷል።

በተጨማሪም በልየታ እና መረጣ ሂደቱ የተሳተፉ የዩኒቨርሲቲ መምህራን በቂ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችም ቢያንስ በልየታ እና ስልጠና ሂደቱ ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገዋል።

ይህን መብት በተጨባጭ ከመተግበር አንፃር የተገለሉ እና የሰብአዊ መብት ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎች እንደማንኛውም የማህበረሰብ አባል በሌሎች መድረኮች ከሚኖራቸው የተሳትፎ መብት ባለፈ - በተለይ ሴቶች፣ የጥቃት ሰለባ ሴቶች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች፣ የአካል ጉዳተኞች እና ህፃናት - ሁኔታዎቻቸውን በማገናዘብ ከእነሱ ጋር ብቻ የሚደረጉ ተጨማሪ ሀገር-አቀፍ የምክክር መድረኮች እንዲዘጋጁላቸው ተደርጓል።

ሰንጠረዥ 3: የሽግግር ፍትህ የምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ መድረክ ተሳታፊዎች የሚለዩበትና የሚመረጡበት ፕሮቶኮል

**Template for Identification and Selection of Participants**

**Details**

Place of the consultation/event:
Catchment areas:
Facilitators (full names):
Process owners:
Intermediary/Interlocutor/s if any:

| No.[1] | Full Name | Sex | Age | Residence[2] | Status/Capacity/Role in the Community (example: victim, CSO, Community or religious leader, expert, youth etc.) | Short Bio[3] | Travel details (if applicable)[4] | Contact |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

1 Please carefully identify and select 60 diverse/heterogonous participants and 6 back up list of participants.
2 If displaced, indicate where from and current residence as well.
3 The profile of participants should reflect inclusivity and diversity of targeted category of participants in terms of (gender, geographic representation, incidents of violations (for victims and affected communities); disability, ethnicity, religious denominations, and other parameters). As regards composition of the participants, i) to the extent possible gender parity should be ensured, and ii) at least 60% of the sixty (60) participants should be victims as defined under the AUTJP.
4 Please provide details of travel arrangements to and from including the actual number of travel days if and when applicable.

### 4.3.1.3.በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ ላይ ምን ያህል ተሳታፊዎች እንዲኖሩ ተደረገ?

ሂደቱ የሚያስፈልገውን አጠቃላይ የግብዓት መጠን እና የሚሰበሰብበትን ስነ-ዘዴ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ባዘጋጃቸው እያንዳንዳቸው የምክክር መድረኮች ላይ የሚገኙ ተሳታፊዎች ቁጥር 60 እንዲሆን ተደርጓል።

ከትግበራ አንፃር በክልል-አቀፍ የምክክር መድረኮች ላይ በአማካይ 59.59 ሰዎች (ወይም ከተጋበዙት ተሳታፊዎች 99.3% የሚሆኑት) ተገኝተዋል።

በባለሙያዎች ቡድኑ በክልሎች፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እና በአዲስ አበባ በተዘጋጁ 58 መድረኮች በድምሩ 3391 ሰዎች የተሳተፉ ሲሆን - በአጋር ተቋማት እና ባባለሙያዎች ቡድኑ ቅንጅት በተዘጋጁ ተጨማሪ 22 መድረኮች ላይ በድምሩ 869 ሰዎች በምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ ተሳትፈዋል።

ሰንጠረዥ 4: በባለሙያዎች ቡድኑ በተዘጋጁ የምክክር/ግብዓት ማሰባሰብ ስራ የተሳተፉ ሰዎች መረጃ፡ ብዛት፡ ስብጥር

| ምክክር የተካሄደበት ክልል | ምክክር የተደረገበት ከተማ | የተሳታፊዎች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጠቅላላ | ሴት | ወንድ | የሙብት ጥሰት ተጎጂዎች ቁጥር (ለብቻ) | |
| | | | | | ሴት | ወንድ |
| አፋር | ሰመራ | 61 | 21 | 40 | 13 | 15 |
| አማራ | | | | | | |
| | ባህር ዳር | 55 | 22 | 33 | 14 | 18 |
| | ደብረታቦር | 57 | 24 | 33 | 16 | 15 |
| | ጎንደር | 57 | 26 | 31 | 17 | 22 |
| | እንጅባራ | 60 | 21 | 39 | 16 | 15 |
| | ደሴ | 60 | 28 | 32 | 16 | 11 |
| | ወልዲያ | 50 | 21 | 29 | 22 | 9 |
| | ደብረብርሀን | 54 | 21 | 33 | 11 | 19 |
| ትግራይ | | | | | | |
| | መቀሌ | 57 | 24 | 33 | 10 | 16 |
| | አዲግራት | 55 | 28 | 27 | 16 | 16 |
| | ሽሬ | 71 | 22 | 49 | 20 | 23 |
| | አድዋ/ አክሱም | 63 | 21 | 42 | 17 | 6 |
| | ማይጨው | 55 | 25 | 30 | 15 | 15 |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | | |
| | አሶሳ | 86 | 39 | 47 | 26 | 15 |
| | ግልገል-በለስ | 55 | 26 | 29 | 15 | 10 |
| ኦሮሚያ | | | | | | |
| | አዳማ | 55 | 13 | 42 | 15 | 15 |
| | አሰላ[35] | 54 | 15 | 39 | 15 | 13 |
| | ጭሮ | 58 | 13 | 45 | 13 | 14 |
| | ባሌ ሮቤ | 59 | 19 | 40 | - | - |
| | አዶላ/ጉጂ | 61 | 7 | 54 | 7 | 14 |
| | ሻሸመኔ | 60 | 9 | 51 | - | - |
| | ቡሌ ሆራ | 65 | 5 | 60 | 5 | 15 |
| | ወሊሶ | 56 | 16 | 40 | 14 | 12 |
| | አምቦ | 55 | 9 | 46 | 9 | 14 |
| | ጅማ | 68 | 20 | 48 | 20 | 20 |
| | ነቀምት | 65 | 23 | 42 | 23 | 27 |
| | መቱ | 57 | 23 | 34 | 15 | 14 |
| | ፍቼ/ሰላሌ | 60 | 28 | 32 | 15 | 15 |
| | ም/ሀረርጌ | 60 | 22 | 38 | 15 | 15 |

[35] በወቅቱ በከተማው በሚፈለገው ደረጃ/መጠን የሆቴል እና አዳራሽ መስተንግዶ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ባለመገኘቱ ተሳታፊዎችን ወደ አዳማ ከተማ በማጓጓዝ ምክክሩ እንዲካሄድ ተደርጓል።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጋምቤላ | | | | | | |
| | ጋምቤላ | 66 | 25 | 41 | 18 | 22 |
| ደ/ምእራብ ኢትዮጵያ | | | | | | |
| | ሚዛን አማን | 57 | 21 | 36 | 13 | 18 |
| | ቦንጋ | 59 | 21 | 38 | 15 | 15 |
| ደቡብ ህ/ብ/ብ | | | | | | |
| | ጂንካ | 64 | 29 | 35 | 15 | 15 |
| | ዲላ | 60 | 28 | 32 | 15 | 12 |
| | አርባምንጭ | 60 | 20 | 40 | 14 | 15 |
| | ኮንሶ/አማሮ | 59 | 17 | 42 | 12 | 13 |
| ማእከላዊ ኢትዮጵያ | | | | | | |
| | ሆሳእና | 57 | 15 | 42 | 14 | 15 |
| | ወልቂጤ | 53 | 14 | 39 | 16 | 23 |
| | ቡታጅራ | 56 | 20 | 36 | 18 | 17 |
| | ወራቤ | 60 | 12 | 48 | 8 | 24 |
| | ወላይታ ሶዶ | 60 | 16 | 44 | 15 | 15 |
| ሲዳማ | | | | | | |
| | ሀዋሳ | 57 | 16 | 41 | 15 | 14 |
| ሶማሌ | | | | | | |
| | ጅግጅጋ | 62 | 15 | 47 | 13 | 11 |
| | ጎዴ | 60 | 22 | 38 | 20 | 19 |
| | ደገሀቡር | 62 | 26 | 36 | 26 | 19 |
| ሀረሪ | | | | | | |
| | ሀረር | 60 | 36 | 24 | 15 | 15 |
| ድሬዳዋ | | | | | | |
| | ድሬዳዋ | 61 | 21 | 40 | 15 | 15 |
| አዲስ አበባ | | | | | | |
| | አዲስ አበባ | 55 | 28 | 27 | - | - |
| | አዲስ አበባ | 65 | 37 | 28 | - | - |
| | | | | | | |
| | 49 | 2922 | 1030 (35.25%) | 1892 (64.75%) | 687 (23.51%) | 710 (24.29%) |

ሰንጠረዥ 5: በባለሙያዎች ቡድኑ ለልዩ ባለድርሻ አካላት በተዘጋጁ የምክክር/ግብዓት ማሰባሰብ ስራ የተሳተፉ ሰዎች ብዛት እና ስብጥር

| የተደረጉ የምክክር መድረኮች | ምክክር የተደረገበት ከተማ | የተሳታፊዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ጠቅላላ | ሴት | ወንድ |
| 'ሀገር-አቀፍ ምክክር ማስጀመሪያ/መክፈቻ፡ የመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ የክልል ተወካዮች፣ የዩኒቨርሲቲ እና የፍትህ ተቋማት ሀላፊዎች' | አዲስ አበባ | 120 | - | - |
| 'ሚዲያ፣ ሲቪል ማህበረሰብ፣ እና ዲሞክራቲክ ተቋማት' | አዲስ አበባ | 59 | 13 | 46 |
| 'የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች/ሀላፊዎች' | አዲስ አበባ | 61 | 5 | 56 |
| 'የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች እና ተፅእኖ ፈጣሪዎች' | አዲስ አበባ | 35 | 15 | 20 |
| 'የሽግግር ፍትህ ሀገር-አቀፍ ባለሙያዎች' | አዲስ አበባ | 45 | 12 | 33 |
| 'ከዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ምክክር' | አዲስ አበባ | 31 | 12 | 19 |
| 'በቀይ ሽብር ፍርድ ሂደት የተሳተፉ የቀድሞ ባለሙያዎች፡ የእርቀሰላም ኮሚሽን አባላት' | አዲስ አበባ | 42 | 6 | 36 |
| 'የሽግግር ፍትህ ዓለም-አቀፍ ኤክስፐርቶች ጋር የተደረገ ምክክር' | አዲስ አበባ | 55 | 21 | 34 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ‘የሽግግር ፍትህ ዓለም-አቀፍ ኤክስፐርቶች ጥልቅ ዎርክሾፕ (ክፍል 2)’ | አዲስ አበባ | 21 | 9 | 12 |
| | 9 | 469 | 93 (19.82%) | 256 (54.58%) |

ሰንጠረዥ 6: በባለሙያዎች ቡድኑ እና አጋር ተቋማት ትብብር በተዘጋጁ የምክክር/ግብዓት ማሰባሰብ መድረክ የተሳተፉ ሰዎች ብዛት እና ስብጥር

| የተደረጉ የምክክር መድረኮች | ምክክር የተደረገበት ከተማ | የተሳታፊዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ጠቅላላ | ሴት | ወንድ |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከሀገር-አቀፍ እና ክልላዊ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ምክክር’ | አዲስ አበባ | - | - | - |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከተመረጡ ምሁራን፣ ከሲቪል ማህበረሰብ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች’ (4) | አዲስ አበባ | 44 | 17 | 27 |
| | አዲስ አበባ | 49 | 12 | 37 |
| | ደሴ | 50 | 39 | 11 |
| | ሰመራ | 57 | 28 | 29 |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከሴቶች ጋር ብቻ’ የተካሄደ ምክክር | ቢሾፍቱ | 71 | 68 | 3 |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከጥቃት ሰለባ ሴቶች ጋር ብቻ’ የተካሄዱ የምክክር መድረኮች’ (2) | መቀሌ | 25 | 25 | |
| | ባህርዳር | 14 | 14 | |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከፌዴራል ዳኝነት አካላት ጋር የተደረገ ምክክር’ | ቢሾፍቱ | 60 | | |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከፌዴራል እና ክልል ከፍተኛ አመራሮች ጋር የተደረገ ምክክር’ | ቢሾፍቱ | 37 | 10 | 27 |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ስደተኞች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች’ (5) | አሶሳ | 60 | 30 | 30 |
| | አሶሳ | 60 | 27 | 33 |
| | መቀሌ | 60 | 27 | 33 |
| | ጭሮ | 59 | 29 | 30 |
| | አዲስ አበባ | 60 | 37 | 23 |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከህፃናትና ከህፃናት መብት ተጣባቂ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ምክክር’ | አዲስ አበባ | 44 | 26 | 18 |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከዩኒቨርሲቲ ምሁራን ጋር የተደረገ ምክክር’ | አዲስ አበባ | 40 | 6 | 34 |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከአካል ጉዳተኞች ጋር የተደረገ ምክክር’ | አዲስ አበባ | 29 | 14 | 15 |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦችና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከንግድ ማህበረሰብ አባላት ጋር የተደረገ ምክክር’ | አዲስ አበባ | - | - | - |
| ‘በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች፣ የፖሊሲ አማራጮችና አካሄዶች ላይ በትግራይ ክልል ከሚገኙ አካዳሚክ ማህበረሰብ ጋር የተደረገ ምክክር’ | መቀሌ | 50 | 8 | 42 |
| | | 869 | 417 | 392 |


### 4.3.1.4. የምክክር መድረክ ተሳታፊዎች ስብጥር

በእያንዳንዱ የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ መርሀ-ግብር ላይ ከሁሉም የማህበረሰብ ክፍል የተወከሉ ተሳታፊዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ - ከተሳተፉ ሰዎች ውስጥ ቢያንስ ግማሽ (50%) የሚሆኑት ሴቶች፣ እንዲሁም


ከአጠቃላይ ተሳታፊዎች ስልሳ ከመቶ (60%) የሚሆኑት የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጠቂ የሆኑ ግለሰቦች እንዲሆኑ ግልፅ የአሰራር ፕሮቶል በማውጣት እንዲተገበር ተደርጓል።

በመሆኑም በባለሙያዎች ቡድኑ በክልሎች፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እና በአዲስ አበባ ከተማ በተዘጋጁ 58 መድረኮች ከተሳተፉ 3391 ተሳታፊዎች ውስጥ 1,123 (33.11%) ሴቶች ሲሆኑ 2,148 (63.34%) ደግሞ ወንዶች ናቸው።

በክልሎች እና ሁለት የከተማ መስተዳድሮች በተደረጉ የምክክር መድረኮች ከተሳተፉ 2,922 አጠቃላይ ተሳታፊዎች ውስጥ 678 ሴት የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ሲሆኑ፣ 710 ደግሞ ወንድ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ናቸው። ይህም ከአጠቃላይ ተሳታፊዎች ውስጥ የተጎጂዎችን ቁጥር 1,388 (47.53%) ያደርገዋል።




ተሳታፊዎች የፆታ ስብጥር - 58 አገርቀፍ መድረኮች




የመብት ጥሰት ተጎጂዎች ምጣኔ - 49 ክልላዊ/ከተማ መስተዳድር መድረኮች

### 4.3.1.5. በክልሎች ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የተመረጡ አስተባባሪዎች መረጣ፣ ሚና እና ስልጠና

ከተሳታፊዎች ልየታና መረጣ አንስቶ እስከ ምክክር መድረኮች ዝግጅት እና የተሳታፊዎች ማረፊያ ሆቴሎች እና የስብሰባ አዳራሾች ማመቻቸት ስራ ሂደት - በየክልሎቹ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የተመረጡ አስተባባሪዎች አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ነበር። በሂደቱ ከ36 ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ 214 የሕግ ትምህርት ቤቶች (እና ጥቂት ሌሎች ፋካልቲ) መምህራንን (እንዲሁም ውስን ሲኒየር ተማሪዎችን)፣ [36] እንዲሁም 12 የድምፅ-ወደ-ፅሁፍ-መቀየር ባለሙያዎችን - የምክክር እና ግብዓት የማሰባሰብ ስራዎቹ አካል ለማድረግ ተችሏል። ይህን አዲስ እና ለየት ያለ አሰራር ተግባራዊ በማድረግ የባለሙያዎች ቡድኑ ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎችን ማሳካት ችሏል።

[36] በዚህ ሂደት የተሳተፉት የሚከተሉት ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው። አርሲ ዩኒቨርስቲ፣ ኦዳ ቡልቱ ዩኒቨርስቲ፣ መደ ወላቡ ዩኒቨርስቲ፣ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ፣ አምቦ ዩኒቨርስቲ፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ፣ መቱ ዩኒቨርስቲ፣ ወለጋ ዩኒቨርስቲ፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ፣ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ፣ ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፣ ወራቤ ዩኒቨርስቲ፣ ወላይታ ዩኒቨርስቲ፣ ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ፣ ጂንካ ዩኒቨርስቲ፣ ቦንጋ ዩኒቨርስቲ፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ፣ ሰላሌ ዩኒቨርስቲ፣ አሶሳ ዩኒቨርስቲ፣ ጋምቤላ ዩኒቨርስቲ፣ ሰመራ ዩኒቨርስቲ፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ፣ ሀረማያ ዩኒቨርስቲ፣ ድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ፣ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ፣ እንጅባራ ዩኒቨርስቲ፣ ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ፣ ደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ፣ ወልዲያ ዩኒቨርስቲ፣ ወሎ ዩኒቨርስቲ፣ አዲግራት ዩኒቨርስቲ፣ መቀሌ ዩኒቨርስቲ፣ አክሱም ዩኒቨርስቲ፣ ራያ ዩኒቨርስቲ፣

**በመጀመሪያ ደረጃ** - ለዚህ አይነቱ የማሳለጥ ስራ የታችኛውን የመንግስት መዋቅር በምንም መልኩ ባለመጠቀም እና ማንኛውንም አይነት ንክኪ (ያልተገባ ጣልቃ-ገብነት) በማስወገድ - ከሂደቱ ጥራት እና ተአማኒነት አንፃር ሊነሱ ይችሉ የነበሩ ችግሮችን ማስቀረት ተችሏል።

**በሁለተኛ ደረጃ** - ወደፊት የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሲጀመር - ሰፊ አካባቢ-አቀፍ ባለቤት እና የዓላማው ሞጋቾች የሚያስፈልገው እንደመሆኑ መጠን በዚህ ደረጃ የአካባቢ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ አባላትን ወደ ስራው ምዕራፍ ማስገባት በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የረጅም ጊዜ ትልም እና ትግበራ ላይ አወንታዊ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይታመናል።

ሰንጠረዥ 7: አስተባባሪ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ዝርዝር

| የተሳተፉ ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር | አጠቃላይ የተሳለጡ መድረኮች ቁጥር | የአስተባባሪዎች ቁጥር | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ጠቅላላ | ሴት | ወንድ |
| 36 | 47 | 214 | 98 | 116 |

በሌላ በኩል ከዩኒቨርሲቲ የተመረጡ አስተባባሪዎች ሚናቸውን በአግባቡ ለመወጣት እንዲችሉ - የሚጠበቅባቸውን የስራ ዝርዝር በውል ስምምነት ከማስቀመጥ ባለፈ - በባለሙያዎች ቡድኑ እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን/ተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን ፅህፈት ቤት የጋራ ትብብር - በበርካታ ዙር የተደራጀ ስልጠና እንዲሰጣቸው ተደርጓል። ስልጠናው በዋናነት በሽግግር ፍትህ ምንነት፣ የኢትዮጵያ ውስን ተመክሮ፣ የባለሙያዎች ቡድኑ ያዘጋጀው የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ስራ ዓላማ እና ስነ-ዘዴ፣ የተሳካ ምክክር ከማካሄድ አንፃር ተሳታፊዎች የሚለዩበትና የሚመረጡበት አካሄድ፣ እንዲሁም የምክክር መድረኮች የሚሳለጡበትና በምክክር ጊዜ የሚነሱ የውይይት ሀሳቦች በተደራጀ መልኩ የሚያዙበትን አሠራር አስመልክቶ - ተግባራዊ በሚደረጉ ሂደቶች ላይ አተኩሮ እንዲሰጥ ተደርጓል።

ሰንጠረዥ 8: ከዩኒቨሲቲዎች የተመረጡ አስተባባሪ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን የስልጠና መርሀ-ግብር መግለጫ

**TRAINING OF FACILITATORS OF REGIONAL PUBLIC CONSULTATIONS ON TRANSITIONAL JUSTICE POLICY OPTIONS IN ETHIOPIA**
**VIRTUAL**
**ROUND __, 20 APRIL 2023**

**PROGRAM**

| Time | Agenda | Responsible Persons |
|---|---|---|
| 8:30-8:45 | Registration (Virtual) | Participants |
| 8:45-9:00 | Welcoming Remark and Introduction | Transitional Justice Working Group of Experts (TJ-WGE) |
| 9:00-9:30 | Brief Overview of TJ and the Past Attempts in Ethiopia | A Member of TJ-WGE |
| 9:30-10:20 | A Glimpse at the Roadmap for TJ Policy Development: Purposes & Methodology of the Public Consultations | TJ-WGE |
| 10:20-11:00 | Discussion | Participants and TG-WGE |
| 11:00-11:40 | The How of Conducting Meaningful Consultations: Challenges and Best experiences in Selecting Participants, Facilitating and Notetaking of Discussions | The EHRC and UN OHCHR-EARO |
| 11:40-12:30 | Discussion | TJ-WGE, EHRC and UN OHCHR-EARO |

### 4.3.1.6. *በምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቶች ያጋጠሙ ውሰንነቶች*

*በእቅድ ደረጃ አጠቃላይ መርሀ-ግብሩ ከ4-5 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ታስቦ የነበረ ቢሆንም - በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ይህን እቅድ በታሰበው ጊዜ ውስጥ መፈፀም አልተቻለም።*

*በታቀደው ጊዜ ውስጥ ለመፈፀም ካልተቻለባቸው ምክንያቶች መካከል አንደኛው ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የተለያዩ የተ.መ.ድ ፅህፈት ቤቶች ዘግይተው የመጡ በርካታ የቅንጅታዊ ተሳትፎ ጥያቄዎች - በጥምረት ተጨማሪ የምክክር መድረኮች የማድረግን አስፈላጊነት ያጎሉበት አጋጣሚ በመፈጠሩ ነው።*

*ሁለተኛው ምክንያት በአማራ እና በትግራይ ክልሎች የሚካሄዱ የምክክር መድረኮችን በተመለከተ - ከፀጥታ እና ሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ መርሀ-ግብሮች ቢያንስ ለሁለት ጊዜ እንዲገፉ ማስገደዳቸው ነው።*

*በሌላ በኩል ምንም እንኳ በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች 80 የምክክር መድረኮችን በተሳካ ሁኔታ ማከናወን ቢቻልም - ከፀጥታ እና ደህንነት ጋር በተያያዙ እና በሌሎች ምክንያቶች ሰባት የታሰቡ እና በጊዜያዊነት ወደ እቅድ ምዕራፍ ተሸጋግረው የነበሩ መርሀ-ግብሮች እንዳይካሄዱ ሆኗል። በውስን አካባቢዎች ከነበረው የግጭት እና አለመረጋጋት ወቅታዊ ሁነት አንፃር ምክክሮቹን በታቀደላቸው ቀናት ውስጥ ማካሄድ የሚቻልበት እድል አልነበረም። ምቹ ሁኔታ*

በሌለበት - ፈታኝ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ችላ በማለት ምክክሮቹን ለማካሄድ መሞከር - ተሳታፊዎችን በበቂ ቁጥር በቦታው እንዳይገኙ ያደርጋል፤ ቢገኙም በስጋት ጫና ውስጥ እንዲወድቁ እና ለብቀላ እርምጃ እንዲጋለጡ የሚያደርግ መሆኑ አይቀርም። ሂደቶቹን በሚያስፈፅሙ አስተባባሪዎች እና የባለሙያዎች ቡድኑ አባላት ላይ የሚፈጥረው የስነ-ልቦና ጫናም በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በመሆኑም በጥቂት ከተሞች - አስቀድመው የታሰቡ የምክክር መድረኮች በፀጥታ ምክንያት ወደሙሉ የእቅድ ዝግጅት ምእራፍ እንዳይገቡ የተደረገ ሲሆን፡ በሌሎች ውስን ከተሞች የታሰቡ የምክክር መድረኮች ደግሞ ዝርዝር እቅድ ወጥቶና ውይይት የሚካሄድባቸው ሆቴሎች እና የሎጂስቲክስ ዝግጅቶች ከተጠናቀቁ በኋላ ፕሮግራሞቹ እንዲሰረዙ ሆኗል። በተጨማሪም በሌሎች ሶስት ከተሞች እቅድ ወጥቶላቸው የነበሩ የምክክር መድረኮች - ምክክር የሚደረግባቸው ቦታዎች/ሆቴሎች ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ - በፀጥታ ስጋት ምክንያት ተሳታፊዎችን ወደ ሌሎች አጎራባች ከተሞች በማጓጓዝ ምክክሮቹ እንዲካሄዱ ተደርጓል።

በመጨረሻም - ምንም እንኳ የዳያስፖራውን ማህበረሰብ ማዕከል ያደረገ ምክክር የማካሄድ ግዴታን አስመልክቶ ጠንከሮ የወጣ አለማቀፍ ተሞክሮ አለ ማለት ባይቻልም - የባለሙያዎች ቡድኑ የዳያስፖራውን ማህበረሰብ ድምፅ እና እይታ ለመረዳት በመሻት ረጅም ጊዜ የወሰደ ዝግጅት አድርጓል። ለዚህም ዝግጅቱ ከሚያስወጣው ከፍተኛ ወጪ አንፃር ከአጋር አካላት ጋር ስምምነት በመፍጠር ለረጅም ጊዜ ዝግጅት ቢያደርግም - በበጀት እጥረት ምክንያት ይኸው ምእራፍ ባለመጠናቀቁ ምክክሩን ማካሄድ አልተቻለም ።

በአጠቃላይ ከላይ የተመለከቱ ጥቂት መርሀ-ግብሮች ሳይካሄዱ በመቅረታቸው - ከግብዓት አሰባሰብ ስነ-ዘዴ እና ባለድርሻ አካላትን ሁሉ ተቀባይነት ባለው መጠን ከመድረስ አንፃር በራሱ የሚፈጥረው የተለየ አሉታዊ ተፅእኖ ባይኖርም - በነዚህም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ ማህበረሰቦችን ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲቻል - ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ተጨማሪ የምክክር መድረኮች እንዲካሄዱ ተደርጓል።

#### 4.3.1.7. በምክክር መድረኮች የተስተዋለው የማህበረሰቡ ከፍተኛ ተሳትፎ ልዩ እንደምታ

ከላይ እንደተመለከተው በምክክር መድረኮች እንዲገኙ የተጠሩት ተሳታፊዎች አማካይ የተሳትፎ ምጣኔ ከ99% በላይ ነው። በተጨማሪም ጥቂት በማይባሉ መድረኮች ላይ በባለቤትነት እና ይመለከተኛል ስሜት ሳይጋበዙ የመጡ እና ለመሳተፍ ጥያቄ ያቀረቡ የሙብት ጥሰት ሰለባ ሰዎችም ነበሩ። ስለሆነም በቂ የህዝብ ተሳትፎን ከማረጋገጥ አንፃር የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ የተሳካ ነበር ማለት ይቻላል።

ይህን ከፍተኛ የተሳትፎ ተነሳሽነት ልዩ ትርጉም የሚያሰጠው ሌላው ምክንያት - በየከተሞቹ በተካሄዱት የምክክር መድረኮች ከተሳተፈው ህዝብ ግማሽ ያህሉ ከከተሞቹ አጎራባች ቀበሌዎች እና ራቅ ካሉ ወረዳዎች የመጡና ተደራራቢ የኑሮ ሀላፊነት ያለባቸው ሴቶች መሆናቸው ነው።

በጥቅሉ ሲታይ በየመድረኮቹ የተሳተፉ የማህበረሰብ ክፍሎች - በባለሙያዎች ቡድኑ የተደረገላቸውን ጥሪ በመቀበል እና በምክክሮቹ ላይ በመገኘት ምልከታዎቻቸውን በነፃነት እና በዝርዝር መግለፃቸው፣ ሰፋፊ ክርክሮችን ማካሄዳቸው፣ እና በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ዙሪያ ያላቸውን ተስፋ እና ስጋት በተለያየ መንገድ ማንፀባረቅ መቻላቸው - ሕዝቡ ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም በአጠቃላይ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ የጣለውን ትልቅ ተስፋ እና እምነት የሚያመላክት ነው።

### 4.3.2. በምክክር ሂደቱ ላይ በነፃ ፈቃድ ስለመሳተፍ

ተሳታፊዎች በምክክር ሂደቶች በነፃ ፈቃድ ለመሳተፍ ያላቸውን መብት በተግባር ከማረጋገጥ አንፃር የቅድመ-ጥንቃቄ እና የአቀራራብ ፕሮቶኮል አስቀድሞ ተዘጋጅቷል። የልየታ ስራውን የሰሩ አስተባባሪ የዩኒቨርሲቲ መምህራንም ለተሳትፎ የሚጋብዟቸው ሰዎችን የሚቀርቡበት የተግባቦትና ነፃ ፈቃድ አጠያየቅ ዘይቤ አስቀድመው

እንዲያውቁት ለማድረግ ስልጠና ተሰጥቷል። የሚጋበዙ ተሳታፊዎች ለመሳተፍ ከመወሰናቸው በፊት - የምክክሩን ዓላማ፣ ዘዴ እና ግብ በዝርዝር እንዲረዱ እና የሚሳተፉትም በፈቃዳቸው ብቻ እንደሆነ እንዲያውቁት ተደርጓል።

በተጨማሪም ተሳታፊዎች በምክክር መድረኮች እና በቡድን ውይይቶች ጊዜ የሚሰጡት ማናቸውም ሀሳብ ግላዊነት እና ምስጢራዊነትን በጠበቀ መልኩ እንደሚያዝ የተገለፀላቸው ሲሆን፣ የቡድን ውይይቶች የድምፅ መቅረፅ ስራዎችም በተዘጋጀው ፕሮቶኮል መሰረት በሰጡት ነፃ ፈቃድ ላይ ብቻ ተመስርቶ እንዲከናወን ተደርጓል።

### 4.3.3. የምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ ተጎጂ-ተኮር እይታን በማረጋገጥ ረገድ የተከተለው አሰራር

የሽግግር ፍትህ ሂደትን ሰብዓዊ መብት ተኮርነት ለማረጋገጥ እና ለውጤታማነቱ የተደላደለ መሰረት ለመፍጠር - ሂደቱ ከጥንስሳ እስከ ትግበራ በሁሉም ምዕራፎች የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎችን ማዕከል ሊያደርግ ይገባል። ይህ ቅድመ-ሁነት በተለይ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ዝግጅት ሂደት ልዩ ትርጉም አለው። በመሰረቱም ምክክርና ግብዓት የማሰባሰብ ስራ ሂደቱ ተጎጂ-ተኮር፣ አካታች እና አሳታፊ የመሆን ግዴታ አለበት። ይህን ማረጋገጥ የሚዘጋጀው የሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የተጎጂዎችን ፍላጎት እና ምልከታ ያካተተ እና ተጎጂዎች የሂደቱ ባለቤት ስለመሆናቸው እውቅና ለመስጠት የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ - የትግበራ ምእራፉም ውጤታማ እንዲሆን ተገቢ አውድ ለመፍጠር ያግዛል።

በመሆኑም የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱን ተጎጂ-ተኮርነት ለማረጋገጥ የባለሙያዎች ቡድኑ የተለያዩ አሰራሮችና ስልቶችን ተፈፃሚ አድርጓል።

**በዚህ ረገድ የተተገበረው የመጀመሪያው እርምጃ፣** የባለሙያዎች ቡድኑ ባዘጋጃቸው ሁሉም መድረኮች ላይ በየመድረኮቹ ከሚሳተፉ 60 ሰዎች ውስጥ ቢያንስ 60% (36 ተሳታፊዎች) ተጎጂዎች እንዲሆኑ የሚያስገድድ የተሳታፊዎች ልየታ እና መረጣ ቴምፕሌት መዘጋጀቱ እና መተግበሩ ነው።

በዚህ ረገድ - 'የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ተጎጂዎች' የሚለው ፅንሰ-ሀሳብ እንዲሁ አንድ ወጥ የሆኑ ተበዳዮችን የሚመለከት ሳይሆን - በደረሰባቸው በደል፣ ለጥሰቶቹ ምክንያት በሆነው አውድ ወይም ሁኔታ አንጻር፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በአካባቢ እና ሌሎች መስፈርቶች መሰረት ብዝሃነትን በሚያሳይ መልኩ በመረዳት - የተሳታፊዎች ልየታ እና መረጣ እንዲከናወን ተደርጓል። በዚህ መስፈርት መሰረትም - የአካል ጉዳት የደረሰባቸው፣ የቤተሰብ አባል የተገደለባቸው፣ የጾታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ፣ የማሰቃየት ድርጊት የተፈፀመባቸው፣ አላግባብ የታሰሩ፣ የተፈናቀሉ እና ንብረት የወደመባቸው ሴቶች፣ ወንዶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን እንዲለዩ እና እንዲሳተፉ ሆኗል።

**ሁለተኛው እርምጃ፣** በምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ ተጎጂዎች በቀረቡ የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ ምልከታቸውን በተገቢ መልኩ እና ያለስጋት እንዲያጋሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠርን የሚመለከት ነው። በመሆኑም በያንዳንዱ የምክክር መድረክ በጉዳት መጠን፣ በአይነት እና በጾታ ላይ የተመሰረተ አንድ የሴት ተጎጂዎች ቡድን እና አንድ የወንድ ተጎጂዎች ቡድን በማደራጀት የትኩረት ቡድኖች ውይይት እንዲሳለጥ ተደርጓል። በዚህም ሂደቱ ተጎጂ-ተኮር እንዲሆን ከማድረግ ባለፈ በየምክክሮቹ ተጎጂዎች ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።

**በተጨማሪም፣** የሂደቱን ተጎጂ-ተኮርነት ለማጠናከር እና ተጎጂዎች በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ ምልከታቸውን እንዲያጋሩ ለማስቻል የባለሙያዎች ቡድኑ ከተ.መ.ድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) ጋር በመተባበር በተጎጂዎች ላይ ብቻ ያተኮሩ አምስት ተጨማሪ መድረኮችን አዘጋጅቷል። በዚህ ረገድ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ላይ ያተኮሩ ሶስት መድረኮች በአሶሳ፣ በመቐለ እና በጭሮ ከተሞች የተዘጋጁ ሲሆን 179 ተጎጂዎችን በማሳተፍ ተጎጂ-ተኮር ምልከታዎች እና ግብዓቶችን ማሰባሰብ ተችሏል።

በተመሳሳይ የባለሙያዎች ቡድኑ ከUN-WOMEN ጋር በመተባበር በጾታዊ ጥሰቶች ሰለባ ሴት ተጎጂዎች ላይ ብቻ ያተኮሩ ሁለት መድረኮችን በመቀሌ እና ባህርዳር ከተሞች በማዘጋጀት የሂደቱን ተጎጂ-ተኮርነት የሚያረጋግጡ ስራዎችን አከናውኗል፡ ተጎጂ-ተኮር ግብዓትም ተሰብስቧል።

### 4.3.4. የምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ የፆታ እይታን በማረጋገጥ ረገድ የተከተለው ልዩ አሠራር

#### 4.3.4.1. መርህ

የፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ ለሽግግር ፍትህ ዓላማ መሳካት ላቅ ያለ አስተዋፅኦ አለው። በብዙ አጋጣሚዎች እንደሚስተዋለው ሴቶች የተለያዩ ጥቃቶች ሰለባ ይሆናሉ፤ ከኢኮኖሚ እና ፖለቲካ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ይገለላሉ፤ ለአድሎአዊ አሠራሮችም የተጋለጡ ናቸው። እነዚህ እና መሰል መዋቅራዊ የማህበረሰብ ችግሮች - ሴቶች በሽግግር ፍትህ ሂደት እኩል እና የነቃ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው የማድረግ አቅም አላቸው።

በመሆኑም በምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ የተለየ መንገድን በመከተል የሴቶችን ሙሉ ተሳትፎ ማረጋገጥ ፍፁም አስፈላጊ ይሆናል። ይህን ለማሳካት የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶች በባለሙያዎች ቡድኑ ተግባራዊ ተደርገዋል።

#### 4.3.4.2. ተመዛዛኝነት ያለው የፆታ ውክልና ለማረጋገጥ የተከወነ የዝግጅት ሥራ

በሀገር-አቀፍ ደረጃ በተደረጉት የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቶች የሴቶች ተመጣጣኝ ውክልና እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው። ይህም አጠቃላይ ሂደቱ የፆታ እይታን ያረጋገጠ እንዲሆን በማድረግ ረገድ - የባለሙያዎች ቡድኑ የተከተለው ልዩ አሠራር ውጤት ነው። ለዚህ ዓላማ ሲባል በተዘጋጀው ፕሮቶኮል ላይ በግልፅ በተቀመጠው መሰረት - በሁሉም የምክክር መድረኮች የሴት ተሳታፊዎች ቁጥር ከወንድ ተሳታፊዎች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። የሴቶችን ተሳትፎ ከማረጋገጥ አንፃርም በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል።

***የመጀመሪያው የዝግጅት ሥራ፥*** ሴቶች በተደረጉት ሀገር-አቀፍ የምክክር መድረኮች ከወንዶች እኩል እንዲሳተፉ የተደረገበት አግባብ ነው። በየአካባቢው ከሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሰራቱ - በክልል የምክክር መድረኮች ላይ የተሻለ የሴት ተሳታፊዎች ቁጥር ለማረጋገጥ ተችሏል። በዚህ ረገድ የዩኒቨርሲቲ አስተባባሪዎች ሚና ከፍተኛ ነበር።

***ሁለተኛው እርምጃ፥*** የሴቶችን ልዩ ማህበረሰባዊ ቁመና እና ድርብርብ ተግዳሮትን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት - በሴቶች ላይ ብቻ ያተኮሩ የተጨማሪ መድረኮች ዝግጅትን የሚመለከት ነው። ከዚህ አንፃር ከUN-WOMEN ጋር በመተባበር ከግንቦት 22-23 2015 ዓ.ም 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከሴቶች ጋር ብቻ የተካሄደ ሀገር-አቀፍ የምክክር መድረክ' በቢሾፍቱ ከተማ ተዘጋጅቷል። በመድረኩ ላይ ከተለያዩ አካባቢዎች እና የሙያ ዘርፎች፣ የሴት መብት ተጣባቂ ድርጅቶች፣ ሴታዊት አደረጃጀቶች፣ የሴት ሚዲያ ባለሙያዎች፣ ሴት ምሁራን፣ ተፅእኖ ፈጣሪዎችና የቀድሞ አምባሳደሮች፣ ሴት መምህራን፣ ሴት የማህበረሰብ ተወካዮች እና ለሴት ተጠቂዎች አገልግሎት ከሚያቀርቡ ድርጅቶች የተወከሉ 68 ሴቶች እና 3 ወንዶች - በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦቹ ላይ የሁለት ቀናት ክርክር እና ውይይት አካሂደዋል። አቋማቸውንም አንፀባርቀዋል።

በተመሳሳይ - ከላይ እንደተመለከተው - የሴቶችን የተሳትፎ አይነት እና መጠን አንድ ደረጃ ከፍ በማድረግ 'በሽግግር ፍትህ ሀሳቦች እና የፖሊሲ አማራጮች ላይ ከፆታ ጥቃት ሰለባ ሴቶች ጋር ብቻ የተካሄዱ የምክክር መድረኮች' በመቀሌ እና በባህርዳር ከተሞች ከሀምሌ 24-26 2015 ዓ.ም ተከናውነዋል።

#### 4.3.4.3. ያጋጠሙ ውስንነቶች

የፆታ ተመጣጣኝ ውክልና እና ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚያስችል ግልፅ ፕሮቶኮል ወጥቶ ወደስራ የተገባ ቢሆንም፣ እንዲሁም በዚህ ረገድ በተከናወነው ስራ የተገኘው የሴት ተሳታፊዎች ቁጥር - አጠቃላይ ሂደቱ ሊያሳካው ከሚሻው ግብ አንፃር ከበቂ በላይ መሆኑ ቢታወቅም፣ በተለያዩ ምክንያቶች በፕሮቶኮሉ ላይ የተመለከተውን 50% የሴቶች ተሳትፎ ሙሉ ለሙሉ እውን ማድረግ አልተቻለም። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አስተዋፅኦ አድርገዋል።

የመጀመሪያው ምክንያት - ሴቶች በተለይም መድረኮችን ከሚያስተናግዱ ከተሞች አጎራባች ቀበሌዎች ወይም ወረዳዎች የሚመጡ ሴት ተሳታፊዎች - ከፍተኛ ቤተሰባዊ ጫና እና ተደራራቢ ማህበረሰባዊ ሀላፊነት ያለባቸው መሆኑ ነው። ይህ ኩነት በአንዳንድ ሴቶች የተሳትፎ ውሳኔ ላይ ምንም ተፅእኖ የለውም ማለት አይቻልም።

በተጨማሪም - በሕዝባዊ ምክክሮቹ ለመሳተፍ ከወረዳ ወደ ዞን ከተማ መጓዝና ለሁለት ቀናት አድሮ መመለስ - ለማናቸውም ሰው ቢሆን ቀላል ውሳኔ አይደለም። በዚህ ረገድ በሴቶች ላይ የሚጣለው የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ባህላዊ ጫናም በቀላሉ የሚገለፅ አይደለም።

በነዚህ ምክንያቶች - በጥቂት መድረኮች ላይ - ሴት ተሳታፊዎች አስቀድመው የሰጡትን የተሳትፎ ፈቃድ በመጨረሻ ሰዓት ላይ የሰረዙበት አጋጣሚ ተፈጥሯል። ይህን የሀሳብ ለውጥ ተከትሎ ተተኪ ሴት ተሳታፊዎችን በእለቱ ለማምጣት የተሰራው ስራ በአንዳንድ መድረኮች ውጤታማ ቢሆንም በውስን ቦታዎች ግን የተሳካ አልነበረም።

ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች በአንዳንድ የምክክር መድረኮች ላይ የወንድ ተሳታፊዎች ቁጥር በተነፃፃሪነት ከፍ እንዲል ማድረጉ የራሱ እንደምታ እንደሚኖረው ግልፅ ነው። ሆኖም በምርጥ ተመክሮም ቢሆን - ሕዝባዊ ምክክርን ጨምሮ ሁሉም የሽግግር ፍትህ ስራዎች ለባህላዊ እሴቶች፣ አስተሳሰቦችና አካባቢያዊ ኩነቶች ልዩ ቦታ በመስጠት መከናወን ያለባቸው ከመሆኑ አንፃር - ተግዳሮቱ ተቀባይነት የሌለው ወይም ፍፁም የማይጠበቅ ነበር ለማለት አይቻልም።

### 4.3.5. የተሳታፊዎችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማረጋገጥ

#### 4.3.5.1. መርህ

አግባብነት ያላቸው መርሆዎችና ጥንቃቄዎችን በመከተል የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ መድረክ ተሳታፊዎችን መምረጥ አንድ ነገር ሆኖ - የተመረጡ ሰዎች ትርጉም ባለው መጠን የሚሳተፉበትን እድል የሚፈጥር ስነ-ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ ፍፁም አስፈላጊ ነው። የምክክር መድረኮች ዝግጅት እና ፍሰት ተሳታፊዎች በንቃት፣ በነፃነት፣ እና በጥልቀት የሚወያዩበት እና ሀሳብ የሚያካፍሉበትን እድል የሚያቀርብ መሆን አለበት። ተሳትፎዎች የይስሙላ ወይም የታይታ እንዳይሆኑ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።


ይህን መሠረታዊ መርህ የተከተለ የምክክር እና ግብዓት የማሰባበሰብ ስራ እውን ከማድረግ አንፃር የባለሙያዎች ቡድኑ በርካታ ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

#### 4.3.5.2. ተሳታፊዎችን በሽግግር ፍትህ ይዘት/ዓላማ ላይ የማንቃት/ማሳወቅ ሥራ

አብዛኛውን ጊዜ - ለምክክር መድረኮች የሚጋበዙ ተሳታፊዎች በተለይም የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ ግለሰቦች እና የተጎዱ ማህበረሰቦች - በሽግግር ፍትህ መሰረታዊ ፅንሰ-ሀሳቦች፣ ጥቅሞች እና ውስንነቶችን ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ የተገደበ ነው። በምክክር መድረኮች እና የትኩረት ቡድን ውይይቶች ላይ የተሳታፊዎች ጥራት እና ትርጉም ያለው ተሳትፎን ማረጋገጥ የሚቻለው - በተሳታፊዎች አንፃር በሽግግር ፍትህ ይዘት እና በምክክሮቹ አጠቃላይ ዓላማ ላይ በደንብ የተደራጀ የማንቃት እና የማሳወቅ ሥራ መሥራት ሲቻል ብቻ ነው። ይህን አስቀድሞ ማከናወን ተሳታፊዎች በይዘት ላይ ያተኮረ ጥልቅ ውይይት ማድረግ የሚችሉበትን የእውቀት ስንቅ ያስጨብጣል።


ከዚህ በመነሳት የባለሙያዎች ቡድኑ ሶስት ተመጋጋቢ መሰረታዊ ዝግጅቶችን ተግባራዊ አድርጓል።

**የመጀመሪያው፥** በሽግግር ፍትህ መሰረታዊ ሀሳቦች፣ ዓላማዎች፣ መርሆዎች፣ ዋቅል የፖሊሲ አማራጮች፣ የሀገራት ተሞክሮ እና ከሂደቱ በሚጠበቁ ተስፋዎች ላይ ዘርዘር ያለ ምልከታን የሚሰዋ ራሱን የቻለ የስልጠና ሰነድ ዝግጅትን የሚመለከት ነው። ከዚህ ጋር ተያያዥ የሆነው ስራ ደግሞ - በአማርኛ የተዘጋጀውን ይህን የስልጠና ሰነድ ቢያንስ በሶስት ዋና ዋና ቋንቋዎች (በሶማሊኛ፣ አፋን ኦሮሞ እና ትግርኛ) እንዲተረጎም በማድረግ የሀሳቦቹን ተደራሽነት ይበልዋ ለማስፋት የተሰራው ስራ ነው።


ኢትዮጵያ፡ መማረፅታት ፖሊሲ ስርዓት ፍትሒ ስግግር

ካብ መዳርግቲ ኣካለት ሪእቶ ንምእካብ ዝተዳለወ ረቂቅ

ጥሪ ፳፻፲፭ ዓ.ም



Itoophiyaa

Fillannoowwan Kallattii Imaammata Haqa Ce'umsaa

Qooda Fudhattoota Irraa Galtee Walitti Qabuuf Kan Qophaa'e

Amajjii 2015

Addis Ababa


KALA DOORASHADA ITOOBIYA EE SIYAASADA CADAALADA

XILLIGA KALA GUURKA

QABYO QORAALKA LOO DIYAARIYAY WADA TASHIGA

DANEEYAYAASHA

WAXAA LADIYAARIYAY BISHII JANUARY EE 2023

**ሁለተኛው ስራ፥** በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ የመጀመሪያውን ቀን መርሀ-ግብር ላይ በአማካይ ለአንድ ሰአት የሚቀይ በቀላል ቋንቋ የሚቀርብ ስልጠና እንዲሰዋ መደረጉ ነው።

**በመጨረሻም፥** በተሳታፊዎችና መላው ሕዝብ ሊኖር የሚችለውን የሽግግር ፍትህ ፅንሰ-ሀሳቦች የእውቀት ክፍተት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት - የባለሙያዎች ቡድኑ አባላት በግል እና በመንግስት የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እና የፕሬስ ድርጅቶች ፊት በመቅረብ ሰፊ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎችን ሰርተዋል። በተጨማሪም ከዋቂት የሲቪል ማህበረሰብ አደረጃጀቶች ጋር በመቀናጀት - በነዚሁ ተቋማት አማካኝነት ማህበረሰብን የማሳወቅ እና የማንቃት ስራ እንዲሰራ ተደርጓል።

በድምሩ ሲታይ ይህ አካሄድ በተሳታፊዎች እውቀት እና የግንዛቤ አቅም ላይ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት ችሏል። ተሳታፊዎች በሚቀርቡ የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ክርክር ወቅት በእውቀት ላይ የተመሰረተ እይታን የሚያጋሩበት እና በውጤቱም ላይ አሻራቸውን የሚተውበትን እድል ፈዋሯል። በተጨባጭም ይህ ስራ - መረጃ ከአንድ ወገን ብቻ ወደ ሌላው የሚፈስበት ሳይሆን - ከአቅራቢዎች ወደ አድማጭ ተሳታፊዎች እንዲሁም ከአድማጭ ተሳታፊዎች ወደ ጋራ መድረክ በተደራጀ መልክ የሚንሸራሸርበትን የውይይት አውድ አመቻችቷል።

በሌላ በኩል የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ-ግብሮቹ በተሳታፊዎች ዘንድ የሽግግር ፍትህ ዓላማዎች እና ተስፋዎችን አስመልክቶ ተጨባጭ ያልሆኑ ወይም የተሳሳቱ አረዳዶች እንዳይኖሩ ለማድረግ የሚያስችሉ ማብራሪያዎች የሚሰጡባቸው መድረኮች ሆነው አገልግለዋል።

### 4.3.5.3. ተለዋዋጭ/አማራጭ የቋንቋ እና ትርጉም አገልግሎት አቅርቦት

በምክክር መድረኮቹ ላይ ተሳታፊዎች ዋራት እና ትርጉም ያለው ውይይት ማድረግ የሚችሉት ከቋንቋ ጋር የሚያያዙ ገዳቢ ኩነቶች የሌሉባቸው እንደሆነ ነው። በዚህም ረገድ በምንም መልኩ የሚገለፅ እንከን እንዳይከሰት በባለሙያዎች ቡድኑ ሰፊ ዋንቃቄ ተደርጓል።

ስለሆነም በሁሉም መድረኮች ላይ የማስጀመሪያ መርሀ-ግብሮች (ማለትም የእምነት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ምርቃትና የፕሮግራም ዓላማ መግለጫዎች) በየአካባቢዎቹ ቋንቋ እንዲካሄዱ ተደርጓል።

በቀጣይ የተከወኑ መርሀ-ግብሮች ከባለሙያዎች ቡድኑ የሚቀርቡ ሁለት ፅሁፎችን የሚመለከቱ ናቸው። በአብዛኞቹ መድረኮች ላይ ተሳታፊዎች ተመሳሳይ ቋንቋ መናገር የሚችሉበትን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት - ፅሁፎቹ በአማርኛ ወይም ተሳታፊዎች ከመረጡ በሌላ የአካባቢው ቋንቋ ወይም በቅልቅል ቋንቋ[37] እንዲካሄዱ ተደርጓል። ምንም እንኳ የባለሙያዎች ቡድኑ አባላት የሁሉም የሀገሪቱ ብሄረሰቦች ቋንቋ እውቀት ባይኖራቸውም - ከዩኒቨርሲቲዎች የተመረጡ አስተባባሪዎችን በአስተርጓሚነት መጠቀም የሚቻልበት እድል የነበረ በመሆኑ - በሁሉም መድረኮች ተሳታፊዎች የሚስማማቸውን ቋንቋ እንዲመርጡ ጥያቄ ቀርቧል።

በየውይይት መድረኮቹ የግማሽ ቀን (ከሰአት በኋላ) የተካሄዱ የትኩረት ቡድን የውይይት መርሀ-ግብሮች ሁሉ ከሞላ ጎደል በየአካባቢው ቋንቋ እንዲሳለጡ እና እንዲካሄዱ ተደርጓል። በዚህ ረገድ በየክልሎቹ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የተመረጡ አስተባባሪዎች በትርጉም፣ በትኩረት ቡድን ውይይት አሳላጭነት፣ እና በማስታወሻ ያዥነት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። አስተባባሪዎች የነበራቸው አስተዋፅኦ - በምክክር ሂደቱ ላይ ማንም ሰው በቋንቋ ምክንያት ወደኋላ እንዳይተው/እንዳይቀር እና ሁሉም በየአቅሙ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ አስችሏል።

### 4.3.5.4. የተሳታፊዎች የፕሌናሪ ውይይት እና የትኩረት ቡድኖች ውይይት መድረኮች ዝግጅት

የተሳታፊዎችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማረጋገጥ የባለሙያዎች ቡድኑ የተከተለው ሌላው ዘዴ ሁለት ዋና ዋና የአካሄድ ገፅታዎች አሉት።


**የመጀመሪያው፥** በምክክር መድረኮቹ የጠዋቱ መርሀ-ግብር የሚሳለጡ ሁለት ፅሁፎችን የማቅረብ ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ - ሙሉ ጊዜውን ለተሳታፊዎች ነፃ እና ያልተቋረጠ ውይይት እንዲተው ማድረግ ነው። በዚህም ተሳታፊዎች ከአቅራቢዎች እና አስተባባሪዎች ከሚሰጡ ማናቸውም አስተያየቶች ሙሉ ለሙሉ እንዲጠበቁ በማድረግ ሀሳባቸውን በነፃነት፣ በራስ መተማመን እና በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰጡ አስችሏቸዋል።

**ሁለተኛው፥** አካሄድ ተሳታፊዎች በአማካይ ከ12-15 አባላት ባሏቸው አራት ንዑሳን ቡድኖች እንዲከፈሉ በማድረግ - በቀረቡ ሁሉም የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ ጥልቅ ውይይት እና ክርክር ያደረጉበት ሂደት ነው። ይህ መድረክ ሙሉ የሰአት በኋላ (ግማሽ ቀን) ጊዜ የተሰጠው ሲሆን - ተሳታፊዎች ረጅም ጊዜ ወስደው ሀሳባችውን በእርጋታና በጥልቀት እንዲያጋሩና ትርጉም ባለው መጠን ተሳትፏቸውን እንዲያረጋግጡ አስችሏቸዋል።

የዚህ ሂደት ዋና ዓላማ ተሳታፊዎች በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ ዝርዝር ክርክር እንዲያካሄዱና እይታቸውን እንዲያጋሩ ማስቻል እንደመሆኑ መጠን - የውይይት ጥያቄዎቹ በጥንቃቄ እና በዝርዝር እንዲቀረፁ ተደርጓል።[38] በተጨማሪም ተሳታፊዎች በቡድን ውይይቱ ዓላማ ላይ፣ በቀረቡ አማራጮች አንፃር ያላቸውን ምልከታ እንዴት ማስረዳት እንደሚኖርባቸው፣ ከቀረቡት ውጭ ሌሎች አማራጮችን ማቅረብ እንደሚችሉ፣ በውይይቱ የሌሎች ተሳታፊዎችን እና አስተባባሪዎችን ሀሳብ እና ክብር መጠበቅ እንደሚኖርባቸው፣ የተሳታፊዎች ሀሳብ ሚስጥራዊነት እንደሚከበር ወዘተ በዝርዝር እንዲገለፅላቸው ተደርጓል።

ሰነድ 1፥ 'በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች- ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለመሰብሰብ የተዘጋጀ የውይይት መድረክ - የቡድን ውይይት ዓላማ፣ መርሆዎችና የመወያያ ጥያቄዎች'

[37] 'የቅልቅል ቋንቋ' ማለት በአንድ መድረክ የተለያዩ ቋንቋዎችን እያደባለቁ ለመግባቢያነት መገልገል ማለት ነው።
[38] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን (ሰነድ)፡ 'በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለመሰብሰብ የተዘጋጀ የውይይት መድረክ የቡድን ውይይት አላማ፣ መርሆዎችና የመወያያ ጥያቄዎች'፡ 2015 አዲስ አበባ



*በሌላ በኩል የሚያስተባብሩ እና ማስታወሻ የሚይዙ ከዩኒቨርስቲዎች የተመረጡ መምህራን ሁሉ - የውይይት መድረኮችን ሲመሩ የሚከተሉት ፕሮቶኮል እና ለተሳታፊዎቹ የሚሰጡት ገለፃ ምን እንደሆነ እንዲያውቁት ለማድረግ ዝርዝር ስልጠና ተሰጥቷል።*

*በድምሩ ከላይ የተመለከቱት የቅድመ-ምክክር መርሀ-ግብር ዝግጅቶች - የግለሰቦችን ግንዛቤ እና የመሳተፍ አቅም በማበልፀግ በአጠቃላይ የምክክር እና ግብዓት የማሰባሰብ ሂደቱ ጥራት እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው አስተዋፅኦ አበርክተዋል።*

### 4.3.5.5.*ያጋጠሙ ውስንነቶች*

*ተሳታፊዎች በሽግግር ፍትህ ይዘት እና ዓላማ ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ እንዲይዙና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ የተሰሩ የማንቃት እና የማሳወቅ ስራዎች በርካታ ቢሆኑም - በቂ ነበሩ ማለት ግን አይቻልም። በሀገራዊው የፖለቲካ አውድ አዲስ የሆነው የሽግግር ፍትህ እሳቤን ውስን በሆኑ መንገዶች ብቻ ወደ ህዝብ አእምሮ በቀላሉ ማስረፅ አይቻልም።*

*በዚህ ረገድ በቀላል አገላለፅ በተዘጋጁ የስነ-ፅሁፍ አማራጮች፣ ድራማዎች እና ቁም-ነገር አዘል ጨዋታዎች የተቃኙ ትኩረት-ሳቢ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር የሚቻልበት እድል ጥቅም ላይ አልዋለም። የባለሙያዎች ቡድኑ የራሱ የኮሚዩኒኬሽን ባለሙያ እና የኮሚዩኒኬሽን ስራዎች በጀት ያልነበረው መሆኑ ለዚህ ክፍተት አስተዋፅኦ አድርጓል።*

*በሌላ በኩል በብዙዎቹ መድረኮች ላይ ከቋንቋ አጠቃቀም እና የትርጉም አገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ይህ ነው የሚባል ጉልህ ችግር ባያጋጥምም - በጥቂት መድረኮች በተለይም መድረኮቹ ከብዙ ብሔር ብሔረሰቦች የተሰባሰቡ ተሳታፊዎችን በያዙባቸው አጋጣሚዎች - (አማርኛን ጨምሮ) ሁሉም ተሳታፊዎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚረዱት አንድ ቋንቋ ማግኘት አዳጋች ነበር። ይህን ተግዳሮት ለማቃለል ከዩኒቨርሲቲዎች የተመደቡ አስተርጓሚዎች እንዲያግዙ ቢደረግም አስተባባሪዎችም ቢሆኑ የሚኖራቸው የአካባቢ ቋንቋ እውቀት ከሁለት ወይም ሶስት ልሳናት የማያልፍ በመሆኑ - በአንዳንድ የደቡባዊ ኢትዮጵያ መድረኮች ጥቂት ተሳታፊዎች ውይይቶችን*

በሚፈለገው ደረጃ ለመረዳት ሲቸገሩ ተስተውሏል። ሆኖም ይህ ውስንነት - በአጠቃላይ የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ስራው ድምር ውጤት ላይ አሉታዊ ውጤት እንደማይኖረው የባለሙያዎች ቡድኑ ያምናል።

በሌላ በኩል በአንድ ከተማ የምክክር መድረክ ላይ ጥቂት ተሳታፊዎች ለግንዛቤ እና ለውይይት የቀረቡትን ሰነዶች በአማርኛም ይሁን በአስተርጓሚ (በአካባቢው ቋንቋ) መቅረባቸውን በመቃወም መድረኩን ለጥቂት ጊዜ ቢረብሹም - በኋላ ላይ በቂ ገለፃ ተሰጥቶ እና ስምምነት ላይ ተደርሶ ምክክሩ በሰላም እንዲጠናቀቅ ተደርጓል።

### 4.3.6. ከጉዳት የመጠበቅ መብት

#### 4.3.6.1. *መርሁ ተፈፃሚ የሆነበት አግባብ*

*በሽግግር ፍትህ ሥራ ማዕቀፍ ግብዓት ለማሰባሰብ የሚከወን ማናቸውም ሥራ በተሳታፊዎቹ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳይኖረው ማድረግ አስፈላጊ ነው። አሰራሩ ማናቸውም የሂደቱ ተሳታፊ ሊደርስበት የሚችለውን የጉዳት አደጋ መገመት የሚችልና የተሳታፊውን ከጉዳት የመጠበቅ መብት የሚያረጋግጥ መሆን ይኖርበታል።*

*በእያንዳንዱ የሽግግር ፍትህ የውይይት መድረክ ከተጋበዙት ተሳታፊዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሰለባ የሆኑ ግለሰቦች ናቸው። ይህ አሰራር ሂደቱን ተጎጂ-ተኮር ከማድረግ አንፃር የተወሰደ እርምጃ ነው።*

*በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ላይ የሚካሄድ ማናቸውም ውይይት በባህርይው ያለፉ ኩነቶችንና የተፈፀሙ በደሎችን የሚዳስስበት ሰፊ እድል ይኖረዋል። ይህም ሆኖ በመላው ሀገሪቱ በተካሄዱ የምክክር መድረኮች ላይ ተሳታፊዎች - በተለይም ያለፈ የሰብአዊ ሙብት ጥሰት ታሪክ ያላቸው ግለሰቦች - በመድረኮች ላይ በሚነሳ ሀሳብ ምክንያት ለአእምሯዊ እና አካላዊ ጉዳት እና ዳግም ስቃይ የሚጋለጡበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ጥንቃቄ ተደርጓል።*

*በዚህ ረገድ የተወሰደው እና በሂደቱም ጠቃሚነቱ የተረጋገጠው አካሄድ - ከጅምሩ የምክክሩ መርህ-ግብር ዋና ትኩረት እና ዓላማ ያለፉ ጥሰቶችን መዘርዘር፣ መነሻቸውን መመርመር ወይም ያስከተሉትን ጉዳት መተንተን ሳይሆን - በጥቅሉ ያለፉ ኩነቶች እንዳይደገሙ ከማድረግ አንፃር ሊወሰዱ የሚገቡ ተጨባጭ እርምጃዎች ምን ይሁኑ በሚል ጥቅል ሃሳብ ላይ ብቻ እንደሆነ ተሳታፊዎች በቅጡ እንዲረዱት የተደረገበት አሰራር ነው። በዚህ መንገድ የባለሙያዎች ቡድኑ አባላት እና አስተባባሪዎች በቂ ጊዜ በመስጠት ተሳታፊዎች ባለፈው ታሪካቸው ትርክት ላይ ብቻ ትኩረት ሳያደርጉ - በጥንቃቄ የግል ጉዳታቸውን ከፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦቹ ጋር እያጣጣሙ እንዲያቀርቡ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።*

#### 4.3.6.2. *ያጋጠሙ ውስንነቶች*

*ከጅምሩ አንስቶ የምክክሮቹን ዓላማ ዘርዝሮ በማስረዳት ብዙዎቹ ተሳታፊዎች በራሳቸው ግለሰባዊ ጉዳት ላይ ብቻ እንዳያተኩሩ ማድረግ ቢቻልም - በመድረኮቹ ላይ ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን ከራሳችው ግላዊ የህይወት ገጠመኝ እና ተሞክሮ ጋር እያዛመዱ ያቀረቡባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት ነበሩ ማለት ግን አይቻልም። ይህ ክስተት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተሳታፊዎችን ለዳግም ስቃይ ያጋለጠበት ሁኔታ ፈጥሯል።*

*ከአደረጃጀትም ይሁን ከሀብት ዝግጅት አንፃር የባለሙያዎች ቡድኑ በዚህ መልኩ ለሚገለፅ የተሳታፊዎች የዳግም ስቃይ ሁኔታ ምላሽ የተዘጋጀ አልነበረም። በመሆኑ ጥቂትም ቢሆኑ - ክስተቶቹ ሲያጋጥሙ ለተጎጂ ተሳታፊዎች ትርጉም ያለው የስነልቦና እና የህክምና ድጋፍ ማድረግ የሚቻልበት እድል አልተመቻቸም።*

### 4.3.7. ደህንነት

*በተቻለ መጠን ሁሉ የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት የተሳታፊዎችን ደህንነት የሚያረጋግጥ ከአደጋ እና ጉዳት ነፃ በሆነ ከባቢያዊ ሁኔታ መካሄድ አለበት። ተሳታፊዎችን ከተሳትፏቸው ጋር በተያያዘ ሊደርስባቸው ከሚችል ማናቸውም አደጋ፣ ጉዳት ወይም የበቀል እርምጃ የሚጠብቅ መሆን አለበት።*

### 4.3.7.1.የተደረጉ የጥንቃቄ ዝግጅቶች እና መርሀው ተፈፃሚ የሆነበት አግባብ

ከዚህ አንፃር ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ የባለሙያዎች ቡድኑ **አራት ዋና ዋና የጥንቃቄ ዝግጅቶችን** አድርጓል።

**አንደኛ፥** ተሳታፊዎች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ሊደርስባቸው የሚችለውን የደህንነት አደጋ ወይም ተፅእኖ ለማስቀረት ሲባል ሁሉም የተሳታፊ ማረፊያዎች እና የምክክር መድረኮች በመንግስት መዋቅር ባለቤትነት ከሚተዳደሩ ፋሲሊቲዎች ውጭ - በግል ሆቴሎች ውስጥ ብቻ እንዲከናወኑ ተደርጓል።

**ሁለተኛ፥** በሁሉም የምክክር መድረኮች ማናቸውም ዓይነት የፀጥታ ወይም ደህንነት አባል እንዳይኖር ወይም በአካባቢው እንዳይታይ ተገቢ የቅድመ-ዝግጅት ስራዎች ተከናውነዋል። በዚህም ተሳታፊዎች በነፃነት ያለምንም ስጋት የሚወያዩበትን፣ እንዲሁም የሚያቀርቡት ሀሳብ ወይም የሚሰነዝሩት ትችትን በተመለከተ ማናቸውም ሌላ ሶስተኛ ወገን የሚያውቅበትን እድል በማስቀረት - የተሻለ መተማመን እና ምቾት እንዲሰማቸው ማድረግ ተችሏል።

**በሶስተኛ ደረጃ፥** መድረኮቹን ያስተናገዱ ሆቴሎች ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ምቾትና ደህንነታቸውም የተሟላ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ሆቴሎቹ ተጨማሪ የውስጥ ዝግጅት እንዲያካሂዱ ግፊት ለማድረግ ተሞክሯል።

**በሌላ በኩል፥** ተሳታፊዎች ከምክክር ሂደቱ እና ከሽግግር ፍትህ አጠቃላይ መርህ-ግብር ዓላማዎች ጋር በተያያዘ ከሚሰሩ ስራዎች በመነሳት - ያልተገባ ወይም ሊተገበር የማይችል ተስፋ እንዳይሰንቁና ከዚህ ጋር የሚያያዝ የስሜት ጉዳት እንዳይደርስባቸው የጥንቃቄ ስራ ተሰርቷል። በዚህ ረገድ የምክክር መርህ-ግብሮቹን ዓላማ በዝርዝር ከማስረዳት ባለፈ የምክክር ምእራፉ ውስን ዓላማ እንዳለው፣ ሂደቱ ለሁሉም የሀገሪቱ ችግሮች ብቸኛ መልስ የሚሰጥ እንዳልሆነ፣ ወደፊትም በአፈፃፀም ደረጃ የሚነሱ ተግዳሮቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ለተሳታፊዎች ግልፅ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

### 4.3.7.2.ከደህንነት ሁኔታ ጋር በተያያዘ ያጋጠሙ እክሎች

የተሳታፊዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ተገቢ የዝግጅት ስራዎች ቢከናወኑም ውስን ክፍተት አልነበረም ማለት ግን አይቻልም።

**በመጀመሪያ ደረጃ፥** ምንም እንኳ ችግር ስለማጋጠሙ ከተሳታፊዎች የቀረበ ሪፖርት ባይኖርም - ተሳታፊዎች ወደመጡባቸው አካባቢዎች ሲመለሱ ከተሳትፏቸው ጋር በተያያዘ ከማንም ሶስተኛ አካል ሊደርስባቸው የሚችል የትኛውም አይነት አደጋን ከመቀነስ አንፃር የባለሙያዎች ቡድኑ የተዘጋጀበት የተቀናጀ የድህረ-ሁነት የምላሽ ሥርዓት አልነበረም።

**በተጨማሪም፥** ከፀጥታና ደህንነት ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በተያያዘ የተወሰኑ መርህ-ግብሮች እንዲዘገዩ ወይም ወደሌላ ከተማ እንዲዘዋወሩ ተደርጓል። ቢያቤሎ የምክክር ዝግጅቱ ከተጠናቀቀና ተሳታፊዎች፣ የባለሙያ ቡድኑ አባላት እና አስተባባሪዎች ወደቦታው ጉዞ ከጀመሩ በኋላ - በዋዜማው በተፈጠረ የፀጥታ እክል ምክንያት ምክክሩ እንዳይካሄድ ሆኗል። በካማሺ የተሳታፊዎች ልየታ ከተጠናቀቀ በኋላ የፀጥታ ሁኔታው አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ ከዚህ አካባቢ የሚወከሉ ተሳታፊዎች ከአሶሳ አካባቢ ተሳታፊዎች ጋር ባንድነት ምክክሮቹን እንዲያካሂዱ ተደርጓል። በትግራይ ክልል ከጊዜያዊ አስተዳደሩ የሚጠበቁ ድጋፎች እና ዋስትናዎችን አስመልክቶ የሚደረገው ንግግር ረጅም ጊዜ በመውሰዱ - መርህ-ግብሮቹ ሁለት ጊዜ እንዲገፉ ምክንያት ሆኗል። በአማራ ክልል የነበረው የፀጥታ ክፍተት አጠቃላይ የክልሉ መርህ-ግብሮች ሁለት ጊዜ እንዲገፉ፣ እንዲሁም ከነበረው የፀጥታ እና ደህንነት ሁኔታ ዳሰሳ በመነሳት የሁለት ከተሞች መርህ-ግብሮች አስቀድሞ በወጣው ፕሮግራም መሰረት እንዳይካሄዱ አስገድዷል። እንዲሁም በዚሁ ክልል የሶስት ከተሞች መርህ-ግብሮች - በተመሳሳይ ስጋት ምክንያት - ከፍተኛ ወጪ በማውጣት እና አስቀድሞ የተመረጡ ተሳታፊዎችን በማጓጓዝ - መድረኮቹ በሌሎች አጎራባች ከተሞች እንዲካሄዱ ተደርጓል።

በኦሮሚያ ክልል ጅማ ከተማ ምክክሩ እየተካሄደ ባለበት ወቅት ከፀጥታ አካላት በቀረበ ጥያቄ ምክንያት መድረኩ ለጥቂት ደቂቃዎች ከተስተጓጎለ በኋላ እንዲቀጥል ተደርጓል።

በጥቅሉ ሲታይ በውስን መድረኮች ከላይ የተመለከቱ እክሎች ቢያጋጥሙም - እንደየሁኔታው አማራጭ አስቻይ አሰራሮችን ወዲያውኑ በመዘርጋት - በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን - የነዚህ አካባቢዎች ነዋሪዎች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ድምፃቸውን የሚያሰሙበትን እድል ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል። የውስን መድረኮች ተሳታፊዎችን ወደ አጎራባች ከተሞች እንዲጓዙ በማድረግ ምክክሮችን ማካሄድ ከዝግጅት፣ ከወጪ፣ ከጊዜ እና ከምቾት አንፃር የራሱ ችግር ቢኖረውም - መድረኮቹ እንዲቀጥሉ መደረጉ - የተሳታፊዎችን መሠረታዊ የመሳተፍ መብት አላጓደለም። በምክክሮቹ ላይ በተንፀባረቁ ሀሳቦች ይዘት ወይም ጥራት ላይም የተለየ ተፅእኖ አላሳደረም።

### 4.3.8. ግልፀኝነትን ስለማስፈን

የሽግግር ፍትህ ስራ የትኛውም ምዕራፍ ዓላማ፣ ሂደት፣ አሠራር እና ስነ-ዘዴን የሚመለከት መረጃ - ለተሳታፊዎችና ለመላው ህዝብ በግልፅ እና በአግባቡ ማቅረብ ተቀዳሚ ግዴታ ነው። በተጨማሪም በተለይ ተሳታፊዎች - ከሂደቱ ጋር በተያያዘ በሚኖራቸው ተሳትፎ ማዕቀፍ የሚሰጧቸው ሀሳቦች ዓላማ እና ጥቅም፣ እንዲሁም የሚወሰዱ ቀጣይ እርምጃዎችን በተመለከተ - በቀላሉ በሚረዱት ቋንቋ በግልፅ እንዲያውቁት ማድረግ ይገባል። ከምክክሮቹ በፊትም ሆነ በኋላ የሚነሱ ጥያቄዎች ወይም መረጃ የማግኘት ፍላጎቶች ካሉም ለነዚህ ምላሽ የሚሰጥበትን አሰራር መዘርጋት ተገቢ ነው። ከዚህ አኳያ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል።

#### 4.3.8.1. ግልፀኝነትን ለማስፈን የተከናወኑ ዝግጅቶች እና የተፈፀሙ ስራዎች

ከዚህ በመነሳት የባለሙያዎች ቡድኑ ግልፀኝነትን ለማስፈን የሚያግዙ በርካታ ስራዎችን አከናውኗል። በቀዳሚነትም አጠቃላይ የተግባቦት ስራዎቹን ፍሰት የሚገዛ ራሱን የቻለ ሰነድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።[39]

የሰነዱ ዋና ዓላማ የባለሙያዎች ቡድኑ - በቅድመ-ፖሊሲ፣ በፖሊሲ እና በድህረ-ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቶች የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለህዝብ ይፋ የሚያደርግበት፣ በተለይም ስለሽግግር ፍትህ ምንነትና አስፈላጊነት፣ በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ላይ የሚደረግ የህዝብ ምክክር ዓላማ እና አስፈላጊነት፣ ከባለሞያዎችና ከህዝብ ውይይቶች የሚገኙ ግብዓቶች በፖሊሲው ስለሚካተቱበት ሁኔታ፣ እና በዝግጅት ሂደቱ ታሳቢ ሊደረጉ ከሚገባቸው ማናቸውም ጉዳዮች ጋር በተያያዘ - አስፈላጊው መረጃ ወቅቱን ጠብቆ ለህዝብ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በሚዲያ ወይም ሌላ ተመራጭ የመገናኛ ዘዴ የሚደርስበትን አግባብ ማመላከት ነው።

በዚህ መሠረት የባለሙያዎች ቡድኑ አባላት በግል እና በመንግስት ባለቤትነት ከሚተዳደሩ የድምፅ፣ ምስል እና ፅሁፍ ሚዲያ ተቋማት ጋር በመተባበር በርካታ ቃለመጠይቆች እና ማብራሪያዎችን እንዲሰጡ ተደርጓል።

የምክክሮቹ ዋና ዋና የስራ ክፍሎች - ለምሳሌ ክልላዊ የምክክር መርሀ-ግብሮች ሲጠናቀቁ - የምክክር ሂደቶችን አሁናዊ ሁኔታ የተመለከቱ ጋዜጣዊ መግለጫዎች በአማርኛ እና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች እንዲሰጡ አድርጓል።

በተጨማሪም በኢትዮጵያ የሚገኙ የውጭ አገራት ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፣ ዓለም- አቀፍ ተቋማት፣ እና የልማት አጋሮች - በምክክሮቹ ላይ በቀጥታ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ባይሆኑም - በሂደቱ ላይ ትልቅ ሚና ስላላቸው - የባለሙያዎች ቡድኑ በተናጠል እና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር - ተደጋጋሚ መድረኮች እንዲዘጋጁና ስለሂደቶቹ ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ አድርጓል።

---

[39] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ'፡ ጥር 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

**Press Release**

June 25, 2023

**High-level consultative exchanges held on transitional justice with the political leadership and commissioners of the Somali Region Truth and Reconciliation Commission**

**Press Release**

**Conclusion of Public Consultations on Transitional Justice Policy Options in the Oromia Region**

**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**ግንቦት 23 ቀን 2015 ዓ.ም**

**በደቡብ ኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች የሚካሄድ ሀገራዊ የሽግግር ፍትህ የህዝብ ምክክርና ግብአት የማሰባሰብ ስራ መርሀ-ግብር ስለመጀመር**

#### 4.3.8.2.ያጋጠሙ ውስንነቶች

ግልፀኝነትን ለማስፈን በተከናወኑ ዝግጅቶች ማዕቀፍ ትልቁ ተግዳሮት የባለሙያዎች ቡድኑ - በተለይ ከሚዲያ ተቋማት የሚቀርቡ ተከታታይ የመረጃ ፍሰት ጥያቄዎችን ለማርካት የሚያስችል ውስጣዊ አደረጃጀት ያልነበረው መሆኑ ነው። የባለሙያዎቹ ቡድኑ የራሱ የኮሚዩኒኬሽን ባለሙያ የሌለው በመሆኑ - የቡድኑ አባላት ይህን ስራ ያከናወኑት በተደራቢነት ብቻ ነበር። ይህም በአባላቱ ላይ ከፍ ያለ የስራ ጫና ከማሳደሩም በላይ - መረጃ ከሚሹ ተቋማት የሚቀርቡ ያላሰለሱ የፕሮግራም ስራ ጥያቄዎችን በሚፈለገው መጠን ለማስተናገድ አልተቻለም።

በተጨማሪም ስለሽግግር ፍትህ ሂደቱ የሚቀርቡ አንዳንድ የተዛቡ የሚዲያ ዘገባዎችን እና በተለያዩ መድረኮች የሚሰራጩ የግለሰብ ፅሁፎች ወይም ትንተናዎችን ለማስተካከል ወይም በምላሽ ለማረም የሚያስችል ግልፅ ፕሮቶኮል አለመኖር - የተሳሳቱ እና ህዝብን የሚያደናግሩ መረጃዎች ተሰፋፍተው እንዲሰራጩ የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

### 4.3.9. የሕዝብ ምክክር ግብዓቶችን በትክክል ስለመያዝ

በየውይይት መድረኮች የሚሰጡ የህዝብ እይታዎች፣ ሀሳቦች እና ስጋቶች የሽግግር ፍትህ ፖሊሲውን ቅርፅ እና ይዘት በመሠረታዊነት ይወስናሉ። ስለሆነም ህዝቡ እና ባለድርሻ አካላት በፅሁፍ ያቀረቧቸውም ይሁን በየመድረኮቹ የገለጿቸው ሃሳቦች፣ አስተያየቶች እና አቋሞች በትክክል የሚያዙበት እና የሚሰነዱበት አሰራር መመስረት ያስፈልጋል።

#### 4.3.9.1.የተከናወኑ የሰነዳ ሥራዎች

የመረጃ/ግብዓት ሰነዳን በተመለከተ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። የሥራ ሂደቱን በዝርዝር የሚመራ ደረጃውን የጠበቀ ማንዋል አስቀድሞ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። በዚሁ መሰረት ሁሉም የጠዋት መርሀ-ግብር ሂደቶች በቪዲዮ እንዲያዙ፣ እንዲሁም ከሰአት በኋላ በሚውለው መርሀ-ግብር የሚከናወኑ የአራት የትኩረት ቡድኖች ውይይቶች በድምፅ ቅጂ እንዲቀረፁ ተደርጓል።

በተጨማሪም የየዕለቱ ውሎ አጠቃላይ ሪፖርት በዝርዝር ፅሁፍ እንዲቀርብ እና እንዲሰነድ፣ እንዲሁም በመቅረፀ-ድምፅ የተያዙ የውይይት መረጃዎች ሁሉ ለዚሁ ዓላማ በተቀጠሩ ባለሙያዎች ወደ ፅሁፍ እንዲቀየሩ በማድረግ በታሪካዊነት ሊጠቀስ የሚችል ሰፊ የመረጃ አያያዝ እና ሰነዳ ስራ ተሰርቷል።

በመጨረሻም በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተሰበሰበውን የፅሁፍ፣ የድምፅ፣ የምስል እና የቪዲዮ መረጃ ደረጃውን በጠበቀ፣ ሥርዓት ባለው እና ለዘለቄታውም በቀላሉ ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ እንዲደራጅ ከሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒታሪያን ኢኒሼቲቭ ኢቫሉዌሽን ሪሰርች (Evaluation Research | Harvard Humanitarian Initiative) ጋር በተደረሰ ስምምነት መሰረት ሙሉ የሰነዳ እና አርካይቭ ስራ እንዲከናወን ተደርጓል።

#### 4.3.9.2. ሰነዳን በተመለከተ አስተባባሪዎች የነበራቸው ሚና

ተሳታፊዎች የሚሰጧቸው ሀሳቦች በትክክል መያዛቸውን ለማረጋገጥ በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ - አስቀድሞ ስልጠና የተሰጣቸው የዩኒቨርሲቲ አስተባባሪዎችን በመጠቀም - ዝርዝር የእለት ሪፖርቶች በጽሁፍ እንዲዘጋጁ ተደርጓል።

ሪፖርቶቹ የሚያዙበት ደረጃውን የጥበቀ ቴምፕሌት አስቀድሞ ተዘጋጅቷል። ይህ ቴምፕሌት ወጥ በሆነ መንገድ ስራ ላይ እንዲውል በመደረጉ - በጠዋት እና የከሰአት መርሀ-ግብሮች ከተሳታፊዎች የቀረቡ ሀሳቦች፣ ዋና ዋና ማጠቃለያዎች፣ እና የልዩነት ነጥቦች በትክክል የሚያዙበት አሠራር ተፈጥሯል።

በሶስቱም መንገዶች የተያዙ የተሳታፊዎች እና ባለድርሻ አካላት ሀሳቦች (ወደ ፅሁፍ ከተቀየሩ በኋላ) አጠቃላይ መረጃው ሶስት ሳምንታትን በወሰደ ጊዜ በእያንዳንዱ የፖሊሲ ጥያቄ ላይ ሀገራዊ፣ ክልላዊ እና ፆታዊ ስእልን በሚያሳይ እና ለትንተና በሚያመች መልኩ በባለሙያዎች ቡድኑ አባላት እንዲደራጅ ተደርጓል።

### 4.3.10. የሂደቱ ገለልተኝነት፣ ነፃነት እና ተአማኒነት

#### 4.3.10.1. መርህ

የሽግግር ፍትህን የሚመመለክት የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ መርሀ-ግብር ተአማኒ፣ ገለልተኛ እና ነፃ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት። ይህ መርህ ሁለት ገፅታዎች አሉት።

**አንደኛው፥** ስራዎቹ ሁሉ ከውጤቱ ጋር የተገናኘ ልዩ ፖለቲካዊ ወይም ተቋማዊ ጥቅም በማያገኙ ነፃ የባለሙያዎች ስብስብ እንዲመሩ ማድረግን የሚመለከት ነው።

**ሁለተኛው፥** የምክክር መድረኮችን እና ግብዓት ማሰባሰብን የሚመለከቱ ሰነ-ዘዴዎች፣ ሰርአቶች እና ስራዎች ሁሉ ከፖለቲካ ጣልቃ-ገብነት፣ ወገንተኝነት እና የራስ ግላዊ ምልከታዎች ነፃ በሆነ መንገድ መከናወን ያለባቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ፣ የአጠቃላይ ሂደቱን ተአማኒነት የማረጋገጥ አስፈላጊነትን የሚመሰርት መርህ ነው።

#### 4.3.10.2. ገለልተኝነት፣ ነፃነት እና ተአማኒነትን ለማረጋገጥ የተከወኑ ስራዎች

የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን - ሀላፊነቱን ከወሰደበት ከህዳር 2015 ዓ.ም ጀምሮ - የምክክር እና ግብዓት ማሰበባሰብ ሂደቱን በገለልተኝነት፣ ነፃነት እና ተአማኒነት ለማከናወን እንዲቻል በርካታ ዝግጅቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ተግባራዊ አድርጓል። በዚህ ረገድ የሚጠቀሰው ዋና ስራ - እያንዳንዱን የስራ ሂደት ሥርዓት ባለው

እና ተገማች በሆነ አሠራር መምራት የሚያስችል ዝርዝር ማንዋል አስቀድሞ ማዘጋጀቱ ነው፡፡[40] ይህ ዝግጅት በዘፈቀዳዊ እና የግል አስተሳሰብ የሚመራ አሠራር ወይም ሂደት እንዳይኖር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

በዝርዝር ሲታይ ለእያንዳንዱ የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ መድረክ የሚጋበዙ ሰዎች ልየታ እና አመራረጥ፣ የሚመረጡ የማህበረሰብ ክፍሎች አይነት፣ የሚመረጡበት መመዘኛ፣ የተሳታፊዎች ብዛት፣ መድረኮች የሚዘጋጁበት፡ የእለት ውሎ ሪፖርቶች እና የተቀረፁ የቪዲዮ እና የድምፅ ማስረጃዎች የሚተረጎሙበትና የሚደራጁበት፡ የተገኙ ግብዓቶች የሚተነተኑበት፣ እንዲሁም የተሳታፊ ማህበረሰቡ ድምር ሀገራዊ እይታ የሚሳልበትን መንገድ የሚመሩ ግልፅ መርሆዎች እና አሠራሮች አስቀድመው እንዲቀረፁ እና ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ በዚህም ሂደቱ ከስሜትና ግላዊ ፍላጎት ወይም ተቋማዊ ተፅእኖ ነፃ በሆነ አግባብ - ደረጃውን እና ገለልተኝነቱን በጠበቀ አውድ እንዲካሄድ በማድረግ - የተሳታፊዎችን እና ባለድርሻ አካላትን ትክክለኛ ድምፅ እና እይታ የሚያንፀባርቅ የግኝት ሪፖርት እንዲወጣ እገዛ አድርጓል፡፡

በዚህ ረገድ የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን ነፃ፣ ገለልተኛ እና ሙያዊ ብቃት ባላቸው የሽግግር ፍትህ እና የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች እንዲካተቱበት መደረጉ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ የባለሙያዎች ቡድኑ 13 አባላት ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከሕግ ሙያ ዘርፍ፣ ከተ.መ.ድ የተለያዩ ፅህፈት ቤቶች፣ ከሰብአዊ መብት ተጣባቂዎች፣ ከግል አማካሪዎች እና የፖሊሲ ማርቀቅ ባለሙያዎች የተውጣጡ መሆን - የግብዓት ማሰባሰቢያ የምክክር ሂደቱ በፍፁም ነፃነት፣ ሙያዊ ሀላፊነት፣ ገለልተኝነት እና ተአማኒነትን የሚካሄድበትን ተጨባጭ እድል ፈጥሯል፡፡

### 4.3.10.3. ሂደቱ ከፖለቲካ ጣልቃገብነት የተጠበቀበት ሁኔታ

መንግስት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ባለቤት እና ዋና ፈፃሚ መሆኑ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ ሆኖም ለባለሙያዎች ቡድኑ በተሰጠው የምክክር፣ ግብዓት ማሰባሰብ እና ፖሊሲ የማርቀቅ ስራ ሂደት ስልጣን እና ሀላፊነት ማዕቀፍ - መንግስት የሚታየው እንደ አንድ ጉልህ ባለድርሻ አካል ነው፡፡ የባለሙያዎች ቡድኑ ከመንግስት መዋቅር በተለይም ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር የነበረው የስራ ግንኙነት - ይህን መሰረታዊ ምልከታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተፈፀመ ነው፡፡ ይህን አቋም የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድኑ ከመጀመሪያው ቀን አንስቶ ግልፅ ያደረገው ሀሳብ ሲሆን - የፍትህ ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራርም ሙያዊ ስምሪቱ በዚህ እሳቤ እንዲመራ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል፡፡

በመሆኑም የባለሙያዎች ቡድኑ የቅድመ-ዝግጅት እና የትግበራ ስራዎች ሁሉ በዚህ መሰረት የተከናወኑ ሲሆን - በምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ የመንግስት መዋቅር ከባለሙያዎች ቡድኑ ስራ ርቀቱን በመጠበቅ - በየትኛውም የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ምዕራፍ ላይ በማናቸውም መልኩ የሚገለፅ ፖለቲካዊ ወይም ሙያዊ ጣልቃገብነት ሳይኖር አጠቃላይ ሂደቱ እንዲጠናቀቅ ሆኗል፡፡

እንዲያም ሆኖ የባለሙያዎች ቡድኑ ሂደቱን በፍፁም ነፃነት፣ ሙያዊ ሀላፊነት፣ ገለልተኝነት እና ተአማኒነትን ለማከናወን የሄደበት ርቀት እና ተግባራዊ ያደረጋቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ - ከጥቂት የሚዲያ ተቋማት እና ግለሰቦች ከሂደቱ ዓላማም ሆነ ከባለሙያዎቹ ነፃነት ጋር በተያያዘ የተሰነዘሩ ትችቶች ወይም የጥርጣሬ ሀሳቦች የሉም ማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡

### 4.3.11. የሀገር መሪነት/የሕዝብ ባለቤትነት መርህ ተፈፃሚ የሆነበት አግባብ

---

[40] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት የባለሙያዎች ቡድን አባላት የአሰራር እና የስነ-ምግባር መመሪያ'፣ ጥር 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ

ማናቸውም የሽግግር ፍትህን የሚመለከት ስራ ወይም በዚህ ረገድ የሚወሰድ የአካሄድ ውሳኔ በሀገሩ መንግስት፣ ሕዝብ እና ቀጥተኛ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት፣ ሀላፊነት፣ ባለቤትነትና ውሳኔ የሚመራ መሆን አለበት።

#### 4.3.11.1. የመርሁ አፈፃፀም

በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህን የተመለከቱ ስራዎች በሀገር መሪነት/ሕዝብ ባለቤትነት መርህ ላይ በመመርኮዝ የማከናወን አስፈላጊነትን በማስረገጥ - ሁሉም የምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደትን የሚመለከቱ እቅዶች፣ ትግበራዎች እና የክትትል ስራዎች በዚህ እሳቤ እንዲከናወኑ ተደርጓል። በተለይም ሀገራዊ ባለቤትነትን ከማረጋገጥ አንፃር በምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ የዝግጅት እና ትግበራ ምዕራፍ ላይ - ሂደቱ ከኢትዮጵያውያን ፍላጎት፣ ተስፋ እና የጋራ ትልም ጋር የተንሰላሰለ፣ ለሀገራዊ አውዱ የተስማማ፣ እንዲሁም አግባብነት ያላቸው የዓለም-አቀፍ መርሆዎችን ያከበረ እንዲሆን ከፍ ያለ ጥረት ተደርጓል። በህዝባዊነቱ ያልተለመደ የፖሊሲ አቀራረፅ አካሄድን በመከተል - የምክክር መድረኮቹ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ሁሉንም ክልሎችና በርካታ ባለድርሻ አካላትን እንዲያሳትፉ ተደርጓል። በዚህም በሂደቱ አንፃር የህዝብ ድጋፍ እና ባለቤትነት ስሜትን ለማስፋት ተሞክሯል።

በሽግግር ፍትህ ዓላማ፣ ግቦች እና አጠቃላይ ሀገራዊ የፖለቲካ ኡደቶች አንፃር የተለያየ፡ አንዳንዴም የተቃረነ ምልከታ ያላቸው ሰዎችን፣ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ በግጭቶች አውድ ያለፉ ማህበረሰቦች እና ተጎጂ ሰዎችን በሂደቶቹ ተሳትፎ እና ድምፅ እንዲኖራቸው ተደርጓል። በዚህ ረገድ በሶማሌ ብሄራዊ ክልል የነበረውን ከባድ ግጭት እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ታሪክ ላይ ተመስርቶ ከተቋቋመው ክልል-አቀፍ የምርመራ፣ እርቅና ካሳ ኮሚሽን[41] ኮሚሽነሮችንና የክልሉ ከፍተኛ አመራር ጋር ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም በጅግጅጋ የውይይት መድረክ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። በዚህም በክልሉ የተጀመሩ የሽግግር ፍትህ ትልሞች እና የትግበራ ሥራዎች ምን መልክ እንዳላቸው ለመረዳት፣ ከሀገር-አቀፉ ሂደት ጋር እንዴት እንደሚጣጣም፣ እና ክልሉ በዚህ ረገድ ያንፀባረቀው ልዩ ፍላጎትና ተስፋ በሀገራዊ የሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ እንዴት ማስተናገድ እንደሚቻል ጥቅል ምክክር ተካሂዷል።

በተመሳሳይ በትግራይ ክልል የሽግግር ፍትህ ህዝባዊ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሥራዎች ያለ እንከን ማከናወን የሚቻልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ አልፎም ክልሉ በሽግግር ፍትህ ስራው ሀገራዊ ጥቅም እና አስፈላጊነት ላይ መሰረታዊ ልዩነት ባይኖረውም - ከሽግግር ፍትህ ሂደት እና አደረጃጀት ጋር በተያያዘ ስጋት፣ ቅሬታ እና የራሱ ሀሳብ ያለው መሆኑን ጠቅሶ - በነዚህ ነጥቦች ዙሪያ 'ከፌዴራል መንግስቱ ከፍተኛ አመራር ጋር ጥልቀት ያለውና ግልጽ መፍትሄዎችን ማስቀመጥ የሚያስችል የሁለትዮሽ ውይይት' የሚካሄድበት ሁኔታ እንዲመቻች ባቀረበው ጥያቄ መሰረት - የክልሉ አስተዳደርን ድምፅ ለመረዳት የሚያስችሉ ተከታታይ መድረኮች ተዘጋጅተዋል። በመሆኑም ሚያዝያ 2015 ዓ.ም በመቀሌ ከተማ፣ እንዲሁም መስከረም 25 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ከትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ከፍተኛ አመራሮች ጋር ዝርዝር ውይይት ተካሂዷል። በተጨማሪም በባለሙያዎች ቡድኑ እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ትብብር በተዘጋጀ መድረክ - በክልሉ ከሚገኙ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባላት ጋር ሐምሌ 22 ቀን 2015 ዓ.ም በመቀሌ ከተማ የደዘተ ውይይት ተካሂዷል። በመጨረሻም ክልሉ ከግጭት አዙሪት ገና እየወጣ ያለ እንደመሆኑ መጠን - በአምስት ከተሞች ከተደረጉ የህዝብ የምክክር መድረኮች በተጨማሪ - የክልሉን ድምፅ በበቂ ሁኔታ ለመረዳት እና በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይም የራሱን አሻራ ማሳደር እንዲችል - ያለውን የውስጥ አቅም በማደራጀት በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ላይ የተመለከቱትን ሀሳቦች የሚተች ወይም አማራጭ ሀሳቦችን በቴክኒካል ደረጃ ዘርዝሮ የሚያቀርብ ሰነድ በማዘጋጀት እንዲያቀርብ እና በተሻለ የባለቤትነት ስሜት በሂደቱ ላይ እንዲሳተፍ መግባባት ላይ ተደርሷል። ሆኖም ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ የታሰበው ቴክኒካል ሰነድ ለባለሙያዎች ቡድኑ አልቀረበም።

---

[41] Somali National Regional State. Commission for Investigation of Violence, Reconciliation and Reparation of Victims in the Somali Region (TRC)). Proclamation No.205/2021

በአጠቃላይ ይህ ሂደት የሽግግር ፍትህ ሥራ በህዝብ ባለቤትነት መርህ ላይ መዋቀር እንዳለበት፣ ለዚህም በፖለቲካው አውድ የተለያየ ድምፅ ወይም አቋም ያላቸውን ሀይሎች ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ እንደሚገባ የሚያስገነዝበውን መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የተሄደውን ርቀት የሚያሳይ ነው።

### 4.3.11.2. የአጋር አካላት ተሳትፎ እና ትብብር

የሽግግር ፍትህ ማናቸውም ምዕራፍ ስራ ወይም አካሄድ በሀገር እና ሕዝብ ፍላጎት፣ ሀላፊነት፣ ባለቤትነትና ውሳኔ የሚመራ መሆን አለበት ሲባል ሌሎች አካላት ምንም ሚና አይኖራቸውም ማለት አይደለም። በርግጥም የሽግግር ፍትህ ማናቸውም ምዕራፍ ስራ - ከሀገር እና ሕዝብ ባሻገር - ከበርካታ ባለድርሻ አጋር ድርጅቶች፣ ዓለም-አቀፍ ተቋማት እና ሀገራት ጋር ጥልቅ ትብብር ማድረግን የሚጠይቅ ነው።

በዚህ ረገድ የሚጠበቁ ስራዎችን በግልፅ አሰራር ላይ ተመስርቶ ከማከናወን አንፃር - የባለሙያዎች ቡድኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚመራ ማንዋል አዘጋጅቷል።[42] ማንዋሉን መሰረት በማድረግ ቡድኑ - በተለይ ከአፍሪካ ህብረት፣ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ ከተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ኮንሶርቲየም፣ ከአሜሪካን ኢምባሲ፣ ከአሜሪካ ዓለም-አቀፍ የልማት ኤጀንሲ፣ ከጀርመን ተራድኦ ድርጅት፣ እና ከተለያዩ የተ.መ.ድ ፅህፈት ቤቶች ጋር ጥልቅ፣ ተከታታይ እና ባለ ብዙ ማዕቀፍ ግንኙነቶችና የትብብር ስራዎችን አከናውኗል።

በነዚህ የትብብር ማእቀፎች አማካኝነትም የምክክር እና ግብዓት የማሰባሰብ ሂደቱ ከተለያዩ አጋር ተቋማት ውስን የፋይናንስ እና የቴክኒካል ድጋፍ አግኝቷል። እገዛዎቹ በተሳታፊዎች ልየታ እና መረጣ ሂደት የመሳተፍ፣ የቴክኒካል ትብብር ድጋፍ፣ ማህበረሰብን የማንቃት፣ የምክክር እና ግብዓት ማሰባበሰብ ሂደትን የሚገዙ ማንዋሎችን ይዘት የመገምገም እና ምክረ-ሀሳብ የማጋራት፣ የምክክር መድረኮችን የመታዘብ፣ እና ሀብት የማሰባሰብ ስራዎችን የማገዝ ተግባራትን ያካተቱ ናቸው። እነዚህ ትብብሮች - የባለሙያዎች ቡድኑን ነፃነት ሳይጋፉ - የሀገር/የህዝብ ባለቤትነት፣ መሪነት እና ወሳኝነት መርሆዎችን ባከበሩ መልኩ ተከናውነዋል።

### 4.3.11.3. የምክክር ሂደቶቹን የተከታተሉ አካላት እና የቀረቡ ምልከታዎች

ከላይ በተጠቀሰው የትብብር ማዕቀፍ - የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት፣ የአሜሪካ ኤምባሲ፣ እና የጀርመን ተራድኦ ድርጅት በክልል ደረጃ ከተካሄዱ የምክክር መድረኮች በተወሰኑት ላይ በአካል በመገኘት የሞኒተሪንግ እና የመታዘብ ስራዎችን አከናውነዋል።

ቢያንስ ሁለት ተቋማት - ማለትም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት - በሁሉም ክልሎች ሀያ ሶስት የምክክር መድረኮች ላይ ባለሙያዎችን በመላክ የሞኒተሪንግ ስራዎችን ሰርተዋል። በሁለት ዙር በጋራ ያዘጋጁት የመድረኮቹ ዝግጅት እና ሂደት የግምገማ ሪፖርቶችንም ለባለሙያዎች ቡድኑ አቅርበዋል። የምክክር ስራዎችን ቀጣይ ሂደት ለማሻሻል የሚያግዙ በርካታ ጠቃሚ ምክረ-ሀሳቦችን በመስጠት ተቋማቱ ስትራቴጂክ አጋርነታቸውን አሳይተዋል።

በተጨማሪም ሁለቱም ተቋማት ከጅምሩ የባለሙያዎች ቡድኑ ባዘጋጀው የምክክር እና ግብዓት ማሰባበሰብ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ ላይ ዝርዝር ምልከታቸውን በፅሁፍ አጋርተዋል። ይህም የሰነዱን ይዘት በማዳበር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

---

[42] የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን፡ 'በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የአጋር አካላት ተሳትፎ ማንዋል'፣ ጥር 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

## ክፍል አምስት

## ከህዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰበባሰብ ሂደቶች የተገኙ ግብአቶች የተሰበሰቡበት፣ የተደራጁበት እና የተተነተኑበት ሥነ ዘዴ

### 5.1. ከምክክር መድረኮችና ከባለድርሻ አካላት ግብዓት የተሰበሰበበት ስነ-ዘዴ

**ዓይነታዊ የጥናት ስነ-ዘዴ**

በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ላይ በሀገርአቀፍ ደረጃ በተደረጉ የምክክር መድረኮች ግብዓት ለማሰባሰብ የተመረጠው የጥናት ሥነዘዴ 'ዓይነታዊ ዘዴ' (Qualitative Method) ነው። በዚህ መሰረት ዝርዝር ግብዓቶችን ለማሰባሰብ እንዲቻል በዋናነት 'የትኩረት ቡድን ውይይት' (Focus Group Discussion) ስልት ተግባራዊ ተደርጓል።

ለዚህ ስራ ሀገራዊ ውጥን አላማ ዓይነታዊ የጥናት ሥነዘዴ የተመረጠበት ዋናው ምክንያት በቀረቡት የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ የሁሉንም ተሳታፊዎች አስተሳሰብ፣ እይታ እና ፍላጎት በጥልቀት ለመረዳት የሚያስችል የጥናት ዘዴ በመሆኑ ነው። በዚህ ሥነዘዴ ማእቀፍ በተለይ ከትኩረት ቡድኖች ውይይት የሚገኝ ግብዓት - በሽግግር ፍትህ ጉዳዮች ዙሪያ የተሳታፊ ማህበረሰቡን አመለካከት እና ተስፋ በዝርዝር በመገንዘብ ለፖሊሲ ቀረፃው ስራ እና ይዘት አስፈላጊው መረጃ የተገኘበት መንገድ ነው።

**በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ ግብዓት ለማሰባሰብ ተግባራዊ የተደረጉ ስልቶች**

የግብዓት አሰባሰብ ስልቱ በዋናነት ሶስት መንገዶችን የተከተለ ነው። እነዚህም በፕሌናሪ መድረኮች ላይ ተሳታፊዎች ጥቅል ሀሳቦችን እንዲሰጡ በማስቻል የሚገኙ ግብዓቶች፣ በትኩረት ቡድኖች ውይይቶች ላይ ተሳታፊዎች በሁሉም የፖሊሲ አማራጮች ላይ በዝርዝር የሚያቀርቡት ምልከታ፣ እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚያጋሯቸው የፅሁፍ አስተያየቶች ናቸው።

**የመጀመሪያውን ስልት በተመለከተ፣** በባለሙያዎች ቡድኑ በተዘጋጁ በእያንዳንዳቸው የምክክር መድረኮች ላይ በአማካይ 60 ተሳታፊዎች እንዲገኙ ተደርጓል። በእያንዳንዱ የግብዓት ማሰባሰቢያ ፕሌናሪ መድረክ ላይ ተሳታፊዎች ከሚቀርቡላቸው የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ጥቅል ገለፃ በመነሳት ክፈት ያሉ ውይይቶች የሚያደርጉበት እድል ተመቻችቷል። እነዚህ የጠዋት (ግማሽ) ቀን መርሀ-ግብሮች በዋናነት ተሳታፊዎች ግልጽ እና ተቀራራቢ ግንዛቤ ኖሯቸው በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውይይት እንዲያደርጉና ውስን ግብዓት እንዲሰጡ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው።

በመድረኮቹ ተሳታፊዎች ቅርፅ ወደያዘ ዝርዝር የፖሊሲ አማራጮች ውይይት መግባት ሳያስፈልጋቸው በሽግግር ፍትህ ላይ ያላቸውን አጠቃላይ እይታ፣ ተስፋ፣ ስጋት እና ጥያቄ አንስተዋል።

**በሌላ በኩል የትኩረት ቡድኖችን መሠረት ያደረገው ሁለተኛው የግብዓት ማሰባበሰብ ስልት** - በባለሙያዎች ቡድኑ (ብቻ) በተዘጋጁ ሁሉም መድረኮች ላይ ተሳታፊዎችን በአራት የተለያዩ የትኩረት ውይይት ቡድኖች ማለትም 'የሴት የሰብዓዊ  መብት ጥሰት ተጎጂዎች'፣ 'የወንድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች'፣ 'የቅልቅል የህብረተሰብ ክፍል ቡድኖች' እና 'የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን (አስተባባሪዎች) ቡድን' በመከፋፈል  የቡድን ውይይቶች እንዲካሄዱ ተደርጓል።

የትኩረት ቡድኖቹ አወቃቀር ተቀራራቢ አመለካከት፣ ፍላጎት ወይም የመብት ጥሰት የኋላ ታሪክ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን በአንድ ስብስብ ስር በማምጣት ምልከታቸውን ከራሳቸው እና ከማህበረሰባቸው ልዩ

ሁኔታዎች ጋር እያንሰላሰሉ በጥልቀት እና በነፃነት እንዲያቀርቡ እድል ሰጥቷል። ፍላጎታቸውን በተሻለ ትኩረት ለመረዳት ከማስቻሉም በላይ ሂደቱንም ተጎጂ እና ሥርዓት-ጾታ ተኮር እንዲሆን አድርጎታል።

በአጠቃላይ በእነዚህ የምክክር መድረኮች ማእቀፍ በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ ዝርዝር ግብዓቶችን የሚሰጡ 216 የትኩረት ውይይት ቡድኖች ተደራጅተዋል።

የዚህ ስልት ትግበራ አንዱ ክፍል - የትኩረት ቡድን ውይይቶች የሚመሩበትን ግልፅ ፕሮቶኮል ማዘጋጀት ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከተው ለዚህ ዓላማ ሲባል የትኩረት ቡድን ተሳታፊዎች ልየታ መስፈርት፣ እንዲሁም የተሳታፊዎችን ስም፣ ጾታ እና እድሜ ዝርዝር መረጃ የሚይዝ ቅጽ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። በተጨማሪም ፕሮቶኮሉ የትኩረት ቡድኖች ውይይት አስተባባሪዎች እና ቃለጉባኤ ያዞችን ሚና፣ የመወያያ ጥያቄዎች ለተሳታፊዎች ግልጽ የማድረግ ስራ ሂደትን፣ ተሳታፊዎች የሚሰጧቸው ሀሳቦች አመዘጋገብ እና የቃለጉባኤ አያያዝን፣ እና የተሳታፊዎችን ነጻ ውይይት ለማሳለጥ የሚያግዙ አሰራሮችን እንዲሸፍን ሆኖ ተዘጋጅቷል። ይህ የዝግጅት ሂደቱ ንዑስ ክፍል መድረኮቹን በአግባቡ እና ወጥ በሆነ መንገድ ለመምራት፣ እንዲሁም ለተሳታፊዎች እና ለትኩረት ቡድን አስተባባሪዎች ግልጽ አካሄድ በመፍጠር የሽግግር ፍትህ ግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ ደረጃውን የጠበቀ ሆኖ እንዲጠናቀቅ አስችሏል።

የትኩረት ቡድኖች ውይይቶች አስቀድመው ለዚሁ አላማ በተዘጋጁ የፖሊሲ አማራጭ የመወያያ ጥያቄዎች መሰረት ተከናውነዋል።

በውይይት መድረኮች ላይ በተነሱ ሃሳቦች፣ አስተያቶች እና የመወያያ ጥያቄዎች ላይ የተሰጡ ዝርዝር ምላሾች በቃለ-ጉባኤ እንዲያዙ፣ እንዲሁም በተሳታፊዎች ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ በመመስረት ውይይቶች በመቅረጸ-ድምጽ እንዲቀረጹ ተደርጓል። በድምጽ ቅጂ የተያዙ መረጃዎችም ወደ ፅሁፍ እንዲቀየሩ በማድረግ የተወያዮቹ ሀሳብ ይዘቱ ሳይቀያየርና ሳይበረዝ እንዲደራጅ ተደርጓል።

የውይይት ሂደቱን በተመለከተ በእያንዳንዱ የትኩረት ቡድኖች ውይይት ላይ አንድ አወያይ፣ እንዲሁም ከተሳታፊዎች የሚሰጡ አስተያየቶችን የሚይዝ አንድ ፀሀፊ በመመደብ ሃሳቦችና አስተያየቶች ሁሉ በትክክል እና በተሟላ ሁኔታ እንዲያዙ ለማድረግ ተሞክሯል።

ከትኩረት ቡድን ውይይቶች አካሄድ አንፃር ስንመለከት - በእያንዳንዱ የፖሊሲ ጥያቄ ላይ ተሳታፊዎች በንፅፅር ባልተገደበ ሁኔታ አስተያየታቸውን መስጠት የሚችሉበት የጊዜ አመዳደብ ስልት ተግባራዊ ተደርጓል። በብዙዎቹ መድረኮች ላይ የፖሊሲ አማራጮችን በያዙ ጥያቄዎች ላይ ውይይቶች ሙሉ ለሙሉ ከተጠናቀቁ በኋላ ተሳታፊዎች ድምጽ በመስጠት አቋማቸውን ከነምክንያቱ እንዲያሳውቁ እድል ተሰጥቷቸዋል። በአብላጫ የተሰጠ ድምጽ፣ አነስተኛ ድምጽ፣ እና የተለዩ ሀሳቦች (አዲስ አማራጮች) በቡድን ጸሐፊው አማካኝነት በማስታወሻ ተመዝግበዋል።

ለእያንዳንዱ የትኩረት ቡድን ውይይት የተመደበ ፀሐፊ ውይይቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በጽሁፍ የያዘውን ሪፖርት - አስቀድሞ በተዘጋጀው የቡድን ውይይት ሪፖርት ማድረጊያ ቅፅ ላይ በመሙላት ፅሁፉን አጠናቅሮ ለባለሙያዎች ቡድኑ እንዲልክ ተደርጓል።

በሁሉም የፕሌናሪ እና የትኩረት ቡድኖች ውይይቶች ላይ መቅረጸ-ምስል እና መቅረጸ-ድምጽ በመጠቀም መረጃ ተይዟል። ይህ የተደረገበት ዋናው ምክንያት በማስታወሻ ያዥ የሚጠናቀር የውይይት ሪፖርት ሁሉንም ሀሳብ በተሟላ ሁኔታ ይዞ በማይገኝበት ጊዜ ወይም ጥርጣሬን የሚያጭር ሁኔታ ቢፈጠር ትክክለኛውን የተሳታፊ ሃሳብ ወይም አስተያየት ከመቅረጸ-ድምጽ በመስማት ማረጋገጥ እንዲቻል ነው። ተሳታፊዎች የሚሰጡት አስተያየት በመቅረጸ-ድምጽ ከመያዙ አስቀድሞ የድምጽ ቀረፃውን ዓላማ በማስረዳት እና የተሳታፊዎችን ፍላጎት በመጠየቅ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ቀረፃ እንዲከናወን ተደርጓል።

**ሶስተኛው የግብዓት አሰባሰብ ስልት፥** በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ላይ በፍትሕ ሚኒስቴር የማህበራዊ ትስስር ገጽ፣ በባለሙያዎች ቡድኑ የኢሜይል አድራሻ እና በባለሙያዎች ቡድኑ አባላት የግል ኢሜይል አድራሻዎች አማካኝነት ከግለሰቦች እና ከተቋማት የተላኩ ግብዓቶችን የሚመለከት ነው። በዚህ ስልትም ከበርካታ ባለድርሻ አካላት የፅሁፍ አስተያየቶችን ማሰባሰብ ተችሏል።

## 5.2. ከምክክር መድረኮች እና ባለድርሻ አካላት የተገኙ ግብዓቶች የተደራጁበት ስነ-ዘዴ

*የባለሙያዎች ቡድኑ ተግባራዊ ያደረገው የመረጃ አደረጃጀት ሥርዓት የዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሆዎችን መሠረት ያደረገ ነው። ስርአቱ በተለይ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት - በሽግግር ፍትህ ምክክር መድረኮች ዝግጅት ማእቀፍ - የመረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት እና ሪፖርት አፃፃፍን አስመልክቶ የሰጠውን የአሠራር መመሪያ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው።[43] የባለሙያዎች ቡድኑ ተግባራዊ ያደረገው ሂደት የተሳታፊዎችን ምልከታ እንደ ወረደ ሙሉ ይዘቱን ጠብቆ ማደራጀትን ዓላማ ያደረገ ነው።*

*በዚህ መሠረት በሁሉም የምክክር መድረኮች[44] በቃለ ጉባኤ አማካኝነት፣ ወይም በድምጽ ቅጂ እና በትራንስክሪፕሽን የተሰበሰቡ ግብዓቶች፣ እንዲሁም ከውስን ባለድርሻ አካላት በፅሁፍ የቀረቡ መረጃዎችን - በተገቢ መንገድ ከማደራጀት እና በሥርዓት ከመለየት አንፃር -* ***በሶስት ደረጃዎች የተከፈሉ ስራዎች*** *ተከናውነዋል።*

***የመረጃ ማደራጀት ሂደቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ ስራ፥*** *በሁሉም የውይይት መድረኮች በተካሄዱ የትኩረት ቡድን ውይይቶች የተሰጡ ግብዓቶችን በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት ማደራጀትን የሚመለከት ነው። ቅፁ በምክክር መድረኮች በወጥነት የተዋቀሩትን አራቱን የትኩረት ቡድኖች (ተጎጂ ሴቶች፡ ተጎጂ ወንዶች፡ ቅልቅል፡ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን) አባላትን ብዛት፣ በእንያዳንዱ የፖሊሲ አማራጮች ላይ የተሰጡ ዝርዝር አስተያየቶችን፣ የተነሱ የልዩነት ሃሳቦችን፣ የቀረቡ ተጨማሪ ምክረ-ሀሳቦች፣ በእያንዳንዱ አማራጭ ላይ በተሳታፊዎች የተሰጠው ድምጽ ብዛት፣ መረጃው የተገኘበት ምንጭ፣ እና በልዩነት የተነሳ የተለየ ምልከታ (ለምሳሌ ከሥርዓተ-ጾታ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ከህጻናት ተሳታፊዎች አንፃር) በሚያሳይ መልኩ የተዘጋጀ ነው።*

*ይህ የመረጃ አደረጃጀት ዘዴ - ግብዓቶች በተሰጡበት አንድ ልዩ ስፍራ ወይም ምክክሮች በተከናወኑበት ክልል ልክ እንዲደራጅ ያስቻለ ሲሆን በብዙሃኑ ተሳታፊዎች የተደገፈም ይሁን በጥቂቶች የተነሳ ሃሳብ ሳይጨመቅ ከነዝርዝር ምክንያቱ በተገቢ ሁኔታ ለመሰነድ አግዟል። በዚህ ረገድ ይህ ዘዴ ተሳታፊዎች አንድን የፖሊሲ አማራጭ ከደገፉበት ጀርባ ባለው ምክንያት ላይ በማተኮር የየራሳቸውን እይታ፣ ስጋት እና ፍላጎት በአግባቡ ለመለየትና ለመሰነድ አስችሏል።*

***የመረጃ ማደራጀት ሂደቱ ሁለተኛ ምዕራፍ፥*** *ከላይ የተመለከተውን የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ መሠረት የሚያደርግ ሲሆን - ዓላማውም 'በክልል ደረጃ በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ በተሳተፉ አራት የትኩረት ቡድኖች'፡ 'ከተመረጡ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር በተከናወኑ የምክክር መድረኮች እና የፅሁፍ ምልከታዎች'፡ እንዲሁም 'ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በተካሄዱ የምክክር መድረኮች' የተሰጡ ሃሳቦችን በየፈርጃቸው* ***አጠቃሎ ማስቀመጥ*** *ነው።*

*በዚህ መሠረት ከሶስቱም የምክክር እና ግብአት ማሰባሰብ ምንጮች የተገኙ ሀሳቦች ሳይደበላለቁ - 'የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች'፡ 'የወንድ ተጎጂዎች ቡድኖች'፡ 'የቅልቅል ቡድኖች'፡ 'የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች'፡ 'ከተመረጡ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር በተከናወኑ መድረኮች የተሳተፉ ቡድኖች' (እና በፅሁፍ የቀረቡ አስተያየቶች)፡ እና 'ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በተካሄዱ የምክክር መድረኮች የተሳተፉ ቡድኖች*

[43] The United Nations Security Council. 'The Rule of Law and Transitional Justice in Conflict and Post-conflict Societies'. Report of the Secretary-General. S/2004/616. 2004.

[44] *ይህ አገላለፅ በክልሎች እና ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች የተደረጉ ምክክሮችን፣ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ከተመረጡ ባለድርሻ አካላት ጋር የተከናወኑ ምክክሮችን፣ እንዲሁም ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በቅንጅት የተካሄዱ የምክክር መድረኮችን ይመለከታል።*

(ወይም ሰዎች)' ተብለው እንዲለዩ በማድረግ - ቡድኖቹ በእያንዳንዱ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጭ ላይ ያቀረቡት ሀሳብ ተጠቃሎ በየፈርጆቹ እንዲደራጁ ተደርጓል። በተጨማሪም ከትኩረት ውይይት ቡድኖች የተሰበሰቡ ግብዓቶች በክልል ደረጃ በወጥነት ተደራጅተዋል።

በተመሳሳይ በልዩነት የተነሱ የየቡድኖቹ ሃሳቦችም በዚሁ አግባብ እንዲደራጁ ተደርጓል። በዚህም - ለአብነት በአንድ ክልል የተለያዩ ከተሞች በትኩረት ውይይት መድረኮች ላይ የተሳተፉ 'ሴት ተጎጂዎች' የሰጡትን ግብዓት ለይቶ በማሰናዳት - በእያንዳንዱ ክልል ደረጃ 'ሴት ተጎጂዎች' በአንድ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጭ ጥያቄ ላይ ምን አቋም አንጸባረቁ የሚለውን ለማዘጋጀትና በግልጽ ለማመልከት ተችሏል። በሌላ አነጋገር የሁሉም ቡድኖች ሃሳብ እርስ በርሱ ሳይቀላቀል በፖሊሲ አማራጭ ጥያቄዎቹ ላይ - 'የየትኩረት ቡድኖቹን ክልል-አቀፍ እይታን' ለማግኘት ተችሏል።

***የመረጃ ማደራጀት ሂደቱ ሶስተኛ ደረጃ ስራ፥*** *በሁለተኛው ምእራፍ የተሰነደውን ግብዓት መሰረት ያደረገ ነው። ዓላማውም በክልልና በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ - እያንዳንዱን የትኩረት ውይይት ቡድን እና ከላይ የተመለከቱ ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ማዕከል በማድረግ የተሰነደውን ግብዓት በሶስት መስመሮች ወደ፡*

(ሀ) 'ሀገር-አቀፍ የየቡድኖች'/'ሀገር-አቀፍ የአራቱም ቡድኖች' የጋራ ምልከታ፣

(ለ) ከተመረጡ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር በተከናወኑ መድረኮች የተሳተፉ ሰዎች (እና በፅሁፍ የቀረቡ አስተያየቶች) የጋራ ምልከታ፣ እና

(ሐ) ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በተካሄዱ የምክክር መድረኮች የተሳተፉ ሰዎች የጋራ ምልከታ መቀየር ነው።

በመሆኑም በዚህ ሂደት - ለምሳሌ በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የትኩረት ውይይት ቡድኖች የሰጡትን ግብዓት በመቀየጥ፣ በሀገር-አቀፍ ደረጃ እያንዳንዱ የትኩረት ውይይት ቡድን በእያንዳንዱ የፖሊሲ አማራጭ ሀሳብ ላይ የያዘውን አቋም ከነምክንያቱ እንዲደራጅ ተደርጓል። በሌላ አነጋገር ይህ አሠራር የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች፣ የወንድ ተጎጂዎች ቡድኖች፣ የቅልቅል ቡድኖች፣ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች በእያንዳንዱ የፖሊሲ ጥያቄ ላይ ያንፀባረቁት አቋም በሀገር-አቀፍ ደረጃ 'በቡድኖች አንፃር' እና 'በአራቱም ቡድኖች ድምር ምልከታ አንፃር' ተቀይጦ የቀረበበት ስልት ነው።

ከላይ በተመለከቱት ሁሉም የመረጃ ማደራጀት ምእራፎች በብዙሃኑ የተደገፉም ሆነ በጥቂት ተሳታፊዎች የተነሱ ሃሳቦችና አመለካከቶች ከነዝርዝር ምክንያቶቻቸው እንዲሰነዱ ተደርጓል። በተለየ መልኩ የተነሱ ሀሳቦች እና ልዩ ትኩረት የሚሹ ማህበረሰቦችን በተመለከተ የተሰጡ እይታዎች - የብዙሃኑን ይሁንታ ባያገኙም እንኳ ባሉበት ደረጃ እንዲካተቱ ተደርጓል።

በትኩረት ቡድኖች ውይይት፣ ከተመረጡ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር በተከናወኑ መድረኮች ውይይት (እና በፅሁፍ ሆነው በቀረቡ አስተያየቶች)፣ እንዲሁም ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በተካሄዱ መድረኮች ውይይት የተገኙ ግብዓቶች ለየብቻ ራሳቸውን ችለው የተደራጁ መሆኑ አንድ ጉዳይ ሆኖ - ሁሉም ባንድነት ተቀይጠው የቀረቡበት ብቸኛው ክፍል በሪፖርቱ ***የመረጃ ማጠቃለያ እና ትንተና ምዕራፍ*** ላይ ብቻ መሆኑን ግልፅ ሊሆን ይገባል።

በመጨረሻም- ከመረጃ አደረጃጀት ጋር በተያያዘ ሰፊ ስራ የመከናወኑን ያክል ውስን ችግሮች ማጋጠማቸው አልቀረም። ከእነዚህ ተግዳሮቶች ውስጥ - የአንዳንድ መድረኮች የእለት ውሎ ሪፖርቶች እና ቃለ-ጉባኤዎች በሚፈለገው መጠን ዝርዝር ሆነው አለመዘጋጀት፣ የጥቂት መድረኮች የትኩረት ውይይት ድምጽ ቅጂዎች ጥራት ደካማ መሆን፣ የውስን ትራንስክሪፕሽን ሰነዶች መጓደል፣ እና በአንዳንድ ቦታዎች በመድረክ ተሳታፊዎች የተሰጡ ድምጾች በተገቢው መልክ አለመገለጽ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እነዚህን ክፍተቶች ከመሙላት አንፃር የባለሙያዎች

ቡድኑ እንደአግባብነቱ ወደ መነሻ የመረጃ ምንጮች እና የድምፅ ቅጂዎች በመመለስ የማመሳከርና የመረጃ ክፍተቱን የማሟላት ስራ አከናውኗል።

## 5.3. ከምክክር መድረኮች እና ባለድርሻ አካላት የተገኙ ግብዓቶች የተተነተኑበት ስነ-ዘዴ

ከላይ እንደተመለከተው መረጃ የመሰብሰብ እና የማደራጀት ሂደቱ በዋናነት አይነታዊ ስነ-ዘዴን (Qualitative Method) መሠረት አድርጎ ተዘጋጅቷል። የተሰበሰቡት ግብዓቶች ትንተናውም አይነታዊ ስነ-ዘዴን የሚከተል ሆኖ - የግኝቶች ማጠቃለያ (መደምደሚያ) ስራውም በከፍተኛ ደረጃ አሃዛዊ መግለጫዎችን ጥቅም ላይ እንዲውል አድርጓል። ሁለቱን አሰራሮች ቀይጦ መጠቀም ያስፈለገበት ዋነኛው ምክንያት ዓይነታዊ ስነ-ዘዴ በሽግግር ፍትህ አማራጭ ጥያቄዎች ላይ - በሁሉም የምክክር መድረኮች - በብዙሃኑንም ሆነ በጥቂት ተሳታፊዎች የተሰጡ ምልከታዎችን ከነምክንያቶቻቸው በገላጭ እና ሀተታዊ አቀራረብ (Descriptive and Narrative Approach) ለመተንተን የሚረዳ ሆኖ በመገኘቱ ሲሆን፡ አሀዛዊ አቀራረብ ደግሞ እያንዳንዱን የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጭ ጥያቄን የደገፉ ቡድኖችን በቡድን ማንነት፣ በክልል እና በሀገር-አቀፍ ደረጃ ለይቶ እና በቁጥር አስደግፎ በማቅረብ - በአብላጫም ይሁን በውስን ድጋፍ የመጡ አማራጮችን በግልጽ ለማመላከት ተመራጭ ስልት በመሆኑ ነው።

ይህ አካሄድ በአንድ የስነ-ዘዴ ማእቀፍ - ገለፃን እና ሃተታን ከአሀዛዊ መረጃ ጋር የሚያቀራኝ እንደመሆኑ መጠን ጊዜ የሚወስድና ሰፊ ስራን የሚጠይቅ መሆኑ አልቀረም። ሆኖም ከሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱ ዓላማ አንፃር - በተለይም የብዙ ተሳታፊዎች እና ክልሎች ሃሳብ በንዑስ ድምፅ ብቻ በመደገፉ ምክንያት በደፈናው እንዳይጨፈለቅ እና ከእይታ ውጭ እንዳይሆን በማድረግ የተሻለ ጥበቃ የሚሰጥ በመሆኑ - ሪፖርቱ በዚህ አግባብ መዘጋጀቱ ፍጹም አስፈላጊ ነበር።

በዚህ ሂደት አማካኝነት መረጃን ለመተንተን ሁለት ዋና ዋና ስልቶች ተግባራዊ ተደርገዋል።

***የመጀመሪያው እና በተለይ የትኩረት ቡድኖች ውይይትን በተመለከተ-*** ከላይ በደረጃ ሁለት የተደራጁትን ግብዓቶች መሠረት በማድረግ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ደረጃ ሁሉም የትኩረት ቡድኖች (የሴት ተሳታፊዎች፡ የወንድ ተሳታፊዎች፡ የቅልቅል፡ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች) የሰጡትን ግብዓት በመተንተንና በመጭመቅ በቁጥር አስደግፎ 'ቡድን-አቀፍ' እና 'ክልል-አቀፍ' የፖሊሲ ምርጫዎችን እንዲያሳይ ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

***ቀጥሎም፥*** በሀገር-አቀፍ ደረጃ ሁሉም የትኩረት ቡድን ተሳታፊዎች (የሴት ተሳታፊዎች፡ የወንድ ተሳታፊዎች፡ የቅልቅል፡ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች) የሰጡትን ግብዓት በመተንተንና በመጭመቅ በቁጥር አስደግፎ 'በሀገር-አቀፍ ደረጃ' በእያንዳንዱ የፖሊሲ አማራጭ ጥያቄ ላይ የተወሰደውን አቋም የሚያሳይ መግለጫ ቀርቧል።

በተመሳሳይ - በቁጥሮች ተደግፎ ባይቀርብም - 'ከተመረጡ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር በተከናወኑ መድረኮች የተሳተፉ ሰዎች (እና በፅሁፍ የቀረቡ አስተያየቶች) ምልከታ' እና 'ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በተካሄዱ የምክክር መድረኮች የተሳተፉ ሰዎች የጋራ ምልከታ' ላይ የተካሄደው የመረጃ ትንተናም - የሁለቱንም ስብሰቦች የፖሊሲ ምርጫዎች በሚያሳይ መልኩ እንዲቀርብ ተደርጓል።

ይህ የግብዓቶች ትንተና ስራ ምዕራፍ - በክልል እና በሀገር-አቀፍ ደረጃ በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ዙሪያ የተሰጡ ምልከታዎች እና አቋሞች ሪፖርት ለማዘጋጀት ወሳኝና የመጨረሻው ምዕራፍ ነው። ይህን ተከትሎ ለሚዘጋጀው ሀገር-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ስራም ዋነኛው የመረጃ መሰረት ነው።

በዚህ የመረጃ መተንተን ስነ-ዘዴ - በየደረጃው ሲወርዱ በመጡ መረጃዎች ላይ በመመስረት በአብላጫ ተሳታፊዎች/ቡድኖች ድጋፍ ያገኙ የፖሊሲ አማራጮች እና ግኝቶችን ከነምክንያቶቻቸው፣ እንዲሁም በተወሰኑ ተሳታፊዎች ብቻ ድጋፍ ያገኙ ሃሳቦች ከነማብራሪያቸው ተለይተው እንዲቀመጡ ተደርጓል።

*በመጨረሻም መረጃዎችን በመተንተን እና ይህን ሪፖርት በማዘጋጀት ሂደት የሚከተሉት መርሆዎች እና ስልቶች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡*

- *የመረጃ መተንተን እና ማጠቃለል ስራው የዓለም-አቀፍና አህጉር-አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎችን፣ እንዲሁም የሽግግር ፍትህ ዓላማን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ማከናወን፡*
- *በግብዓት ማሰባሰቢያ መድረክ የተሳተፉ ተሳታፊዎችን ማንነት እንዲሁም ግላዊ ምልከታ ሚስጥራዊነትን መጠበቅ፡*
- *በየትኛችም ቡድኖች የተነሱ ምልከታዎችን እና ሃሳቦችን በተቻለ መጠን ሁሉ በቁጥር የተደገፉ እንዲሆኑ በማድረግ ግለሰባዊ ፍቅደ-ንባብን ማስቀረት፡*
- *የሪፖርቱ ሃተታዊ አቀራረብ ዘይቤ የአብዛኞቹ ተሳታፊዎች ድጋፍ ያገኘውን የፖሊሲ አማራጭ ሀሳብ በቁጥር አስደግፎ ከማስቀመጥ ባለፈ በእያንዳንዱ የፖሊሲ አማራጭ ስር በአነስተኛ ተሳታፊዎች/ቡድኖች የተነሱ ሀሳቦችን ከነምክንያታቸው ማመላከት፣ እንዲሁም በተለየ መልኩ የቀረቡ ተጨማሪ አማራጮችን ማካተት፡*
- *በተመሳሳይ ቁጥር የተሳታፊዎች ድጋፍ ያገኙ ሁለት የተለያዩ የፖሊሲ አማራጭ ሃሳቦች በሚኖሩበት ጊዜ የተሰጡ ሃሳቦችን ይዘት፣ ምክንያታዊነትና በዓለም-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ሕጎችና ተመክሮዎች ያላቸውን ተቀባይነት፣ እንዲሁም ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ ተሳታፊዎች ሃሳብን ማዕከል በማድረግ ማቅረብ፡*
- *የተጎጂዎች በተለይም ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች (ሴቶች፡ ህጻናት፡ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች፡ አረጋውያን፡ ተፈናቃዮች እና ስደተኞች) ሃሳብ እና እይታ በእያንዳንዱ አማራጭ ስር በተቻለ መጠን ግልጽ ሆኖ እንዲመላከት ማድረግ፡ እና*
- *በግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ የተሰጡ ግብዓቶችን በማያሳንስ፡ በማይበርዝ እና በማይጨፈልቅ መልኩ ማቅረብ፡፡*

*በዚህ የትንተና ሂደት አልፎ የሚዘጋጀው **'የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች - የሕዝብ ምክክር እና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት'** ለህዝብ ይፋ የሚደረግ ይሆናል፡፡*

## ክፍል ስድስት

## ዋና ዋና ግኝቶች

### 6.1. በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ላይ የተንፀባረቁ ዝርዝር ግኝቶች ይዘት

በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ላይ ከተካተቱ የሽግግር ፍትህ ሂደት ዋና ዋና አምዶች ውስጥ አንዱ የወንጀል ክስን በመመስረት ተጠያቂነት የማስፈን ተግባር ነው፡፡ በዚህ ረገድ በምክክር መድረኮቹ ላይ አራት ጥያቄዎች ለውይይት ቀርበዋል፡፡ እነዚህም፣-

- የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?
- በየትኛዎቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ይመስረት?
- የፍርድ ሂደትን ማን ያከናውነው? እና
- የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው? የሚሉ ናቸው፡፡

በነዚህ ጥያቄዎች ላይ '216 ሀገራዊ የትኩረት ውይይት ቡድኖች'፣ 'ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች'፣ እና 'ሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት' ውይይት አድርገዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ መነሻ የሚሆኑ የተለያዩ አማራጮች ቀርበዋል፡፡

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ 'በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች'፣ 'ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' እና 'በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መደረኮች ተሳታፊዎች' የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል፡፡

### 6.2. የወንጀል ተጠያቂነት፥ ክስ፣ ምርመራ እና የፍርድ ሂደትን በተመለከተ

#### 6.2.1. የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?

ከወንጀል ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ በውይይት ሂደቱ ግብዓት የተሰበሰበበት የመጀመሪያው ርእሰ-ጉዳይ 'በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' የሚል ነው፡፡ ዓላማውም የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊያያቸው የሚገቡ የወንጀል አይነቶችን ወሰን ማበጀት ነው፡፡

በዚህ ጥያቄ ስር ሁለት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ አማራጭ አንድ 'ጉልህ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ወይም ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ማከናወን' የሚል ነው፡፡ አማራጭ ሁለት ደግሞ 'ሁሉንም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ወይም ወንጀሎችን ያካተተ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' የሚል ነው፡፡ በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ እና በማወያያ መጠይቁ ላይ በግልጽ እንደተመላከተው እነዚህ ሁለት አማራጮች ለውይይቶቹ በመነሻነት ብቻ የቀረቡ እንጂ ሌሎች አማራጮችን በሚዘጋ መልኩ የተዘጋጁ እንዳልሆነ ለተሳታፊዎች በበቂ ሁኔታ ተብራርቷል፡፡ ተሳታፊዎችም ተገቢ የሚሉት አማራጭ ካለ ማቅረብ እንደሚችሉ ተገልፆላቸዋል፡፡

##### 6.2.1.1.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

I. **የሴት ተጎጂዎች ቡድን**

**ሀ. በአብላጫው የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በሁሉም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት' (አማራጭ 2)**

በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል ለሚለው ጥያቄ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ አብዛኞቹ 27.5 ቡድኖች (ወይም 56.12%) ሁሉንም ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎችን ያካተተ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል።

ለዚህም የሚከተሉትን ነጥቦች በምክንያትነት አቅርበዋል፣-

- በጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ወይም ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ብቻ ማከናወን ካለው ሰፊና ስር የሰደደ ችግር አንፃር 'የዚህን ቡድን አጥፊ ብቻ ጠየቃችሁ' የሚል ወቀሳ ያሥነሳል፤
- በወንጀሎች መካከል ማበላለጥ ሊኖር አይገባም፣ የምናለያይ ከሆነ የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት እንጋፋለን፣ በሰብአዊ መብት ጥሰት የአንዱ ጉዳት ከሌላው ጉዳት ይበልጣል ብሎ ማወዳደርም አይቻልም፤
- ከሁሉም ወንጀል ጀርባ የተጎጂዎች ቁስል (የአካል፣ የአዕምሮ እና ሥነልቦና ጉዳት) አለ፣ እነዚህ ተጎጂዎች ፍትህ አገኙ የሚባለው ሁሉም በየደረጃው ተጠያቂ ሲሆን ነው፤
- በሁሉም ጥፋት ላይ ክስ መመስረት ግለሰባዊ ተጠያቂነትን ያረጋግጣል፣ የተሟላ ፍትህ እንዲኖር ያደርጋል፤
- የወንጀል ትንሽ ትልቅ የለውም፣ ከብት የሰረቀም ሰው የገደለም በጥፋቱ ልክ ሊጠየቅ ይገባል፤
- በወንጀሎች መካከል ልዩነት ማድረግ ለፈፃሚዎች ድርጊቱን ይበልጥ እንዲገፋበት በር ይከፍታል፤
- በከባድ ወንጀሎች ላይ ብቻ ማተኮር ሰላም አያመጣም፣ ቀላል ወንጀሎችን ያበራክታል፣ ይህም አድጎ ወደ ከባድ ጥፋት ሊያመራ ይችላል፤
- ትንሽ ሆነ ትልቅ የመብት ጥሰት የሚጎዳው ህዝብን ነው፣ ስለሆነም ሁሉም ጥሰት ያካተተ ተጠያቂነት ሊኖር ይገባል፤
- ቀላል ወንጀሎች ለማህበረሰባዊ ግንኙነት መሻከር እና እምነት ማጣት የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱ ስለሆነ ሁሉንም በአግባቡ መመርመር ያስፈልጋል፤
- በሁሉም ወንጀሎች ላይ ማተኮር የተጠያቂነት አስተሳሰብ እንዲሰርፅ፣ የሕግ በላይነት እንዲከበር ያደርጋል፤
- እስካሁን እየተደጋገሙ ለተፈጸሙ ጥሰቶች አንዱ ምክንያት በተወሰኑት ላይ ብቻ እያተኮርን መምጣታችን እንደመሆኑ መጠን ያለፈውን በአግባቡ እንፈትሽ ብለን ከተነሳን የምንተወው ጥሰት መኖር የለበትም፤
- ወደፊትን ለማስተካከል ካሰብን ጊዜና ገንዘብ ምክንያት ሊሆኑ አይገባም፣ በማያዳግም መልኩ ሁሉንም መርምረን ምላሽ ለመስጠትና ፍትህ ለማስፈን በሁሉም አይነት ወንጀሎች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል፤
- በሁሉም ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ክስ መመስረት አስፈላጊ መሆኑን እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይ የአስገድዶ መድፈር፣ ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ እና ንብረት ማውደም የበለጠ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

## ለ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'ጉልህ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት' (አማራጭ 1)

በሌላ በኩል በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 21.5 ቡድኖች (ወይም 43.88%) የክስ ሂደቱ ጉልህ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። ለዚህም ያቀረቧቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- በሁሉም የመብቶች ጥሰትና ወንጀሎች ላይ ለመስራት ሰፊ በጀት፣ ጊዜ እና የሰው ሀብት ይጠይቃል፣ የአገሪቷ ነባራዊ ሁኔታ ይህን አይፈቅድም፤
- በትግራይ ጦርነት የውጭ ሃይሎች ተሳታፊ ስለነበሩ በዓለም ዓቀፍ ሕግ መሠረት በሚለዩ ዋና ዋና ተጠያቂዎች ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ በቂ ነው፤
- በሀገሪቷ ለረጅም ጊዜ ከተንሰራፋው አለመረጋጋትና መፈናቀል አንፃር በርካታ ወንጀሎች የተፈፀሙ በመሆኑ በሁሉም ላይ ክስ መመስረት ከተፈጻሚነት አንጻር አዳጋች ነው፤

- በከባድ ወንጀሎች ላይ ተጠያቂነት ማስፈን ከተቻለ ሌሎች ወንጀል ፈጻሚዎችን ማስተማር ይችላል፤
- ሁሉንም ጥሰቶች ለማዳረስ መሞከር ትልልቅ ጥሰቶች ተገቢ ትኩረት እንዳያገኙ ያደርጋል፤
- በሁሉም ወንጀሎች ላይ ማተኮር የፍትህ አሰጣጥ ሂደቱን ሊያጓትት ይችላል፡ በአንፃሩ ጉልህ በሆኑ የመብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ማተኮር ፈጣን እና ውጤታማ የክስ እና ፍትህ ሂደት እንዲኖር ይረዳል፤
- በከባድ ወንጀሎች ላይ አተኩሮ መስራት እንደ እውነት ፍለጋ እና እርቅ ያሉ ሌሎች የሽግግር ፍትህ አማራጮችን ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛል፤

በሌላ በኩል አንዳንድ ተሳታፊዎች የክስ ሂደቱ በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ሊያተኩር እንደሚገባ ገልጸው - የከባድ ወንጀሎች ትርጓሜም እንደ አስገድዶ መድፈር፣ ቤት ማቃጠል፣ ከባድ ስርቆት እና ግድያ የመሳሰሉትን ወንጀሎች ሊያካትት እንደሚገባ ሀሳብ አቅርበዋል።

የተወሰኑ ተሳታፊዎች ደግሞ ሌላ አማራጭ አቅርበው ተከራክረዋል። ክስ ሙሉ ለሙሉ አያስፈልግም፣ ያለፈው በይቅርታ ዘግተን እና ረስተን በወደፊቱ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡ ወደኋላ መመለስ የፊቱን ማበላሸት ነው የሚል ይዘት ያለው ሀሳብ ሰጥተዋል።

ሰንጠረዥ 9፡ 'የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' - የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | የቡድን ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | 0 | 2 |
| 2 | አፋር | 1 | 0 | 1 |
| 3 | አማራ | 7 | 1 | 6 |
| 4 | ቤንሻንጉል | 2 | 2 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 1 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0.5 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 1 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 6 | 8 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 0 | 1 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 2 | 1 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 4 | 5 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 1 | 1 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 5 | 0 |
| | ድምር | 49 | 21.5 | 27.5 |

## II. የወንድ ተጎጂ ቡድኖች

### ሀ. በአብዛኛው የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ 'ጉልህ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት' (አማራጭ 1)

በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል በሚለው ጥያቄ ላይ በሀገርአቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂዎች ቡድኖች ውስጥ 30.5 ቡድኖች (ወይም 64.89%) 'ጉልህ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊከናወን ይገባል' ብለዋል። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶችን አስቀምጠዋል፡-

- በሁሉም ወንጀሎች ላይ ክስ ለመመስረት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም እና ጊዜ አይፈቅድም፣ ውጤታማና የተፋጠነ የክስ ሂደት እንዳይኖር ያደርጋል፤

- ብዙ ጥፋቶች/ወንጀሎች ከመፈጸማቸው አንጻር ሁሉንም መክሰስ የምርመራ፣ ክስ እና ፍርድ ሂደቱ እንዲጓተት በማድረግ ለተበዳዮች እና ለማህበረሰቡ የዘገየ ፍትህን ያመጣል፣ መሰላቸትን ይፈጥራል፤
- በሁሉም ወንጀሎች ላይ ክስ መመስረት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰው እስር ቤት እንዲገባ ያደርጋል፣ ከሽግግር ፍትህ ዓላማ አንጻርም አያስኬድም፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ እንዳይሳካ ተግዳሮት ይፈጥራል፤
- የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ በጉልህ የመብት ጥሰቶች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ቢሰራ ሌሎች ጥሰቶችን በባህላዊ ስርዓት፣ ይቅርታ፣ ምህረት፣ ምክር፣ ለአጥፊዎች ስልጠና በመስጠት መፍትሄ መስጠት ያስችላል፣ ይህም በተራው ተጨማሪ ቁርሾ እንዳይፈጠር ይረዳል፤
- ይህን አማራጭ መከተል በከባድና አሰቃቂ ወንጀሎች ላይ ትኩረት እንዲደረግ ያግዛል፤
- ከሽግግር ፍትህ ዓላማ አንጻር ይህ አማራጭ ሂደቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፤

በሌላ በኩል አንዳንድ የቡድኖች ተሳታፊዎች የጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ትርጉም ሰፋ ብሎ ብዙ የመብት ጥሰቶችን በሚያካትት መልኩ መቃኘት እንዳለበት - በተለይም የብሄር ግጭት ቅስቀሳ፣ የዘር ማጥፋት፣ ንብረት መውረስ፣ ሰው መግደል፣ ማሰቃየት፣ አካል ማጉደል እና ጅምላ ጭፍጨፋ እና የመሳሰሉትን ወንጀሎች መሸፈን እንደሚገባው ጠቁመዋል።

ለ. በተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'በሁሉም ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት' (አማራጭ 2)

በሌላ በኩል 16.5 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች (ወይም 35.1%) የክስ ሂደቱ 'ሁሉንም ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ያካተተ ሊሆን ይገባል' ሲሉ አቋማቸውን ያሳወቁ ሲሆን ምክንያቶቻቸውንም እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- የወንጀል ትንሽ እና ትልቅ የለውም፣ ለትንንሽ ወንጀሎች ሁሉ ተጠያቂነት አለመመስረቱ አሁን ላለንበት ቀውስና የሕግ የበላይነት አለመከበር የዳረገ ስለሆነ በሁሉም ጥሰቶች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል፤
- ዛሬ ትንሽ ተብሎ የተተወ ወንጀል ነገ አድጎ ሀገር ሊያፈርስ ይችላል፣ ስለዚህ ሁሉንም ከስር ከመሠረቱ በመያዝ ትክክለኛ ፍትህ ማስፈን ይገባል፤
- ሙሉ ፍትህ ለማስፈንና አጥፊዎችን ለማስተማር እንዲቻል የትኛውም የወንጀል ድርጊት ሊታለፍ አይገባም፤
- ቀላል የሚባሉ ወንጀሎች ለተጎጂው ከባድ ሊሆኑ ስለሚችሉ በሁሉም ጥፋቶች ላይ ተጠያቂነት ሊኖር ይገባል (በምሳሌ ሲያስረዱ አንድ ተሳታፊ በሰሜኑ ጦርነት ማእቀፍ ከደረሰባቸው የንብረት ዘረፋ ባለፈ የደረሰባቸው ስድብ እና የሞራል ስብራት በራሱ እስከአሁን ያማል ብለዋል)፤
- በሚዛን ሲታዩ ህዝብን እያማረሩና እያሰቃዩ ያሉት ጥፋቶች ጉልህ የማይባሉት ናቸው፤
- በሁሉም ወንጀል ላይ ተጠያቂነት ካልሰፈነ በሽግግር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል፣ ሌላ ቁርሾ ሊተውም ይችላል፤
- በሁሉም ወንጀሎች ላይ ተጠያቂነት ከተመሰረተ ህብረተሰቡ ትምህርት ሊወስድ ይችላል፤
- የሽግግር ፍትህ ዓላማ ሰላምና እርቅ ማምጣት ነው፡ ሰላምና እርቅ የተወሰኑ ጥሰቶችን መርጦ በመክሰስ ሊሳካ አይችልም፤
- የሰብዓዊ መብቶች በባህሪያቸው ተያያዥ ናቸው፡ አንዱን መርጦ ሌላውን ጉዳት መተው አግባብ አይሆንም።

ሰንጠረዥ 10፡ 'የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' - የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | የቡድን ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 5 | 2 |
| 4 | ቤንሻንጉል | 2 | 2 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0.5 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 0 | 1 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 12 | 2 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 2.5 | 0.5 |
| 11 | ደቡብ ሀ/ብ/ብ | 9 | 0.5 | 8.5 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 1 | 1 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 4 | 1 |
| | **ድምር** | 47 | 30.5 | 16.5 |

### III. ቅልቅል ቡድን

**ሀ. በቅልቅል ቡድኖች በአብላጫ የተደገፈ አማራጭ፡ 'ጉልህ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት' (አማራጭ 1)**

በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል በሚለው ጥያቄ ላይ በሀገርአቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ ከተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ከተውጣጡ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 66 ቡድኖች (ወይም 68.75%) የሚሆኑት 'የክስ ሂደቱ ጉልህ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል' የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። የሚከተሉት ነጥቦች በምክንያትነት ተጠቅሰዋል።

- በመደበኛ ጊዜ ከሚታየው በተለየ አካሄድ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ናቸው፤
- ከተፈፀሙ ወንጀሎች ብዛት፣ አይነት፣ ስፋትና ክብደት፣ ከአጥፊዎች ብዛት አኳያ በሁሉም ወንጀሎች ላይ ክስ መመስረት ከጊዜ፣ ከሀብት እንዲሁም ከመረጃ አንጻር ፈታኝ ይሆናል፤
- የፍትህ ተቋማት ለዚህ የሚበቃ አቅም የላቸውም፣ በዚህ መንገድ ቢኬድ የሀገሪቱን ቀርቶ የአንድ መንደር ችግር እንኳ መፍታት አይቻልም፣ የፍትህ መጓተትና መዛባትን ያስከትላል፣ በተጎጂዎች ዘንድም ፍትህ የማጣት ብሎም ተስፋ የመቁረጥ ስሜትን ሊያጭር ይችላል፤
- በሁሉም ወንጀሎች ላይ ክስ ይመስረት ቢባል ለጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የሚሰጠው ትኩረት ሊቀንስ ይችላል፣
- በሁሉም ወንጀሎች ላይ ክስ መመስረት አምራች የሆነውን ኃይል በብዙ ቁጥር በእስር የማቆየት ውጤት ሊኖረው ይችላል፣ ሁሉም ይጠየቅ ይታሰር ከተባለ ሀገሪቱ በሙሉ እስር ቤት የመሆን እድሏ የሰፋ ነው፤
- በጉልህ ጥሰቶች ላይ ማተኮር ለሌሎች የሽግግር ፍትህ አማራጮች እና የግጭት አፈታት ዘዴዎች ተፈጻሚነት እድል ይሰጣል፤
- የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ውጤት እንዲያመጣ የሚታለፉ ጥሰቶች መኖር አለባቸው፣ ይህ አካሄድ ሁሉንም ወንጀሎች በመቅጣት ሊመጣ የሚችለውን ቅራኔ ለማስቀረት ይረዳል፤
- የሽግግር ፍትህ ዋና ዓላማ ግጭት ማስቀም፣ ዘላቂ ሰላም እና ፍትህን ማስፈን በመሆኑ በባህሪው በሁሉም ወንጀሎች ላይ ማተኮር አይገባውም፣ ትኩረቱ በሰብዓዊነት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ የጦር ወንጀል፣ ዘር ማጥፋት ወዘተ በመሳሰሉ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ መሆን አለበት፤
- የሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ በከፍተኛ ወንጀሎች/የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አንፃር ክስ መመስረትን ግድ የሚል ነው፣ ቀለል ያሉ (ጉልህ ያልሆኑ) ጉዳዮች በእርቅ፣ ምህረት፣ ባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓቶች ማስተናገድ ይቻላል፤

- ቀለል ያሉ ጉዳዮች በባህላዊ መንገድ እንዲታዩ ማድረግ ለባህላዊ ሥርዓቶቻችን መጎልበት አስተዋጽኦ ያደርጋል፣ ጉዳዮችን ከፍርድ ቤት በተሻለ ፍጥነት በመቋጨት ሰላምና እውነተኛ እርቅን የማውረድ አቅም አለው፡ በተጨማሪም የሀገርን ሀብት ይቆጥባል፤

በተጨማሪም አንዳንድ የቅልቅል ቡድኖች ተሳታፊዎች 'ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት' ወይም 'ከባድ ወንጀል' የተሰኙ ቃላት ሲተረጎሙ በርካታ ጥሰቶችን በተለይም በህጻናት፡ ሴቶች እና በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት በሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው መዘጋጀት እንደሚገባቸው ሃሳብ አቅርበዋል።

ለ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በሁሉም ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት' (አማራጭ 2)

በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል በሚለው ጥያቄ ላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ከተውጣጡ 96 ቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 30 ቡድኖች (ወይም 31.25%) 'የክስ ሂደቱ ሁሉንም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎችን ያካተተ ሊሆን ይገባል' የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። ለዚህ ያቀረቧቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ይህ አማራጭ የሕግ የበላይነት እንዲከበር፣ ሁሉም ላጠፋው ጥፋት ተጠያቂነት እንዲኖርበት፣ ፍትህም ያለ አድልዎ ለሁሉ እንዲሰፍን ያደርጋል፤
- የሀብት ችግር ከሠው መብት እና ህይወት አይበልጥም፣ ስለሆነም ይህ አማራጭ ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል፤
- ወንጀል ትንሽና ትልቅ የለውም፣ ሁሉም የማህብረሰቡን ሰላም ያውካሉ፣ ፍትህን ይደፈጥጣሉ፤
- ጉልህ የሆኑና ያልሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ብሎ ለመመደብ መለኪያው ግልጽ አይደለም፣ ይህም ተጠያቂ መሆን ያለባቸው ሰዎች ሳይካተቱ ሊቀሩ የሚችሉበትን መንገድ ይከፍታል፣ በተጎጂዎች ዘንድም ቅሬታን ይፈጥራል፤
- የወንጀል ሀሳብ በራሱ ክፋት ነው፣ ሀብት፡ ህይወትና ሀገር የሚያጠፋ ስለሆነ ሁሉንም መቅጣት ይገባል፤
- የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም፣ የተወሰኑ ጥሰቶችን ብቻ ነጥሎ ማየት የተሟላ ፍትህ አያስገኝም፤
- ጉዳዮችን በፍጥነት ለመጨረስ ተብሎ በገሚስ የወንጀል አይነቶች ላይ ብቻ ክስ ቢመሰረት ችግርን ከስር ከመሰረቱ ለመፍታት አያግዝም፣ ጊዜ ሰጥቶ ለሁሉም ወንጀሎች ተጠያቂነትን መመስረት ያስፈልጋል፤
- ትንንሽ የሚባሉ የመብት ጥሰቶች አድገው ዛሬ ላይ በሀገሪቱ ለሚስተዋሉ ውስብስብ ችግሮች ምክንያት ሆነዋል፣ በእነዚህ ላይ ሙሉ ተጠያቂነት ካልተመሰረተ ወንጀል መለማመድ ይመጣል፣ ይህም ለወንጀል መስፋፋትና ወደፊት ለሚፈጠር ቁርሾ ምክንያት ይሆናል፤
- ትልልቅ ወንጀሎች ብቻ ክስ ይመስረትባቸው ቢባል በሀገሪቱ ከተንሰራፋው የጥቅም ትስስር አንፃር መጠየቅ የሚገባቸው ቀርተው መቅረት ያለባቸው ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ፤
- በሁሉም ጥሰቶች ላይ ተጠያቂነት ቢመሰረት ለካሳና ለእርቅ ብቻ ሳይሆን በታሪክ ለመሰነድ ይረዳል፤
- እያንዳንዱ ወንጀል ከተበዳይ አንጻር ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ሊሆን ይችላል፣ የተበዳይን የፍትህ ፍላጎት ማሟላት የሚቻለው ሁሉንም ጥሰት እንደአግባብነቱ ማካተት ሲቻል ነው።

ከላይ የተጠቀሱት አስተያየቶች እንዳሉ ሆኖ ጥቂት የቅልቅል ቡድኖች ተሳታፊዎች በሁለት ምክንያቶች በክስ አማራጭ አስፈላጊነት ላይ ጥያቄ አንስተዋል። አንደኛው - ችግራችን ከፍ ያለ ውስብስብ የብሄር እና የፖለቲካ ችግር ነው፡ ስለሆነም ሁሉንም ጥሰት በይቅርታ አልፎ መሻገር ያስፈልጋል የሚል ነው። ሁለተኛው - አሁን ካለው የሀገሪቱ ነባራዊ የግጭት እና አለመረጋጋት ሁኔታ አንጻር ክስ መመስረትና ተጠያቂነትን ማስፈን ፍጹም አስቸጋሪ ነው የሚል ነው።

ሰንጠረዥ 11፡ 'የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' - የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | የቡድን ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | 2 | 4 |
| 2 | አፋር | 2 | 2 | 0 |
| 3 | አማራ | 13 | 10 | 3 |
| 4 | ቤንሻንጉል | 4 | 2 | 2 |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | 1 | 1 |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 1 | 1 |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 1 | 1 |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 23.5 | 3.5 |
| 9 | ሲዳማ | 2 | 2 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 4 | 3 | 1 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 11.5 | 6.5 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 2 | 2 |
| 13 | ትግራይ | 10 | 5 | 5 |
| | **ድምር** | 96 | 66 | 30 |

## IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን

### ሀ. በአብላጫው የተደገፈ አማራጭ፡ 'ጉልህ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት' (አማራጭ 1)

በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል በሚለው ጥያቄ ላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች መካከል ሁሉም በሚባል ደረጃ (23 ቡድኖች ወይም 95.8%) 'የክስ ሂደቱ ጉልህ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎች ላይ ሊያተኩር ይገባል' የሚል አቋም ይዘዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ነጥቦች በምክንያትነት አቅርበዋል።

- ጥሰቶቹ በመጠን እና በአይነት ሰፊ በመሆናቸው ከአቅምና ተፈጻሚነት፣ እንዲሁም ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ አንፃር ሲታይ የክስ ሂደቱ በጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ማተኮር አለበት፤
- በሁሉም ላይ ክስ ይመስረት ቢባል ውጤታማ ሊሆን አይችልም፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊሸከመው አይችልም፣ የበቀል አዙሪት ውስጥም ይከታል፤
- በሁሉም ላይ ክስ መመስረት ከምርመራ አንፃር ውስብስብ ይሆናል፣ ማስረጃ ማግኘት አዳጋች ይሆናል፤
- ፍርድ ቤቶች ካለባቸው ጫና አንጻር የክስ ሂደቱ ጉልህ በሆኑ የመብት ጥሰቶች ላይ ሊያተኩር ይገባል፤
- ይህ አማራጭ ውስብስብ በሆኑና በማህበረሰቡ ላይ ቀውስ ባስከተሉ አለም አቀፍ ወንጀሎች ላይ ተጠያቂነትን በትኩረት ለማረጋገጥ ያስችላል፡ ሌሎች ወንጀሎች በአማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ ሊታዩ ይችላሉ፤
- የሽግግር ፍትህ ዓላማ ማህበራዊ ትስስርን አክሞ ሀገርን ማሸጋገር እንደመሆኑ መጠን ሂደቱ በከባድ ወንጀሎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል።

ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ተሳታፊዎች የክስ ሂደቱ በአማራጩ ላይ በተዘረዘሩት የወንጀል አይነቶች ብቻ መገደብ የለበትም፡ የዓለም አቀፍ ሕግ ጥሰት ባህሪ ባይኖራቸው እንኳ ከባድ ወንጀል ሊባሉ የሚችሉ በተለይም እንደ መደፈር እና ጾታዊ ጥቃቶችን የመሳሰሉ ድርጊቶች 'ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት/ወንጀል' በሚለው ዝርዝር ውስጥ ሊካተቱ ይገባል የሚል ሃሳብ አንስተዋል።

### ለ. በተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቡድን የተደገፈ አማራጭ፡ 'በሁሉም ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት (አማራጭ 2)

በሌላ በኩል በጉዳዩ ላይ ከተወያዩ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 1 ቡድን (ወይም 4.2%) 'የክስ ሂደቱ ሁሉንም ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎችን ያካተተ ሊሆን ይገባል' ብለዋል። ለዚህም የሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ቀርበዋል።

- በሰብዓዊ መብቶች መካከል ማበላለጥ አይኖርም፣ የማይነጣጠሉ ናቸው፣ ወንጀልን ትንሽና ትልቅ ብሎ መክፈልም ተገቢ አይደለም፣ በሁሉም ወንጀሎች ላይ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል፣ የአንደኛው መብት መጣስ ለሌላው መብት መጣስ አስተዋጽኦ አለው፤
- እኩልነት እንዲሰፍን፣ ተጎጂዎች እንዲረኩ፣ ወንጀል እንዲቆም ከተፈለገ ጥፋቶችን ማበላለጥ አይገባም፣ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ እምነት የሚኖረው በሁሉም ጥሰቶች ላይ ተጠያቂነት ሲሰፍን ነው፤
- በሁሉም ወንጀሎች ላይ ምርመራና ክስ መጀመር የማህበረሰቡን የፍትህ ጥያቄ በተሻለ ደረጃ ያረካል፣ በውስን ጥሰቶች ላይ ብቻ በማተኮር ለሁሉም ተበዳዮች ተገቢ ፍትህ ማስፈን አይቻልም፤
- በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ዘላቂ መፍትሄ እንዲመጣ ከተፈለገ በሁሉም ጥሰቶች/ወንጀሎች አንፃር ተጠያቂነትን ማስፈን ያስፈልጋል።

ሰንጠረዥ 12፡ 'የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' - የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 5 | 5 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል | 1 | 1 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0.5 | 0.5 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | 7 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | - | - | - |
| 10 | ሶማሌ | 1 | 1 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 3 | 2.5 | 0.5 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | - | - | - |
| 13 | ትግራይ | 4 | 4 | 0 |
| | **ድምር** | 24 | 23 | 1 |

### 6.2.1.2.'በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

'በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 (የሴት ተጎጂዎች፣ ወንድ ተጎጂዎች፣ ቅልቅል፣ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን) ቡድኖች ውስጥ 142 ቡድኖች (ወይም 65.74%) 'ጉልህ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' የሚል አቋም ይዘዋል። ቀሪዎቹ 74 ቡድኖች (ወይም 34.26%) ደግሞ 'በሁሉም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል ብለዋል'።

**ይህ ግኝት ውይይቶቹ ከተካሄዱባቸው ክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች አንጻር ሲተነተን**

በአዲስ አበባ እና ደቡብ ህ/ብ/ብ ክልል በሁሉም ጥፋቶች ላይ ክስ ይመስረት የሚለው አማራጭ የበለጠ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፡ በሀረሪ እና ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የቀረቡት ሁለቱም አማራጮች እኩል ድጋፍ አግኝተዋል። በቀሩት ክልሎች ማለትም በአፋር፣ አማራ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ኦሮሚያ፣

ሲዳማ፣ ሶማሌ እና ትግራይ ክልል ደግሞ የክስ ሂደቱ ጉልህ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ሊያተኩር ይገባል የሚለው አማራጭ የተሻለ ድጋፍ አግኝቷል።

**ግኝቱ ከተለያዩ ቡድኖች አንጻር ሲታይ**

በሁሉም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል የሚለው አማራጭ በሴት ተጎጂዎች ቡድን የተሻለ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፡ በሌሎች ቡድኖች (ማለትም በወንድ ተጎጂዎች፣ በቅልቅል፣ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች) ግን የክስ ሂደቱ በጉልህ ጥሰቶች ላይ ሊያተኩር ይገባል የሚለው አማራጭ የበለጠ ተቀባይነት አግኝቷል።

ሁሉም ቡድኖች አቋማቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አስደግፈው ያቀረቡ ሲሆን - እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።

***ሀ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'ጉልህ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት (አማራጭ 1)' - ምክንያቶች***

በአራቱም ቡድኖች ውይይቶች ላይ ይህን አቋም በመደገፍ በተሳታፊዎች ከተነሱት ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- የሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ፣ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች መጠን እና ስፋት፣ እንዲሁም የአጥፊዎች ብዛት ሲታይ በሁሉም ጥሰቶች ላይ ክስ ይመስረት ቢባል 'የሀገሪቱን ቀርቶ የአንድ መንደር ችግር' እንኳ በቅጡ መፍታት ያስቸግራል፤
- በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የቀየው አለመረጋጋትና መፈናቀል ለበርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ወንጀሎች መፈፀም ምክንያት ሆኗል፡ በዚህ ነባራዊ ሁኔታ በሁሉም ጥፋቶች ላይ ክስ መመስረት የሚታሰብ አይሆንም፡ ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ እና የፍትህ ተቋማት አቅም፣ ጊዜ እና የሰው ሀይል በላይ መሆኑ አይቀርም፤
- በሁሉም ጉዳዮች ላይ ክስ መመስረት በበቀል አዙሪት ውስጥ ይከታል፤
- ይህን አማራጭ መከተል የፍትህ መጓተትን ያመጣል፣ በተጎጂዎች ዘንድም ፍትህ ማጣት ብሎም ተስፋ መቁረጥን ያስከትላል፤
- በመሆኑም በሁሉም የሰብዓዊ  መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ከማተኮር ይልቅ ጉልህ በሆኑ ጥፋቶች ላይ ብቻ መስራት ውጤታማ እና ፈጣን የክስና ፍትህ ሂደት እንዲኖር ያደርጋል፤
- በተጨማሪም ከሽግግር ፍትህ ዓላማ አንጻር የክስ ሂደቱ ትኩረት በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ማድረግ ሌሎች ጥፋቶች በአማራጭ አላባዎች እንዲታዩ ያስችላል፤
- የሽግግር ፍትህ ዋና ዓላማ ግጭት ማስቀም፣ ዘላቂ ሰላም እና ፍትህን ማስፈን እንደመሆኑ መጠን ባህሪያዊ አካሄዱ በሁሉም ወንጀሎች ላይ ከማተኮር ይልቅ ውስብስብ በሆኑ፣ ትልቅ ቀውስ ባስከተሉ፣ እና በመደበኛ ጊዜ ከሚታየው በተለየ መልኩ ምላሽ በሚያስፈልጋቸው ከባድ ጥፋቶች ላይ ብቻ መሆን አለበት፤
- ከዚህ አኳያ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ውጤት እንዲያመጣ የሚታለፉ ጥሰቶች መኖር አለባቸው፣ ይህ አካሄድ ሁሉንም ወንጀሎች በመቅጣት ሊመጣ የሚችለውን ቁራኔ ያስቀራል፣ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ዳግም ሊያገረሽ የሚችል ቁርሾና ኩርፊያ ለማስቀረት ይረዳል፤
- ከዚህ አልፎም በሁሉም ወንጀሎች ላይ ክስ ለመመስረት መሞከር ከፍተኛ ቁጥር ያለውን አምራች ኃይል ወደ እስር ቤቶች የመላክ ውጤት ይኖረዋል፣ ይህም ሌላ ጣጣ ይዞ ከመምጣቱ ባለፈ ትልልቅ ጥሰቶችም ተገቢ ትኩረት እንዳያገኙ ያደርጋል፤

በሌላ በኩል ጥቂት ተሳታፊዎች የ'ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች' ትርጉም ብዙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በሚያካትት መልኩ መቃኘት እንዳለበት ገልፀዋል። ይህም በተለይ እንደ አስገድዶ መድፈር፣ በሴቶች

እና ህጻናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን፣ የብሄር ግጭት መቀሰቀስን፣ የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ ንብረት መውረስ ወይም ማውደም፣ ግድያ፣ ማሰቃየት፣ አካል ማጉደል፣ እና ጅምላ ጭፍጨፋ የመሳሰሉ ድርጊቶችን ሊያካትት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

**ለ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'በሁሉም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት (አማራጭ 2)' - ምክንያቶች**

በዚህ ረገድ በተወሰኑ ቡድኖች ጎልቶ የወጣው አቋም የሚከተለውን ይመስላል።

- 'የወንጀል ትንሽና ትልቅ የለውም'፣ ስለሆነም ተጠያቂነትን በማስፈን ሂደት በጥሰቶችን መካከል ትንሽ እና ትልቅ እያሉ ልዩነት መፍጠር ተገቢ አይደለም፤
- ቀላል የሚባሉ ወንጀሎች በማህበረሰብ ውስጥ ለግንኙነቶች መሻከር እና እምነት ማጣት አስተዋጽኦ አድርገዋል፣ ሕዝቡን ለከፍተኛ መማረር እና እንግልት ዳርገውታል፣ ዛሬ ትንሽ ተብለው የሚተው ወንጀሎች ነገ ሀገር የሚያፈርሱ ናቸው፣ 'ትንሽ እሳት ከገለባ ላይ ሲወድቅ ብዙ ጉዳት ያደርሳል፣ አሉባልታና ወሬን ትንሽ ነው ብለን ከተውን ነገ የዘር ማጥፋት እና ጦርነት ሊቀሰቅስ ይችላል'፤
- በሁሉም ጥፋቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ክስ መመስረት የሕግ የበላይነትን ያረጋግጣል፣ በተሻለ ሰላምን ይፈጥራል፣ በሁሉም ላይ ተጠያቂነትን ያረጋግጣል፣ ለተጎጂዎችም የተሻለ ፍትህን ይሰጣል፤
- በሌላ በኩል ጊዜ እና ሀብትን ምክንያት በማድረግ በትንንሽ ጥፋቶች ላይ ተጠያቂነት ከቀረ የወንጀል ልምምድን ያመጣል፣ ወንጀለኞች ድርጊታቸውን እንዲገፉበት በር ይከፍታል፣ በሽግግር ሂደቱም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል፣ ሌላ ቁርሾም ሊተው ይችላል፤
- በመርህ ደረጃም ቢሆን ሰብዓዊ መብቶች የማይነጣጠሉ ናቸው፣ የአንደኛው መብት መጣስ ለሌላው መብት መጣስ አስተዋጽኦ አለው፤
- ፍትህን ለሁሉም ተጎጂዎች ከማስፈን አንጻር ይህ አማራጭ ተገቢ ነው፣ ከሁሉም ወንጀል ጀርባ የተጎጂዎች ቁስል (የአካል፣ የአዕምሮ እና ሥነልቦና ጉዳት) አለ፣ ቀላል/ከባድ የሚለው ክፍፍልም ቢሆን አንጻራዊ ነው፡ በተጎጂው ዓይን ሊታይ ይገባል፤
- ጉልህ የሆኑ/ያልሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ብሎ ለመመደብ መለኪያው ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም፣ ይህም ተጠያቂ መሆን ያለባቸው ሰዎች ሳይካተቱ ሊቀሩ የሚችሉበትን መንገድ ሊከፍትና በተጎጂዎች ዘንድም ቅሬታን ሊፈጥር ይችላል፤


ሰንጠረዥ 13፡ 'የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' - ሀገር-አቀፍ (የአራቱም ቡድኖች በክልል ደረጃ) ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | 2 | 6 |
| 2 | አፋር | 5 | 4 | 1 |
| 3 | አማራ | 32 | 21 | 11 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 7 | 2 |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 2.5 | 2.5 |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 3 | 2 |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 2 | 2 |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 48.5 | 13.5 |
| 9 | ሲዳማ | 4 | 3 | 1 |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 8.5 | 2.5 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 18.5 | 20.5 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | 4 | 4 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 13 | ትግራይ | 24 | 18 | 6 |
| | **ድምር** | **216** | **141** | **75** |

ሰንጠረዥ 14፡ 'የትኛቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' - ሀገር-አቀፍ የአራቱም ቡድኖች ማጠቃለያ

| | | **ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት** | **አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት** | **አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት** |
|---|---|---|---|---|
| 1 | **ሀገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ** | 49 | 21.5 | 27.5 |
| 2 | **ሀገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ** | 47 | 30.5 | 16.5 |
| 3 | **ሀገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ** | 96 | 66 | 30 |
| 4 | **ሀገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ** | 24 | 23 | 1 |
| | **ሀገራዊ የአራቱም ቡድኖች ማጠቃለያ** | **216** | **141** | **75** |
| | | | | |




'የትኛቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

### 6.2.1.3.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

በዚህ ርእስ ስር - ከህጻናት ፓርላማ ተወካዮች፣ በህጻናት መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ተቋማት ተወካዮች፣ ያታዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴት ተሳታፊዎች፣ በሴቶች መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች የተወከሉ ተሳታፊዎች፣ የአካል ጉዳት

*ካለባቸውና ከአረጋውያን ተሳታፊዎች፣ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጋር በተደረጉ የተለያዩ የልዩ ትኩረት የምክክር መድረኮች ማእቀፍ የተሰጡ ግብዓቶች እንደሚከተለው ተጠቃለዋል።*[45]

*'የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ - አብዛኞቹ ከጾታዊ ጥቃት ያገገሙ ሴት ተሳታፊዎች፣ የህጻናት ፓርላማ ተሳታፊዎች፣ እንዲሁም በህጻናት መብት ላይ የሚሰሩ ተቋት ተወካዮች፣ አካል ጉዳት ያለባቸው ተሳታፊዎችና አረጋውያን፣ እንዲሁም የተወሰኑ የሃገር ውስጥ ተፈናቃይ የሴት እና የወንድ ተጎጂዎች እና የቅልቅል ቡድን ተሳታፊዎች - የወንጀል ተጠያቂነት ሂደቱ በጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት እንዲኖረው ጠይቀዋል።*

*ተሳታፊዎቹ ለዚህ በዋናነት ያቀረቡት ምክንያት - ሁሉንም ጥፋተኞች ለመክሰስ ያለው ነባራዊ ሁኔታ፣ የጊዜ እና የገንዘብ አቅም የሚፈቅድ አይደለም፣ በሁሉም ወንጀሎች ላይ ክስ መመስረት ሀገርን በበቀል አዙሪት ውስጥ ያስገባል፣ ጉልህ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ማከናወን ውጤታማነቱን እና አፈጻጸሙን የተሻለ ያደርገዋል የሚል ነው። በተጨማሪም የሽግግር ፍትህ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚያገለግል ልዩ ሥርዓት መሆኑን ከግምት በማስገባት ሂደቱን ለእንዲህ ዓይነት ወንጀሎች ብቻ መጠቀም የተሻለ ውጤታማ ያደርገዋል ብለዋል።*

*ነገር ግን ከባድ/ጉልህ የሚባሉ የወንጀል አይነቶች በአግባቡ መዘርዘር፡ ግልፅ በሆነ መመዘኛም መለየት ያለባቸው መሆኑን ተሳታፊዎቹ አስገንዝበዋል። በዚህም አግባብ በሴቶች እና በህጻናት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በከባድ ወንጀል ማእቀፍ መታየት አለባቸው ብለዋል። በተጨማሪም በአካል ጉዳተኞች እና በአረጋውያን ላይ የሚደርሱ የመብት ጥሰቶች በልዩ ሁኔታ መታየት ይኖርባቸዋል የሚል ሀሳብ አንስተዋል።*

*በሌላ በኩል ከሴቶች መብት ተወካዮች ጋር በተደረገ የምክክር መድረክ እና ከሃገር ውስጥ ተፈናቃዩች ጋር በተካሄደው ምክክር የተወሰኑ ሴት ተጎጂዎች፡ ወንድ ተጎጂዎችና ቅልቅል ቡድን፡ እንዲሁም የተወሰኑ ከጾታዊ ጥቃት ያገገሙ ሴት ተሳታፊዎች እና የሕጻናት መድረክ ውይይቶች ተሳታፊዎች - የክስ ሂደቱ ሁሉንም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን/ወንጀሎችን ያካተተ ሊሆን ይገባል ብለዋል።*

*ለዚህ የሰጡት ዋና ምክንያት ሁሉም ወንጀል እኩል ነው፡ ምንም እንኳን ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ቢሆንም ወንጀሎችን ከምንጩ ማድረቅ ይገባል፡ ለዚህም ሁሉንም ወንጀሎች አጣምሮ መክሰስ ያስፈልጋል የሚል ነው። በዚህ ረገድ ወንጀሎቹ እጅግ በጣም ብዙ በመሆናቸው የክስ ጉዳዮቹ ትኩረት በአስገድዶ መድፈር እና ከፍርድ ውጭ በተፈፀሙ ግድያዎች ላይ መሆን አለበት በማለት አጽንኦት ሰጥተው ተከራክረዋል። በተለይም በሴቶች ላይ ለደረሰው ሰፊ ጥሰት ግልፅ እውቅና በመስጠት በፖሊሲው የሚቀመው የተጠያቂነት መሰረት ራሱን ችሎ መመስረት አለበት የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።*

### 6.2.1.4.*ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ*

*የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን በአዲስ አበባ እና አካባቢው በልዩ ባለድርሻ አካላት ላይ ያተኮሩ የምክክር መድረኮችን በተለያዩ ጊዜያት አዘጋጅቷል። ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እና አመራሮች፣ ከሃገር ውስጥ ምሁራን፣ ከፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች እና አመራሮች፣ ከሚዲያ ሲቪክ ማህበረሰብ እና ዲሞክራሲ ተቋማት ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።*

---

[45] *በዚህ ርእስ ስር የተመለከቱ ማጠቃለያዎች በሚከተሉት መድረኮች ላይ ከተሳታፊዎች በተገኙ ግብአቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ከህጻናት ፓርላማ ተወካዮች እና በህጻናት መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ተቋማት ተወካዮች ጋር መስከረም* 10-11/2016 *ዓ.ም በአዳማ የተደረገ መድረክ፤ ፆታዊ ጥቃት ደርሶባቸው ካገገሙ ሴት ተጎጂዎች ጋር ሀምሌ* 24-26 2015 *ዓ.ም በባህር ዳር እና በመቀሌ የተደረጉ መድረኮች፤ በሴቶች መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ተሳታፊዎች ጋር ግንቦት* 22-23 2015 *በቢሾፍቱ የተደረገ መድረክ፤ የአካል ጉዳት ካለባቸው እና ከአረጋውያን ጋር መስከረም* 19 2016 *ዓ.ም በአዲስ አበባ የተካሄደ መድረክ፤ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ስደተኞች ጋር በአሶሳ፡ መቀሌ፡ ጭሮ እና አዲስ አበባ የተደረጉ የምክክር መድረኮች።*

ከዚህም በተጨማሪም በርካታ በሽግግር ፍትህ ዙሪያ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት እና ግለሰቦች አስተያየቶችን እና ምክረ-ሃሳቦችን ለባለሙያዎች ቡድኑ በጽሁፍ አቅርበዋል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ካውንስል፣ የሰብዓዊ መብት ማዕከል፣ የዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት ግሎባል ክሪሚናል ጀስቲስ ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (NEWA) እና ICTJ ጥምረት ሪፖርት፣ ICTJ፣ እና Commission for the Investigation of Violence in SRS and Reconciliation and Reparation of Victims ያቀረቧቸው ዝርዝር ሰነዶች ተጠቃሽ ናቸው።

በመድረክ ውይይቶች እና በፅሁፍ የተሰጡ አስተያየቶች እና ምክረ ሃሳቦች እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።

የወንጀል ተጠያቂነት አስመልክቶ በጥቅሉ የተሰጠው ግብዓት የሽግግር ፍትህ ስርዓቱ ያለፉትን አሰቃቂ ድርጊቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ እና ፍትህን ለማረጋገጥ እንጂ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባቸውን ሰዎች ላለመክሰስ ወይም በጥቅሉ ይቅር ብሎ ለማለፍ ያለመ ሊሆን አይገባውም፡ ስለሆነም የሚዘጋጀው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በግልጽ የአጥፊዎችን መከሰስ እና መቀጣት የሚያፀና ሆኖ መዘጋጀት አለበት የሚል ነው።

'የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ በሁሉም ባለድርሻ አካላት የተንፀባረቀው መሰረታዊ ሀሳብ ሁሉንም የመብት ጥሰቶች በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ መክሰስ ስለማይቻል ትኩረቱ በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል የሚል ነው።

ለዚህም የህገ-መንግስቱ አንቀጽ 28 ዓላማ ይህን የሚያረጋግጥ መሆኑ፡ እንዲሁም በጉልህ መብት ጥሰቶች ላይ ማተኮር ከሀገር-አቀፍም ሆነ አለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የሚጣጣም እና ለግለሰብ ተበዳዩችም ክስ ለማቅረብ እድል የሚሰጥ መሆኑን በምክንያትነት ቀርቧል።

በሌላ በኩል የክስ ጉዳይ እና ሂደቱ የተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን የፍትህ ፍላጎት ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መከናወን እንደሚኖርበት፡ እንዲሁም ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ክስ በሚቀርብባቸው ጉልህ ጥሰቶች ማእቀፍ ውስጥ መካተት እንዳለባቸው አመላክተዋል። በተጨማሪም 'ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' የሚለው ፅንሰ-ሃሳብ ከአለም አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ሕጎች አንጻር በአግባቡ መተንተን እንዳለበት የተነሳ ሲሆን - ጉልህ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የአለም-አቀፍ ሰብአዊነት ህግን (International Humanitarian Law) ስለማያካትት ፅንሰ-ሃሳቡ 'gross violations of international human rights law and serious violations of international humanitarian law constituting crimes under international laws' በሚል መተካት ወይም በዚህ መልኩ መታየት ያለበት መሆኑ፡ እንዲሁም ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ከወሲባዊ ጥቃት በተለይም አስገድዶ መድፈር ባለፈ ሰፋ ባለ መልኩ አካላዊ ስልቦናዊ እና ማህበራዊ ጥቃቶችን በሚያካትቱ መልክ በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ ትርጓሜ እንዲሰጣቸው ምክረ-ሃሳብ ተሰጥቷል።

### 6.2.2. በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?

ከወንጀል ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ ውይይት የተካሄደበት እና ግብዓት የተሰበሰበበት ሁለተኛው ጉዳይ 'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' የሚል ነው። ይህ ጥያቄ የሽግግር ፍትህ የክስ ሂደት ሊያካትታቸው የሚገቡ አጥፊዎችን ለመለየትና ለመወሰን የተዘጋጀ ነው። በዚህ ጥያቄ አንፃር ለተሳታፊዎች ሁለት መነሻ አማራጮች ቀርበዋል።

- አማራጭ 1: ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ማለትም በጠንሳሾች፣ ትእዛዝ በሰጡ፣ ባቀዱ፣ በመሩ እና ከፍተኛ ሀላፊነት ኖሮባቸው ሀላፊነታቸውን ባልተወጡ ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል የሚል ነው።

- አማራጭ 2: ደግሞ በማንኛውም ደረጃ የተሳተፉ አጥፊዎችን ያካተተ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል የሚል ነው።

በዚህ ጥያቄ ላይ '216 ሀገራዊ የትኩረት ውይይት ቡድኖች'፡ 'ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች'፡ እና 'ሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት' ውይይት አድርገዋል።

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ 'በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች'፡ 'ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' እና 'በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መደረኮች ተሳታፊዎች' የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል።

### 6.2.2.1.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

#### I. የሴት ተጎጂዎች ቡድን

**ሀ. በአብዛኛው የሴት ተጎጂዎች ቡድን የተደገፈው አማራጭ፡ 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ማለትም በጠንሳሾች፣ ትእዛዝ በሰጡ፣ ባቀዱ፣ በመሩ እና ከፍተኛ ኃላፊነት ኖሮባቸው ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ ሰዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' (አማራጭ 1)**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ 'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች 29 ቡድኖች (ወይም 59%) የሚሆኑት በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ የወንጀል ተጠያቂነት የማረጋገጥ ስራ ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ነጥቦች በምክንያትነት አቅርበዋል።

- ከፍተኛ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ችግሩን ከምንጩ ለማየት እና በትእዛዝ እና ግፊት ወደ ወንጀል ድርጊት የገቡትን አጥፊዎች ያስተምራል፣ 'መንጋው እንዲበተን እረኛውን ምታ' እንደሚባለው፤
- በዋነኝነት ወንጀሎችን የሚጠነስሱና አመራር የሚሰጡ ባይኖሩ ወንጀሎች አይፈጸሙም ነበር፤
- ከፍተኛ ፈጻሚዎች የሚጠየቁበትን አውድ ይፈጥራል፣ ወንጀሎችን በከፍተኛ ደረጃ የሚፈጽሙና ሀገር የሚያጠፉት በከፍተኛ ቦታ ላይ ያሉ ባለስልጣናት (ለምሳሌ ሚኒስትሮች፣ ከንቲባዎች ወዘተ) ሊሆኑ ስለሚችሉ የክስ ሂደቱ ትኩረት በእነሱ ላይ እንዲሆን ለማድረግ ያስችላል፣ ይህ አካሄድ ለቀጣይ ባለስልጣኖች እና አጥፊዎች ትምህርት ይሰጣል፤
- የኤርትራ መንግስት አመራሮች እና ወታደሮችን ጨምሮ የተለያዩ ባለስልጣናት እና ከፍተኛ የህይማኖት መሪዎች ለተፈጸሙ ጥሰቶች አስተዋፅኦ ስለነበራቸው ተጠያቂነቱ ከእነሱ መጀመር አለበት፤
- ይህ አማራጭ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከነበረው ጦርነት ጋር በተያያዘ ለብዙ ሰው ህይወት መጥፋት ምክንያት በሆኑት አካላት  ላይ ለማተኮር ያስችላል፤
- ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች እስከ ታች ድረስ ጥሰቶችን የሚፈፅሙት በሰንሰለት እንደመሆኑ መጠን የእነሱ ተጠያቂ መሆን ሌሎች ጠንካራ እርምት/ትምህርት እንዲወስዱ ይደርጋል፤
- አውቀው ወይም በቸልተኝነት ወይም ሳያውቁ ባጠፉ ሰዎች መካከል ተገቢ ልዩነት በመፍጠር ፍትሀዊነት እንዲሰፍን ያግዛል፤
- ከፍተኛ ተሳትፎ ካላቸው ውጭ ያሉት ብዙዎቹ አጥፊዎች የዋና አጥፊዎች መሣሪያ ናቸው፣ ሥራ በማጣት፣ በጥቅም ተታለው፣ በስሜት ተገፋፍተው ወይም በውሸት ትርክት ተነድተው የበላይ ትዕዛዝ የፈፀሙ ናቸው፡ ያለፈቃዳቸው ለፈፀሙት ወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ብዙ ውጤት አያስገኝም፣ በሌላ አሠራር ቢጠየቁ ይመረጣል፤

- ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ለወንጀሉ ዓላማ መሳካት ፍላጎቱ ኣላቸው፡ ለደረሰው ጥፋት መነሻ እና አስፈጻሚ፣ የችግሩ ጠንሳሽ፣ ጀማሪ እና ግምባር-ቀደም ተዋናይ ሆነው ወንጀሉን ያቀዱ/የመሩ፣ በእጃቸው ያለውን ሁሉ ተጠቅመው ሌሎቹን የማሳመን እና በጉዳዩ ላይ ተሳታፊ የማድረግ ዋና ስራ የሰሩ፣ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ዕውቀት ኖሯቸው የተንቀሳቀሱ፣ ሊመጣ የሚችለውን ጉዳት እያወቁ የመብት ጥሰት የፈፀሙ ግለሰቦች የክስ ሂደቱ ትኩረት መሆን አለባቸው፤
- ይህ አማራጭ ወንጀልን ለመከላከል እና ተመሳሳይ ጥሰት እንዳይፈጸም ለማድረግ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፤
- ፍትህ እንዲሰፍን እና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤
- በፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን የስራ ጫና እንዲቀንስ ይረዳል፣ በግልጽ የሚታይ እና በአጭር ጊዜ የሚተገበር ውጤታማ የክስ ሂደት እንዲኖር ያደርጋል፤
- ለክስ ሂደት መረጃና ማስረጃ ለማግኘትና ለማሰባሰብ ተመራጭ ነው፤
- ባለፉት ጊዜያት በርካታ የማህበረሰብ ክፍል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በጥሰቶች ተሳታፊ ነበር፡ ሁሉንም ተጠያቂ ማድረግ የፍትሕ ሂደቱን ከባድ፣ አፈጻጸሙንም አስቸጋሪ ያደርገዋል፤
- ጊዜና ገንዘብ በመቆጠብ ሀገራዊ ኢኮኖሚውን እና የሰው ሀብት አቅም በአግባቡ ለመጠቀም ይረዳል፤
- ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስልቶችን (ለምሳሌ እውነት ማውጣት፣ እርቅ ወዘተ) በአግባቡ ለመተግበር ይረዳል፣ የሽግግር ፍትህ ዓላማን ለማሳካት ያግዛል፤
- ሁሉንም በመክሰስ የሚመጣ ሌላ ቁርሾ ያስቀራል፣ ለእርቅ በር ይከፍታል፤

በተጨማሪም አብዛኞቹ ቡድኖች 'ከፍተኛ ኃላፊነት ያላቸው' ሲባል በመንግስት ሥልጣን ላይ ያሉትን ብቻ የሚመለከት እንዳልሆነ በአጽንኦት ገልጸዋል።

**ለ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'የወንጀል ክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ውስጥ በተሳተፉ ሰዎች ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል'** (አማራጭ 2)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ 'የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተወሰኑት 20 ቡድኖች (ወይም 41%) የሚሆኑት 'የወንጀል ክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ውስጥ በተሳተፉ ሰዎች ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል' የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። ይህን አማራጭ ለመደገፍ በምክንያትነት የቀረቡት ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

- ጥሰቱ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እስከሆነ ድረስ በማንኛውም ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት በየደረጃው እና በየአካባቢው ያሉ አጥፊዎችን ያካተተ እንዲሆን ያደርጋል፤
- ወንጀልን ከግብ የሚያደርሰው የሁሉም ፈጻሚዎች ድምር ተግባር በመሆኑ ሁሉም እንደየተሳትፎ ደረጃው እንዲጠየቅ ለማድረግ ያስችላል፤
- ሰዎች ሁሉ እኩል ናቸው፣ ትዕዛዝ ሰጭዎችም ሆኑ ፈጻሚዎች መጠየቅ አለባቸው፤
- ይህ አማራጭ አዛዥ/ታዛዥ በማለት ተገቢ ያልሆነ ልዩነት እንዳይፈጠር፣ በሀሳብም ይሁን በተግባር የተሳተፈ ሁሉ እንደየተሳትፎ መጠኑ እንዲጠየቅ ያደርጋል፤
- የጥሰቱ የመጀመሪያ ደረጃ ተሳታፊዎች/አነሳሾች ከላይ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ የሚገኙ እንደመሆኑ መጠን 'አጥፊውም ከአጥፊው በስተጀርባ ያሉት' ኃላፊነት መውሰድ አለባቸው፤
- በሁሉም ጥፋተኞች ላይ ተጠያቂነት ማስፈን ወንጀል እንዳይስፋፋ ያደርጋል፣ ችግርን ከስር ለመፍታት ያግዛል፤
- የወንጀል ድርጊቶችን ባለማበላለጥ ህብረተሰቡ አጥፍቶ ሳይማር እንዳይቀርና ተደጋጋሚ የሆኑ ጥሰቶች እንዳይፈፀሙ ያደርጋል፣ ሁሉንም ፈጻሚ ተጠያቂ በማድረግ ማንም ሰው ከሕግ እንዳያመልጥ ያግዛል፤
- ግለሰቦች የበላይ ትዕዛዝ በሚፈፅሙበት ጊዜ የድርጊቱን ሕጋዊነት በመመርመር ለሕገወጥ ትዕዛዝ እምቢተኝነታቸውን መግለፅ ሲገባቸው ይህን ባላደረጉበት መጠን ተጠያቂ እንዲሆኑ ያስችላል፤

- ወንጀለኞች በየትኛውም ደረጃ ተሳትፈው ለፈፀሙት ወንጀል ተጠያቂ አለማድረግ በድርጊታቸው ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ተበዳዮች ፍትህን ይነሳል፣ ጥላቻ ያሳድጋል፣ ተጎጂዎች ፍትህን በእጃቸው እንዲይዙ ያበረታታል፣ የሕብረተሰቡን የፍትህ ጥያቄ ያጓድላል፤
- በየደረጃው ያሉ ሁሉም ሰዎች የተከሰሱ እንደሆነ ተጨማሪ ጥሰት እንዳይፈጸም ለመከላከልና ለማስተማር ይረዳል፣ ወንጀል የሠራ ሰው አስተሳሰብ ካልተገራ ለነገ መጥፎ ትምህርት ይሰጣል፣ ወንጀለኞችን ያበረታታል፤
- የሕግ አንዱ ዓላማ ሰዎችን ማስተማር እንደመሆኑ መጠን ወንጀሉ በቀጣይ እንዳይደገም ወይም ሰዎች ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲታቀቡ አጥፊዎች መቀጣት አለባቸው፤
- ሁሉም በከባድ ወንጀል ድርጊት የተሳተፉ ሰዎች ጭካኔ የተሞላበት ወንጀል የፈጸሙ ስለሆኑ ሊጠየቁ ይገባል፤
- ይህ አማራጭ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ፍትህ እንዲያገኙ ይረዳል፤
- በትግራይ የደረሰው በደል እጅግ ከባድ ስለሆነ በሁሉም አይነት ወንጀሎች የተሳተፉ፣ ከላይ ትእዛዝ ያስተላለፉ፣ የገደሉ፣ ሆስፒታሎችን ያፈረሱ፣ መሠረተ ልማት ያጠፉ፣ እንደ ቡድንም ሆነ ግለሰብ ተደራጅተው የዘረፉ፣ የደፈሩ ከላይ አዛዦች እስከ ታችኛው መዋቅር ያሉ መጠየቅ አለባቸው፤
- ይህ አማራጭ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሁሉንም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እንዲፈታ ያስችለዋል፤
- ፍትህን ለማስፈን፣ የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ፣ ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ሠላም ለማቀም ይረዳል፤

ሰንጠረዥ 15፡ 'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' - የሴት ጉዳተኛ ቡድኖች ሀገር-አቀፍ/ክልል ደረጃ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | 0 | 2 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 4 | 3 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 2 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0.5 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 0 | 1 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 9 | 5 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 2 | 1 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 4.5 | 4.5 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 0 | 2 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 4 | 1 |
| | ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | 49 | 29 | 20 |

### II.የወንድ ተጎጂ ቡድኖች

**ሀ. በአብዛኛው የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ፡ 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ማለትም በጠንሳሾች፣ ትእዛዝ በሰጡ፣ ባቀዱ፣ በመሩ እና ከፍተኛ ኃላፊነት ኖሮባቸው ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ ሰዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' (አማራጭ 1)**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ 'የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 37 ቡድኖች (ወይም 78.7%) የሚሆኑት በሽግግር ፍትህ ሂደት

የወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል የሚል አቋም ይዘዋል። በምክንያትነትም የሚከተሉትን ነጥቦች አንስተዋል።

- ሁሉንም አጥፊዎች ተጠያቂ ማድረግ ከሀገር ኢኮኖሚ፣ ከወንጀሎቹ ውስብስብነት እና የማስፈጸም አቅም አንጻር ሲታይ ከባድ ነው፣ ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ስጋቶችን ለመቀነስ፣ እንዲሁም የተፋጠነ ፍትህ ለማስፈን ከፍተኛ ተሳትፎ ባላቸው ላይ ማተኮር ያስፈልጋል፤
- በሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ብዙ ሰው በወንጀል ድርጊት ተሳትፏል፣ ሁሉም ይከሰስ ቢባል ማስረጃ ለማግኘት ያለው እድል አነስተኛ ነው፣ የማስፈፀም አቅሙም ይህን አይፈቅድም፣ ሌላ ቀውስም ይዞ ይመጣል፤
- ይህ አማራጭ ውጤታማ፣ ተደራሽ እና ተግባራዊ የክስ ሂደት ለማከናወን የተመቸ ነው፤
- አብዛኛዎቹ ጥሰቶች የፖለቲካ ይዘት አላቸው፣ የሚታቀዱትም ሆነ የሚመሩት በውስን ሰዎች ነው፤
- ግጭትን የሚጀምሩ ዋና ተዋንያን ናቸው፣ ድርጊት ፈጻሚዎች የሚከተሉት ዋናዎቹን ነው፣ የንብ አውራ ተጠያቂ ከሆነ ሌላው ተከታይ ይበተናል፣ ቀያሹ ተጠያቂ ሳይደረግ ጀሌውን/ተከታዩን መክሰስ ማረሚያ ቤቶችን ከማጨናነቅ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም፤
- በሁሉም ጥሰቶች የተሳተፉ ሰዎችን መክሰስና ተጠያቂ ማድረግ ሂደቱን አስቸጋሪ ያደርገዋል፣ 'ክብሪት በራሱ ጉዳት የለውም፣ ዋናው ጥፋት አድራሽ ክብሪት ለኳሹ ነው፣ ተለኳሹ ክብሪት ግን ወይ ያቃጥላል ወይ ይቃጠላል'፣ ስለሆነም የክሱ ትኩረት በጥፋት ጠንሳሾች ላይ መሆን አለበት፤
- ከከፍተኛ አጥፊዎች ውጭ ያሉ ሌሎች ተሳታፊዎች ብዙ ጊዜ ተላላኪ ናቸው፣ የሚፈፅሙትን ወንጀል ውጤት በአግባቡ አይረዱም፣ የሀላፊ ትእዛዝ ለመፈፀም በሌሎች አስገዳጅነት ወይም አነሳሽነት የሚሳተፉ ናቸው፣ ገሚሶቹም በፕሮፓጋንዳ ተታለው ወይም በስሜት ተገፍተው የገቡ ናቸው፣ ስለሆነም የክስ ሂደቱ እነሱን የሚያካትት ሊሆን አይገባም፣ ዋናዎቹን መቅጣት ሁሉንም አጥፊዎች እንደመቅጣት ሊቆጠር ይችላል፤
- በከፍተኛ ደረጃ ተጠያቂ የሆኑትን ድርጊትን ያቀዱ፣ የመሩ፣ ጉልህ ጥፋት የፈፀሙ፣ ወደ ጦርነት እንዲገባ ያደረጉ፣ ጦርነትን የጠነሰሱ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር የበላይ ሀላፊዎችን ማካተት ሌሎች ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲታቀቡ ያደርጋል፤
- ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው፣ በተለይም በመንግስት መዋቅር የሚገኘው አመራር ከላይ እስከ ታች መጠየቅ አለበት፣ ህዝብን የሚያስገድለው፣ የሚያደራጀው፣ የሚያስታጥቀው፣ የሚያፈናቅለው ይህ አመራር ነው፤
- ተጠያቂነት መጀመር የሚገባው በህዝብ ላይ ጉዳት ለማድረስ በግልጽ ዝተው ጥፋት እንዲፈጸም ትዕዛዝ በሰጡ የጦር እና የፖለቲካ አመራሮች ነው፤
- ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው ሰዎች ተጠያቂ ከተደረጉ ታች ላሉ ፈጻሚዎች ትምህርት ይሰጣል፣ ወደፊት ተመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ያስተምራል፤
- ዋና አጥፊዎች ታች ድረስ ችግር የሚፈጥሩት በሰንሰለት ነው፣ የእነሱ መጠየቅ ሌሎቹ እንዲታረሙ ያደርጋል፤
- ከዋና ዋና አጥፊዎች ውጪ በተለያየ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸውን አጥፊዎች በተለያየ አግባብ አስተምሮ መመለስ ይቻላል፣ ጉዳያቸው እንደ እርቅ ባሉ ሌሎች መንገዶች ወይም በመደበኛ የፍትህ ሥርዓት ሊታይ ይችላል፤

### ለ. በተወሰኑ የወንድ ተኀጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'የወንጀል ክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ውስጥ በተሳተፉ ሰዎች ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል' (አማራጭ 2)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ 'የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 10 ቡድኖች (21.2%) የሚሆኑት በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚከናወነው የክስ ሂደት በማንኛውም ደረጃ በሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ወይም

ወንጀሎች ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን ያካተተ ሊሆን ይገባል የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት ያቀረቧቸው ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በሁሉም አጥፊዎች ላይ ተጠያቂነት ካልተመሠረተ በባህላዊ አሠራር መሠረት ደም መመለስን ይገፋፋል፤
- ከላይ ያለውን አመራር ብቻ ተጠያቂ አድርጎ የታች ፈፃሚዎች ከማህበረሰቡ ጋር አብረው እንዲኖሩና ጠዋት ማታ በነፃነት እንዲታዩ ማድረግ የአብሮነት መስተጋብርን ያውካል፤
- ከፍተኛ ተሳትፎ ከነበራቸው ውጭ ያሉት ሰዎች የማይጠየቁ ከሆነ ነገ ዋና ጠንሳሽ/መሪ ሆነው የባሰ ጥሰት የሚፈፅሙበት እድል ሊፈጠር ይችላል፣ ስለዚህ ችግርን ከስሩ ለማድረቅ እንዲረዳ፣ ጥሰት እንዳይደገም፣ ፍትህም እንዲሰፍን ሁሉንም ተጠያቂ ማድረግ ይሻላል፤
- ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፣ ወንጀል እስከተፈፀመ ድረስ በአጥፊዎች መካከል ልዩነት ማድረግ አይገባም፣ ሁሉም እንደየተሳትፎው ተጠያቂ ማድረግ ወደፊት የወንጀል ተባባሪ እንዳይኖር ያደርጋል፤
- ሁሉንም የወንጀል ተሳታፊዎች ማካተት ካልተቻል ትክክለኛ ፍትህ ማስፈን አይቻልም፤
- ወንጀልን ከኋላ ሆነው የመሩና ያቀዱን መለየት እና ለፍርድ ማቅረብ ከባድ ነው፣ ስለሆነም ከፍተኛ ተሳትፎ ባላቸው ላይ ማተኮር የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን ከወንጀል ማምለጫ መሳሪያ እንዲሆን ያደርገዋል፤
- ይህ አማራጭ እውነተኛ ተጠያቂነት እና ፍትህ ለማስፈን፣ የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ፣ ለውጥ ለማምጣት፣ ከችግር አዙሪት ለመውጣት እና እርቅና ሰላም ለማምጣት ይረዳል፤
- ፍትህ ከጊዜና ገንዘብ በላይ ነው፣ ሁሉንም አጥፊዎች ተጠያቂ ማድረግ ጊዜና ሀብት ይጠይቃል የሚለው ምክንያት ተቀባይነት የለውም፤
- አንዳንዴ ተራ ወታደሮች/ሰዎች ከበላይ አመራር ትእዛዝ ውጭ ወንጀል ይፈፅማሉ፣ ይህ አማራጭ አሰቃቂ ወንጀል የፈጸሙትን በአግባቡ ተጠያቂ ለማድረግ ያስችላል፤
- የተጎጂዎች ፍትህ የማግኘት መብት ያሳካል፤
- በወንጀሉ መሪዎች ላይ የማስረጃ እጥረት ሊኖር ስለሚችል ፈፃሚው ሁል ጊዜ ትዕዛዝ እየወሰደ ወንጀል መፈጸምን እንደስራ ሊለማመድ ይችላል፤
- የወንጀል ተሳታፊዎችን አቃጅና ፈጻሚ ብሎ በመለያየት ማየት አይቻልም፣ ወንጀል እንዲፈጸም ትዕዛዝ የሰጠም ሆነ ወንጀሉን በቀጥታ የፈጸመ ሁሉ የሃሳብና ተግባር አንድነት አላቸው፤
- አዛዡም ታዛዡም ካልተጠየቁ በሀገር ደረጃ ወንጀልን መከላከልና ማስቆም አይቻልም፤
- ድርጊቱን በፈጸሙ ላይ ክስ ከተመሠረተ ያቀዱትን፣ ትዕዛዝ የሰጡትን እና መሪዎችን ማግኘትና ተጠያቂ ማድረግ ቀላል ያደርገዋል፤
- የወንጀለኛ ትንሽና ትልቅ የለውም፣ ያልተቀጣ ጥፋተኛ ትምህርትና እርምት አይወስድም፤

ሰንጠረዥ 16፡ 'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' - የወንድ ጉዳተኛ ቡድኖች ሀገር-አቀፍ/ክልል ደረጃ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 7 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 2 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0.5 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 0 | 1 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 10 | 4 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 10 | ሶማሌ | 3 | 3 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 6.5 | 2.5 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 2 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 3 | 2 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 47 | 37 | 10 |

III. **የቅልቅል ቡድኖች**

***ሀ. በአብዛኛው የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ፡ 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ማለትም በጠንሳሾች፣ ትእዛዝ በሰጡ፣ ባቀዱ፣ በመሩ እና ከፍተኛ ሀላፊነት ኖሮባቸው ሀላፊነታቸውን ባልተወጡ ሰዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል'*** (አማራጭ 1)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ 'የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች 61.5 (ወይም 64.06%) የሚሆኑት በሽግግር ፍትህ ሂደት የወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል፡፡ ምክንያታቸውንም እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

- የመብት ጥሰቶች እየተፈጸሙ ያሉት ተቋማዊ በሆነ መልኩ የመንግስትን ሃላፊነት፣ አደረጃጀት እና ሃብት በመጠቀም ነው፤
- አዛገሮች/ጠንሳሾች ወንጀልን ሊያስቀሙና ያጠፉትን ሊቀጡ ሲገባ ያሰቡት እንዲፈፀም ነገሮችን ያመቻቹ/የሰሩ በመሆኑ ክሱ እነሱን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት፣ ጠንሳሾች ሁሌም የጥሰቱ ውጤት ፈላጊዎች ናቸው፣ ድርጊቱን በቀጥታ ከሚፈፀሙት ሰዎች በላይ የበለጠ አደገኛ ናቸው፤
- በከፍተኛ ሃላፊነት ላይ ያሉ ሰዎች አሁን ሀገሪቱ ላለችበት ችግር ዋና ምክንያት ናቸው፣ ስለሆነም ትኩረቱ ከፈጻሚዎች ይልቅ በሃላፊዎቹ ላይ መሆን አለበት፤
- ቀስቃሾች ባይኖሩ ፈጻሚ አይኖርም፣ ስለሆነም በዋናዎቹ ላይ ማተኮር ተገቢ ነው፤
- በተለያዩ ግጭቶች እጃቸውን ባስገቡ የመንግስት ባለስልጣናት ላይ ተጠያቂነት ሊሰፍን ይገባል፣ በሰሜኑ ጦርነት ብዙ ጥሰቶች ቢፈፀሙም ጥፋቱን የመሩት ጥቂት ናቸው፣ ሌላው ፈጻሚ ሰለባ ነው፤
- አማራጩ ከገንዘብ፣ ከጊዜ፣ ከወንጀል ተሳታፊዎች ብዛት፣ ከውጤት እና ከተቋማት አቅም ማነስ አንፃር ተመራጭ ነው፤
- ሁሉም ይከሰስ ቢባል ሰላም አያመጣም፣ ማስረጃም በቀላሉ አይገኝም፤
- ለረጅም ጊዜ በሀገራችን ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ ወንጀሎች ተፈፅመዋል፣ እነዚህን ሁሉ ለማጣራት ረጅም ጊዜ ይፈጃል፣ ይህም ፍትህን ያዘገያል፣ ሁሉንም መክሰስ ሆነ መቅጣት በተጨባጭ አይቻልም፣ ሌሎች የሽግግር ፍትህ አማራጮች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ያደርጋል፤
- ይህ አማራጭ ለቀልጣፋ እና ውጤታማ የፍትህ ሥርዓት የተመቸ ነው፣ የሌሎች ሀገራት ልምድም ይህን ያሳያል፣ የፍትህ ሥርዓቱ ሊሸከመው በሚችለው ልክ እንዲሆን ያስችላል፤
- ተበዳዮች ቶሎ ፍትህ ያገኛሉ፣ ቁስላቸው ይሽራል፤
- ጥሰቶች እንዳይስፋፉና እንዳይበራከቱ፣ ተመሳሳይ ጥሰቶች እንዳይደገሙ ከጠንሳሹ ለማድረቅ ያግዛል፤
- ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው በአግባቡ ከተቀጡ ሌሎቹ ትምህርት ይወስዳሉ፤
- በዋና ዋና አጥፊዎች ላይ ክስ/ተጠያቂነት ማስፈን ከተቻለ የታች ፈጻሚዎች ይስተካከላሉ፤
- ሁሉም ጥፋተኞች ይጠየቁ ከተባለ ከሽግግር ፍትህ ዓላማ ጋር አብሮ አይሄድም፣
- ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ሁሉም ይጠየቅ ቢባል የሚተርፍ የህብረተሰብ ክፍል የለም፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ታሳሪን ለማስተናገድ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ አይፈቅድም፣ ኪሳራ ያስከትላል፣ ከአቅም በላይ ይሆናል፣

ስለሆነም ሁሉንም ተጠያቂ ከማድረግ ይልቅ አማራጭ የሽግግር ፍትህ አላባዎችን መጠቀም ይሻላል፣ ትኩረቱ ትዕዛዝ በሰጡ ላይ መሆን አለበት፣ ውሃ ወደ ላይ አይወጣም ወደታች ይፈሳል እንጂ፤

- የሽግግር ፍትህ ዋና ዓላማ እርቅና ሰላም ማስፈን ነው፣ ሌሎች ተሳታፊዎች በይቅርታ ሊታለፉ ይችላሉ፤
- የሽግግር ፍትህ ሂደት ዓላማውም ትኩረቱም ከፍተኛ ጥሰቶች ላይ ነው፤
- ዋና አጥፊዎች ላይ ያተኮረ ክስ የሽግግር ሂደቱን ውጤታማ ያደርጋል፤
- ጥፋቶች በአብዛኛው በስልጣን ፈላጊ ሰዎች አቀናባሪነትና መሪነት የሚፈፀሙ ናቸው፣ እነዚህን ተከትለው የሚገቡ ሰዎች ባለማወቅ፣ ባለማስተዋል፣ አማራጭ አጥተው፣ ተገደው፣ ተቀጥረው ወይም ለህይወታቸውና ለቤተሰባቸው ሲሉ የተሳተፉ/የታዘዙ ስለሆነ ሊካተቱ አይገባም፤
- ከፍተኛ ባለስልጣናት በሕግ ተጠያቂ ከሆኑ ማህበረሰቡ በሀገሪቱ የሕግ የበላይነት አለ፣ ፍትህም ሰፍኗል ብሎ እንዲያምን ያደርገዋል፤

**ለ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'የወንጀል ክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ውስጥ በተሳተፉ ሰዎች ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል'** (**አማራጭ** 2)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ 'የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 34.5 (ወይም 35.93%) የሚሆኑት በማንኛውም ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል ሲሉ አቋማቸውን ገልፀዋል። በምክንያትነት የተነሱት ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

- የጥፋት ትንሽ/ትልቅ የለውም፣ ያጠፋ ሁሉ እንደየደረጃው መጠየቅ አለበት፣ አለበለዚያ አጠገቡ ሆኖ የጎዳው ሰው ሳይጠየቅ ቢቀር በማህበረሰቡ ውስጥ ቅሬታ ይፈጥራል፤
- በወንጀል የተሳተፈ አጥፊ እንደየደረጃው ካልተጠየቀ የእርስ በእርስ በቀልን ያስፋፋል፤
- የተወሰኑ አጥፊዎች/ትእዛዝ የሰጡ ሰዎች ብቻ ቢጠየቁ ፈጻሚዎች አይማሩም፣ ጥሰትን ሊያስፋፉ ይችላል፤
- የሰብዓዊ መብት ጥሰት ትንሽ/ትልቅ የሚል ልዩነት የለውም፣ ወንጀል የፈጸሙ ሁሉ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ግልፅ መልእክት ያስተላልፋል፤
- ትንንሽ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እየሰፉ ለትልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መነሻ እየሆኑ ነው፤
- ዛሬ ላይ በአነስተኛ ደረጃ ተሳታፊ የሆነ ወንጀለኛ ነገ ዋና ተዋናይ ሆኖ ሊመጣ ይችላል፤
- ወንጀል ወንጀል እስከሆነ ድረስ በየትኛውም ደረጃ ያለ ተሳታፊ ተጠያቂ መሆን አለበት፤
- የተሟላ ፍትህ ለመስጠት፣ ቀጣይ ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ፣ ተጠያቂነት እንዳለም ለማስተማር ይረዳል፤
- ወንጀል ወደውና ፈቅደው የፈፀሙ ዝቅተኛ አጥፊዎች ቢቀጡ ከስህተታቸው የመማር እድል ይፈጥርላቸዋል፤
- በዋንኞቹ ላይ ማተኮር ከዚህ በፊት ተሞክሮ ለውጥ አላመጣም፣ ይህ አካሄድ ለማስተማርም ሆነ እና ቀጣይ የወንጀል ድርጊትን ለመከላከል ፋይዳው እምብዛም ነው፤
- የወንጀል ተጎጂ የሆነ ሰው የሚያውቀው ወንጀሉን የጠነሰሰውን/ያስፈፀመውን ሰው ሳይሆን ወንጀሉን የፈፀመውን ነው፣ ፍትህ የሠፈነ መስሎ የሚታየው አጥፊው ሲቀጣ ነው፣ ስለሆነም ሁሉም አጥፊዎች ተጠያቂ በሚሆኑበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ማድረግ ተገቢ ነው፤
- ህገወጥ ትዕዛዝ ተቀብለው ለጥቅም ወይም በሌላ ዓላማ ወንጀል የፈፀሙ ሁሉ መጠየቅ አለባቸው፤
- በየትኛው ደረጃ የተሳተፉ አጥፊዎች በሀገራችን ለተፈጠረው ቀውስ ሀላፊነት አለባቸው፤
- ህብረተሰቡን የሚያማርሩትና ከባድ ጥሰት የሚፈፅሙት ታች ያሉ ግለሰቦች ናቸው፣ በቁጥርም ከዋናዎቹ የሚበዙና በማሕበረሰቡ ውስጥ ተሰግስገው የሚገኙ ናቸው፤

- ወንጀል እንዲፈጸም ያዘዘውም ሆነ ታዞ የፈጸመው ሀላፊነት አለባቸው፣ የታዘዘውም ቢሆን የተላለፈለት መመርያ ህገወጥ ከሆነ እምቢ የማለት መብት ስለሚኖረው በማንኛውም ደረጃ በጥሰቶች የተሳተፉ ሰዎችን ተጠያቂ ማድረግ ተገቢ ነው፤
- በጥፋት የተሳተፈ ሰው እንደየጥፋቱ መጠን መጠየቅ አለበት፣ ተገድጄ ነው የሚባል ነገር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፣ ሰው ከእንስሳ የሚለየው የራሱ ህሊና ስላለው ነው፤
- ለተበዳይ ተገቢ ፍትህ ከመስጠት አንጻር ሁሉም እንደየተሳትፎ ደረጃው ተጠያቂ መሆን አለበት፤
- ቁስል የማዳን ሥራ ነው እስከተባለ ድረስ እያንዳንዱ ሰው ቁስሉ እንዲሽር ሁሉም ያጠፋ ሰው ቅጣት ማግኘት አለበት፤
- ሁሉንም ተጠያቂ ማድረግ ማህበረሰቡ ወንጀልን እንዲፀየፍና ዘላቂነት ያለው ሰላም ለመፍጠር ይረዳል፤
- የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ስኬታማ እንዲሆን ሰዎች ወንጀሉን ለመፈፀም የነበራቸውን መጥፎ ሀሳብና ድርጊት ታሳቢ በማድረግ በሁሉም ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል፤

**በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች ተሳታፊዎች የቀረበ አዲስ/ሌላ አማራጭ**

የተወሰኑ ተሳታፊዎች የወንጀል ክስ ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው ሰዎች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት በሚለው ሀሳብ ተስማምተው - ነገር ግን ሁሉንም ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ አስፈላጊ አለመሆኑን ገልፀዋል። ለባህላዊ የግጭት አፈታት ዘይቤዎች ተገቢ ቦታ መሰጠት እንዳለበት በመጥቀስ - አጥፊዎች በህይማኖት መሪዎችና በባህላዊ ሥርዓት ሊዳኙ እንደሚገባ ተከራክረዋል።

ይህ አሰራር ከጊዜና ከገንዘብ ጋር ተያይዞ ተመራጭ ያልሆነውን የአማራጭ ሁለትን ደካማ ጎን ይቀርፋል። በፍርድ ሂደቱ በተለያየ ደረጃ የተሳተፉ አጥፊዎችን በሀይማኖት አባቶችና የባህል ፍትህ ተቋማት እንዲዳኙ ማድረግ የማህበረሰቡን እሴት ያጎለብታል፣ ለእርቅ ይረዳል፣ ለተበዳይ የፍትህ ስሜትን ይፈጥራል፣ ተጠያቂነትንም ከእርቅ ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት ያደርገዋል በማለት አዲስ/ሌላ አማራጭ አቅርበዋል።

ሰንጠረዥ 17፡ 'በዩትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' - የቅልቅል ቡድኖች ሀገር-አቀፍ/ክልል ደረጃ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | 4 | 2 |
| 2 | አፋር | 2 | 2 | 0 |
| 3 | አማራ | 13 | 9 | 4 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | 4 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | 2 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 0 | 2 |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 0 | 2 |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 20 | 7 |
| 9 | ሲዳማ | 2 | 2 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 4 | 2 | 2 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 9.5 | 8.5 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 2 | 2 |
| 13 | ትግራይ | 10 | 5 | 5 |
| | ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | 96 | 61.5 | 34.5 |

## IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን

***ሀ. በአብዛኛው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ፣ 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ማለትም በጠንሳሾች፣ ትእዛዝ በሰጡ፣ ባቀዱ፣ በመሩ እና ከፍተኛ ሀላፊነት ኖሮባቸው ሀላፊነታቸውን ባልተወጡ ሰዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል'*** (***አማራጭ*** 1)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ 'የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 16.5 ቡድኖች (ወይም 68.75%) የሚሆኑት በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ የወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል ብለዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ነጥቦች በምክንያትነት ቀርበዋል።

- ሁሉንም ወደ ክስ የምንወስድ ከሆነ ከውጤታማነት አንጻር ውስንነት ይኖረዋል፣ ብዙ ሀብት፣ የሰው ሃይል እና ጊዜ ይጠይቃል፣ ምክንያቱም ውስብስብ እና በርካታ ጉዳዮች ስለሚታዩ፤
- በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገሪቱ በርካታ ሰዎች ጥፋት ውስጥ ተሳታፊ ሆነዋል፣ ስለሆነም በሁሉም ላይ ክስ መመስረት አይቻልም፣ ይሁን ቢባል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ ብዙ ጥቅም አይኖረውም፤
- ሁሉንም ቀርቶ በዋና ዋናዎቹ ላይ እንኳን ክስ መሥርቶ መጨረስ አዳጋች ነው፤
- አማራጩ ለክትትልና ለአፈፃፀም ይመቻል፣ ዋና ጠንሳሾች ባይኖሩ ድርጊቱ አይፈፀምም፣ በከፍተኛ ደረጃ የተሳተፉ ሲከሰሱ በሁለተኛ ደረጃ የተሳተፉ ይማራሉ ('ትልቁን አሳ አጥምዶ ሌሎቹን ማስተማር') ፤
- አቅደው ብዙሀኑ እንዲሳተፍ ባደረጉ ላይ ያተኮረ ተጠያቂነት እንዲኖር ከተደረገ ተጽዕኖው ከፍተኛ ነው፤
- ብዙ ወንጀሎች የሚፈጸሙት ከሥርዓት ብልሹነት ጋር በተያያዘ ነው፣ ይህም የሚፈጸመው ከላይ ባሉ ሰዎች ነው፣ ስለሆነም የነገር ጠንሳሽ የሆኑት ቢጠየቁ ቅጣቱ ይበልጥ አስተማሪ ይሆናል፤
- የጉዳዩ ዋና አቀነባባሪዎችን ሀሳብ በቀላሉ ማግኘት ይቻላል፣ የሁሉንም ሀሳብ ማግኘት ግን ከባድ ነው፤
- ይህ አማራጭ ዘላቂ ሰላም ያመጣል፣ ዋናዎቹ ሲጠየቁ ተመሳሳይ ወንጀል እንዳይደገም ያደርጋል፤
- የከፍተኛ ፈፃሚዎች ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ከሌሎቹ ፈፃሚዎች ከፍ ያለ ነው፤
- ሁሉንም ጥፋተኞች መክሰስ ፍትህ በተገቢው ጊዜና መጠን ለመስጠት አያስችልም፣ የተጓተተ ፍትህ እንዲኖር ያደርጋል፤
- ከዋና ዋና አጥፊዎች ውጭ ያሉትን በሌሎች የሽግግር ፍትህ አማራጮች ማየት የተሻለ ነው፣ ለእርቅ እና ሌሎች የሽግግር ፍትህ መንገዶች እድል ይሰጣል፤
- ዋነኞቹ አጥፊዎችን በመደበኛ የፍትህ ስርአት ተጠያቂ የማድረግ እድል ዝቅተኛ ነው፤

***ለ. በተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ ሀሳብ፣ 'የወንጀል ክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ የሰብዓዊ ሙብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ውስጥ በተሳተፉ ሰዎች ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል'*** (***አማራጭ*** 2)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ 'የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 7.5 ቡድኖች (ወይም 31.25%) የሆኑት የወንጀል ክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ በሰብአዊ ሙብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን በማካተት ሊከናወን ይገባል ብለዋል። ለዚህም በምክንያትነት የሚከተሉትን ሀሳቦች አንስተዋል።

- የሽግግር ፍትህ ከዋና የወንጀል ሕግ መርሆዎች ጋር መጣጣም አለበት፣ የበላይ ትዕዛዝ መከላከያ መሆን አይችልም፣ ስለሆነም ሁሉም ወንጀል አድራጊ እንደተሳትፎ ደረጃው መጠየቅ አለበት፤
- ጥፋተኞችን ትንሽና ትልቅ ብሎ መለየት በራሱ አስቸጋሪ ነው፣ የክስ ሂደቱ ሁሉም ላይ ማተኮር አለበት፤
- ወንጀልን ትልልቅ አጥፊዎች ታች ካሉት ጋር ትስስር ፈጥረው ስለሚፈፅሙ ሁሉንም መጠየቁ ተገቢ ነው፤
- ይህ አማራጭ ተመሳሳይ ወንጀሎች እንዳይደገሙ ለማድረግና ለማስተማር ይረዳል፣ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ እድል ይሰጣል፤

- የዕዝ ሰንሰለትን ማስረዳት አስቸጋሪ ነው፣ ብዙ ወንጀሎች አብረው በኖሩ ሰዎች መካከል የተፈፀሙ ናቸው፣ ዋና ፈፃሚውን ከተጠያቂነት ነፃ ማድረግ ቀጣይነት ያለው እርቅ ላይ የተመሰረተ ሰላም ለማምጣት አያስችልም፤
- አንድ ወታደራዊ አዛዥ ማዘዝ የሚችለው ይህን ቦታ እንቆጣጠር በሚል እንጂ ከባድ ወንጀል እንዲፈፅም ብሎ አይደለም፣ ቢኖርም ጥቂት ነው፣ ብዙው ወንጀል የሚፈጸመው ታች ባሉ ወታደሮች ነው፣ አድርግ ሳይባል ወንጀል የሚፈፅመውም ቀላል አይደለም፤
- በትንሹ ጉዳይ ያልተቀጣ ነገ ትልቁን ወንጀል ከመፈፀም ወደኋላ አይልም፤
- ሰዎች ወንጀል ሰርተው ያለመጠየቅ/የማምለጥ እድል የሚሰጣቸው ከሆነ ማህበረሰባዊ አብሮነትን ችግር ውስጥ ይከታል፤
- የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ ሁሉም አጥፊዎች ያለ ልዩነት መከሰስ አለባቸው፣ ሰብአዊ መብቶች እኩልና የማይነጣጠሉ ናቸው፣ ማበላለጥ ሊኖር አይገባም፤
- ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ታስበው/ታቅደው የሚፈፀሙ በመሆናቸው ከተጠያቂነት ውጭ ማድረግ አግባብ አይደለም፤
- ከአመራሩ እኩል አንዳንዴም ከዛ በላይ አሰቃቂ ወንጀሎችን በቀጥታ የፈጸሙ ሰዎች ተጠያቂ ማድረግ ይገባል፤
- በሁሉም ዋና ወንጀሎች የተሳተፈ ማንኛውም ሰው መጠየቅ አለበት፤
- ይህ አማራጭ መንግስት ጉልህ የመብት ጥሰቶችን የመክሰስ ዓለም አቀፍ ግዴታውን እንዲያሟላ ያግዛል፤
- የተጎዱ ሰዎች የእዝ ሰንሰለትን በሚገባ አይረዱም፣ የሚያውቁት ድርጊቱን በቀጥታ የፈፀመባቸውን አካል ነው፣ ፈጻሚዎቹን ሁሉ መክሰስ በተጎጂዎች ዘንድ የፍትህ ስሜት ያሰፍናል፣ እርካታ ይሰጣል፤
- የድርጊት ፈፃሚዎች ለወንጀሎች አስተዋፅኦ አላቸው፣ ተለይተው ለመደበኛው የፍትህ ሥርዓት የሚተው ጉዳይ ካለ የስራ ድግግሞሽን ይፈጥራል፤

ሰንጠረዥ 18፡ 'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' - የከፍተኛ ተቋማት መምህራን ቡድኖች ሀገር-አቀፍ/ክልል ደረጃ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 5 | 5 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | 1 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 1 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | 5 | 2 |
| 9 | ሲዳማ | 0 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 1 | 0 | 1 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 3 | 3 | 0 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 0 | 0 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 4 | 0.5 | 3.5 |
| | ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | 24 | 16.5 | 7.5 |

#### 6.2.2.2.'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጥያቄ ላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 144 ቡድኖች (ወይም 66.66%) የሚሆኑት ከፍተኛ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል።

ቀሪዎቹ 72 ቡድኖች (ወይም 33.34%) ደግሞ በማንኛውም ደረጃ የተሳተፉ አጥፊዎችን ያካተተ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል የሚል ጠንካራ አቋም ይዘዋል።

**ይህ ግኝት ውይይቶቹ ከተካሄዱባቸው ክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች አንጻር ሲተነተን**

ይህ መረጃ ውይይቱ ከተካሄደበት ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር አንጻር ሲተነተን በአፋር፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ብ/ብ/ህ እና ትግራይ ክልል እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር አብዛኞቹ ቡድኖች 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' ብለዋል።

በአንጻሩ አብዛኞቹ በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ቡድኖች እና ሁሉም በሀረሪ ክልል የሚገኙ ቡድኖች 'በማንኛውም ደረጃ ተሳታፊ የሆኑ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የቀረቡት ሁለት አማራጮች እኩል ድጋፍ አግኝተዋል።

**ግኝቱ ከተለያዩ ቡድኖች አንጻር ሲታይ**

ከቡድን አንጻር ሲታይ በአራቱም ሀገራዊ ቡድኖች ማለትም በሴት ተጎጂዎች፣ በወንድ ተጎጂዎች፣ በቅልቅል እና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች አብላጫ ተሳታፊዎች 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር እንደሚገባ' በማመን አማራጭ አንድን ደግፈዋል።

የአዲስ አበባ፣ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ እና የሀረሪ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ደግሞ ሙሉ በሙሉ አማራጭ ሁለትን ደግፈዋል። በአንጻሩ ሁሉም የወንድ ተጎጂ ቡድኖች አማራጭ አንድን ደግፈው አቋማቸውን ገልፀዋል። የጋምቤላ እና የሀረሪ ቅልቅል ቡድኖች፣ እና የሀረሪና የድሬዳዋ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች በተመሳሳይ አማራጭ ሁለትን ደግፈዋል።

የቡድን ምርጫዎችን በክልል ደረጃ ስንመለከት - በዋናነት በሀረሪ ክልል የሚገኙ አራቱም ቡድኖች በተመሳሳይ ሁኔታ አማራጭ ሁለትን ደግፈዋል።

ከወንጀል ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ በትኩረት ቡድን ውይይቶች ላይ ተሳታፊዎቹ ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ ይበጃል ያሉትን አማራጭ ሲጠቁሙ የተለያዩ ነጥቦችን በምክንያትነት አስቀምጠዋል። እነዚህም በሚከተለው መልኩ ተጠቃለው ቀርበዋል።

**ሀ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል (አማራጭ 1)' - ምክንያቶች**

- *ወንጀል በከፍተኛ ደረጃ የሚፈጽሙና ሀገር የሚያምሱት የሀገር አመራሮችን ጨምሮ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች ናቸው፣ ወንጀል የጠነሰሱና አመራር የሚሰጡ ባይኖሩ ጥሰቶች ከጅምሩም አይፈጸሙም ነበር፣ ስለሆነም ችግሩን ከምንጩ ለማድረቅ የክሶቹ ትኩረት ከፍተኛ የተሳትፎ ደረጃ ባላቸው አጥፊዎች ላይ መሆን አለበት፤*
- *ቀስቃሾች ባይኖሩ ፈጻሚዎች አይኖሩም፣ ጥፋቶች በአብዛኛው ስልጣን በሚሹ ሰዎች አቀናባሪነትና መሪነት የተፈፀሙ ናቸው፤*
- *እነዚህ አጥፊዎች ለወንጀሉ ዓላማ ፍላጎት ስላላቸው፣ ለደረሰው ጉዳት መነሻ እና አስፈጻሚ ስለሆኑ፣ ድርጊቱን ስለወጠኑ፣ ግምባር ቀደም ተዋናዮች እና ከዋኞች ስለሆኑ፣ ለራሳቸው ጥቅም በእጃቸው ያለውን*

ሀብት ተጠቅመው ሌሎችን በማነሳሳታቸው፣ በጉዳዩ ላይ ዕውቀት ኖሯቸው፣ አስበውና አቅደው ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት እያወቁ ውጤቱን በመፈለግ ከባድ ጥሰቶችን ስለፈፀሙ የክስ ሂደቱ በነዚህ አካላት ላይ ማተኮር አለበት፤

- በሌሎች ለሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በዋነኝነት ኃላፊነት የሚወስዱና ወንጀሎቹ እንዳይፈጸሙ የማድረግ ኃላፊነት የነበረባቸው እነዚህ ሰዎች ናቸው፤
- የዋነኛ አጥፊዎች ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ከሌሎቹ ፈጻሚዎች ከፍ ያለ ነው፣ ስለሆነም እነሱን መቅጣት ሁሉንም አጥፊዎች እንደመቅጣት ሊቆጠር ይችላል፤
- ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች በሰሜን ኢትዮጵያ ከነበረው ጦርነት ጋር በተያያዘ ለብዙ ሰው ህይወት መጥፋት ምክንያት ናቸው፤
- ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው ባለስልጣኖችን ተጠያቂ ማድረግ ለቀጣይ ሀላፊዎችና አጥፊዎች ትምህርት ይሰጣል፤
- ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ከተከሰሱ ታች ያሉ ወንጀል ፈጻሚዎች አይበዙም፣ እንዲታረሙ እና ተመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ያስተምራል፤
- ዋነኛ አጥፊዎች በመደበኛ የፍትህ ሥርዓት ተጠያቂ የመሆናቸው እድል ዝቅተኛ ስለሆነ በዚህ አማራጭ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ተጠያቂ መሆናቸው ተገቢ ነው፤
- ከከፍተኛ አጥፊዎች መካከል በህዝብ ላይ ጉዳት ለማድረስ ዝተው ጥፋት እንዲፈጸም ትዕዛዝ በሰጡ የጦር እና የፖለቲካ አመራሮች ላይ ትኩረት በመስጠት ተጠያቂነት መመስረት አለበት፤
- በበላይ አካላት ላይ ተጠያቂነት ይሰፈን ሲባል የውጭ አካላትንም ማሳተፍ አለበት፣ በተለያየ አደረጃጀት ስር የሚገኙ አመራሮች ከፍተኛ ሀላፊዎች ባይሆኑም መካተት አለባቸው፤
- ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ተጠያቂ ሳይደረጉ ሌሎች ጥሰት ፈፃሚዎችን መክሰስ ማረሚያ ከማጨናነቅ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም፤
- አውቆ እና በቸልተኝነት ወይም ሳያውቅ ባጠፋው መካከል ልዩነት ማድረግ ፍትሀዊ ነው፤
- ከፍተኛ ደረጃ ካላቸው አጥፊዎች ውጭ ያሉ ጥሰት ፈፃሚዎች ሥራ በማጣት፣ በጥቅም ተታለው፣ በስሜት ተገፋፍተው፣ በውሸት ትርክት ወይም በፕሮፓጋንዳ ተመርተው የሚፈፅሙትን ወንጀል ውጤት በአግባቡ ስለማይረዱ እነሱን ማካተት ተገቢ አይደለም፤
- እነዚህ ሰዎች የዋነኞቹ አጥፊዎች መሳሪያ እና ተላላኪ ስለሆኑ፣ ትዕዛዝ ተቀብለው ያለፈቃዳቸው ወንጀል ስለሚፈጽሙ፣ ትዕዛዝ ካልፈፀሙ እርምጃ ስለሚወሰድባቸው  እነሱን ተጠያቂ ማድረግ ውጤት አያስገኝም፤
- አነስተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸውን ሰዎች ከመክሰስ ይልቅ በማስተማር መመለስ ይቻላል፣ ጉዳዮቻቸውን በቀላሉ በሀገር ሽማግሌዎች፣ በምህረት፣ እንደ ጃርሳ ቢያ ባሉ ባህላዊ ወይም ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች አማካኝነት እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል፣ በርካታ ባህላዊ ሥርዓቶች ያሉ እንደመሆኑ መጠን ሁሉንም ጉዳይ ወደ ክስና ፍርድ ቤቶች ከመውሰድ ይልቅ በአማራጭ ተቋማት ማየት ተገቢ ነው፤
- በሌላ በኩል አንዳንድ ተሳታፊዎች ከከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ካላቸው ሰዎች ውጪ ያሉ አጥፊዎች ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከሀይማኖት ተቋማት፣ ከሴቶች፣ እና ከወጣቶች በተውጣጣ ራሱን የቻለ ተቋም ጉዳያቸውን ማየት አስፈላጊ መሆኑን ሀሳብ አቅርበዋል፤
- ባለፉት ጊዜያት አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በጥሰቶች ተሳታፊ ስለነበር፣ የተፈፀሙ ወንጀሎችና በደሎችም ሰፊ ስለሆኑ ሁሉንም አጥፊዎች ተጠያቂ ማድረግ ሌላ ቀውስ ይዞ ይመጣል፣ ከፍተኛ የሰው ኃይልና ወጪን ይጠይቃል፣ የፍትሕ ሂደቱንም ከባድ እና ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ያደርገዋል፣ ይህም በተራው የፍትህ መጓተትን ያስከትላል፤
- በአንጻሩ ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ማተኮር ጊዜ ይቆጥባል፣ ያለውን ውስን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል፣ ይህም አማራጩን የተሻለ አውድ-ተኮር ያደርገዋል፤

- ከፍተኛ ደረጃ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ለእርቅ እና ሌሎች የሽግግር ፍትህ መንገዶች እድል ይሰጣል፣ የሽግግር ፍትህ ዓላማን ለማሳካት ያግዛል፣ ሰላም እንዲመጣ ያደርጋል፣ ተበዳዮች ቶሎ ፍትህ እንዲያገኙና ቁስላቸው እንዲሽር ያስችላል፤
- ይህ አማራጭ ወንጀልን ለመከላከልና ተመሳሳይ ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ ያስችላል፣ ጥሰቶች እንዳይስፋፋ እና እንዳይበራከቱ ያደርጋል፣ ውጤታማ፣ ተደራሽና የተቀላጠፈ የክስ ሂደት እንዲኖር ያግዛል፤
- ፍትህ እንዲሰፍንና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣ የፍትህ ሥርዓቱ ሊሸከመው በሚችለው ልክ የፍርድ ቤቶችን ጫና በመቀነስ የተፋጠነ ፍትህ እንዲገኝ ያግዛል፤
- ሁሉንም በመክሰስ የሚመጣ ሌላ ቁርሾ ያስቀራል፤
- ለክስ ሂደቱ መረጃና ማስረጃ ለማግኘትና ለማሰባሰብ የተሻለ አካሄድ ነው፤

**ለ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'የወንጀል ክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ውስጥ በተሳተፉ ሰዎች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት** (**አማራጭ** 2) - **ምክንያቶች**


- ጥሰቶች ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን እስካመላከቱ ድረስ በየደረጃው ያሉ አጥፊዎችን ያካተተ የክስ ሂደት መኖር አለበት፤
- በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አንፃር መንግስት ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ዓለምአቀፍ ግዴታ አለበት፤
- ወንጀል እስከተፈፀመ ድረስ በአጥፊዎች መካከል ልዩነት ማድረግ አይገባም፣ ሁሉም በጥፋቱ እና ተሳትፎ ደረጃው ልክ ተጠያቂ መሆን አለበት፤
- ወንጀልን ከግብ የሚያደርሰው የሁሉም ወንጀል ፈጻሚዎች ድምር ተግባር ነው፣ በሀገራችን ለተፈጠረው ቀውስ ከአዛዥና መሪ በላይ አሰቃቂ ወንጀል የፈጸሙትም በአግባቡ ተጠያቂ መሆን አለባቸው፤
- በጥቅም፣ በትእዛዝ፣ በፍርሀት ወይም በሌላ ምክንያት ህገወጥ ትዕዛዝ ተቀብለው ወንጀል የፈፀሙ ሁሉ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፣ የሽግግር ፍትህ ስራ ከወንጀል ሕግ መርሆዎች ጋር መጣጣም አለበት፣ ስለሆነም የበላይ ሀላፊ ትዕዛዝ በመከላከያነት ሊቀርብ አይገባም፣ የታዘዘው ሰውም ቢሆን የተላለፈለት መመርያ ህገወጥ ከሆነ ያለመቀበል መብት አለው፤
- ከፍተኛ ተሳትፎ ከነበራቸው ውጭ ያሉትን የምንተው ከሆነ ነገ ዋና ጠንሳሽ/መሪ ሆነው የሚመጡበት እድል ይፈጠራል፤
- ወንጀልን ከኋላ ሆነው የመሩ እና ያቀዱትን ለመለየት እና ለፍርድ ለማቅረብ ካለው ነባራዊ ችግር አንፃር ሌላ አማራጭ መከተል የሽግግር ፍትህ አሠራርን ከወንጀል የማምለጫ አጋጣሚ እንዲሆን ያደርጋል፤
- በሁሉም አጥፊዎች ላይ ተጠያቂነት የማይሰፍን ከሆን በባህላዊ ሥርዓት መሰረት ደም መመለስና መቃባት ውስጥ ያስገባል፤
- ብዙዎቹ አጥፊዎች ከስር የሚገኙና በህብረተሰቡ የሚታወቁ እንደመሆኑ መጠን ህብረተሰቡ ፍትህ የሚያገኘው እነዚህ አካላት ጭምር ተጠያቂ ሆነው ሲያይ ነው፤
- ተጎጂዎችን ጉዳት የሚያደርስባቸው በእዝ ሰንሰለቱ ታችኛው እርከን ላይ የሚገኝና የሚያውቁት ሰው ነው፣ ድርጊቱን በቀጥታ የፈፀመባቸው ሰው ተጠያቂ ሳይሆን እያዩ አብረው እንዲኖሩ ማድረግ በራሱ እንደተጨማሪ በደል ሊታይ ይችላል፣ ለበቀልና ጥላቻ ያነሳሳል፣ ተጎጂዎች ፍትህን በእጃቸው እንዲያስገቡም ይገፋፋል፤
- ይህ አማራጭ ወንጀል እንዳይስፋፋ ያደርጋል፣ ችግርን ከስር ለመፍታት፣ ወንጀለኞች ተሸሽገው ሌላ ተጨማሪ ዕድል እንዳያገኙ ለማድረግ፣ ህብረተሰቡ አጥፍቶ ሳይማር እንዳይቀር፣ ተደጋጋሚ ጥሰቶች እንዳይፈፀሙ ያደርጋል፤
- ይህ አማራጭ ፍትህ እንዲሰፍን፣ ተበዳዮች ፍትህ እንዲያገኙ ለማድረግና ቁስላቸው እንዲሽር ይረዳል፤
- ማህበረሰቡ ወንጀልን እንዲፀየፍ፣ የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥና ዘላቂነት ያለው ሰላም ለመፍጠር ይረዳል፤

ሰንጠረዥ 19፡ 'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል'- ሀገር-አቀፍ (የአራቱም የትኩረት ውይይት ቡድኖች) ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | 4 | 4 |
| 2 | አፋር | 5 | 5 | 0 |
| 3 | አማራ | 32 | 25 | 7 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 9 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 4 | 1 |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 2 | 3 |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 0 | 4 |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 44 | 18 |
| 9 | ሲዳማ | 4 | 4 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 7 | 4 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 23.5 | 15.5 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | 4 | 4 |
| 13 | ትግራይ | 24 | 12.5 | 11.5 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 216 | 144 | 72 |

ሰንጠረዥ 20፡ 'በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል'፣ ሀገር-አቀፍ (የአራቱም የትኩረት ውይይት ቡድኖች) ማጠቃለያ

| | | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 49 | 29 | 20 |
| 2 | አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 47 | 37 | 10 |
| 3 | አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ | 96 | 61.5 | 34.5 |
| 4 | አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ | 24 | 16.5 | 7.5 |
| | **አገራዊ የአራቱም የትኩረት ቡድኖች ማጠቃለያ** | **216** | **144** | **72** |
| | | | | |




‘በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል’፥ ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

### 6.2.2.3.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች[46] ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

‘በየትኛዎቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል’ ለሚለው ጥያቄ በአብዛኞቹ የሴቶች ብቻ መድረክ ተሳታፊዎች፣ የህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን፣ በወንድና ሴት የሃገር ውስጥ ተፈናቃይ ተጎጂዎች፣ እንዲሁም ከፆታዊ ጥቃት ካገገሙ ሴቶች ጋር በተደረጉ የምክክር መድረኮች የተገኙ ተሳታፊዎች በአብላጫ ድጋፍ ያገኘው ሃሳብ - ትኩረቱ ከፍተኛ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ሊሆን ይገባል የሚለው አማራጭ ነው።

ለዚህም በምክንያትነት ዋናዎቹን ተጠያቂ ማድረግ ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይደገሙ ያደርጋል፣ ነገር ግን ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው ሰዎች ሲመረጡ እንደየደረጃው የነበራቸውን ተሳትፎ ማየት ያስፈልጋል፡ ከፍተኛ ተሳትፎ የሚለው ሀሳብም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ (state and non state actors) የሚሸፍን ስለመሆኑ በፖሊሲው ላይ በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል ብለዋል። የመንግስት አካላት፣ የሚዲያ ተቋማት፣ ለፆታ ጥቃት ሰለባዎች በጊዜ ተገቢውን እርዳታ እና እገዛ ማቅረብ ያልቻሉ ተቋማት አመራሮችን በየደረጃው ተጠያቂ ማድረግ ይገባል የሚል ተጨማሪ ሃሳብ አንስተዋል። የኤርትራ መንግስት ሀይሎች የመብት ጥሰት ጉዳይም በዚህ ማእቀፍ በአግባቡ መካተት እንዳለበት ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን አቅርበዋል።

በሕጻናት ላይ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረክ ቡድኖች፣ የተወሰኑ የሴቶች ብቻ መድረክ ተወካዮች እንዲሁም የተወሰኑ የህጻናት መድረክ ተሳታፊዎች እና አብዛኞቹ የተፈናቃዮች መድረክ የቅልቅል ቡድን ተሳታፊዎች ደግሞ አማራጭ ሁለትን ደግፈዋል። ተሳታፊዎቹ በማንኛውም ደረጃ በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወንጀሎች ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን በማካተት የሚከናወን የክስ ሂደት አማራጭን መከተል ተገቢ ነው፡ ከዛ በኋላ በምህረት ማየት ይቻላል፡ ካሁኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የፈፀሙትን ሁሉ ‘ከፍተኛ ተሳትፎ የላቸውም’ በሚል ብቻ ከወንጀል ተጠያቂነት ውጭ ማድረግ አይገባም፡ ፈፃሚዎችን ሁሉ ተጠያቂ ማድረግ ያስፈልጋል በማለት አስተያየት ሰጥተዋል።

### 6.2.2.4.ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ[47]

---

[46] በዚህ ርእስ ስር - ከህጻናት ፓርላማ ተወካዮች፣ በህጻናት መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ተቋማት ተወካዮች፣ ፆታዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴት ተሳታፊዎች፣ በሴቶች መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች የተወከሉ ተሳታፊዎች፣ የአካል ጉዳት ካለባቸውና ከአረጋውያን ተሳታፊዎች፣ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጋር በተደረጉ የተለያዩ የልዩ ትኩረት የምክክር መድረኮች ማእቀፍ የተሰጡ ግብዓቶች ተጠቃለዋል።

‘በየትኛዎቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል’ በሚለው የፖሊሲ ጥያቄ ላይ ‘በሌሎች ባለድርሻ አካላት’ የቀረቡት አስተያየቶች እና ምክረ-ሃሳቦች - ትኩረት ሊሰጥ የሚገባው ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ ነው፣ እንዲሁም በግጭት እና ጦርነት ወቅት በሚፈጸሙ ጾታን መሰረት ባደረጉ ወንጀሎች እና ወሲባዊ ጥቃቶች ላይ በተሳተፉ ሁሉም ሰዎች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል ብለዋል። ሆኖም የደረሰው የመብት ጥሰት ንብረት ማውደምን የሚመለከት ከሆነ ትኩረቱ ከፍተኛ ተሳትፎና ተጠያቂነት ባላቸው ሰዎች ላይ ብቻ እንዲሆን ሃሳብ ተሰጥቷል።

በሌላ በኩል ውስን ተሳታፊዎች ትእዛዝ ሰጪዎች፣ ኃላፊዎች፣ እና ጠንሳሾች ለተበዳዩ ማህበረሰብ ሩቅ ናቸው፣ የሚታወቁት ፈፃሚዎች እና ትእዛዝ ተቀባዮች ብቻ ስለሆኑ እነዚህን ተጠያቂ ማድረግ ለካሳ እና ለእርቅ ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋል። ዋና ወንጀል ፈፃሚዎች እና ቀጥታ ተሳታፊዎች ሲጠየቁ ተበዳይ እርካታ ይኖረዋል፣ ስለሆነም የወንጀል ተጠያቂነቱ በኃላፊዎች ላይ ብቻ መንጠልጠል የለበትም የሚል ሃሳብ አንስተዋል።

በውስን ተሳታፊዎች ደግሞ ህጻናት መሳሪያ ካነገቡ ሃይሎች ጋር ግንኙነት በሚኖራቸው ጊዜ ሁሉ ሊታዩ የሚገባው እንደተጎጂ (survivors) ነው፣ አያያዛቸውም ከዓለም አቀፍ ሕግ ጋር በተጣጣመ እና ለልጆቹ ጠቃሚ በሆነ መንገድ መሆን አለበት፣ በመብት ጥሰት የተከሰሱ ህጻናት/ወጣቶችም ከአለም አቀፍ ሕጎች በተለይም ከወጣት ጥፋተኞች ደረጃ አኳያ መታየት አለባቸው፣ የህጻናት ልዩ ፍላጎት እና ጥቅም (best interest) መርህም መከበር እንዳለበት ተመላክቷል።

### 6.2.3. የፍርድ ሂደትን ማን ያከናውነው?

#### 6.2.3.1.መግቢያ

የወንጀል ተጠያቂነትን ከመመስረት አንፃር ውይይት የተካሄደበትና ግብዓት የተሰበሰበበት ሌላው መሰረታዊ ጉዳይ ‘ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል’ የሚለውን የሚመለከት ነው።

በዚህ ረገድ በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አማራጮች ሰነድ ላይ ሁለት መነሻ አማራጮች ቀርበዋል።

አማራጭ አንድ ‘በከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውስጥ በብቃት፣ ትምህርት ዝግጅት፣ ልምድ እና ሙያዊ ታማኝነት ላይ የተመሰረተ ተገቢ ልየታ በማድረግና ብቁ የሆኑትን በመመደብ ልዩ ችሎት ማቋቋም፣ ክሶቹን መስማት እና ውሳኔ መስጠት’ የሚል ነው።

ሁለተኛው አማራጭ ‘በህገ መንግስቱ መሰረት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚሰይመው ይግባኝ ሰሚ እና የመጀመሪያ ደረጃ ችሎቶች ያሉበት አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክሶቹን በመስማት ውሳኔ መስጠት’ የሚል ነው።

በዚህ ጥያቄ ላይ ‘216 ሀገራዊ የትኩረት ውይይት ቡድኖች’፣ ‘ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች’፣ እና ‘ሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት’ ውይይት አድርገዋል።

[47] በዚህ ርእስ ስር - የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን በአዲስ አበባ እና አካባቢው በተለያዩ ጊዜያት ከልዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እና አመራሮች፣ ከሃገር ውስጥ ምሁራን፣ ከፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች እና አመራሮች፣ ከሚዲያ ሲቪክ ማህበረሰብ እና ዲሞክራሲ ተቋማት ጋር በተደረጉ የምክክር መድረኮች የተገኙ ግብአቶች፣ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የተመድ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ካውንስል፣ የሰብዓዊ መብት ማዕከል፣ የዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት ግሎባል ክሪሚናል ጀስቲስ ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (NEWA) እና ICTJ ጥምረት ሪፖርት፣ ICTJ፣ እና Commission for the Investigation of Violence in SRS and Reconciliation and Reparation of Victims የቀረቡ የፅሁፍ አስተያየት እና ምክረ-ሀሳቦች ይዘት ተጠቃለው ቀርበዋል።

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ 'በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች'፡ 'ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' እና 'በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል።

### 6.2.3.2.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

#### I. የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች

#### ሀ. በአብዛኛዉ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ፡ 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም'

'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ አማራጭ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች ከተወያዩ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 35.49 ቡድኖች (ወይም 72.44%) የሚሆኑት አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም ይገባል የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ሀሳቦች በምክንያትነት አቅርበዋል።

- አሁን ባለው እይታ ፍርድ ቤቶች የነጻነት፣ ገለልተኝነት እና ተአማኒነት እጦት ችግር አለባቸው፣ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ ህዝቡ ከፍተኛ ቅሬታ ሲያሰማ ቆይቷል፤
- ያሉት ፍርድ ቤቶች ጥሰቶች ሲፈፀሙ የነበሩ፣ ዝም ያሉ ወይም ሀላፊነታቸውን በአግባቡ ያልተወጡ ናቸው፣ በጥሰት የሚጠየቅ ሥርዓት አካል ናቸው፣ ሀላፊነታቸውን በቅጡ ቢወጡ ኖሮ አሁን የሚስተዋለው ቀውስ እዚህ ደረጃ አይደርስም ነበር፤
- የህዝብ አመኔታ በሌላቸው ፍርድ ቤቶች ጉዳይ አይቶ መወሰን ከባድ ጥያቄ ያሥነሳል፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱንም ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም ማህበረሰቡ የሚያምንበትና ፍትህ የሚያገኝበት መድረክ የመሆን እድሉ የሰፋ ነው፤
- በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የሚመሰረቱ ክሶች ከፖለቲካ ገለልተኛ በሆነ፣ አድልዎ በሌለው እና የተሟላ አቅም ባለው ልዩ ፍርድ ቤት ሊታዩ ይገባል፣ በመደበኛ ፍርድ ቤት ከታዩ ለከፍተኛ ባለስልጣኖች ጫና ይጋለጣሉ፤
- አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም የተፋጠነ ፍትህ ለመስጠት ይረዳል፤
- አሁን ላጋጠመው ዘርፈ ብዙ ችግር ያሉት ተቋማት መፍትሄ አያመጡም፤
- ያጋጠሙት ጥሰቶች ልዩ ትኩረትና ጥንቃቄን የሚሹ ናቸው፤
- በሚቀርቡ ውስብስብ ጉዳዮች ላይ በቂ እውቀት ያለው ዳኛ የማይገኝበት ሁኔታ የሰፋ ነው፤
- መደበኛ ፍርድ ቤቶች አሁን ባለባቸው ጫና ላይ ተጨማሪ የሽግግር ፍትህ ሀላፊነት ቢሰጣቸው ስራውን በአግባቡ የሚወጡበት እድል አነስተኛ ነው፣ ስራው በቁጥርም ሆነ በይዘት ከተቋማቱ አቅም በላይ ይሆናል፤
- አዲስ ተቋም ማደራጀት ሰፊ ሀብት የሚጠይቅ ቢሆንም ለፍትህ ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል፤
- ማህበረሰቡ የሚፈልገው አዲስ ፍርድ ቤት ተቋቁሞ ሀገሪቱን በአዲስ መልክ ወደ አዲስ መንገድ የሚወስዳት እንጂ በነባሩ ሥርዓት ለውጥ ለማምጣት መሞከርን አይደለም፤

በተጨማሪም ይህን አማራጭ ከደገፉት ቡድኖች የተወሰኑት አዲስ ፍርድ ቤት ከማቋቋም ባለፈ ዳኞች በህዝብ ተአማኒነት ያላቸው፣ ልምድ ያካበቱ ሊሆኑ እንደሚገባ፣ የፍርድ ሂደቱን ገለልተኛ ሆኖ የሚታዘብ አካል ቢኖርና ህዝቡ ሂደቱን በቀጥታ እንዲከታተለው ቢደረግ የተሻለ እንደሚሆን ገልፀዋል።

#### ለ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በልየታ ላይ የተመሰረተ ልዩ ችሎት ማቋቋም'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ በተካሄደው የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውይይት 8.5 ቡድኖች (ወይም 17.34%) የሚሆኑት ስራው 'በልየታ ላይ የተመሰረተ ልዩ ችሎት በማቋቋም' መከናወን አለበት የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚከተሉትን ሀሳቦች አንስተዋል፡፡

- አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም እጅግ ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል፣ ረጅም ጊዜ ይወስዳል፣ ፍትህን በተፋጠነ ጊዜ ለመስጠት አያስችልም፣ ስለሆነም ያሉትን አጥርቶ መጠቀም የተሻለ ነው፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ይቋቋም ቢባል እንኳ የሚፈለገው ልምድ ያለው ባለሙያ ካሉት ተቋማት ውጭ ከየትም ሊመጣ አይችልም፣ አሁን ባሉት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ዳኞች በቂ ልምድ/ችሎታ አላቸው፣ እነዚህኑ መጠቀም ለስራው ቅልጥፍና ያግዛል፤
- የፍርድ ቤቶችን መሰረታዊ ክፍተት አዲስ ተቋም በመመስረት ሳይሆን የፈጻሚ ዳኞችን ሙያዊ አቅምና ሥነ ምግባር በማሻሻል መሙላት ይቻላል፤
- አሁን ባሉት ፍርድ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች ሕጉን፣ ደንቡንና ሥነ ስርዓቱን በተሻለ ደረጃ ስለሚያውቁ ስራው በነሱ ቢከናወን የተሻለ ውጤታማ ይሆናል፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ቢቋቋም ተቀባይነቱ እና ውጤታማነቱ ገና ያልተረጋገጠ ስለሚሆን ሙሉ ለሙሉ አስተማማኝ አይሆንም፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ያዘገየዋል፤
- የሽግግር ፍትህ ጉዳይ የሚታየው ለተወሰነ ጊዜ ነው፣ ስለሆነም አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም አስፈላጊ እና አዋጪ አይሆንም፤

### ሐ. ጥቂት የሴት ተጎጂ ቡድኖች የደገፉት ሌላ አማራጭ፡ 'ክሶች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ማድረግ'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 5 ቡድኖች (ወይም 10.2%) የፍርድ ሂደቱ 'ገለልተኛ በሆነ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መታየት አለበት' የሚል ሀሳብ አንፀባርቀዋል፡፡ ለዚህ አዲስ አማራጭ የተለያዩ ምክንያቶችን ያቀረቡ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተፈጸመው ድርጊት የዓለማቀፍ ወንጀል ሕግ ጥሰት ስለሆነ በዓለምአቀፍ ፍርድ ቤት መታየት ይገባዋል፤
- በኢትዮጵያ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች (ተቋማት) ለተፈፀሙ ወንጀሎች አስተዋፅኦ ያደረጉ ወይም ተሳታፊ የነበሩ እንደመሆኑ መጠን ትክክለኛ እና ገለልተኛ ውሳኔ ሊሰጡ አይችሉም፣ በወንጀሉ ተሳታፊ የሆነ አካል የወንጀሉን ጉዳይ መልሶ ለማየት ስልጣንም ሆነ ሞራልም አይኖረውም፤
- በሀገር ውስጥ ገለልተኛ ተቋም ይቋቋም ቢባል እንኳን መንግስት ተጠያቂ እንደመሆኑ መጠን በተቋሙ ላይ ተፅእኖ መፍጠሩ አይቀርም፣ ስለሆነም በሀገር ውስጥ ተቋም መታየቱ ትርጉም አይኖረውም፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ይቋቋም ቢባል እንኳን የሚሾሙት ዳኞች ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነጻ ሆነው እንዲሰሩ ማድረግ አይቻልም፣ የዳኞች አኗኗርም ለተጽዕኖ የተጋለጠ ነው፣ ስለሆነም ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቢሆን የተሻለ ነው፤
- በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረውን ጦርነት በማስቆም ረገድ የውጭ ሀገራት አስተዋፅኦ የነበራቸው እንደመሆኑ መጠን የተጠያቂነት ጉዳይም በገለልተኛ ዓለም-አቀፍ ተቋም ሊታይ ይገባል፤

### መ. ውስን ተሳታፊዎች የደገፉት ሌላ/አዲስ አማራጭ፡ 'ቅይጥ ፍርድ ቤት ማቋቋም'

በተወሰኑ ቡድኖች ውስጥ የነበሩ ጥቂት ተሳታፊዎች እንደ ተ.መ.ድ ወይም አፍሪካ ህብረት ያሉ ሶስተኛ አካላትን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ አግባብ ልዩ ፍርድ ቤት ሆኖ ቢቋቋም፣ እንዲሁም ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ባለሙያዎች የተካተቱበት ሆኖ ቢደራጅ የተሻለ ነው የሚለውን አዲስ አማራጭ አቅርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 21፡ 'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' - የሴት ጉዳተኞች ቡድን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ ማጠቃለያ (በቁጥር)

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ (አለም አቀፍ ፍ/ቤት) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | 1 | 1 | |
| 2 | አፋር | 1 | 0 | 1 | |
| 3 | አማራ | 7 | 2 | 5 | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 1 | 1 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 1 | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0.5 | |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 0 | 1 | |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 3 | 11 | |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 0 | 1 | |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 0 | 3 | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 0 | 8 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 1 | 1 | |
| 13 | ትግራይ | 5 | 0 | 1 | 4 |
| | ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | 49 | 8.5 | 35.5 | 5 |

## II. የወንድ ተጎጂ ቡድኖች

### ሀ. በአብዛኛው የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ፡ 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 35.5 ቡድኖች (ወይም 75.53%) የሚሆኑት አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም ያስፈልጋል የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። ምክንያታቸውንም እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- አሁን ያሉት ፍርድ ቤቶች ነጻ እና ገለልተኛ አይደሉም፣ ፍትህ ለማስፈን የሚያስችል በቂ ቁመና የላቸውም፣ የመንግስት/የአስፈፃሚው አካል ተፅዕኖ አለባቸው፤
- ነጻና ገልለተኛ ፍርድ ቤት ማቋቋም ተጎጂዎች/ማህበረሰቡ ፍትህ እንደሚገኝ አምነው እንዲመጡ ይረዳል፣
- አዲስ ፍርድ ቤት ነጻ፣ ገለልተኛ እና ታማኝነት ያለው ተቋም እንዲኖር ያደርጋል፤
- ከችግሩ ግዝፈት፣ ውስብስብነት እና ከተቋማቱ ደካማ አቅም አንጻር፣ እንዲሁም ፍርድ ቤቶች በሙስና እና ትስስር የሚሰሩ በመሆኑ አዲስ ተቋም ያስፈልጋል፤
- ያሉት ፍርድ ቤቶች መደበኛ ስራቸውን በአግባቡ ባላከናወኑበት ሁኔታ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የሚታዩ ከባድና ውስብስብ ወንጀሎችን ለማየት አቅምና ብቃት አይኖራቸውም፣ የህዝብ አመኔታም አያገኙም፤
- አሁን ያሉት ተቋማት እስካሁን በተፈጸሙ ወንጀሎች በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ተሳትፎ ነበራቸው፤
- አሁን ያሉት ፍርድ ቤቶች መንግስትን ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው፡ ፍትህ ሰጪ ተቋማት አይደሉም፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም በህዝብ ተሳትፎ ታማኝና አቅም ያላቸው ዳኞችን ለመምረጥና በተቋሙ ላይ አመኔታ ለመመስረት ያስችላል፤
- የአቅም እጥረት ቢኖርም ከፍትህ የሚበልጥ ጉዳይ ስለማይኖር የተፈለገው ዋጋ ተከፍሎም ቢሆን አዲስ፣ ራሱን የቻለና እራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም ያስፈልጋል፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ቢቋቋም የክስ ሂደቱ እንዲፋጠን ይረዳል፤

- ያሉት ፍርድ ቤቶች በርካታ የዘገዩ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ጉዳዮችን ሲያንከባልሉ፣ ፍትህንም ሲያዛቡ የቆዩ ናቸው፣ ይህም ለወንጀሎች መበራከት እና ፍርድ መጓደል አንዱ ምክንያት ነው፣ ይህ ሁነት ያሉትን ተቋማት ተመራጭ አያደርጋቸውም፤
- ያለፈውን ስንክሳር በአግባቡ ፈትቶ እና ፍትህ አስፍኖ ለመሻገር ከታሰበ ያሉት ብዙ ተቋማት ወደኋላ የሚመልሱ እንጂ ወደፊት የሚያሻግሩ ባለመሆናቸው አዲስ ተቋም ማደራጀት ተመራጭ ነው፤

## ለ. በውሰን የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'በልየታ ላይ የተመሰረተ ልዩ ችሎት ማቋቋም'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች 6.5 ቡድኖች (ወይም 13.82% ) 'በከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውስጥ በብቃት፣ ትምህርት ዝግጅት፣ ልምድ እና ሙያዊ ታማኝነት ላይ የተመሰረተ ተገቢ ልየታ በማድረግና ብቁ የሆኑትን በመመደብ ልዩ ችሎት ማቋቋም፣ ክሶቹን መስማት እና ውሳኔ መስጠት' ይገባል የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። ያቀረቧቸው ዋና ዋና ምክንያቶችም የሚከተሉት ናቸው።

- አዲስ ተቋም መመስረት ጊዜ ይወስዳል፣ ሀገሪቱ ካለችበት የኢኮኖሚ ሁኔታ አንፃርም ያስቸግራል፤
- ሀገሪቱ ያላትን የሰው ሃይልና ጊዜ ለመቆጠብ፣ እንዲሁም ለተበዳዮች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል፤
- አዲስ ተቋም በመመስረት አዳዲስ ባለሙያዎች እንዲመጡ ሲደረግ የልምድ ማነስ ችግር ሊያጋጥም ይችላል፣ ስለሆነም ሲሰሩ የቆዩትን ዳኞች በልዩ ሙያዊ ብቃትና ገለልተኝነትን እንዲሰሩ የሚያደርግ አሰራር በመዘርጋት ክሶች በልዩ ችሎት እንዲታዩ ማድረግ የተሻለ ነው፤
- ዋናው ትኩረት አዲስ ተቋም በመመስረት ላይ ሳይሆን ያሉትን ከመንግስት ተጽዕኖ በማላቀቀ ላይ መሆን አለበት፣ ተቋማቱ ከፖለቲካና ሌሎች ተፅዕኖዎች ነጻ በማድረግ ገለልተኛ ሆነው እንዲሰሩ ተገቢ ልየታ እና ማጥራት በማድረግ ማስተካከል ይቻላል፤
- ዳኞች ተገቢ የልየታ ስራ ተካሂዶ በትምህርት ዝግጅታቸው፣ በሙያዊ ታማኝነታቸው እና በልምዳቸው እስከተመረጡ ድረስ አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም የሚጨምረው ፋይዳ የለም፤
- አሁን ያለው የፍርድ ቤት መዋቅር የተዘረጋ ተቋማዊ አሰራር እና ሥርዓት አለው፣ በቀላሉ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፤
- ምንም እንኳን አሁን ባሉት ፍርድ ቤቶች የወንጀል ተባባሪ የነበሩ ሰዎች ሊኖሩ ቢችሉም በዛው ልክ ሀላፊነታቸውን በሚገባ የሚወጡ ሙያተኞችም አሉ፣ ብቃት እና ታማኝነት ያላቸውን ዳኞች በጥንቃቄ በመምረጥ የክስ ሂደቱን በፍርድ ቤት ውስጥ በሚቋቋም ልዩ ችሎት መስማት የተሻለ ነው፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም ከህገ መንግስቱ አኳያ ብዙ ጥያቄዎችን ያሥነሳል፣ ቢያንስ የሕገ መንግስቱን መሻሻል ይጠይቃል፤
- ገለልተኛ የዲሞክራሲና የፍትህ ተቋማትን ለማጠናከር ልዩ ችሎት በማቋቋም መፈተሽ እንጂ በየጊዜው አዳዲስ ተቋማትን መመስረት ውጤታማ ስራ አይሆንም፤

## ሐ. ጥቂት ቡድኖች የደገፉት ሌላ/አዲስ አማራጭ፣ 'ክሶች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ማድረግ'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 4 ቡድኖች (8.5%) በመነሻ አማራጭነት ከቀረቡት ውጭ የሆነ የራሳቸው አዲስ አማራጭ ያለውን ጠቀሜታ አንስተው ተከራክረዋል። ክሶቹ መታየትና ውሳኔ ማግኘት ያለባቸው በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ነው የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ገለልተኛ እና ነፃ ሆኖ የሚሰራ ተቋም ነው፤
- በሀገሪቱ ያሉ ፍርድ ቤቶች ክሱን ይዩ ቢባል የውጭ ሃይሎች የፈፀሙትን ወንጀል መመልከት የሚችሉበት እድል የለም፤
- ባሉትም ሆነ ልዩ ወይም አዲስ ሆነው በሚቋቋሙ ፍርድ ቤቶች ላይ የህዝብ እምነት የለም፤

- ከጥሰቶቹ ጉልህነት አንጻር የተጠያቂነት ስራውን ገለልተኛነቱ በተረጋገጠ አለም አቀፍ ፍርድ ማከናወን ይገባል፤

**መ. በጥቂት የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ድጋፍ ያገኘ ሌላ/አዲስ አማራጭ፡ 'ቅይጥ ፍርድ ቤት ማቋቋም'**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች 1 ቡድን (2.1%) የክስ ጉዳዮች በኢትዮጵያ እና ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ትብብር በሚቋቋም ልዩ/ጥምር/ቅይጥ ዓለም አቀፋዊ ፍርድ ቤት እንዲታይ ማድረግ ያስፈልጋል በማለት አዲስ አማራጭ አቅርቧዋል። የቅይጥ ፍርድ ቤት ሀሳብ የውጭ ዜግነት ያላቸው ዳኞች ተ.መ.ድበው የሚሰሩበትን ሁኔታ ታሳቢ የሚያደርግ ነው።

ለዚህ ያቀረቡት ምክንያት የሀገር ውስጥ የፍትሕ ተቋማት ነፃነት እና አቅሙ የላቸውም፣ በእስከ ዛሬዎቹ ግጭቶች እና ሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሚና ነበራቸው፡ ስለሆነም ለዚህ ስራ የሚመጥን ቁመና የላቸውም የሚል ነው።

ሰንጠረዥ 22፡ 'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' - የወንድ ጉዳተኞች ቡድኖች ክልል እና ሀገር-አቀፍ ምልከታ ማጠቃለያ (በቁጥር)

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ (አለም አቀፍ ፍ/ቤት) | አዲስ (ቅይጥ ፍ/ቤት) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 | | |
| 2 | አፋር | 1 | 0 | 1 | | |
| 3 | አማራ | 7 | 2 | 5 | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 1 | 1 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 1 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0.5 | | |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 0 | 1 | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 1 | 13 | | |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 0 | 1 | | |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 0 | 3 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 1 | 7 | 1 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 1 | 1 | | |
| 13 | ትግራይ | 5 | 0 | 1 | 3 | 1 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 47 | 6.5 | 35.5 | 4 | 1 |

**III. የቅልቅል ቡድኖች**

**ሀ. አብዛኞዎቹ የቅልቅል ቡድኖች የደገፉት አማራጭ፡ 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም'**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 65.5 ቡድኖች (ወይም 68.2%) የሚሆኑት 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክሶቹን በመስማት ውሳኔ መስጠት' የሚለውን አማራጭ በመደገፍ አቋማቸውን ገልፀዋል። ለዚህም በምክንያትነት የሚከተሉትን መከራከሪያ ነጥቦች አንስተዋል።

- በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚኖረው ተቀባይነት፣ እንዲሁም ከችግሩ ግዝፈት፣ ውስብስብነትና አንገብጋቢነት አንጻር አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክሶቹን መስማት ያስፈልጋል፤
- ገለልተኛ፣ ሁሉንም በእኩል የሚያዩ፣ በመርህ ላይ የተመሰረቱ፣ በሙያ ብቃታቸው ብቻ የተመረጡ ዳኞች እንዲኖሩ ያስችላል፣ ከመንግስት ጋር ንኪኪ ያልነበራቸው ተመልምለው እንዲገቡ ያደርጋል፤
- የፍትህ ሥርዓቱን ተአማኒነትና ገለልተኝነት ያረጋግጣል፤

- በአዲስ መንፈስ በአዲስ አደረጃጀት መምጣት የህዝቡን አመኔታ ለማግኘት ይረዳል፣ አዲስ አስተሳሰብ፣ የሰው ሀይል እና አሰራር ለመዘርጋት ልዩ እድል ይፈጥራል፤
- ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በውጤታማነት ለመስራት ያግዛል፤
- ፍርድ ቤቶች ከፓርቲ እና መንግስት ተፅዕኖ ነጻ አይደሉም፣ በጥቅም የተሳሰሩ ናቸው፣ ሙስናና ብልሹ አሠራር የተንሰራፋባቸው ናቸው፣ ዳኞች በብቃታቸው ሳይሆን በገዢው ፓርቲ ተመልምለው የገቡ ናቸው፣ ፍትህ ያሰፍናሉ ተብሎም አይጠበቅም፣ አዲሱ አደረጃጀት አሁን ባሉት ፍርድ ቤቶች የሚስተዋለውን ችግር ይቀርፋል፤
- ያሉት ፍርድ ቤቶች ፍትህ በተገቢ መጠን አላሰፈኑም፣ በሰብዓዊ መብት ጥሰት ተባባሪነትም ክስ የሚቀርብባቸው ናቸው፣ በፖለቲካ ነክ ወንጀሎች የተጠረጠሩ ሰዎችን ነፃ ናቸው ብለው ከፈረዱ በኋላ እንኳን የተጠርጣሪዎችን የአካል ነፃነትን ማስከበር አይችሉም፤
- ስራ ላይ ያሉት ፍርድ ቤቶች በመደበኛ ስራዎች የተጨናነቁ ናቸው፣ ተጨማሪ ጉዳዮችን ለማየት ይቸገራሉ፤
- የሽግግር ፍትህ ዓላማ ቅራኔዎችን ማስወገድ እስከሆነ ድረስ የክስ ሂደቱ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊካሄድ አይችልም፤
- ያሉት ፍርድ ቤቶች በጣም ወሳኝ የሆነውን የሽግግር ፍትህ ሁነት በስኬት ያስፈፅማሉ ተብሎ አይጠበቅም፤
- የሽግግር ፍትሕ አዲስ ሀሳብ ነው፣ ከመደበኛው የፍርድ ቤቶች አሠራር የተለየ ችሎታ፣ ልምድና ገለልተኝነትን ይጠይቃል፣ ስለሆነም አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም የተሻለ ነው፤
- በሰው ኃይል የተጠናከረና ትኩረቱን ከሽግግር ፍትህ ጋር በተያያዙ የክስ ሂደቶች ላይ ያደረገ አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም ተመራጭ ነው፤

### ለ. ውስን የቅልቅል ቡድኖች የደገፉት አማራጭ፡ 'በልየታ ላይ የተመሰረተ ልዩ ችሎት ማቋቋም'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 24.5 ቡድኖች (ወይም 25.5%) 'በልየታ ላይ የተመሰረተ ልዩ ችሎት ይቋቋም' የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚከተሉትን መከራከሪያ ነጥቦች አንስተዋል፡፡

- የነበሩትን ተቋማት እያፈረስን ሳይሆን እየገነባን ነው መሄድ ያለብን፣ ችግር ያለባቸውን በማስወጣት የተሻሉትንም በመምረጥ ባሉት ፍርድ ቤቶች ውስጥ ልዩ ችሎት በመፍጠር የክስ ሂደቱ ሊከናወን ይገባል፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም ሳያስፈልግ የተሻለ ስልጠና እና እውቀት ያላቸውን በልዩ ችሎት ማደራጀት ይቻላል፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም በራሱ ፍትህን አያመጣም፣ "ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም"፣ ሁሉንም ችግር ይፈታል ማለትም አይቻልም፣ የሚሾሙት ዳኞች አሁን ካሉት ተቋማት የሚወጡ ከሆነ ደግሞ አዲስ ማቋቋሙ ትርጉም የለውም፤
- ዳኞች ከፖለቲካ ነጻ ናቸው ተብሎ ይገመታል፣ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ካለባቸው አዲስ ቢቋቋምም ልዩነት አያመጣም፣ ስለሆነም ትኩረቱ ተቋማቱን ከፖለቲካ ተጽእኖ ነጻና ገለልተኛ በማድረግ፣ በብቃታቸውና ታማኝነታቸው በሚመረጡበት አግባብ ላይ መሆን አለበት፣ በመለየትና በማጥራት ልዩ ችሎት ውስጥ በጥንቃቄ የተመረጡ ሰዎችን ብቻ በመመደብ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት መስራት ይቻላል፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም ጊዜና ሰፊ ሀብት ይፈጃል፣ አሁን ለታሰበው ዓላማም ላይደርስ ይችላል፣ ይቋቋም ቢባል እንኳ መንግስት ያን ለማድረግ ፈቃደኛ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለም፤
- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም የሕገ መንግስት ጥያቄ ማሥነሳቱ አይቀርም፤
- ልዩ ችሎት ማቋቋም ያለውን የሰው ሀይልና አቅም እንድንጠቀም ያስችላል፣ ለተቋም ግንባታም ይረዳል፤

- ይህ አማራጭ የሽግግር ፍትህ ዋና ዋና ጉዳዮችን በልዩ ችሎት በማየት በተቀላጠፈ ሁኔታ የፍርድ ሂደቱን ለማከናወን ይረዳል፤

### ሐ. የተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የደገፉት ሌላ/አዲስ አማራጭ፣ 'ክሶች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ማድረግ'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 3.5 ቡድኖች (3.64%) ክሶቹ በገለልተኛ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መታየት አለባቸው የሚል አማራጭ አቅርበዋል። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶችን የሰጡ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- አዲስ ፍርድ ቤትም ሆነ በልዩ ሁኔታ የሚቋቋሙ ችሎቶች ነፃ እና ገለልተኛ ሊሆኑ፣ ትክክለኛ ፍትህም ሊሰጡ አይችሉም፣
- አዲስ የሚቋቋምም ሆነ ልዩ ፍርድ ቤት በሚባሉ ተቋማት የሚሳተፉ ሰዎች በቀደሙ የወንጀል ድርጊቶች የተነካኩ ናቸው፣
- በሀገር ውስጥ ገለልተኛ ተቋም ይቋቋም ቢባል እንኳ መንግስት ተጠያቂ እንደመሆኑ መጠን በተቋሞቹ ላይ ተፅእኖ መፍጠሩ አይቀርም፣ በመሆኑም ክሱ በሀገር ውስጥ ተቋም መታየቱ ትርጉም አይኖረውም፣
- ተጠያቂነት በተገቢ ደረጃ ሊረጋገጥ የሚችለው ክሱ በገለልተኛ ዓለም አቀፍ ተቋም ሲታይ ነው፣
- ካለው ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ እና ችግር አንጻር ነጻና ገለልተኛ አካል የሚሆነው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ብቻ ነው፣
- በሀገራችን ህዝቦች መካከል መተማመን ስለሌለ ሶስተኛ አካል እንዲዳኝ እድል ሊሰጥ ይገባል፣
- በአመዛኙ የተፈጸመው ዓለም አቀፍ ወንጀል ስለሆነ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መታየት ይኖርበታል፣
- የሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት የውጭ ሀይሎች ተሳታፊ የሆኑበት ጦርነት እንደመሆኑ መጠን ጉዳዮቹ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መታየት አለባቸው፣
- ህዝቡ ባሉት የሀገር ውስጥ ተቋሞች ላይ ዕምነት የለውም፤

### መ. ጥቂት የቅልቅል ቡድኖች እና ተሳታፊዎች የደገፉት አዲስ አማራጭ፡ 'ቅይጥ ፍርድ ቤት ማቋቋም'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች 2.5 ቡድን (2.6%) የክስ ሂደቱን የመስማት እና ውሳኔ የመስጠት ተግባር በቅይጥ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሊከናወን ይገባል የሚለውን አማራጭ ደግፈው ተከራክረዋል። የሚከተሉትን ነጥቦች በምክንያትነት አንስተዋል።

- የክስ ጉዳይን ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች መተው መጓተትን ይፈጥራል፣ የመንግስት ተፅእኖም ከባድ ነው፣
- የሰብዓዊ  መብቶች ጥሰት ጉዳይ በአንድ አካል ብቻ የተፈጸመ ሳይሆን መንግስትም የተነካካበት ነው፣ በዚህ አውድ የሀገር ውስጥ የፍትህ ተቋማት ጉዳዩን ይዩት ቢባል በመንግስት አካላት ላይ ተጠያቂነት የማስፈን አቅማቸው አጠራጣሪ ያደርገዋል፣ በመሆኑም መንግስትን ጨምሮ በተለያዩ ወገኖች ለደረሱ ጥፋቶች ተጠያቂነትን ለመመስረት ቅይጥ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ያስፈልጋል፣
- ስለሆነም ጉልህ የሰብዓዊ  መብት ጥሰቶችን ሊያይ የሚችል ልዩ ቅይጥ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መንግስት ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና ከአፍሪካ ህብረት ጋር በመተባበር መመስረት አለበት።

### ሠ. ውስን ተሳታፊዎች ያነሱት ሀሳብ፡ 'ባህላዊ ሥርዓቶችን መጠቀም'

ጥቂት ተሳታፊዎች ባህላዊ ፍርድ ቤት እና መደበኛ ፍርድ ቤትን በማቀላቀል መጠቀም ይገባል የሚል ሀሳብ አንስተዋል። ምክንያቱ በዝርዝር ባይጠቀስም ባህላዊ ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም በክስ ሂደቱ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሚገባ በጥቂት ተሳታፊዎች ተጠቁሟል።

ሰንጠረዥ 23፡ 'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' - የቅልቅል ቡድኖች ክልል እና ሀገር-አቀፍ ምልከታ ማጠቃለያ (በቁጥር)

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ (አለም አቀፍ ፍ/ቤት) | አዲስ (ቅይጥ ፍ/ቤት) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | 2 | 3 | 1 | |
| 2 | አፋር | 2 | 0 | 2 | | |
| 3 | አማራ | 13 | 2 | 11 | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | 1 | 3 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | 0 | 2 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 1.5 | 0.5 | | |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 0 | 2 | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 10 | 17 | | |
| 9 | ሲዳማ | 2 | 1.5 | 0.5 | | |
| 10 | ሶማሌ | 4 | 1 | 3 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 3 | 15 | | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 2 | 2 | | |
| 13 | ትግራይ | 10 | 0.5 | 4.5 | 2.5 | 2.5 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | **96** | **24.5** | **65.5** | **3.5** | **2.5** |

## IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን

### ሀ. አብዛኛዎቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የደገፉት አማራጭ፡ 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 13.5 ቡድኖች (56.25%) ለተጠያቂነት ሂደቱ አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም ያስፈልጋል የሚለውን አማራጭ መርጠዋል። የሚከተሉትን ሀሳቦች በምክንያትነት አንስተዋል።

- አሁን ያሉት ፍርድ ቤቶች የተዓማኒነት፣ የነጻነትና ገለልተኝነት ችግር አለባቸው፣ የሚሰሩትም በተጽዕኖ ሥር ነው፣ የነዚህን ተቋማት ክፍተት ለማስተካከል ይረዳል፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ጉዳዩን የሚያዩት ባለሙያዎች ከተለያየ ልምድ እና የአገልግሎት ቦታዎች እንዲውጣጡ እድል ይሰጣል፣
- ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ላይ ጫናን ለማስወገድ ይረዳል፣
- መደበኛ ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ጉዳዮች የተጨናነቁ ስለሆነ ተመራጭ አይሆኑም፣
- አማራጩ የክስ ሂደቱን በተለየ መልኩ ለማየትና ገለልተኛነቱ ለማረጋገጥ ይረዳል፣
- ለሽግግር ፍትህ ሂደት ክስ ውጤታማነት የተሻለ አማራጭ ነው፣
- በሽግግር ፍትህ አላባዎችና ዓላማዎች እውቀትና ዝግጁነት ያላቸውን ሰዎች አደራጅቶ የክስ ሂደቱን ለማከናወን ያስችላል፣
- አሁን ባሉት ፍርድ ቤቶች ስር ልዩ ችሎት በማቋቋም መስራት የተለየ ነጻነትን አያስገኝም፣ ቀድሞ የማጥራት ስራ ቢሰራ እንኳ በፍርድ ቤት ላይ ያለው አሉታዊ የህዝብ አመኔታ አይቀንስም፣
- ጉዳዩን በተለየ መልኩ በትኩረት ለማየትና ገለልተኛ፣ ተቀባይነትና ተአማኒነት ያለው የፍትህ ተቋም ለመመስረት ያግዛል፣
- ልዩ ፍርድ ቤቱ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 78(4) መሠረት ሕግን ተከትሎ የሚቋቋም ፍርድ ቤት በመሆኑ የሕገመንግስት ጥያቄ አያስነሳም፣

- ነፃና ገለልተኛ አዲስ ፍርድ ቤት በማቋቋም የሽግግር ፍትህ ጉዳዮች እንዲታዩ ማድረግ የተሻለ ፍትህ የማስገኘት እድል ይፈጥራል፣
- በሽግግር ፍትህ የሚታዩ ጉዳዮች ልዩ እውቀት የሚፈልጉ ጉዳዮች በመሆናቸው በልዩ/አዲስ ፍርድ ቤቶች መታየት ይኖርባቸዋል፤

### ለ. በተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በልየታ ላይ የተመሠረተ ልዩ ችሎት ማቋቋም'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 5.5 (22.91%) የሚሆኑት ልዩ ችሎት በማቋቋም ክሶቹን በመስማት ውሳኔ መስጠት' ያስፈልጋል የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም የሽግግር ሂደቱን ያጓትታል፣ ሀብትና አቅም ይጠይቃል፣ ተግባራዊነቱም አጠራጣሪ ነው፣ በልዩ ችሎት የክስ ሂደቱ ቢታይ የተሻለ ነው፣
- አዲስ የሚቋቋም ተቋም ነጻና ገለልተኛ እንደሚሆን ዋስትና የለም፣ ሀብትና ጊዜ ከማባከን ይልቅ ያሉትን በማስተካከል ልዩ ችሎት ማቋቋም ይመረጣል፣
- የተቋማት ገለልተኝነት እና ነፃነት አዲስ ተቋም በማቋቋም ብቻ ሊመጣ አይችልም፣
- ባሉት ፍርድ ቤቶች ስር ሪፎርም በመስራት፣ ብቁ፣ ነጻና ገለልተኛ ባለሙያዎችን በመመደብ ልዩ ችሎት ማቋቋምና መስራት የተሻለ ውጤት ያስገኛል፣ ከጊዜ እና ከሀብት አንጻርም ተመራጭ ነው፣
- አሁን ባሉ ተቋማት ውስጥ በሙያና በሥነ-ምግባር ብቃት ያላቸው፣ ገለልተኛ የሆኑ፣ የነፃነት ጥያቄ የማይነሳባቸው ሰዎች አሉ፣ ተገቢ የቅድመ ልየታ ስራ በመስራት አዲስ ችሎት መመስረት ይቻላል፣
- አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም ሕገመንግስታዊ ጥያቄ ያሥነሳል፣
- የሽግግር ፍትህ ያስፈለገው በብዙ ቦታዎች ጥሰት በመፈፀሙ ምክንያት እንደመሆኑ መጠን ብዙ ቦታዎችን መዳሰሱ አይቀርም፣ ሆኖም በየቦታው አዳዲስ ፍርድ ቤቶችን ማቋቋም በተጨባጭ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ሀሳብ አይደለም፤

### ሐ. በተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አዲስ አማራጭ፡ 'ቅይጥ ፍርድ ቤት ማቋቋም'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 3.5 ቡድኖች (ወይም 3.64%) የሚሆኑት ከቀረቡት አማራጮች ውጭ አዲስ አማራጭ አቅርበዋል። ኢትዮጵያውያንና የውጭ ዳኞችን የያዘ ቅይጥ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት በማቋቋም የተጠያቂነት ሂደቱ ሊከናወን ይገባል ብለዋል። ምክንያታቸውም እንደሚከተለው ይቀርባል።

- ዳኞች ብቃት ቢኖራቸውም አሁን ያሉት ፍርድ ቤቶች ነጻና ገለልተኛ አይደሉም፣
- ልዩ ፍርድ ቤት ቢቋቋም ብቁ የሰው ኃይል በዘርፉ አይገኝም፣
- ከተአማኒነት አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋም ፍርድ ቤት ተቀባይነት አይኖረውም፣
- በሀገራችን በተፈጸሙ ወንጀሎች ከሀገር ውጪ ያሉ አካላት ተሳትፈዋል፣ አለም አቀፍ ተቋማት ጣልቃ ካልገቡ ተገቢው ፍትህ አይገኝም፣ ይህ አማራጭ ለክስ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣
- አሁን ያሉት ተቋማት በህዝብ ላይ ለተፈጸመ በደል ያደረጉት አስተዋፅኦ የለም፣ ለፖለቲካ ፍጆታ የሚውሉ ናቸው፣
- ራሳችን መርምረንና አጣርተን ራሳችን ፈራጅ ልንሆን አንችልም፣
- የቅይጥ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሀሳብ ከተበዳይ እና ተከሳሽ አንጻር ነፃና ገለልተኛ በመሆን እምነትን ይገዛል፤

**መ. በተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አዲስ አማራጭ፡ 'ክሶች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ማድረግ'**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 1.5 (ወይም 6.25%) የሚሆኑት የተጠያቂነት ሂደቱ መከናወን ያለበት በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት አማካይነት ሊሆን ይገባል በማለት አዲስ አማራጭ አቅርበዋል፡፡ ምክንያታቸውንም እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

- ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ገለልተኛ እና ነፃ ሆኖ ሊሰራ ይችላል፣
- የሀገሪቱ ፍርድ ቤቶች ጉዳዮችን ይዩ ቢባል የውጭ ሃይላት የፈፀሙት ወንጀል ያለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተገቢው ፍትህ አይገኝም፣
- ሀገራዊ ፍርድ ቤቶች የተአማኒነትና ተቀባይነት ችግር አለባቸው፣ ለደረሰው በደል እና ጥሰትም በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ተጠያቂ ናቸው፣
- ሀገራት በራሳቸው ጉዳይ ዳኛ ሊሆኑ አይገባም፤

ሰንጠረዥ 24፡ 'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' - የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ክልል እና ሀገር-አቀፍ ምልከታ ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ (አለም አቀፍ ፍ/ቤት) | አዲስ (ቅይጥ ፍ/ቤት) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 | | |
| 2 | አፋር | 1 | 0 | 1 | | |
| 3 | አማራ | 5 | | 3 | | 2 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | 0 | 1 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 1 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0 | 1 | | |
| 7 | ሀረሪ | 0 | 0 | 0 | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | 1 | 6 | | |
| 9 | ሲዳማ | 0 | 0 | 0 | | |
| 10 | ሶማሌ | 1 | 1 | 0 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 3 | 2.5 | 0.5 | | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 0 | 0 | 0 | | |
| 13 | ትግራይ | 4 | 1 | 0 | 1.5 | 1.5 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 24 | 5.5 | 13.5 | 1.5 | 3.5 |

### 6.2.3.3.'የፍርድ ሂደትን ማን ያከናውነው' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' የሚለውን በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 150 ቡድኖች (ወይም 69.44%) 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም' የተጠያቂነት ሂደቱን ማከናወን ያስፈልጋል የሚል አቋም ይዘዋል፡፡ 45 ቡድኖች (ወይም 20.83%) ደግሞ 'በልየታ ላይ የተመሰረተ ልዩ ችሎት በማቋቋም' ክሶቹን መስማትና ውሳኔ መስጠት ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ 14 ቡድኖች (ወይም 6.48%) የሚሆኑ ቡድኖች ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በመጠቀም ክሶቹን መስማትና ውሳኔ መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ የቀሩት 7 ቡድኖች (ወይም 3.2%) ደግሞ ሌላ አማራጭን አቅርበዋል፡፡

**ማጠቃለያው በክልሎች ደረጃ ሲታይ**

አብዛኞቹ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም' ያስፈልጋል የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል፡፡ ጋምቤላ እና ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል ሁለቱንም አማራጮች እኩል የደገፉ ሲሆን፡ በአንጻሩ በትግራይ ክልል ከነበሩ 24 የትኩረት ውይይት ቡድኖች ውስጥ 16 የሚሆኑት አዲስ አማራጭ አቅርበዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 11 ቡድኖች 'ክሶች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ማድረግ' የሚለውን ሀሳብ የደገፉ ሲሆን፣ የተቀሩት 5 ቡድኖች ደግሞ 'ቅይጥ ፍርድ ቤት ማቋቋም' የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል፡፡

በተመሳሳይ በአማራ ክልል ከነበሩት ውስጥ 2 ቡድኖች፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ከነበሩት ቡድኖች ውስጥ ውስን ተሳታፊዎች 'ቅይጥ ፍርድ ቤት ማቋቋም' የሚለውን የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል፡፡ በአዲስ አበባ ከነበሩት ውስጥ 1 ቡድን፣ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከነበሩት ውስጥ 2 ቡድኖች ደግሞ 'ክሶች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ማድረግ' ያስፈልጋል የሚለውን አማራጭ ደግፈው ተከራክረዋል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ጥቂት ተሳታፊዎች ተጠያቂነትን 'የባህላዊ ሥርዓቶችን በመጠቀም' ማስፈን ይገባል የሚለውን የተለየ ሀሳብ አንስተዋል፡፡

***ግኝቱ በቡድን ደረጃ ሲተነተን***

*ሁሉም ቡድኖች በአብዛኛው አማራጭ ሁለትን መደገፋቸው ታይቷል፡፡*

ከቡድኖቹ የተሰበሰበውን ግብዓት መሰረት በማድረግ የሀገር-አቀፍ ግኝቶች ማጠቃለያ በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

***ሀ. በአራቱም ቡድኖች በሀገር-አቀፍ ደረጃ አብላጫ ድጋፍ ያገኘው አማራጭ፡ 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም'***

'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ከተወያዩ 216 ቡድኖች ውስጥ 150 ቡድኖች 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም' የተጠያቂነት ሂደቱን ማከናወን ያስፈልጋል የሚለውን ሀሳብ ደግፈው ተከራክረዋል፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን ዋና ዋና ምክንያቶች አንስተዋል፡፡

- *አሁን ያሉት ፍርድ ቤቶች የተዓማኒነት፣ የነጻነት እና የገለልተኝነት ችግር አለባቸው፣ የህዝብ አመኔታ ሳይኖራቸው ፍትህን ለማስፈን የሚያስችል በቂ ቁመና ሊኖራቸው አይችልም፣ የመንግስት ተፅዕኖ አለባቸው፣ የሽግግር ፍትህ ክሶች በነሱ ይታይ ቢባል የከፍተኛ ባለስልጣኖች ጫና ይኖራል፣*
- *በተቋሞቹ ውስጥ የትኛውን ያህል የማጥራት ስራ ቢሰራ ህዝቡ በፍርድ ቤት ላይ ያለውን አሉታዊ አመኔታ መቀነስ አይቻልም፣*
- *አሁን ያሉት ፍርድ ቤቶች የሥርዓቱ አካል ናቸው፣ የህዝብ አመኔታ በሌላቸው ተቋማት ከመጠቀም ይልቅ ገለልተኛ፣ ተቀባይነትና ተአማኒነት ያለው ፍትህ የሚገኝበት አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም የሽግግር ፍትህን ከፖለቲካ ገለልተኛ በሆነ እና በማያዳላ፣ ማህበረሰቡም በሚያምንበት አሠራር እንዲከናወን ያስችላል፣*
- *ያሉት ተቋማት በተፈጸሙ ወንጀሎች በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ተሳትፎ ነበራቸው፣ በጥፋቱ ወቅት ተጠያቂነትን አላሰፈኑም፣ ለጥፋቱ የተባባሩ ናቸው፣ ፍትህ ማስፈን ቢችሉ ኖሮ ይህ ቀውስ አይደርስም ነበር፣*
- *የአቅም እጥረት ቢኖርም ከፍትህ የሚበልጥ ነገር ስለሌለ የተፈለገው ዋጋ ተከፍሎ አዲስ ራሱን የቻለ እና እራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም ይገባል፣*
- *ለሽግግር ፍትህ ውጤት ስኬታማነት የፈጀውን ያህል ጊዜ እና ሀብት ቢፈጅ እንኳ አዲስ ፍርድ ቤት በማቋቋም ተጠያቂነትን ማስፈን ይገባል፣*
- *ወንጀሎቹ በጣም ትኩረትና ጥንቃቄን የሚሹ ናቸው፣ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ይህን ጉዳይ ለመሸከም እና ለማሳካት አይችሉም፣*
- *የተፈጸሙት ጥሰቶች በባህሪያቸው በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታዩ የሚገባቸው አይደሉም፣*

- ያሉት ፍርድ ቤቶች በርካታ የዘገዩ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ውሳኔዎች አሏቸው፣ አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም ተደራራቢ የስራ ጫና እንዳይኖር ያደርጋል፣
- የሽግግር ፍትሕ አዲስ ሀሳብ ነው፣ ከመደበኛው የፍርድ ቤት አሠራር የተለየ ችሎታና ልምድን ይጠይቃል፣ ስለሽግግር ፍትህ አላባዎችና ዓላማዎች እውቀት እና ዝግጁነት ያላቸውን ሰዎች በልዩ ፍርድ ቤት አደራጅቶ የክስ ሂደቱን ማከናወን ይገባል፣
- አዲስ የሚቋቋመው ፍርድ ቤት ገለልተኛ አካላትን (ቦርድ፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች ወዘተ በሚያሳትፍ መልኩ)፣ ለህዝብ አስተያየትም ክፍት ሆኖ መሥራት ይኖርበታል፣ ዳኞች በታማኝነታቸው፣ በሥነ ምግባራቸው፣ በብቃታቸው እና ሀገር ወዳድነታቸው የሚለዩ፣ ግልፅ መስፈርት ወጥቶም የሚመረጡ መሆን አለባቸው፣
- የሚቋቋመው አዲስ ተቋም በሙሉ ነጻነት እንዲሰራ ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው፣ የመንግስት አካላትንም ሆነ ግለሰቦችን መቅጣት የሚችል፣ የማህበረሰቡንም እምነት የሚያገኝ ፍርድ ቤት መሆን ይገባዋል፡፡

**ለ. በተወሰኑ ቡድኖች በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተደፈው አማራጭ፡ 'በልየታ ላይ የተመሰረተ ልዩ ችሎት ማቋቋም'**

'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ከተሳተፉ 216 ቡድኖች ውስጥ 45 ቡድኖች የተጠያቂነትን ስራውን 'በልየታ ላይ የተመሰረተ ልዩ ችሎት በማቋቋም' ማካሄድ ይገባል የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶችን አቅርበዋል፡፡

- ሀገሪቱ ካለችበት የኢኮኖሚ ደረጃ አንፃር አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክሶቹን መስማትና ውሳኔ መስጠት ተመራጭ አይደለም፣ ወጪ ይጠይቃል፣ ረጅም ጊዜ ይወስዳል፣ ሰፊ የሰው ሃይል ይፈልጋል፣
- ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም የፍትህ መዘግየት ያመጣል፣ የሽግግር ሂደቱንም ሊያጓትት ይችላል፣
- የነበሩ ተቋማትን እያፈረሱ መሄድ ተገቢ አይደለም፣ አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም በራሱ የተለየ ውጤት አያመጣም፣ ትኩረቱ ያሉትን ፍርድ ቤቶች ከፖለቲካ ተጽእኖ ነጻና ገለልተኛ በማድረግ፣ ዳኞችንም በብቃትና በታማኝነት መስፈርት መምረጥ በሚቻልበት አግባብ ላይ መሆን ይኖርበታል፣
- "ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም"፡ ልዩ/አዲስ ስለተባለ ብቻ ልዩ አይሆንም፣
- ፍርድ ቤቶች ላይ የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ የሚያስፈልገው አዲስ ፍርድ ቤት ማቋቋም ሳይሆን የሚፈለገውን የሰው ኃይል በልዩ ችሎት ማደራጀት ነው፣
- አዲስ ተቋም መስርቶ አዳዲስ ባለሙያዎች ማምጣት ቢፈለግ የልምድ ማነስ ሊያጋጥም ይችላል፣ ስለሆነም ባሉት ፍርድ ቤቶች ውስጥ ሲሰሩ የቆዩትን ዳኞች መመዘኛ አውጥቶ በመምረጥ በልዩ ችሎት አማካኝነት ክሶች እንዲታዩ ማድረግ የተሻለ ነው፣
- ልዩ ፍርድ ቤትን ማቋቋም ከህገ መንግስቱ አኳያ ብዙ ጥያቄዎችን ያሥነሳል፡፡

**ሐ. በጥቂት ቡድኖች በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተደገፈ ሌላ/አዲስ አማራጭ፡ 'ክሶች በዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ማድረግ'**

'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ ከተሳተፉ 216 ቡድኖች ውስጥ 14 ቡድኖች 'ክሶች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲታዩ የማድረግ' አማራጭን ደግፈው ቀርበዋል፡፡ ምክንያታቸውንም እንደሚከተለው ሰጥተዋል፡፡

- አዲስ የሚቋቋምም ሆነ ልዩ ችሎት በጥሰት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት አካላትን/ሰዎችን የሚያካትቱ ናቸው፣ በተፈፀሙ ወንጀሎች ጉልህ ኣስተዋፅኦ ያደረጉ፣ ደጋፊ የነበሩ ሰዎች/አካላት ገለልተኛ ውሳኔ ሊሰጡ ኣይችሉም፣
- ካለው ነባራዊ ሁኔታ እና ችግር አንጻር ነጻና ገለልተኛ አካል ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ብቻ ነው፣ በህዝብ መካከል መተማመን ስለሌለ ሶስተኛ አካል ሊዳኝ ይገባል፣
- የተፈጸመው ዓለም አቀፍ ወንጀል ነው፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ደግሞ የውጭ ሀይሎች ተሳትፈዋል፣ ስለዚህም ክሶቹ ነጻና ገለልተኛ በሆነ ተቋም መታየት ይኖርባቸዋል፣ በዚህ ረገድ ልዩ ችሎትም ሆነ አዲስ የሚቋቋም ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍትህ ሊሰጡ ኣይችሉም፣
- የሀገር ውስጥ ገለልተኛ ተቋም ይቋቋም ቢባል እንኳን የመንግስት አካላት ተጠያቂ ሊሆኑ ስለሚችሉ ተፅእኖ መፍጠራቸው አይቀርም፣ ስለሆነም በሀገር ውስጥ ተቋም መታየቱ ትርጉም ኣይኖረውም፣
- አዲስ ፍርድ ቤት ቢመሰረትም የሚሾሙት ዳኞች ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነጻ ሆነው እንዲሰሩ ማድረግ አይቻልም።

### መ. በጥቂት ቡድኖች በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተደገፈ ሌላ/አዲስ አማራጭ፡ 'ቅይጥ ፍርድ ቤት ማቋቋም'

'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በተወሰኑ ቡድኖች እና ጥቂት ተሳታፊዎች የቀረበው አዲስ ሀሳብ እንደ ተ.መ.ድ እና አፍሪካ ህብረት ያሉ ሶስተኛ ወገኖች ተሳትፎን በሚያረጋግጥ አግባብ ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገራት ባለሙያዎች የሚካተቱበት ልዩ ቅይጥ ፍርድ ቤት ማቋቋም ያስፈልጋል የሚል ነው። በምክንያትነትም የሚከተሉትን ነጥቦች አንስተዋል።

- የሀገር ውስጥ የፍትሕ ተቋማት ነፃነት እና ዐቅም የላቸውም፣ በነበሩት ግጭቶችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችም ሚና ነበራቸው፣
- የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በአንድ አካል ብቻ የተፈጸሙ አይደሉም፣ የመንግስት አካላትንም ያካትታሉ፣ በዚህ አውድ ለተፈፀሙ ወንጀሎች የሀገር ውስጥ የፍትህ ተቋማት ክሶችን ይዩ ቢባል በመንግስት አካላት አንፃር ተጠያቂነት የማስፈኑን ስራ አጠራጣሪ ያደርገዋል፣
- የሀገር ውስጥ ተቋማት የመንግስት ተፅእኖ አለባቸው፣ ዳኞች ብቃት ቢኖራቸው እንኳ ነጻና ገለልተኛ አይሆኑም፣
- ከተአማኒነት አንጻር ሀገር ውስጥ የሚቋቋም ፍርድ ቤት ተቀባይነት አይኖረውም፣
- በተፈጸሙ ወንጀሎች የውጭ ሀገር ሀይሎች ተሳትፈዋል፣ አለምአቀፋዊ ይዘት ያላቸው ተቋማት ካልተካተቱ ተገቢ ፍትህ አይገኝም፣
- ቅይጥ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ከተበዳይም ሆነ ከተከሳሽ አንጻር ነፃና ገለልተኛ ነው፡ የተሻለ እምነት ይጣልበታል፣
- ልዩ ችሎት ወይም አዲስ ፍርድ ቤት ቢቋቋም በዘርፉ ብቁ የሰው ኃይል አይገኝም፣
- ሀላፊነቱ ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ቢሰጥ መጓተት እና የፍትህ መጓደልን ያመጣል።

### ሠ. ጥቂት ተሳታፊዎች ያነሱት ሀሳብ፡ 'ባህላዊ ስርአቶችን መጠቀም'


'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ ጥቂት ተሳታፊዎች የባህላዊ ፍርድ ቤትና እና መደበኛ ፍርድ ቤትን አቀላቅለን መጠቀም ይገባል በማለት አዲስ ሀሳብ አንስተዋል። ባህላዊ ፍርድ ቤቶችን ማቋቋም፣ እንዲሁም በክስ ሂደቱ ላይ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ሰንጠረዥ 25፡ 'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' - የሁሉም ቡድኖች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ (አለም አቀፍ ፍ/ቤት) | አዲስ (ቅይጥ ፍ/ቤት) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | 3 | 4 | 1 | |
| 2 | አፋር | 5 | 0 | 5 | | |
| 3 | አማራ | 32 | 6 | 24 | | 2 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 3 | 6 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 0 | 5 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 2.5 | 2.5 | | |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 0 | 4 | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 15 | 47 | | |
| 9 | ሲዳማ | 4 | 1.5 | 2.5 | | |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 2 | 9 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 6.5 | 30.5 | 2 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | 4 | 4 | | |
| 13 | ትግራይ | 24 | 1.5 | 6.5 | 11 | 5 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | **216** | **45** | **150** | **14** | **7** |

ሰንጠረዥ 26፡ 'ክሶችን ከመስማት እና ውሳኔ ከመስጠት ጋር የሚያያዘው የሽግግር ፍትህ አንኳር ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል' - ሀገር-አቀፍ የአራቱም ቡድኖች ማጠቃለያ

| | | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ (አለም-አቀፍ ፍርድ ቤት) | አዲስ (ቅይጥ ፍ/ቤት) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 49 | 8.5 | 35.5 | 5 | |
| 2 | ሀገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 47 | 6.5 | 35.5 | 4 | 1 |
| 3 | ሀገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ | 96 | 24.5 | 65.5 | 3.5 | 2.5 |
| 4 | ሀገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ | 24 | 5.5 | 13.5 | 1.5 | 3.5 |
| | **ሀገራዊ የአራቱም የትኩረት ቡድኖች ማጠቃለያ** | **216** | **45** | **150** | **14** | **7** |
| | | | | | | |




***'ክሶችን በየትኛው የፍርድ ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ሊታዩ ይገባል' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ***

### 6.2.3.4.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ[48]

**በእነዚህ መድረኮች - አብዛኛው የሴቶች ብቻ መድረክ ተሳታፊዎች፣ አካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን፣ የህጻናት መብት ተወካዮች፡ እና የሃገር ውስጥ ተፈናቃይ የሴት ቡድኖች፡ የተወሰኑ የወንድ እና የቅልቅል ቡድን ተሳታፊዎች 'አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም' የተጠያቂነት ሂደቱን ማከናወን ያስፈልጋል የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል።**

**ለዚህ የሰጡት ምክንያት፡**

- **አሁን ያሉት ፍርድ ቤቶች ብዙ ጥቃት ሲፈፀም የነበሩ፣ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የስርአቱ ተሳታፊ የሆኑ፡ ያዩ ወይም የደገፉ በመሆኑ መፍትሄ ይሰጣሉ ተብሎ አይታመንም፣**
- **ከፍ ያለ የተአማኒነት የገለልተኝነት እና የቅቡልነት ጥያቄ የሚነሳባቸው ናቸው፣ በሙስናም የተዘፈቁ በመሆኑ ምንም ቢሻሻሉ እንኳ ይህን እይታ በቀላሉ መቀየር አይቻልም፣**
- **በመሆኑም እነዚህን ተቋማት መጠቀም ለሽግግር ፍትህ ትግበራ እንቅፋት ስለሚፈጥር ሌላው አማራጭ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፣**
- **በተጨማሪም ራሱን የቻለ አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም የአካል ጉዳተኞችን እና የሥነ-ፆታ ክፍተቶችን ባሟላ መልኩ ለማደራጀት የተሻለ እድል ይፈጥራል የሚል ነው።**

**ይህንን አማራጭ መደገፋቸውን ተከትሎ ተጨማሪ ምክረ ሃሳቦች የሰጡ ሲሆን እነዚህም፡-**

- **የተቋሙ ነፃነት እና ተቀባይነት ጉዳይ ከዚህ ጋር በቀጥታ የተያያዘ በመሆኑ ገለልተኛ ተቋም በመመስረት ሂደት አስፈጻሚው አካል ተሳትፎ ሊኖረው አይገባም፣ በተለይም የዳኞች መረጣ ሂደት እና የአሰራር ስርአቱ አደረጃጀት ሙሉ ለሙሉ በገለልተኛ አካል መከናወን አለበት፣**
- **የዳኞች አቅም ግንባታም መሰረታዊ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፣**

[48] በዚህ ርእስ ስር - ከህጻናት ፓርላማ ተወካዮች፣ በህጻናት መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ተቋማት ተወካዮች፣ ፆታዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴት ተሳታፊዎች፣ በሴቶች መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች የተወከሉ ተሳታፊዎች፣ የአካል ጉዳት ካለባቸውና ከአረጋውያን ተሳታፊዎች፣ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጋር በተደረጉ የተለያዩ የልዩ ትኩረት የምክክር መድረኮች ማእቀፍ የተሰጡ ግብዓቶች ተጠቃለዋል።

- በይግባኝ ስርአቱ አደረጃጀት/ሂደት ላይም ቢያንስ የአፍሪካ ተቋማትን ማካተት እና መተግበር ያስፈልጋል የሚሉ ናቸው።

በሌላ በኩል አብዛኛው የህጻናት ፓርላማ ተወካይ ህጻናት እንዲሁም የተወሰኑ የተፈናቃይ ወንዶች እና የቅልቅል ቡድን አባላት፣ የሴቶች ብቻ መድረክ ተሳታፊዎች እና የህጻናት መብት ተወካይ ተሳታፊዎች የተጠያቂነት ስራውን 'በልየታ ላይ የተመሰረተ ልዩ ችሎት በማቋቋም' ማካሄድ ይገባል የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል። በምክንያትነትም የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።

- አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት ቢቋቋም የተለየ ነገር ያመጣል ተብሎ አይጠበቅም፣
- አሁን ካለው የሰው ሀይል ስብስብ ውጭ ልምድ ያለው ባለሙያ በማግኘት ረገድ ተግዳሮት ያጋጥመዋል፣
- ከጊዜና ከወጪ አንፃርም ልዩ ችሎት ይሻላል ነገር ግን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ቢካተቱበት ጥሩ ይሆናል፣
- ሌላው አማራጭ የህገ-መንግስት ማሻሻያ ስራን ስለሚጠይቅ እና ተግባራዊ ማድረግ ስለሚያስቸግር የሚደገፍ አይሆንም።

በተጨማሪም ውስን የህጻናት መብት ተወካዮች፣ በተወሰኑ የተፈናቃይ የወንዶች እና የቅልቅል ቡድኖች ተሳታፊዎች እና በሴቶች ብቻ መድረኮች ላይ የነበሩ ተሳታፊዎች አዳዲስ አማራጮችን አቅርበዋል።

አንዱ ቅይጥ ፍርድ ቤት (የሀገራዊ እና አለማቀፋዊ ውህድ) የሆነ ፍርድ ቤት ማቋቋምን የተመለከተ ሲሆን ይህ አደረጃጀት ከፍተኛ ተአማኒነትን ለማምጣት እንደ አማራጭ ማየት ያስፈልጋል፣ ይህ ከሆነ የአሸናፊዎች ፍትህ እንዳይሆን ያደርጋል በማለት ሀሳብ ሰጥተዋል።

የተወሰኑ ተሳታፊዎች ደግሞ አለም-አቀፍ ፍርድ ቤትን መጠቀም ያስፈልጋል ያሉ ሲሆን ለዚህም በምክንያትነት በሰሜኑ ጦርነት የውጭ አካል ጣልቃ የገባ በመሆኑ፣ በፍርድ ሂደቱ ነጻ ገለልተኛ እና ፍትሀዊ ውሳኔን ለማግኘት እንዲቻል፣ እንዲሁም በስራ ላይ ያሉ የፍትህ ተቋማት በጦርነቱ ሂደት የተሳተፉ በመሆኑ በራሳቸው ጉዳይ ዳኛ ሊሆኑ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል። የመንግስት ከፍተኛ አመራር እና የኤርትራ ሀይሎች ጉዳይ በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቢታይ፣ ሌሎች ጉዳዮች በልዩ ፍርድ ቤት ቢስተናገዱ ትክክለኛ ፍትህ ለማስፈን ይረዳል የሚል ተጨማሪ አማራጭ ሀሳብ አቅርበዋል።

በሌላ በኩል ባህላዊ የፍትህ ተቋማት ተጠያቂነትን ከማስፈን አንጻር በጥንቃቄ የሚለይ እና ከሴቶች መብት ጋር ተጣጥሞ የሚተገበር ሚና ኖሯቸው ውስን ጉዳዮችን እንዲያዩ ቢደረግ ጠቃሚ ነው የሚል ተጨማሪ ሃሳብም በጥቂት ተሳታፊዎች ተሰጥቷል።

### 6.2.3.5.ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ[49]

ክሶችን የሚያዩ ፍርድ ቤቶችን በሚመለከት የቀረቡት ምክረ-ሃሳቦች በጥቅሉ ሲታዩ ነባር ተቋማትን መጠቀም ያለው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ግልጽ ቢሆንም ተቋማቱን እንጠቀም ከተባለ የፍትህ ስርአቱን ተቀባይነትና ተአማኒነት ለማረጋገጥ እንዲቻል የተቋማቱን ነፃነት መመስረት፡ በተለይም የተቋማቱ ባለሙያዎች ያላቸው ብቃት፣ ቁርጠኝነት፣

---

[49] በዚህ ርእስ ስር - የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን በአዲስ አበባ እና አካባቢው በተለያዩ ጊዜያት ከልዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እና አመራሮች፣ ከሃገር ውስጥ ምሁራን፣ ከፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች እና አመራሮች፣ ከሚዲያ ሲቪክ ማህበረሰብ እና ዲሞክራሲ ተቋማት ጋር በተደረጉ የምክክር መድረኮች የተገኙ ግብአቶች፡ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የተመድ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ካውንስል፣ የሰብዓዊ መብት ማዕከል፣ የዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት ግሎባል ክሪሚናል ጀስቲስ ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (NEWA) እና ICTJ ጥምረት ሪፖርት፣ ICTJ፣ እና Commission for the Investigation of Violence in SRS and Reconciliation and Reparation of Victims የቀረቡ የፅሁፍ አስተያየት እና ምክረ-ሀሳቦች ይዘት ተጠቃለው ቀርበዋል።

ነፃነት እና የወንጀል ሰለባዎችን እና ሌሎች ለፍትህ መስፈን አስፈላጊ የሆኑ አካላትን አሳታፊነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡ ለዚህም የሕግ የተቋማት ማሻሻያ ስራ ማካሄድ ይገባል የሚል ነው።

የተቋማት ማሻሻያ በአጠቃላይ የፍትህ ስርአቱ ላይ የረጅም ጊዜ ተጽእኖ ስላለው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ማሻሻያው የጾታ እኩልነትን በሁሉም ደረጃ በማገናዘብ ለወደፊት አካታች የፍትህ ሥርዓት ለመገንባት ይረዳል። ይህን ወደ ተግባር በማምጣት ማእቀፍ ለግጭት ተጎጂዎች በተለይም ለጾታ እና ጾታ ተኮር ሰለባዎች ፍትህን ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል ተንቀሳቃሽ ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ ወይም የፍርድ ቤቶች ቁጥር እንዲጨምር፡ ተጎጂዎችን ማዕከል ያደረገ አካሄድ ለመተግበር የሚያስችል የሴቶች እና ህጻናት ልዩ ችሎቶች እንዲመሰረቱ፡ እንዲሁም ለደህንነት እና ፍትህ ተቋማት ሀላፊዎች ልዩ ስልጠና እና የአቅም ግንባታ ስራ እንዲሰጥ ማድረግ ይገባል የሚሉ ምክረ-ሀሳቦችን አቅርበዋል።

በሌላ በኩል ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኞች እና አመራር ጋር በተደረገው ምክክር ላይ ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም አማራጭ ሊሆን አይገባም፡ የተጠያቂነት ሂደቱ በከፍተኛ እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ውስጥ ተገቢ ልየታ በማድረግ እና ልዩ ችሎት በማቋቋም ቢፈፀም ይሻላል የሚል አስተያየት የቀረበ ሲሆን በምክንያትነትም፡

- በህገ መንግስቱ የተቋቋመ የዳኝነት አካል ይህ ፍርድ ቤት በመሆኑ የተጠያቂነት ስራን ህገ መንግስቱን ባከበረ መልኩ ለመተግበር ይረዳል፡
- አሁን ያለውን ፍርድ ቤትን በማጠናከር የህዝብ አመኔታ እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል፡
- ዳኞች በብቃት፡ በትምህርት ዝግጅት፡ በልምድ፡ በሥነ ምግባር፡ በሙያዊ ታማኝነት፡ እና በብቃት ተለይተው ቢመደቡ በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የሚታሰበውን አላማ ለማሳካት ያስችላል የሚል ሃሳብ አቅርበዋል።

በሌላ በኩል ከሀገር ውስጥ ፍርድ ቤቶች በተጨማሪ የውጭ አካላትን ያካተተ ቅይጥ ፍርድ ቤት እንዲሁም አለም አቀፍ የወንጀል ችሎት ማቋቋም እንደ አማራጭ እንዲታዩ በጥቂት የባለድርሻ አካላት ተሳታፊዎች ምክረ ሃሳብ ቀርቧል። በምክንያትነትም በሌሎች አገሮች ውጤታማነቱ ስለታየ ለኢትዮጵያም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡ የባለሙያዎችን አቅም ያጎለብታል፡ ስለ ግጭትና ተፈጻሚ ሕጎች የሚያውቁ ባለሙያዎች ጉዳዩን እንዲይዙ ያስችላል፡ በአማካሪ ደረጃም ቢሆን አለም አቀፍ ባለሙያዎች በችሎቶቹ ውስጥ መካተታቸው ለአንዳንድ ተበዳዮች ምቾት ይሰጣል፡ የገለልተኝነት እና ተቀባይነት ችግሮችንም ይፈታል የሚሉ መከራከሪያዎች ተጠቅሰዋል።

### 6.2.4. የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?

#### 6.2.4.1.መግቢያ

የወንጀል ተጠያቂነትን ከመመስረት ጋር በተያያዘ ውይይት የተካሄደበት እና ግብዓት የተሰበሰበበት ሌላው ጉዳይ 'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚል ነው። በዚህ ጥያቄ አንፃር ሁለት የውይይት መነሻ አማራጮች ቀርበዋል።

አማራጭ አንድ 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ በምርመራ እና ክስ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን ማዋቀር' የሚል ሲሆን፣ አማራጭ ሁለት ደግሞ 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋም ውጭ ሌላ የምርመራና ክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር (አዲስ) የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን መመደብ' የሚል ነው።

በዚህ ጥያቄ ላይ '216 ሀገራዊ የትኩረት ውይይት ቡድኖች'፡ 'ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች'፡ እና 'ሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት' ውይይት አድርገዋል።

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ 'በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች'፡ 'ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' እና

'በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል።

#### 6.2.4.2.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

**I. የሴት ተጎጂዎች ቡድን**

***ሀ. በአብላጫው የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር (አዲስ) የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን መመደብ' (አማራጭ 2)***

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 38 ቡድኖች (77.55%) የሚሆኑት 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ' መከናወን አለበት የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶችን የሰጡ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- *ያሉት ተቋማት የህዝብ እምነት የሚጣልባቸው አይደሉም፣ የሽግግር ፍትህ ሂደት አንዱ ዓላማ ችግር ያለባቸውን ተቋማት በመተው የተሻሉ ተቋማትን መፍጠር ነው፣ ስለሆነም የምርመራና ክስ ሂደቱ ነፃ እና ገለልተኛ በሆነ አዲስ ተቋም ሊተገበር ይገባል፣*
- *ያሉት ተቋማት ሰብአዊ መብትን የሚያስከብሩ ሳይሆኑ ዋነኞቹ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና ረገጣ ፈፃሚዎች ናቸው፣ ገለልተኛ እና ነፃ አይደሉም፣ በብልሹ አሰራርና ሙስና ተዘፍቀዋል፣ ህብረተሰቡ ተማሮባቸዋል፣ አዲስ ተቋም ማቋቋም የምርመራና የክስ ሂደቱን ገለልተኛ፣ ነጻ፣ ከሙስና የጸዳ እና ታማኝነት ያለው እንዲሆን ያደርገዋል፣*
- *ምርመራ ከማድረግ እና ክስ ከመመስረት ባለፈ ጥሰት የፈፀሙ ወንጀለኞችን ለመለየትና ለሕግ ለማቅረብ የሚያስችል ቁመና ያለው፣ የጥቅም ግጭት የሌለበት፣ ከፖለቲከኞች ጫና የፀዳ አዲስ እና ገለልተኛ ተቋም ያስፈልጋል፣*
- *ከብቃትና አቅም አንጻር ያሉት ተቋማት በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የሚሰራን ይህን ውስብስብ ስራ ለማከናወን ያስቸግራቸዋል፣*
- *ያሉትን ተቋማት መጠቀም በመደበኛ የፍትህ ስርአቱ ላይ አላስፈላጊ ጫና ይፈጥራል፣*
- *የአዲስ ተቋም ግንባታ ገንዘብ የሚፈጅ ቢሆንም ቅድሚያ ለፍትህ መሰጠት አለበት፣*
- *ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ እውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን በመመልመል አዲስ ተቋም ማቋቋም በራሱ ነጻና ገልለተኛ የመሆን አወንታዊ እይታን ይፈጥራል።*

***ለ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ በክስ እና ምርመራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን ማዋቀር' (አማራጭ 1)***

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 7 ቡድኖች (14.3%) የሚሆኑት 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ በምርመራ እና ክስ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር' መከናወን አለበት የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶችን የሰጡ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- *አዲስ ተቋም ለማዋቀር ጊዜ ይወስዳል፣ በመሆኑም ባሉት ተቋማት ውስጥ በልዩ የምልመላ መስፈርት/ልየታ መሰረት ቡድን በመመስረት ቢሰራ ጉዳዮችን በፍጥነት ለማየትና የተቀላጠፈ ፍትህ ለማስፈን ይረዳል፣*

- አዲስ ተቋም ከፍተኛ የሀገር ሀብት ይበላል፣ ጊዜ ይወስዳል፣ ለመንግስት ጣልቃ ገብነት የተጋለጠ መሆኑም አይቀርም፣ ተጨማሪ ወጪ አውጥቶ አዲስ ከማቋቋም ያሉትን ማጠናከርና መጠቀም ተመራጭ ነው፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ሂደቱን ሊያጎትተው ይችላል፣
- ባሉት ተቋማት ውስጥ በሥራቸው፣ በልምዳቸው፣ በታማኝነታቸው እና በትምህርት ደረጃቸው የተሻሉ ፖሊሶች/ዓቃቤ ሕጎች አሉ፣ አዲስ ከሚገቡት የተሻለ የምርመራና ክስ የመመስረት ልምድ አላቸው፣ ስለሆነም ትኩረቱ በተገቢ ልየታ ላይ መሆን አለበት፣
- ልዩ ዓቃቤ ሕግ ማቋቋም የስልጣን ሽኩቻ ያስከትላል።

**ሐ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አዲስ አማራጭ፣ 'ልዩ ዓለምአቀፍ ተቋም'**

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 4 ቡድኖች (ወይም 8.2%) የሚሆኑት የክስ ሂደቱን የሚሰማ ልዩ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እና የምርመራ እና የክስ ሂደቶችን የሚያከናውን ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋም መመስረት አለበት ብለዋል። ለዚህ አማራጭ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- የተፈጸመው ዓለምአቀፍ ወንጀል ነው፣
- የኢትዮጵያ የፍትህ ተቋማት በትግራይ ክልል ለተፈፀመ ወንጀል ጉልህ ኣስተዋፅኦ አድርገዋል፣ በጦርነቱ ተሳታፊ/ደጋፊ የነበረ አካል ትክክለኛ እና ገለልተኛ ውሳኔ ሊሰጥ ኣይችልም፣
- ገለልተኛ የሀገር ውስጥ ተቋም ይቋቋም ቢባል እንኳን የመንግስት አካላት ተጠያቂ እንደመሆናቸው መጠን መንግስት በተቋሙ ላይ ተፅእኖ መፍጠሩ አይቀርም፣
- ጦርነቱን እንዲቀም ያደረጉ የተለያዩ የውጭ ሀገራት አሉ፤ ስለሆነም የተጠያቂነት ስራ በገለልተኛ ዓለም አቀፋዊ ተቋም መከናወን አለበት።

ሰንጠረዥ 27፡ 'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' - የሴት ጉዳተኛ ቡድኖች ሀገር-አቀፍ/ክልል ደረጃ ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | 0 | 2 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 1 | 6 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 0 | 2 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0.5 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 0.5 | 0.5 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 3 | 11 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 0 | 3 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 0 | 9 | 0 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 0 | 2 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 0 | 1 | 4 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 49 | 7 | 38 | 4 |

## II. የወንድ ተጎጂዎች ቡድን

### ሀ. በአብላጫው የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን መመደብ' (አማራጭ 2)

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 35 ቡድኖች (ወይም 74.5%) የሚሆኑት ስራው 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም እና የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ' ቢከናወን ተመራጭ ነው ሲሉ አቋማቸውን ገልፀዋል። በምክንያትነትም የሚከተሉትን ነጥቦች አቅርበዋል።

- ይህ አማራጭ ተቋማዊ ነጻነቱን የጠበቀ ገለልተኛ እና ውጤታማ አሰራር ለመመስረት ያስችላል፣
- ያሉት ተቋማት ተጠያቂነታቸው ለአስፈጻሚው አካል በመሆኑ ከፍተኛ የገለልተኝነት ጥያቄ አለባቸው፣ እምነት አይጣልባቸውም፣ በሕግ ሳይሆን በፖለቲከኞች ትዕዛዝ እና በጎጠኛ ስሜት የሚመሩ ናቸው፣
- በብልሹ አሰራር ይታማሉ፣ ተገቢ ፍትህ ወይም መፍትሄ ይሰጣሉ ተብሎ አይጠበቅም፣ ከሚስተዋለው ከፍተኛ የገለልተኝነት እጦት እና የሙስና ድርጊት መስፋፋት አንጻር አሁን ያሉት ተቋማት እና ባለሙያዎች ምርጫ ሆነው ሊቀርቡ አይገባም፣
- ያሉት ተቋማት ከፍርድ ቤት በላይ ከፍተኛ የሙብት ጥሰት ሲፈፅሙ የቆዩ ወይም በተፈጸሙት ላይ ተገቢ መከላከል ያላደረጉ ናቸው፣ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ቁመና የላቸውም፣
- ከአገራዊ ችግሩ ግዝፈት አንጻር፣ እንዲሁም አሁን ያሉት የፍትህ ተቋማት በኔትወርክ የተሳሰሩ መሆናቸው ራሱን የቻለ ተቋም ማደራጀትን ይበልጥ ተመራጭ ያደርገዋል፣ ይህን አጋጣሚ መጠቀም ነፃ፣ ገለልተኛ፣ ታማኝ እና ቅቡል የሆነ ተቋም ለመገንባት ሚናው ከፍተኛ ነው፣
- አገሪቷ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ በአዲስ ትገነባለች ከተባለ ለዚህ ስራ አዲስ ፖሊስ እና ዐቃቤ ሕግ ማዋቀር ያስፈልጋል፣ በተለመደው አሰራር መቀጠል ውጤታማ የሽግግር ፍትህ ሂደት እንዳይኖር ያደርጋል፣
- ጉዳዮችን በትኩረት እና በፍጥነት አይቶ ውሳኔ የሚሰጥ በአዲስ የሰው ኃይል የተደራጀ አዲስ የፖሊስ/ ዓቃቤ ሕግ ተቋም ያስፈልጋል፣ በውስጡም ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ እውቀትና ልምድ ያላቸው ነፃና ገለልተኛ የምርመራና ዐቃቤ ሕግ ባለሙያዎች መመልመል ያስፈልጋል፣
- ከሽግግር ፍትህ ዓላማ አንፃር አዲስ ተቋም ማደራጀት ሀብት ቢፈጅም ቅድሚያ ለፍትህ መስጠት አለበት፣
- ያሉት ፖሊሶችና አቃቢያነ ሕጎች ከፍተኛ የሥራ ጫና አለባቸው፣ የሽግግር ፍትህ ስራን መጨመር ብዙ ችግር ይዞ ይመጣል፣
- ዓለም አቀፍ የምርመራ ቡድን ቢመሰረት ቋንቋን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች የተሟላ ሥራ መሥራት አይችልም።

### ለ. በተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን ማዋቀር' (አማራጭ አንድ)

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 8 ቡድኖች (ወይም 16.32%) የሚሆኑት የክስና ምርመራ ስራው 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ በምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር' ማከናወን ይገባል ሲሉ አቋማቸውን ገልፀዋል። ተሳታፊዎቹ አቋማቸውን የሚደግፉ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ነባር የምርመራና ክስ ባለሙያዎች የተሻለ የምርመራና ክስ አመሰራረት ልምድ አላቸው፣ በተቋማቱ ውስጥ የሙያ ብቃት፣ ገለልተኝነት እና የግለሰብ ስብዕናን መሰረት ያደረገ ልየታና ማጥራት በማካሄድ ልዩ ቡድን አደራጅቶ ወደስራ መግባት ውጤታማ ያደርጋል፣
- ትኩረቱ ያሉትን አገራዊ ተቋማት ችግሮች ነቅሶ በማሻሻል፣ የእርምት እርምጃ በመውሰድ እና ስለ ሽግግር ፍትህ የተለየ ስልጠና በመስጠት ወደ ጥቅም በሚገባበት ሁኔታ ላይ መሆን አለበት፣
- ብቃትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች አሉ፣ ገለልተኛ ሆነው የሚሰሩበት የአሰራር ሥርዓት ቢዘረጋ የተሻለ ልምዳቸውን በመጠቀም በአዲስ ሞራልና መነሳሳት ውጤታማ ስራ ሊሰሩ ይችላሉ፣
- "ምንም ቢሆን የጠገበ ጅብ ይሻላል"፣ አዲስ ተቋማትን ከመመስረት ካሉት የተሻሉትን መርጦ ማሰማራት እና ጥብቅ የክትትል ስርአት መዘርጋት የተሻለ ነው፣
- አዲስ ተቋም መመስረት ሀብት ይጠይቃል፣ ጊዜ ይወስዳል፣ የፍትህ መጓተት ያስከትላል፣
- አዲስ ተቋም ማደራጀት ገንዘብና ጊዜ ከማባከን ያለፈ ትርጉም ያለው ፋይዳ አይኖረውም፣ በሌላ በኩል በተቋማቱ ውስጥ ልዩ ቡድን ማቋቋም ያለውን ውስን አገራዊ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል፣
- አዲስ ተቋም ቢመሰረት ተፈላጊው ልምድና ችሎታ ላይገኝ ይችላል።

### ሐ. በተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አዲስ አማራጭ፥ 'ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋም' መጠቀም

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 4 ቡድኖች (ወይም 8.5%) የሚሆኑት የምርመራና የክስ ጉዳዮች 'በልዩ ዓለም አቀፍ ተቋም' ወይም 'ተመሳሳይ ቅይጥ ተቋም' አማካኝነት መከናወን አለበት በማለት ተከራክረዋል።

ለዚህ የሰጡት ምክንያት አሁን ስራ ላይ ያሉት የፖሊስና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ገለልተኛና ነፃ ሆነው የምርመራና ክስ የማቅረብ ሥራዎችን ሊያከናውኑ አይችሉም፡ ይሰሩ ቢባል እንኳ በወንጀሎቹ የውጭ ሃይላት ተሳትፎ ያለ እንደመሆኑ መጠን በሀገር-አቀፍ ተቋማት አማካኝነት ውጤታማ በሆነ መንገድ ማጣራት የሚቻልበት እድል የለም የሚል ነው። ስለሆነም አንድ አለም ዓቀፍ ገለልተኛ መርማሪ ቡድን ቢደራጅና ስራውን ቢያካሂድ የተሻለ ነው ብለዋል።

ሰንጠረዥ 28፡ 'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' - የወንድ ጉዳተኛ ቡድኖች ሀገር-አቀፍ/ክልል ደረጃ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | | |
| 2 | አፋር | 1 | 0 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 0 | 7 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 1 | 1 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0.5 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 0.5 | 0.5 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 4 | 10 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 0 | 1 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 0 | 3 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 2 | 6 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 0 | 2 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 0 | 2 | 3 |

| | ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | 47 | 8 | 35 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|

III. **የቅልቅል ቡድን**

***ሀ. አብዛኛው የቅልቅል ቡድን የደገፈው አማራጭ፣ 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን መመደብ' (አማራጭ ሁለት)***

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 75.5 ቡድኖች (ወይም 78.64%) የሚሆኑት የምርመራ እና ክስ ጉዳዮች 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም እና የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ' መከናወን አለበት የሚለውን ሀሳብ ደግፈው ተከራክረዋል። ምክንያቶቻቸውንም እንደሚከተለው ዘርዝረዋል።

- አሁን ያሉት የምርመራ እና የዐቃቤ ሕግ ተቋማት እምነት የሚጣልባቸው አይደሉም፣ የሽግግር ፍትህ ሂደት ከሚጠይቀው ነፃ እና ገለልተኛ የምርመራ ስራ አንፃር ይህን ሀላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ቁመና የላቸውም፣
- አዲስ ተቋም መመስረት አሁን ያለውን ወገንተኝነት፣ አድሎአዊነት፣ የሥነ-ምግባር ጥሰት እና የአቅም ማነስ ችግሮችን ለመቀነስ ይረዳል፣
- በእስካሁኑ አገራዊ ጉዞ ፖሊስና ዐቃቤ ሕግ ስራቸውን በአግባቡ ቢያከናውኑ ኖሮ የሽግግር ፍትህ ባላስፈለገ ነበር፣
- ፖሊስና ዓቃቤ-ሕግ ተቋማት በተፈፀሙ የሰብዓዊ  መብት ጥሰቶች ውስጥ እጃቸው የለበትም አይባልም፣ በአቅመ-ደካሞች ላይ ብቻ ያተኩራሉ፣ ለባለስልጣናት እና ከፍተኛ ወንጀል ፈጻሚዎች ህገወጥ ከለላ ያደርጋሉ፣ ስለሆነም ንክኪ የሌላቸውን መርጦ በአዲስ ማዋቀር የተሻለ ነው፣ የችግሩ ምንጭ/ክፍል የነበረ አካል የመፍትሄው አካል መሆን አይችልም፣
- በነበረው ግጭት/ጦርነት ወቅት የፍትህ አካላት ተሳትፎ ነበራቸው፣ ተጠያቂ የሚሆኑ አካላት የስራው ማዕከል መሆን የለባቸውም፣ ራሳቸው አጥፍተው ራሳቸውን ተጠያቂ ሊያደርጉ አይችሉም፣ የወንጀል ማጣራት ስራውን ያካሂዱ ቢባል እንኳ ሂደቱን ሊያስተጓጉሉ ይችላሉ፣
- በፍርድ ቤቶች ላይ ለታጣው እምነት ትልቁን ሚና የተጫወቱት የፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ናቸው፣ እነዚህን አላት መጠቀም ያለውን ችግር ከማባባስ ባለፈ የታሰበውን ፍትህ እና ዘላቂ ሰላም አያመጣም፣
- አሁን ያሉት የፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት በመንግስት ተጽእኖ ስር የወደቁ፣ በገዢው ፓርቲ የተመረጡ ናቸው፣
- የፖሊስ እና  ዓቃቤ  ሕግ ተቋማት መሰረታዊ የአቅም ችግር አለባቸው፣
- ለሽግግር ፍትህ ስራ ውጤታማነት የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር ብቃት እና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የተመላ ልዩ ነጻና ገለልተኛ የዓቃቤ ሕግ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ቅድመ-ሁነት ነው፣
- አዲስ ፍርድ ቤት ከተቋቋመ በተመሳሳይ አዲስ የፖሊስና ዓቃቤ ሕግ ተቋም ቢኖር ተመራጭ ነው፣ ስራው በነበረው ዓቃቤ ሕግ የሚሰራ ከሆነ ውጤት አያመጣም፣
- የሽግግር ፍትህ ዓላማ ነባር ቅራኔዎችን ማስወገድ እስከሆነ ድረስ የክስ ሂደቱ ተአማኒነት በሌላቸው መደበኛ የፍትህ ተቋማት ሊካሄድ አይችልም፣
- በነባሩ ተቋም ውስጥ የተለየ ቡድን በመመስረት ብቻ የሚመጣ ለውጥ አይኖርም፣
- በነባር ተቋማት ላይ ያለውን ችግር በአንድ ጊዜ ፈትቶ እና ተቋማትን አጥርቶ ለሽግግር ፍትህ ተግባር ለማዋል ረጅም ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ አዲስ ተቋም ማቋቋም ይበልጥ ተመራጭ ነው፣

- የፖሊስና የዓቃቤ ሕግ ስራ በራሱ በጣም ብዙ ነው፣ የሽግግር ፍትህ ስራን መደረብ የሚታሰብ አማራጭ ሊሆን አይገባም፣ ከጉዳዩ ውስብስብነት አንጻር በዚህ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ሌላ ተቋም ያስፈልጋል፣
- ልዩ ብቃት ያለው ተቋም ማቋቋም ለሽግግር ፍትሕ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች አገራዊ ጉዳዮችም ይጠቅማል፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ከበጀት አንፃር አስቸጋሪ ቢሆንም አሁን ካለው የፖሊስ እና የዓቃቤ ሕግ የሥራ ጫና እና የገለልተኝነት ችግር አንፃር የተሻለው አማራጭ ነው።

በሌላ በኩል ሁለት ቡድኖች በአይነቱ አዲስ የሆነና ከሁሉም ባህላዊ አሰራሮች ልምድ የሚቀስም የምርመራ አካል ያስፈልጋል፣ በባለሙያዎቹ ስብስብ ውስጥም የሀገር ሽማግሌዎችን፣ አባ ገዳዎችን ወዘተ ያካተተ ሊሆን ይገባል ሲሉ ሀሳባቸውን ገልፀዋል።

## ለ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ ሀሳብ፡ 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን ማዋቀር' (አማራጭ አንድ)

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 13.5 ቡድኖች (ወይም 14%) የሚሆኑት የምርመራና ክስ ሂደቱ 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር' መከናወን አለበት የሚል አቋም ይዘዋል። ለዚህም የሚከተሉት ምክንያቶች ተጠቅሰዋል።

- ባሉት የፖሊስ እና የዐቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ ብቁ ባለሙያዎች አሉ፣ እነዚህን በማብቃት፣ ክፍተቶቻቸውን በመሙላት፣ የተሻሉትን መርጦ እና በሽግግር ፍትህ ስራ ትኩረት ያደረጉ ስልጠናዎችን ሰጥቶ መጠቀም ይሻላል፣
- እምነት ያጎደሉት ውስን አባላት ናቸው፣ እነሱን በመተካት የምርመራና ክስ ሂደቱን መምራት ይቻላል፣
- አሁን ባሉት ተቋማት ጋር ያለው ችግር የአፈፃፀም እንጂ የተቋም ችግር አይደለም፣ ዐቃቤ ሕግና ፖሊስ ክፍተት ቢኖርባቸውም ስራቸው ብዙውን ጊዜ በፍርድ ቤቶች እይታ ስር ነው፣ ስለሆነም ሙሉ ለሙሉ መቀየር አያስፈልግም፣
- ሁል ጊዜ ማፍረስ የለብንም፣ ትኩረቱ አዲስ ተቋም በመገንባት ላይ ሳይሆን ያሉትን በአግባቡ እንዲሰሩ በማድረግ ላይ መሆን አለበት፣ አዲስ ተቋም መመስረት ለችግሩ መፍትሄ አይሆንም፣
- ልዩ ተቋም ማቋቋም ከፋይናንስ፣ ከሰው ሃይል፣ ከልምድ እና ሂደቱን በጊዜ ከማከናወን አንጻር ተመራጭ አይሆንም፣
- ልዩ የፖሊስ ወይም የዐቃቤ ሕግ ተቋም 'ልዩ' ስለተባለ ብቻ ልዩ አይሆንም፣ ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም፣ 'ልዩ ፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ' ማቋቋም ትርፉ የሀገርን ሀብት ማባከን ብቻ ነው።

## ሐ. በጥቂት የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ ሀሳብ፡ 'ልዩ አለም አቀፍ ተቋም' መጠቀም (ሌላ/አዲስ አማራጭ)

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 5 ቡድኖች (ወይም 5.2%) የሚሆኑት የምርመራና ክስ ሂደቶችን የሚያከናውን 'ልዩ አለም አቀፍ ተቋም' መጠቀም ያስፈልጋል የሚል አዲስ ሀሳብ አቅርበዋል።

ይህን አቋም ሲያስረዱም በሀገር ውስጥ በሚቋቋም ኣካል ላይ እምነት አለመኖሩን፣ እንዲሁም ዓለም ቀፋዊ መልክ ያለው ወንጀል ተፈጽሟል ተብሎ ስለሚታመን የምርመራና ክስ ሂደቶቹ በአለም አቀፍ ባለሙያዎች ሊመራ ይገባዋል የሚል ክርክር አቅርበዋል።

*ሰንጠረዥ 29፡ 'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' - የቅልቅል ቡድኖች ሀገር-አቀፍ/ክልል ደረጃ ማጠቃለያ*

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | 2 | 4 | 0 |
| 2 | አፋር | 2 | 0 | 2 | 0 |
| 3 | አማራ | 13 | 2 | 11 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | 1.5 | 2.5 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | 1 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 0.5 | 1.5 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 0 | 2 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 4 | 23 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | 2 | 0.5 | 1.5 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 4 | 1 | 3 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 1 | 17 | 0 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 0 | 4 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 10 | 0 | 5 | 5 |
| | ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | 96 | 13.5 | 77.5 | 5 |

## IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን

### ሀ. በአብዛኛው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን መመደብ' (አማራጭ ሁለት)

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች መካከል 19.5 ቡድኖች (ወይም 81.25%) የሚሆኑት የምርመራ እና ክስ ሂደቱ 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ' መከናወን አለበት ሲሉ አቋማቸውን አሳውቀዋል፡፡ ይህ አቋማቸውን ለመደገፍም የሚከተሉትን ነጥቦች አቅርበዋል፡፡

- ባለው ነባራዊ ሁኔታ የዓቃቤ ሕግና የፖሊስ ተቋማት በሕግ ሳይሆን በፖለቲከኞች ትእዛዝ፣ በጎጠኛ ስሜት የሚመሩ ናቸው፣ ገለልተኛ እና ከጫና ነጻ አይደሉም፣ ስለሆነም ስራው ይህን መመዘኛ በሚያሟላ አዲስ ተቋም መመራት አለበት፣
- በነዚህ መዋቅሮች ስር በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈፅመዋል፣ ጥፋቶች ሲፈፀሙም ተቋማቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሲሳተፉ ነበር፣ ስለሆነም ገለልተኛ ሊሆኑ አይችሉም፣
- ተቋማቱ በሰብዓዊ መብት ጥሰት የተሳተፉ በመሆኑ የሚሰራ ማናቸውም የልየታ ስራ በተቋሞቹ ላይ ያለውን የገለልተኛነት፣ ነጻ የመሆን እና የአመኔታ ጥያቄን ሊያስቀር አይችልም፣
- አዲስ ተቋም በቀደሙ ተቋማት ላይ የሚነሱ የሥነ-ምግባር/የሙያ ብቃት ችግሮችን ለማረቅ እድል ይሰጣል፣ አዳዲስ ባለሙያዎች እንዲካተቱ ያደርጋል፣ አፋጣኝና ውጤታማ የምርምራና ክስ ሂደት እንዲኖር ያስችላል፣
- የሽግግር ፍትህ ስራ በጊዜ የተገደበ ነው፣ ስለሆነም ተቋማትን ወደማብቃት ስራ ሊገባ አይችልም፣ ያሉ ተቋማትን ማጥራት ረጅም ጊዜ ይወስዳል፣ ከዚህ አንፃር ሌላ አማራጭ መከተል ከሽግግር ፍትህ አጣዳፊነት ጋር አብሮ አይሄድም፣

- የሽግግር ፍትህ ልምምድ በሃገራችን የለም፣ ስለ ሽግግር ፍትህ አላባዎች እና ዓላማዎች እውቀት እና ዝግጁነት ያላቸውን ሰዎች በልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም አደራጅቶ የክስ ሂደቱን ማከናወን የተሻለ ነው፣ የህዝብ አመኔታ ጥያቄን ለማስተካከል ይረዳል፣ የግለሰብና የተቋም ነጻነትኝ ለማረጋገጥ ያግዛል፣
- ለሽግግር ፍትህ ዓላማ የተቋቋመ፣ ስራውን በልዩ ትኩረት መስራት የሚችል የፍትህ ተቋም ያስፈልጋል፣
- ለሽግግር ፍትህ ዓላማ መሳካት የአዲሱ ተቋም ባለሙያዎች ለህዝብ አስተያየት ክፍት በሆነ ሂደት፣ በግልፅ የአመራረጥ እና አሿሿም መመዘኛ፣ በአስፈፃሚው አካል ሳይሆን በህዝብ ጠቋሚነት ሊመረጡ ይገባል።

**ለ. በተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አለም አቀፍ ተቋም' መጠቀም (አዲስ/ሌላ አማራጭ)**

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች መካከል 3 ቡድኖች (ወይም 12.5%) የሚሆኑት የምርመራና ክስ ሂደቱ በአለም አቀፍ ተቋም ሊመራ እንደሚገባ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል። ይህን ሲያስረዱም መጀመሪያውኑም ጉዳዩ በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት መታየት አለበት የሚለውን አቋም ስለደገፉ ተመሳሳይ ሂደትን መከተል አስፈላጊ በመሆኑ፣ የፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት የገለልተኝነት እና ነፃነት ችግሮች ስላሉባቸው፣ እንዲሁም የውጭ ሀይሎች በወንጀሎች የተሳተፉበት ሁኔታ ስላለ - ይህ አማራጭ የተሻለው አማራጭ ነው ሲሉ ክርክራቸውን አቅርበዋል።

በሌሎች ቡድኖች ውስጥ የነበሩ ጥቂት አስተያየት ሰጪዎች ደግሞ የምርመራና ክስ ስራው የሀገር ውስጥ እና የውጭ ተቋማትን አንድ ላይ በመቀየጥ በሚደራጅ ተቋም ሊመራ ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል።

**ሐ. በጥቂት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ ሀሳብ፡ 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን ማዋቀር' (አማራጭ አንድ)**

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች መካከል 1.5 ቡድኖች (ወይም 6.25%) የሚሆኑት የምርመራና ክስ ሂደቱ 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር' ሊመራ ይገባል የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች በአስረጅነት ጠቅሰዋል።

- ባሉት ተቋማት ላይ ማስተካከያዎችን በማድረግ የመጠቀም አማራጭ የገንዘብ እና የሰው ሀይል ወጪን ለመቆጠብ ይረዳል፣ ከተግባራዊነት አንጻርም የተሻለ ነው፣
- አዲስ ተቋም ማደራጀት ለአላስፈላጊ የጊዜ ብክነት ይዳርጋል፣
- ሲጀመርም የተለየ ነጻ እና ገለልተኛ የምርመራ እና የዓቃቤ ሕግ ተቋም ማቋቋም ይቻላል ወይ የሚለው ጥያቄ በቀላሉ የሚመለስ አይደለም፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም በተለየ መንገድ የሚፈታው ችግር የለም፣ በአመዛኙ በአገሪቱ ካለው ባለሙያዎች ስብስብ የሚውጣጣ መሆኑ አይቀርም፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ለተቋማት ዘላቂ ግንባታ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የለም።

*ሰንጠረዥ 30፡ 'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' - የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን ማጠቃለያ (ሀገር-አቀፍ እና በክልል)*

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | | |
| 2 | አፋር | 1 | 0 | 1 | 0 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | አማራ | 5 | 0 | 5 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | 0 | 1 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0 | 1 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | 0 | 7 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | | | | |
| 10 | ሶማሌ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 3 | 0.5 | 2.5 | 0 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | | | | |
| 13 | ትግራይ | 4 | 0 | 1 | 3 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 24 | 1.5 | 19.5 | 3 |

### 6.2.4.3.'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' የሚለውን ጥያቄ መሰረት አድርገው በቀረቡት መነሻ አማራጮች ዙሪያ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 170 ቡድኖች (ወይም 78.7%) የሚሆኑት የምርመራ እና ክስ ስራዎች 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ' ሊከናወኑ ይገባል በማለት አቋማቸውን ገልፀዋል።

በሌላ በኩል 30 ቡድኖች (ወይም 13.88%) የሚሆኑት ደግሞ የምርመራ እና ክስ ስራዎች 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር' ሊተገበሩ ይገባል በማለት ሀሳባቸውን ገልፀዋል።

ቀሪዎቹ 16 ቡድኖች (ወይም 7.4% ) የሚሆኑት ደግሞ አዲስ አማራጭ በማቅረብ የምርመራ እና ክስ ስራዎች በአለም አቀፋዊ ተቋማት አማካኝነት ሊከናወኑ ይገባል የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል።

**ይህ ግኝት የውይይት መድረኮቹን ካስተናገዱ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች አንጻር ሲተነተን**

በአስሩም ክልሎች እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች ማለትም በአዲስ አበባ፣ አፋር፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ድሬዳዋ፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ሶማሌ፣ ደቡብ ህ/ብ/ብ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ አብዛኞቹ ቡድኖች የምርመራ እና ክስ ስራው 'አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ' መከናወን አለበት የሚለውን አማራጭ መርጠዋል።

ከትግራይ እና ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ውጭ - በሁሉም ክልሎች በጣም ውስን ቡድኖች የምርመራ እና ክስ ሂደቶች 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር' ሊተገበሩ ይገባል ብለዋል።

በትግራይ ክልል የሚገኙ አብዛኞቹ ቡድኖች (ከ24 ቡድኖች 15) እና በደቡብ ህ/ብ/ብ ክልል የሚገኝ አንድ ቡድን የምርመራ እና ክስ ስራው በአለም አቀፍ ተቋም አማካኝነት መከናወን አለበት የሚል አዲስ አማራጭ አቅርበዋል።

**ግኝቱ ከትኩረት ቡድኖች አንፃር ሲተነተን**

ግኝቱ ከትኩረት ውይይት ቡድኖች አንጻር ሲታይ አራቱም ቡድኖች (ማለትም ሴት ጉዳተኞች፣ ወንድ ጉዳተኞች፣ በቅልቅል እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች) በሀገር-አቀፍ ደረጃ ሲታዩ

አብላጫዎቹ ቡድኖች የምርመራ እና ክስ ስራው ‘አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ’ መከናወን አለበት የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል።

በሌላ በኩል በትግራይ ክልል አራቱም የትኩረት ውይይት ቡድኖች በከፍተኛ ደረጃ የምርመራ እና ክስ ስራው ‘በአለም አቀፍ ተቋም’ ይሰራ የሚለውን አዲስ አማራጭ አቅርበዋል።

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ ‘በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች’፡ ‘ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች’ እና ‘በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች’ **የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተጠቃለው ቀርበዋል።**

***ሀ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ ‘አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን መመደብ’ - ምክንያቶች***

- *ያሉት የምርመራ እና የዐቃቤ ሕግ ተቋማት የህዝብ እምነት የሚጣልባቸው አይደሉም፣ የሽግግር ፍትህ ሂደት አንዱ ዓላማ ችግር ያለባቸውን ተቋማት በመተው የተሻሉ ተቋማትን መፍጠር ነው፣ ስለሆነም የምርመራና ክስ ሂደቱ ነፃ እና ገለልተኛ በሆነ አዲስ ተቋም ሊተገበር ይገባል፣*
- *ያሉት ተቋማት ተጠያቂነታቸው ለአስፈጻሚው አካል በመሆኑ ከፍተኛ የገለልተኝነት ጥያቄ አለባቸው፣ በገዢው ፓርቲ የተመረጡ ናቸው፣ እምነት አይጣልባቸውም፣ በመንግስት ተጽእኖ ስር ወድቀዋል፣ በሕግ ሳይሆን በፖለቲከኞች ትዕዛዝ እና በጎጠኛ ስሜት ይመራሉ፣ ስለሆነም ተገቢ ፍትህ ይሰጣሉ ተብሎ አይጠበቅም፣*
- *ያሉት ተቋማት ሰብአዊ መብትን የሚያስከብሩ ሳይሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና ረገጣ ፈፃሚዎች ናቸው፣ ከፍርድ ቤት በላይ ከፍተኛ ጥሰት ሲፈፅሙ የቆዩ ወይም በተፈጸሙት ላይ ተገቢ መከላከል ያላደረጉ ናቸው፣ በአቅመ-ደካሞች ላይ ብቻ ያተኩራሉ፣ ለባለስልጣናት እና ከፍተኛ ወንጀል ፈጻሚዎች ህገወጥ ከለላ ያደርጋሉ፣ ገለልተኛ እና ነፃ አይደሉም፣ በብልሹ አሰራር እና ሙስና ተዘፍቀዋል፣ ህብረተሰቡ ተማሮባቸዋል፣ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ቁመና የላቸውም፣*
- *የችግሩ ምንጭ/ክፍል የነበረ አካል የመፍትሄው አካል መሆን አይችልም፡ አይገባምም፣ ራሳቸው አጥፍተው ራሳቸውን ተጠያቂ ሊያደርጉ አይችሉም፣ የወንጀል ማጣራት ስራውን ያካሂዱ ቢባል እንኳ ሂደቱን ሊያስተጓጉሉ ይችላሉ፣ ስለሆነም ንክኪ የሌላቸውን መርጦ በአዲስ ማዋቀር የተሻለ ነው፣*
- *ተቋማቱ በሰብዓዊ መብት ጥሰት የተሳተፉ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚሰራ ማናቸውም የልየታ ስራ በተቋሞቹ ላይ ያለውን የገለልተኛነት፣ ነጻ የመሆን እና የህዝብ አመኔታ ጥያቄን ሊያስቀር አይችልም፣*
- *በነባሩ ተቋም ውሰጥ የተለየ ቡድን በመመስረት ብቻ የሚመጣ ለውጥ አይኖርም፣*
- *በእስካሁኑ አገራዊ ጉዞ ፖሊስና ዐቃቤ ሕግ ስራቸውን በአግባቡ ቢያከናውኑ ኖሮ ቀድሞውንም የሽግግር ጊዜ ፍትህ ባላስፈለገ ነበር፣*
- *አዲስ ተቋም በቀደሙ ተቋማት ላይ የሚነሱ የሥነ-ምግባር/የሙያ ብቃት ችግሮችን ለማረቅ እድል ይሰጣል፣ ያለውን ወገንተኝነት፣ አድሎአዊነት፣ የሥነ-ምግባር ጥሰት እና የአቅም ማነስ ችግሮችን ለመቀነስ ይረዳል፣ አዳዲስ ባለሙያዎች እንዲካተቱ ያደርጋል፣ አፋጣኝ እና ውጤታማ የምርምራ እና ክስ ሂደት እንዲኖር ያስችላል፣*
- *ለሽግግር ፍትህ ዓላማ የተቋቋመ፣ ስራውን በልዩ ትኩረት መስራት የሚችል፣ ምርመራ ከማድረግና ክስ ከመመስረት ባለፈ ጥሰት የፈፀሙ ወንጀለኞችን ለመለየትና ለሕግ ለማቅረብ የሚያስችል ቁመና ያለው፣ የጥቅም ግጭት የሌለበት፣ ከፖለቲከኞች ጫና የፀዳ አዲስ እና ገለልተኛ ተቋም ያስፈልጋል፣*

- አማራጩ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ነፃ፣ ገለልተኛ፣ ታማኝ እና ቅቡል የሆነ ተቋም ለመገንባት ሚናው ከፍተኛ ነው፣
- ያሉት ፖሊሶችና አቃቢያነ-ሕጎች ከፍተኛ የሥራ ጫና አለባቸው፣ ከብቃትና አቅም አንጻር ተቋማቱ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የሚሰራውን ውስብስብ ስራ ለማከናወን ከባድ ይሆንባቸዋል፣ የሽግግር ፍትህን ዓላማ ማሳካት አይችሉም፣
- ያሉትን ተቋማት መጠቀም በመደበኛ የፍትህ ስርአቱ ላይ አላስፈላጊ ጫና ይፈጥራል፣ ጉዳዮችን በትኩረትና በፍጥነት አይቶ ውሳኔ የሚሰጥ በአዲስ የሰው ኃይል የተደራጀ አዲስ የፖሊስ/ ዓቃቤ ሕግ ተቋም ያስፈልጋል፣ በውስጡም ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ እውቀትና ልምድ ያላቸው ነፃና ገለልተኛ የምርመራና ዐቃቤ ሕግ ባለሙያዎች መመልመል ይገባል፣
- የሽግግር ፍትህ ዓላማ ነባር ቅራኔዎችን ማስወገድ እስከሆነ ድረስ የክስ ሂደቱ ተአማኒነት በሌላቸው መደበኛ የፍትህ ተቋማት ሊካሄድ አይችልም፣ አገሪቱ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ በአዲስ ትገነባለች ከተባለ ለዚህ ስራ አዲስ ተቋም ማዋቀር ያስፈልጋል፣
- የሽግግር ፍትህ ስራ በጊዜ የተገደበ ነው፣ ስለሆነም ተቋማትን ወደማብቃት ስራ ሊገባ አይችልም፣ ያሉ ተቋማትን ማጥራት ረጅም ጊዜ ይወስዳል፣ ከዚህ አንፃር ሌላ አማራጭ መከተል ከሽግግር ፍትህ አጣዳፊነት ጋር አብሮ አይሄድም፣
- የሽግግር ፍትህ ልምምድ በሃገራችን የለም፣ ስለ ሽግግር ፍትህ አላባዎችና ዓላማዎች እውቀት እና ዝግጁነት ያላቸውን ሰዎች በልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም አደራጅቶ የክስ ሂደቱን ማከናወን የተሻለ ነው፣ የህዝብ አመኔታ ጥያቄን ለማስተካከል ይረዳል፣ የግለሰብ እና የተቋምን ነጻነት ለማረጋገጥ ያግዛል፣
- ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ እውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን በመመልመል አዲስ ተቋም ማቋቋም በራሱ ነጻና ገልለተኛ የመሆን አወንታዊ እይታኝ ይፈጥራል፣
- ከሽግግር ፍትህ ዓላማ አንፃር አዲስ ተቋም ማደራጀት ሀብት ቢፈጅም ቅድሚያ ለፍትህ መሰጠት አለበት፣
- አዲስ ፍርድ ቤት ከተቋቋመ በተመሳሳይ አዲስ የፖሊስና ዓቃቤ ሕግ ተቋም ቢኖር ተመራጭ ነው፣ ስራው በነበረው ዓቃቤ ሕግ የሚሰራ ከሆነ ውጤት አያመጣም፣
- ዓለም አቀፍ የምርመራ ቡድን ቢመሰረት ቋንቋን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች የተሟላ ሥራ መሥራት አይችልም፣
- ልዩ ብቃት ያለው ተቋም ማቋቋም ለሽግግር ፍትሕ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች አገራዊ ጉዳዮችም ይጠቅማል፣
- ለሽግግር ፍትህ ዓላማ መሳካት የአዲሱ ተቋም ባለሙያዎች ለህዝብ አስተያየት ክፍት በሆነ ሂደት፣ በግልፅ የአመራረጥ እና አሿሿም መመዘኛ፣ በአስፈፃሚው አካል ሳይሆን በህዝብ ጠቋሚነት ሊመረጡ ይገባል።

**ለ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፣ 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የክስ ሂደት ምርመራ እና ክስ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን ማዋቀር' - ምክንያቶች**

- ዋናው ትኩረት ያሉት አገራዊ ተቋማት ችግሮችን ነቅሶ በማሻሻል፣ የእርምት እርምጃ በመውሰድ እና ስለ ሽግግር ፍትህ የተለየ ስልጠና በመስጠት ወደ ጥቅም በሚገቡበት ሁኔታ ላይ መሆን አለበት፣
- እምነት ያጎደሉት ውስን አባላት ናቸው፣ እነሱን በመተካት የምርመራና ክስ ሂደቱን መምራት ይቻላል፣
- አሁን ያሉት ተቋማት ያለባቸው ችግር የአፈፃፀም ነው፣ የተቋም አይደለም፣ ዐቃቤ ሕግ እና ፖሊስ ክፍተቶች ቢኖርባቸውም ስራቸው ብዙውን ጊዜ በፍርድ ቤቶች እይታ ስር የሚያልፍ ነው፣ ስለሆነም ተቋማቱን ሙሉ ለሙሉ መቀየር አያስፈልግም፣
- እንደ ሀገር ሁል ጊዜ ማፍረስ የለብንም፣ ትኩረቱ አዲስ ተቋም በመገንባት ላይ ሳይሆን ያሉትን በአግባቡ እንዲሰሩ በማድረግ ላይ መሆን አለበት፣ ሁሌም አዲስ ተቋም መመስረት ለችግሩ መፍትሄ አይሆንም፣

- ባሉት ተቋማት ውስጥ በሥራቸው፣ ልምዳቸው፣ ታማኝነታቸው እና በትምህርት ደረጃቸው የተሻሉ ፖሊሶች/ዓቃቤ ሕጎች አሉ፣ አዲስ ከሚገቡት የተሻለ የምርመራ/ክስ የመመስረት ልምድ አላቸው፣ ስለሆነም ትኩረቱ በተቋማቱ ውስጥ የሙያ ብቃት፣ ገለልተኝነት እና የግለሰብ ስብዕናን መሰረት ያደረገ ተገቢ የልየታና የማጥራት ስራ በመስራት ላይ መሆን አለበት፣ ገለልተኛ ሆነው የሚሰሩበት ሥርዓት ቢዘረጋ የተሻለ ልምዳቸውን በመጠቀም በአዲስ ሞራልና መነሳሳት ውጤታማ ስራ ሊሰሩ ይችላሉ፣
- አዲስ ተቋም ማዋቀር ጊዜ ይወስዳል፣ ባሉት ተቋማት ውስጥ በልዩ የምልመላ መስፈርት/ልየታ መሰረት ልዩ ቡድን በመመስረት ቢሰራ ጉዳዮችን በፍጥነት ለማየትና የተቀላጠፈ የፍትህ ስርአት ለማስፈን ይረዳል፣
- "ምንም ቢሆን የጠገበ ጅብ ይሻላል"፣ አዲስ ተቋማትን ከመመስረት ካሉት የተሻሉትን መርጦ ማሰማራት፣ ጥብቅ የክትትል ስርአት መዘርጋት የተሻለ ነው፣
- አዲስ ተቋም ከፍተኛ የሀገር ሀብት ይበላል፣ ጊዜ ይወስዳል፣
- አዲስ ተቋም ለመንግስት ጣልቃ ገብነት የተጋለጠ መሆኑ አይቀርም፣ ተጨማሪ ወጪ አውጥቶ አዲስ ከማቋቋም ያሉትን ማጠናከርና መጠቀም ተመራጭ ነው፣
- ልዩ ተቋም ማቋቋም ከፋይናንስ፣ ከሰው ሃይል፣ ከልምድና ሂደቱን በጊዜ ከማከናወን አንጻር ተመራጭ አይሆንም፣ ሂደቱን ሊያጓትት ይችላል፣ በሌላ በኩል በተቋማቱ ውስጥ ልዩ ቡድን ማቋቋም ያለውን ውስን አገራዊ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል፣
- ሲጀመርም የተለየ ነጻ እና ገለልተኛ የምርመራ እና የዓቃቤ ሕግ ተቋም ማቋቋም ይቻላል ወይ የሚለው ጥያቄ በቀላሉ የሚመለስ አይደለም፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም በተለየ መንገድ የሚፈታው ችግር የለም፣ የሚመጣው ሀይልም ባመዛኙ በአገሪቱ ካለው የባለሙያዎች ስብስብ የሚውጣጣ መሆኑ አይቀርም፣
- አዲስ ተቋም ቢመሰረት ተፈላጊው ልምድና ችሎታ ላይገኝ ይችላል፣
- ልዩ የፖሊስ ወይም የዐቃቤ ሕግ ተቋም 'ልዩ' ስለተባለ ልዩ አይሆንም፣ ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም፣ 'ልዩ ፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ' ማቋቋም ትርፉ የሀገርን ሀብት ማባከን ብቻ ነው፡፡
- ልዩ ዓቃቤ ሕግ ማቋቋም የስልጣን ሽኩቻ ያስከትላል፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ለተቋማት ዘላቂ ግንባታ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የለም።

### ሐ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'በአለም አቀፍ ተቋም ማከናወን' - ምክንያቶች

- አሁን ስራ ላይ ያሉት የፖሊስና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ገለልተኛና ነፃ ሆነው የምርመራና ክስ የማቅረብ ሥራዎችን ሊያከናውኑ አይችሉም፣
- በእስካሁኑ ሂደት የተፈጸመው ዓለም አቀፍ ወንጀል ነው፣
- የኢትዮጵያ ፍትህ ተቋማት በትግራይ ክልል ለተፈፀመ ወንጀል ጉልህ ኣስተዋፅኦ አድርገዋል፣ በጦርነቱ ተሳታፊ/ደጋፊ የነበረ አካል ትክክለኛ እና ገለልተኛ ውሳኔ ሊሰጥ ኣይችልም፣
- ገለልተኛ የሀገር ውስጥ ተቋም ይቋቋም ቢባል እንኳን የመንግስት አካላት ተጠያቂ እንደመሆናቸው መጠን መንግስት በተቋሙ ላይ ተፅእኖ መፍጠሩ አይቀርም፣
- የሀገር ውስጥ ተቋም ስራውን ይስራ ቢባል እንኳ በወንጀሎቹ የውጭ ሃይላት ተሳትፎ ያለ እንደመሆኑ መጠን በሀገር-አቀፍ ተቋማት ውጤታማ በሆነ መንገድ ማጣራት የሚቻልበት እድል የለም፣ ስለሆነም አንድ አለም ዓቀፍ ገለልተኛ መርማሪ ቡድን ቢደራጅና ስራውን ቢያካሂድ የተሻለ ነው፣
- ጦርነቱን እንዲቆም ያደረጉ የተለያዩ የውጭ አገራት አሉ፣ ስለሆነም የተጠያቂነት ስራ በገለልተኛ ዓለም አቀፋዊ ተቋም መከናወን አለበት።


ሰንጠረዥ 31፡ 'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' - ሀገር-አቀፍ የአራቱም ቡድኖች ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ | ጠቅላላ የቡድኖች | አማራጭ 1 የደገፉ | አማራጭ 2 የደገፉ | አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|

| | መስተዳድር | ብዛት | ቡድኖች ብዛት | ቡድኖች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | 2 | 6 | 0 |
| 2 | አፋር | 5 | 1 | 4 | 0 |
| 3 | አማራ | 32 | 3 | 29 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 2.5 | 6.5 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 1 | 4 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 1.5 | 3.5 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 1 | 3 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 11 | 49 | 2 |
| 9 | ሲዳማ | 4 | 1.5 | 2.5 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 2 | 9 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 3.5 | 34.5 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | 0 | 8 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 24 | 0 | 9 | 15 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 216 | 30 | 170 | 16 |

ሰንጠረዥ 32፡ 'የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን ማን ያከናውነው?' - ሀገር-አቀፍ የአራቱም ቡድኖች ማጠቃለያ

| | | **ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት** | **አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት** | **አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት** | **አዲስ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት** |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 49 | 7 | 38 | 4 |
| 2 | አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 47 | 8 | 35 | 4 |
| 3 | አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ | 96 | 13.5 | 77.5 | 5 |
| 4 | አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ | 24 | 1.5 | 19.5 | 3 |
| **አገራዊ የአራቱም የትኩረት ቡድኖች ማጠቃለያ** | | 216 | 30 | 170 | 16 |
| | | | | | |




***የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራ ማን ያከናውነው' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ***

### 6.2.4.4.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ[50]

አብዛኞቹ የሴቶች ብቻ መድረክ ተሳታፊዎች፣ ጾታዊ ጥቃት ተፈጽሞባቸው ያገገሙ ሴቶች መድረክ ተሳታፊዎች፣ አካል ጉዳተኛ እና አረጋውን መድረክ ተሳታፊዎች፣ የህጻናት ፓርላማ ተሳታፊዎች፣ የህጻናት መብት ተወካይ ተሳታፊዎች፣ እንዲሁም የተወሰኑ የተፈናቃይ የሴት የወንድ እና የቅልቅል ተጎጂ ቡድን መድረኮች ተሳታፊዎች - አሁን ካለው የዓቃቤ ህግ ተቋማት ውጭ ሌላ ምርመራና ክስን የሚያስተባብር ተቋም እንዲቋቋም ሃሳብ ሰጥተዋል። በምክንያትነትም የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።

- አሁን ያሉት ተቋማት የመንግስት አንድ ክፍል ስለሆኑ ነፃና ገለልተኛ አይደሉም፣
- የፆታ ጥቃት ሰለባዎችን ጨምሮ ለሁሉም ጉዳተኞች ፍትህን መስጠት አልቻሉም፣
- በፖሊስ መዋቅር ላይ ከሚቀርበው የስሞታ ብዛት አንፃር አሁን ያሉት ፖሊሶች ራሳቸው ተጠያቂ ሊሆኑ የሚችሉበት ሰፊ እድል አለ፣
- ከገለልተኝነት እና ቅቡልነት አንጻር ሌላ ገለልተኛ ተቋም ተቋም ማደራጀት የተሻለ ነው።

በተጨማሪም በህጻናት እና በሴቶች መብት ተወካዮች በኩል በዚህ አማራጭ ስር የሚከተሉት ምክረ-ሀሳቦች ተሰጥተዋል።

- የሚቋቋመው ተቋም ለህጻናትና ለሴቶች ጉዳይ ልዩ አደረጃጀት ሊኖረው ይገባል፣
- በምርመራ ስራው ሴት ባለሙያዎች ትርጉም ባለው መልክ/መጠን መሳተፍ የሚችሉበት ልዩ አደረጃጀት መኖር አለበት፣
- የሕጻናት ጉዳይ ውስብስብ እና የተለየ ክህሎትን ስለሚፈልግ የፎረንሲክ አቅምን ጨምሮ የማህበራዊ ጉዳይ ባለሙያዎች የተካተቱበት ቡድን መደራጀት ይኖርበታል።

በሌላ በኩል የተወሰኑ የተፈናቃይ ሴት ተጎጂ ቡድኖች እና ከላይ በተገለጹት ሁሉም መድረኮች ላይ የተሳተፉ ጥቂት የማይባሉ ተሳታፊዎች ስራውን 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የክስ ሂደት በምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር' ማከናወን ይገባል የሚለውን አማራጭ

[50] በዚህ ርእስ ስር - ከህጻናት ፓርላማ ተወካዮች፣ በህጻናት መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ተቋማት ተወካዮች፣ ፆታዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴት ተሳታፊዎች፣ በሴቶች መብት ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች የተወከሉ ተሳታፊዎች፣ የአካል ጉዳት ካለባቸውና ከአረጋውያን ተሳታፊዎች፣ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጋር በተደረጉ የተለያዩ የልዩ ትኩረት የምክክር መድረኮች ማእቀፍ የተሰጡ ግብዓቶች ተጠቃለዋል።

ደግፈዋል። በምክንያትነትም አሁን ያለው ተቋም በሪፎርም ሂደት ውስጥ እንዲያልፍ በማድረግ ለስራው ብቁ ማድረግ ይቻላል፣ ለብቻው አዲስ ተቋም ማቋቋም ከፍተኛ በጀትና የሰው ሃይል ይጠይቃል፣ ረጅም ጊዜ ይፈጃል፣ ስለዚህ ልዩ ቡድን መመስረት ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታና ከወጪ አንፃር የተሻለ አማራጭ ነው በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ውይይት ወቅት የተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የስራ ሂደቱ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ባለሙያዎች በሚውጣጣ ቅይጥ ተቋም ሊሰራ ይገባል ያሉ ሲሆን፡ የተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች ደግሞ ምርመራና ክስ ነጻና ገለልተኛ በሆነ አለም-አቀፍ ተቋም ሊመራ ይገባል በማለት ሃሳብ ሰጥተዋል። ጥቂት የቅልቅል ቡድኖች ደግሞ አዲስ ተቋም ሆኖ ባለሙያዎቹ በቀጥታ በህዝብ የሚመረጡበት አሰራር መመስረት ይመረጣል ብለዋል።

#### 6.2.4.5.ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ[51]

ምርመራ እና ክስን የሚያከናውኑ ተቋማትን በሚመለከት ሂደቱ - በተለይ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ሲያይ - የማስረጃ ማሰባሰብ ስራዎችን ክብደት እና ውስብስብነት በመረዳት የማስረጃ ምዘና በልዩ ሁኔታ የሚታይበት መንገድ እንዲጤን፣ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህጻናት የሚያገለግሉ ልዩ የምርምራና የክስ ሂደቶች/ቡድኖች እንዲደራጁ ቢደረግ፣ በተለይም ወንጀል የመፈጸሙን የማስረዳት ሸክም በተበዳይ/ከሳሽ ላይ ብቻ ሳይሆን በተከሳሽ ላይ እንዲወድቅ ቢደነገግ የተሻለ ፍትህ ለማረጋገጥ ያስችላል የሚል ተጨማሪ ምክረ-ሃሳብ አቅርበዋል።

## 6.3. እውነትን ማፈላለግ እና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት

### 6.3.1. መግቢያ

እውነትን ማፈላለግና እርቅን በተመለከተ ሁለት ጥያቄዎች ለትኩረት ውይይት ቡድኖች ቀርበዋል። እነዚህም፥ ‘እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል’? እንዲሁም ‘እውነትን የማፈላለግና የእርቅ ሂደት በየትኛው ተቋም ሊከናወን ይገባል?’ የሚሉ ናቸው።

በዚህ ጥያቄ ላይ ‘216 ሀገራዊ የትኩረት ውይይት ቡድኖች’፡ ‘ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች’፡ እና ‘ሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት’ ውይይት አድርገዋል።

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ ‘በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች’፡ ‘ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች’ እና ‘በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች’ የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል።

### 6.3.2. እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች ሊተገበሩ ይገባል?

[51] በዚህ ርእስ ስር - የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን በአዲስ አበባ እና አካባቢው በተለያዩ ጊዜያት ከልዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እና አመራሮች፣ ከሃገር ውስጥ ምሁራን፣ ከፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች እና አመራሮች፣ ከሚዲያ ሲቪክ ማህበረሰብ እና ዲሞክራሲ ተቋማት ጋር በተደረጉ የምክክር መድረኮች የተገኙ ግብአቶች፡ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የተመድ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ካውንስል፣ የሰብዓዊ መብት ማዕከል፣ የዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት ግሎባል ክሪሚናል ጀስቲስ ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (NEWA) እና ICTJ ጥምረት ሪፖርት፣ ICTJ፣ እና Commission for the Investigation of Violence in SRS and Reconciliation and Reparation of Victims የቀረቡ የፅሁፍ አስተያየት እና ምክረ-ሀሳቦች ይዘት ተጠቃለው ቀርበዋል።

እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች ሊተገበሩ ይገባል የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ለተወያዮች መነሻ አማራጮች ቀርበዋል። በአማራጭ 1 ስር የቀረበው የጉዳይ ስፋት 'ለሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች' የሚል ሲሆን፣ በአማራጭ 2 ስር የቀረበው ደግሞ 'ለተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች' የሚል ነው። ተወያዮች ሌላ አማራጭ ካላቸውም እንዲያቀርቡ ተጠይቀዋል።

### 6.3.2.1.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

#### I. የሴት ተጎጂዎች ቡድን

#### ሀ. በአብላጫው የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'ለሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች'

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በአገር አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች መካከል 19 ቡድኖች (ወይም 38.77%) የሚሆኑት ስራው በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ መተግበር አለበት የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- እውነት ማፈላለግ እና እርቅ በሁሉም የመብት ጥሰቶች ላይ ከተከናወነ ጥላቻ እንዲቀንስ ያደርጋል፣ መግባባት ይፈጥራል፣ ሰላም ያሰፍናል፣ ሰላማዊ ማህበራዊ ግንኙነት ያስቀጥላል፣ በአንፃሩ ሂደቱ የተወሰኑ ጉዳዮችን ብቻ የሚሸፍን ከሆነ ቂምና በቀልን ይፈጥራል፣
- የእውነት ማፈላለግ ሂደት ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ መልህቅ ነው፣ እውነት ከተጣራ ይቅር ማለት ይቻላል፣ እውነት ካልታወቀ፣ ይቅር ካልተባለ እና እርቅ ካልመጣ ወደፊት መጓዝ አይታሰብም፣
- ዕውነትን ማፈላለግና ማጥራት ለሁሉም ጉዳዮችና ጥሰቶች ወሳኝ ሚና አለው፣ ለየትኛውም የመብት ጥሰት መጀመርያው ዕውነቱ እንዲታወቅ ማድረግ ነው፣ በዚህ ዕውነት መሠረት ተጠያቂነት ሊመጣ ይችላል፣
- ይቅርታ ለማድረግ በቅድሚያ እውነቱ በሙሉ ሊወጣ ይገባል፣ የእውነት ትንሽ የለውም፣ ሁሉም ጉዳይ መሸፈን መቻል አለበት፣ የሁሉም ጥሰት አይነቶች እውነት መውጣት ለእርቅ ዋናው መሠረት ነው፣
- እውነት ማውጣት በተወሰኑ ወንጀሎች ላይ ብቻ የሚንጠለጠል ከሆነ ለሌላ ብጥብጥ የመዳረጉ እድል ከፍተኛ ነው፣ ስለሆነም በህብረተሰቡ ውስጥ ትክክለኛ እርቅ እንዲፈጠር ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በሁሉም ጉዳዩች/ጥሰቶች ላይ እውነትን ማጣራት ይገባል፣
- ይህን አማራጭ መተግበር በሰዎች አእምሮ ውስጥ ፍትህ አለ የሚለውን ሀሳብ ይፈጥራል፣
- በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ብዙ ችግር ደርሷል፣ እያንዳንዱ የመብት ጥሰት በተጎጂው ላይ ጥሎት የሚያልፈው ጠባሳ አለ፣ ቁስሉ የሚሽረው እውነቱ ሲወጣ ነው፣ ይህን ማድረግ በቀጣይ ትውልድ ረገድ የደረሰው ግፍ ዳግም እንዳይፈፀም፣ ትምህርትም እንዲወሰድበት ያደርጋል፣
- ያለ እውነት ማጣራትና እርቅ ፍትህ አይሰፍንም፣ በዳይ እና ተበዳይ ፊት ለፊት ተገናኝተው ይቅርታ መጠያየቅ አለባቸው፣
- እውነትን ማፈላለጉ እርቅን ለማምጣት ብቻ አይደለም፣ ስለሆነም ለዕርቅ ስራ የሚውለው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል፣ ሌሎች እንደጥፋቱ ሁኔታ መቀጣት አለባቸው፣፣
- እውነት ማፈላለግ ለሁሉም ወንጀሎች መከናወኑ አንድ ጉዳይ ሆኖ እርቅ ግን እንደ ወንጀሉ አይነት ሊለያይ ይችላል፣ የተበዳይ ቁስል ሳይድን የሚመጣ ዕርቅ ይኖራል ብሎ ማመን ይከብዳል፣
- በግድያ ለተሳተፉ ይቅርታ ማድረግ ከባድ ነው፡ መቀጣት አለባቸው፣ ማፈናቀል እና ሌሎች መሰል ጥፋቶች ግን በይፋ ይቅርታ ከተጠየቀባቸው በይቅርታ ሊታለፉ ይገባል።

#### ለ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'ለሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች'

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች መካከል 18.5

ቡድኖች (ወይም 37.75%) የሚሆኑት ሂደቱ በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ መተግበር አለበት የሚል አቋም ይዘዋል።

### ሐ. በጥቂት የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'ለተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' (አማራጭ 2)

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ቡድኖች መካከል 3.5 ቡድኖች (ወይም 7.14%) የሚሆኑት ሂደቱ በተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ መተግበር አለበት የሚል አቋም ይዘዋል። ከቡድን ቡድን ቢለያይም ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- በሁሉም ጉልህ ጥሰቶች ላይ እውነት የማፈላለግ ተግባር ይከናወን ቢባል ጊዜ ይወስዳል፣ ዋናው ጉዳይ በተወሰኑ ጥሰቶች ላይ ትኩረት አድርጎ በፍጥነት መፍትሄ የሚገኝበት፣ የተፈናቀሉትም ወደ ቀያቸው የሚመለሱበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ ነው፣ (የአማራ ክልል የሴት ቡድኖች ውስን ተሳታፊዎች)
- እውነት የማጥራቱ ሥራ በተፈናቃይ ሁኔታዎች እና በግድያ ወንጀሎች ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ አለበት፣ በሁሉም ላይ እውነት የማጥራቱ ሥራ መሞከር ተግባራዊነቱን አስቸጋሪ ያደርገዋል፣
- ከብሔር ጋር በተያያዘ (ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ ወዘተ በማንነት እየተለዩ) ለሚፈጠሩ ችግሮችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ ለቤተሰባዊ ችግሮች እና ለእርስ በርስ ግጭቶች መፍቻነት እውነትን ማፈላለግና እርቅን መጠቀም ተገቢ ነው።

### መ. በአንድ የሴት ቡድን የተደገፈ አማራጭ፡ 'በህይወት የመኖር መብትና የሴቶች መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ አለበት' (ሌላ/አዲስ አማራጭ)

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች መካከል 1 ቡድን (ወይም 2.04%) ሂደቱ በህይወት የመኖር መብት ጥሰት እና የሴቶች መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ አለበት የሚል አማራጭ አቅርቧል።

ሰንጠረዥ 33፡ 'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች/ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል'? - የሴት ተጎጂ ቡድኖች አገር-አቀፍ/ክልል ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | በሁሉም ሰብዓዊ መብት ጥሰት ላይ (አዲስ አማራጭ) | ሌላ አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | 2 | 0 | 0 | |
| 2 | አፋር[52] | 1 | 0 | 0 | 0 | |
| 3 | አማራ | 7 | 2 | | 5 | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 1 | 0 | 1 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 | 0 | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 | 0 | |
| 7 | ሀረሪ[53] | 1 | 0 | 0 | 0 | |
| 8 | ኦሮሚያ[54] | 14 | 6 | 0 | 5 | 1 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 | 0 | |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 2 | 0 | 0 | |

[52] አንድ ቡድን ሀሳብ አልሰጠም።
[53] አንድ ቡድን ሀሳብ አልሰጠም።
[54] ሁለት ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ[55] | 9 | 1.5 | 3.5 | 2 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 1 | 0 | 1 | |
| 13 | ትግራይ | 5 | 0 | 0 | 5 | |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 49 | 18.5 | 3.5 | 19 | 1 |

II. **የወንድ ተጎጂዎች ቡድን**

**ሀ. በተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'ሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' (አማራጭ 1)**

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 15 ቡድኖች (ወይም 31.91%) የሚሆኑት እውነትን የማጣራት እና የእርቅ ተግባራት በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ መተግበር አለባቸው የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል፡፡ ይህንን አማራጭ ለመደገፍ የቀረቡት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዕውነትን የማጥራት ጉዳይ ለተወሰኑ ጉዳዮች ብሎ መገደብ ተገቢ አይሆንም፣ የተጣሱት ሁሉም መብቶች ናቸው፣ ለሰው ልጅ እኩል ጥቅም አላቸው፣ ስለሆነም ድንበር ሳይበጅላቸው እኩል ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፣
- ከሰብዓዊ መብቶች እርስ በርስ ተያያዥነት አንጻር ሁሉም ጥሰቶች በእውነት ፍለጋና እርቅ ሂደት መካተት አለባቸው፣ ሰብአዊ መብቶች የሚነጣጠሉ አይደሉም፣
- የሁሉም ተጎጂ ወገኖች መብትና ስሜት ሊጠበቅ ይገባል፣ ለአንዱ ጉልህ የሆነው ለሌላው ቀላል ሊሆን ይችላል፣ አማራጩ የዚህ አይነት ልዩነትን ለማስወገድ ይረዳል፣
- ሁሉንም የሰብዓዊ መብት ጥሰት አስመልክቶ እውነትን ማውጣት የቆየ ቁስልን ለማከም፣ በሀሰት ትርክት የሚፈጠር ግጭትን ለማስቀረት ያግዛል፣ ፍትህ ያሰፍናል፣ መጠየቅ ያለበትን ለመጠየቅ ይረዳል፣ ይቅርታ ለማድረግ የሚተው ጉዳይ መኖር የለበትም፣
- ይህ አማራጭ ትክክለኛ እርቅና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት፣ የማህበረሰብን ግንኙነት ለማጠናከር ያስችላል፣
- የሽግግር ፍትህን ዕውን ለማድረግ እውነት በየደረጃው በሁሉም ጉዳዮች አንፃር ሊጠራ ይገባል፣
- "እውነት እውነት ነው" በማንኛውም ሁኔታ ተደብቆ መቅረት የለበትም፣ በሁሉም ጉልህ የመብት ጥሰቶች እውነት አለኝ የሚል ሁሉ እውነቱ ሊወጣለት ይገባል፣
- በሁሉም ጥሰቶች ላይ የክስ ሂደት ባይኖር እንኳ በሁሉም ጥሰቶች ላይ እውነት ሊወጣ ይገባል፣ ይህን ማድረግ ለተጎጂው ቁስሉ የሚሽረበትን እድል ይፈጥራል፣
- ይህ አማራጭ 'ጉልህ ያልሆነ ጥሰት' የሚለውን የልዩነት መስመር በግልጽ ስለማይነግር ጉልህ ያልሆኑ ጥሰቶች ሁሉ ጭምር እንዲሸፈኑ እና እንዳይደገሙ ለማድረግ ይረዳል፣
- እውነትን ማጣራትና እርቅ ለፍትህ መስፈን አስፈላጊ ናቸው፣
- ጥሰትን አስመልክቶ እውነትን የማጥራት ሥራ የሽግግር ፍትህ ሂደት ዋናው መሰረት ነው፣ የሚታወቁ እውነቶች ሳይነገሩ መታለፍ አይኖርባቸውም፣ ሁሉንም ጥሰቶች አስመልክቶ የሚወጣ እውነት አገሪቱን ወደ ሰላም ያመጣል፡፡

**ለ. በአብዛኛው የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'ለተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' (አማራጭ 2)**

[55] ሁለት ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም፡፡

‘እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 17.5 ቡድኖች (ወይም 37.23%) የሚሆኑት ሂደቱ በተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ መተግበር አለበት የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል። ይህን አማራጭ ለመደገፍ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- በሁሉም ጥፋቶችና አጥፊዎች ላይ እውነት ማፈላለግ/እርቅ ማካሄድ ከባድና ውስብስብ ይሆናል፣ ባለው አገራዊ ኢኮኖሚና የሰው ሃይል አቅም ይህን ማድረግ አዳጋች ነው፣ በአሰራር ደረጃም አስቸጋሪ ይሆናል፣
- ለሁሉም ጥሰቶች መፍትሄ መስጠት አይቻልም፣ ሁሉንም በእርቅ መጨረስም አያስኬድም፣
- በሁሉም ጉዳይ ላይ እውነት ይጣራ ከተባለ በውጤታማነቱ ላይ ከፍ ያለ ተግዳሮት ይፈጥራል፣
- የሽግግር ፍትህን በጊዜ መስመር ለማስያዝ ሂደቱ በውስን ጉልህ የመብቶች ጥሰት ላይ ማተኮር ይኖርበታል፣
- እውነትን ማፈላለግና እርቅን በዋናነት ከብሔር ጋር ተያይዞ በማንነት ምክንያት ለሚፈጠሩ ችግሮችና የመብት ጥሰቶች፣ እንዲሁም ለእርስ በእርስ ግጭቶች መፍቻነት ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ ነው፣
- ሂደቱ ለዛሬዎቹ ግጭቶች መነሻ በሆኑ የተዛቡ ትርክቶች/የታሪክ አተያዮች ላይ በተቻለ መጠን ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል።

**ሐ. በተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ ‘በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ላይ’**

‘እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 12.5 ቡድኖች (ወይም 26.59%) የሚሆኑት ሂደቱ በሁሉም (ጉልህ) የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ መተግበር አለበት የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል።

**መ. በጥቂት ተሳታፊዎች  የተደገፈ አማራጭ፡ ‘የተለየ ሀሳብ’**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ የተወሰኑ ተሳታፊዎች የከፉ የሰብዓዊ መብቶት ጥሰቶች፣ ዘር ማጥፋት፣ እና በተለያዩ ሥርዓት-መንግሥታት የተፈጸሙ ከባድ ስልታዊና መንግስት-አቀፍ ጥሰቶች በወንጀል ተጠያቂነት ማዕቀፍ እንጂ በእውነትና እርቅ ሂደት ሊታዩ አይገባም የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።

‘እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች 2 ቡድኖች (ወይም 4.2%) ሥራው በተወሰኑ ቀላል በሚባሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ያተኮረ መሆን አለበት የሚል አቋም አራምደዋል።

ሰንጠረዥ 34፡ ‘እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች/ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል’? - የወንድ ተጎጂ ቡድኖች አገር-አቀፍ/ክልል-አቀፍ ምልከታ

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ላይ አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 1 | 4 | 2 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 0 | 1 | 1 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 0 | 1 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0.5 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 8 | 4 | 2 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 1 | 2 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ[56] | 9 | 0.5 | 4.5 | 2 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 1 | 1 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 0 | 0.5 | 4.5 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 47 | 15 | 17.5 | 12.5 |

## III. የቅልቅል ቡድን

### ሀ. በአብዛኞዎቹ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ'

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች መካከል 30.5 ቡድኖች (ወይም 31.77%) የሚሆኑት ሂደቱ በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ መተግበር አለበት የሚለውን ሀሳብ አራምደዋል። ይህን አማራጭ ለመደገፍ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ሁሉንም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተመለከተ እውነት ማፈላለግና የእርቅ ተግባር ማከናወን አገር/ህዝብ ወደፊት በሰላም አብሮ እንዲኖር ያደርጋል፣
- በሁሉም የወንጀል ዓይነቶች ላይ እውነትን ማጥራትና ማወቅ ለአስተምህሮ፣ በክስ ማዕቀፍ ውስጥ የሚወድቁትንና የማይወድቁትን ለመለየት፣ በምሕረት የሚታለፈውን ለመምረጥ፣ በእርቅ ለመጨረስና ለታሪክ ለማስቀመጥ እድል ይሰጣል፣
- በሁሉም ጥሰቶች ላይ እውነትን ማጥራት ማህበረሰብ በሁሉም ጥሰቶች አንፃር ምን ተከሰተ፣ በማን፣ የት እና መቼ የሚለውን ለማወቅ ያስችላል፣
- ሁሉም ሰብአዊ መብቶች አይበላለጡም፣ አይተናነሱም፣ ስለሆነም በሁሉም ጉዳዮች/ጥሰቶች ላይ ያተኮረ እውነትን የማጣራት ስራ ሊሰራ ይገባል፣
- ጉልህ የሆነና ያልሆነ የሚለው ጉዳይ ላልተገባ አተያይ በር ስለሚከፍት እውነት ማጥራትና እርቅ በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ሊከናወን ይገባል፣
- ጉልህ የሚባለው ጉዳይ እንደየአከባቢው ሁኔታ ልዩነት ሊኖረው ቢችልም በተቻለ መጠን ሁሉ በሁሉም የመብት ጥሰቶች ላይ እውነት እንዲወጣ ቢደረግ አገር ይፈወሳል፣
- ወንጀሎችና ጥሰቶች በተበዳይ አይን እኩል ክብደት አላቸው፣ ሂደቱ ለሁሉም ጉልህ ጥሰቶች ተመሳሳይ ትኩረትና ክብደት ሊሰጥ ይገባል፣ ተበድያለሁ ለሚል አካል ብቸኛው ማዳኛ መንገድ እውነትን ማውጣትና እውቅና መስጠት ነው፣ ቂም በሆዱ የያዘን ማህበረሰብ ይዞ አገራዊ እርቅ ማምጣት አይታሰብም፣
- ሂደቱ በተወሰኑ ጥፋቶች ላይ ብቻ የሚከናወን ከሆነ ተጎጂዎች ቁስላቸው እንዳይሽር፣ ተዳፍኖም እንዲቀር ያደርጋል፣ ቀይቶም ሊያገረሽ ይችላል፣
- በተለያዩ ስርአቶች በአገረ-መንግስቱ ግንባታ ሂደት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ የዘር ወይም ጅምላ ጭፍጨፋዎች እና ሃሰተኛ የታሪክ ትርክቶች አሁን ላለንበት አገራዊ ቀውስ ምክንያት ሆነዋል፣ ስለሆነም የወንጀሉ ደረጃ ግምት ውስጥ ሳይገባ በሁሉም ጥሰቶች ላይ ትኩረት መደረግ አለበት፣
- እውነት ካልወጣ የታሰበው ሀገራዊ እርቅ ሊሳካ አይችልም፣ "እውነት በሌለበት ሰላም የለም" "Bakka dhugaan hin jirre nagaan hin jiru" የሚለው አባባል ጉዳዩን በደንብ ይገልጸዋል፣

[56] ሁለት ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም።

- ለሁሉም የመብት ጥሰቶች እውነት መመስረት ለሽግግር ፍትህና ዕርቅ ስራ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፣ ቂም በቀልን ያስቀራል፣ መተማመንን ለማምጣት ያግዛል።

**ለ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ' (አማራጭ 1)**

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 29.5 ቡድኖች (ወይም 30.72%) የሚሆኑት የስራ ሂደቶቹ በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ መተግበር አለባቸው የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል።

**ሐ. በተወሰኑ ቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'በተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ' (አማራጭ 2)**

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 ቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 24 ቡድኖች (ወይም 25%) የሚሆኑት እውነትን የማጣራት እና የእርቅ ሂደቶች በውስን ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ መተግበር አለባቸው የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል። በምክንያትነትም የሚከተሉትን ነጥቦች አንስተዋል።

- ከጥሰቶች/አጥፊዎች ብዛት አንፃር በሁሉም ጉልህ የመብት ጥሰቶች ላይ እውነትን ማፈላለግ አስቸጋሪ ነው፣
- ሂደቱ ከሚወሰደው ጊዜ፣ ጉልበት፣ ሀብት እና ውጤታማነት አንፃር በሁሉም ጥሰት ላይ እውነት ለማውጣት መሞከር ሊተገበር የሚችል ሀሳብ አይደለም፣ ቶሎ ወደ እርቅ፣ ሰላምና ሀገራዊ መግባባት ለመምጣት ያስቸግራል፣ ስለሆነም በተወሰኑ ጉልህ ጥሰቶች ላይ ማተኮር ግድ ይላል፣
- ሁሉንም ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች ለመክሰስ ማሰብ አፈፃፀሙ አስቸጋሪ ይሆናል፣ በመሆኑም ቀላል የወንጀል ጉዳዮች ሁሉ በእውነት/እርቅ ሂደት እንዲፈቱ ማድረግ ተገቢ ነው፣
- በሂደቱ በዘር ማጥፋት ወንጀል፣ የጦር ወንጀል፣ በሰዎች እና በንብረት ላይ በሚፈፀሙ ከባድ ጥፋቶች፣ ኢሰብአዊ ድብደባ፣ መድፈር፣ በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀም ወንጀል ወዘተ ላይ ትኩረት ቢደረግ የተሻለ ይሆናል።

**መ. በጥቂት ቡድን የቀረበ ሌላ አማራጭ**

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች መካከል አንድ ቡድን (1.04%) የሚሆነው እውነት ማፈላለግ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ሊተገበር ይገባል፣ እርቅን በተመለከተ ግን ከእርስ በእርስ ጦርነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ቢተኮር ይመረጣል ብሏል።

በሌላ በኩል አንድ ቡድን (1.04%) በዓለም አቀፍ ሕግ መሰረት መታየት ያለባቸው ጉዳዮች በቅድሚያ ከተለዩ በኋላ ብቻ በዕርቅ ሊታዩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ እውነት የማውጣት ተግባር ሊከናወን ይገባል ብሏል።

*ሰንጠረዥ 35፡ 'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች/ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል'? - አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች በአገር-አቀፍ/ክልል-አቀፍ ምልከታ*

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሁሉም የሰብአዊ መብት ጥሰት አዲስ አማራጭ | ሌላ አዲስ አማራጭ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | 6 | 0 | 0 | | |
| 2 | አፋር | 2 | 2 | 0 | 0 | | |
| 3 | አማራ | 13 | 3 | 4 | 4 | | 2 ቡድኖች ሀሳብ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | አልሰጡም |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | 3.5 | 0.5 | 0 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | 1 | 1 | 0 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 0 | 1 | 0 | | 1 ቡድን ሀሳብ አልተሰጠም |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 1 | 0 | 1 | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 4 | 7 | 13 | 1 | 2 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 9 | ሲዳማ | 2 | 1 | 1 | 0 | | |
| 10 | ሶማሌ | 4 | 4 | 0 | 0 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 3 | 6.5 | 4.5 | 1 | 3 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 0 | 1 | 1 | | 2 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 13 | ትግራይ | 10 | 1 | 2 | 7 | | |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 96 | 29.5 | 24 | 30.5 | 2 | 10 |

## IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን

### ሀ. በአብዛኛዎቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ ‘በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ’ (አማራጭ 1)

‘እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች መካከል 14 ቡድኖች (ወይም 58.33%) የሚሆኑት እውነትን ማጣራት እና እርቅ በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ መተግበር አለበት የሚል አቋም ይዘዋል። ይህን አማራጭ ለመደገፍ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ሰብአዊ መብቶች አይነጣጠሉም፣ የአንዱ መብት መጣስ በተለይም የኢኮኖሚ/የማህበራዊ መብቶች መጣስ ለሲቪልና ፖለቲካ መብቶች መጣስ በቀጥታ አስተዋጽኦ አለው፣ መብቶችን መነጣጠል በራሱ ኢፍትሀዊ ነው፣
- ሂደቱ የተወሰኑ ጥሰቶችን ብቻ ይሸፍን ከተባለ ወጥነት የሌለው አድሎአዊ አሰራርን ያመጣል፣ በማህበረሰብ ዘንድ ቅሬታን ይፈጥራል፣
- ይህ አማራጭ የሁሉንም ተበዳዮች ፍላጎት ማካተት ያስችላል፣ ለተጎጂዎች እርካታ ይፈጥራል፣ ለእርቅና አብሮ መኖር መሰረት ይጥላል፣
- ተጎጂዎች የደረሰባቸውን በደል በሙሉ እንዲናገሩ እድል መስጠት የግጭትን ኡደት ለመለወጥ ያስችላል፣
- እውነትን ማፈላለግ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ አይደለም፣ ስለሆነም ተጠያቂነት በማይመሰረትበት ጉዳይ ጭምር የሁሉም እውነት መውጣት የመብት ጥሰቶችን ሽፋን ያሳካል።

### ለ. በተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ ‘ለተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች’ (አማራጭ 2)

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 3 ቡድኖች (ወይም 12.5%) የስራ ሂደቱ በውስን ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ መተግበር አለበት የሚል ሀሳብ አራምደዋል። ይህን አማራጭ ለመደገፍ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ እውነት የማፈላለግ ስራ መስራት የሚቻል አይደለም፣ ትኩረቱ በተወሰኑት እና ለቁርሾ ምክንያት በሆኑት ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል፣
- በዋናነት እንደ ሀገር የሚለያዩን እና ጎልተው የሚታዩት ጉዳዮች ከማንነት፣ ከብሄርና ከሀይማኖት መብቶች ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ጥሰቶች ናቸው፣ የነዚህ ጥሰቶች እውነት ሊወጣ ይገባል፣
- ሌላ አማራጭ መከተል የሽግግር ፍትህ ስራውን ወሰን ለማስመር እክል ይፈጥራል፣
- የሽግግር ፍትህ ስራን የሚሰራው አካል ስልጣኑ በጊዜ የተገደበ ነው፣ የሁሉም ጥሰት እውነት ይውጣ ከተባለ የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን ወደኋላ በጣም ይጎተታል፣ በሁሉም ጉዳይ ላይ ግብዓት ለመሰብሰብም ጊዜው ሊበቃ አይችልም፣ አልፎም አንዳንድ ጉዳዮች ተነካክተው በአግባቡ ሳይፈቱ ሊቀሩ ይችላሉ፣ ስለሆነም ለሰላምና ለእርቅ በሚበጁ ዋና ዋና ጥሰቶች ላይ ብቻ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል፣
- እውነት የማውጣትና የእርቅ ሂደቱ በሲቪልና በፖለቲካ መብቶች ላይ ማተኮር አለበት፣ ምክንያቱም ለአብሮ መኖር ፈተና የሚሆኑት ኩነቶች በዋናነት የሚመነጩት ከነዚህ መብቶች መጣስ ስለሆነ።

*ሰንጠረዥ 36፡ 'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል'? - አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቡድኖች አገር አቀፍ/ክልል-አቀፍ ምልከታ*

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰት | ሌላ አዲስ አማራጭ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| 2 | አፋር | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 ቡድን ሀሳብ አልተሰጠም |
| 3 | አማራ | 5 | 2 | 0 | 2 | 0 | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 ቡድን ሀሳብ አልተሰጠም |
| 7 | ሀረሪ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | 5.5 | 1.5 | 0 | 0 | |
| 9 | ሲዳማ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| 10 | ሶማሌ | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 3 | 2 | 1 | 0 | 0 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| 13 | ትግራይ | 4 | 2.5 | 0.5 | 0 | 1 | |
| | **ሀገር-አቀፍ** | **24** | **14** | **3** | **2** | **1** | **4** |

| | ማጠቃለያ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|

## 6.3.2.2.'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል'? - አገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 77 ቡድኖች (ወይም 35.64%) የሚሆኑት ሂደቱ ሁሉንም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መሸፈን ይገባዋል የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል።

በሌላ በኩል 64 ቡድኖች (ወይም 29.62%) የሚሆኑት ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ የእውነት ማፈላለግና የዕርቅ ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል የሚል አማራጭ አቅርበዋል።

48 ቡድኖች (ወይም 22.22%) የሚሆኑት ደግሞ ሂደቱ በተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ሊያተኩር ይገባዋል የሚል ሀሳብ አራምደዋል።

4 ቡድኖች (ወይም 1.85%) ደግሞ አዲስ አማራጭ አቅርበዋል። ሌሎች 23 የትኩረት ውይይት ቡድኖች (ወይም 10.64%) በጥያቄው ላይ ሀሳብ አልሰጡም።

### ግኝቱ ውይይቶቹ ከተካሄዱባቸው ክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች አንጻር ሲተነተን

ይህ መረጃ ውይይቱ ከተካሄደባቸው ክልሎች/የከተማ አስተዳደሮች አንጻር ሲተነተን በአማራ እና ትግራይ ክልል ቡድኖች በአብላጫው የእውነት ማፈላለግና የእርቅ ተግባራት በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ላይ ሊሆን ይገባል ሲሉ (የቀድሞው) የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል በአብዛኛው 'የተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት' የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። ጋምቤላ ክልል ለአማራጭ 1 እና አማራጭ 2 እኩል ድምጽ ሲሰጥ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል አማራጭ 1፣ አማራጭ 2 እና 'በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ላይ' የሚሉት አማራጮች እኩል ድምጽ አግኝተዋል። ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት ክልሎች በአብላጫው 'በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ' መተግበር አለበት የሚለውን አማራጭ (1) ደግፈዋል።

### ግኝቱ ከተለያዩ ቡድኖች አንጻር ሲታይ

ከቡድን አንጻር ሲታይ የሴት ተጎጂዎች እና የቅልቅል ቡድኖች እኩል በሚባል ድምጽ 'በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት' እና 'በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' ላይ የሚሉት አማራጮች ድጋፍ አግኝተዋል።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች በአብላጫ የተደገፈው ሀሳብ የእውነት ማጣራትና እርቅ ስራ ሂደት 'በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' ላይ ሊተገበር ይገባል የሚለው ነው።

የወንድ ተጎጂ ቡድኖች በአብላጫ 'በተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ይተግበር' የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል።

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ 'በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች'፡ 'ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' እና 'በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' **የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተጠቃለው ቀርበዋል።**

### ሀ. አገር አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'ሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' እና 'ሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' ላይ ያተኮረ እውነትን የማፈላለግና የእርቅ ተግባር - ምክንያቶች

- ሰብአዊ መብቶች አይነጣጠሉም፣ አይበላለጡም፣ አይተናነሱም፣ የአንዱ መብት መጣስ ለሌሎች መብቶች መጣስ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ አለው፣ መብቶችን መነጣጠል በራሱ ኢፍትሀዊ ነው፣ ስለሆነም በሁሉም ጉዳዮች/ጥሰቶች ላይ ያተኮረ እውነትን የማጣራት ስራ ሊሰራ ይገባል፣
- ዕውነትን የማጣራት ጉዳይ ለተወሰኑ ጉዳዮች ብሎ መገደብ ተገቢ አይሆንም፣ የተጣሱት ሁሉም መብቶች ናቸው፣ ለሰው ልጅ እኩል ጥቅም አላቸው፣ ድንበር ሳይበጅላቸው እኩል ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፣
- ይህ አማራጭ ጉልህ ያልሆነ ጥሰት የሚለውን የልዩነት መስመር በግልጽ ስለማይነግር ጉልህ ያልሆኑ ጥሰቶች ጭምር እንዲሸፈኑ እና እንዳይደገሙ ለማድረግ ይረዳል፣
- ጉልህ የሆነና ያልሆነ የሚለው ጉዳይ ላልተገባ አተያይ በር ስለሚከፍት እውነት ማጥራትና እርቅ በሁሉም የሰብዓዊ  መብት ጥሰቶች ላይ ሊከናወን ይገባል፣
- ጉልህ የሚባለው ጉዳይ እንደየአከባቢው ሁኔታ ልዩነት ሊኖረው ቢችልም በተቻለ መጠን በሁሉም የሙብት ጥሰቶች ላይ እውነት እንዲወጣ ቢደረግ አገር ይፈወሳል፣
- ሁሉንም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተመለከተ እውነት ማፈላለግና የእርቅ ተግባር ማከናወን አገር/ህዝብ ወደፊት በሰላም አብሮ እንዲኖር ያደርጋል፣
- በሁሉም ጥሰቶች ላይ እውነትን ማጥራት ማህበረሰብ በሁሉም ጥሰቶች አንፃር ምን ተከሰተ፣ በማን፣ የት እና መቼ የሚለውን ለማወቅ ያስችላል፣ ለአስተምህሮ፣ በክስ ማዕቀፍ ውስጥ የሚወድቁትንና የማይወድቁትን ለመለየት፣ በምሕረት የሚታለፈውን ለመምረጥ፣ በእርቅ ለመጨረስና ለታሪክ ለማስቀመጥ እድል ይሰጣል፣
- ሁሉንም የሰብዓዊ መብት ጥሰትን አስመልክቶ እውነትን ማውጣት የቆየ ቁስልን ለማከም፣ በሀሰት ትርክት የሚፈጠር ግጭትን ለማስቀረት ያግዛል፣ ፍትህ ያሰፍናል፣ መጠየቅ ያለበትን ለመጠየቅ ይረዳል፣ ጥላቻ እንዲቀንስ ያደርጋል፣ መግባባት ይፈጥራል፣ ሰላም ያሰፍናል፣ ሰላማዊ ማህበራዊ ግንኙነት ያስቀጥላል፣
- ሂደቱ የተወሰኑ ጥሰቶችን ብቻ ይሸፍን ከተባለ ወጥነት የሌለው አድሎአዊ አሰራርን ያመጣል፣ በማህበረሰብ ዘንድ ቅሬታን ይፈጥራል፣ ቂምና በቀልን ይፈጥራል፣
- ይቅርታ ለማድረግ በቅድሚያ እውነቱ በሙሉ ሊወጣ ይገባል፣ የእውነት ትንሽ የለውም፣ የሁሉም ጥሰት አይነቶች እውነት መውጣት  ለእርቅ ዋናው መሠረት ነው፣
- በተለያዩ ስርአቶች በአገረ-መንግስቱ ግንባታ ሂደት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ የዘር ወይም ጅምላ ጭፍጨፋዎች እና ሃሰተኛ የታሪክ ትርክቶች አሁን ላለንበት አገራዊ ቀውስ ምክንያት ሆነዋል፣ ስለሆነም የወንጀሉ ደረጃ ግምት ውስጥ ሳይገባ በሁሉም ጥሰቶች ላይ ትኩረት መደረግ አለበት፣
- በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ብዙ ችግር ደርሷል፣ እያንዳንዱ የሙብት ጥሰት በተጎጂው ላይ ጥሎት የሚያልፈው ጠባሳ አለ፣ ቁስሉ የሚሽረው እውነቱ ሲወጣ ነው፣ ይህን ማድረግ በቀጣይ ትውልድ የደረሰው ግፍ ዳግም እንዳይፈፀም፣ ትምህርትም እንዲወሰድበት ያደርጋል፣
- ይህ አማራጭ የሁሉንም ተበዳዮች ፍላጎት ማካተት ያስችላል፣ ለተጎጂዎች እርካታ ይፈጥራል፣ ለእርቅና አብሮ መኖር መሰረት ይጥላል፣ ተጎጂዎች የደረሰባቸውን በደል በሙሉ እንዲናገሩ እድል መስጠት የግጭትን ኡደት ለመለወጥ ያስችላል፣
- እውነት ካልወጣ የታሰበው ሀገራዊ እርቅ ሊሳካ አይችልም፣ "እውነት በሌለበት ሰላም የለም" "Bakka dhugaan hin jirre nagaan hin jiru" የሚለው አባባል ጉዳዩን በደንብ ይገልጸዋል፣
- ያለ እውነት ማጣራትና እርቅ ፍትህ አይሰፍንም፣ በዳይ እና ተበዳይ ፊት ለፊት ተገናኝተው ይቅርታ መጠያየቅ አለባቸው፣
- ወንጀሎችና ጥሰቶች በተበዳይ አይን እኩል ክብደት አላቸው፣ ሂደቱ ለሁሉም ጉልህ ጥሰቶች ተመሳሳይ ትኩረትና ክብደት ሊሰጥ ይገባል፣ ተበድያለሁ ለሚል አካል ብቸኛው ማዳኛ መንገድ እውነትን ማውጣትና እውቅና መስጠት ነው፣ ቂም በሆዱ የያዘን ማህበረሰብ ይዞ አገራዊ እርቅ ማምጣት አይታሰብም፣

- የሁሉም ተጎጂ ወገኖች መብትና ስሜት ሊጠበቅ ይገባል፣ ለአንዱ ጉልህ የሆነው ለሌላው ቀላል ሊሆን ይችላል፣ አማራጩ የዚህ አይነት ልዩነትን ለማስወገድ ይረዳል፣
- "እውነት እውነት ነው" በማንኛውም ሁኔታ ተደብቆ መቅረት የለበትም፣ በሁሉም ጉልህ የመብት ጥሰቶች እውነት አለኝ የሚል ሁሉ እውነቱ ሊወጣለት ይገባል፣ ሂደቱ በተወሰኑ ጥፋቶች ላይ ብቻ የሚከናወን ከሆነ ተጎጂዎች ቁስላቸው እንዳይሽር፣ ተዳፍኖም እንዲቀር ያደርጋል፣ ቆይቶም ሊያገረሽ ይችላል፣
- እውነትን ማፈላለጉ እርቅን ለማምጣት ብቻ አይደለም፣ ስለሆነም ለዕርቅ ስራ የሚውለው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል፣ ሌሎች እንደጥፋቱ ሁኔታ መቀጣት አለባቸው፣
- በሁሉም ጥሰቶች ላይ የክስ ሂደት ባይኖር እንኳ በሁሉም ጥሰቶች ላይ እውነት ሊወጣ ይገባል፣ ይህ ለተጎጂው ቁስሉ የሚሽረበትን እድል ይፈጥራል፣
- እውነት ማፈላለግ ለሁሉም ወንጀሎች መከናወኑ አንድ ጉዳይ ሆኖ እርቅ ግን እንደ ወንጀሉ አይነት ሊለያይ ይችላል፣ የተበዳይ ቁስል ሳይድን የሚመጣ ዕርቅ ይኖራል ብሎ ማመን ይከብዳል፣
- ለገደሉ ይቅርታ ማድረግ ከባድ ነው፣ መቀጣት አለባቸው፣ ማፈናቀል እና ሌሎች መሰል ጥፋቶች ግን በይፋ ይቅርታ ከተጠየቀባቸው በይቅርታ ሊታለፉ ይችላሉ፣
- እውነትን ማፈላለግ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ አይደለም፣ ስለሆነም ተጠያቂነት በማይመሰረትበት ጉዳይ ጭምር የሁሉም እውነት መውጣት የመብት ጥሰቶችን ሽፋን ያሳካል፣፣
- ይህን አማራጭ መተግበር በሰዎች አእምሮ ውስጥ ፍትህ አለ የሚለውን ሀሳብ ይፈጥራል፣
- ይህ አማራጭ ትክክለኛ እርቅና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት፣ የማህበረሰብን ግንኙነት ለማጠናከር ያስችላል፣
- ጥሰትን አስመልክቶ እውነትን የማጣራት ሥራ የሽግግር ፍትህ ሂደት ዋናው መሰረት ነው፣ የሚታወቁ እውነቶች ሳይነገሩ መታለፍ አይኖርባቸውም፣ ለሁሉም የመብት ጥሰቶች እውነት መመስረት ለሽግግር ፍትህና ዕርቅ ስራ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፣ ቂም በቀልን ያስቀራል፣ መተማመንን ለማምጣት ያግዛል፣
- የእውነት ማፈላለግ ሂደት ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ መልህቅ ነው፣ እውነት ከተጣራ ይቅር ማለት ይቻላል፣ እውነት ካልታወቀ፣ ይቅር ካልተባለ እና እርቅ ካልመጣ ወደፊት መጓዝ አይታሰብም፣
- የሽግግር ፍትህን ዕውን ለማድረግ እውነት በየደረጃው በሁሉም ጉዳዮች አንፃር ሊጠራ ይገባል።

**ለ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'በተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ' ያተኮረ እውነትን የማፈላለግና የእርቅ ተግባር - ምክንያቶች**

- ሂደቱ ከሚወሰደው ጊዜ፣ ጉልበት፣ ሀብት እና ውጤታማነት አንፃር በሁሉም ጥሰት ላይ እውነት ለማውጣት መሞከር ሊተገበር የሚችል ሀሳብ አይደለም፣ በቶሎ ወደ እርቅ፣ ሰላምና ሀገራዊ መግባባት ለመምጣት ያስቸግራል፣ ስለሆነም በተወሰኑ ጉልህ ጥሰቶች ላይ ማተኮር ግድ ይላል፣
- ከጥሰቶች/አጥፊዎች ብዛት አንፃር በሁሉም ጉልህ የመብት ጥሰቶች ላይ እውነትን ማፈላለግ አስቸጋሪ ነው፣ ከባድና ውስብስብ ይሆናል፣
- ሁሉንም ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች ለመክሰስ ማሰብ አፈፃፀሙ አስቸጋሪ ይሆናል፣ በመሆኑም ቀላል የወንጀል ጉዳዮች ሁሉ በእውነት/እርቅ ሂደት እንዲፈቱ ማድረግ ተገቢ ነው፣
- የሽግግር ፍትህን በጊዜ መስመር ለማስያዝ ሂደቱ በውስን ጉልህ የመብቶች ጥሰት ላይ ማተኮር ይኖርበታል፣ ሌላ አማራጭ መከተል የሽግግር ፍትህ ስራውን ወሰን ለማስመር እክል ይፈጥራል፣
- የሂደቱ ትኩረት በተወሰኑ ለቁርሾ ምክንያት በሆኑና መሰል ጥሰቶች ላይ በመስራት በፍጥነት መፍትሄ የሚገኝበትና የተፈናቀሉት ወደ ቀያቸው የሚመለሱበት ሁኔታ እንዲፈጠር በማድረግ ላይ መሆን አለበት፣
- እውነት የማጣራቱ ሥራ በተፈናቃይ ሁኔታዎች፣ በግድያ ወንጀሎች፣ በሲቪልና በፖለቲካ መብቶች ላይ ማተኮር አለበት፣ ለአብሮ መኖር ፈተና የሆኑት ኩነቶች በዋናነት የሚመነጩት ከነዚህ መብቶች መጣስ ነው፣

- እንደ ሀገር የሚለያዩን እና ጎልተው የሚታዩት ጉዳዮች ከማንነት፣ ከብሄርና ከሀይማኖት መብቶች ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ጥሰቶች ናቸው፣ የነዚህ ጥሰቶች እውነት ሊወጣ ይገባል፣ ይህ አማራጭ ከብሔር ጋር ተያይዞ በማንነት ምክንያት ለሚፈጠሩ ችግሮች፣ የመብት ጥሰቶች እና የእርስ በእርስ ግጭቶች መፍቻነት ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ ነው፣
- ሂደቱ ለዛሬዎቹ ግጭቶች መነሻ በሆኑ የተዛቡ ትርክቶች/የታሪክ አተያዮች፣ በዘር ማጥፋት ወንጀል፣ የጦር ወንጀል፣ በሰዎች እና በንብረት ላይ በሚፈፀሙ ከባድ ጥፋቶች፣ ኢሰብአዊ ድብደባ፣ መድፈር፣ በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀም ወንጀል ወዘተ ላይ ትኩረት ቢያደርግ የተሻለ ይሆናል፣
- የሽግግር ፍትህ ስራን የሚሰራው አካል ስልጣኑ በጊዜ የተገደበ ነው፣ የሁሉም ጥሰት እውነት ይውጣ ከተባለ የሽግግር ፍትህን የጊዜ ወሰን ወደኋላ ይጎትታል፣ በሁሉም ጉዳይ ላይ ግብዓት ለመሰብሰብም ጊዜው ሊበቃ አይችልም፣ አልፎም አንዳንድ ጉዳዮች ተነካክተው በአግባቡ ሳይፈቱ ሊቀሩ ይችላሉ፣ ስለሆነም ለሰላምና ለእርቅ በሚበጁ ዋና ዋና ጥሰቶች ላይ ብቻ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## ሐ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፣ አዲስ አማራጭ

- የእውነት ማፈላለግና የዕርቅ ሥራ በተወሰኑ ቀላል በሚባሉ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ያተኮረ መሆን አለበት፣
- ሂደቱ በሀይወት የመኖር እና የሴቶች መብት ጥሰቶች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፣
- ከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ ዘር ማጥፋትና በተለያዩ ሥርዓት-መንግሥታት የተፈጸሙ ከባድ ስልታዊና መንግስት-አቀፍ ጥሰቶች በወንጀል ተጠያቂነት ማዕቀፍ እንጂ በእውነትና እርቅ ሂደት ሊታዩ አይገባም፣
- እውነት ማፈላለግ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ሊተገበር ይገባል፣ እርቅን በተመለከተ ግን ከእርስ በእርስ ጦርነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ቢተኮር ይመረጣል፣
- በዓለም አቀፍሕግ መሰረት መታየት ያለባቸው ጉዳዮች በቅድሚያ ከተለዩ በኋላ ብቻ በዕርቅ ሊታዩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ እውነት የማውጣት ተግባር ሊከናወን ይገባል፡፡

ሰንጠረዥ 37፣ 'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል'? - አገራዊ የአራቱም ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሁሉም የሰብአዊ መብት ጥሰት (አዲስ አማራጭ) | አዲስ አማራጭ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | 8 | 0 | 0 | 0 | |
| 2 | አፋር | 5 | 3 | 0 | | 0 | 2 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 3 | አማራ | 32 | 8 | 8 | 13 | 0 | 3 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 5.5 | 1.5 | 2 | 0 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 3 | 1 | 1 | 0 | |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 1.5 | 1.5 | 0 | 0 | 2 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 2 | 0 | 1 | 0 | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 23.5 | 12.5 | 20 | 2 | 4 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 9 | ሲዳማ | 4 | 3 | 1 | | 0 | |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 7 | 2 | | | 2 ቡድኖች |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ሀሳብ አልሰጡም |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 7 | 15.5 | 8.5 | 1 | 7 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | 2 | 2 | 2 | 0 | 2 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 13 | ትግራይ | 24 | 3.5 | 3 | 16.5 | 1 | |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 216 | 77 | 48 | 64 | 4 | 23 |

ሰንጠረዥ 38፡ 'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል'? - አገራዊ የአራቱም ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ (በቡድኖች)

| | | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰት | አዲስ አማራጭ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 49 | 18.5 | 3.5 | 19 | 1 | 7 |
| 2 | አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 47 | 15 | 17.5 | 12.5 | 0 | 2 |
| 3 | አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ | 96 | 29.5 | 24 | 30.5 | 2 | 10 |
| 4 | አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ | 24 | 14 | 3 | 2 | 1 | 4 |
| | **አገራዊ የአራቱም የትኩረት ቡድኖች ማጠቃለያ** | 216 | 77 | 48 | 64 | 4 | 23 |
| | | | | | | | |

### 6.3.2.3. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

የመጀመሪያውን ጥያቄ አስመለክቶ አብዛኞቹ የህጻናት ፓርላማ አባላት፣ ጾታዊ ጥቃት ደርሶባቸው ያገገሙ ሴቶች እና የወንድ ተፈናቃይ ተጎጂዎች፣ የአካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ተሳታፊዎች አማራጭ አንድን በመደገፍ በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ የእውነት ማፈላለግ እና እርቅ ተግባር ሊከናወን ይገል ብለዋል።

በሌላ በኩል አብዛኛዎቹ የህጻናት መብት ተወካዮች፡ እና ተፈናቃይ ሴት ተጎጂዎች እና ተፈናቃይ የቅልቅል ቡድኖች ሂደቱ በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ማተኮር እንዳለበት አንስተዋል። ይህ አማራጭ ካለው ጊዜና ገንዘብ አንፃር አዋጪ ከመሆኑም በላይ ያለውን ውጥረት ለመቀነስ እንደሚረዳ ገልጸዋል። በተጨማሪም እውነት የማውጣቱ ተግባር በቡድን ተኮር ተግባራት ላይ እንጂ በግለሰባዊ ጉዳዮች ላይ መካሄድ የለበትም የሚል አስተያየት ሰጥተዋል።

የተወሰኑ የተፈናቃይ የቅልቅል ቡድኖች ደግሞ እንደ ዘር ማጥፋት፣ ኢሰብአዊ ድብደባ፣ ከፍርድ ውጭ ግድያ፣ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ እና አስገድዶ መድፈር ያሉ ጉልህ የመብት ጥሰቶች በወንጀል ክስ እንጂ በእውነትና እርቅ ማእቀፍ ሊታዩ አይገባም የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።

### 6.3.2.4. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ[57]

[57] በዚህ ርእስ ስር - የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን በአዲስ አበባ እና አካባቢው በተለያዩ ጊዜያት ከልዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እና አመራሮች፣ ከሃገር ውስጥ ምሁራን፣ ከፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች እና አመራሮች፣ ከሚዲያ

በእነዚህ ተሳታፊዎች እውነትን ማፈላለግና እርቅን በተመለከተ የሚከናወኑ ተግባራትን አስመልክቶ የተሰጠው ሀሳብ ተጠቃሎ ሲታይ - የኢትዮጵያ ታሪክ አከራካሪና ዋነኛ የግጭት መንስኤ በመሆኑ የእውነት ፍለጋ ስራ ትኩረት ታሪካዊ ውዝግቦችን በመፍታት ላይ መሆን እንዳለበት የሚያመላክት ነው። እውነትን በመፈለግ ሂደት ውስጥ በአንድ በኩል የተለያዩ መንግስታት በግለሰቦች ላይ አደረሱ የተባለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነቅሶ ማውጣት፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል የተደረጉ ግጭቶችና የደረሱ በደሎችን የመለየት አስፈላጊነትን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት ብለዋል። የሃቅ ማፈላለጉ ስራ የጋራ ሪከርድ እንዲኖር፡ እንዲሁም ተጎጂዎችና ምስክሮች የደረሰውን በደል እንዲናገሩ እና እንዲታወቅላቸው በሚያስችል መልኩ መከናወን ይኖርበታል የሚል ሃሳብ ተሰጥቷል።

'እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ሂደቱ በተለይ ጾታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች እና በግጭት ወቅት የሚገጥሙ ወሲባዊ ጥቃቶችን በተለየ መንገድ ሊሸፍን እንደሚገባ ምክረ-ሃሳብ የተሰጠ ሲሆን ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች በማህበረሰብ ሊገጥማቸው የሚችለውን ተጽእኖ ተቋቁመው እውነቱን በማውጣት ሂደት እንዲሳተፉ ማድረግ እንደሚገባ፡ ለዚህም የተለያዩ የተሳትፎ አማራጮችን ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ተገልጿል። ለዚህ ሂደት የሚቋቋሙ ተቋማዊ አደረጃጀቶች አካታችና አሳታፊ እንዲሆኑም ምክረ ሃሳብ ተሰጥቷል።

በሌላ በኩል እውነት የማውጣት እና የእርቅ ስራው በሲቪልና ፖለቲካል መብቶች ጥሰቶች ላይ ብቻ መገደብ የለበትም፡ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የባህል መብት ጥሰቶችንም ማካተት አለበት የሚል ሃሳብ በብዙ ተሳታፊዎች ተሰጥቷል።

### 6.3.3. እውነት የማፈላለግና እርቅ የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?

#### 6.3.3.1. የተለያዩ የትኩረት ውይይት ቡድኖች እይታ

**I. የሴት ተጎጂዎች ቡድን**

**ሀ. በአብላጫ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 1)**

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች መካከል 30 ቡድኖች (ወይም 61.22%) የሚሆኑት ይህ የስራ ሂደት 'አዲስ በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን' አማካኝነት መተግበር አለበት የሚል አቋም ይዘዋል። ምክንያቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- እውነት ማውጣት በጣም አስፈላጊ ነገር ግን ከባድና ውስብስብ ስራ ነው፣ ራሱን የቻለ በዚህ ጉዳይ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ ተቋም መኖር አለበት፣
- አዲስ ኮሚሽን ማደራጀት ስራውን በገለልተኛነት በመስራት የታለመው ዓላማ ዕውን እንዲሆን ይረዳል፣ ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ከተፈለገ ከመንግስት ተጽእኖ የተላቀቀ ነጻና ገለልተኛ ተቋም መመስረት ያስፈልጋል፣

---

ሲቪክ ማህበረሰብ እና ዴሞክራሲ ተቋማት ጋር በተደረጉ የምክክር መድረኮች የተገኙ ግብአቶች፡ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የተመድ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ካውንስል፣ የሰብዓዊ መብት ማዕከል፣ የዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት ግሎባል ክሪሚናል ጀስቲስ ፅህፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (NEWA) እና ICTJ ጥምረት ሪፖርት፣ ICTJ፣ እና Commission for the Investigation of Violence in SRS and Reconciliation and Reparation of Victims የቀረቡ የፅሁፍ አስተያየት እና ምክረ-ሀሳቦች ይዘት ተጠቃለው ቀርበዋል።

- ነባር ተቋማት እውነትን የማፈላለግ እና የእርቅ ሥራ ሊሠሩ አይችሉም፣ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት አለባቸው፣ በሕዝብ ዘንድ አመኔታ የላቸውም፣ ከአድልአዊ አሰራር የፀዱ አይደሉም፣
- ነባር ተቋማት ቀደም ሲል የደረሰውን የመብት ጥሰት ማስቆም አልቻሉም፣ በሥራቸው የማህበረሰቡን ችግር በእኩልነት አይተው መፍትሔ ሊሰጡ አልቻሉም፣
- አሁን ባሉት ተቋማት ላይ እምነት የለም፣ በተለያየ አግባብ በጥሰቱ ተሳታፊ ነበሩ፣ ስለሆነም ነጻ፣ ገለልተኛ እና ተአማኒ የሆነ ራሱን የቻለ ተቋም ማቋቋም ያስፈልጋል፣
- ኢሰመኮ እና ሌሎች ተቋማት ችግሮችን እያዩ ያለፉና ውጤታማ ሥራ ለመስራት የተቸገሩ ናቸው፣ ተጨማሪ ሀላፊነት ቢሰጣቸው ትርጉም ያለው ስራ አይሰሩም፣
- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንም ሆነ ኢሰመኮ የየራሳቸው ሰፊ ስራ አላቸው፣
- ይበልጥ ተደራሽ ለመሆንና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ አዲስ ተቋም ሊቋቋም ይገባል፣
- አደረጃጀቱ ሁሉንም ማህበረሰብ የሚወክሉ አባላት ያሉት፣ ከሀይማኖት መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና ህብረተሰቡ የሚያምናቸው አባላትን የያዘ፣ የሙያ ብቃታቸው እና ሥነ-ምግባራቸው የተረጋገጠ ሰዎችን ያካተተ ቢሆን ውጤታማ ያደርገዋል፣
- የሚቋቋመው አዲስ ተቋም ሥራውን ሲሠራ በመሠረታዊነት የማህበረሰቡን ነባራዊ ሁኔታ በደንብ ያገናዘበ መሆን አለበት፣ በሂደቱ የዳበሩ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶችን ማሳተፍ ይኖርበታል።

## ለ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 2)

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች መካከል 7 ቡድኖች (ወይም 14.28%) የሚሆኑት እውነትን የማፈላለግ እና እርቅን የማምጣቱ ስራ 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን' አማካኝነት መተግበር አለበት የሚል ሀሳብ አንፀባርቀዋል። ምክንያቶቻቸው እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

- አዲስ ተቋም ማቋቋም ጊዜ፣ ገንዘብ እና የሰው ሃይል ይጠይቃል፣
- ኮሚሽኑ ካለው ልምድ እና ተደራሽነት አንፃር ተገቢ ማሻሻያ በማድረግ ስራው በዚህ ተቋም ሊሰራ ይገባል፣
- ተቋሙ የሰብዓዊ  መብት ጥሰቶችን በመመርመርና በማጣራት አሳማኝ ሪፖርቶችን ሲያወጣ የቀየ፣ በህዝብ አመኔታ ያገኘ ነው፣ አሠራሩም ግልጽ ነው፣ በመሆኑም ይህን ሥራ በውጤታማነት ለማከናወን አይቸገርም፣
- ኮሚሽኑ አሁን ላይ ተቀራራቢ ይዘት ያለው ስራ እየሠራ ነው።

## ሐ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 3)

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች መካከል 3 ቡድኖች (ወይም 6.12%) የሚሆኑት ስራው በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን መተግበር አለበት የሚል ሀሳብ አቅርበዋል። የሚከተሉትን ምክንያቶች ሰጥተዋል።

- አዲስ ኮሚሽን ቢቋቋም ጊዜ ከማጓተት ያለፈ ለውጥ አያመጣም፣
- ኮሚሽኑ ከጅምሩ በጣም ጥሩ ስራ እየሰራ ነው፣ ይህን ሀላፊነት በተሻለ ውጤታማነት ሊወጣ ይችላል፣
- ኮሚሽኑ የተቋቋመበት ዓላማ ከዚህ ተግባር ጋር የተቀራረበ በመሆኑ ውጤታማነቱን ያግዛል።

## መ. በሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስን ተሳታፊዎች የቀረበ 'ሌላ አማራጭ'

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ ጥቂት የሴት ተጎጂ ቡድኖች ተሳታፊዎች በተለያየ ቁጥር 'ተመሳሳይ አቋም ሳያንፀባርቁ' የሚከተሉትን '(የተለያዩ) አማራጮች' ጠቁመዋል።

- ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶቻችን ማህበረሰቡ የሚያምንባቸው በደንብ የዳበሩ አሰራሮች አሏቸው፣ እነዚህን አሰራሮች ለእውነት ማፈላለግና ለእርቅ ተግባራት መጠቀም ያስፈልጋል፣ ትክክለኛውን እውነት ለማውጣት ያግዛሉ፣ የሚደረገው እርቅ እና ሰላም ዘላቂ እንዲሆን ይረዳሉ፣
- እውነት የማፈላለግ እና የእርቅ ሂደት በማህበረሰቡ የተሻለ ተቀባይነት ባላቸው የሀይማኖት አባቶች ቢከወን ተመራጭ ነው፣
- ሂደቱን ከባህላዊ ግጭት አፈታት ተቋማት፣ ከነባር ተቋማት (የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን) እና አዲስ ከሚቋቋመው ኮሚሽን የተውጣጣ ቡድን በቅንጅት ቢያከናውነው ውጤታማ ይሆናል፣ ባህላዊ ተቋማት እውነት ማፈላለግንና እርቅን በተመለከተ የረጅም ጊዜ ልምድ አላቸው፣ ኮሚሽኑ በተለመደው መንገድ ሳይሆን ተአማኒነት ባለው አካሄድ የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎችና የሐይማኖት አባቶችን አካትቶ ወደስራ እንዲገባ ማድረግ የበለጠ ህዝባዊ አመኔታ እንዲኖረው ያደርጋል፣
- እውነት ማፈላለግን ተከትሎ እርቅ የማስፈን ስራ የሚመጣ በመሆኑ ማህበረሰቡ የሚስማማበት እውነት ላይ መድረስ ያስፈልጋል፣ ለዚህም ሁሉንም የእምነት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ያካተተ ሥርዓት መገንባት ተገቢ ነው፣
- ሂደቱ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በጋራ ቢከናወን ውጤታማ ይሆናል፣
- ሂደቱ አዲስ በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን እና በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ቅንጅት ቢመራ የተሻለ ነው፣
- ሂደቱ አዲስ በሚቋቋም ዓለም-አቀፍ የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ሊከናወን ይገባል፣ ምክንያቱም በትግራይ ክልል የነበረው ግጭት የውጭ ሀይሎች ተሳትፎ ነበረው፣ በፌዴራል ተቋማት ላይ ያለው ዕምነትም አነስተኛ ነው፣
- እውነት የማፈላለግ ሥራው ገለልተኛ የሆነና ከፖለቲካ ነፃ የሆነ፣ እንዲሁም በጥሰት የተጎዱ አካባቢዎች ምሁራንን ያካተተ መሆን አለበት።

ሰንጠረዥ 39፣ 'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' - አገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ አማራጭ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 0.5 | 0 | 0 | 0.5 |
| 3 | አማራ | 7 | 5 | 0 | 1 | 1 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 1 | 0.5 | 0.5 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 11 | 2 | 1 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 1 | 2 | 0 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 6 | 1 | 0 | 2 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 0.5 | 0.5 | 0.5 | 0.5 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | ትግራይ | 5 | 0 | 0 | 0 | 5 |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 49 | 30 | 7 | 3 | 9 |

## II. የወንድ ተጎጂዎች ቡድን

### ሀ. በአብላጫ የተደገፈው አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 1)

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 31 ቡድኖች (ወይም 65.95%) የሚሆኑት የስራው ሂደት 'አዲስ በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን' አማካኝነት መተግበር አለበት የሚል ሀሳብ አንፀባርቀዋል። ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- አሁን በስራ ላይ ያሉት ተቋማት ሰፊ ሀላፊነት አለባቸው፣ ስራቸውን በአግባቡ ይወጡ ዘንድ ሌላ ስልጣን መደረብ አይገባም፣ ስልጣን መጨመር የተያዘውን ዓላማ ለማሳካት አመቺ አይሆንም፣
- አሁን ባሉት ተቋማት ላይ የህዝብ አመኔታ የለም፣ ከፖለቲካ ጋር ንክኪ አላቸው፣ በሚሰሩት ስራ ላይ ተጨባጭ ተስፋ መጣል ይከብዳል፣
- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የገለልተኝነት ጥያቄ አለበት፣ ትንሽ መግለጫ ከማውጣት ባለፈም የሚጠበቀውን ያህል ስራ እየሰራ አይደለም፣ ኮሚሽኑ እና ሌሎች ነባር ተቋማት ፊት ጀምሮ የነበሩ ተቋማት ናቸው፣ ጥሰቶችን እያዩ አልፈዋል፣ የአቅምና የብቃት ውስንነትም አለባቸው፣ ተጨማሪ ስራ ቢሰጣቸው ውጤታማ አይሆኑም፣
- አገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ በአግባቡ በህዝብ ውይይት የተቋቋመ አይደለም፣ ተቀባይነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው፣ እስካሁንም ይህ ነው የሚባል ስራ አልሰራም፣ ለዚህ ተግባር አመቺ አይሆንም፣
- እውነት የማፈላለግ ሥራ አሁን ባሉ ተቋማት እንዲሠራ ማድረግ እውነቱን እንደማዳፈን እና የባሰ ችግር እንዲመጣ እንደማድረግ የሚቆጠር ነው፣
- ይህ የስራ ሂደት በዚሁ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ በሚሰራ፣ ከማህበረሰቡ ድጋፍ ባለው፣ እምነት በሚጣልበት አዲስ ተቋም ማከናወን ይገባል፣ ስራው ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በሚቋቋም አካል መተግበሩ ውጤታማ የመሆን እድሉን ያሰፋዋል።

ይህን አማራጭ የደገፉ የተወሰኑ ቡድኖች ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ተጨማሪ 'አማራጮች/ሀሳቦች' አቅርበዋል።

- ተቋሙ ሲቋቋም በመሰረታዊነት መደአ (የአፋር ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት) ማካተት አለበት፣ ይህ ለተቋሙ ተቀባይነት፣ በተግባር ለሚገጥሙት ክፍተቶች ሁነኛ መፍትሄ ይሆናል፣
- አዲስ በሚቋቋመው ኮሚሽን ውስጥ በህዝብ ተቀባይነት ያላቸው የሀይማኖት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች ሊሳተፉ ይገባል።

### ለ. በጥቂት ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ማከናወን' (አማራጭ 2)

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገርአቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 5.5 ቡድኖች (ወይም 11.7%) የሚሆኑት ስራው በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን መተግበር አለበት ብለዋል። ምክንያቶቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ኮሚሽኑ በሀገር ደረጃ የተሻለ ስራ እየሰራ ነው፣ በገለልተኛነትም ሆነ በአቅም ደረጃ እየተሻሻለ የመጣ ተቋም ነው፣ እውነት የማፈላለግ ስራው በዚህ ተቋም ቢመራ ውጤታማ ይሆናል፣
- ኮሚሽኑ በሰብአዊ መብት ጥበቃ ጉዳይ ልምድ አለው፣ የጥሰቶች መረጃ ይዟል፣ እርቅን የማምጣት አቅም አለው፣ ስለሆነም ኮሚሽኑን በማጠናከር ስራው በራሱ እንዲካሄድ ቢደረግ የተሻለ ነው፣

- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ትኩረቱ በተቋቋመበት ስራ ላይ ብቻ መሆን አለበት፣ የሽግግር ፍትህ ስራን ደርቦ መስራት የለበትም፣
- አዲስ የሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር የሚነፃፀር ልምድ አይኖረውም፣ ስራውን በሚፈለገው ፍጥነት መጨረስ አይችልም፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ጊዜና ወጪ ይጠይቃል።

### ሐ. በጥቂት ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማከናወን' (አማራጭ 3)

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 5.5 ቡድኖች (ወይም 11.7%) ቡድኖች ሂደቱ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን መመራት አለበት ሲሉ አቋማቸውን ገልፀዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- በአገሪቱ ያሉ ችግሮች ዋናው ምንጭ በታሪክ ላይ ያለው የተለያየ አረዳድ እና ትርክት ነው፣ መጀመሪያ እውነት ምንድን ነው የሚለውን ማወቅ፣ ቀጥሎም እርቅ መፈጸም ያስፈልጋል፣ ለዚህ ተግባር የምክክር ኮሚሽኑ ትክክለኛው ተቋም ነው፣
- ኮሚሽኑ የተቋቋመው በሀገር ደረጃ የተፈጠሩ ችግሮችን ተከትሎ እንደመሆኑ መጠን በአንፃራዊነት ገለልተኛነቱ ጥያቄ ውስጥ ገና አልገባም፣ ይህን ተግባር በተሻለ መልኩ ሊፈፅም ይችላል፣
- የኮሚሽኑ አባላት የህዝብ አመኔታ ያላቸው ሰዎች ናቸው፣ ተቋሙም ተአማኒ ነው፣ ይህን ሂደት በአዲስ ጉልበትና መንፈስ መምራት ይችላል፣
- ኮሚሽኑ ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር እየሰራ ያለ ተቋም በመሆኑ በተጓዳኝ ተያያዥ የሆኑ የእውነት ማፈላለግና የእርቅ ተግባራትን ሊያከናውን ይገባል፣ የራሱን የምክክር መድረኮች ሲያከናውን ብዙ እውነታዎችን የሚረዳበት እድል ስለሚፈጠር ውጤታማ የሚሆንበት የተሻለ እድል አለው፣
- ከአሰራር አንፃር ግን ኮሚሽኑ በሃይማኖት አባቶች እና በሀገር ሽማግሌዎች ሊታገዝ ይገባል፣
- በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ላይ እምነት የለም፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ብክነትን ያስከትላል።

### መ. በጥቂት ቡድኖች የቀረበ 'ሌላ አማራጭ'

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 5 ቡድኖች (ወይም 10.63%) የሚሆኑት የሚከተሉትን 'ሌሎች አማራጮች/ሀሳቦች' ጠቁመዋል።

- ከተለመደው የአመራረጥ ሥርዓት በተለየ መንገድ፣ ተአማኒነት ባለው አካሄድ የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት አባቶችን በማካተት የሚቋቋም አዲስ የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ስራውን እንዲሰራ ማድረግ ሂደቱ ህዝባዊ አመኔታ እንዲኖረው፣ ትክክለኛ እርቅ እንዲሰፍን ያደርጋል፣
- አዲስ ተቋም ከማቋቋም ይልቅ የቀረቡት ነባር ተቋማት (የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና አገራዊ የምክክር ኮሚሽን) ይበልጥ ገለልተኛ ሆነው የሚደራጁበትን መንገድ በመፈለግ ሂደቱን በቅንጅት እንዲመሩ ማድረግ የተሻለ ነው፣
- እውነት የማፈላለግ ተግባር ከፍተኛ ሀብትና ልምድ ይጠይቃል፣ በመሆኑም በአለም አቀፍ ተቋም እንዲከናወን ማድረግ ተመራጭ ነው፣
- እስካሁን በኢትዮጵያ ተቋም አለ የሚያሰኝ ሁኔታ የለም፣ ሰላምም የለም፣ ያሉት ተቋማት እምነት የሚጣልባቸው አይደሉም፣ ስለሆነም ሂደቱ ከቀረቡት አማራጮች ውጭ በዓለም አቀፍ ወይም ቅይጥ ተቋም መከናወን አለበት።

ሰንጠረዥ 40፡ ‘እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?’ - አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 3 | አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 3.5 | 2.5 | 1 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 1 | 0 | 0 | 1 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 0.5 | 0 | 0.5 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 10 | 2 | 2 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 3 | 0 | 0 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 6 | 1 | 1 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 1 | 0 | 0 | 1 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 3 | 0 | 0 | 2 |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 47 | 31 | 5.5 | 5.5 | 5 |

## III. የቅልቅል ቡድኖች

### ሀ. በአብላጫው የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ ‘አዲስ በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን’ (አማራጭ 1)

‘እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 60 ቡድኖች (ወይም 62.5%) የሚሆኑት ስራው ‘አዲስ በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን’ አማካኝነት መተግበር አለበት የሚል አቋም ይዘዋል። ለዚህም ምክንያቶቻቸውን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- በስራ ላይ ያሉ ተቋማት ህዝብን ማዕከል ያደረጉ አይደሉም፣ ነጻና ገልልተኛ አይደሉም፣ የመንግስት ፍላጎት እና የጥቂቶችን ድምጽ የሚያስተጋቡ ናቸው፣
- ነባር ተቋማት ከመንግስት ጣልቃ-ገብነት ነፃ አይደሉም፣ ይህን ሀላፊነት ለመፈጸም ብቃት የላቸውም፣
- አሁን ያሉት ተቋማት መሬት ላይ ጠብ የሚል ነገር አልሰሩም፣ የህዝብ አመኔታ የላቸውም፣ ለሀቅ ማፈላለግ ተግባር በእነዚህ ተቋማት ላይ እምነት መጣል ያስቸግራል፣
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ካሁን ቀደም የገለልተኝነት እና የተዓማኒነት ጥያቄ ሲነሳባቸው ቆይቷል፣ በመንግስት ላይ የሚፈለገውን ያህል ተጽእኖ መፍጠር እና ለውጥ ማምጣት አልቻሉም፣ ስለሆነም እውነት የማፈላለግን ስራ በተገቢ ደረጃ ይወጡታል ተብሎ አይታመንም፣ ለዚህ የሚያስፈልገው ብቃትም አላቸው ማለት ይከብዳል፣
- ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ራሱ ምክክር አድራጊ ራሱ እውነት አፈላላጊ ሊሆን አይችልም፣
- ሁለቱም ኮሚሽኖች የራሳቸው ዓላማና ተልዕኮ አላቸው፣ ሀላፊነቱ ለነሱ ቢሰጥ የስራ መደራረብና ጫና ይፈጥራል፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ያደናቅፋል፣

- ከተግባሩ ውስብስብነት አንጻር ይህን ስራ ብቻ የሚሰራ አዲስ ተቋም ያስፈልጋል፣ በአዲስ ሥልጣን፣ ብቃትና የሰው ሀይል የተደራጀ ተቋም ለየት ያለ አሰራር እና አቅም ወደ ሥርዓቱ ያስገባል፣ ለስራው የተሻለ ጊዜና ትኩረት ለመስጠት ያስችላል፣
- የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ መሰል ስራ በአዲስ ተቋም ማካሄድን ያሳያል፣ ይህ አማራጭ ተቋሙ ገለልተኛና የህዝብ ተቀባይነት እንዲኖረው፣ የተሻለ በጀትና የባለሙያ ድጋፍ እንዲያገኝ፣ በነጻነት እንዲወስን ያስችላል፣
- ለተጎጂዎች የህሊና እረፍት ከመስጠት አንጻር በህዝብ ተሳትፎ አዲስ፣ ነጻና ገለልተኛ ተቋም በማቋቋም የሽግግሩን ፍትህን መምራት ተገቢ ነው፣ ሂደቱን ስኬታማ ያደርገዋል።

ይህን አማራጭ የደገፉ የተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የሚከተሉትን (የተለያዩ) ተጨማሪ ሀሳቦች አቅርበዋል።

- እስካሁን ህዝቡ የተቸገረበት ጉዳይ እምነት ነው፣ በተለመደው በመንግስት (ከላይ ወደ ታች በሚፈስ) አሰራር ብቻ አዲስ ተቋም ማቋቋም ተገቢ አይሆንም፣ መተማመን እንዲኖር ከተፈለገ ሰፊውን ህዝብ ባሳተፈ መንገድ አዲስ ህዝባዊ ተቋም ሊመሰረት ይገባል፣
- ኮሚሽኑ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሴቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ እና ከሰብአዊ መብት ኮሚሽንና ከምክክር ኮሚሽን የተውጣጡ አባላት ሊኖሩት ይገባል፣ የባህላዊ እውቀት ባለቤቶችን (ለምሳሌ አባገዳ/ሃዳ ሲንቄ ወዘተ) እና ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶችን በማካተት ስራውን ሊያከናውን ይገባል፣
- የሚቋቋመው ኮሚሽን የውጭ ባለሙያዎችን ማካተት አለበት፣ ይህም ቅቡልነቱን፣ ተአማኒነቱን እና ገለልተኛነቱን አስተማማኝ ያደርገዋል፣
- አዲስ የሚቋቋመው ኮሚሽን በሁሉም ክልል የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ያካተተ መሆን አለበት፣ ባለሙያዎቹ በተመለከተ ዘርና ሃይማኖት ግንዛቤ ውስጥ ሣይገባ በትምህርት ዝግጅት፣ በሙያ ታማኝነት እና በሥራ ልምድ ብቁ የሆኑትን ብቻ በመምረጥ ወደስራ መግባት ይኖርበታል፣
- የኮሚሽኑ ሀላፊዎች የመመልመያ መስፈርት በህዝብ ጥቆማና ይሁንታ የመጣ መሆን አለበት።

**ለ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 3)**

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 13 ቡድኖች (ወይም 13.54%) የሚሆኑት የስራ ሂደቱ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት መተግበር አለበት ብለዋል። ለዚህ ያቀረቧቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- በሀሰት ትርክቶች ላይ መስማማት ባይቻል ችግሩን ማለፍ ስለማይቻል የስራው ባለቤት ለመሆን ኮሚሽኑ የተሻለ ተቋማዊ ቁመና/እድል አለው፣
- የምክክር ኮሚሽኑ ትኩረት ሰጥቶ እየሄደባቸው ካሉ እንቅስቃሴዎች አንጻር ሀላፊነቱ ቢሰጠው ያገኘውን ልምድ በመጠቀም በውጤታማነት ሊወጣው ይችላል፣
- ተቋሙ የመንግስት ሳይሆን የህዝብ እንደመሆኑ መጠን የተበዳዮች ድምጽ በጉልህ የመሰማት እድል ያገኛል፣
- ኮሚሽኑ ነጻና ገለልተኛ ስለሆነ እውነትን የማፈላለግና የማውጣት አቅም ይኖረዋል፣
- የምክክር ኮሚሽኑ ለተቀራራቢ ዓላማ የተቋቋመና የአሰራር ሥርዓትን የዘረጋ በመሆኑ ይህን ተቋም በማጠናከር መጠቀም ይገባል፣
- አዲስ ተቋም የማቋቋም ሂደት ዘገምተኛ ሊሆን ይችላል፣
- ተቋማትን ማብዛት በራሱ ችግር አለው፣ ከፍተኛ የሰው ሀይል እና ሀብት ይፈልጋል።

አማራጭ ሶስትን የደገፉ ውሰን የቅልቅል ቡድኖች ተሳታፊዎች የሚከተለውን ተጨማሪ ሀሳብ አቅርበዋል፣

- የምክክር ኮሚሽኑ አሁን ባለው ስልጣን አገራዊ የምክክር ስራዎችን ከማከናወን ባለፈ የሽግግር ፍትህ ስራዎችን ማከናወን አይችልም፣ ስለሆነም የስልጣኑን አድማስ በማስፋት፣ ተገቢ የባለሙያ ድጋፍ በማድረግ፣ እና ተቋማዊ አወቃቀሩን በማሻሻል ሂደቱን እንዲመራ ማድረግ የተሻለ ውጤት ያስገኛል።

**ሐ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 2)**

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች 10.5 ቡድኖች (ወይም 10.93%) የሚሆኑት የስራ ሂደቱ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን አማካኝነት መተግበር አለበት የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። ለዚህ የሰጡት ምክንያት እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ኮሚሽኑ ቀደም ሲል የነበረበትን የገለልተኝነት እና የተዓማኒነት ጥያቄ በመቅረፍ ገለልተኛ መሆኑን በተለያየ አግባብ አሳይቷል፣ ህዝባዊ ቅቡልነቱ እየተሻሻለ መጥቷል፣ እውነትን አውጥቶ መንግስትን የሚሞግት ተቋም ሆኗል፣ ይህ ቁመናው ትክክለኛ እውነት ለማውጣት ያግዛል፣
- ኮሚሽኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሲፈጸም ሪፖርት ሲያወጣ ቀይቷል፣ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ የቆመን ተቋም ትቶ ሌላ ማቋቋም ተገቢ አይሆንም፣
- ኮሚሽኑ በቂ መረጃ እና ልምድ ያለው የሰው ሀይል አለው፣ ውጤታማ የመሆን እድሉ የሰፋ ነው፣
- በአንፃሩ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከተመሰረተ ጊዜ አንስቶ እስካሁን የጎላ ሚና ሲጫወት አልታየም፣
- አሁን ባለ ተቋም መጠቀም ከኢኮኖሚ አንፃር ተመራጭ ነው፣ አዲስ ተቋም ማደራጀት ከፍተኛ የሀገር ሀብት ይፈልጋል፣
- አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም ረዘም ያለ ጊዜ ይጠይቃል፣ የሽግግር ፍትህ ዓላማን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከግብ እንዳይደርስ ያደርጋል።

**መ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የቀረበ 'ሌላ አማራጭ'**

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 11 ቡድኖች (ወይም 11.45%) የሚሆኑት የሚከተሉትን ልዩ ልዩ አማራጮች አቅርበዋል።

- ጉዳዩ ከባድና ውስብስብ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በጥምረት ቢሰሩት የተሻለ ይሆናል፣ በአንድ ተቋም ብቻ ሊሰራ አይገባም፣
- ሁለቱም ተቋማት ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ተቋማት ናቸው፣ ያሉባቸውን ውስንነቶች በመቅረፍ በጥምረት ቢሰራ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል፣
- ለእያንዳንዱ ጉዳይ (ክስ፣ ሀቅ ማፈላለግ፣ እርቅ፣ ተቋማዊ ማሻሻያ፣ ማካካሻ ወዘተ) ራሱን የቻለ ኮሚሽን ይቋቋም ከተባለ ሂደቱ እርስ በእርሱ ያልተሳሰረ/የተበታተነ ይሆንና የሽግግር ፍትህ ስራዎችን ውጤታማነት ይፈትናል፣ ስለሆነም አጠቃላይ የሽግግር ፍትህን የሚመራ አንድ ትልቅ ተቋም ሊኖር ይገባል፣
- አዲስ ተቋም በማቋቋም አገራዊ ችግሮችን የመፍታት ሙከራ ብዙ ጊዜ ተሞክሮ አልተሳካም፣ ስለሆነም ሀገር በቀል የሆኑ ባህላዊ የእርቅ ሥርዓቶችን ባካተተ መልኩ አዲስ የሀቅና እርቅ ኮሚሽን በማቋቋም ቢተገበር የተሻለ ነው፣
- ባህላዊ የግጭት አፈታት ተቋማት ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ጋር በመመጋገብ ሂደቱን የሚመሩበት ሁኔታን ማጤን ተገቢ ነው፣

- ነባርም ይሁኑ አዲስ የሚመሰረቱ ተቋማት ገለልተኛ ሆነው ስራቸውን ስለማይሰሩ የውጭ ተሳትፎ ያለበት ተቋማዊ አደረጃጀት ማሰብ ያስፈልጋል፣ አዲስ ተቋም ስለተቋቋመ ብቻ ጠንክሮ/ነፃ ሆኖ ይሰራል ማለት አይደለም፣ አሁን በአገራችን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ተቋማት ጠንካራ እና ገለልተኛ ሊሆኑ አይችሉም፣ ስለሆነም በአለም አቀፍ ደረጃ የሀገር ውስጥ ተቋማትን የሚያግዙ ከገዢው ፓርቲ/አስፈፃሚ አካል ጫና ውጪ የሆኑ ተቋማት ተሳትፎ አስፈላጊ ነው፣
- እውነት ለማፈላለግና እርቅ ለማካሄድ አለምአቀፋዊ ተቋም ሃላፊነት ሊሰጠው ይገባል፣ የውጭ ሀይል በትግራይ ክልል የፈፀመውን እውነታ የሚያጣራ እንደሁኔታው ከኢትዮጵያውያን ተሳትፎ ውጭ የሆነ ወይም የተቀላቀለ አባላት ያሉት ተቋም ሊቋቋም ይገባል፣
- እንደአግባብነቱ የአፋርን የባህል ፍትህ ሥርዓት ለእውነት ማፈላለግና እርቅ ተግባራት መጠቀም ያስፈልጋል፣ የአፋር ህዝብ በዚህ ረገድ የዳበረ የግጭት መፍቻ ሥርዓት አለው፣ ማህበረሰቡ የሚያምንበትና አሁንም የሚጠቀምበት ነው፣ ከመደበኛ ሥርዓት ወይም ከእውነት ኮሚሽን በበለጠ በማህበረሰቡ አመኔታ እና ተቀባይነት ይኖረዋል።

ሰንጠረዥ 41፡ 'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' - አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 3 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | 5 | 1 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 2 | 1 | 0.5 | 0 | 0.5 |
| 3 | አማራ[58] | 13 | 7 | 2 | 2 | 1 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | 2 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 1 | 0 | 1 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 2 | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 21 | 4 | 2 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | 2 | 0.5 | 0 | 1 | 0.5 |
| 10 | ሶማሌ | 4 | 4 | 0 | 0 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 11 | 1 | 5 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 13 | ትግራይ | 10 | 4 | 0 | 0 | 6 |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 96 | 60.5 | 10.5 | 13 | 11 |

## IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች

### ሀ. በአብላጫ የተደገፈ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 1)

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 18.5 ቡድኖች (ወይም 77%) የሚሆኑት - እውነትን የማፈላለግ እና እርቅ የማምጣት የስራ ሂደት 'አዲስ

[58] አንድ ቡድን ሀሳብ አልሰጠም።

በሚቋቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን' አማካኝነት መተግበር አለበት የሚለውን ሀሳብ ደግፈው ተከራክረዋል። ምክንያታቸውን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- የሽግግር ፍትህ ሥራ ሰፊ እና ትኩረት የሚፈልግ ስራ ነው፣ ጊዜና ሀብት ይጠይቃል፣ ስለሆነም በዚህ ተግባር ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ተቋም ያስፈልጋል፣ አዲስ ተቋም ቢደራጅ በተሻለ አስተሳሰብና አሠራር ውጤታማ ሥራ ሊሠራ ይችላል፣ ለተጎጂዎችም አዲስ ተስፋ ያመጣል፣
- አዲስ ተቋም መመስረት እውነትን ለማውጣትና እርቅን በትክክል ለማውረድ፣ ለተዓማኒነት፣ ለገለልተኝነት እና ለነጻነት አስፈላጊ ነው፣
- በአማራጭ የቀረቡት ሌሎች ተቋማት የተቋቋሙለት ራሱን የቻለ ተግባርና ሀላፊነት አለ፣ ስለሆነም ጥሩ አማራጭ አይሆኑም፣ ይህን የሥራ ሂደት በሌሎች ተቋማት ላይ መደረብ በፍጹም አስፈላጊ አይደለም፣ እውነት የማፈላለግና የእርቅ ሰራው በተገቢ አትኩሮት እንዳይከናወን ያደርጋል፣
- በአማራጭ የቀረቡት ተቋማት ክፍተት አለባቸው፣ የገለልተኝነት፣ ነጻነት እና ተዓማኒነት ጥያቄ የሚነሳባቸው ናቸው፣ የተደራሽነት ችግርም አለባቸው፣ ሂደቱን በአግባቡ መምራት ይችላሉ ወይ የሚለውም አጠያያቂ ነው፣
- ሁሉንም ማህበረሰብ ያካተተ አዲስ ኮሚሽን ተቀባይነት ይኖረዋል፣ ሀገር በቀል የእውነት ማፈላለጊያ ዘዴዎችን ለመጠቀም ያስችላል፣
- ከአደረጃጀት አንፃር ኮሚሽኑ አካታች መሆን ይገባዋል፣ የሁሉንም ባህል፣ ሀይማኖት እና ማህበረሰብ እይታ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፣ የሀላፊዎቹ አመራረጥ ከአስፈፃሚው አካል ውጪ መሆን አለበት፣ ተመራጮች የሚመረጡበት ሂደትም ፍትሃዊና ግልጽ መሆን አለበት።

## ለ. በጥቂት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 2)

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 1.5 ቡድኖች (ወይም 6.25%) የሚሆኑት እውነትን የማፈላለግ እና እርቅ የማምጣት የስራ ሂደት በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን መተግበር አለበት ብለዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ኮሚሽኑ አሁን ላይ የሚታዩ/የሚጨበጡ ሥራዎችን በመሥራት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው፣
- ኮሚሽኑ ስራዎቹን ገለልተኛ ሆኖ እየሰራ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ፣ ማስረጃዎችን የያዘ፣ ቀድሞ የተደራጀ እና አቅም ያካበተ መሆኑ ተመራጭ ተቋም ያደርገዋል፣
- በእስካሁኑ ሂደት ኮሚሽኑ የሚሰራቸው ስራዎች ከሽግግር ፍትህ ተግባር ጋር ተቀራራቢ ናቸው፣ ይህም እውነት የማውጣት ስራዎችን ለማከናወን ብቁ ያደርገዋል፣
- እንደአስፈላጊነቱ ኮሚሽኑን እንደገና በማዋቀርና የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ ይህን የስራ ሀላፊነት መተግበር የሚችልበትን እድል መፍጠር ተገቢ ነው።

## ሐ. በጥቂት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 3)

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 2 ቡድኖች (ወይም 8.33%) የሚሆኑት የስራ ሂደቱ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ሊተገበር ይገባል የሚል አቋም ይዘዋል። ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ኮሚሽኑ የተፈፀሙ ጥሰቶችን ለማወቅ የተሻለ እድል አለው፣ የታሰበው ስራ ኮሚሽኑ ከሚሰራው ስራ ጋር የሚያያዝ በመሆኑ የተግባር መደጋገም ያስቀራል፣
- የሽግግር ፍትህ ስራ እና የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ስራ በእጅጉ የሚገናኙ በመሆኑ የኮሚሽኑን ሥልጣን በመጨመር ይህን ሀላፊነት ደርቦ እንዲሠራ ማድረግ ሀብትና ጊዜ ይቆጥባል፣
- የምክክር ኮሚሽኑ ካሉት ተቋማት ሁሉ የተሻለ ተዓማኒነት አለው፣
- ኮሚሽኑ በተሻለ ሁኔታ የተዋቀረና ጉዳዮችን እያየ ያለ ተቋም ነው፣ ይህ ቁመናው ተጨማሪውን ስራ በውጤታማነት እንዲሰራ ያስችለዋል፣
- አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም ጊዜ እና ሀብት ይፈልጋል፣

### መ. በጥቂት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የቀረበ 'ሌላ አማራጭ'

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 2 ቡድኖች (ወይም 8.33%) የሚሆኑት እውነትን የማፈላለግ እና እርቅ የማምጣቱ ስራ የሚከተሉትን ሌሎች (የተለያዩ) አማራጮችን በመጠቀም መተግበር ይገባል የሚል ሀሳብ ሰንዝረዋል።

- እውነት የማውጣት ስራ ጊዜና ሀብት ይወስዳል፣ ስለሆነም ይህን ሀላፊነት መሸከም የሚችል ባለሙያ እና በጀት ያለው አዲስ ድብልቅ ተቋም ቢቋቋም ተመራጭ ይሆናል፣
- እውነትን የማጣራትና እርቅ የማውረድ ተግባር አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ተቋም እና በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የጋራ ቅንጅት ሊተገበር ይገባል፣
- ይህ የስራ ሂደት ከውጪ እና ከኢትዮጵያ የተውጣጣ አባላት ያሉት ዓለም-አቀፍ/ቅይጥ ሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን በማቋቋም መከናወን አለበት፣ ይህ አደረጃጀት ቅቡልነቱን ለማፅናት ያግዛል።

ሰንጠረዥ 42፡ 'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' - አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 3 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | አማራ | 5 | 5 | 0 | 0 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | 0.5 | 0.5 | 0 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | 5 | 1 | 1 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 3 | 2 | 0 | 1 | 0 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 4 | 2 | 0 | 0 | 2 |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 24 | 18.5 | 1.5 | 2 | 2 |

## 6.3.3.2.'እውነትን የማፈላለግና እርቅ የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

### ሀ. በአብላጫው የተደገፈው ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'

'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ - በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 140 ቡድኖች (ወይም 64.81%) የሆኑት የስራ ሂደቱ 'አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን' አማካኝነት ሊተገበር ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል።

### ለ. በጥቂት ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን' ወይም 'በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን' አማካኝነት ማከናወን

በሌላ በኩል በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 24.5 ቡድኖች (ወይም 11.34%) የሆኑት ይህ የስራ ሂደት 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን' አማካኝነት ሊከናወን ይገባል የሚለውን ሀሳብ አቅርበው ተከራክረዋል። 23.5 ቡድኖች (ወይም 10.87%) የሆኑት ደግሞ ስራው በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ሊሰራ እንደሚገባ በማመን ምክንያቶቻቸውን ዘርዝረው አቅርበዋል።

ቀሪዎቹ 2 ቡድኖች (ወይም 0.93%) የሆኑት በተለያየ አተያይ አዲስ ያሏቸውን አማራጮች አቅርበዋል።

### ግኝቱ ውይይቶቹ ከተካሄዱባቸው ክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች አንጻር ሲተነተን

ይህ መረጃ ውይይቱ ከተካሄደባቸው ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች አንጻር ሲተነተን ከአንድ ክልል ውጭ በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ የትኩረት ቡድኖች ውይይት በአብዛኛው ቡድን የተደገፈው ሀሳብ እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት 'አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን' አማካኝነት ሊሰራ ይገባል የሚል ነው።

በሌላ በኩል በትግራይ ክልል በሁሉም ቡድኖች በአብላጫ ድጋፍ ያገኘው አዲስ አማራጭ ሀሳብ እውነትን የማፈላለግና እርቅ የማውጣት ሂደት አለም-አቀፍ ተቋምን በመጠቀም ሊከናወን ይገባል የሚል ነው።

### ግኝቱ ከተለያዩ ቡድኖች አንጻር ሲታይ

ግኝቱ ከቡድን አንጻር ሲታይ - በአራቱም አገራዊ ቡድኖች ማለትም በሴቶች፣ በወንዶች፣ በቅልቅል እና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ሁሉ በአብላጫ ድጋፍ ያገኘው ሀሳብ እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት 'አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን' አማካኝነት ሊሰራ ይገባል የሚል ነው።

ሰንጠረዥ 43፡ 'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' - አገራዊ የአራቱም ቡድኖች ማጠቃለያ (ሀገር-አቀፍና ክልል ምልከታ)


| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 3 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | **8** | 6 | 2 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | **5** | 3.5 | 0.5 | 0 | 1 |
| 3 | አማራ[59] | **32** | 20.5 | 4.5 | 4 | 3 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | **9** | 3.5 | 2 | 1.5 | 2 |
| 5 | ድሬዳዋ | **5** | 5 | 0 | 0 | 0 |

[59] አንድ ቡድን ሀሳብ አልሰጠም።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ጋምቤላ | **5** | 3.5 | 0 | 1.5 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | **4** | 4 | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | **62** | 47 | 9 | 6 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | **4** | 1.5 | 0 | 2 | 0.5 |
| 10 | ሶማሌ | **11** | 9 | 2 | 0 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | **39** | 25 | 3 | 7 | 4 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | **8** | 2.5 | 1.5 | 1.5 | 2.5 |
| 13 | ትግራይ | **24** | 9 | 0 | 0 | 15 |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 216 | 140 | 24.5 | 23.5 | 27 |

ሰንጠረዥ 44፡ 'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' - አገራዊ የአራቱም ቡድኖች ማጠቃለያ (በቡድን)

| | | **ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት** | **አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት** | **አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት** | **አማራጭ 3 የደገፉ ቡድኖች ብዛት** | **ሌላ/አዲስ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት** | **ማስታወሻ** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **አገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ** | 49 | 30 | 7 | 3 | 9 | 0 |
| 2 | **አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ** | 47 | 31 | 5.5 | 5.5 | 5 | 0 |
| 3 | **አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ** | 96 | 60.5 | 10.5 | 13 | 11 | 1 |
| 4 | **አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ** | 24 | 18.5 | 1.5 | 2 | 2 | 0 |
| | **አገራዊ ማጠቃለያ** | **216** | **140** | **24.5** | **23.5** | **27** | **1** |
| | | | | | | | |



### 6.3.3.3.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

ተቋማዊ አደረጃጀትን በሚመለከት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሴቶች ብቻ መድረክ ተሳታፊዎች፣ የህጻናት ፓርላማ አባላትና የህጻናት መብት ተወካዮች፣ ተፈናቃይ ወንድ ተጎጂዎችና ተፈናቃይ የቅልቅል ቡድኖች፣ ግማሽ ያህሉ ከጾታዊ ጥቃት ያገገሙ ሴቶችና፣ ሴት ተፈናቃዮች፣ እንዲሁም የተወሰኑ አካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ተሳታፊዎች - በአማራጭ አንድ ሥር የተቀመጠውን አዲስ የሚቋቋም ኮሚሽን ሀሳብን ደግፈዋል። በዋናነት ያቀረቧቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ሌሎቹ ተቋማት የተቋቋሙበት የየራሳቸው የሆነ ስራ አላቸው፡ ስለሆነም ለነሱ ተደራቢ ሥራ ከመስጠት ይልቅ አዲስ ማቋቋም ይበልጥ ውጤታማ ያደርጋል፣
- ኮሚሽኑን ጨምሮ አሁን ያሉት ተቋማት በርካታ ግፍ ሲፈፀም ቀመው ያዩ/ምላሽ ያልሰጡ እንደመሆናቸው መጠን አሁን ላይ እውነት ማፈላለግና ዕርቅ ላይ የተሳካ ስራ ይሰራሉ ተብሎ አይታመንም፣ ገለልተኛነታቸው ላይ ሁሌም ጥያቄ ይነሳል፣
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ጊዜና ገንዘብ የሚጠይቅ ቢሆንም ለሰላምና ለመብት መከበር ሲባል ምንም ያክል ገንዘብ ቢወጣ እንደጉዳት/ተግዳሮት መታየት አይኖርበትም።

በተጨማሪም እውነትን ከማፈላለግና ከእርቅ ስራ ጋር ተያይዞ የሴቶች ብቻ መድረክ የሚከተሉትን ምክረ-ሃሳቦች አቅርቧል።

- የአዲሱ ተቋም አባላት አመራረጥ ግልጽና አሳታፊ መሆን አለበት፡ ከአስፈጻሚው ጣልቃ ገብነትም ነጻ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፣
- አዲሱ ተቋም የሴቶችን ጉዳይ በልዩ ሁኔታ የሚያስተናግድበት አሰራር/አደረጃጀት ሊኖረው ይገባል፣
- የሚቋቋመው ተቋም ከሁሉም የተውጣጣ ሆኖ የሀገር ሽማግሌዎችን እና ታዋቂ ሰዎችን የሚያካትት መሆን አለበት።

በሌላ በኩል በሁሉም መድረኮች የተወሰኑ ተሳታፊዎች 'ሌሎች የተለያዩ  አማራጮችን' አቅርበዋል። ጥቂት የማይባሉ ተሳታፊዎች ደግሞ ስራው በሰብአዊ መብት ኮሚሽን እንዲከናወን ሃሳብ አቅርበዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች ሰጥተዋል።

- ተቋሙ ከዚህ በፊት ነጻና ገለልተኛነቱን የሚያረጋግጡ ተያያዥ ሥራዎችን ሲሠራ የቆየ መሆኑ፣
- ተቋሙ ለዚህ የሚያመች ቁመና ያለው መሆኑ (አካታችነት፡ ለሴቶች የሚሰጠው ትኩረት ወዘተ)፣
- ተቋሙ ያለፉ ጥሰቶችን ሲያጠራ እና ሪፖርቶችን ሲያወጣ መቆየቱ።

ከዚህ በተጨማሪ ውስን ተፈናቃይ ወንዶች እውነት ማፈላለግና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት በአለም አቀፍና በሃገር ውስጥ ባለሙያዎች ቅይጥ ተቋም አማካኝነት ቢሆን ቢከናወን ተመራጭ ነው የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።

### 6.3.3.4.ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

'እውነትን ማፈላለግና እርቅን የማውጣት ሂደቱን በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?' የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የተሰጡ አስተያየቶች በጥቅሉ ስራው በአዲስ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽን ሊከናወን ይገባል የሚል ነው።

## 6.4. በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ምህረት

### 6.4.1. መግቢያ

በፖሊሲ አማራጮች ሰነዱ ላይ ከተካተቱ የሽግግር ፍትህ ሂደት ዋና ዋና አምዶች ውስጥ አንዱ ምህረት ነው። ምህረትን አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተካሄደው ውይይት በሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው። የመጀመሪያው 'ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ/የማያደርጉ መስፈርቶች ምን ሊሆኑ ይገባል? የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው - ምህረት በተለያዩ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ ይሰጥ ከተባለ 'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ሊያከናውነው ይገባል?' የሚል ነው።

በዚህ ጥያቄ ላይ 216 የትኩረት ቡድኖች ውይይት አድርገዋል። ለጥያቄዎቹ መነሻ የሚሆኑ አመላካቾች/አማራጮችም ቀርበዋል። በእያንዳንዱ መድረክ - የትኩረት ቡድን ውይይቱ በአራት የተለያዩ ቡድኖች ተከፍሎ ተካሂዷል።

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ 'በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች'፡ 'ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' እና 'በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል።

### 6.4.2. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ መስፈርቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

በኢትዮጵያ ለመተግበር በሚታሰበው የሽግግር ፍትህ ሂደት - በተለያየ ደረጃ ጥፋት ለፈፀሙ ሰዎች ቅድመ ሁኔታዎችን ባሟላ መልኩ ምህረት የሚደረግበትን አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ምህረት ለመስጠት የሚያስችሉ ቅደመ-ሁኔታዎችን በግልጽ ማስቀመጥ፡ ምህረት የሚሰጥባቸውን የወንጀል አይነቶች መወሰን፡ የምህረት አሰጣጥ ስነ-ሥርዓትና ሂደቶችን መዘርዘር፡ እንዲሁም ምህረት የመስጠትን ሂደት ግልጽና ገለልተኛ በሆነ መንገድ የሚያስተናግዱ ተቋማት እና አደረጃጀቶችን መወሰን ያስፈልጋል።

ከአለማቀፍ ተሞክሮ ለመረዳት እንደሚቻለው - ምህረት ለመስጠት የሚጠቀሱ ቅድመ-ሁኔታዎች የተለያዩ ናቸው። ዋና ዋናዎቹ አጥፊዎች በወንጀሉ ከነበራቸው የተሳትፎ መጠንና የወንጀሉ ይዘት/ክብደት፡ አጥፊዎች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ በሚኖራቸው ተሳትፎ/ትብብር፡ አጥፊዎች እውነትን በማውጣት/በማጥራት ረገድ ከሚኖራቸው ትብብር፡ ከፀፀት እና ይቅርታ መጠየቅ፡ እንዲሁም ከተለያዩ ተቋማት ጋር ከሚኖራቸው ትብብር ጋር የሚያያዙ ናቸው።

#### 6.4.2.1.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

**I. የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች**

***ሀ. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች***

በመላ ሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች በተደረገው ውይይት የምህረት ቅደመ-ሁኔታዎችን አስመልክቶ የሴት ተጎጂ ቡድኖች አባላት የሚከተሉት የምህረት ቅድመ-ሁኔታዎች ጎልተው ይወጡ ዘንድ ሀሳባቸውን አጋርተዋል።

- በምህረት አሰጣጥ ሂደት ጥፋትን ማመን፡ ይቅርታ መጠየቅ፡ ካሳ መክፈል፡ መጸጸት፡ እና የወንጀሉ ዓይነት እና የተሳትፎ መጠን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ፣
- የበዳይና ተበዳይ ስምምነት፡ እንዲሁም የተበዳይ ሁኔታና ፍላጎት፣
- አጥፊው እውነትን የሚያወጣ ከሆነ (ለምሳሌ ከእውነት አፈላላጊ ተቋም ጋር ትብብር ማድረግ)፡ ጥፋቱ የተፈፀመበት ሁኔታ (ለምሳሌ በመገደድ የተፈፀመ፡ የአጥፊው ስነ-ምግባር፡ ጥሰቱ በስህተት/ባለማወቅ የተፈጸመ ከሆነ)፣
- የአጥፊው የወንጀል ታሪክ (ከዚህ ቀደም ወንጀል ያልሰራ ከሆነ)፡ እድሜና የትምህርት ደረጃ፡ በማህበረሰቡ የነበረው መልካም ባህሪ ሁኔታ፣

- አጥፊው በወንጀል ምርመራ ሂደቱ ላይ ያደረገው/የሚያደርገው አስተዋጽኦ፣
- የአጥፊው የጤንነትና የዕድሜ ሁኔታ፡ ለህብረተሰቡ የሚደቅነው አደጋ (ስጋት)፣
- አጥፊው ካሳ ለመክፈል ያለው ዝግጁነት፣
- ለሚመለከተው አካል ራሱን አሳልፎ የሰጠ መሆን/አለመሆን።

ከዚህ ጋር በተያያዘ - ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶችና የሚቀመጡ መመዘኛዎች ተበዳዮችን የሚያሳምኑ መሆን እንዳለባቸውም ሀሳብ ቀርቧል። ይህን በተመለከተ - በተለይ በትግራይ ክልል የነበሩ ተሳታፊዎች ምህረት የመስጠት ሂደት ከመጀመሩ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገቡ የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎችን ዘርዝረዋል።

- የተፈናቀሉ ወገኖች ወደ የቦታቸው እንዲመለሱ ማድረግ፣
- የወደሙ ተቋሞች በሙሉ ወደ ስራ የሚገቡበት ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ለተበዳዮች ተመጣጣኝ ካሳ መስጠት፡ በተለይ በጅምላ የተገደሉ ሰዎች የሚካሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- የክልሉን ህዝብ ችግር መሬት ላይ ወርዶ በማጥናት ኣስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ፣
- የውጭ እና የውስጥ ተፋላሚ ሃይሎች ከክልሉ ሙሉ ለሙሉ እንዲወጡ ማድረግ፡ በፕሪቶሪያ የተደረገውን ስምምነት መፈፀም፣
- የሃይማኖት ተቋማት ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ።

በተጨማሪም - ምህረትን በተመለከተ በሕግ መሰረት ለምህረት ብቁ ተብለው ተለይተው የሚቀመጡ ሁኔታዎች መደንገግ ያለባቸው መሆኑ ተመልክቷል። ይህም በተለይ የአጥፊውን የተሳትፎ ደረጃ እና የተጠረጠረበት ወንጀል አይነት በዓለም-አቀፍ እና አገራዊ የወንጀል ሕግ መሰረት ለምህረት የሚያበቃ መሆን አለመሆኑ አስቀድሞ በሕግ በግልፅ ሊቀመጥ እንደሚገባው ሀሳብ አቅርበዋል።

### ለ. ለምህረት ብቁ የማያደርጉ ኩነቶች

በሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች በተደረገው ውይይት ምህረት መስጠት የማይቻልባቸው ሁኔታዎችን አስመልክቶ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ሀሳባቸውን ሰጥተዋል። ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- በግፍ ግድያ፡ ዘር ማጥፋት ወንጀል፡ ጭካኔ የተመላበት/ኢሰብአዊ አያያዝ ድርጊቶች መሳተፍ፣
- ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲፈፀም ትእዛዝ የሰጠ፡ ያቀደ፡ የመራ፡ እና ያስፈጸመ መሆን፣
- አለመፀፀት፡ እውነትን ለማውጣት አለመተባበር፣
- ከፍተኛ የወንጀል ተሳትፎ፡ በወንጀል ስራ ያለው ተደጋጋሚ ተሳትፎ፣
- በተለይ በሴቶች ላይ ጭካኔ በተመላበት ሁኔታ የአስገድዶ መድፈር፡ ግብረሶዶም ወይም መሰል በደል መፈፀም።

### ሐ. ምህረትን በተመለከተ የተነሱ ልዩ (ንዑስ) ሃሳቦች

በውይይቶቹ ላይ ተሳታፊ ከነበሩት ውስጥ ውስን ሰዎች ምህረት በፍፁም ሊሰጥ አይገባም በማለት ክርክር አቅርበዋል። ለዚህ የሰጡት ምክንያት ምህረት መስጠት ወንጀል እንዲስፋፋ ያደርጋል የሚል ነው። ከዚህ በመነሳት ምህረት እንደ አንድ ሽግግር ፍትህ ስልት መቀረቡ ተገቢ አይደለም ሲሉ ሞግተዋል።

## II. የወንድ ተጎጂዎች ቡድኖች

### ሀ. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

- የአጥፊው መፀፀት፡ የበደላቸውን ሰዎች/ማህበረሰብ ይቅርታ መጠየቅና መካስ፡ የተጎጂዎች ለይቅርታ ምላሽ መስጠት፡ ተመሳሳይ ድርጊት ላለመፈፀም ቃል መግባት፣
- የአጥፊው የንቃተ-ህሊና ደረጃ፡ በጥፋት የተሳተፈው በፈቃዱ ወይም በሌሎች ግፊት መሆን/አለመሆን፣

- በወንጀሎቹ የነበረው የተሳትፎ ደረጃ፡ የወንጀሎቹ አይነት፣

**ለ. ለምህረት ብቁ የማያደርጉ መስፈርቶች**

- ህዝብን ማፈናቀል፡ ህይወት ማጥፋት፡ በዘር ማጥፋት፡ በሰብዕና ላይ የሚፈጸም ወንጀል፡ በአስገድዶ መድፈር፡ ጠለፋ፡ በኢሰብአዊ ድብደባ እና በጦር ወንጀል መሳተፍ፣
- ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን መፈፀም፡ በድርጊቶቹ ዋና አጥፊ መሆን፣
- የሀገር ክህደት መፈጸም፣
- ሬሳ ማቃጠል፡ ለአስክሬን ክብር መንፈግ፡ ቀብር መከልከል፣
- እህልና ውሀ ማገድ፡ መከልከል፣
- በወንጀል ድርጊት በተደጋጋሚ መሳተፍ፡ ከማህበረሰቡ ባህልና ወግ ውጭ የሆኑ ወንጀሎችን መፈጸም፣

**ሐ. ምህረትን በተመለከተ የተነሱ ውስን ሃሳቦች**

ውስን ተሳታፊዎች ምህረት ወንጀለኞች ሌላ ወንጀል እንዲሠሩ የሚያበረታታ በመሆኑ በማናቸውም ሁኔታ ሊሰጥ አይገባም የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። በተጨማሪም የምህረት ሂደት መከወን ያለበት በበዳይ እና በተበዳይ መካከል እንጅ በመንግስት እና በጥቃት አድራሽ መካከል ሊሆን አይገባም የሚል አስተያየት ተሰጥቷል።

**III. የቅልቅል ቡድኖች**

**ሀ. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች**

የቅልቅል ቡድን አባላት ምህረት ለእርቅ እና ዘላቂ ሰላም እጅጉን አስፈላጊ መሆኑን፡ እንዲሁም ምህረትና ይቅርታ የህዝቡ ነባር እሴቶች መሆናቸውን በመግለፅ - ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶችን እንደሚከተለው አንስተዋል።

- የወንጀሉ ክብደትና የተሳትፎ ደረጃ (ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰት ፈፃሚዎች ሳይካተቱ)፡ ወንጀሉ በግብታዊነት፡ በግዳጅ ወይም በአጃቢነት የተፈፀመ መሆን/አለመሆን፣
- የሀገር ብሄራዊ ጥቅም የተነካበት ደረጃ፣
- ጥፋትን ማመን፡ በመፀፀት በግልፅ ይቅርታ መጠየቅ፡ ተመጣጣኝ ካሳ መክፈል፣
- እውነትን በማውጣት ሂደት የነበረው ተሳትፎ፡ በተለይም የወንጀልን እቅድ፡ መሪ፡ ዓላማ እና አጠቃላይ ሁኔታ አስመልክቶ ለሚመለከተው አካል መንገር እና የእውነትና እርቅ ሂደቱን ማገዝ።

ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ውስን ተሳታፊዎች ተጨማሪ ሃሳቦችን አቅርበዋል።

- ጥፋተኝነት በፍርድ ሳይረጋገጥ ምህረት ሊኖር አይገባም፣
- በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 28 መሰረት ምህረት ሊሰጣቸው የማይገቡ ወንጀሎች መጠበቅ አለባቸው፣
- ሀገርና ህዝብን ለጥፋት/ለእልቂት የዳረጉ ግለሰቦች ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ምህረት ሊሰጣቸው አይገባም፣
- የምህረት አሰጣጥ የተጎዱ ሰዎችን ሞራልና ስሜት በማይነካ መልኩ መከናወን አለበት፣
- በተጨማሪም ምህረት የሚሰጠው የተፈናቀለው ህዝብ ወደ ቀዬው ከተመለሰ እና ተበዳዮች ተገቢ ማካካሻ ካገኙ በኋላ መሆን አለበት።

**ለ. ለምህረት ብቁ የማያደርጉ መስፈርቶች**

- ሆን ብሎ ሰውን መግደል፡ ሬሳ ማቃጠል፡ መሬት ላይ መጎተት፡ በሬሳ መጫወት፡ እንዳይቀበር መከልከል፣
- ሰውን ከነቤቱ ማቃጠል፡ ሰውን እንደ እንስሳ አንገት በመቁረጥ መግደል፣
- በመሳሪያ አስፈራርቶ በወንድ ላይ የጾታ ጥቃት መፈጸም፣
- ሰውን አስሮ ማሰቃየት፣

- ለችግረኞች የምግብና የመሠረታዊ ሸቀጦችን ፍሰት ሆን ብሎ መከልከል፡ እንዲራቡ ማድረግ፣
- በህገ መንግስቱ ምህረት በሚያስከለክሉ ጉዳዮች መሳተፍ፣
- በዘር ማጥፋት፡ ከባድ የጦር ወንጀል፡ በሰብአና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፡ በሴቶች ህፃናትና አዛውንቶች ላይ የሚፈፀሙ ከባድ የመብት ጥሰቶች፡ በአስገድዶ መድፈር፡ ሰዎችን በማፈናቀል እና መሰል ድርጊቶች መሳተፍ፣
- ከባድ ዓለም-አቀፍ ወንጀል፡ የሀገር ክህደት ወንጀል መፈጸም።

**ሐ. ምህረትን በተመለከተ የተነሱ ውስን ሃሳቦች**

ውስን ተሳታፊዎች ምህረት በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ሊሰጥ አይገባም የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። ችግሮችን ከማባባስ ውጭ አዲስ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ ምህረትና ይቅርታ ብሎ ያመጣው መሰረታዊ ለውጥ የለም። ስለሆነም ለየትኛውም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምህረት መኖር የለበትም የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።

IV. **የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን**

**ሀ. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች**

- እውነቱን መናገር፡ ለእውነት ማፈላለጉ ሂደት ቀና ትብብር ማድረግ፡ ካሳ መስጠት፡ መፀፀት፡ ይፋዊ በሆነ መንገድ ይቅርታ መጠየቅ፡ ኃላፊነትን መውሰድ፣
- የጥፋተኛው የተሳትፎ ደረጃ፡ ጥፋቱን ለመፈጸም ያነሳሳው ጉዳይ፡ የጥፋቱ ደረጃ፣
- የጥፋተኛው ባህሪ፡ የመታረም ዝንባሌ፡ ለሀገር የሰጠው አበርክቶ፡ የበጎ ፈቃድና ህዝባዊ አገልግሎት ተሳትፎ፡ ሰላማዊነት፣
- ባለስልጣን ከሆነ ስልጣን መልቀቅ፡ እንዲሁም ህዝብን በይፋ ይቅርታ መጠየቅ።

**ለ. ለምህረት ብቁ የማያደርጉ መስፈርቶች**

- ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ወይም ከባድ ወንጀል መፈፀም (ማቀድ፡ ማዘዝ፡ መምራት)፣
- በአለም-አቀፍ ሕግ እና በህገ-መንግስቱ ምህረት የማያሰጡ ተብለው የተለዩ ወንጀሎችን መፈፀም።

**ሐ. ምህረትን በተመለከተ የተነሱ ልዩ (ንዑስ) ሃሳቦች**

- የሽግግር ፍትህን ሀሳብ የሚያጠፋ በመሆኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የፈፀሙ ሰዎች በፍፁም ምህረት ሊሰጣቸው አይገባም፣
- አገራዊው ሁነት መደበኛ የማይባል ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ከህገ-መንግስታዊ አሰራር እይታ በላይ ነው፡ ስለሆነም ከህገ-መንግስቱ በላይ የሆነ እርምጃ መውሰድ ይጠይቃል፡ በዚህ መሰረት ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በምህረት አሠራር ሊታዩ ይገባል።

### 6.4.2.2.ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

**ሀ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች/ኩነቶች'**

በመላ ሀገሪቱ በተደረጉ በእያንዳንዳቸው የሴት ተጎጂዎች፡ ወንድ ተጎጂዎች፡ ቅልቅል ቡድኖች፡ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውይይቶች ላይ የምህረት ቅደመ-ሁኔታዎች በዝርዝር ተጠቁመዋል። **ሀሳቦቹ እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።**

- በምህረት አሰጣጥ ሂደት ጥፋትን ማመን፡ መጸጸት፡ የተበደሉ ሰዎችን/ማህበረሰብ ይፋዊ በሆነ መንገድ ይቅርታ መጠየቅ፡ ተመጣጣኝ ካሳ መክፈል፡ ተመሳሳይ ድርጊት ላለመፈፀም ቃል መግባት፣
- የተጎጂዎች ለይቅርታ ምላሽ መስጠት፡ ፣
- የበዳይና ተበዳይ ስምምነት፡ እንዲሁም የተበዳይ ሁኔታና ፍላጎት፣

- አጥፊው በወንጀሎቹ የነበረው የተሳትፎ ደረጃ፡ የወንጀሎቹ አይነት (ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰት ፈፃሚዎች ሳይካተቱ)፣
- የአጥፊው የንቃተ-ህሊና ደረጃ፡ ወንጀሉ በግብታዊነት፡ በግዳጅ ወይም በአጃቢነት የተፈፀመ መሆን/አለመሆን፡ በጥፋት የተሳተፈው በፈቃዱ/በሌሎች ግፊት መሆን/አለመሆን፡ ጥሰቱ በስህተት/ባለማወቅ የተፈጸመ ከሆነ፣
- አጥፊው እውነትን በማውጣት ሂደት የነበረው ተሳትፎ (ለምሳሌ ከእውነት አፈላላጊ ተቋም ጋር ትብብር ማድረግ)፡ የወንጀልን እቅድ፡ መሪ፡ ዓላማ እና አጠቃላይ ሁኔታ አስመልክቶ ለሚመለከተው አካል መንገር እና የእውነትና እርቅ ሂደቱን ማገዝ፣
- የአጥፊው የወንጀል ታሪክ (ከዚህ ቀደም ወንጀል ያልሰራ ከሆነ)፡ እድሜና የትምህርት ደረጃ፡ በማህበረሰቡ የነበረው መልካም ባህሪ ሁኔታ፣
- ጥፋተኛው ለሀገር የሰጠው አበርክቶ፡ የበጎ ፈቃድና ህዝባዊ አገልግሎት ተሳትፎ፡ ሰላማዊነት፣
- የአጥፊው የጤንነትና የዕድሜ ሁኔታ፡ ባህሪ፡ የመታረም ዝንባሌ፡ ለህብረተሰቡ የሚደቅነው አደጋ (ስጋት)፣
- አጥፊው በወንጀል ምርመራ ሂደቱ ላይ ያደረገው አስተዋጽኦ፣
- ለሚመለከተው አካል ራሱን አሳልፎ የሰጠ መሆን/አለመሆን፣
- የሀገር ብሄራዊ ጥቅም የተነካበት ደረጃ፣
- ባለስልጣን ከሆነ ስልጣን መልቀቅ፡ እንዲሁም ህዝብን በይፋ ይቅርታ መጠየቅ።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ - በተለይ በትግራይ ክልል የነበሩ ተሳታፊዎች ምህረት የመስጠት ሂደት ከመጀመሩ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገቡ የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎችን ዘርዝረዋል።

- የተፈናቀሉ ወገኖች ወደ የቦታቸው እንዲመለሱ ማድረግ፣
- የወደሙ ተቋሞች በሙሉ ወደ ስራ የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ለተበዳዮች ተመጣጣኝ ካሳ መስጠት፡ በተለይ በጅምላ የተገደሉ ሰዎች የሚካሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- የክልሉን ህዝብ ችግር መሬት ላይ ወርዶ በማጥናት አስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ፣
- የውጭ እና የውስጥ ተፋላሚ ሃይሎች ከክልሉ ሙሉ ለሙሉ እንዲወጡ ማድረግ፡ በፕሪቶሪያ የተደረገውን ስምምነት መፈፀም፣
- የሃይማኖት ተቋማትን ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ፣

ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ውስን ተሳታፊዎች ተጨማሪ ሃሳቦችን አቅርበዋል።

- ጥፋተኝነት በፍርድ ሳይረጋገጥ ምህረት ሊኖር አይገባም፣
- በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 28 መሰረት ምህረት ሊሰጣቸው የማይገቡ ወንጀሎች መጠበቅ አለባቸው፣
- ሀገርና ህዝብን ለጥፋት/ለእልቂት የዳረጉ ግለሰቦች ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ምህረት ሊሰጣቸው አይገባም፣
- የምህረት አሰጣጥ የተጎዱ ሰዎችን ሞራልና ስሜት በማይነካ መልኩ መከናወን አለበት፣
- በተጨማሪም ምህረት የሚሰጠው የተፈናቀለው ህዝብ ወደ ቀዬው ከተመለሰ እና ተበዳዮች ተገቢ ማካካሻ ካገኙ በኋላ መሆን አለበት።

### ለ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡ 'ለምህረት ብቁ የማያደርጉ መስፈርቶች/ኩነቶች'

በተመሳሳይ በመላ አገሪቱ በተደረጉ በእያንዳንዳቸው የሴት ተጎጂዎች፡ ወንድ ተጎጂዎች፡ ቅልቅል ቡድኖች፡ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውይይቶች ላይ ተሳታፊዎች ምህረት ሊሰጥ የማይችልባቸውን ሁኔታዎች አስመልክቶ በርካታ ሃሳቦችን አንስተዋል። እነዚህ ምልከታዎች እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።

- በአለም-አቀፍ ሕግ እና በህገ መንግስቱ ምህረት በሚያስከልክሉ ጉዳዮች መሳተፍ፣፣።
- ከባድ ዓለም-አቀፍ ወንጀል መፈጸም፣

- ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ወይም ከባድ ወንጀል ማቀድ፣ ማዘዝ፣ መምራት፣ ማስፈፀም፣ መፈፀም፣፣
- ሆን ብሎ/በግፍ ግድያ፣ በዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በጦር ወንጀል መሳተፍ፣ በሰብዕና ላይ የሚፈጸም ወንጀል፣ ጭካኔ በተመላበት/ኢሰብአዊ ድብደባ ወይም አያያዝ ድርጊቶች መሳተፍ፣ ሰውን አስሮ ማሰቃየት፣፣
- በሴቶች ላይ ጭካኔ በተመላበት ሁኔታ የአስገድዶ መድፈር፣ ግብረሶዶም ወይም መሰል በደል መፈፀም፣
- ከማህበረሰቡ ባህልና ወግ ውጭ የሆኑ ወንጀሎችን መፈጸም፣ ጠለፋ፣
- በመሳሪያ አስፈራርቶ በወንድ ላይ የጾታ ጥቃት መፈጸም፣ አስገድዶ መድፈር፣
- ሰውን ከነቤቱ ማቃጠል፣ ሰውን እንደ እንስሳ አንገቱን በመቁረጥ መግደል፣
- ሬሳ ማቃጠል፣ መሬት ላይ መጎተት፣ ለአስክሬን ክብር መንፈግ፣ ቀብር መከልከል፣
- እህልና ውሀ ማገድ፣ መከልከል፣ ለችግረኞች የምግብና የመሠረታዊ ሸቀጦችን ፍሰት ሆን ብሎ መክልከል፣ እንዲራቡ ማድረግ፣
- ህዝብን ማፈናቀል፣
- የሀገር ክህደት መፈጸም፣
- በወንጀል ስራ ያለው ተደጋጋሚ ተሳትፎ፣ በድርጊቶቹ ዋና አጥፊ መሆን፣
- አለመፀፀት፣ እውነትን ለማውጣት አለመተባበር፣

---

### 6.4.2.3.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

የምህረት ቅድመ ሁኔታዎችን በሚመለከት በሁሉም መድረኮች የተሰጡ ግብአቶች እንደሚከተለው ተጠቃለዋል፡፡

ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ፥

- የተፈፀመው ወንጀል ከባድ ካልሆነ፣
- ያጠፋው ሰው ከተፀፀተ፣ ይቅርታ ከጠየቀ እና ማካካሻ ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነ፣
- እውነትን በማውጣት ተግባር ላይ ለመሳታፍ ፈቃደኛ ከሆነ፣
- በትምህርት ቤት፣ የዕምነት ተቋማት እና በመሳሰሉት መሰረታዊ ልማቶች ላይ ጉዳት ያላደረሰ፣
- በተፅዕኖ እና በትዕዛዝ ሥር የነበረ አጥፊ ከሆነ፡፡

ለምህረት ብቁ የማያደርጉ ጥፋቶች፥

- በሕገወጥ የሕፃናት ዝውውር እና በህፃናት ላይ ወንጀል መፈጸም፣
- የሀገርን ሚስጥር ማውጣት፣ የጦር ወንጀል፣ ሀገር መክዳት፣ የጅምላ ግድያን ጨምሮ ከባድ ወንጀሎችን መፈፀም፣
- በየትኛውም ወንጀል ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው ግለሰቦች፣
- ከጾታዊ ጥቃት ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን መፈፀም፡፡

### 6.4.2.4.ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

የምህረት ቅድመ-ሁኔታዎችን በሚመለከት በጉልህ አለም አቀፍ ወንጀል ለተከሰሱ ሰዎች ምህረት ከሚከለክሉ አለም-አቀፍ ሕጎችና ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር የሚጣጣመው የህገ-መንግስቱ አንቀጽ 28 እንዳይጣስ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በተሳታፊዎች ምክረ-ሃሳብ ቀርቧል፡፡ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 28 በተደነገጉት ላይ ይቅርታና ምህረት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ቢያንስ ህገ-መንግስታዊ ትርጉም ወይም ማሻሻያ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ተገልጿል፡፡

**ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ፥**

- በመብት ጥሰት የነበረ ተሳትፎ መጠን/አይነት እና በዕውነት ማመን፣
- የማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት መስማማት፣
- ከተወሰነ ሙያዊ ሐላፊነት ለመነሳት መስማማት፣
- የተጎጂዎችን ፍላጎት ለማሟላት መጣር፣
- የተጋላጭ የማህረሰብ ክፍሎችን ፍላጎትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን።

**ለምህረት ብቁ የማያደርጉ ጥፋቶች፥**

- በሰሜኑ ጦርነት ማእቀፍ (ትግራይ፣ አፋር፣ አማራ) የተፈፀሙ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎች፣
- የዘር ማጥፋት፣ የጦር ወንጀሎች እና በሰብዕና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን መፈፀም፣
- ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን፣ እንዲሁም በግጭት ማእቀፍ ውስጥ የጾታ ጥቃቶችን እና በህጻናት ላይ ወንጀሎችን መፈፀም።

### 6.4.3. ምህረት የመስጠትን ሂደት ማን ያከናውነው?

#### 6.4.3.1.መግቢያ

በሽግግር ፍትህ የምህረት ሂደቱ አቀራረጽ እና ይዘት መሰረታዊ የመሆኑን ያህል ምህረት የሚሰጠው አካል ህጋዊነት እና ተቀባይነትም ለስኬቱ ትልቅ ሚና ይጫወታል። በዚህ ረገድ ለውይይት መነሻ እንዲሆኑ ሁለት መሰረታዊ የአደረጃጀት አማራጮች ቀርበዋል።

የመጀመሪያው አማራጭ **'አዲስ ኮሚሽን በማቋቋም የምህረት ስራዎችን ማከናወን'** የሚል ነው። በሌሎች አገራት ልምድ እንደታየው - በሽግግር ፍትህ ሂደት - ከእውነት ማግኘት ጋር ተዛምዶ የሚሰጥ ምህረት ግቡን እንዲያሳካ እና ተግባራዊ አፈጻጸሙም ስኬት እንዲያገኝ ለማድረግ የምህረት ሂደቱን ነጻና ገለልተኛ ሆኖ በሚቋቋም የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽን አማካኝነት መምራት ያስፈልጋል። የምህረትን አካሄድ በተመለከተ - የሽግግር ፍትህ ሂደቱን በሚገዛው የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ አስፈላጊ የሕግ ድንጋጌዎች እንዲኖሩ ማድረግ ተገቢ ነው።

ሁለተኛው አማራጭ **'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት'** የሚል ነው። ይህ አካሄድ የምህረት አሰጣጥና አፈጻጸም ስነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1089/2010ን በማሻሻል እና ለሽግግር ጊዜ ፍትህ ተገቢ በሆነ መልኩ በመቃኘት - የፍትህ ሚኒስቴር፣ የምህረት ቦርዱ፣ እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምርመራ የሚያካሂዱበት እና ውሳኔ የሚሰጡበትን ሂደት መከተል ማለት ነው።

ተሳታፊዎች ከሁለቱ አማራጮች ውጭ ሌላ ተቋማዊ አደረጃጀት መመስረት ተገቢ ነው የሚል እይታ ካላቸውም ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ገለፃ ተደርጓል።

#### 6.4.3.2.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

I. **የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች**

**ሀ. በአብዛኛው የሴት ተጎጂዎች ቡድን የተደገፈ አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 1)**

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች መካከል 37.5 ቡድኖች (ወይም 76.5%) የሚሆኑት የምህረት መስጠት ስራን 'አዲስ ኮሚሽን በማቋቋም ማከናወን' ይገባል የሚል አቋም ደግፈው ተከራክረዋል። ለዚህ የሰጡት ምክንያት እንደሚከተለው ይቀርባል።

- አሁን ስራ ላይ ያለው የምህረት ቦርድም ሆነ ሌሎች ተቋሞች የብቃት፣ የገለልተኛነት እና የአሳታፊነት ክፍተት አለባቸው፣

- የምህረት ሂደቱ በመንግስት ተቋማት የሚከናወን ከሆነ ገለልተኛ አይሆንም፡ ባሉት ተቋማት ላይ ህዝቡ በቂ እምነት የለውም፡
- ምህረት ሊሰጥ የሚገባው እውነቱን ባፈላለገውና በቂ መረጃ ባለው አካል መሆን አለበት፡
- በነባሩ የምህረት አሰጣጥ ሕግና ስርዓት መሰረት ሰከናወን የቀየው ምህረት የተዛባና ፍትሃዊነት የሚጎድለው ነው፡
- ምህረት በእውነት ማፈላለጉ ተግባር ላይ መመስረት አለበት፡ በቀረበለት ጥልቅ ምርመራ ወይም የዕውነት አጣሪና አፈላላጊ ውጤት ላይ በመመስረት እና ኩነቶችን በመገምገም ምህረትን የሚሰጥ ገለልተኛ ተቋም ማቋቋም ያስፈልጋል፡ ይህ አዲስ ተቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን መሆን አለበት፡
- አጠቃላይ የምህረት ሰጪው ተቋም አመሰራረትና የምህረት አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽ፡ አሳታፊና አካታች በሆነ መልኩ መከናወን አለበት።

## ለ) በተወሰኑ የሴት ተጎጂዎች ቡድን የተደገፈ አማራጭ፡ 'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት' (አማራጭ 2)

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 3 ቡድኖች (ወይም 6.12%) የሚሆኑት - የምህረት መስጠቱ ሂደት (በአዋጅ ቁጥር 1089/2010 መሰረት በተቋቋመው የምህረት ቦርድ) አማካኝነት 'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት' ይመረጣል የሚል አቋም ይዘዋል። ለዚህም ያቀረቡት ምክንያት የሚከተለው ነው።

- ምህረት የመስጠት ሂደት ቀጣይነት ያለው ተግባር ነው፡ በመሆኑም የሂደቱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ ይህ አማራጭ የተሻለ ነው፡
- በአዋጅ ቁጥር 1089/2010 ላይ ተገቢ ማሻሻያ በማድረግ በጊዜ እና በፍጥነት ውሳኔዎችን ማሳለፍ የሚቻልበት እድል መፍጠር ይቻላል፡
- አሁን ያለው አደረጃጀት ከህዝቡ ጋር የኖረ የህዝቡን ችግር የሚያውቅ ነው፡ አዲስ ተቋም መመስረት ችግሮችን በአግባቡ ላይረዳ ወይም ለመረዳት የሚዘገይ ሊያደርገው ይችላል፡
- አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም የሀብት ብክነትን ያስከትላል።

## ሐ) በውስን የሴት ተጎጂዎች ቡድን የተደገፉ 'ሌሎች አማራጮች'

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 7.5 ቡድኖች (ወይም 15.3%) የሆኑት ተጨማሪ አማራጮችን አቅርበዋል። ቡድኖቹ እና አቋሞቻቸው አንድ ወጥ ባይሆኑም ዝርዝር ምክንያቶቻቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ባህላዊ ተቋሞች (ለምሳሌ በአፋር ክልል እንዳለው ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት) የምህረት ሂደትን እንዲያከናውኑ ቢደረጉ ለማህበረሰቡ ልምድና ባህል ትልቅ ቦታ ይሰጣል፡
- በትግራይ ክልል ከደረሰው ጥፋት አንፃር ይህን ሀላፊነት ለሀገር ውስጥ ተቋማት መስጠት ተገቢ አይሆንም፡ እምነት የሚጣልባቸውም አይደሉም፡ ስራው በገለልተኛ ዓለም-አቀፍ ተቋም ሊያከናወን ይገባል፡ (አራት ቡድኖች)፡
- ምህረት ትክክለኛና የህዝብን አመኔታ ባተረፈ መልኩ እንዲሰጥ ለማስቻል በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ቢከናወን ይመረጣል፡ (አንድ ቡድን)፡
- አሁን ካለው አገራዊ የኢኮኖሚ አቅም አንፃር ምህረት የመስጠት ስራ በአገራዊ የምክክር ኮሚሽን ቢሠራ የተሻለ ይሆናል፡ (ውስን ተሳታፊዎች)፡

- በአዋጅ ቁጥር 1089/2018 መሰረት የተቋቋመው የምህረት ቦርድ የፖለቲካ ጫና ሊደረግበት ይችላል፡ ስለሆነም ምህረት የመስጠቱ ሂደት በፍርድ ቤት ሊከናወን ይገባል፡ (አንድ ቡድን)፡
- ምህረት መስጠት አስፈላጊ አይደለም፡ የግድ ይሰጥ ከተባለ ግን ነፃና ገለልተኛ በሆነ ፍርድ ቤት መካሄድ አለበት፡ (ውስን ተሳታፊዎች)፡

ሰንጠረዥ 45፡ 'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' - የሴት ተጎጂ ቡድኖች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታ በቁጥር

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | 0.5 | 1 | ኢሰመኮ (0.5) |
| 2 | አፋር | 1 | | | ባህላዊ ተቋሞች (1) |
| 3 | አማራ | 7 | 7 | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 2 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | | |
| 7 | ሀረሪ[60] | 1 | | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 12 | 2 | |
| 9 | ሲዳማ | 1 | | | ፍርድ ቤት (1) |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 3 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 8 | | ፍርድ ቤት (1) |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 2 | | |
| 13 | ትግራይ | 5 | 1 | | አለማቀፍ (4) |
| | ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | 49 | 37.5 | 3 | 7.5 |

## II. የወንድ ተጎጂዎች ቡድን

### ሀ. በአብዛኛው የወንድ ተጎጂዎች ቡድን የተደገፈ አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 1)

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 41 ቡድኖች (ወይም 87.2%) የሆኑት የምህረት መስጠት ስራውን 'አዲስ ኮሚሽን በማቋቋም ማከናወን' ይገባል የሚል አቋም ደግፈዋል፡፡ ለዚህ የሰጡት ምክንያት እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

- አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን ምህረት የመስጠቱ ሂደት ቢከናወን የህዝብ ተቀባይነት/ተአማኒነት ይኖረዋል፡
- በአዋጅ ቁጥር 1089/2010 መሰረት የተቋቋመው ቦርድ በአግባቡ እየሰራ አይደለም፡ ንቁ እንቅስቃሴ የለውም፡ ውጤታማ ስራ ሲሰራም አልታየም፡
- የምህረት አዋጁ በፖለቲካ የተጠለፈ ነው፡ ካሁን ቀደም በግልጽ ህዝብን ሲበድሉ፡ ሲገድሉ እና ሲጨፈጭፉ ለነበሩ አካላትን ጭምር ምህረት እንዲያገኙ ያደረገ ነው፡ በዚህም ፍትህ አጓድሏል፡
- ገለልተኛ እና ነጻ ተቋም ማደራጀት ለሽግግር ፍትህ ሂደት መሰረታዊ ሁነት ነው፡
- ለጉዳዩ ትኩረት ለመስጠት እና ፍትሐዊ/ሚዛናዊ ሆኖ ለመወሰን አዲስ ተቋም የተሻለ እድል አለው፡
- አዲስ ተቋም ማደራጀት ከእርቅና ሌሎች ስልቶች ጋር አቀናጅቶ መስራት ያስችላል፡

[60] አንድ ቡድን ሀሳብ አልሰጠም፡፡

- የሽግግር ፍትህ አውድ ከመደበኛው የፍትሕ ስርዓት ይለያል፡ ስለሆነም ሂደቱ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በሚቋቋም አዲስ ኮሚሽን ሊከናወን ይገባል፡
- የሚመሰረተው አዲስ ኮሚሽን ሁሉን-አቀፍ፡ አሳታፊ መሆን አለበት፡ ተጎጂዎችም በሚቋቋመው ኮሚሽን መወከል/መሳተፍ አለባቸው።

**ለ) በተወሰኑ የወንድ ተጎጂዎች ቡድን የተደገፈ አማራጭ፡ 'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት'** (አማራጭ 2)

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 3 ቡድኖች (ወይም 6.38%) የሆኑት - 'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት' የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። ለዚህ የሰጡት ምክንያት እንደሚከተለው ይቀርባል።

- ለሁሉም የሽግግር ፍትህ ጉዳዮች አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም አይገባም፡ በነባሩ የምህረት ቦርድ መጠቀም የማይቻልበት ምክንያት የለም፡
- ተቋም ማብዛት ብክነት እንጂ ለውጥ አያመጣም፡ ተጎጂዎችን በማሳተፍ፡ የነበረውን ቦርድ በመፈተሸና በማስተካከል መጠቀም ተመራጭ አካሄድ ነው፡
- ምህረት የመስጠት ሥራ የምህረት ቦርዱ ሀላፊነት ሆኖ መቀጠል አለበት፡ ቦርዱ የዳበረ የምህረት አሰጣጥ ስርዓት እውቀት ያለው ከመሆኑም በላይ የምህረት አሰጣጥ ሂደት ለሚኖረው ውስብስብ ባህሪ የተመቸ ቁመና አለው፡
- ይህን ሀላፊነት አዲስ ለሚቋቋመው የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን መስጠት ትልቅ የስራ ጫና በመፍጠር ኮሚሽኑ የተጣለበትን ሀላፊነት በአግባቡ እንዳይወጣ ይደርገዋል።

**ሐ) በተወሰኑ የወንድ ተጎጂዎች ቡድን የተደገፉ የተለያዩ 'ሌሎች አማራጮች'**

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 3 ቡድኖች (ወይም 6.38%) የሆኑት የተለያዩ አማራጮችን አቅርበዋል።

- ሁለት ቡድኖች በሀገር ውስጥ ተቋማት እምነት እንደሌላቸው በመግለፅ ምህረት የመስጠት ስራው በዓለም-አቀፍ (ወይም ቅይጥ) ተቋማዊ አደረጃጀት ሊመራ ይገባል የሚል አዲስ ሀሳብ ደግፈው ተከራክረዋል፡
- አንድ ቡድን ስራው አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት መሰራት ያለበት ሆኖ ኮሚሽኑ ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶችን ባካተተ/ባሳተፈ መልኩ ስራዎቹን እንዲያከናውን ቢደረግ በማህበረሰብ ደረጃ የተሻለ ተቀባይነት እንዲኖረው ያስችላል የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።
- ውስን ተሳታፊዎች የምህረት አሰጣጡ በሀገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት አባቶች አማካኝነት ቢከናወን ተመራጭ ነው ብለዋል፡
- ሌሎች ውስን የቡድን አባላት ደግሞ ከተሰጠው ሀላፊነት ጋር ተያያዥ ስለሆነ ምህረት የመስጠት ተግባር በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ሊከናወን ይገባል የሚል አቋም ይዘዋል።

*ሰንጠረዥ 46፡ 'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' - የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታ ማጠቃለያ በቁጥር*

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | | |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | አማራ | 7 | 5 | 1 | ምክክር ኮሚሽን (1) |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 2 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | | |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 1 | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 14 | | |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | | |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 3 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 7 | 2 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 2 | | |
| 13 | ትግራይ | 5 | 3 | | አለማቀፍ/ቅይጥ ተቋም (2) |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 47 | 41 | 3 | 3 |

**III. የቅልቅል ቡድን**

**ሀ) በአብዛኛው የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 1)**

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 70.5 ቡድኖች (ወይም 73.43%) - የምህረት መስጠት ስራውን 'አዲስ ኮሚሽን በማቋቋም ማከናወን' ይገባል የሚል አቋም ደግፈዋል። ለዚህ የሰጡት ምክንያት እንደሚከተለው ይቀርባል።

- ይህ አማራጭ ወጥ የሆነ የምህረት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖር ያስችላል፡
- በአዋጅ የተቋቋመው የምህረት ቦርድ ብዙ ጥፋት አድርሷል፡ ተአማኒ አይደለም፡
- እየተተገበረ ያለው የምህረት አሰጣጥ ሂደት ኢ-ፍትሃዊ እና የተሳሳተ ነው፡ የተበዳዩን ሀሳብ ማዕከል ያደረገ አይደለም፡ ይህን ለሽግግር ሂደት መጠቀም ውጤታማ አያደርግም፡
- በአብዛኛው ምህረት ሊሰጥ የሚገባው እውነቱን ባፈላለገውና በቂ መረጃ ባለው ተቋም መሆን አለበት፡
- አዲስ ተቋም የማደራጀት አስፈላጊነት በሌሎች አገራት ተሞክሮ ታይቷል፡ የህዝብ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡
- አዲስ፡ ነፃ እና ገለልተኛ ተቋም ማደራጀት ለተበዳይ ፍትህ ለመስጠት ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል፡ አዲስ አሰራር እና ተሞክሮ ለማስተዋወቅ፡ እንዲሁም ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት የተሻለ አማራጭ ነው፡
- አዲስ ተቋም የተሻለ በጀትና የባለሙያ ድጋፍ ይኖረዋል፡ ስልጣንና ተግባሩን በነጻነት ለመወሰን ያስችላል፡
- የሚመሰረተው ኮሚሽን የሀይማኖት አባቶች/የሀገር ሽማግሌዎችን ባካተተ መልኩ መስራት አለበት።

**ለ) በተወሰኑ የቅልቅል ቡድን የተደገፈ አማራጭ፡ 'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት' (አማራጭ 2)**

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 15.5 ቡድኖች (ወይም 16.14%) የሆኑት - 'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት' ያስፈልጋል የሚለውን አቋም ደግፈዋል። የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ስራው በአዋጅ ቁጥር 1089/2010 መሰረት በተቋቋመውና ልምድ ባለው የምህረት ቦርድ ቢሰራ ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል፡

- ከበጀት እና ከጊዜ አንጻር አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም ተመራጭ አይሆንም፡ አዲስ ተቋም ማቋቋም ከወጪ ባለፈ የሚጨምረው እሴት የለም፡
- አዲስ ኮሚሽን ተዓማኒነት ለማስፈን ቢያግዝም ከአገሪቱ ኢኮኖሚ አቅም አንጻር ተመራጭ አይሆንም።

### ሐ) በውስን ተሳታፊዎች የተደገፉ 'ሌሎች አማራጮች'

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 8 ቡድኖች (ወይም 8.33%) የሆኑት በተለያዩ መንገዶች የተገለጹ 'ሌሎች አማራጮችን' ደግፈዋል።

ሁለት ቡድኖች 'በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን' አማካኝነት እንዲሰራ፡ ሌላ 1 ቡድን 'በሀገር ሽማግሌዎች' እንዲከናወን፡ ተጨማሪ 3 ቡድኖች ደግሞ 'ገለልተኛ እና አለማቀፋዊ (ወይም ቅይጥ) በሆነ ተቋም' እንዲሰራ የየራሳቸውን ሀሳብ አቅርበዋል። አንድ ቡድን ምህረት በተበዳዮች ብቻ ሊሰጥ ይገባል ሲል ተከራክሯል። ወጥነት በሌለው መልኩም ቢሆን ቡድኖቹ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- የምህረት ስራ ትክክለኛና የህዝብ አመኔታ ባተረፈ መልኩ እንዲሰጥ ለማስቻል በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ሊሰጥ ይገባል፡
- ስራው በአገራዊ የምክክር ኮሚሽን ወይም በሀገር ሽማግሌዎች ቢሰራ ይበልጥ ተመራጭ ነው፡ ጊዜና ወጪ ይቆጥባል፡
- ምህረት የመስጠት ስራ ሂደት የየማህበረሰቡን ባህል፡ ወግና ሃይማኖት ግምት ውስጥ በማስገባት በሚቋቋም ኮሚሽን ቢከናወን ውጤታማ ይሆናል፡
- በባህላዊ ሥርዓት (ለምሳሌ በገዳ) ማዕቀፍ የሚሰጥ ምህረት በህዝብ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አለው፡ ለእርቅና ለዘላቂ ሰላምም መሠረት ነው፡ ስለሆነም ይህ ከባቢያዊ የአሰራር ሥርዓት ሀላፊነት ሊሰጠው ይገባል፡
- በርካታ ብሄሮችን ማዕከል ባደረጉ ግጭቶች ማዕቀፍ ለሚፈፀሙ በደሎች የምህረት ስራው በኮሚሽን ብቻ እንዲካሄድ ማድረግ ችግር ያጭራል፡ ለዚህ ዓላማ ከተጋጩ ብሄሮች ውስን አባላት የሚውጣጡበትን አሰራር ማሰብ ተገቢ ነው፡ በሌላ አካል እንዲሁ ከላይ በወረደ ሂደት የሚሰጥ ምህረት ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል፡
- በሀገር ውስጥ ተቋማት ላይ እምነት ስለሌለ የምህረት መስጠት ስራ በገለልተኛ/ዓለምአቀፍ ተቋም መከናወን አለበት።

ሰንጠረዥ 47፡ 'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' - የቅልቅል ቡድኖች ሀገር-አቀፍ እና ክልል አቀፍ ማጠቃለያ በቁጥር

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | 4 | 1 | ባህላዊ ተቋሞች (1) | |
| 2 | አፋር | 2 | 2 | | | |
| 3 | አማራ | 13 | 9 | 3 | | 1 ቡድን አስተያየት አልሰጠም |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | 2.5 | 0.5 | በምክክር ኮሚሽን (1) | |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | 2 | | | |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 2 | | | |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 2 | | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 22 | 5 | | |
| 9 | ሲዳማ | 2 | 2 | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ሶማሌ | 4 | 3 | 1 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 11 | 4 | በምክክር ኮሚሽን (1) በሽማግሌዎች (1) | 1 ቡድን አስተያየት አልሰጠም |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 3 | 1 | | |
| 13 | ትግራይ | 10 | 6 | | - አለማቀፋዊ/ቀይጥ (3)<br>- በተበዳዮች ብቻ (1) | |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 96 | 70.5 | 15.5 | 8 | 2 |

## IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች

### ሀ. በአብዛኛው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' (አማራጭ 1)

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 21 ቡድኖች (ወይም 87.5%) የሆኑት - ምህረት የመስጠት ስራን 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' ይገባል ብለዋል፡፡ ለዚህ የሰጡት ምክንያት እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

- አሁን ባሉት ተቋማት ላይ አመኔታ የለም፡ አዲስ ተቋም ነጻና ገለልተኛ ሆኖ መስራት ያስችላል፡
- አዲስ ተቋም ስራውን በትኩረት ለመስራት እድል ይሰጣል፡
- በአዋጅ ቁጥር 1089/2010 መሰረት የተቋቋመው የምህረት ቦርድ ወንጀለኞችን በጅምላ እየለቀቀ አገሪቱን አሁን ላለችበት ችግር አጋልጧል፡፡

### ለ. በተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት' (አማራጭ 2)

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 3 ቡድኖች (ወይም 12.5%) የሆኑት ይህን አማራጭ ደግፈዋል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት ያቀረቡት ቦርዱ ይህን ስራ ብቻ ለመስራት የተቋቋመ እስከሆነ ድረስ ተመሳሳይ ሥራ የሚሰራ ሌላ ተቋም ማቋቋም አያስፈልግም የሚል ነው፡፡

ሰንጠረዥ 48፡ 'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' - የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ በቁጥር

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | | |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | | |
| 3 | አማራ | 5 | 4 | 1 | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | 1 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | | |
| 7 | ሀረሪ | 0 | 0 | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | 7 | | |
| 9 | ሲዳማ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ሶማሌ | 1 | 1 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 0 | | | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 3 | 2 | 1 | |
| 13 | ትግራይ | 4 | 3 | 1 | |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 24 | 21 | 3 | |

### 6.4.3.3.'የምህረት ሂደቱ በማን ሊከናወን ይገባል?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

**ሀ. በሀገር-አቀፍ ደረጃ በአብዛኛዎቹ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' - ምክንያቶች**

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 170 ቡድኖች (ወይም 78.7%) የሚሆኑት የስራ ሂደቱን 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' ይገባል የሚለውን አቋም ይዘው ተከራክረዋል፡፡

**ይህም መረጃ በቡድን አይነት ተለይቶ ሲታይ** - ከአጠቃላይ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 37.5 ቡድኖች፣ ከአጠቃላይ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 41 ቡድኖች፣ ከአጠቃላይ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 70.5 ቡድኖች፣ እንዲሁም ከአጠቃላይ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 21 ቡድኖች 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት የምህረት ስራ ማከናወን' የሚለውን አማራጭ መርጠዋል፡፡

**ይህ መረጃ በአካባቢያዊ ስርጭት እይታ ሲታይ** ደግሞ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት የምህረት ስራ ማከናወን' የሚለው ሀሳብ በ13 ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ከፍተኛውን ድጋፍ ያገኘ አማራጭ ነው፡፡

ተሳታፊዎች ይህን አቋማቸውን የሚደግፉ በርካታ ምክንያቶችን ሰጥተዋል፡፡ እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

- አሁን ስራ ላይ ያለው የምህረት ቦርድም ሆኑ ሌሎች ተቋሞች የብቃት፣ የገለልተኛነት እና የአሳታፊነት ክፍተት አለባቸው፣
- የምህረት ሂደቱ በመንግስት ተቋማት የሚከናወን ከሆነ ገለልተኛ አይሆንም፣ ባሉት ተቋማት ላይ ህዝቡ በቂ እምነት የለውም፣
- በነባሩ የምህረት አሰጣጥ ሕግና ስርዓት መሰረት ሲከናወን የቆየው ምህረት የተዛባና ፍትሃዊነት የሚጎድለው ነው፣ ቦርዱ በአግባቡ እየሰራ አይደለም፣ ንቁ እንቅስቃሴ የለውም፣ ውጤታማ ስራ ሲሰራም አልታየም፣ አሰራሩ የተበዳይን ሀሳብ ማዕከል ያደረገ አይደለም፣ ይህን ለሽግግር ሂደት መጠቀም ውጤታማ አያደርግም፣
- የምህረት አዋጁ በፖለቲካ የተጠለፈ ነው፣ ካሁን ቀደም በግልጽ ህዝብን ሲበድሉ፣ ሲገድሉ እና ሲጨፈጭፉ ለነበሩ አካላትን ጭምር ምህረት እንዲያገኙ ያደረገ ነው፣ ወንጀለኞችን በጅምላ እየለቀቀ አገሪቱን አሁን ላለችበት ችግር አጋልጧል፣ ፍትህ አጓድሏል፣
- ምህረት ሊሰጥ የሚገባው እውነቱን ባፈላለገውና በቂ መረጃ ባለው አካል መሆን አለበት፣ በቀረበለት ጥልቅ ምርመራ ወይም የዕውነት አጣሪ ውጤት ላይ በመመስረት እና ኩነቶችን በመገምገም ምህረትን የሚሰጥ ገለልተኛ ተቋም ማቋቋም ያስፈልጋል፣ ይህ ተቋም የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን መሆን አለበት፣
- አዲስ ተቋም የማደራጀት አስፈላጊነት በሌሎች አገራት ተሞክሮ ታይቷል፣
- አዲስ፣ ነፃ እና ገለልተኛ ተቋም ማደራጀት ለተበዳይ ፍትህ ለመስጠት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፣ አዲስ አሰራር እና ተሞክሮ ለማስተዋወቅ፣ እንዲሁም ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት የተሻለ አማራጭ ነው፣
- አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን በኩል ምህረት የመስጠቱ ሂደት ቢከናወን የህዝብ ተቀባይነት/ተአማኒነት ይኖረዋል፣

- ለጉዳዩ ትኩረት ለመስጠት እና ፍትሐዊ/ሚዛናዊ ሆኖ ለመወሰን አዲስ ተቋም የተሻለ እድል አለው፣
- አዲስ ተቋም ማደራጀት ከእርቅና ሌሎች ስልቶች ጋር አቀናጅቶ ለመስራት ያስችላል፤
- አዲስ ተቋም የተሻለ በጀትና የባለሙያ ድጋፍ ይኖረዋል፤ ስልጣንና ተግባሩን በነጻነት ለመወሰን፤ ስራውንም በትኩረት ለመስራት እድል ይሰጣል፤
- ይህ አማራጭ ወጥ የሆነ የምህረት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖር ያስችላል፤
- ገለልተኛ እና ነጻ ተቋም ማደራጀት ለሽግግር ፍትህ ሂደት መሰረታዊ ሁነት ነው፣
- የሽግግር ፍትህ አውድ ከመደበኛው የፍትሕ ስርዓት ይለያል፤ ስለሆነም ሂደቱ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በሚቋቋም አዲስ ኮሚሽን ሊከናወን ይገባል፤
- የምህረት ሰጪው አዲስ ተቋም አመሰራረትና የምህረት አሰጣጥ ሂደት ግልጽ፣ አሳታፊና አካታች በሆነ መልኩ መከናወን አለበት፣ የሚመሰረተው ኮሚሽን ሁሉን-አቀፍ፣ አሳታፊ መሆን አለበት፣ ተጎጂዎችም በሚቋቋመው ኮሚሽን መወከል/መሳተፍ አለባቸው።
- የሚመሰረተው ኮሚሽን የህይማኖት አባቶች/የሀገር ሽማግሌዎችን ባካተተ መልኩ መስራት አለበት።

### ለ. በሀገር-አቀፍ ደረጃ በውስን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን መስጠት' - ምክንያቶች

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 23.5 ቡድኖች (ወይም 10.9%) የሆኑት - 'አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በመጠቀም ምህረትን የመስጠት' ስራዎችን ማከናወን ይገባል ሲሉ አቋማቸውን ገልፀዋል።

**ይህም መረጃ ከቡድኖች ስብጥር አንፃር ሲታይ** ከአጠቃላይ 49 የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች ውስጥ 3 ቡድኖች፣ ከአጠቃላይ 47 የወንድ ተጎጂዎች ቡድኖች ውስጥ 3 ቡድኖች፣ ከአጠቃላይ 92 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 15.5 ቡድኖች፣ እንዲሁም ከአጠቃላይ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 2 ቡድኖች ድጋፋቸውን የቸሩት የፖሊሲ አማራጭ ነው።

ተሳታፊዎች ይህን አቋማቸውን የሚደግፉ በርካታ ምክንያቶችን ሰጥተዋል። እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።

- በአዋጅ ቁጥር 1089/2010 ላይ ተገቢ ማሻሻያ በማድረግ በጊዜ እና በፍጥነት ውሳኔዎችን ማሳለፍ የሚቻልበትን እድል መፍጠር ይቻላል፤
- ምህረት የመስጠት ሂደት ቀጣይነት ያለው ተግባር ነው፣ በመሆኑም የሂደቱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ ይህ አማራጭ የተሻለ ነው፣
- ቦርዱ ይህን ስራ ብቻ ለመስራት የተቋቋመ እስከሆነ ድረስ ተመሳሳይ ሥራ የሚሰራ ሌላ ተቋም ማቋቋም አያስፈልግም፣
- አሁን ያለው አደረጃጀት ከህዝቡ ጋር የኖረ፤ የህዝቡን ችግር የሚያውቅ ነው፣ አዲስ ተቋም መመስረት ችግሮችን በአግባቡ ላይረዳ ወይም ለመረዳት የሚዘገይ ሊሆን ይችላል፤
- ምህረት የመስጠት ሥራ የምህረት ቦርዱ ሀላፊነት ሆኖ መቀጠል አለበት፣ ቦርዱ የዳበረ የምህረት አሰጣጥ ስርዓት እውቀት፣ እንዲሁም የምህረት አሰጣጥ ሂደት ለሚኖረው ውስብስብ ባህሪ የተመቸ ቁመና አለው፣
- ለሁሉም የሽግግር ፍትህ ጉዳዮች አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም አይገባም፣ ተቋም ማብዛት ለውጥ አያመጣም፤
- ከበጀት እና ከጊዜ አንጻር አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም ብክነትን ያስከትላል፤ ተጎጂዎችን በማሳተፍ፣ የነበረውን ቦርድ በመፈተሸና በማስተካከል መጠቀም ተመራጭ አካሄድ ነው፣
- አዲስ ኮሚሽን ተዓማኒነት ለማስፈን ቢያግዝም ከአገሪቱ ኢኮኖሚ አቅም አንጻር ተመራጭ አይሆንም።
- ይህን ሀላፊነት አዲስ ለሚቋቋመው የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን መስጠት ትልቅ የስራ ጫና በመፍጠር ኮሚሽኑ የተጣለበትን ሀላፊነት በአግባቡ እንዳይወጣ ይደርገዋል።

### ሐ. በሀገር-አቀፍ ደረጃ ጥቂት ቡድኖች/ተሳታፊዎች የደገፏቸው 'ሌሎች አማራጮች' - ምክንያቶች

'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ የተወሰኑ ቡድኖች 'የተለያዩ ይዘት ያላቸው ተጨማሪ አማራጮችን' አቅርበዋል፡፡

በሌሎች ሁሉም ክልሎች 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት የምህረት ስራ ማከናወን' የሚለው አማራጭ በላቀ ሁኔታ ድጋፍ ቢያገኝም፣ በትግራይ ክልል በተካሄደው ውይይት ከአጠቃላይ 24 ቡድኖች ውስጥ 10 ቡድኖች በሀገር ውስጥ ተቋማት ላይ እምነት እንደሌላቸው በመግለፅ ገለልተኛ የሆነ ዓለምአቀፍ ተቋም ምህረት የመስጠቱን የስራ ሂደት እንዲያከናውን አዲስ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ ሂደቱ በዓለም-አቀፍ/ቅይጥ ተቋም ይመራ የሚለውን አማራጭ ያራመዱ ሌሎች ቡድኖችም አሉ፡፡

ሌላው በ3 የውይይት ቡድኖች ድጋፍ የተሰጠው ሀሳብ ባህላዊ ተቋሞች በምህረት አሰጣጥ ሂደት ተሳትፎ ይኑራቸው የሚለው አቋም ነው፡፡ ውስን አስተያየት ሰጪዎች ደግሞ የምህረት መስጠቱ ስራ በፍርድ ቤት፣ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን፣ ወይም በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ሊሰጥ ይገባል የሚል ሀሳብ አንፀባርቀዋል፡፡

ተሳታፊዎቹ 'የተለያዩ/ተፃራሪ ይዘት ያላቸው ተጨማሪ አማራጮችን' ለመደገፍ የሰጧቸው ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡


- ምህረት ትክክለኛና የህዝብ አመኔታ ባተረፈ መልኩ እንዲሰጥ ለማስቻል በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ቢከናወን ይመረጣል፣
- አሁን ካለው አገራዊ የኢኮኖሚ አቅም አንፃር ስራው በአገራዊ የምክክር ኮሚሽን ቢሰራ ይበልጥ ተመራጭ ነው፣ ጊዜና ወጪ ይቆጥባል፣ ከተሰጠው ሀላፊነት ጋር ተያያዥ ነው፣
- ምህረት መስጠት አስፈላጊ አይደለም፣ የግድ ከተባለ ግን ነፃና ገለልተኛ በሆነ ፍርድ ቤት መካሄድ አለበት፣
- በአዋጅ ቁጥር 1089/2010 መሰረት የተቋቋመው የምህረት ቦርድ የፖለቲካ ጫና ሊደረግበት ይችላል፣ ስለሆነም ምህረት የመስጠቱ ሂደት በፍርድ ቤት ሊከናወን ይገባል፣ (አንድ ቡድን)
- የምህረት አሰጣጡ ሂደት በሀገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት አባቶች አማካኝነት ቢከናወን ይመረጣል፣
- ምህረት የመስጠት ስራ ሂደት የየማህበረሰቡን ባህል፣ ወግና ሃይማኖት ግምት ውስጥ በማስገባት በሚቋቋም ኮሚሽን ቢከናወን ውጤታማ ይሆናል፣
- በትግራይ ክልል ከደረሰው ጥፋት አንፃር ይህን ሀላፊነት ለሀገር ውስጥ ተቋማት መስጠት ተገቢ አይሆንም፣ እምነት የሚጣልባቸውም አይደሉም፣ ስራው በገለልተኛ ዓለም-አቀፍ ተቋም ሊያከናወን ይገባል፣
- በሀገር ውስጥ ተቋማት እምነት የለም፣ ምህረት የመስጠት ስራው በዓለምአቀፍ (ወይም ቅይጥ) ተቋማዊ አደረጃጀት ሊመራ ይገባል፣
- ባህላዊ ተቋሞች (ለምሳሌ በአፋር ክልል እንዳለው ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት) የምህረት ሂደትን እንዲያከናውኑ ቢደረጉ ለማህበረሰቡ ልምድና ባህል ትልቅ ቦታ ይሰጣል፣
- ስራው አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት መሰራት ያለበት ሆኖ ኮሚሽኑ ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶችን ባካተተ/ባሳተፈ መልኩ ስራዎቹን እንዲያከናውን ቢደረግ በማህበረሰብ ደረጃ የተሻለ ተቀባይነት እንዲኖረው ያስችላል፣
- በባህላዊ ሥርዓት (ለምሳሌ በገዳ) ማዕቀፍ የሚሰጥ ምህረት በህዝብ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አለው፣ ለእርቅና ለዘላቂ ሰላምም መሠረት ነው፣ ስለሆነም ይህ ከባቢያዊ የአሰራር ሥርዓት ሀላፊነት ሊሰጠው ይገባል፣
- በርካታ ብሄሮችን ማዕከል ባደረጉ ግጭቶች ማዕቀፍ ለሚፈፀሙ በደሎች የምህረት ስራው በኮሚሽን ብቻ እንዲካሄድ ማድረግ በራሱ ችግር ያጭራል፣ ስለሆነም ከተጋጩት ብሄሮች ውስን አባላት የሚውጣጡበትን አሰራር ማሰብ ተገቢ ነው፣ እንዲሁ ከላይ በወረደ ሂደት በሌላ አካል የሚሰጥ ምህረት ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል፡፡

ሰንጠረዥ 49፡ 'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' - ሀገር-አቀፍ (የአራቱም ቡድኖች) ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | 4.5 | 2 | ኢሰመኮ (0.5)<br>ባህላዊ ተቋሞች (1) | |
| 2 | አፋር | 5 | 4 | | ባህላዊ ተቋሞች (1) | |
| 3 | አማራ | 32 | 25 | 5 | ምክክር ኮሚሽን (1) | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 7.5 | 0.5 | ምክክር ኮሚሽን (1) | |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 5 | | | |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 5 | | | |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 3 | | | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 55 | 7 | | |
| 9 | ሲዳማ | 4 | 3 | | ፍርድ ቤት (1) | |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 10 | 1 | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 28 | 7 | ምክክር ኮሚሽን (1)<br>ፍርድ ቤት (1)<br>ሽማግሌዎች (1) | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | 7 | 1 | | |
| 13 | ትግራይ | 24 | 13 | 1 | አለማቀፍ/ቅይጥ (9)<br>በተበዳዮች ብቻ (1) | |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 216 | 170 | 24.5 | 18.5 | 3 |

ሰንጠረዥ 50፡ 'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' - ሀገር-አቀፍ (የአራቱም ቡድኖች) ማጠቃለያ

| | | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 49 | 37.5 | 3 | 7.5 | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 2 | አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 47 | 41 | 3 | 3 | |
| 3 | አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ | 96 | 70.5 | 15.5 | 8 | 2 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 4 | አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ | 24 | 21 | 2 | 1 | |
| **አገራዊ የአራቱም የተኩረት ቡድኖች ማጠቃለያ** | | 216 | 170 | 23.5 | 19.5 | 3 |
| | | | | | | |




*'ምህረትን የመስጠት ሂደት ማን ያከናውነው?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ*

### 6.4.3.4.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

ሁሉም የሕጻናት ቡድን ተሳታፊዎች፣ አካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ተሳታፊዎች፣ የህጻናት መብት ተወካይ ተሳታፊዎች፣ አብዛኞቹ ከጾታዊ ጥቃት ያገገሙ ሴት ተሳታፊዎች፣ የተፈናቃይ ሴትና ተፈናቃይ ቅልቅል ቡድን ተሳታፊዎች፣ እና አብዛኞቹ የሴቶች ብቻ መድረክ ተሳታፊዎች - የስራ ሂደቱ አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ሊሰራ ይገባል ብለዋል።

በምክንያትነትም የምህረት አሰጣጡ ከቅቡልነት አንፃር ትክክለኛና የህዝብን አመኔታ ያለው እንዲሆን ለማስቻል፡ እንዲሁም ሌሎች ሀገሮች ለዚህ አላማ ራሱን የቻለ ተቋም የሚጠቀሙ በመሆኑ አዲስ ኮሚሽን መመስረት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የተሻለ አማራጭ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል። አሁን ያለው ተቋም አካል ጉዳተኞች የሚያካትት አለመሆኑም እንደ ክፍተት ተነስቷል።

በተጨማሪም አዲስ ኮሚሽን በሚቋቋምበት ጊዜ ተበዳይን ማእከል ያደረገ የምህረት ሂደት እንዲኖር ህፃናት እና በህፃናት ዙርያ የሚሠሩ ተቋማት (ወይም የፓርላማ አባላት) እና አካል ጉዳተኛ ሰዎችን በኮሚሽኑ ውስጥ ሊያካትት ይገባል በማለት ሀሳብ ሰጥተዋል።

በሌላ በኩል የተወሰኑ ተሳታፊዎች የስራ ሂደቱ ቀደም ሲል በተቋቋመው የምህረት ቦርድ አማካኝነት ሊከናወን ይገባል የሚል አቋም ይዘዋል። ምክንያቱም ለሁሉም ጉዳይ አዲስ ተቋም ማቋቋም አይገባም፡ በቦርዱ በኩል በልምድ የዳበረ ተቋማዊ አሰራር ያለ በመሆኑ ተገቢውን ማሻሻያ (ለምሳሌ የሴቶችና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ የሚስተናገድበትን አሰራር) በማከል እና ቦርዱን በማጠናከር መጠቀሙ ይሻላል የሚል ሀሳብ ተነስቷል።

### 6.4.3.5.ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

የምህረት መስጠቱን ሂደት አዲስ በሚቋቋም ተቋም አማካኝነት ቢከናወን ከዚህ ቀደም የታዩ ድክመቶች ለማረም ያስችላል። እምነትን ያጠናክራል። ነባር ተቋማትን መጠቀም ያለው ኢኮኖሚዊ ጥቅም ግልጽ ቢሆንም - እነዚህን ተቋማት እንጠቀም ከተባለ ነፃነታቸውን ማረጋገጥ፡ በተለይም የተቋማቱ ባለሙያዎች ያላቸው ብቃት፣ ቁርጠኝነት፣ እና ነፃነት መመስረት ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ አቅርበዋል። ይህ ደግሞ የሕግ ማሻሻያዎችን ማከናወን ይጠይቃል።

ለምሳሌ አሁን ስራ ላይ ያለው የይቅርታና ምህረት ማስፈጸሚያ ሕግ የሽግግር ሂደቱን ውጤታማነትና ተአማኒነት በሚያረጋግጥ መልኩ በመሰረታዊነት መሻሻል ይኖርበታል።

## 6.5. ማካካሻ

### 6.5.1. መግቢያ

በሽግግር ፍትህ ሂደት ማካካሻ - ለደረሱ የመብት ጥሰቶች ወይም የሐብት ውድመቶች ውጤታማና ተመጣጣኝ የገንዘብ ወይም የገንዘብ ያልሆነ ካሳ፡ መጠገኛ፡ ማደሻ ወይም ወደነበረበት ሁኔታ የመመለሻ መንገዶችን የያዘ ስልት ነው። የማካካሻ ፍትህ ዓላማ የተበዳዮችን ጉዳት መፈወስ እና የአጥፊዎችን ባህሪ ማስተካከል ነው።

ማካካሻን በተመለከተ ለሁሉም የትኩረት ቡድኖች ውይይት ሶስት ዋና ዋና ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው - 'የማካካሻ ሂደት በየትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል' የሚል ሲሆን፡ ሁለተኛው 'የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው/ሊተገበሩ ይገባል' የሚል ነው። ሶስተኛው እና የመጨረሻው ጥያቄ ደግሞ 'የማካካሻ ስርአቱን ማን ሊመራው ይገባል' የሚል ነው።

በትኩረት ቡድን ውይይቶቹ ላይ የተሳተፉ 216 ቡድኖች - በእያንዳንዱ መድረክ በአራት የትኩረት ቡድን ተከፍለው - በሶስቱም ጥያቄዎች ላይ ጥልቅ ውይይትና ክርክር አካሂደዋል። በማብራሪያ የተደገፉ መልሶቻቸውንና አቋሞቻቸውንም ገልፀዋል።

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ 'በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች'፡ 'ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' እና 'በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል።

### 6.5.2. የማካካሻ ሂደት በየትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል?

#### 6.5.2.1. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

**I. የሴት ተጎጂዎች ቡድን**

'የማካካሻ ሂደት በየትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ - በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።

- በመርህ ደረጃ ሁሉም ተጎጂዎች እንደየጉዳቱ አይነት እና መጠን ማካካሻ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡ 'ቤት የፈረሰበትም ልጅ የሞተበትም ካሳ ያስፈልገዋል፡ መቸም መንግስት ልጅ ወልዶ አይሰጥም'፡
- ሆኖም ቅድሚያ መሰጠት ካለበት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው፡ የአእምሮ ጉዳትን ጨምሮ ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው፡ የጤና እክል ያለባቸው፡ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ መጠለያ የሚገኙ፡ ንብረታቸው በህገወጥ መልኩ የተወረሰባቸው፡ ያለ ሕግ ለረጅም ጊዜ በእስር የቆዩ፡ የተደፈሩ፡ ቤተቦቻቸውን ያጡ፡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው ተጎጂዎች፡ እና ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች (ሴቶች፡ ህጻናት፡ በጦርነት ምክንያት ወላጅ ያጡ ህፃናት፡ አካል ጉዳተኞች፡ አረጋውያን) በማካካሻ ስርአቱ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል።

**II. የወንድ ተጎጂዎች ቡድን**

'የማካካሻ ሂደት በየትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ - በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ 47 የወንድ ተጎጂዎች ቡድኖች የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።

- *ሁሉም ተጎጂዎች በደረሰባቸው የጉዳት አይነት እና ደረጃ መሰረት ሊካሱ ይገባል፡*
- *ሆኖም ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የተፈፀመባቸው፣ የሞትና አካል መጉደል የደረሰባቸው፣ የስነ-ልቦና እና የአዕምሮ ቀውስ ያጋጠማቸው፣ ከመኖሪያ ቤታቸው እና ከሀብት ንብረታቸው የተፈናቀሉ፣ የንብረት ጉዳት የደረሰባቸው፣ ምግብ እና መጠለያ የሌላቸው፣ አቅመ-ደካማ የሆኑ፣ ቤተሰባቸውን ያጡ ህጻናት፣ ለህፃናት፣ ቤተሰብ በሞት ያጡ ሰዎች፣ የቤተሰብ አባል ደብዛ የጠፋባቸው፣ አስቸኳይ ህክምና የሚያስፈልጋቸው፣ የመደፈር ሰለባ የሆኑ፣ የማሰቃየት ሰለባ የሆኑ፣ የተደጋጋሚ የመብት ጥሰት ሰለባዎች፣ ያለ ህጋዊ ምክንያት ታስረው የቆዩ፣ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ በጦርነቱ ምክንያት በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ፣ ለወደሙ ህዝባዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት፣ እንደ ማህበረሰብ የተናቁ የተሰደቡ ባህላቸው የተተካባቸውና የተንቋሸሹ ሰዎች/ጉዳተኞች - የተለየ ትኩረት በማድረግ በቅድሚያ የማካካሻ ስርአቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል።*

***በተወያዮች የተነሱ ተያያዥ ምክረ-ሃሳቦች***

- *ማካካሻዎች ትርጉም እንዲኖራቸው በቅድሚያ የየአካባቢውን ሰላም ማስጠበቅ ያስፈልጋል፡ በጦርነት የተጎዱ መሰረት-ልማቶች የበጀት ድጎማን ጨምሮ የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡*
- *ማካካሻን የመዘርጋት ኃላፊነት የመንግስት ነው፣*
- *ማህበረሰቡ ለካሳ ለእርካታ እና ለፈውስ የሚጠቀምባቸው የዳበሩ ልምዶች በማካካሻ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ በማካተት መተግበር ያስፈልጋል።*

III. ***የቅልቅል ቡድን***

*'የማካካሻ ሂደት በየትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ - በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ* 96 *የቅልቅል ቡድኖች የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።*

- *ሁሉም ተጎጂዎች በደረሰባቸው የጉዳት አይነት እና ደረጃ መሰረት ሊካሱ ይገባል፡*
- *ሆኖም የተሰደዱ፣ ቤታቸው የፈረሰባቸው፣ ተፈናቃዮች፣ ህጻናቶች፣ እርጉዞች፣ የተደፈሩ ሴቶች፣ ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው፣ አካል ጉዳተኞች፣ ለተደራራቢ ጉዳት የተዳረጉ፣ ሴቶች፣ ህጻናት፣ ያለ አሳዳጊ የቀሩ ህፃናት፣ አረጋውያን፣ ንብረታቸውን ያጡ፣ ሆነ ተብሎ በተፈፀመ ድርጊት ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው (በተለይም ኢሰብአዊ ድብደባ፣ ግድያ፣ አስገድዶ መድፈር፣ መፈናቀል፣ ከባድ የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመት ያጋጠማቸው)፣ የወደሙ ተቋማት፣ ተደራራቢ የመብት ጥሰትና ጉዳት የደረሰባቸው፣ ከጉዳቱ ያላገገሙ፣ የአእምሮ ጉዳት የደረሰባቸው፣ ያለ ህጋዊ ምክንያት ታስረው የቆዩ፣ እና እንደ ማህበረሰብ የተናቁ የተሰደቡ ባህላቸው የተተካባቸው እና የተንቋሸሹ ጉዳተኞች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል፡*
- *በተጨማሪም ጾታዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ተጎጂዎች አንጻር ዛሬም ድረስ ከነጉዳታቸው የሚገኙና ለቀጠለ የማህበረሰብ ስድብና ማሸማቀቅ የተጋለጡ ተጎጂዎች በተለየ ሁኔታ ቅድሚያ በመስጠት አስፈላጊ የኢኮኖሚና የስነልቦና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡*
- *በሌላ በኩል ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ክሶ ሌሎች ተጎጂዎችን መተው በራሱ ለሌላ ግጭት መነሻ ሊሆን ይችላል፡ ስለሆነም ዘላቂ ሰላም እና አንድነትን ለማምጣት በሁሉም ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል፡*
- *መንግስት የውጭ ድጋፍ በማፈላለግ ጭምር ሁሉንም ተጎጂዎች መካስ ይኖርበታል፡*
- *ከአካሄድ አንፃር ጥልቅ ጥናት ተደርጎ በግለሰብና በድርጅቶች ላይ የደረሰው ውድመት በዝርዝር እንዲለይና በማካካሻ ስርዓቱ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲካተት ማድረግ ያስፈልጋል።*

IV. ***የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን***

‘የማካካሻ ሂደት በየትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ - በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል፡፡

የማካካሻ ስርአቱ ትኩረት የጉልህ ሰብአዊ መብት ጥሰት ቀጥተኛ ተጎጂዎች በሆኑ፣ ከባድ የመብት ጥሰት በተፈፀመባቸው፣ በማንነታቸው ምክንያት ጥቃት በደረሰባቸው፣ በተፈናቀሉ፣ ቤተሰብ በተገደለባቸው፣ (በግጭቱ) ወላጅ በሞት ባጡ፣ የአካልና የሥነ-ልቦና ጉዳት በደረሰባቸው፣ ግድያ ወይም ጾታዊ ጥቃት በተፈጸመባቸው፣ ልዩ እይታ በሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች (ህጻናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች)፣ እና ህልውናቸው አደጋ ላይ በወደቀባቸው ሰዎች ላይ ሆኖ እና ለነዚህ ቅድሚያ በመስጠት ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

### 6.5.2.2.የማካካሻ ሂደት የትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል? - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

‘የማካካሻ ሂደት በየትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገሪቱ ሁሉም ክልሎች በተደረገው ውይይት ላይ በሁሉም ቡድኖች የተንፀባረቁ ዋና ዋና አቋሞች እና ምክረ-ሀሳቦች እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

- በመርህ ደረጃ ሁሉም ተጎጂዎች እንደየጉዳቱ አይነትና መጠን ማካካሻ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡ ‘ቤት የፈረሰበትም ልጅ የሞተበትም ካሳ ያስፈልገዋል፡ መቸም መንግስት ልጅ ወልዶ አይሰጥም’፡
- ቅድሚያ መሰጠት ካለበት የሚከተሉት ዝርዝሮች በመጀመሪያው ረድፍ ላይ የሚታሰቡ መሆን አለባቸው፦ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው፣ የስነ-ልቦና እና የአዕምሮ ቀውስ ያጋጠማቸው፣ ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው፣ የጤና እክል ያለባቸው፣
- ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ መጠለያ የሚገኙ፣ የንብረት ጉዳት የደረሰባቸው፣ ንብረታቻው በህገወጥ መልኩ የተወረሰባቸው፣ ምግብ እና መጠለያ የሌላቸው፣
- ሆነ ተብሎ በተፈፀመ ድርጊት ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው (በተለይም ኢሰብአዊ ድብደባ፣ ግድያ፣ አስገድዶ መድፈር፣ መፈናቀል፣ ከባድ የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመት ያጋጠማቸው)፣ ተደራራቢ የመብት ጥሰትና ጉዳት የደረሰባቸው፣
- የመደፈር ሰለባ የሆኑ፣ ጾታዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ተጎጂዎች አንጻር ዛሬም ድረስ ከነጉዳታቸው የሚገኙና ለቀጠለ የማህበረሰብ ስድብና ማሸማቀቅ የተጋለጡ ተጎጂዎች፣ አስቸኳይ ህክምና የሚያስፈልጋቸው፣
- ያለ ሕግ ለረጅም ጊዜ በእስር የቆዩ፣ የማሰቃየት ሰለባ የሆኑ፣ ከጉዳቱ ያላገገሙ፣ ቤተቦቻቸውን ያጡ፣ አቅመ-ደካማ የሆኑ፣ ቤተሰባቸውን ያጡ ህጻናት፣ የቤተሰብ አባል ደብዛ የጠፋባቸው፣
- ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች (ሴቶች፣ ህጻናት፣ በጦርነት ወላጅ ያጡ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን)፣
- በማንነታቸው ምክንያት ጥቃት የደረሰባቸው፣ እንደማህበረሰብ የተናቁ የተሰደቡ ባህላቸው በግድ የተተካባቸውና የተንቋሸሹ ሰዎች/ጉዳተኞች፣
- የወደሙ ህዝባዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት፣
- ማካካሻዎች ትርጉም እንዲኖራቸው በቅድሚያ የየአካባቢውን ሰላም ማስጠበቅ ያስፈልጋል፡ በጦርነት የተጎዱ መሰረተ-ልማቶች የበጀት ድጎማን ጨምሮ የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡
- ማካካሻን የመዘርጋት ኃላፊነት የመንግስት ነው፣ መንግስት የውጭ ድጋፍ በማፈላለግ ጭምር ሁሉንም ተጎጂዎች መካስ ይኖርበታል፡
- ማህበረሰቡ ለካሳ፡ ለእርካታ እና ለፈውስ የሚጠቀምባቸው የዳበሩ ልምዶች በማካካሻ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ በማካተት መተግበር ያስፈልጋል፡

- በሌላ በኩል ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ክሶ ሌሎች ተጎጂዎችን መተው በራሱ ለሌላ ግጭት መነሻ ሊሆን ይችላል፡ ስለሆነም ዘላቂ ሰላምና አንድነትን ለማምጣት በሁሉም ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል፡
- ከአካሄድ አንፃር ጥልቅ ጥናት ተደርጎ በግለሰብና በድርጅቶች ላይ የደረሰው ውድመት በዝርዝር እንዲለይና በማካካሻ ስርዓቱ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲካተት ማድረግ ያስፈልጋል።

### 6.5.2.3.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

'የማካካሻ ስርአቱ በየትኛዎቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል' የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ በአብዛኞቹ የምክክር መድረኮች ላይ የተንፀባረቀው ተመሳሳይ ሃሳብ ትኩረቱ የበለጠ ተጋላጭነት ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እና ተፈናቃዮች ላይ መሆን አለበት የሚል ነው።

በተሳታፊዎች የቀረቡ ዝርዝሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፦ ሴቶች፡ ህፃናት፡ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን፣ ከባድ የአካል ጉዳት፡ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት እና አስገድዶ መድፈር የተፈፀመባቸው ተጎጂዎች፣ ቤተሰባቸውን በሞት ያጡ ተጎጂዎች፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት፣ ከቤተሰብ ጋር ሆነ ከቤተሰብ ውጭ የተፈናቀሉ ህፃናት፣ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተጎጂዎች፣ ከባድ የንብረት ጉዳት የደረሰባቸው ተጎጂዎች፣ እና በሙብት ጥሰት ምክንያት የአካል ጉዳት እና የስነ-አእምሮ ችግር የደረሰባቸው ሰዎች።

በተጨማሪ የጉዳቱ መጠን/አይነት ይለያይ እንጂ ሁሉም ተጎጂዎች በመርህ ደረጃ እንደየጉዳቱ መጠን ሊካሱ ይገባል የሚል ሃሳብም ከተሳታፊዎች ተነስቷል።

### 6.5.2.4.ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

ማካካሻን አስመልክቶ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ምክረ-ሃሳቦች በዋናነት የካሳ ሂደቱ ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚፈልግ ተግባር መሆኑን አጽንኦት የሰጡ ሲሆን፡ የካሳ ጉዳይ አመታትን ሊወስድ የሚችል የስራ ሂደት በመሆኑ የማካካሻ ፕሮግራሞች ተጎጂዎችን በጾታ፣ በእድሜ፣ በኢኮኖሚያዊ አቅም፣ እና በደረሰ የጉዳት አይነትና መጠን መሰረት እንዲቀረፁ ማድረግ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

በተጨማሪም አስቸኳይ የተጎጂዎች ድጋፍ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ - በተለይም ከባድ የአካል ጉዳት እና አስገድዶ መድፈር ወንጀል ለተፈፀመባቸው ሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ወላጆቻቸውን ላጡ/ለተፈናቀሉ ህፃናት እና ለአረጋውያን የአእምሮ፡ የማህበራዊ ድጋፍ እና የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን መተግበር በሚያስችል መልኩ መከናወን እንደሚኖርበት አመልክተዋል።

## 6.5.3. በማካካሻ ስርዓት የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው/ሊተገበሩ ይገባል?

### 6.5.3.1.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

#### I. የሴት ተጎጂዎች ቡድን

'በማካካሻ ስርዓት የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው/ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።

- የማካካሻው አይነት እንደ ጉዳቱ አይነት የተለያየ ሊሆን ይገባል፡
- የስነ-ልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የምክር አገልግሎትና የማገገሚያ ስርአቶችን መዘርጋት ያስፈልጋል፡
- ለተፈናቀሉ እና ንብረታቸውን ላጡ ሰዎች የመልሶ ማቋቋም፡ የህክምና፡ የሥነ-ልቦና አገልግሎት፡ የምግብ እና መጠለያ ድጋፍ፡ እንዲሁም ጉዳቱ ዳግም እንደማይፈፀም ዋስትና መስጠት ይገባል፡ እነዚህ ድጋፎች የአካባቢን ሰላምና ደህንነት በዘላቂነት የሚያስጠብቅ አሰራር በማቀም፡ የወደሙ የማህበራዊ አገልግሎት

*መስጫዎችን መልሶ በመገንባት፣ ጅምላ ግድያ በተፈፀመባቸው ቦታዎች ላይ ሃውልት/ማስታወሻ ወይም ሙዝየም በማቆም ሊተገበሩ ይችላሉ፣*

- *ከተፈናቃዮች ጋር በተያያዘ የመልሶ ማቋቋም ስራ የሚሰራው በቅድሚያ የተፈናቀሉበትን አካባቢ ሰላም ለማስጠበቅ የሚያስችል አሰራር በማቆም ብቻ መሆን አለበት፣*
- *ካሳን በተመለከተ የሚሰጠው መጠን እንደደረሰው የጥሰት መጠን የሚለያይ ሆኖ የካሳው ዘዴ እንደ አሰፈላጊነቱ የግል፣ የጋራ እና መልሶ ማቋቋምን ሊያካትት ይገባል፣*
- *የማካካሻ ሂደቱ በሕግ፣ በሃይማኖት እና በባህል ስርአቶች ሊመራ የሚችልበት እድል ኖሮ በተለይ በባህላዊ አሰራር ለሚከናወን ማካካሻ ስራ ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል።*

## II. ***የወንድ ተጎጂዎች ቡድን***

*'በማካካሻ ስርዓት የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው/ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ* 47 *የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።*

- *ጉዳት የደረሰው በግል እና በቡድን ጥሰት በተፈፀመባቸው ሰዎች ላይ ስለሆነ እና የጉዳቱ ዓይነትም ስለሚለያይ የማካካሻ ስርአቱ በቡድን ለተጎዱ ሕዝባዊ ይቅርታ በመጠየቅ፣ በግል ለተጎዱ ደግሞ እንደሁኔታው የተፈናቀሉትን መልሶ በማቋቋም፣ ቁሳዊ እና የሞራል ጉዳት ካሳ በመስጠት፣ የስነ-ልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው ደግሞ የህክምና እና ማገገሚያ አገልግሎቶችን በማቅረብ ቅድሚያ ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፣*
- *በተጨማሪም የማካካሻ ሥርዓት አካታች መሆን አለበት፣ አንድን የማካካሻ አይነት ብቻ ነጥሎ ማየት ተገቢ አይሆንም፣ በተለይም መልሶ ማቋቋምን የሚመለከት የማካካሻ ስራ አካላዊ እና አዕምሯዊ ስብራቶችን በሚያክም እና ወደ ነበሩበት የማህበራዊ ህይወት በሚመልስ መልኩ ተቀናጅቶ ሊተገበር ይገባል።*

## III. ***የቅልቅል ቡድን***

*'በማካካሻ ስርዓት የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው/ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ* 96 *የቅልቅል ቡድኖች የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።*

- *ለሁሉም ጥሰት እንደየጉዳቱ መጠን ማካካሻ ሊሰጥ ይገባል፣*
- *የማካካሻው አይነት ለጥሰት/ጉዳት እውቅና መስጠት፣ መልሶ ማቋቋም፣ የማገገሚያ አገልግሎት ማቅረብ፣ ቁሳዊ ወይም የገንዘብ ካሳ መስጠት፣ የወደመ ሐብት መልሶ መገንባት፣ እንዲሁም የስራ እድል እና ጡረታ መብት ማመቻቸትን ሊያጠቃልል ይገባል፣*
- *ለእያንዳንዱ ጥሰት በግለሰብ ደረጃ መርዳት አስቸጋሪ ስለሚሆን የማካካሻ ስርአቱ በዋናነት በማህበረሰብ ደረጃ ሊተገበር ይገባል፣ ሆኖም ሁሉም የተለያየ ጉዳት የደረሰበት እንደመሆኑ መጠን እንደየጉዳቱ አይነትና መጠን በግለሰብ ደረጃ ማካካሻ ለመስጠት ጥረት ሊደረግ ይገባል፣*
- *ተፈናቃዮችን በተመለከተ በቅድሚያ ሰላማዊ ኑሮ መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፣ ቀጥሎም የተፈናቀሉ ዜጎችን ማቋቋምና ወደ ነበሩበት ህይወት መመለስ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፣ ወደ ተፈናቀሉበት ቦታ መመለስ የማይቻል ከሆነ ከጊዜያዊ መጠልያ ወጥተው በዘላቂነት የሚኖሩበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፣*
- *ስነልቦናዊ ጉዳት የሚጠገንበት ሁኔታ በደንብ አፅንኦት ሊሰጠው ይገባል፣ በደንብ ሳይታከም ቀርቶ ነገ በበቀል ስሜት/ስነ-ልቦና የሚመለስ ትውልድ እንዳይመጣ ድጋፉ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።*

## IV. ***የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች***

'በማካካሻ ስርዓት የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው/ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።

- የሚሰጠው ማካካሻ አይነት ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም፣ አይገባምም፣ እንደደረሰው ጉዳት ይለያያል፣
- ለማካካሻዎች ቅደም ተከተል ከመስጠት ይልቅ እንደ ሁኔታው እየታየ ሁሉም የማካካሻ ስርአቶች ሊተገበሩ ይገባል፣
- በቅድሚያ አስተማማኝ ሰላም ማስፈንና ለመኖር አስፈጊ የሆኑ መሰረት-ልማቶችን (ለምሳሌ ጤና፣ ውሃ) መልሶ መገንባት ያስፈልጋል፣ የጋራ ተጠቃሚነትን ያገናዘበ ካሳ፣ መልሶ ማቋቋም እና የስነ ልቦና ድጋፍ ማድረግ ይገባል፣ የማቋቋሚያ ስልጠና ማመቻቸትም አንዱ የማካካሻ አይነት መሆን አለበት፣
- በግለሰብ ደረጃ ለሁሉም የገንዘብ ካሳ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ አይቀርም፣ ስለሆነም ይህ አማራጭ እንዳለ ሆኖ ሰዎች በጋራ የሚገለገሉባቸው ተቋማትን መገንባት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

## 6.5.3.2. 'በማካካሻ ስርዓት ምን አይነት የማካካሻ አይነቶች ሊተገበሩ ይችላሉ?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

'በማካካሻ ስርዓት የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው/ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ ሁሉም ቡድኖች ባደረጉት ውይይት ላይ የተንፀባረቁ ዋና ዋና አቋሞች እና ምክረ-ሀሳቦች እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።

- የማካካሻው አይነት እንደየጉዳቱ አይነት የተለያየ ሊሆን ይገባል፣ ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም፣ አይገባምም፣
- የማካካሻው አይነት ለጥሰት/ጉዳት እውቅና መስጠትን፣ መልሶ ማቋቋም፣ የማገገሚያ አገልግሎት ማቅረብ፣ ቁሳዊ ወይም የገንዘብ ካሳ መስጠት፣ የወደመ ሐብት መልሶ መገንባት፣ እንዲሁም የስራ እድል እና የጡረታ መብት ማመቻቸትን ሊያጠቃልል ይገባል፣
- የስነ-ልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የምክር አገልግሎትና የማገገሚያ ስርአቶችን መዘርጋት ያስፈልጋል፣
- ለተፈናቀሉ እና ንብረታቸውን ላጡ ሰዎች በቅድሚያ ሰላማዊ ኑሮ መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር፣ ቀጥሎም የመልሶ ማቋቋምና ወደ ነበሩበት ህይወት መመለስ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፣ የህክምና፣ የሥነ-ልቦና አገልግሎት፣ የምግብ እና መጠለያ ድጋፍ፣ እንዲሁም ጉዳቱ ዳግም እንደማይፈፀም ዋስትና መስጠት ይገባል፣ ወደተፈናቀሉበት ቦታ መመለስ የማይቻል ከሆነ ከጊዜያዊ መጠልያ ወጥተው በዘላቂነት የሚኖሩበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፣
- እነዚህ ድጋፎች የአካባቢን ሰላምና ደህንነት በዘላቂነት የሚያስጠብቅ አሰራር በማቅም፣ የወደሙ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫዎችን መልሶ በመገንባት፣ ጅምላ ግድያ በተፈፀመባቸው ቦታዎች ላይ ሃውልት/ማስታወሻ ወይም ሙዝየም በማቆም ሊተገበሩ ይችላሉ፣
- ጉዳት የደረሰው በግል እና በቡድን ጥሰት በተፈፀመባቸው ሰዎች ላይ ስለሆነ እና የጉዳቱ ዓይነትም ስለሚለያይ የማካካሻ ስርአቱ በቡድን ለተጎዱ ሕዝባዊ ይቅርታ በመጠየቅ፣ በግል ለተጎዱ ደግሞ እንደ ሁኔታው ከላይ የተመለከቱትን አገልግሎቶችን በማቅረብ ቅድሚያ ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፣
- ለመኖር አስፈጊ የሆኑ መሰረት-ልማቶችን (ለምሳሌ ጤና፣ ውሃ) መልሶ መገንባት ያስፈልጋል፣ የጋራ ተጠቃሚነትን ያገናዘበ ካሳ፣ መልሶ ማቋቋም እና የስነ ልቦና ድጋፍ ማድረግ ይገባል፣ የማቋቋሚያ ስልጠና ማመቻቸትም አንዱ የማካካሻ አይነት መሆን አለበት፣
- የሚሰጠው የካሳ መጠን እንደደረሰው የጥሰት መጠን የሚለያይ ሆኖ የካሳው ዘዴ እንደ አስፈላጊነቱ የግል፣ የጋራ እና መልሶ ማቋቋምን ሊያካትት ይገባል፣
- ለእያንዳንዱ ጥሰት በግለሰብ ደረጃ መርዳት አስቸጋሪ ስለሚሆን የማካካሻ ስርአቱ በዋናነት በማህበረሰብ ደረጃ ሊተገበር ይገባል፣ ሰዎች በጋራ የሚገለገሉባቸው ተቋማትን መገንባት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፣

ሆኖም ሁሉም የተለያየ ጉዳት የደረሰበት እንደመሆኑ መጠን እንደየጉዳቱ አይነትና መጠን በግለሰብ ደረጃ ማካካሻ ለመስጠት ጥረት ሊደረግ ይገባል፡

- የማካካሻ ሂደቱ በሕግ፡ በሃይማኖት እና በባህል ስርአቶች ሊመራ የሚችልበት እድል ኖሮ በተለይ በባህላዊ አሰራር ለሚከናወን ማካካሻ ስራ ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል፡
- በተጨማሪም የማካካሻ ሥርዓት አካታች መሆን አለበት፡ አንድን የማካካሻ አይነት ብቻ ነጥሎ ማየት ተገቢ አይሆንም፡ በተለይም መልሶ ማቋቋምን የሚመለከት የማካካሻ ስራ አካላዊ እና አዕምሯዊ ስብራቶችን በሚያክም እና ወደ ነበሩበት የማህበራዊ ህይወት በሚመልስ መልኩ ተቀናጅቶ ሊተገበር ይገባል።
- ስነልቦናዊ ጉዳት የሚጠገንበት ሁኔታ በደንብ አፅንኦት ሊሰጠው ይገባል፡ በደንብ ሳይታከም ቀርቶ ነገ በበቀል ስሜት/ስነ-ልቦና የሚመለስ ትውልድ እንዳይመጣ ድጋፉ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።
- ለማካካሻዎች ቅደም ተከተል ከመስጠት ይልቅ እንደ ሁኔታው እየታየ ሁሉም የማካካሻ ስርአቶች ሊተገበሩ ይገባል።

### 6.5.3.3.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

'በማካካሻ ስርዓት የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው/ሊተገበሩ ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች እንደየጉዳቱ አይነት ሁሉንም አይነት ማካካሻ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን የጠቀሱ ሲሆን፡ የማካካሻ አይነቱን በተመለከተ በተበዳዮቹ ሁኔታና ፍላጎት ጭምር ሊወሰን ይገባል ብለዋል።

የትኛው የማካካሻ  ዓይነት ሊተገበር ይገባል ለሚለው ጥያቄ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰጥተዋል።

- ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ኢንቨስትመንቶችን ማበረታታትና ድጋፍ የሚያገኙበትን ስርዓት መዘርጋት፣
- ለተጎጂ አካባቢዎች ልዩ የብድር ስርዓት ማዘጋጀት እና የረዥም ጊዜ የበጀት ድጋፍ የሚሰጥበትን መንገድ ማዘጋጀት፣
- በመንግስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በኩል ለተጎጂዎች የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ፣
- ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የህክምና፡ የመጠለያ፡ የመልሶ ማቋቋም እና የማገገሚያ ስራዎች ማከናወን፣
- ለተጎጂዎች ማህበራዊ፡ ስነልቦናዊ እና የህክምና ድጋፎችን ማቅረብ፣
- ንብረት የጠፋባቸው እና የተፈናቀሉ ሰዎችን ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ/መልሶ ማቋቋም፣
- የመልሶ ማቋቋም፡ ማገገሚያና በማህበረሰብ ደረጃ የሚከናወኑ የማካካሻ ስልቶችን የወንድና የሴት ተጎጂዎችን ልዩ ፍላጎት በሚመልሱ አግባብ መተግበር።

## 6.5.4. የማካካሻ ሥርዓትን ማን ሊመራው ይገባል?

### 6.5.4.1.መግቢያ

በተቋማዊ ጉዳዮች ማዕቀፍ 'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል' የሚለው ርእሰ-ጉዳይን በተመለከተ ለተወያዮች አራት መነሻ ተቋማዊ አማራጮች ቀርበዋል።

የመጀመሪያው አማራጭ - 'የግል ካሳ ጉዳይ በመደበኛው የሕግ ሥርዓት በፍርድ ቤቶች እንዲታይ መተው' የሚል ሲሆን፡ ሁለተኛው አማራጭ ስራውን 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን' አማካኝነት ማከናወን የሚያስችል ነው። ሶስተኛው አማራጭ ሀላፊነቱን 'ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን' የሚሰጥ ሲሆን፡ አራተኛው አማራጭ ይህን ሂደት 'በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን' አማካኝነት ማካሄድን የሚያስብ ነው። ከዚህ ውጭ የሚታይ የተሻለ አማራጭ ቢኖር ተሳታፊዎች ማቅረብ የሚችሉ መሆኑ ተገልያላቸዋል።

### 6.5.4.2.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

## I. የሴት ተጎጂዎች ቡድን

### ሀ. በአብዛኛው የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 37 ቡድኖች (ወይም 75.5%) የሆኑት - የስራ ሂደቱ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን' አማካኝነት ሊከናወን ይገባል የሚል አቋም ይዘዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- አሁን ያሉት ፍርድ ቤቶች እና ኮሚሽኖች ከፍተኛ የሥራ ጫና አለባቸው፥
- ስራ ላይ ያሉት ተቋማት ገለልተኛ እና ውጤታማ አይደሉም፡ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አልተወጡም፡ የህዝብ አመኔታ የላቸውም፡
- አዲስ ተቋም መመስረት በአጭር ጊዜ በትኩረት ወደ ስራ ለመግባትና ስራውን ለማጠናቀቅ ያስችላል፡
- የሙብት ጥሰቶቹና የደረሱት ጉዳቶች ከተራ ወንጀሎችና የካሳ ዓይነቶች ስለሚለዩ የማካካሻ ሥርዓቱን አዲስ፥ ራሱን የቻለ፥ ነፃና ገለልተኛ በሆነ ተቋም እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡
- አዲስ ኮሚሽን ሲቋቋም የሀገር ሽማግሌዎችን ባካተተ ሁኔታ ሊቋቋምና ሊዋቀር ይገባል።

### ለ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'የማካካሻ ስራው በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 3.5 ቡድኖች (ወይም 7.14%) የሚሆኑት ይህ የስራ ሂደት በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ሊሰራ ይገባል የሚል ሀሳብ አንፀባርቀዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ኮሚሽኑ ጉዳዮችን እንደየጉዳት መጠናቸው በገለልተኝነት በመመርመር ማካካሻ ለመስጠት አመኔታ የሚጣልበት ተቋም ነው፥
- ኮሚሽኑ በጉዳዩ ላይ ልምድ አለው፥ በምርመራና በማጣራት ዘርፍ የካበተ ተሞክሮ እና እውቀት ስላለው ጉዳዮችን በአግባቡ በመረዳት ስራውን በውጤታማነት ማከናወን ይችላል።

### ሐ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'የማካካሻ ስራው በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች ውስጥ 1.5 ቡድኖች (ወይም 3.08%) የሆኑት - ስራውን የመምራት ሀላፊነት ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እንዲሰጥ ሀሳብ አቅርበዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች ዘርዝረዋል።

- ኮሚሽኑ አሁን ላለንበት ውስብሰብ ችግሮች መፍትሄ ለማምጣት የተቋቋመ ነው፥
- ከዚህ አንፃር ኮሚሽኑ የማካካሻ ጉዳዮችን በማጣራት እልባት ሳይሰጥ ወደ ሌሎች የምክክር ሥርዓቱ ስራዎች ሊያመራ አይገባም።

### መ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ 'ሌላ/አዲስ አማራጭ'

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 3 ቡድኖች (ወይም 6%) የሚሆኑት - ሀላፊነቱ ለሀገር ሽማግሌዎች እንዲሰጥ አዲስ አማራጭ አቅርበዋል። ይህ አማራጭ የካሳ ስራን በፍትሃዊነት ለማካሄድ እና ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ያስችላል የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል።

ሁለት የሴት ተጎጂ ቡድኖች (ወይም 4.08%) የሚሆኑት የማካካሻ ስርአቱ ገለልተኛ እና አለማቀፋዊ (ወይም ቅይጥ) በሆነ ተቋም እንዲመራ ሀሳብ አቅርበዋል።

አንድ የሴት ተጎጂ ቡድን (ወይም 2.04%) ደግሞ የማካካሻ ስርአቱ በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን እና ከትግራይ ክልል በተውጣጡ ባለሙያዎች ቅንጅት ሊመራ ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቋል። እንዲሁም አንድ ቡድን የማካካሻ ስርአቱ በሼሪዐ ፍርድ ቤት ሊመራ እንደሚገባ አማራጭ አቅርበዋል።

ሰንጠረዥ 51፡ 'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል?' የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | የግል ካሳን በፍርድ ቤቶች እንዲታይ ማድረግ | አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን | በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን | በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን | ሌላ/አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | | 1 | 1 | | |
| 2 | አፋር | 1 | | | 1 | | |
| 3 | አማራ | 7 | | 6.5 | 0.5 | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | | 2 | | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | | 1 | | | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | | 0.5 | | 0.5 | |
| 7 | ሀረሪ | 1 | | 1 | | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | | 11 | 1 | 1 | ባህላዊ ተቋሞች (1) |
| 9 | ሲዳማ | 1 | | 1 | | | |
| 10 | ሶማሌ | 3 | | 2 | | | ሼሪያ ፍርድ ቤት (1) |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | | 7 | | | የሀገር ሽማግሌዎች (2) |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | | 2 | | | |
| 13 | ትግራይ | 5 | | 2 | | | አለማቀፍ/ቅይጥ (2) የባለሙያዎች ቡድን ከትግራይ ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት (1) |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 49 | | 37 | 3.5 | 1.5 | 7 |

### II. የወንድ ተጎጂዎች ቡድን

### ሀ. በአብዛኛው የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 36 ቡድኖች (ወይም 76.59%) የሚሆኑት - ይህ ሀላፊነት አዲስ የሚቋቋም ኮሚሽን ስራ እንዲሆን ሀሳብ አቅርበዋል። ሀሳባቸውን ለመደገፍ የሚከተሉትን ምክንያቶች ሰጥተዋል።

- አሁን ያሉት ተቋማት የሥራ ጫና አለባቸው፡
- ያሉት ተቋማት ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ነፃ አይደሉም፡ የህዝብ አመኔታ የላቸውም፡
- ጉዳዩን በፍርድ ቤት ለማስኬድ መሞከር ተበዳይን ማዕከል ያደረገ አሰራር አይሆንም፡ ወጪም ይጠይቃል፡
- የማካካሻ ሂደቱ ፍትሀዊና ተአማኒነት እንዲኖረው ነፃና ገለልተኛ በሆነ አዲስ ተቋም ሊተገበር ይገባል፡
- ከከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ከእርስ በእርስ ጦርነት በኋላ በሚተገበር የሽግግር ፍትህ ሂደት ማዕቀፍ የሚነሱ የማካካሻ ጥያቄዎች በመደበኛው ጊዜ በግል ተበዳዮች ከሚነሱ ጥያቄዎች የተለየ ባህሪና ክብደት አላቸው፡ ስለሆነም እነዚህን ጉዳዮች በመደበኛው የማካካሻ አሰራር ለመፍታት መሞከር ዓላማው እንዳይሳካ ያደርገዋል።

**ለ. በተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'የማካካሻ ስራው በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'**

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 6 ቡድኖች (ወይም 12.76%) የሚሆኑት ስራው በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ቢሰራ ይመረጣል ሲሉ ሀሳባቸውን ገልፀዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ኮሚሽኑ አሁን የሚሰራው ስራ ውጤታማ ነው፡ ከመብት ጉዳዮች ጋር በተገናኘ የዳበረ ልምድ አለው፡
- ኮሚሽኑ ጥሰቶች ሲፈፀሙ ሪፖርት የሚያወጣና መረጃዎችም ያሉት በመሆኑ ጉዳቶችን በቅርበት ለማወቅ እና ለመከታተል እድል ይሰጠዋል፡

**ሐ. በተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'የማካካሻ ስራው በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'**

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል አንድ የወንድ ቡድን (ወይም 2%) ስራው በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት እንዲሰራ ሀሳብ ሰጥተዋል። ምክንያቶቻቸውም የሚከተሉት ናቸው።

- ተጎጂዎች በመደበኛው ፍርድ ቤት ሥርዓት ማካካሻ ለመጠየቅ አቅም/ችሎታ አይኖራቸውም፡
- ኮሚሽኑ በምክክር ሂደቱ ብዙ ግንዛቤዎችን ይይዛል፡ ከዚህ ሁነት በመነሳት የማካካሻ ስርአቱን በተገቢ ደረጃ ለማከናወን የተሻለ እድል አለው።

**መ. በተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'የማካካሻ ስራው በአዲስ አማራጭ ማከናወን'**

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 2.5 ቡድን (5.3%) ስራው በገለልተኛ አለም አቀፍ ተቋም ወይም በቅይጥ ተቋም ሊመራ ይገባል ብለዋል። በአንጻሩ አንድ ቡድን (2.13%) የማካካሻ ስርአቱ በባህላዊ ተቋም ሊመራ ይገባል ብለዋል።

*ሰንጠረዥ 52፡ 'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል?' የወንድ ተጎጂዎች ቡድኖች ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ*

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | የግል ካሳ በፍርድ ቤቶች እንዲታይ ማድረግ | አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን | በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን | በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን | ሌላ/አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | | | | |
| 2 | አፋር | 1 | | | 1 | | |
| 3 | አማራ | 7 | | 3.5 | 2.5 | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | | 2 | | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | | 1 | | | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | | 0.5 | 0.5 | | |
| 7 | ሀረሪ | 1 | | 1 | | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | | 10 | 2 | 1 | ባህላዊ ተቋም (1) |
| 9 | ሲዳማ | 1 | | 1 | | | |
| 10 | ሶማሌ | 3 | | 3 | | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | | 8 | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | | 2 | | | |
| 13 | ትግራይ | 5 | | 2.5 | | | አለማቀፍ/ ቅይጥ (2.5) |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 47 | | 34.5 | 6 | 1 | 3.5 |

## III. የቅልቅል ቡድን

### ሀ. በአብዛኛው የቅልቅል ቡድን የተደገፈ አማራጭ፣ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች መካከል 71 ቡድኖች (ወይም 73.95%) የሆኑት አዲስ የሚቋቋም ኮሚሽንን መርጠዋል። ሀሳባቸውን ለመደገፍም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ከተአማኒነት፣ ተቀባይነት፣ ገለልተኛነት እና ውጤታማነት አንፃር አዲስ የሚቋቋም ተቋም ተመራጭ ነው፣
- አዲሱ ተቋም ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስራዎችን ስለሚያከናውን እና የሁሉንም ሀሳብና ፍላጎት ማዕከል ስለሚያደርግ፣ ፍትህ እና እውነትን በተሟላ መልክ ማስመለስም ስለሚያስፈልግ ሀላፊነቱ ለአዲስ ኮሚሽን ሊሰጥ ይገባል፣
- ያሉት ተቋማት ከፍተኛ የሥራ ጫና አለባቸው፣
- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እስካሁን እየሄደበት ባለው ስራ ትንሽ የሚታትር ቢሆንም ተሰሚነቱ በሚፈለገው ልክ አልመጣም፣ የሚያወጣው ሪፖርትም አልፎ አልፎ ገለልተኝነት ይጎድለዋል፣ በአጠቃላይም ኮሚሽኑ ተጽእኖ ፈጣሪ ተቋም አይደለም፣ የማካካሻ ስራ ለመስራት ብቁ አይሆንም፣
- ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሀላፊነት ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ ስራውን በአግባቡ አላከናወነም፣ በህዝብ ዘንድ ያለው ተቀባይነት እምብዛም አይደለም፣ ሲመረጥም ከፖለቲካ ፓርቲዎች ብዙ ተቃውሞ ገጥሞታል፣ ስለሆነም አብዛኛውን የፖለቲካ ማህበረሰብ በሚያረካ መልኩ ሊሰራ አይችልም፣
- የግል ካሳ ጉዳይን በመደበኛ የሕግ ሥርአት በፍርድ ቤቶች እንዲታይ ማድረግ በገንዘብ የማይተመኑ ጉዳዮች እንዳይታዩ የማድረግ ውጤት ይኖረዋል፣
- አዲስ የሚቋቋመው ኮሚሽን ሲደራጅ በባለሙያ ብቻ ሳይሆን ከባህላዊ ስርዓቶች፣ የሀይማኖት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች የተለያዩ አዋቂዎችን፣ እንዲሁም የስነ-ልቦና እና የሌሎች ሙያዎች ባለቤቶችን አሳትፎ የሚሰራ መሆን አለበት።

### ለ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'የማካካሻ ስራው በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች መካከል 9 ቡድኖች (ወይም 9.37%) የሆኑት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንን መርጠዋል። ለዚህ አቋማቸውም የሚከተሉትን ደጋፊ ምክንያቶች ሰጥተዋል።

- ኮሚሽኑ ሲጀመርም የተቋቋመው የዜጎችን መብት ለማስከበር ስለሆነ ይህን ስራ ደርቦ መስራት ይችላል፣
- በአሁን ጊዜ ኮሚሽኑ የተሻለ አፈጻጸም እያሳየ ያለ በመሆኑና ከሃላፊነቱ ጋር የተያያዘ የዳበረ ልምድ እና ተደራሽነት ስላለው የማካካሻ ስራን በነፃነት፣ በፍትሃዊነት እና በውጤታማነት ሊመራ ይችላል፣

### ሐ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'የማካካሻ ስራው በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች መካከል 7 ቡድኖች (ወይም 7.2%) የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንን ደግፈው ተከራክረዋል። ለዚህ አቋማቸውም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ኮሚሽኑ ከሌሎች ተቋማት የተሻለ ተቀባይነት አለው፣ አካታች ነው፣
- ኮሚሽኑ አዲስ፣ ነፃ እና የማህበረሰቡን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ የመረዳት አቅም ያለው ተቋም ነው፣
- ኮሚሽኑ አሁን የሚሠራው ሥራ ከማካካሻ ተግባር ጋር ተቀራራቢ ይዘት አለው፣ ስለሆነም ሀላፊነቱ ቢሰጠው የሰው ሀይል እና የገንዘብ ሀብትን በውጤታማነት ለመጠቀም ያስችላል።

### መ. አዲስ/ሌሎች አማራጮች

በሌላ በኩል 'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች መካከል 2 ቡድኖች (2.08%) ሀላፊነቱ ለመደበኛው የፍርድ ቤት ስርዓት ሊተው ይገባል ያሉ ሲሆን፣ 3 ቡድኖች (ወይም 3.12%) ደግሞ ትግበራው ባህላዊ የፍትህ ተቋማትን መሰረት አድርጎ ሊሳለጥ ይገባል ብለዋል። ሌሎች 2 ቡድኖች (ወይም 2.08%) ደግሞ ስራው በገለልተኛ ዓለም-አቀፍ (ወይም ቅይጥ) ተቋም ሊመራ ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል።

ሰንጠረዥ 53፡ 'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል?' የቅልቅል ቡድኖች ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | የግል ካሳን በፍርድ ቤቶች እንዲታይ ማድረግ | አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን | በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን | በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን | ሌላ/አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | | 4 | 1 | | ባህላዊ ተቋም (1) |
| 2 | አፋር | 2 | | | | | ባህላዊ ተቋም (2) |
| 3 | አማራ | 13 | | 8 | 4 | 1 | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | | 4 | | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | | 1 | | 1 | |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | | 1 | | 1 | |
| 7 | ሀረሪ | 2 | | 2 | | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | | 23 | 3 | 1 | |
| 9 | ሲዳማ | 2 | | 2 | | | |
| 10 | ሶማሌ | 4 | | 4 | | | |
| 11 | ደቡብ ሀ/ብ/ብ | 18 | 1 | 13 | 1 | 3 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 1 | 3 | | | |
| 13 | ትግራይ | 10 | | 8 | | | አለማቀፍ/ቅይጥ (2) |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 96 | 2 | 73 | 9 | 7 | 5 |

## IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን

### ሀ. በአብዛኛው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን የተደገፈ አማራጭ፡ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን'

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን መካከል 17 ቡድኖች (ወይም 70.83%) የሆኑት አዲስ የሚቋቋም ኮሚሽንን መርጠዋል። ምክንያቶቻቸውን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- ሌሎች ተቋማት የራሳቸው በቂ የሥራ ጫና አለባቸው፣
- የማካካሻ ሥርዓት መተግበር ከባድ እና ውስብስብ የስራ ሂደት ነው፣ ትኩረት ሰጥቶ ይህንን እና ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስራዎችን ባንድነት የሚተገብር ነጻና ገለልተኛ ተቋም ያስፈልጋል፣
- መደበኛው ፍርድ ቤት ለምርጫ መቅረብ የለበትም፣ ይህ አማራጭ ከሽግግር ፍትህ ሀሳብ እና ዓላማ ጋር አብሮ አይሄድም።

**ለ. የተለያዩ አማራጮች**

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን መካከል 3 ቡድኖች (ወይም 12.5%) የሆኑት የግል ካሳ ጉዳይ በመደበኛው የሕግ ሥርዓት በፍርድ ቤቶች እንዲታይ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ፣ ሁለት ቡድኖች (ወይም 8.33%) የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንን፣ አንድ ቡድን (ወይም 4.16%) የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንን፣ እንዲሁም ሌላ አንድ ቡድን (ወይም 4.16%) ቀይጥ ኮሚሽን ማቋቋም ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል።

ሰንጠረዥ 54፡ 'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል?' የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | የግል ካሳን በፍርድ ቤቶች እንዲታይ ማድረግ | አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን | በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን | በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን | ሌላ/አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | | | | | |
| 2 | አፋር | 1 | | 1 | | | |
| 3 | አማራ | 5 | 2 | 3 | | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | | | | 1 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | | 1 | | | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | | 1 | | | |
| 7 | ሀረሪ | 0 | | 0 | | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | | 7 | | | |
| 9 | ሲዳማ | | | | | | |
| 10 | ሶማሌ | 1 | | 1 | | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 3 | 1 | 1 | | 1 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 0 | | 0 | | | |
| 13 | ትግራይ | 4 | | 2 | 1 | | ቀይጥ 1 |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 24 | 3 | 17 | 1 | 2 | 1 |

### 6.5.4.3.'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይምራው?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይምራው' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 159.5 ቡድኖች (ወይም 73.84%) የሚሆኑት የማካካሻ ስርአቱ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን' አማካኝነት ሊከናወን ይገባል የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል።

ከአጠቃላይ 216 ቡድኖች ውስጥ 19.5 ቡድኖች (ወይም 9.03%) ደግሞ የማካካሻ ሂደቱ 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን' አማካኝነት እንዲከናወን ሀሳብ ሰጥተዋል።

በሌላ በኩል 11 ቡድኖች (ወይም 5.09%) አገራዊ የምክክር ኮሚሽንን የመረጡ ሲሆን፣ 5 ቡድኖች (ወይም 2.31) የሆኑት የግል ካሳ በመደበኛው የሕግ ሥርዓት በፍርድ ቤት ሊመራ ይገባል የሚለውን አማራጭ ደግፈው ተከራክረዋል፡፡

የማካካሻ ስርአቱን ውጤታማ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር - ተሳታፊዎች ከተዘጋጁት የተለዩ ሌሎች አማራጮችንም አቅርበዋል። በመሆኑም 7.5 ቡድኖች (ወይም 3.47%) የሚሆኑት የማካካሻ ስርአቱ በገለልተኛ አለም-አቀፍ ወይም ቅይጥ ተቋም መመራት አለበት የሚል አቋም ሲይዙ፣ 7 ቡድኖች (ወይም 3.24%) ደግሞ ይህ የስራ ሂደት በባህላዊ ተቋማት ሊተገበር ይገባል ብለዋል፡፡ አንድ ቡድን የማካካሻ ስርአቱ በሼሪአ ፍርድ ቤት ሊመራ ይገባል ሲል፣ አንድ ሌላ ቡድን በበኩሉ የማካካሻ ስርአቱ ከሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን እና ከትግራይ ክልል ባለሙያዎች በተውጣጣ የባለሙያዎች ቡድን ሊመራ ይገባል ብለዋል።

**ግኝቱ ውይይቶቹ ከተካሄዱባቸው አካባቢዎች አንፃር ሲተነተን**

ይህ መረጃ ውይይቱ ከተካሄደበት ክልል/ከተማ አስተዳደር አንጻር ሲተነተን በአማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ሶማሌ፣ ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ብ/ብ/ህ እና ትግራይ ክልል፣ እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች - አብዛኞቹ ቡድኖች የማካካሻ ስርአቱ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን' አማካኝነት ይሰራ ለሚለው ሀሳብ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል።

በአፋር ክልል ከተሳተፉ አምስት የትኩረት ቡድኖች መካከል ሁለቱ ስራው 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን' መመራት አለበት ያሉ ሲሆን፣ ሌሎች ሁለት ቡድኖች ደግሞ በመድአ (የአፋር ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት) እንዲከናወን በምክንያት የተደገፈ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል ምንም እንኳ በሀገር-አቀፍ ደረጃ በአብዛኛው የትኩረት ቡድኖች ድጋፍ ባያገኝም በትግራይ ክልል 6.5 ቡድኖች የማካካሻ ስርአቱ ነጻና ገላልተኛ በሆነ አለም-አቀፍ ወይም ቅይጥ ተቋም ሊመራ እንደሚገባ በአፅንኦት ገልፀዋል፡፡

**ግኝቱ ከቡድኖች ስብጥር አንፃር ሲተነተን**

ግኝቱ ከቡድኖች ስብጥር አንጻር ሲታይ - በአራቱም አገራዊ ቡድኖች ማለትም በሴት ተጎጂዎች፣ በወንድ ተጎጂዎች፣ በቅልቅል እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች በሙሉ በከፍተኛ አብላጫ የተመረጠው 'አዲስ ኮሚሽን ይቋቋም' የሚለው አማራጭ ነው፡፡

ተሳታፊዎች አቋሞቻቸውን የሚደግፉ በርካታ ምክንያቶችን የሰጡ ሲሆን ሀሳቦቹ እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።

### ሀ. በሀገር-አቀፍ ደረጃ በአብዛኛዎቹ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' - ምክንያቶች

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይምራው' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 159.5 ቡድኖች (ወይም 73.84%) የሆኑት - የስራ ሂደቱ 'አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን' አማካኝነት ሊሰራ ይገባል የሚል አቋም ይዘዋል፡፡ ሀሳባቸውን የሚደግፉ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል፡፡

- አሁን ያሉት ፍርድ ቤቶች እና ኮሚሽኖች ከፍተኛ የሥራ ጫና አለባቸው፣
- ስራ ላይ ያሉት ተቋማት ከመንግስት ጣልቃ-ገብነት ነፃ አይደሉም፣ ገለልተኛ እና ውጤታማ አልሆኑም፣ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አልተወጡም፣ የህዝብ አመኔታ የላቸውም፣

- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እስካሁን እየሄደበት ባለው ስራ ትንሽ የሚታትር ቢሆንም ተሰሚነቱ በሚፈለገው ልክ አልመጣም፡ የሚያወጣው ሪፖርትም አልፎ አልፎ ገለልተኛነት ይጎድለዋል፡ በአጠቃላይም ኮሚሽኑ ተጽእኖ ፈጣሪ ተቋም አይደለም፡ የማካካሻ ስራ ለመስራት ብቁ አይሆንም፡
- ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሀላፊነት ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ ስራውን በአግባቡ አላከናወነም፡ በህዝብ ያለው ተቀባይነት እምብዛም አይደለም፡ ሲመረጥም ከፖለቲካ ፓርቲዎች ተቃውሞ ገጥሞታል፡ ስለሆነም አብዛኛውን የፖለቲካ ማህበረሰብ በሚያረካ መልኩ ሊሰራ አይችልም፡
- መደበኛው ፍርድ ቤት ለምርጫ መቅረብ የለበትም፡ ይህ አማራጭ ከሽግግር ፍትህ ሀሳብ እና ዓላማ ጋር አብሮ አይሄድም፡ ተበዳይን ማዕከል ያደረገ አሰራር አይሆንም፡ ወጪም ይጠይቃል፡
- የግል ካሳ ጉዳይን በመደበኛ የሕግ ሥርአት በፍርድ ቤቶች እንዲታይ ማድረግ በገንዘብ የማይተመኑ ጉዳቶች እንዳይታዩ የማድረግ ውጤት ይኖረዋል፡
- ከከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ከእርስ በእርስ ጦርነት በኋላ በሚተገበር የሽግግር ፍትህ ሂደት ማዕቀፍ የሚነሱ የማካካሻ ጥያቄዎች በመደበኛው ጊዜ በግል ተበዳዮች ከሚነሱ ጥያቄዎች የተለየ ባህሪና ክብደት አላቸው፡ እነዚህን ጉዳዮች በመደበኛው የማካካሻ አሰራር ለመፍታት መሞከር ዓላማው እንዳይሳካ ያደርገዋል፡ ስለሆነም የማካካሻ ሥርዓቱን አዲስ፡ ራሱን የቻለ፡ ነፃና ገለልተኛ በሆነ ተቋም እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡
- የማካካሻ ሥርዓት መተግበር ከባድ እና ውስብስብ የስራ ሂደት ነው፡ ትኩረት ሰጥቶ በአጭር ጊዜ ይህንን እና ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስራዎችን ባንድነት የሚተገብር ነጻና ገለልተኛ ተቋም ያስፈልጋል፡
- ከተአማኒነት፡ ተቀባይነት፡ ገለልተኛነት እና ውጤታማነት አንፃር አዲስ የሚቋቋም ተቋም ተመራጭ ነው፡
- አዲስ ኮሚሽን ሲቋቋም የሀገር ሽማግሌዎችን ባካተተ ሁኔታ ሊደራጅ ይገባል፡
- አዲስ የሚቋቋመው ኮሚሽን - ባለሙያዎችን ብቻ ሳይሆን ከባህላዊ ስርዓቶች፡ የሀይማኖት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች የተለያዩ አዋቂዎችን፡ እንዲሁም የስነ-ልቦና እና የሌሎች ሙያዎች ባለቤቶችን አሳትፎ የሚሰራ መሆን አለበት።

### ለ. በሀገር-አቀፍ ደረጃ በውሰን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' - ምክንያቶች

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይምራው' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 19.5 ቡድኖች (ወይም 9.03%) የሆኑት - የስራ ሂደቱ 'በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን' ሊሰራ ይገባል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። ሀሳባቸውን ለመደገፍ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ኮሚሽኑ አሁን የሚሰራው ስራ ውጤታማ ነው፡ ከሙብት ጉዳዮች ጋር በተገናኘ የዳበረ ልምድ አለው፡
- ኮሚሽኑ በምርመራና በማጣራት ዘርፍ ያካበተው ተሞክሮ እና እውቀት ጉዳዮችን በአግባቡ በመረዳት ስራውን በውጤታማነት ለማከናወን ያስችለዋል፡
- ኮሚሽኑ ጥሰቶች ሲፈፀሙ ሪፖርት የሚያወጣና መረጃዎችም ያሉት በመሆኑ ጉዳቶችን በቅርበት ለማወቅ እና ለመከታተል እድል ይሰጠዋል፡
- ኮሚሽኑ ሲጀመርም የተቋቋመው የዜጎችን ሙብት ለማስከበር ስለሆነ ይህን ስራ ደርቦ መስራት ይችላል፡
- ኮሚሽኑ ጉዳዮችን እንደየጉዳት መጠናቸው በመመርመር ማካካሻ ለመስጠት አመኔታ የሚጣልበት ተቋም ነው፡ የማካካሻ ስራን በነፃነት፡ በፍትሃዊነት እና በውጤታማነት ሊመራ ይችላል።

### ሐ. በሀገር-አቀፍ ደረጃ በንዑስ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ማከናወን' - ምክንያቶች

'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይምራው' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 11.5 ቡድኖች (ወይም 5.32%) የሚሆኑት የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንን መርጠዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- ኮሚሽኑ ከሌሎች ተቋማት የተሻለ ተቀባይነት አለው፣ አካታች ነው፣
- ኮሚሽኑ አዲስና ነፃ እንደመሆኑ መጠን የማህበረሰቡን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ የመረዳት አቅም አለው፣
- ኮሚሽኑ አሁን የሚሠራው ሥራ ከማካካሻ ተግባር ጋር ተቀራራቢ ይዘት አለው፣ ስለሆነም ሀላፊነቱ ቢሰጠው የሰው ሀይልና የገንዘብ ሀብትን በውጤታማነት ለመጠቀም ያስችላል።
- ኮሚሽኑ በምክክር ሂደቱ ብዙ ግንዛቤዎችን ይይዛል፡ ከዚህ ሁነት በመነሳት የማካካሻ ስርአቱን በተገቢ ደረጃ ለማከናወን የተሻለ እድል አለው፣
- ኮሚሽኑ አሁን ላለንበት ውስብስብ ችግሮች መፍትሄ ለማምጣት የተመሰረተ ተቋም ነው፣
- ተጎጂዎች በመደበኛው ፍርድ ቤት ሥርዓት ማካካሻ ለመጠየቅ አቅም/ችሎታ አይኖራቸውም።

### መ. በውሰን ቡድኖች የተደገፉ 'ሌላ/አዲስ አማራጮች'


'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይምራው' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 7 ቡድኖች (ወይም 3.24%) የሚሆኑት ስራው በባህል ተቋማት እንዲመራ ሀሳብ ያቀረቡ ሲሆን፣ 7.5 ቡድኖች (ወይም 3.47%) ደግሞ ገለልተኛ አለማቀፋዊ ወይም ቅይጥ ተቋም በማቋቋም መከናወን አለበት የሚል አማራጭ አቅርበዋል።

ሰንጠረዥ 55፡ 'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል?' - ሀገር-አቀፍ (የአራቱም ቡድኖች) ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | የግል ካሳ በፍርድ ቤቶች ማየት | አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን | በሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን | በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን | ሌላ/አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | 0 | 5 | 2 | 0 | የባህል ተቋማት (1) |
| 2 | አፋር | 5 | 0 | 1 | 2 | 0 | የባህል ተቋማት (2) |
| 3 | አማራ | 32 | 2 | 21 | 7 | 1 | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 0 | 8 | 0 | 1 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 0 | 3 | 1 | 1 | |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 0 | 3 | 1 | 1 | |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 0 | 4 | 0 | 0 | |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 0 | 51 | 6 | 3 | የባህል ተቋማት (2) |
| 9 | ሲዳማ | 4 | 0 | 4 | 0 | 0 | |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 0 | 10 | 0 | 0 | ሺሪአ ተቋም (1) |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 2 | 27 | 1 | 4 | የባህል ተቋማት (2) |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | 1 | 7 | 0 | 0 | |
| 13 | ትግራይ | 24 | 0 | 15.5 | 1 | 0 | አለማቀፍ/ቅይጥ ተቋም (7.5) ቀንጅት (1) |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 216 | 5 | 159.5 | 19.5 | 11.5 | 16.5 |

ሰንጠረዥ 56፡ 'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል?' - ሀገር-አቀፍ (የአራቱም ቡድኖች) ማጠቃለያ (በቡድኖች)

| | | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | የግል ካሳ በፍርድ ቤቶች ማየት | አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን | በኢ/ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን | በኢ/አገራዊ ምክክር ኮሚሽን | ሌላ/አዲስ አማራጭ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 49 | 0 | 37 | 3.5 | 1.5 | 7 | |
| 2 | አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 47 | 0 | 34.5 | 6 | 1 | 3.5 | 2 |
| 3 | አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ | 96 | 2 | 71 | 9 | 7 | 5 | 2 |
| 4 | አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ | 24 | 3 | 17 | 1 | 2 | 1 | |
| | **አገራዊ የአራቱም የትኩረት ቡድኖች ማጠቃለያ** | 216 | 5 | 159.5 | 19.5 | 11.5 | 16.5 | 4 |
| | | | | | | | | |




*'የማካካሻ ሥርዓትን ማን ይመራዋል/ያስተባብረዋል?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ*

### 6.5.4.4.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

የማካካሻ ስርአት ተቋማዊ አደረጃጀትን በተመለከተ ሁሉም የሕጻናት እና በህጻናት ጉዳይ ላይ የሚሰሩ ተወካዮች፣ ሁሉም አካል ጉዳተኛና አረጋውያን ተሳታፊዎች፣ እንዲሁም ግማሽ ያህሉ ከጾታዊ ጥቃት ያገገሙ ሴት ተሳታፊዎች፣ የሴቶች ብቻ መድረክ ተሳታፊዎች፣ እና የተወሰኑ የሃገር ውስጥ ተፈናቃይ ወንዶች፡ ተፈናቃይ ሴቶችና ተፈናቃይ የቅልቅል ቡድኖች ተሳታፊዎች 'አዲስ የሚቋቋም ኮሚሽን' ሥራውን ሊያስተባብረው ይገባል

በማለት ሀሳባቸውን ሰጥተዋል። ምክንያታቸውም ለህዝቡ አመኔታ ሲባል ማካካሻ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ቢሰጥ የተሻለ ይሆናል የሚል ነው። በተሳታፊዎች የሚከተሉት ምክረ-ሃሳቦችም ተነስተዋል።

- የማካካሻው ስርአት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ከዘላቂ ተቋማት ስራዎች ጋር መተሳሰር አለበት፣
- አዲስ የሚቋቋመው ተቋም የማካካሻ ስራውን ለሴቶች ጉዳት ልዩ ትኩረት በሚሰጥና የውስጥ አደረጃጀት በሚኖረው አግባብ ማካሄድ ይኖርበታል፣
- አዲስ የሚቋቋመው ኮሚሽን ከሚወስናቸው አንዳንድ ውሳኔዎች ለፍርድ ቤት ይግባኝ የሚጠየቅበት ሂደት አብሮ ሊፈተሽ ይገባል።

በሌላ በኩል ግማሽ ያህሉ ከጾታዊ ጥቃት ያገገሙ ሴት ተሳታፊዎች፣ ተፈናቃይ የሴቶች እና የወንዶች ቡድኖች፣ እንዲሁም የተወሰኑ የሴቶች ብቻ መድረክ ተሳታፊዎች የማካካሻ ስርአቱ በሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አማካኝነት መከናወን አለበት ብለዋል። በተጨማሪ የተወሰኑ የተፈናቃይ ሴቶችና የተፈናቃይ ቅልቅል ቡድን አባላት ደግሞ የማካካሻ ስርአቱን የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሊመራው ይገባል የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል።

### 6.5.4.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

የማካካሻ ስርአቱን የትኛው ተቋም ይምራው የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ - ተሳታፊዎች አሁን ያሉት ተቋማት ተደራራቢ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ውጤታማ ሆነው ሊያከናውኑት አይችሉም፣ አቅምም አይኖራቸውም፣ ስለሆነም ነጻና ገለልተኛ ሆኖ የሚሰራ አዲስ ኮሚሽን አቋቁሞ መስራት የተሻለ ነው የሚል ሀሳብ ሰጥተዋል።

በተጨማሪም ለስርአተ-ጾታ ምላሽ የሚሰጥ እና አካታች ተቋም በመመስረት ስራው አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት መከናወን አለበት ሲሉ ምክረ-ሃሳብ አቅርበዋል። የሚቋቋመው ተቋም የሚሰጠው አገልግሎት የሴት፣ የወንድ፣ የህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና የጉዳት ተጋላጭ ተጎጂዎችን ልዩ ፍላጎት ግምት ውስጥ የሚያስገባ መሆን እንዳለበትም ተመላክቷል።

## 6.6. ተቋማዊ ማሻሻያ

### 6.6.1. መግቢያ

በሽግግር ፍትህ ሂደት አንድ ሀገር ከእርስ በእርስ ግጭት፣ ጦርነት ወይም ጭቆና መላቀቅ በኋላ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥቃት ያደረሱ ወይም አድርሰዋል ተብለው የሚታመኑ ሰዎችን በኃላፊነት ቦታ ህዝብን እንዲያገለግሉ ማድረግ ለሚታሰበው የእርቅ እና የሰላም ሂደት እንቅፋት ይፈጥራል። ስለሆነም ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በመቅረፅ በእንደዚህ አይነት ተግባር ላይ ተሰማርተው የነበሩ የመንግስት ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በመለየት፣ በማጥራት እና ከስራ በማሰናበት ወይም ሌሎች አስፈላጊ ህጋዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ተቋማዊ ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም ተቋማቱን በተገቢዉ መልኩ ለመቀየርና የተቋማቱን ተአማኒነት፣ተቀባይነት እና አሰራር በመለወጥ ዘላቂ የሆነ ማሻሻያ እንዲኖር መሰረት ይጥላል።

የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ ሶስት ዋና ዋና ሂደቶች ያካትታል። እነዚህም 'ተቋማት/ግለሰቦችን መለየት እና ማጥራት'፣ 'ከስራ እና ከሀላፊነት ማግለል' እና 'የሕግ እና የአሰራር ለውጥ' መተግበርን የሚመለከቱ ናቸው።

ተቋማዊ ማሻሻያን በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሴት ተጎጂዎች፣ የወንድ ተጎጂዎች፣ የቅልቅል እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች በሶስት ዋና ዋና ጥያቄዎች ዙሪያ ውይይት እና ክርክር አድርገዋል። እነዚህ ጥያቄዎች በሽግግር ፍትህ ሂደት፡-

- 'በየትኞቹ ተቋማት ላይ ቅድሚያ በመስጠት የልየታ፣ የማጥራትና የማሻሻል ተግባር ሊከናወን ይገባል?'፣
- 'ተመሳሳይ ወንጀሎችና የመብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ምን አይነት የእርምት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል?'፣

- እንዲሁም 'እነዚህ ተግባራት በምን አይነት ተቋም ሊከናወኑ ይገባል?' የሚሉ ናቸው።

ከሁሉም የምክክር መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች የመረጧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በተለይ 'በትኩረት የውይይት ቡድኖች የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች'፡ 'ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' እና 'በሌሎች የተመረጡ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረኮች ተሳታፊዎች' የተሰጡ ግብዓቶች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል።

## 6.6.2. 'በየትኞቹ ተቋማት ላይ ቅድሚያ በመስጠት የመለየት እና የማጥራት ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል?'

### 6.6.2.1.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

#### I. የሴት ተሳታፊዎች ቡድን

'በየትኞቹ ተቋማት ላይ ቅድሚያ በመስጠት የልየታ፡ የማጥራትና የማሻሻል ተግባር ሊከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ 49 የሴት ተሳታፊ ቡድኖች ውይይት አድርገዋል። በቅድሚያ የመለየት እና የማጥራት ተግባር ሊከናወንባቸው የሚገቡ ተቋማትን እንደሚከተለው ዘርዝረዋል።

- የፍትህ ተቋማት (ፍርድ ቤት፡ አቃቤ ሕግ፡ ማረሚያ ቤት፡ ፍትህ ሚኒስቴር)፡
- የደህንነት ተቋማት (ፖሊስ፡ መከላከያ፡ ሚሊሻያ)፡
- ከፌዴራል እስከ ታችኛው መዋቅር ያለው አመራር፡ የቀበሌ፡ የወረዳ፡ የዞን አመራር፡
- የመንግስት የላይኛው አስተዳደር (በተለይ ሕግ አውጪ እና አስፈፃሚ)፡
- እንባ ጠባቂ ተቋም፡ ኢሰመኮ፡ ዩኒቨርሲቲዎች፡ ማዘጋጃ ቤቶች፡ ሚዲያ፡ የፖለቲካ ተቋማት፡
- የሀይማኖት፡ የባህል እና ሲቪል ማህበረሰብ ተቋሞች።

#### II. የወንድ ተሳታፊዎች ቡድን

'በየትኞቹ ተቋማት ላይ ቅድሚያ በመስጠት የልየታ፡ የማጥራትና የማሻሻል ተግባር ሊከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ 47 የወንድ ተሳታፊ ቡድኖች ውይይት አድርገዋል። በቅድሚያ የመለየት እና የማጥራት ተግባር ሊከናወንባቸው የሚገቡ ተቋማትን ዘርዝረዋል።

በዚህ መሰረት ከላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ - የልየታ፡ ማጥራት እና ማሻሻል ስራው የሀገር መከላከያን፡ የክልል ፍትህ ቢሮዎችን፡ የክልል ልዩ ሀይሎችን፡ እና ሕዝባዊ ፖሊስን ማካተት እንዳለበት ምክረ-ሀሳባቸውን አቅርበዋል።

#### III. የቅልቅል ቡድን

'በየትኞቹ ተቋማት ላይ ቅድሚያ በመስጠት የልየታ፡ የማጥራትና የማሻሻል ተግባራት ሊከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ከላይ ከተጠቀሱት ተቋማት በተጨማሪ - የልየታ፡ ማጥራት እና ማሻሻል ስራው አክቲቪስቶችን፡ የትምህርት ተቋማትን፡ በኦሮሚያ ክልል የተቋቋመውን ጋቸና ሲርና የሚባል አደረጃጀትን፡ የመሬት አስተዳደር አካላትን፡ እና የሴቶችና ህጻናት ፅህፈት ቤቶችን ሊያካትት ይገባል ብለዋል።

#### IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን

'በየትኞቹ ተቋማት ላይ ቅድሚያ በመስጠት የልየታ፡ የማጥራትና የማሻሻል ተግባር ሊከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖችም በተመሳሳይ ከላይ ከቀረቡት በተጨማሪ - የኢሚግሬሽን መስሪያ ቤት፡ ጉምሩክ ኮሚሽን፡ ጸረ-ሙስና ኮሚሽን፡ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ እና የፌደሬሽን ምክር ቤት ቅድሚያ ተሰጥቶ በልየታ እና ማጥራት ስራዎች ከሚሸፈኑ ተቋማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ሲሉ ምልከታቸውን አጋርተዋል።

### 6.6.2.2.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

አብዛኛዎቹ በሁሉም መድረኮች ላይ የተገኙ ተሳታፊዎች በፌዴራል ደረጃ እና ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉ ተቋማት በማሻሻያ ሂደት ሊያልፉ ይገባል፡ በተጨማሪም ጦርነት ሲነሳ ወይም ግጭቶች ሲፈጠሩ ዝም ያሉ ተቋማት እና ሀላፊነታቸውን ያልተወጡ ተለይተው በተመሳሳይ ሂደት መሻሻል ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ለልየታ፡ የማጥራትና የማሻሻል ተግባር በተሳታፊዎች ከተለዩ ተቋማት ውስጥ የፍትህ እና የጸጥታ ዘርፍ ተቋማት (ፖሊስ፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ አቃቤ ህግ፣ ፍርድ ቤት፤ ደህንነት)፡ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሰላም ሚኒስቴር፣ የአደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ መከላከያ ሚኒስቴር፣ የሚሊሻ እና ደንብ ማስከበር አደረጃጀቶች፣ የቀበሌ እና ወረዳ አስተዳደሮች፣ ኢሠመኮ፣ የሚድያና ብሮድካስት ተቋማት፣ የእንባ ጠባቂ እና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ተቋማት፣ ህግ አውጪ እና አስፈፃሚ፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ እና የሀይማኖት ተቋማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በሌላ በኩል ተመሳሳይ ወንጀሎች እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች በተመለከተ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ምክረ-ሀሳቦች አቅርበዋል።

- የተቋማትን ነጻነትና ገለልተኝነት የሚያስጠብቅ ስርአት መዘርጋት፣
- የፖለቲካ ጣልቃ ገብነትን ማስቀረት፣
- የአቅም ግንባታ ስራዎች ማከናወን፣
- በግለሰብም ሆነ በተቋም ደረጃ የክትትልና የቁጥጥር ተግባራትን አጠናክሮ ማስቀጠል፣
- በሚድያ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ማከናወን፣
- የሀይማኖት አባቶች አማኙን በተገቢ የይዘት ትኩረት እንዲያስተምሩ ማድረግ፣
- የትምህርት ስርአቱን በመፈተሽ ማስተካከል፣
- የሌሎች ሀገራት ልምዶችን ማየት፡ መቀመር።

### 6.6.2.3.ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

'የትኞቹን ተቋማት ቅድሚያ በመስጠት የመለየት እና የማጥራት ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄን በተመለከተ በተሳታፊዎች በቀረቡ ሁሉም ምክረ-ሃሳቦች ላይ የተቋማዊ ማሻሻያ አስፈላጊነት ከፍተኛ አጽንኦት ተሰጥቶታል።

ተቋማዊ ሪፎርምን የሚመለከቱ ሀሳቦች በሶስት በመክፈል ተዳሰዋል። የመጀመሪያው የሽግግር ፍትህን ተግባራዊ ለማድረግ በሥራ ላይ ያሉ ተቋማትን (የሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የምክክር ኮሚሽንን) ሪፎርም ማድረግ ወይም አዲስ ኮሚሽን ማቋቋምን የሚመለከት ነው።

ሁለተኛው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በግጭት ወይም በሰላም ማስከበር ሥራ ላይ ተሳታፊ በመሆናቸው በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ትኩረት የሚሰጣቸው ተቋማት ናቸው። ይህም በዋናነት ከሰብዓዊ መብት ረገጣ ጋር ተያይዞ ስማቸው የሚነሱ ተቋማትን (ለምሳሌ የደህንነት ተቋማት፣ ፖሊስ፣ ዓቃቤ ሕግ፣ በተወሰነ መልኩም የዳኝነት አካላትን) የሚመለከት ነው። የነዚህ ተቋማት ሪፎርም እውነት ለማፈላለግ፣ ክስ ለመመስረት፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና የእርቅ ሂደትን ለማከናወን በአጠቃላይም ከግጭት ወደ ሰላም ግንባታ የሚደረገውን ሂደት የተሳካ ለማድረግ አስፈላጊ ነው።

በሶስተኛ ደረጃ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ሙስና፣ ሌብነት፣ አድሎአዊ አሰራርን በአጠቃላይ ከብልሹ አሰራር የፀዳ የመንግስት አስተዳደር ለመገንባት አስፈላጊ የሪፎርም ሥራ መስራትን የሚመለከት ነው። በዚህ መልኩ የሚደረግ ማሻሻያ ለሽግግር ሂደቱ መሳካት መደላድል ለመፍጠርና ሰላምና ዲሞክራሲ ለመገንባት አስፈላጊ መሆኑን በተሳታፊዎች ምክረ-ሀሳብ ተመላክቷል።

በሌላ በኩል ተመሳሳይ ወንጀሎች እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በተመለከተ በተሳታፊዎች የሚከተሉት ነጥቦች ተነስተዋል፡፡

- የመንግስት ባለስልጣናትና ሰራተኞች ንቃተ-ሕግ ማሻሻል፡ በአለምአቀፍ ሰብአዊ መብቶች/ሰብአዊነት ሕጎች ዙሪያ ሁሉን አቀፍ የስልጠና ፕሮግራሞችን ማደራጀት፣
- የመለየትና የማጥራት እርምጃዎች ግልጽና በሆነ መስፈርትና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መከናወናቸውን ማረጋገጥ፣
- የተቋማትን ሚዛን መጠበቅ እና እኩል እንዲጠናከሩ ማድረግ፣
- ተጠያቂነትን ማስፈን፣
- በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚያጋጥሙ ጥሰቶችን አስመልክቶ የወንጀል ሕግ ማሻሻያ ማካሄድ፡ ጾታዊ ጥቃትን የተመለከተ ራሱን የቻለ ሕግ እንዲወጣ ማድረግ፣
- የተቋማት ማሻሻያ ስራዎች የስርአተ ጾታ እይታ እንዲኖራቸው ማድረግ፡ አካታች የተቋም አደረጃጀት መፍጠር የለውጥ ስራው አካል እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በስርአተ ጾታ ዙሪያ ተከታታይ ስልጠናዎችን በመስጠት ግንዛቤ መፍጠር፣ ጾታዊ ጥቃት ያደረሱ፣ እንዲደርስ ትእዛዝ የሰጡ ወይም መፈጸሙን ማስቀም ያልቻሉ አመራሮች በየደረጃው የማጥራትና የመለየት ስራ እንዲከናወንባቸው ማድረግ፡፡

### 6.6.3. ተመሳሳይ ወንጀሎች/የመብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ምን አይነት የእርምት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል?

በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሴት ተጎጂዎች፡ የወንድ ተጎጂዎች፡ የቅልቅል፡ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች - 'በየትኞቹ ተቋማት ላይ ቅድሚያ በመስጠት የልየታ፡ የማጥራትና የማሻሻል ተግባራት ሊከናወን ይገባል?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ - ጥልቅ ውይይት እና ክርክር በማድረግ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን ከማስቻል አንፃር የሚከተሉት ምክረ-ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲደረጉ አቋማቸውን ገልፀዋል፡፡

- ለሁሉም አገራዊ ችግር (መፈናቀል፡ ግድያ ወዘተ) ምንጭ የሆነውን ህገ-መንግስታዊ አወቃቀር ማሻሻል፡
- በፖለቲካዊ ምህዳር ዙሪያ አቃፊና አካታች ስርዓት መዘርጋት፡ ስርአቱን በማስተካካል በህዝቡ መካከል የሚነሱ ቅራኔዎችን የሚቀንሱ ተጨባጭ ስራዎችን ማከናወን፡
- የሕግ የበላይነትን በቁርጠኝነት ማስከበር፡
- በጥናት ላይ የተመሰረተ የሕግና የተቋም ማሻሻያ ማካሄድ፡ ሕጎችና ፖሊሲዎች ሲወጡ እስከ ቀበሌ ወርደው ከማሕበረሰቡ ጋር ውይይትና መተማመን የሚፈጠርበት አሰራር መዘርጋት፡
- ግልፅ የተጠያቂነት እና የአቤቱታ ስርዓት መዘርጋት፡ በከፍተኛ አመራሩ ላይ ጠንካራ ተጠያቂነት ማስፈን፡ ወንጀል የፈፀሙትን ያለከለላ ተጠያቂ ማድረግ፡ ቀጣይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፡
- ችግር ሲፈጥሩ በነበሩ ኃላፊዎች፡ አመራሮችና ሰራተኞች ላይ አስፈላጊ ማጣራት በማድረግ እንደፈጸሙት ጥፋት ክብደት ከኃላፊነት ዝቅ የማድረግ፡ የማንሳት፡ ከስራ የማገድ፡ የማሰናበት፡ እና የሕግ ተጠያቂነት ስራን የሚያሳልጡ ጠንካራ አሰራሮች መዘርጋት፡
- በሰብአዊ መብት ጥሰት በተሳተፉ አካላት ላይ በቁርጠኝነት ቅጣት መጣል፡ በዲሲፕሊን የማነጽ እና ከስራ የማግለልና የማሰናበት ስራዎችን ባንድነት ማካሄድ፡
- የመለየት፡ የማጥራትና የአቅም ግንባታ ሥራ መስራት የሚያስችሉ ኩነቶችን ማዘጋጀት፡ በሁሉም ተቋማት ቋሚ የልየታና የማጥራት ስራ የሚሰራ ክፍል አደራጅቶ ቀጣይነት ያለው የክትትል ስራ መስራት፡
- የተቋማት የሰው ኃይል የሚመረጥበት፡ የሚመደብበትና የሚታገድበትን አሰራር ማስተካከል፡
- የባለሙያዎችን አቅም መገንባት፡ ብዝሀነትን ያረጋገጠ በእውቀት/ችሎታ ላይ የተመሰረተ የቅጥር/ሹመት ሰርአት መዘርጋት፡ የተቋም ሀላፊዎችን አሿሿም በጥንቃቄ ማከናወን፡

- ተቋማት በተማሩ፣ ነጻና ገለልተኛ በሆኑ፣ ከፖለቲካና ከካድሬ አስተሳሰብ በጸዱ ባለሙያዎች እንዲመሩ የሚያደርግ አሰራር መዘርጋት፣
- የፀጥታ አካላትን የቁጥር መስፈርት ማስተካከል፡ የደህንነት እና የአስፈፃሚ አካል ጣልቃ-ገብነትን መቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮች ማዘጋጀት፣
- የመከላከያ ሰራዊትን የስልጠና ማንዋል መከለስ፡ የጸጥታ ሀይል አባላትን በተሻለ ስነ ምግባር ማነጽ፣
- የፖሊስና ዐቃቤ ሕግ የምርመራና ክስ አሰራር ማሻሻል፡ አቅምና ስነ-ምግባርን የሚመለከቱ የሕግ/ፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማካሄድ፣ የፍትህ ተቋማት ኃላፊዎችን አሿሿም ከፖለቲካ ወገንተኝነት ማላቀቅ፣ የዐቃቤ ሕግ ተጠሪነት ለፓርላማ እንዲሆን መስራት፣
- በፍትህ ተቋማት ላይ የሚደረገው የመንግስት ጣልቃ ገብነት እንዲቆምና እንዲስተካከል ማድረግ፣
- የፍርድ ቤቶችን ነጻነትና ገለልተኝነት ለማጠናከር የሚረዱ እርምጃዎችን መውሰድ፣
- ስለ ሰብዓዊ መብቶች አያያዝ በየጊዜው ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ በቅድሚያ በሰዎች አመለካከት ላይ መስራት፣
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ እምባ ጠባቂ ተቋም፣ እና ሚድያ ተቋማት ከስራ ኣስፈፃሚ ተፅእኖ ሙሉ ለሙሉ ነፃ ሆነው በሚሰሩበት ሁኔታ ላይ ጠንካራ ማሻሻያ ማካሄድ፣ የኮሚሽኑን የስልጣን ኃላፊነት ማጠናከር፣
- በሁሉም አካባቢዎች/ቦታዎች የስልጣን ክፍፍል እና ውክልና ማስፈን፣ ክልሎች በፌዴራል በቂ ውክልና እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የመልካም ስነ-ምግባር እሴቶችን ማዕከል ያደረጉ አሰራሮችን መዘርጋት፣ ከዘረኝነት የፀዱ መሆናቸውን መፈተሽ፣ እርምጃ መውሰድ፣
- ጽንፈኛ ሃሳቦች እንዲገቱ ማድረግ፣ የሰላም ባህላዊ እሴቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣
- ከሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት ተቋማት ጋር ትስስር መፍጠር፣
- ጠንካራ የሚዲያ ሪፎርም ማካሄድ፣
- የሀይማኖት ተቋማት የማህበረሰብን ትሥሥር እና አንድነት የሚያጠናክሩ ስራዎች እንዲሠሩ አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር።

### 6.6.4. የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ?

#### 6.6.4.1.መግቢያ

በተቋማዊ ጉዳዮች ማዕቀፍ 'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ' የሚለውን ርእሰ-ጉዳይ በተመለከተ ለተወያዮች ሁለት መነሻ ተቋማዊ አማራጮች ቀርበዋል።

የመጀመሪያው አማራጭ - 'የተቋማትን ለውጥ የሚያስተገብር የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ስልጣን የተሰጠው ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ ተቋም በማቋቋም ተግባራቶቹን ማከናወን' (ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም ተግባራቶቹን ማከናወን) የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው አማራጭ 'በሁሉም ተቋማት ውስጥ የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ሀላፊነት ያላቸው ቡድኖችን በማዋቀር ተግባራቶቹን ማከናወን' (በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር ተግባራቱን ማከናወን') የሚል ነው። ከዚህ ውጭ የሚታይ የተሻለ አማራጭ ቢኖር ተሳታፊዎች ይህንኑ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑ ተገልያላቸዋል።

#### 6.6.4.2.የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

I. **የሴት ተጎጂዎች ቡድን**

***ሀ. በአብዛኛዎቹ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም ተግባራቶቹን ማከናወን'***

‘የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 43.5 (ወይም 88.7%) የሆኑት - ስራው ‘ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም’ መከናወን አለበት የሚለውን አማራጭ መርጠዋል። ይህን አማራጭ ለመደገፍ የተሰጡ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ህብረተሰቡ አሁን ባለው የተቋማት አሠራር ሥርዓት ደስተኛ አይደለም፡ አመኔታ የለውም፡
- የማሻሻያ ተግባራቱን ተቋማቱ በራሳቸው እንዲያደርጉ መፍቀድ ለውጦች እንዳይመጡና የሽግግሩ ሂደት እንዲደናቀፍ ከመወሰን አይለይም፡ በተቋማቱ ውስጥ የጠራ አሰራር ስለሌለ እርስ በእርሳቸውም በጥቅም የተሳሰሩ ስለሆነ ያለ አድሎ ጨክነው ለውጥ የሚያመጣ ማሻሻያ ያደርጋሉ ተብሎ አይጠበቅም፡
- ጥፋት ያለባቸው ተቋማት ራሳቸውን ያሻሽሉ የሚለው ሀሳብ ተግባራዊ ይሆናል ብሎ ማመን ያዳግታል፡
- አሁን ያሉ ተቋማት የሰብአዊ መብት ጥሰቱ አካል የነበሩ ናቸው፡ የበደሉ አካላት/ሰዎች መልሰው ለለውጥ ጉዞ ሀላፊነት መታጨት የለባቸውም፡
- ነባር ተቋማት ለመንግሥት ጫና ተጋላጭ ናቸው፡ በገለልተኝነት ስራውን ሊሰሩ አይችሉም፡
- አዲስ ተቋም ገለልተኛ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው፡ በህዝብ አመኔታ ሊያገኝ ይችላል፡ አዲስ ስለሚቋቋምም አሳታፊ ሊሆን ይችላል፡ በበቂ ባለሙያ ለማደራጀት የተሻለ እድል አለው።

## ለ. በተወሰኑ የሴት ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ ‘በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር ተግባራቱን ማከናወን’

‘የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 5.5 ቡድኖች (ወይም 11.2%) የተቋም ማሻሻያ ተግባራቱ ‘በየተቋማቱ ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር’ ሊከናወን ይገባል የሚለውን አማራጭ ደግፈው ተከራክረዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች ጠቅሰዋል።

- ይህ አማራጭ (የውስጥ ቡድኖችን በማዋቀር ማሻሻያዎችን መተግበር) ከተደራሽነት አንፃር ተገቢ ነው፡
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ረጅም ጊዜ እና አቅም ይፈልጋል፡ አስፈላጊ ማሻሻያዎችን በማድረግ ነባሩን ተቋም መጠቀም ይመረጣል፡
- ይህ አማራጭ እምነት እንዲኖር፡ እንዲሁም ውጤታማ ሥራ ለመስራት ያስችላል፡
- ለውጥ/ማሻሻያ የሚፈልገውን ልዩ ጉዳይ የሚያውቁት ራሳቸው ተቋሞቹ ናቸው፡ ስለሆነም በየተቋማቱ የልየታ፡ የማጥራት እና ከስራ የማገለል ሀላፊነት በውስጥ ቡድኖች ማከናወን ይበልጥ ውጤታማ ያደርጋል፡ ከአድልዎ ጋር የሚያያዙ ስጋቶችን ለመቀነስ ታማኝ እና ገለልተኛ የሆኑ ሰዎችን ለስራው መምረጥ ይቻላል።

ሰንጠረዥ 57፡ ‘የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ’ - የሴት ተጎጂዎች ቡድን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አዲስ በሚቋቋም አካል | በተቋማት ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | 1.5 | 0.5 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 6 | 1 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 2 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 1 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 12 | 2 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 9 | ሲዳማ | 1 | 0 | 1 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 3 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 8 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 2 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 5 | 0 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 49 | 43.5 | 5.5 |

## II. የወንድ ተጎጂዎች ቡድን

'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 46 ቡድኖች (ወይም 97.87%) የሆኑት ስራው 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም' መከናወን አለበት የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። የተሰጡ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ህዝቡ አሁን ባሉት ተቋማት ተስፋ ቆርጧል፡ ገለልተኛ አይደሉም፡ የህዝቡ አመኔታ የላቸውም፡
- የተቋማትን ችግር አንጥሮ የሚያወጣ፡ ከተጽእኖ ነጻ የሆነ ተቋም ያስፈልጋል፡ ለዚህ ደግሞ አሁን ያሉት ተቋማት ብቁ አይደሉም፡
- ሀላፊነቱ ቢሰጣቸው ተቋማቱ ራሳቸውን ያሻሽላሉ ብሎ ማመን ይቸግራል፡ የትኛውም ተቋም በራሱ ላይ ጨክኖ ጠንካራ እርምጃ አይወስድም፡
- በተቋሞች ውስጥ የራስን ችግር በራስ የመፍታት ልማድ የለም፡
- ተቋሞች ውስጥ ለውስጥ እርስ በርስ በጥቅም የተሳሰሩ ናቸው፥ ይህን ሰንሰለት በአጭር ጊዜ ውስጥ መበጠስ አይቻልም፡
- አሁን ያሉት ተቋማት በራሳቸው የችግሩ ምንጭ የነበሩ ናቸው፥ ስለሆነም ይህን ስራ ሊሰሩ አይገባም።

ሰንጠረዥ 58፡ 'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ' - የወንድ ተጎጂዎች ቡድን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ[61]

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አዲስ በሚቋቋም አካል | በተቋማት ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 7 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 2 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 1 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ[62] | 14 | 13 | 0 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 3 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 9 | 0 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 2 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 5 | 0 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 47 | 46 | 0 |

[61] አንድ ቡድን ሀሳብ አልሰጠም።
[62] አንድ ቡድን ሀሳብ አልሰጠም።

### III. የቅልቅል ቡድን

### ሀ. በአብዛኛዎቹ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አቋም፡- ‘ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም ተግባራቶቹን ማከናወን’

‘የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 78.5 ቡድኖች (ወይም 81.7%) የሆኑት ስራው ‘ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም’ መከናወን አለበት የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። የተሰጡ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- አሁን ያሉት ተቋማት ነጻና ገለልተኛ ናቸው የሚል እምነት የለም፣
- የአብዛኞቹ ተቋማት ችግር የሚመነጨው ከኃላፊዎች ነው፡ አንዳንዶቹ ችግሮች ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ስለሆኑ ኃላፊዎችን በሚነኩ ጉዳዮች የትኛውም ሰው በራሱ ላይ አይፈርድም፣ ወይም አይፈቅድም፣
- ተቋማት ራሳቸውን ማሻሻል አይችሉም/አይፈልጉም፣ ጨክነው ለውጥ የሚያመጣ እርምጃ አይወስዱም፣
- አሁን ያሉት ተቋማት የብዙዎቹ ችግሮች መንስኤ ናቸው፡ መልሶ እነሱኑ ለችግሩ መፍትሄ ፈልጉ ማለት ተገቢ አይሆንም፣ መሰረታዊ ለውጥ የሚመጣው ነጻ እና ገለልተኛ አካል በማቋቋም ብቻ ነው፡
- ከታሪክ እንደሚስተዋለው በተቋማት የውስጥ ተነሳሽነት የተከወኑ ለውጦች አልተሳኩም፣ በየተቋማቱ ልዩ የጸረ-ሙስና ቡድን ተቋቁሞ ውጤት አላመጣም፣ ስለሆነም የማጥራት ሥራው ሙሉ ለሙሉ በነፃና ገለልተኛ አካል ሊተገበር ይገባል፣
- አደረጃጀትን በተመለከተ ተቋሙ የሁሉም ብሄረሰብ፡ ህዝብ፡ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት አባቶች ተሳትፎን በሚያረጋግጥ መልኩ የመለየትና የማጥራት ስራዎችን ማከናወን ይኖርበታል።

### ለ. ውስን የቅልቅል ቡድኖች የደገፉት አማራጭ፡ ‘በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር ተግባራቱን ማከናወን’

‘የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 15.5 ቡድኖች (ወይም 16.1%) የሆኑት - የተቋም ማሻሻያ ተግባራቱ ‘በየተቋማቱ ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር’ ሊከናወን ይገባል የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች ጠቅሰዋል።

- ይህ አማራጭ ተቋማት እና ሀላፊዎች በአግባቡ የሚረዱትን የውስጥ ችግር በተሻለ ውጤታማነት እንዲፈቱ ያስችላል፡ የእያንዳንዱ ተቋም ባህሪና ችግር ይለያያል፡ እውነተኛ ለውጥ የሚመጣው ከውስጥ ብቻ ነው፡
- ችግሩ በሁሉም ተቋማት ላይ የሚታይ ፈተና ነው፡ ስለሆነም ተቋማቱን ማሻሻልና ባሉበት ማጠናከር እንጂ አፍርሶ መሥራት ተገቢ አይደለም፣
- ይህ አማራጭ የማጥራት ሥራውን በቋሚነት ለመስራት ያስችላል።

### ሐ. አንድ ቡድን የደገፈው አቋም፡ አዲስ አማራጭ

- ‘የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 1 ቡድን (ወይም 1%) የተቋም ማሻሻያ ተግባራቱ በፍትህ ሚኒስቴር አማካኝነት ሊተገበር እንደሚገባ በመግለፅ አዲስ አማራጭ አቅርቧል።

ሰንጠረዥ 59፡ ‘የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ’ - የቅልቅል ቡድን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አዲስ በሚቋቋም አካል | በተቋማት ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር | ሌላ/አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | 3 | 1 | 1 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | አፋር | 2 | 1 | 1 | |
| 3 | አማራ | 13 | 11 | 2 | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | 3 | 1 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | 1.5 | 0.5 | |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 2 | 0 | |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 1 | 1 | |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 22 | 5 | |
| 9 | ሲዳማ | 2 | 1 | 1 | |
| 10 | ሶማሌ | 4 | 3 | 1 | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 18 | 0 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 4 | 0 | |
| 13 | ትግራይ | 10 | 8 | 2 | |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 96 | 78.5 | 15.5 | 1 |

## IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን

### ሀ. በአብዛኛዎቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የተደገፈ አቋም፡- 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም ተግባራቶቹን ማከናወን'

'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 20 ቡድኖች (ወይም 83.33%) የሆኑት - ስራው 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም' መከናወን አለበት የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል፡፡ የተሰጡ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድን መመስረት ቡድኑ በነጻነትና በድፍረት ችግሩን ለመመርመርና ለማውጣት የሚችልበትን እድል አይፈጥርም፣ ለቁጥጥር አያመችም፣ ለውጤታማ ስራ እንቅፋት መሆኑ አይቀርም፣
- ይህ አማራጭ በተቋማት ላይ የስራ ጫና እንዳይፈጠር ያደርጋል፣
- በኮሚቴ የሚሰየሙ ሰዎች ተደራቢ የስራ ሀላፊነት ስለሚኖራቸው ለውጥን በየተቋሙ በኮሚቴ ለማካሄድ መወጠን ውጤት አያመጣም፣
- አዲስ አካል ማቋቋም ከሰው ሃይልና ከአደረጃጀት አንጻር የተሻለ ነጻነት ይሰጣል፣ አዲሱ ተቋም ችግሩ ከመነጨበት ተቋም የተነጠለ ስለሚሆን ተቀባይነት ያለው ስራ ለመስራት እና ችግሩንም በሚገባ ለመመርመር ያስችለዋል፡፡

### ለ. ውስን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የደገፉት አማራጭ፣ 'በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር ተግባራቱን ማከናወን'

'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 4 ቡድኖች (ወይም 16.6%) የሆኑት - የተቋም ማሻሻያ ተግባራቱ 'በየተቋማቱ ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር' ሊከናወን ይገባል የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች ጠቅሰዋል፡፡

- ስራው በአዲስ ተቋም ቢሰራ እያንዳንዳቸው ተቋማት ምን እንደሚሰሩ፣ ምን ጠንካራ ወይም ደካማ ጎን እንዳላቸው ለመለየት ይቸገራል፣ ብዙ ጊዜም ሊፈጅ ይችላል፣
- ከነባር ተቋማት ውስጥ ይህን ስራ ለመስራት የሚያስችል የስነ-ምግባር ሆነ የሙያ ብቃት ያላቸው ሰዎች ይኖራሉ፣ እነዚህን በመጠቀም ተቋማት በራሳቸው አቅም የለውጥ ስራውን እንዲመሩ ማድረግ ውጤታማ ያደርጋል፣

- ይህ አማራጭ ጊዜና ሀብት ለመቆጠብ ይረዳል።

ሰንጠረዥ 60፡ 'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ' - የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አዲስ በሚቋቋም አካል | በተቋማት ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 5 | 3 | 2 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | 1 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | 6 | 1 |
| 9 | ሲዳማ | 0 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 1 | 1 | 0 |
| 11 | ደቡብ ሀ/ብ/ብ | 3 | 2 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 0 | 0 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 4 | 4 | 0 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 24 | 20 | 4 |

### 6.6.4.3.'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ?' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 187.5 ቡድኖች (ወይም 86.8%) የሚሆኑት የስራ ሂደቱ 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም' መከናወን አለበት የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል።

ከአጠቃላይ 216 ቡድኖች ውስጥ 25.5 ቡድኖች (ወይም 11.8%) ደግሞ ስራው 'በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር' ማከናወን ይገባል የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል።

አንድ ቡድን የተቋም ማሻሻያ ስራው በፍትህ ሚኒስቴር አማካኝነት ሊሰራ ይገባል በማለት አዲስ አማራጭ አቅርቧል።

**ግኝቱ ውይይቶቹ ከተካሄዱባቸው ክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች አንጻር ሲተነተን**

'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ የግኝቱ ክልላዊ ስብጥር ሲታይ በሁሉም ክልሎች በሚባል ደረጃ በከፍተኛ መጠን የተደገፈው አማራጭ የስራ ሂደቱ 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም' መከናወን አለበት የሚለው ነው።

ነገር ግን በሲዳማ ክልል ሁለቱም አማራጮች በእኩል የቡድኖች ቁጥር ድጋፍ አግኝተዋል።

በመሆኑም 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል ማቋቋም' የሚለው አማራጭ በክልልም ሆነ በቡድኖች ደረጃ የአብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ተቀዳሚ ምርጫ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል።

**ግኝቱ ከቡድኖች ስብጥር አንጻር ሲተነተን**

ግኝቱ ከቡድኖች አንጻር ሲታይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች ውስጥ 43.3 ቡድኖች 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል ማቋቋም' የሚለውን አማራጭ የደገፉ ሲሆን፣ 5.5 ቡድኖች ደግሞ 'በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን ማዋቀር' የሚለውን አማራጭ መርጠዋል።

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂዎች ቡድኖች ውስጥ 46 ቡድኖች 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል ማቋቋም' የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል።

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 78.5 ቡድኖች 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል ማቋቋም' የሚለውን አማራጭ የደገፉ ሲሆን፣ 15.5 ቡድኖች ደግሞ 'በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን ማዋቀር' የሚለውን አማራጭ መርጠዋል።

በመጨረሻም በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን መካከል 20 ቡድኖች 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል ማቋቋም' የሚለውን አማራጭ የደገፉ ሲሆን 4 ቡድኖች ደግሞ 'በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን ማዋቀር' የሚለውን አማራጭ መርጠዋል።

ተሳታፊዎች አቋሞቻቸውን የሚደግፉ በርካታ ምክንያቶችን የሰጡ ሲሆን - ሀሳቦቹ በሚከተለው መልክ ተጠቃለው ቀርበዋል።

***ሀ) በሀገር-አቀፍ ደረጃ በአብዛኛዎቹ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ 'ገለልተኛና ነጻ የሆነ አዲስ አካል ማቋቋም' - ምክንያቶች***

'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ ተሳታፊዎች በከፍተኛ መጠን የመረጡትን አቋም የሚደግፉ ሃሳቦች/ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ህብረተሰቡ አሁን ባለው የተቋማት አሠራር ሥርዓት ደስተኛ አይደለም፣ ነጻና ገለልተኛ ናቸው የሚል እምነት የለም፣
- የማሻሻያ ተግባራቱን ተቋማቱ በራሳቸው እንዲያደርጉ መፍቀድ ለውጦች እንዳይመጡና የሽግግሩ ሂደት እንዲደናቀፍ ከመወሰን አይለይም፣ በተቋማቱ ውስጥ የጠራ አሰራር ስለሌለ እርስ በእርሳቸውም በጥቅም የተሳሰሩ ስለሆነ ያለ አድሎ ጨክነው ለውጥ የሚያመጣ ማሻሻያ ያደርጋሉ ተብሎ አይጠበቅም፣ የትኛውም ተቋም በራሱ ላይ ጨክኖ ጠንካራ እርምጃ አይወስድም፣
- የአብዛኞቹ ተቋማት ችግር የሚመነጨው ከኃላፊዎች ነው፣ አንዳንዶቹ ችግሮች ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ስለሆኑ ኃላፊዎችን በሚነኩ ጉዳዮች የትኛውም ሰው በራሱ ላይ አይፈርድም፣ ወይም አይፈቅድም፣
- አሁን ያሉት ተቋማት የሰብአዊ መብት ጥሰቱ አካል የነበሩ ናቸው፣ የችግሩ ምንጭ የነበሩ/የበደሉ አካላት/ሰዎች ለችግሩ መፍትሄ ፈልጉ መባል ወይም ለለውጥ ጉዞ በሀላፊነት መታጨት የለባቸውም፣ መሰረታዊ ለውጥ የሚመጣው ነጻ እና ገለልተኛ አካል በማቋቋም ብቻ ነው፣
- ነባር ተቋማት ለመንግሥት ጫና ተጋላጭ ናቸው፣ በገለልተኝነት ስራውን ሊሰሩ አይችሉም፣
- ከታሪክ እንደሚስተዋለው እስከዛሬ በተቋማት የውስጥ ተነሳሽነት የተከወኑ ለውጦች አልተሳኩም፣ በየተቋማቱ ልዩ የጸረ-ሙስና ቡድን ቢቋቋምም ውጤት አላመጣም፣ ስለሆነም የማጥራት ሥራው ሙሉ ለሙሉ በነፃና ገለልተኛ አካል ሊተገበር ይገባል፣
- በተቋሞች ውስጥ የራስን ችግር በራስ የመፍታት ልማድ የለም፣
- ይህ አማራጭ በተቋማት ላይ የስራ ጫና እንዳይፈጠር ያደርጋል፣
- የተቋማትን ችግር አንጥሮ የሚያወጣ፣ ከተጽእኖ ነጻ የሆነ ተቋም ያስፈልጋል፣ ለዚህ ደግሞ አሁን ያሉት ተቋማት ብቁ አይደሉም፣
- በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድን መመስረት ቡድኑ በነጻነትና በድፍረት ችግሩን ለመመርመርና ለማውጣት የሚችልበትን እድል አይፈጥርም፣ ለቁጥጥር አያመችም፣ ለውጤታማ ስራ እንቅፋት መሆኑ አይቀርም፣
- አዲስ ተቋም ገለልተኛ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው፣ በህዝብ አመኔታ ሊያገኝ ይችላል፣ አዲስ ስለሚቋቋምም አሳታፊ ሊሆን ይችላል፣ በበቂ ባለሙያ ለማደራጀት የተሻለ እድል አለው፣

- አዲስ አካል ማቋቋም ከሰው ሃይልና ከአደረጃጀት አንጻር የተሻለ ነጻነት ይሰጣል፡ አዲሱ ተቋም ችግሩ ከመነጨበት ተቋም የተነጠለ ስለሚሆን ተቀባይነት ያለው ስራ ለመስራትና ችግሩንም በሚገባ ለመመርመር ያስችለዋል፡
- አደረጃጀትን በተመለከተ ተቋሙ የሁሉም ብሄረሰብ፡ ህዝብ፡ የሀገር ሸማግሌዎች እና የሃይማኖት አባቶች ተሳትፎን በሚያረጋግጥ መልኩ የመለየትና የማጥራት ስራዎችን ማከናወን ይኖርበታል።

**ለ) በሀገር-አቀፍ ደረጃ በውስን ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር ተግባራቱን ማከናወን' - ምክንያቶች**

'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ?' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ ተሳታፊዎች በውስን ድምፅ የመረጡትን አቋም የሚደግፉ ሃሳቦች/ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ለውጥ/ማሻሻያ የሚፈልገውን ልዩ ጉዳይ የሚያውቁት ራሳቸው ተቋሞቹ ናቸው፡ ስለሆነም በየተቋማቱ የልየታ፡ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ሀላፊነት በውስጥ ቡድኖች ማከናወን ይበልጥ ውጤታማ ያደርጋል፡ እውነተኛ ለውጥ የሚመጣው ከውስጥ ብቻ ነው፡ ሆኖም ከአድልዎ ጋር የሚያያዙ ስጋቶችን ለመቀነስ ታማኝ እና ገለልተኛ የሆኑ ሰዎችን ለስራው መምረጥ ይቻላል፡
- በነባር ተቋማት ውስጥ ይህን ስራ ለመስራት የሚያስችል የስነ-ምግባር ሆነ የሙያ ብቃት ያላቸው ሰዎች ይኖራሉ፡ እነዚህን በመጠቀም ተቋማት በራሳቸው አቅም የለውጥ ስራውን እንዲመሩ ማድረግ ውጤታማ ያደርጋል፡
- አዲስ ተቋም ማቋቋም ረጅም ጊዜ እና አቅም ይፈልጋል፡ አስፈላጊ ማሻሻያዎችን በማድረግ ነባሩን ተቋም መጠቀም ይመረጣል፡
- ችግሩ በሁሉም ተቋማት ላይ የሚታይ ፈተና ነው፡ ስለሆነም ተቋማቱን ማሻሻልና ባሉበት ማጠናከር እንጂ አፍርሶ መሥራት ተገቢ አይደለም፡
- ይህ አማራጭ በሂደቱ ላይ እምነት እንዲኖር፡ እንዲሁም ውጤታማ ሥራ ለመስራት ያስችላል፡ ከተደራሽነት አንፃርም ተገቢ ነው፡
- ስራው በአዲስ ተቋም ቢሰራ እያንዳንዳቸው ተቋማት ምን እንደሚሰሩ፡ ምን ጠንካራ ወይም ደካማ ጎን እንዳላቸው ለመለየት ይቸገራል፡ ብዙ ጊዜም ሊፈጅ ይችላል፡
- ይህ አማራጭ ጊዜና ሀብት ለመቆጠብ ይረዳል።
- ይህ አማራጭ የማጥራት ሥራውን በቋሚነት ለመስራት ያስችላል።


ሰንጠረዥ 61፡ 'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ' - የአራቱም ቡድኖች ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አዲስ በሚቋቋም አካል | በተቋማት ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር | ሌላ/አዲስ አማራጭ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | 4 | 2 | 1 | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 2 | አፋር | 5 | 4 | 1 | | |
| 3 | አማራ | 32 | 27 | 5 | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 8 | 1 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 4.5 | 0.5 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 5 | 0 | | |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 3 | 1 | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 53 | 8 | | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 9 | ሲዳማ | 4 | 2 | 2 | | |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 10 | 1 | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 37 | 2 | | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | 8 | 0 | | |
| 13 | ትግራይ | 24 | 22 | 2 | | |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 216 | 187.5 | 25.5 | 1 | 2 |

ሰንጠረዥ 62፡ 'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ' - የአራቱም ቡድኖች ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ (በቡድኖች)

| | | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አዲስ በሚቋቋም አካል | በተቋማት ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር | ሌላ/አዲስ አማራጭ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 49 | 43.5 | 5.5 | | |
| 2 | አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 47 | 46 | 0 | | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 3 | አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ | 96 | 78.5 | 15.5 | 1 | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 4 | አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ | 24 | 20 | 4 | | |
| | **አገራዊ የአራቱም የትኩረት ቡድኖች ማጠቃለያ** | **216** | **188** | **25** | **1** | **2** |
| | | | | | | |




'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት በማን ይከናወኑ' - የቡድኖች ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

### 6.6.4.4.ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

**አብዛኛዎቹ የሕጻናት ቡድኖች፣ በህጻናት መብት ዙሪያ የሚሰሩ ተሳታፊዎች፣ አካል ጉዳተኛና አረጋውያን ተሳታፊዎች፣ ከጾታዊ ጥቃት ያገገሙ ሴቶች፣ የተፈናቃይ ቅልቅል ቡድን ተሳታፊዎች እንዲሁም የሴቶች ብቻ**

መድረክ ተሳታፊዎች - ተቋማዊ ማሻሻያውን የትኛው ተቋም ይምራው ለሚለው ጥያቄ ይህ የስራ ሂደት አዲስ አካል በማቋቋም ማከናወን የተሻለ ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል ከተፈናቃዮች የተወሰኑ የሴትና የወንድ ተጎጂ ቡድኖች እንዲሁም በሴቶች ብቻ መድረክ ላይ ከተሳተፉ ውስን ሰዎች በዋነኝነት የተቋምን ችግር እና የችግሩን ምንጭ የሚያውቀው ራሱ ተቋሙ በመሆኑ በሁሉም ተቋማት ውስጥ የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ሀላፊነት ያላቸው ቡድኖች በማዋቀር ተግባራቶቹን ራሳቸው እንዲያከናውኑ እድል መስጠት ያስፈልጋል የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። ይህም አዳዲስ ሪፎርሞችን በቀልጥፍና ለመተግበር ያስችላል የሚል ምክንያት አንስተዋል።

### 6.6.4.5.ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

'የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራቱ በማን ይከናወን' የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ገለልተኛና ነጻ በሆነ አካል እንዲተገበር ምክረ-ሃሳብ ያቀረቡ ሲሆን - ፍርድ ቤቶችን የማጥራት ስራን በተመለከተ በህገ መንግስቱ መሰረት ሊፈፀም ይገባል፡ ሌሎች ተቋማት ግን የልየታ ስራ የሚሰራ አካል በማደራጀት ማከናወን ተመራጭ ነው የሚል ሃሳብ ቀርቧል።

## 6.7. የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር?

### 6.7.1. መግቢያ

ስኬታማ በሆኑ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች የታየው አንዱ ጠቃሚ አካሄድ - በሂደቱ የሚሸፈነውን የጊዜ መነሻ እና መዳረሻ መወሰን ነው። ሂደቱ እጅግ የራቀ የመነሻ ጊዜ ኖሮት - ወሰኑ እጅግ እንዲሰፋ፡ እና ማስረጃ እና ምስክሮች በማይገኙበት ጊዜ እንዲጀምር ማድረግ ስራው ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል። በሌላ በኩል በጣም የቀረበ የመነሻ ጊዜ ኖሮት ዋና ዋና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተከሰቱበትን ጊዜ የማያካትት ከሆነ - የታሰበለትን ዓላማ ለማሳካት አይችልም። ስለሆነም በሀገራችን ለመተግበር በሚታሰበው ሂደት - ሀገራዊ አውዱን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት - የጊዜ ወሰኑን ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር?' ለሚለው ጥያቄ አምስት መነሻ አማራጮች ቀርበዋል። የመጀመሪያው አማራጭ 'ከ1983 ዓ.ም በፊት ያለውን ጊዜ' የሚሸፍን ሲሆን፡ ሁለተኛው አማራጭ 'ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ጊዜ'፣ ሶስተኛው 'ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ጊዜ'፣ አራተኛው አማራጭ 'ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ጊዜ'፣ እንዲሁም አምስተኛው አማራጭ 'ለክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ እና ለእርቅና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ' የሚሉ ናቸው። አማራጮቹ ለተሳታፊዎች በበቂ ሁኔታ የተብራሩ ከመሆኑም በላይ ተሳታፊዎችም ሌላ አማራጭ ካለ ማቅረብ እንደሚችሉ ተገልፆላቸዋል።

በዚህ ጥያቄ ላይ 216 ቡድኖች ጥልቅ ውይይት እና ክርክር አድርገዋል። በእያንዳንዱ መድረክ - የትኩረት ቡድኖቹ ውይይት በአራት የተለያዩ ቡድኖች (የሴት ተጎጂዎች፡ የወንድ ተጎጂዎች፡ የቅልቅል፡ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች) ተከፍሎ ተካሂዷል።

ከሁሉም መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች በጥያቄው ላይ ያቀረቧቸው አማራጮች፡ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፡ በእያንዳንዱ የትኩረት ቡድን የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል።

### 6.7.2. የተለያዩ የትኩረት ውይይት ቡድኖች እይታ

#### I. የሴት ተጎጂዎች ቡድን

**ሀ. ለክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፡ ለእውነት ማፈላለግ፡ እርቅ ማስፈንና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ (አማራጭ አምስት)**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖችች ውስጥ 15 ቡድኖች (ወይም 30.61%) የሚሆኑት የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ለክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ ማስፈንና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ' ሊተገበር ይገባል የሚለውን አማራጭ መርጠዋል።

ይህን አማራጭ ከመረጡ 15 ቡድኖች ውስጥ 9 ቡድኖች በኦሮሚያ ክልል የተሳተፉ ቡድኖች ሲሆኑ፣ 5 ቡድኖች ደግሞ (በቀድሞው) የደቡብ ህ/ብ/ብ ክልል የተሳተፉ ቡድኖች ናቸው። አንድ ቡድን ደግሞ በትግራይ ክልል ከተሳተፉ ቡድኖች ባንዱ የተመረጠ ነው።

በዚህ መሰረት ምንም እንኳ በተጎጂ ሴቶች ቡድኖች ዘንድ ይህ አማራጭ ከሌሎቹ አማራጮች ሁሉ ላቅ ያለውን ድጋፍ ያገኘ ቢሆንም - በክልል ደረጃ ሲታይ ግን በዋናነት በሶስት ክልሎች ውስጥ በተሳተፉ ቡድኖች ድምፅ መሰረት ብቻ የአብላጫነት ደረጃ ያገኘ አማራጭ ነው።

ይህን አቋም ለመደገፍ የሴት ጉዳተኞች ቡድኖች ያቀረቧቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ብዙዎቹ አገራዊ ችግሮች ከህገ-መንግስቱ መቀረፅ/መተግበር ጋር ተያይዘው የሚነሱ በመሆኑ ለክስ ጉዳዮች ይህ የጊዜ ማዕቀፍ ተገቢ ነው፣
- ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅና ሌሎች የሽግግር ፍትህ ጉዳዮች አተገባበር ወደኃላ በመሄድ ተገቢነት ያላቸው ጥያቄዎች ከሚነሱበት ዘመን ጀምሮ ያለውን እውነት መፈለግ/መመስረት ይገባል፡ ይህም አሉ የሚባሉ ቅራኔዎችን ለመፍታት ያስችላል፡ የአገሪቱ የአለመግባባት ምንጮች ከዳግማዊ ምኒሊክ ዘመነ-መንግስት አንስቶ ሊመዘዙ የሚችሉ በመሆኑ ይህ የጊዜ ማዕቀፍ ሳንፈጠር ጀምሮ ተከስተዋል የሚባሉ የማያግባቡ ክስተቶች፣ ታሪኮች እና የቁርሾ መነሻዎች ከስር ከመሰረት በማየት እውነትን ለመፈለግ እና ለመመስረት ያስችላል።

**ለ. ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ አራት)**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖችች ውስጥ 14.5 ቡድኖች (29.59%) ይህን የጊዜ አማራጭ ደግፈዋል።

የግኝቱን ክልላዊ ስርጭት ስንመለከት - ከላይኛው (አማራጭ አምስት) በተለየ መልኩ - ይህ አማራጭ በስምንት ክልሎች በተሳተፉ ቡድኖች ድጋፍ አግኝቷል። ሶስቱ ቡድኖች (በቀድሞው) የደቡብ ህ/ብ/ብ ክልል፡ 2 ቡድኖች በትግራይ ክልል፡ 2 ቡድኖች በደቡብ ምራብ ኢትዮጵያ ክልል፡ 2 ቡድኖች በአማራ ክልል፡ 2 ቡድኖች በኦሮሚያ ክልል፡ 1 ቡድን በጋምቤላ ክልል፡ 1 ቡድን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፡ 1 ቡድን በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር፡ እንዲሁም 1.5 ቡድን በአዲስ አባባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ናቸው።

ይህን አቋም ለመደገፍ የሴት ጉዳተኞች ቡድኖች ያቀረቧቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- የሕግ የበላይነት የተዳከመውና በርካታ ግጭቶች የተከሰቱት ከ2010 ጀምሮ ነው፣ ስለሆነም ትኩረቱ በዚህ ዘመን በተፈፀሙ አሰቃቂ ጥሰቶች ላይ መሆን አለበት፣
- ከ2010 ዓ.ም ቢጀመር የሽግግር ፍትህን ዓላማ በቶሎ ለማሳካት ያግዛል፡ ጉዳዮች ወደኋላ የዘመን ማዕቀፍ በተንተቱ ቁጥር ሂደቱ የሚንዛዛበትና የፍትህ ፍሬዎችን በፍጥነት ማየት የማይቻልበት ሁነት ይፈጠራል፡
- በቅርብ አመታት በርካታ ግጭቶች/ጦርነቶች ተካሂደዋል፡ የሽግግር ፍትህ ከዚህ ጊዜ ቢጀምር ማስረጃዎችን በበቂ መጠን እና ጥራት ለማግኘት ይቻላል፡ ጊዜው ወደኋላ በራቀ ቁጥር ማስረጃ ማግኘት የተወሳሰበ ይሆናል፡
- ያለፈን ነገር መነካካት የተረሳ ቁስል እና ህመም ማስታወስ ይሆናል፡ ሀገርን እና ህዝብን ወደ ባሰ ሁኔታ ሊከት ይችላል፡

- በኋላኛው ዘመን ኩነቶች ላይ አብዝተን ባተኮርን መጠን አሁን ፊታችን ላይ የቀመውን ግዙፍ ችግር ለመፍታት የምንቸገርበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፣
- አሁን ያለው ትውልድ መዳን አለበት፣ እስካሁን ያለፉ ስርአቶችን ስንተችና ሀላፊ ስናደርግ ቆይተናል፣ አሁን የተሻለ የሚሆነው ወደራሳችን ማየት፣ ራስን በራስ መተቸትና ራስን ማረም ነው፣ ለዚህ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ያለው የጊዜ ማዕቀፍ ይበልጥ ተመራጭ ነው፣
- የሽግግር ፍትህ ስራ ከ2010 ዓ.ም ቢጀምር አሁን ላለው ማሕበረሰብ በቀጥታ ተደራሽ ያደርገዋል፣
- በትግራይ ጦርነት በርካታ የሰብአዊ መብት ጥሰት የተፈፀመውና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ የተፈናቀለው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ስለሆነ ጊዜውን ተመራጭ ያደርገዋል።

### ሐ. ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ ሁለት)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 49 የሴት ተሳታፊ ቡድኖች ውስጥ 10 ቡድኖች(ወይም 20.4%) ይህን የጊዜ አማራጭ ደግፈዋል። አማራጩ በስድስት ክልሎች (አማራ፣ ሶማሌ፣ ሲዳማ፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ሀረሪ፣ ኦሮሚያ) በተሳተፉ ቡድኖች ድጋፍ አግኝቷል።

ይህን አቋም ለመደገፍ የሴት ጉዳተኞች ቡድኖች ያቀረቧቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ከማንነት ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ግድያዎች፣ ማፈናቀሎች፣ ዘረፋዎች፣ የብሄር ክፍፍል፣ ድንበር መከለል ወዘተ በስፋት መታየት የጀመሩት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣ ስለሆነም የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከዚህ ጊዜ ሊጀምር ይገባል፣
- በሁሉም ዘመን የተፈፀመ ጥሰት ይታይ ቢባል የማስረጃ፣ የጊዜና የገንዘብ እጥረት ያጋጥማል፣ ይህም ዓላማው እንዳይሳካ ያደርገዋል።

### መ. ከ1983 ዓ.ም በፊት ያለውን በሚያካትት መልኩ (አማራጭ አንድ)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 49 የሴት ተሳታፊ ቡድኖችች ውስጥ 4.5 ቡድኖች (ወይም 9.18%) የሚሆኑት ይህን አማራጭ መርጠዋል። ሁለቱ በኦሮሚያ፣ 1 ቡድን በአፋር፣ 1 ቡድን በትግራይ፣ እንዲሁም ሌላ ቡድን (በቀድሞው) የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል የሚገኙ ናቸው። ለዚህ አቋም በቡድኖቹ አባላት የሚከተሉት ምክንያቶች ተጠቅሰዋል።

- የአፋር እና ሶማሌ ማህበረሰቦች ውስብስብ ግንኙነት ዘመናት ያስቆጠረ ነው፣ ችግሮቹን በትክክል ለመፍታት ወደ ኋላኛው ጊዜ መመለስና ከግጭቶቹ ታሪካዊ መሰረት መጀመር አለበት፣
- የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ ከ1983 ዓ.ም በፊት ጀምሮ የነበሩ ጉዳዮችን ማየት መቻል አለበት፣ በእርግጥ ይህን ማድረግ ምርመራ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን ለማግኘት አዳጋች ሊያደርገው ይችላል፣ ቢያንስ ግን ለተፈፀሙ ወንጀሎች እና የመብት ጥሰቶች እውቅና በመስጠት ህብረተሰቡ እንዲማርባቸው ማድረግ ይገባል፣
- ባለፉት (ረጅም) ዘመናት የተፈፀሙ በደሎችን በአግባቡ መፍታትና መፍትሄ መስጠት ለአሁኑ ሆነ ለሚመጣው ትውልድ አስተዋፅኦዉ እጅግ ከፍ ያለ ነው፣
- የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከጅማሮዉ ሊነሳ ይገባል፣ አገሪቱ የምትናጥባቸው ብዙዎቹ ስንክሳሮች የዛሬ ሳይሆኑ ከጥንት ጀምሮ የወረዱ ናቸው፣ የተደበቁ እውነቶች ካልወጡ ከችግር አዙሪት መውጣት አይቻልም፣ የኖሩ ቁስሎች በጊዜ ሳይገደቡ መታጠብ፣ መታከም፣ መፈወስ አለባቸው።

### ሠ. (ሌላ) አማራጭ

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 49 የሴት ተሳታፊ ቡድኖችች ውስጥ 2.5 ቡድኖች (5.1%) የሚሆኑት ሌላ አማራጭ አቅርበዋል። በነዚህ ቡድኖች እይታ የተወሳሰበ አገራዊ ችግር በአብዛኛው የተከሰተው ከ2012 ዓ.ም

ወዲህ እንደመሆኑ መጠን የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከዚህ ጊዜ ሊጀምር ይገባል የሚል ነው፡፡ ከዚህ በፊት በነበረው የታሪክ ሂደት ላይ ጊዜ ማጥፋት ጥቅም የለውም፣ ትርፉ ልፋት ብቻ ነው። ስለሆነም ተመራጩ አካሄድ አሁን ባለው ፈተና ላይ ማተኮር ነው፡፡

## ረ. ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ ሶስት)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 49 የሴት ተጎጂዎች ቡድኖችች ውስጥ 1.5 ቡድኖች (3.06%) የሚሆኑት ይህን የጊዜ አማራጭ ደግፈዋል፡፡ ምክንያታቸውም አገሪቱ አሁን ለምታያቸው በማንነትን ላይ የተመሰረቱ ግጭቶች ዋና መነሻ ህገ-መንግስቱ ነው የሚል ነው፡፡

ሰንጠረዥ 63፡ 'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' የሴቶች ተጎጂዎች ቡድን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | የቡድን ብዛት | አማራጭ 1 'ከ1983 በፊት' | አማራጭ 2 'ከ1983 ጀምሮ' | አማራጭ 3 'ከ1987 ጀምሮ' | አማራጭ 4 'ከ2010 ጀምሮ' | አማራጭ 5 'ለክስ ከ1987፣ ለሌላ መረጃ ከተገኘበት' | ሌላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | | | | 1.5 | | 0.5 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | | | | | |
| 3 | አማራ | 7 | | 4 | 1 | 2 | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | | 1 | | 1 | | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | | | | 1 | | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | | | | 1 | | |
| 7 | ሀረሪ | 1 | | 0.5 | | | | 0.5 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 2 | 0.5 | | 2 | 9 | 0.5 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | | 1 | | | | |
| 10 | ሶማሌ | 3 | | 3 | | | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 0.5 | | 0.5 | 3 | 5 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | | | | 2 | | |
| 13 | ትግራይ | 5 | 1 | | | 2 | 1 | 1 |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 49 | 4.5 | 10 | 1.5 | 15.5 | 15 | 2.5 |

## II. የወንድ ተጎጂዎች ቡድን

## ሀ. ለክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለእውነት ማፈላለግ፣ ለእርቅ ማስፈንና ለማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ/ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ (አማራጭ አምስት)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖችች ውስጥ 12.5 ቡድኖች (ወይም 29.59%) የሚሆኑት የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ለክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ ማስፈንና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ' ሊተገበር ይገባል የሚለውን አማራጭ መርጠዋል፡፡

ይህን አማራጭ ከሰባት ክልሎች (ብቻ) የተሳተፉ ቡድኖች መርጠውታል፡፡ እነዚህም ኦሮሚያ ክልል (5.5 ቡድኖች)፣ (የቀድሞ) ደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል (2 ቡድኖች)፣ ድሬዳዋ (1 ቡድን)፣ ቤኒሻንጉል-ጉምዝ (1 ቡድን)፣ ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል (1 ቡድን)፣ ሀረሪ ክልል (1 ቡድን)፣ እንዲሁም ሲዳማ ክልል (1 ቡድን) ናቸው፣ ለዚህ የጠቀሷቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ላለንበት አገራዊ ምስቅልቅል አስተዋጾ ያደረገው ህገ-መንግስቱ ነው፣ ስለሆነም የክስ ሂደት ህገ-መንግስቱ ከጸደቀበት ጊዜ ሊጀምር ይገባል፣

- በክስ ጉዳይ ማስረጃ ማግኘት አዳጋች ስለሚሆን ከ1987 ዓ.ም በፊት የነበሩ ሰዎችን አግኝቶ በሕግ መጠየቅ አይቻልም፡
- ከ1987 በፊት ህገ-መንግስት አልነበረም፡ ከዛ በፊት የተፈጸሙት ጉዳዮችን አስመልክቶ ተጠያቂነት መመስረት ሊከብድ ይችላል፡
- እውነት ለማፈላለግ መረጃና ማስረጃ እስከተገኘ ወደ ኋላ ሊኬድ ይገባል፡
- ይህ አማራጭ ዘላቂ እርቅና ሰላም ለማምጣት፡ ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/በደሎች እንዳይደገሙ ለማድረግ፡ የዛሬውን ትውልድ በሰላም አብሮ እንዳይኖር ያደረጉ በታሪክ የተቋጠሩ ቂሞችን ፋይል ዘግቶ ለማለፍ - በጊዜ እና በሁኔታዎች መገደብ ሳያስፈልግ ቁስሎቹን በደንብ አጥቦ ለመዳን ያስችላል።

**ለ.** ከ2010 ዓ.ም **ጀምሮ (አማራጭ አራት)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ12 ቡድኖች (25.5%) የሚሆኑት የተደገፈ ሲሆን፡ አካባቢያዊ ስርጭቱም ስድሰት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም ትግራይ ክልል (2 ቡድኖች)፡ (የቀድሞ) ደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል (4 ቡድኖች)፡ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል (1 ቡድን)፡ በኦሮሚያ ክልል (1.5 ቡድኖች)፡ አፋር ክልል (0.5 ቡድን)፡ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል (1 ቡድን) ናቸው።

ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- በታሪክ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከባድና ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የተከሰተው፡ እንዲሁም ሰፋፊ ቁርሾዎች/ክፍተቶች የተፈጠሩት ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡
- ይህ የጊዜ ማዕቀፍ በዛሬው እድሜ የደረሰንባቸውን መጠነ-ሰፊ ጉዳዮች ለመሸፈን ያስችላል፡
- የሽግግር ፍትህ ስራው ከረጅም ዘመን ከጀመረ ትግበራው ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል፡ ያሁን ዘመን ፈተና ብቻውን በቂ ነው፡
- የድሮ ቁስሎችን በመነካካት ወጣቶችን ወደማይሆን ሀሳብ ማስገባት አያስፈልግም፡ ዘመን የጠገቡ ጠባሳዎች ካሉ ልንማርባቸው እንጂ እንደገና እያነሳን ልንቀሳቀስልባቸው አይገባም፡
- በማይጠቅመን ትላንት ላይ ጊዜያችንን ከመጨረስ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ በቅርብ ጊዜያት በተከሰቱ ችግሮች ላይ አተኩሮ ቢተገበር ተመራጭ ነው።

**ሐ.** ከ1983 ዓ.ም **ጀምሮ (አማራጭ ሁለት)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ10 ቡድኖች (21.27%) በሚሆኑት የተደገፈ ሲሆን፡ አካባቢያዊ ስርጭቱም ስድሰት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም አማራ ክልል (4 ቡድኖች)፡ ኦሮሚያ ክልል (2 ቡድኖች)፡ ሶማሌ ክልል (1.5 ቡድኖች)፡ (የቀድሞ) ደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል (1 ቡድን)፡ አፋር ክልል (0.5 ቡድን)፡ ጋምቤላ ክልል (1 ቡድን) ናቸው።

ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች ጠቅሰዋል።

- አሁን የምናየው አገራዊ ችግር መንስኤዎች በዋናነት የተፈጠሩት ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡
- ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የተፈጸሙ ወንጀሎች በአይነት አሰቃቂ፡ በብዛትም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው፡
- ወደ ኋላ ዘመን እንመልከት ቢባል መረጃም ሆነ ማስረጃ ማግኘት አስቸጋሪ የሆናል፡
- የክስ ሂደቱ ከ1983 ዓ.ም ቢጀምር አስፈላጊ ማስረጃዎች ሊገኙ ባይችሉ እንኳ ቢያንስ የተፈጸሙ በደሎች በእውነት አፈላላጊ ተቋማት ተለይተው ለህዝብ ውይይት እንዲቀርቡ ማድረግ ይቻላል፡

**መ.** ከ1983 ዓ.ም **በፊት የተፈጸሙትን ጥቅተተ መልኩ (አማራጭ አንድ)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ9 ቡድኖች (5.1%) በሚሆኑት የተደገፈ ሲሆን፣ አካባቢያዊ ስርጭቱም አምስት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም 3.5 ቡድኖች በኦሮሚያ ክልል፣ 3 ቡድኖች በትግራይ ክልል፣ 1 ቡድን በአማራ ክልል፣ 1 ቡድን (በቀድሞው) የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል፣ እንዲሁም 0.5 ቡድን በሶማሌ ክልል ናቸው።

ቡድኖቹ ሀሳባቸውን የሚደግፉ ምክንያቶችን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- የሀገሪቱ ቁስል የሚጀምረዉ ከ1983 ዓ.ም በፊት ነው፡ አለ የሚባልን ችግር ሁሉ ከሥረ-መሰረቱ በማየት የሽግግር ፍትህ ማምጣት ከተፈለገ ይህ የጊዜ እይታ ተገቢ ነው፡
- ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ወደ ኋላ በመሄድ በወሳኝ የታሪክ ኩነቶች ላይ ውይይት ማድረግ ይገባል፣ ለዚህም የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከ1983 ዓ.ም በፊት ያለውን ጊዜ ሊሸፍን ይገባል።
- በዚህ የጊዜ ማዕቀፍ ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተከስተዋል፣ ይህ ጊዜ ሁሉንም ጉዳዮች ለማየት ዕድል ይሰጣል፣ ከታሪክ ጋር አሉ የሚባሉትን ግጭቶችን ለመፍታት ያግዛል፣
- ለረጅም ዘመን ተጠያቂነት ስላልነበር ግጭቶች በተደጋጋሚ እንዲነሱ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፣ በዚህ የጊዜ ማዕቀፍ መሰረት ፍትህ ማስፈን ለዕርቅ በር ይከፍታል፣ ሁሉንም ወገን ያስደስታል።

## ሠ. ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ ሶስት)

ይህ የጊዜ አማራጭ በ3 ቡድኖች (6.38%) በሚሆኑት የተደገፈ ሲሆን፣ አካባቢያዊ ስርጭቱም ሶስት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም 2 ቡድኖች በአማራ ክልል፣ 1 ቡድን በኦሮሚያ ክልል፣ 1 ቡድን (በቀድሞው) የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል፣ እንዲሁም 1 ቡድን በሶማሌ ክልል ናቸው።

ቡድኖቹ ሀሳባቸውን የሚደግፉ ምክንያቶችን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- ህገ-መንግስቱ ከጸደቀበት ጊዜ መጀመር ከህጋዊነት መርህ፣ እንዲሁም ህገ-መንግስቱ እውቅና ከሰጣቸው መብቶች አንጻር ተገቢ ነው፡
- ይህ የጊዜ ማዕቀፍ ማስረጃና አጥፊዎችን በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል፣
- ከ1987 ዓ.ም በፊት ለተፈጸሙ ጥሰቶች አጥጋቢ ባይሆንም ምላሽ ተሰጥቷል፣
- ከዚህ የጊዜ ማዕቀፍ ርቆ ወደ ኋላ መጓዝ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ይሆናል፣ ምክንያታዊም አይደለም።

ሰንጠረዥ 64፡ 'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' የወንድ ተጎጂዎች ቡድን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | የቡድን ብዛት | አማራጭ 1 'ከ1983 በፊት' | አማራጭ 2 'ከ1983 ጀምሮ' | አማራጭ 3 'ከ1987 ጀምሮ' | አማራጭ 4 'ከ2010 ጀምሮ' | አማራጭ 5 'ለክስ ከ1987፣ ለሌላ መረጃ ከተገኘበት' | ሌላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | | | | | |
| 2 | አፋር | 1 | | 0.5 | | 0.5 | | |
| 3 | አማራ | 7 | 1 | 4 | 0 | 2 | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | | | | 1 | 1 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | | | | | 1 | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | | 1 | | | | |
| 7 | ሀረሪ | 1 | | | | | 1 | |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 3.5 | 2 | 1 | 1.5 | 5.5 | 0.5 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | | | | | 1 | |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 0.5 | 1.5 | 1 | | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 1 | 1 | 1 | 4 | 2 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ | 2 | | | | 1 | 1 | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ኢትዮጵያ | | | | | | | |
| 13 | ትግራይ | 5 | 3 | | | 2 | | |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 47 | 9 | 10 | 3 | 12 | 12.5 | 0.5 |

### III. የቅልቅል ቡድን

**ሀ. ለክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ ማስፈንና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ/ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ (አማራጭ አምስት)**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 96 የቅልቅል ቡድኖች ውስጥ 32.5 ቡድኖች (ወይም 33.85%) የሚሆኑት የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ለክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ ማስፈንና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ' ሊተገበር ይገባል የሚለውን አማራጭ መርጠዋል።

የዚህ የጊዜ አማራጭ አካባቢያዊ ስርጭት ስምንት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም ኦሮሚያ ክልል 11.5 ቡድኖች፣ (የቀድሞው) የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል 7 ቡድኖች፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 4 ቡድኖች፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 3 ቡድኖች፣ በአማራ ክልል 2 ቡድኖች፣ በትግራይ ክልል 2 ቡድኖች፣ በሲዳማ ክልል 1 ቡድን፣ በሀረሪ ክልል 1 ቡድን፣ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር 1 ቡድን ናቸው።

ቡድኖቹ ሀሳባቸውን የሚደግፉ ምክንያቶችን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- አሁን ያለው የአገሪቱ ችግር ዋናው መሠረቱ የ1987 ዓ.ም ሕገ-መንግሥት ነው፣ ብዙ ወንጀሎች እና ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተፈፀሙት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣
- አማራጩ ከህገ-መንግስት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት ያስችላል፣
- ለትልልቅ ክሶች የሕገ-መንግስት መሠረት መኖሩ አስፈላጊ ነው፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ/እውቅና የተደረገላቸው ሕገ-መንግስቱ ከፀደቀበት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣ ስለሆነም የክስ ጉዳይ ከዚህ መጀመሩ ሕጋዊ አግባብነት አለው፣
- ከ1987 ዓ.ም በፊት ለተፈጸሙ ጥሰቶች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ማስረጃ ማግኘት አዳጋች ነው፣ ከዚህ ዘመን መጀመሩ ተመራጭ ነው፣ መረጃና ማስረጃ የማግኘት እድልን ይጨምራል፣
- ከ1987 ዓ.ም በፊት ይጀመር ቢባል የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ ስለማይሰራ በብዙ የወንጀል ድርጊቶች አንፃር ለመተግበር ያስቸግራል፣
- አማራጩ ከ1987 ዓ.ም በፊት ያሉ አገራዊ ብሶቶች/ችግሮችን በእውነት ማፈላለግ፣ በእርቅና በማካካሻ ሥርዓት ለመፍታት ያስችላል፣ ይህም ለሕግ የበላይነት፣ ለዘላቂ ሰላም እና ለእኩልነት መስፈን ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፣
- አማራጩ ከ1987 ዓ.ም በፊት በአገረ-መንግስት ግንባታ ወቅት ተፈጸሙ የሚባሉ የመብት ጥሰቶችን በተመለከተ እውነትን በማፈላለግ ሃሰተኛ ትርክቶችን ለማረምና ለማስወገድ ይረዳል፣ ተንከባለው የመጡ ዝንፈቶችና ቁርሾዎች ቢኖሩ ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ ወደኋላ ሂዶ ጉዳዮቹን ለማየት እድል ይሰጣል፣
- አማራጩ ከቀረቡት ሁሉም አመራጮች ይበልጥ ተመራጭ ነው፣ ሁሉንም ያማከለ ነው።

**ለ. ከ1983 ዓ.ም በፊት የተፈጸሙትን ጥፋቶች መልኩ (አማራጭ አንድ)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ23 የቅልቅል ቡድኖች (23.95%) የተደገፈ ሲሆን፣ አካባቢያዊ ስርጭቱም ስምንት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም 11.5 ቡድኖች በኦሮሚያ ክልል፣ 3 ቡድኖች በቀድሞ ደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል፣ 2.5 ቡድኖች በትግራይ ክልል፣ 2 ቡድኖች በአማራ ክልል፣ 1 ቡድን በሀረሪ ክልል፣ 1 ቡድን በጋምቤላ፣ 2 ቡድኖች በአፋር ክልል ናቸው።

ቡድኖቹ ሀሳባቸውን የሚደግፉ ምክንያቶችን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- በሀገራችን የተከሰቱ የቆዩ የመብት ጥሰቶችና ውስብስብ ወንጀሎችን በመሸፈን ለችግሮች የማያዳግም መፍትሄ ለመስጠት ይረዳል፡
- ክስም እርቅም በጊዜ መገደብ የለበትም፡ ተከሳሽ የሚሆን ሰው በህይወት ባይኖር እንኳ ጉዳዩ ተመርምሮ ጥፋተኛ ከሆነ ጥፋተኝነቱ መረጋገጥ፡ ጥፋተኛ ካልሆነ ነጻ መሆኑ መታወቅ አለበት፡
- ጥሩውን ብቻ ሳይሆን መጥፎውንም ታሪክ በአግባቡ ለማወቅ ያግዛል፡ ህዝብ ከ1983 ዓ.ም በፊትም ቢሆን ሰፊ የመብት ጥሰት ተፈፅሞበታል፡ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ባለው ጊዜ ላይ ብቻ ማተኮር ለዚህ ህዝብ ፍትህ መንሳት ይሆናል፡
- በደርግ ጊዜ በደረሰ የመብት ጥሰት እስካሁን ደረስ ከነጉዳታቸው የሚኖሩ ዜጎች አሉ፡ ስለሆነም ማስረጃ እስከተገኘ ድረስ ከ1983 ዓ.ም በፊትም ለደረሰ ጥፋት ተጠያቂነት ሊኖር ይገባል፡
- አሁን ያለንበት የችግር ስንክሳር - ወደኋላ ከታሪክ የሚመመዝ ነው፡ ዛሬ የሚታዩት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከ1983 ዓ.ም በፊት የጀመሩ ናቸው፡ የሽግግር ፍትህ በየትኛውም ወቅት ቢሆን ለደረሰ የመብት ጥሰት ተገቢ ፍትህ መስጠት መቻል አለበት፡ ትክክለኛ የሽግግር ፍትህ ለመተግባር እና ወደ ፊት ለመጓዝ በደንብ ወደ ኋላ ዞሮ መመልከትና ያለፈውን ማጥራት ያስፈልጋል፡ ይህ አካሄድ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን የተሟላ እና ዘላቂ ያደርገዋል፡
- ምዕተ-ዓመታትን ያስቆጠሩ ችግሮች ተደራርበው ቆይተዋል፡ እውነተኛ ሰላምና ፍትህ ይረጋገጥ ከተባለ ችግርን ከስሩ ማጥራት ያስፈልጋል፡ የዛሬው ችግር ዛሬ የተወለደ ሳይሆን የቆየ እውነት እና ፍትህ የማጣት ችግር የወለደው ነው፡
- የሽግግር ፍትህ ዓላማው እውነትን ማውጣት እና ማህበረሰብን ከማህበረሰብ እና ሀገርን ከሀገር ማስታረቅ እስከሆነ ድረስ በጊዜ መገደብ አያስፈልገውም፡ እውነት ያለው የተቀበረው ትናንትና ውስጥ ነው የሚል አካል ካለ ሊወጣለት ይገባል እንጂ ያንተ እውነት ከቆይታው የተነሳ ሻግቷል/አልፎበታል ሊባል አይገባም፡
- የሽግግር ፍትህ የመጨረሻ ግብ አገራዊ መግባባት ለመፍጠር ነው፡ ስለሆነም ምንም ገደብ ሳይደረግበት ሁሉን ተበዳይ ነኝ የሚለውን ማካተት አለበት፡ ወደ ኋላ ተመልሶ ችግሮችን የምናይበት መነፅር መሆን መቻል አለበት፡ በመሆኑም በሁሉም ጊዜያት የነበሩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን መሸፈን ይኖርበታል።

**ሐ. ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ ሁለት)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ13.5 የቅልቅል ቡድኖች (14.06%) የተደገፈ ሲሆን፡ አካባቢያዊ ስርጭቱም ሰባት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም አማራ ክልል 5 ቡድኖች፡ ኦሮሚያ ክልል 0.5 ቡድን፡ ሶማሌ ክልል 2 ቡድኖች፡ ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል 3 ቡድኖች፡ አዲስ አበባ 1 ቡድን፡ ድሬዳዋ 1 ቡድን፡ (የቀድሞ) ደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል 1 ቡድን ናቸው።

ለዚህም የሚከተሉት ምክንያቶች ተጠቅሰዋል።

- በዘር፡ በብሔርና በሀይማኖት ግልፅ ክፍፍል የመጣው፡ ሀይማኖት እና ብሄር-ተኮር ጥቃቶች መፈፀም የጀመሩት፡ ተጠያቂነት የጠፋው፡ የአገሪቷን ቅርፅ የሚቀይር ሁኔታም የተፈጠረው ከ1983 በኋላ ነው፡ ስለሆነም አማራጩ በዚህ ዘመን የበዙ ብሔር-ተኮር ጥቃቶችንና ማንነትን መሠረት ያደረጉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በበለጠ ሁኔታ ለመሸፈን ያስችላል፡
- (ከ1983 ዓ.ም በፊት) ወደኋላ ተመልሶ ሰዎች የሚከሰሱበትን ስርዓት ማምጣት በጊዜ ሂደት የተረሱ ቁርሾዎችና በደሎች እንዲያገረሹ ያደርጋል፡ ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣል፡
- ከ1983 ዓ.ም በፊት የተፈጸሙ ጥፋቶችን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ መንገዶች አጥፊዎች እንዲጠየቁ ተደርጓል፡ ስለሆነም የሽግግር ፍትህ ትግበራው ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን ለማየት ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ባሉ ጥሰቶች ላይ ማተኮር አለበት፡

- የሽግግር ፍትህ ሂደት ማስረጃ ሊገኝባቸው በሚችሉ ጊዜያት በተፈጸሙ ጥሰቶች ላይ ማተኮር አለበት።

**መ. ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ ሶስት)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ10.5 (10.93%) በሚሆኑት የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ ሲሆን፣ አካባቢያዊ ስርጭቱም ስምንት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም 1.5 ቡድኖች በኦሮሚያ ክልል፣ 3 ቡድኖች (በቀድሞው) ደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል፣ 2 ቡድኖች በአማራ ክልል፣ 1 ቡድን በሶማሌ ክልል፣ 1 ቡድን በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ 1 ቡድን በሲዳማ ክልል፣ 1 ቡድን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ናቸው።

ቡድኖቹ ሀሳባቸውን የሚደግፉ ምክንያቶችን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- የኢትዮጵያ ችግሮች ምንጭ/መሰረቱ 1987 ዓ.ም ነው፣ ህገ-መንግስቱ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ሀገር በብሔር/ብሔረሰብ ተለያይቶ የከፋ ጉዳት ደርሷል፣ ሰዎች በነፃነት ተዘዋውረው በመሥራት መብታቸው ላይ ገደብ ተጥሏል፣ በዜጐች መካከል መጠራጠር ተፈጥሯል፣ ኢትዮጵያዊነት እንዲሸረሸር ሆኗል፣ ይህ አማራጭ ከዚህ ጊዜ ወዲህ የተበረዘውን የታሪክ ትርክት ለማስተካከል ያስችላል፣
- ከጊዜ አንጻር ቀረብ ያለ መሆኑ ከ1987 ዓ.ም በኋላ የጀመሩ ብዙ ጥሰቶችን አጥርቶ ለመሸፈን ያስችላል፣ ተጠያቂነትን ለማስፈን ይረዳል፣
- የቆዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ ቀደም ባለው ዘመን የፈፀሙት ሰዎች በብዛት ስለሌሉ እና መረጃም ስለማይገኝ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከ1987 ዓ.ም እንዲጀምር ማድረግ ይመረጣል፣
- ያለጊዜ ገደብ ሁሉንም ጉዳዮች ወደኋላ ሄዶ በሽግግር ፍትህ ሂደት ማካተት እንደ ሀሳብ ጥሩ ቢሆንም ሊተገበር የሚችል አይደለም፣ ረጅም ጊዜና ሰፊ ሀብት ይጠይቃል፣ ኢኮኖሚው ይህን መሸከም አይችልም፣
- የሽግግር ፍትህ እንደስሙ በሽግግር ላይ የሚያተኩር ነው፣ የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ነው፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉንም ጉዳይ በተጨባጭ ማዳረስ አይቻልም።
- ከጊዜ፣ ከሀብት፣ ከማስረጃ አንጻር ሲታይ ይህ የጊዜ ማዕቀፍ ለሽግግር ፍትህ ዓላማ ይበልጥ ተመራጭ ነው፣

**ሠ. ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ አራት)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ9.5 የቅልቅል ቡድኖች (9.89%) በሚሆኑት የተደገፈ ሲሆን፣ አካባቢያዊ ስርጭቱም አራት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም 4.5 ቡድኖች በትግራይ ክልል፣ 3 ቡድኖች (በቀድሞ) የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል፣ 1 ቡድን በኦሮሚያ ክልል፣ 1 ቡድን ቢጋምቤላ ክልል ናቸው።

ቡድኖቹ ሀሳባቸውን የሚደግፉ ምክንያቶችን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- ሀገር ወደለየለት የግጭት ሁነት የገባው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣
- በዘመን ወደኋላ በሄድን ቁጥር ጉዳዮች እየሰፉ እና እየተወሳሰቡ ይመጣሉ፣ ማስረጃ ላይገኝም ይችላል፣ ከቅርብ ጊዜ መጀመር በቂ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል፣
- ለሽግግር ፍትህ ዓላማ በጣም ወደ ኋላ የሚሄድ የጊዜ ማዕቀፍ ችግር መፍታቱ ቀርቶ ሌላ ችግር ሊወልድ ይችላል፣ በቀደሙ ጊዜያት በነበሩ ታሪኮችና ጉዳዮች ላይ በቀላሉ መግባባት ያዳግታል፣ ከረጅም ጊዜ በፊት የተፈፀሙ ጥሰቶችን በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ማስተናገድ ከባድ ከመሆኑም በላይ ለሌላ ቅራኔ የሚያጋልጥ ይሆናል፣
- በዘመን ብዙ ወደኋላ መጓዝ የራሱ ውስብስብ ችግሮችን ይዞ ይመጣል፣ ተበዳይ ነኝ የሚል ሰው ብዙ ነው፣ ታሪካዊ አረዳዶች/ትውስታዎች የተዛቡ/የተበረዙ የመሆን እድላቸው የሰፋ ነው፣ በሽግግር ፍትህ የሁሉንም ማህበረሰብ ችግሮች የማዳረስ እድል እጅግ ጠባብ ነው፣
- በዘመን ወደኋላ ብዙ መጓዝ ለሽግግር ፍትህ ትግበራው ረጅም ሂደትን ይፈልጋል፣ በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ አይቻልም፣ ተፈፃሚ የመሆን እድሉ ዜሮ ነው፣

- ሂደቱ በጣም ወደኋላ የሚለጠጥ ከሆነ ዛሬ ላለንበት ወቅት ይበልጥ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ትኩረት እንዳይሰጣቸው፣ ሂደቱም ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡ ህዝብ በዋናነት የሚመርጠው የቅርብ ጊዜ ችግሩ እንዲፈታለት ነው፣
- ከ2010 ዓ.ም መጀመር ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ ውስን የጊዜ ወሰን በመስጠት ፈጣን የሽግግር ጊዜ ፍትህ ሂደት እንዲኖር ያደርጋል።

## ረ. (ሌላ) አማራጭ

ይህ የጊዜ አማራጭ በ6 ቡድኖች (6.25%) በሚሆኑት የተደገፈ ሲሆን፡ አካባቢያዊ ስርጭቱም አማስት ክልሎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም 1 ቡድን በትግራይ ክልል፡ 2 ቡድኖች በአማራ ክልል፡ 1 ቡድን በሶማሌ ክልል፡ 1 ቡድን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፡ እንዲሁም 1 ቡድን በኦሮሚያ ክልል ናቸው።

ቡድኖቹ ሀሳባቸውን የሚደግፉ የተለያዩ (አንዳንዴም አብረው የማይሄዱ) ምክንያቶችን አቅርበዋል።

*ሰንጠረዥ 65፡ 'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' የቅልቅል ቡድን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ*

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | የቡድን ብዛት | አማራጭ 1 'ከ1983 በፊት' | አማራጭ 2 'ከ1983 ጀምሮ' | አማራጭ 3 'ከ1987 ጀምሮ' | አማራጭ 4 'ከ2010 ጀምሮ' | አማራጭ 5 'ለክስ ከ1987፣ ለሌላ መረጃ ከተገኘበት' | ሌላ[63] |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | | 1 | 1 | | 3 | 1 |
| 2 | አፋር | 2 | 2 | | | | | |
| 3 | አማራ | 13 | 2 | 5 | 2 | | 2 | 2 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | | | | | 4 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | | 1 | | | 1 | |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 1 | | | 1 | | |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 1 | | | | 1 | |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 11.5 | 0.5 | 1.5 | 1 | 11.5 | 1 |
| 9 | ሲዳማ | 2 | | | 1 | | 1 | |
| 10 | ሶማሌ | 4 | | 2 | 1 | | | 1 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 3 | 1 | 3 | 3 | 7 | |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | | 3 | 1 | | | |
| 13 | ትግራይ | 10 | 2.5 | | | 4.5 | 2 | 1 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 96 | 23 | 13.5 | 10.5 | 9.5 | 32.5 | 6 |

# IV. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን

'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች የትኩረት ውይይት ያደረጉ ሲሆን - በቀረቡ ሁሉም አማራጮች ላይ አቋማቸውን በተለያየ መንገድ ገልፀዋል። አቋም የወሰዱበትን አማራጭ ለመደገፍ ዝርዝር ምክንያቶችን ሰጥተዋል። እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

## ሀ. ለክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ ማስፈንና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ (አማራጭ አምስት)

[63] 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም።

ይህ የጊዜ አማራጭ በ9.5 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች (39.58%) በሚሆኑት የተደገፈ ሲሆን፡ አካባቢያዊ ስርጭቱም ስድስት ክልሎችን ያቀፈ ነው፡፡ እነዚህም 5 ቡድኖች በኦሮሚያ ክልል፡ 1 ቡድን (በቀድሞ) የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል፡ 1 ቡድን በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል፡ 1 ቡድን በአማራ ክልል፡ 0.5 ቡድን በትግራይ ክልል፡ 1 ቡድን በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ናቸው፡፡

ቡድኖቹ ለዚህ ምልከታቸው የሚከተሉትን ምክንያቶች ጠቅሰዋል፡፡

- ሂደቱ ከ1987 ዓ.ም ቢጀምር የምርመራ ስራዎችን በሚገባ ለመስራትና ማስረጃ ለማደራጀት ያስችላል፡ በክስ ጉዳይ አጥፊዎችን ተጠያቂ ለማድረግ ብዙ ዘመን ወደኋላ በመሄድ መፈፀም አይቻልም፡ ስለሆነም ለክስ ዓላማ የቀረበው አማራጭ ተገቢ ነው፡
- የህገ-መንግስት መሠረት መኖር ለክስ ጉዳይ እንዲሁም ለሌሎች የሽግግር ፍትኅ አላባዎች የተሻለ እድል ይፈጥራል፡
- ይህ የጊዜ ማዕቀፍ ከበደል ትርክቶች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ሁሉንም ፍላጎቶችን ለማስተናገድ ያመቻል፡ በተለይም እውነት ለማውጣትና ለተፈፀመሙ ጥሰቶች እውቅና ለመስጠት ሰፊ እድል ይሰጣል፡፡

## ለ. (ሌላ) አማራጭ

ይህ የጊዜ አማራጭ በ6 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች (25%) የተደገፈ ሲሆን፡ አካባቢያዊ ስርጭቱም አራት ክልሎችን ያቀፈ ነው፡፡ እነዚህም 2 ቡድኖች በትግራይ ክልል፡ 2 ቡድኖች በአማራ ክልል፡ 1 ቡድን (በቀድሞ) ደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል፡ እና 1.5 ቡድን በኦሮሚያ ክልል ናቸው፡፡

የቀረቡት (የተለያዩ/አብረው የማይሄዱ) አማራጮች እና የተሰጡ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ለሽግግር ፍትህ ትግበራ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ ተገቢ አይደለም፡ መረጃ/ማስረጃን እስካለ ድረስ አስፈላጊ የሽግግር ፍትህ ስልቶችን እንደየአግባብነቱ መተግበር የተሻለ ነው፡
- ለክስ ጉዳይ ከ1983 ዓ.ም ዓ.ም ጀምሮ፡ ለእርቅና እውነት ማፈላለግ ስራ ደግሞ ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ ቢሆን አካታች ፖሊሲ ለመቅረጽ ያስችላል፡ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የተፈጸሙ መታለፍ የሌለባቸው በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አሉ፡
- ለክስ ጉዳይ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ፡ ለሌላ ጉዳይ መረጃ/ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ መሄድ ተመራጭ ነው፡
- ለክስ ጉዳይ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ (ምርጫውን ተከትሎ የተፈጸሙ በርካታ ጥሰቶች ስላሉ)፡ እንዲሁም ለሌሎች ጉዳዮች ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ ቢካተት ተመራጭ ነው፡፡

## ሐ. ከ1983 ዓ.ም በፊት የተፈጸሙትን ጥቅተተ መልኩ (አማራጭ አንድ)

ይህ የጊዜ አማራጭ በ5 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች (20.83%) የተደገፈ ሲሆን፡ አካባቢያዊ ስርጭቱም አምስት ክልሎችን ያቀፈ ነው፡፡ እነዚህም 1 ቡድን በትግራይ ክልል፡ 1 ቡድን በሶማሌ ክልል፡ 1 ቡድን በአፋር ክልል፡ 1 ቡድን (በቀድሞ) የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል፡ እንዲሁም 1 ቡድን በጋምቤላ ክልል ናቸው፡፡

ቡድኖቹ ሀሳባቸውን የሚደግፉ ምክንያቶችን እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

- አብዛኛው የኢትዮጵያ ችግር መነሻው ከታሪክ አረዳድ የሚመነጭ ነው፡ ዛሬ ላይ ብዙ ህዝብ እሮሮ እያሰማ የቀጠለ እንደመሆኑ መጠን በዘመን ወደኋላ ሄዶ ጉዳዮችን መፈተሽ ተገቢ ነው፡
- ዋናው ትኩረት ክስ ላይ ሳይሆን የታሪክ ስብራቶችን በመጠገን ላይ መሆን አለበት፡ ለደረሱ በደሎች እውቅና መስጠት፡ መተማመን እና ወደዚያ ላለመመለስ ቃል መግባት ያስፈልጋል፡
- ከ1983 ዓ.ም በፊት ያለውን ጊዜ ተመራጭ የሚያደርገው የሚያመጣው retributive effect ብቻ ሳይሆን ለጥሰቶች እውቅና የሚሰጥበትን እድልም ስለሚፈጥር ነው፡፡

**መ. ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ ሁለት)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ1.5 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች (6.25%) በሚሆኑት ብቻ የተደገፈ አማራጭ ነው።

**ሠ. ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ ሶስት)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ1 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን (4.1%) በሚሆኑት ብቻ የተደገፈ አማራጭ ነው።

**ረ. ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ (አማራጭ አራት)**

ይህ የጊዜ አማራጭ በ0.5 ቡድን (2.08%) ብቻ የተደገፈ አማራጭ ነው።

ሰንጠረዥ 66፡ 'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' - የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ሀገር-አቀፍ እና ክልል-አቀፍ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | የቡድን ብዛት | አማራጭ 1 'ከ1983 በፊት' | አማራጭ 2 'ከ1983 ጀምሮ' | አማራጭ 3 'ከ1987 ጀምሮ' | አማራጭ 4 'ከ2010 ጀምሮ' | አማራጭ 5 'ለክስ ከ1987፣ ለሌላ መረጃ ከተገኘበት' | ሌላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | | | | | | |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | | | | | |
| 3 | አማራ | 5 | | 1 | 1 | | 1 | 2 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | | | | | 1 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | | | | | 1 | |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | | | | | |
| 7 | ሀረሪ | | | | | | | |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | | 0.5 | | | 5 | 1.5 |
| 9 | ሲዳማ | | | | | | | |
| 10 | ሶማሌ | 1 | 1 | | | | | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 3 | 1 | | | | 1 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | | | | | | | |
| 13 | ትግራይ | 4 | 1 | | | 0.5 | 0.5 | 2 |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 24 | 5 | 1.5 | 1 | 0.5 | 9.5 | 6.5 |

### 6.7.3. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ በሀገር-አቀፍ ደረጃ በቀረቡት መነሻ አማራጮች ላይ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ 69.5 ቡድኖች (ወይም 32.17%) የሆኑት 'ለክስ ዓላማ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለሌላ ጉዳይ መረጃ/ማስረጃ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ይተግበር' የሚለውን አማራጭ መርጠዋል። ስለሆነም ይህ አማራጭ በተሳታፊዎች ከፍተኛውን ድጋፍ ያገኘ አማራጭ ሆኗል።

በመቀጠልም ከ216 ቡድኖች ውስጥ በ41.5 ቡድኖች (ወይም 19.21%) ከፍተኛ የተሳታፊዎች ድጋፍ ያገኘው አማራጭ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ከ1983 ዓ.ም በፊት' ጀምሮ ባለው የጊዜ ማዕቀፍ ላይ ይተግበር የሚለው አማራጭ ነው።

በሶስተኛ ደረጃ ከ216 ቡድኖች ውስጥ በ37.5 ቡድኖች (17.36%) ድጋፍ ያገኘው ሀሳብ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ' ባለው የጊዜ ማዕቀፍ ላይ ይተገበር የሚለው አማራጭ ነው።

በተቀራራቢ ቁጥር - በአራተኛ ደረጃ ከ216 ቡድኖች ውስጥ በ35 ቡድኖች (16.2%) ድጋፍ ያገኘው ሀሳብ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ' ባለው የጊዜ ማዕቀፍ ላይ ይተግበር የሚለው ነው።

በመጨረሻም የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ' ባለው የጊዜ ማዕቀፍ ላይ ይተግበር የሚለው ሃሳብ በ16 ቡድኖች (7.4%) የተደገፈ ሲሆን፣ 15.5 ቡድኖች (7.17%) ደግሞ ከሁሉም የተለየ 'ሌላ አማራጭ' አቅርበዋል።

**ግኝቱ ውይይቶቹ ከተካሄዱባቸው ክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች አንጻር ሲተነተን**

ከላይ የተመለከተው ግኝት ውይይቶቹ ከተካሄዱባቸው ክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች አንጻር ሲታይ፣

- በአዲስ አባባ ከተማ መስተዳድር፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በሀረሪ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ እንዲሁም (በቀድሞው) የደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ለክስ ዓላማ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለሌላ ጉዳይ መረጃ/ማስረጃ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ይተግበር' የሚለው አማራጭ ከፍተኛ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፣
- በአፋር ክልል 'ከ1983 ዓ.ም በፊት' የሚለው አማራጭ፣ በአማራ እና በሶማሌ ክልል 'ከ1983 ጀምሮ' የሚለው አማራጭ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 'ከ1983 ጀምሮ' እና 'ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ' የሚሉት አማራጮች፣ እንዲሁም በጋምቤላ ክልል 'ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ' የሚለው አማራጭ በቀዳሚነት ድጋፍ አግኝተዋል።

**ግኝቱ ከቡድኖች ስብጥር አንጻር ሲተነተን**

አጠቃላይ አገራዊ ሰዕሉን ከቡድኖች ስብጥር አንጻር የተመለከትነው እንደሆነ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ለክስ ዓላማ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለሌላ ጉዳይ መረጃ/ማስረጃ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ይተግበር' የሚለው አማራጭ የሁሉም ቡድኖች የመጀመሪያ ምርጫ ሆኗል።

ነገር ግን ከስር በተመለከተው ሰንጠረዥ ላይ እንደሚታየው ሌሎች አማራጮችን በተመለከተ ሰፊ ልዩነት አለ። የሴትና ወንድ ተጎጂዎች ቡድኖች አቋም ተቀራራቢ ቢሆንም ከሌሎቹ ቡድኖች ፍላጎቶችና እይታ የተለየ ነው። ስለሆነም የሚወጣው ፓሊሲ ይህን ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይገባል።

በተጨማሪም አገራዊ ማጠቃለያው የቡድኖችን ብዛት መሰረት አድርጎ የተሰላ በመሆኑና በምጥጥን የቅልቅል ቡድኖች ከሌሎቹ ቡድኖች በከፍተኛ ቁጥር የሚበልጡ በመሆኑ - በአጠቃላዩ አገራዊ የቡድኖች ምልከታ ላይ የራሱን ተጽእኖ ያሳደረ መሆኑን ሊታወቅ ይገባል። ከዚህ አንፃር የሚቀረፀው ፓሊሲ ይህን የቡድኖች ቁጥር ምጥጥን ግምት ውስጥ ባካተተ መልኩ የሚቀረፅ መሆን ይኖርበታል።

**ሀ. በሀገር-አቀፍ ደረጃ በአብዛኛዎቹ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፣ - 'ለክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ ማስፈንና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ/ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ' - ምክንያቶች**

ይህ አማራጭ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 216 ቡድኖች ውስጥ የ69.5 ቡድኖችን ድጋፍ በማግኘት በቀዳሚነት የተመረጠ ሲሆን፣ ተሳታፊዎች ይህን አቋም ለመደገፍ የሰጧቸው ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- አሁን ያለው የአገሪቱ ችግር ዋናው መሠረቱ የ1987 ዓ.ም ሕገ-መንግሥት ነው፣ ብዙ ወንጀሎች እና ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተፈፀሙት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣
- ብዙዎቹ አገራዊ ችግሮች/ምስቅልቅሎች ከህገ-መንግስቱ መቀረፅና መተግበር ጋር ተያይዘው የሚነሱ በመሆኑ ለክስ ጉዳዮች ይህ የጊዜ ማዕቀፍ ተገቢ ነው፣

- ከ1987 ዓ.ም በፊት ለተፈጸሙ ጥሰቶች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ማስረጃ ማግኘት አዳጋች ነው፡ ከ1987 በፊት የነበሩ ሰዎችን አግኝቶ በሕግ መጠየቅ ሊከብድ ይችላል፡ ስለሆነም ከዚህ ዘመን መጀመሩ መረጃና ማስረጃ የማግኘት እድልን ይጨምራል፡
- ከ1987 ዓ.ም በፊት ይጀመር ቢባል የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ ስለማይሰራ በብዙ የወንጀል ድርጊቶች አንፃር ለመተግበር ያስቸግራል፡
- ለትልልቅ ክሶች የሕገ-መንግስት መሠረት መኖር አስፈላጊ ነው፡ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ/እውቅና የተደረገላቸው ሕገ-መንግስቱ ከፀደቀበት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡ ስለሆነም የክስ ጉዳይ ከዚህ መጀመሩ ሕጋዊ አግባብነት አለው፡
- ለእውነት ማፈላለግ፡ እርቅና ሌሎች የሽግግር ፍትህ ጉዳዮች አተገባበር ወደኋላ በመሄድ ተገቢነት ያላቸው ጥያቄዎች ከሚነሱበት ዘመን ጀምሮ ያለውን እውነት መፈለግ/መመስረት ይገባል፡ ይህም አሉ የሚባሉ ቅራኔዎችን ለመፍታት ያስችላል፡ የአገሪቱ የአለመግባባት ምንጮች ከዳግማዊ ምኒሊክ ዘመነ-መንግስት አንስቶ ሊመዘዙ የሚችሉ በመሆኑ ይህ የጊዜ ማዕቀፍ ሳንፈጠር ጀምሮ ተከስተዋል የሚባሉ የማያግባቡ ክስተቶች፡ ታሪኮች እና የቁርሾ መነሻዎች ከስር ከመሰረት በማየት እውነትን ለመፈለግ እና ለመመስረት ያስችላል።
- ይህ አማራጭ ዘላቂ እርቅና ሰላም ለማምጣት፡ ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/በደሎች እንዳይደገሙ ለማድረግ፡ ሃሰተኛ ትርክቶችን ለማረምና ለማስወገድ፡ የዛሬውን ትውልድ በሰላም አብሮ እንዳይኖር ያደረጉ በታሪክ የተቋጠሩ ቂሞችን ፋይል ዘግቶ ለማለፍ - በጊዜ እና በሁኔታዎች መገደብ ሳያስፈልግ ቁስሎቹን በደንብ አጥቦ ለመዳን ያስችላል።
- አማራጩ ከ1987 ዓ.ም በፊት ያሉ አገራዊ ብሶቶችን/ችግሮችን በእውነት ማፈላለግ፡ በእርቅና በማካካሻ ሥርዓት ለመፍታት ያስችላል፡
- አማራጩ ከቀረቡት ሁሉም አማራጮች ይበልጥ ተመራጭ ነው፡ ሁሉንም ያማከለ ነው።

**ለ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፦ 'ከ1983 ዓ.ም በፊት የተፈጸሙትን ጥሰቶች መልኩ' - ምክንያቶች**

ይህ አማራጭ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ የ41.5 ቡድኖችን ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፡ ተሳታፊዎች ይህን አቋም ለመደገፍ የሰጧቸው ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- አሁን ያለንበት የችግር ሰንክሳር - ወደኋላ - ከታሪክ የሚመመዝ ከጥንት ጀምሮ የወረደ ነው፡ ዛሬ የሚታዩት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከ1983 ዓ.ም በፊት የጀመሩ ናቸው፡ የሽግግር ፍትህ በየትኛውም ወቅት ቢሆን ለደረሰ የመብት ጥሰት ተገቢ ፍትህ መስጠት መቻል አለበት፡ የተደበቁ እውነቶች ካልወጡ ከችግር አዙሪት መውጣት አይቻልም፡ የኖሩ ቁስሎች በጊዜ ሳይገደቡ መታጠብ፡ መታከም፡ መፈወስ አለባቸው።
- ትክክለኛ የሽግግር ፍትህ ለመተግባር እና ወደ ፊት ለመጓዝ በደንብ ወደ ኋላ ዞሮ መመልከትና ያለፈውን ማጥራት ያስፈልጋል፡ ይህ አካሄድ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን የተሟላ እና ዘላቂ ያደርገዋል፡
- የአገሪቱ ቁስል የሚጀምረዉ ከ1983 ዓ.ም በፊት ነው፡ ምዕተ-ዓመታትን ያስቆጠሩ ችግሮች ተደራርበው ቆይተዋል፡ እውነተኛ ሰላምና ፍትህ ይረጋገጥ ከተባለ ወደ ኋላ በመሄድ በወሳኝ የታሪክ ኩነቶች ላይ ውይይት ማድረግ፡ ችግርን ከስሩ ማጥራት ያስፈልጋል፡
- ባለፉት (ረጅም) ዘመናት የተፈፀሙ በደሎችን በአግባቡ መፍታትና መፍትሄ መስጠት ለአሁኑ ሆነ ለሚመጣው ትውልድ አስተዋፅኦዉ እጅግ ከፍ ያለ ነው፡
- የሽግግር ፍትህ ዓላማው እውነትን ማውጣት እና ማህበረሰብን ከማህበረሰብ እና ሀገርን ከሀገር ማስታረቅ እስከሆነ ድረስ በጊዜ መገደብ አያስፈልገውም፡ እውነት ያለው የተቀበረው ትናንትና ውስጥ ነው የሚል አካል ካለ ሊወጣለት ይገባል እንጂ ያንተ እውነት ከቆይታው የተነሳ ሻግቷል/አልፎበታል ሊባል አይገባም፡

- ህዝብ ከ1983 ዓ.ም በፊትም ቢሆን ሰፊ የመብት ጥሰት ተፈፅሞበታል፡ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ባለው ጊዜ ላይ ብቻ ማተኮር ለዚህ ህዝብ ፍትህ መንሳት ይሆናል፡
- ከ1983 ዓ.ም በፊት ጀምሮ የነበሩ ጉዳዮችን ማየት - ምርመራ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን ለማግኘት አዳጋች ሊያደርገው ይችላል፡ ቢያንስ ግን ለተፈፀሙ ወንጀሎች እና የመብት ጥሰቶች እውቅና በመስጠት ህብረተሰቡ እንዲማርባቸው ማድረግ ይገባል፡
- ለረጅም ዘመን ተጠያቂነት ስላልነበር ግጭቶች በተደጋጋሚ እንዲነሱ ምክንያት ሆኖ ቀይቷል፡ በዚህ የጊዜ ማዕቀፍ መሰረት ፍትህ ማስፈን ለዕርቅ በር ይከፍታል፡ ሁሉንም ወገን ያስደስታል፡
- በደርግ ጊዜ በደረሰ የመብት ጥሰት እስካሁን ደረስ ከነጉዳታቸው የሚኖሩ ዜጎች አሉ፡ ስለሆነም ማስረጃ እስከተገኘ ድረስ ከ1983 ዓ.ም በፊትም ለደረሰ ጥፋት ተጠያቂነት ሊኖር ይገባል፡
- ዋናው ትኩረት ክስ ላይ ሳይሆን የታሪክ ስብራቶችን በመጠገን ላይ መሆን አለበት፡ ለደረሱ በደሎች እውቅና መስጠት፡ መተማመን እና ወደዚያ ላለመመለስ ቃል መግባት ያስፈልጋል፡
- የአፋር እና ሶማሌ ማህበረሰቦች ውስብስብ ግንኙነት ዘመናት ያስቆጠረ ነው፡ ችግሮቹን በትክክል ለመፍታት ወደ ኋላኛው ጊዜ መመለስና ከግጭቶቹ ታሪካዊ መሰረት መጀመር አለበት።

**ሐ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡- 'ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ' - ምክንያቶች**

ይህ አማራጭ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ የ37.5 ቡድኖችን ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፡ ተሳታፊዎች ይህን አቋም ለመደገፍ የሰጧቸው ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- በዘመን ወደኋላ በሄድን ቁጥር ጉዳዮች እየሰፉ እና እየተወሳሰቡ ይመጣሉ፡ ማስረጃም ላይገኝ ይችላል፡ ከቅርብ ጊዜ መጀመር በቂ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል፡
- ከ2010 ዓ.ም መጀመር ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ ውስን የጊዜ ወሰን በመስጠት ፈጣን የሽግግር ጊዜ ፍትህ ሂደት እንዲኖር ያደርጋል፡
- ያለፈን ነገር መነካካት የተረሳ ቁስል እና ህመም ማስታወስ ይሆናል፡ ሀገርን እና ህዝብን ወደ ባሰ ሁኔታ ሊከት ይችላል፡ ወጣቶችን ወደማይሆን ሀሳብ ማስገባት አያስፈልግም፡ ዘመን የጠገቡ ጠባሳዎች ካሉ ልንማርባቸው እንጂ እንደገና እያነሳን ልንቀሳሰልባቸው አይገባም፡
- ለሽግግር ፍትህ ዓላማ በጣም ወደ ኋላ የሚሄድ የጊዜ ማዕቀፍ ችግር መፍታቱ ቀርቶ ሌላ ችግር ሊወልድ ይችላል፡ በቀደሙ ጊዜያት በነበሩ ታሪኮችና ጉዳዮች ላይ በቀላሉ መግባባት ያዳግታል፡ ከረጅም ጊዜ በፊት የተፈፀሙ ጥሰቶችን በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ማስተናገድ ከባድ ከመሆኑም በላይ ለሌላ ቅራኔ የሚያጋልጥ ይሆናል፡
- ተበዳይ ነኝ የሚል ሰው ብዙ ነው፡ ታሪካዊ አረዳዶች/ትውስታዎች የተዛቡ/የተበረዙ የመሆን እድላቸው የሰፋ ነው፡ በሽግግር ፍትህ የሁሉንም ማህበረሰብ ችግሮች የማዳረስ እድል እጅግ ጠባብ ነው፡
- የሕግ የበላይነት የተዳከመውና በርካታ ግጭቶች የተከሰቱት ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡ ስለሆነም ትኩረቱ በዚህ ዘመን በተፈፀሙ አሰቃቂ ጥሰቶች ላይ መሆን አለበት፡
- በታሪክ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከባድና ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የተከሰተው፡ እንዲሁም ሰፋፊ ቁርሾዎች/ክፍተቶች የተፈጠሩት ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡ የሽግግር ፍትህ ከዚህ ጊዜ ቢጀምር ማስረጃዎችን በበቂ መጠን እና ጥራት ለማግኘት ይቻላል፡ ጊዜው ወደኋላ በራቀ ቁጥር ማስረጃ ማግኘት የተወሳሰበ ይሆናል፡
- በኋላኛው ዘመን ኩነቶች ላይ አብዝተን ባተኮርን መጠን አሁኑ ፊታችን ላይ የቀመውን ግዙፍ ችግር ለመፍታት የምንቸገርበትን ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡ በማይጠቅመን ትላንት ላይ ጊዜያችንን ከመጨረስ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ በቅርብ ጊዜያት በተከሰቱ ችግሮች ላይ አተኩሮ ቢተገበር ተመራጭ ነው፡ ሂደቱን

ወደኋላ መለጠዋ ዛሬ ላለንበት ወቅት ይበልጥ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ትኩረት እንዳይሰጣቸው፣ ሂደቱም ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፣

- ሂደቱ ከ2010 ዓ.ም ቢጀምር የሽግግር ፍትህን ዓላማ በቶሎ ለማሳካት ያግዛል፣ የፍትህ ፍሬዎችን በፍጥነት ማየት የሚቻልበት ሁነት ይፈጠራል፣ አሁን ላለው ማሕበረሰብ በቀጥታ ተደራሽ ያደርገዋል፣
- የሽግግር ፍትህ ስራው ከረጅም ዘመን ከጀመረ ትግበራው ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል፣
- አሁን ያለው ትውልድ መዳን አለበት፣ እስካሁን ያለፉ ስርአቶችን ስንተችና ሀላፊ ስናደርግ ቆይተናል፣ አሁን የተሻለ የሚሆነው ወደራሳችን ማየት፣ ራስን በራስ መተቸትና ራስን ማረም ነው፣ ለዚህ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ያለው የጊዜ ማዕቀፍ ይበልጥ ተመራጭ ነው፣ በዛሬው እድሜ የደረሰንባቸውን መጠነ-ሰፊ ጉዳዮች ለመሸፈን ያስችላል፣
- በትግራይ ጦርነት በርካታ የሰብአዊ መብት ጥሰት የተፈፀመውና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ የተፈናቀለው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ስለሆነ ጊዜውን ተመራጭ ያደርገዋል።

***መ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡- 'ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ' - ምክንያቶች***

*ይህ አማራጭ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ የ35ቡድኖችን ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፣ ተሳታፊዎች ይህን አቋም ለመደገፍ የሰጧቸው ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።*

- ከማንነት ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ግድያዎች፣ ማፈናቀሎች፣ ዘረፋዎች፣ የብሄር ክፍፍል፣ ድንበር መከለል፣ ሀይማኖትና ብሄር-ተኮር ጥቃቶች በስፋት መታየት የጀመሩት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣ ስለሆነም የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከዚህ ጊዜ ሊጀምር ይገባል፣
- ተጠያቂነት የጠፋው፣ የአገሪቷን ቅርፅ የሚቀይር ሁኔታ የተፈጠረው ከ1983 ዓ.ም በኋላ ነው፣ አማራጩ በዚህ ዘመን የበዙ ብሔር-ተኮር ጥቃቶችንና ማንነትን መሠረት ያደረጉ የሙብት ጥሰቶችን በበለጠ ሁኔታ ለመሸፈን ያስችላል፣
- ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የተፈጸሙ ወንጀሎች በአይነት አስቃቂ፣ በብዛትም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው፣
- (ከ1983 ዓ.ም በፊት) ወደኋላ ተመልሶ ሰዎች የሚከሰሱበትን ስርዓት ማምጣት በጊዜ ሂደት የተረሱ ቁርሾዎችና በደሎች እንዲያገረሹ ያደርጋል፣ ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣል፣
- ከ1983 በፊት የተፈጸሙ ጥፋቶችን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ መንገዶች አጥፊዎች እንዲጠየቁ ተደርጓል፣ ስለሆነም የሽግግር ፍትህ ትግበራው ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን ለማየት ከ1983 ወዲህ ባሉ ጥሰቶች ላይ ማተኮር አለበት፣
- በሁሉም ዘመን የተፈፀመ ጥሰት ይታይ ቢባል የማስረጃ፣ የጊዜና የገንዘብ እጥረት ያጋጥማል፣ ይህም ዓላማው እንዳይሳካ ያደርገዋል፣ የሽግግር ፍትህ ሂደት ማስረጃ ሊገኝባቸው በሚችሉ ጊዜያት በተፈጸሙ ጥሰቶች ላይ ማተኮር አለበት፣
- የክስ ሂደቱ ከ1983 ዓ.ም ቢጀምር አስፈላጊ ማስረጃዎች ሊገኙ ባይችሉ እንኳ ቢያንስ የተፈጸሙ በደሎች በእውነት አፈላላጊ ተቋማት ተለይተው ለህዝብ ውይይት እንዲቀርቡ ማድረግ ይቻላል።

***ሠ. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ፡- 'ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ' - ምክንያቶች***

*ይህ አማራጭ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች ውስጥ የ16 ቡድኖችን ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፣ ተሳታፊዎች ይህን አቋም ለመደገፍ የሰጧቸው ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።*

- ህገ-መንግስቱ ከጸደቀበት ጊዜ መጀመር ከህጋዊነት መርህ አንጻር፣ እንዲሁም ህገ-መንግስቱ እውቅና ከሰጣቸው መብቶች አንጻር ተገቢ ነው፣
- የኢትዮጵያ ችግሮች ምንጭ/መሰረቱ 1987 ዓ.ም ነው፣ ህገ-መንግስቱ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ሀገር በብሔር/ብሔረሰብ ተለያይቶ የከፋ ጉዳት ደርሷል፣ ሰዎች በነፃነት ተዘዋውረው በመሥራት መብታቸው

ላይ ገደብ ተጥሏል፡ በዜጐች መካከል መጠራጠር ተፈጥሯል፡ ኢትዮጵያዊነት እንዲሸረሸር ሆኗል፡ ይህ አማራጭ ከዚህ ጊዜ ወዲህ የተበረዘውን የታሪክ ትርክት ለማስተካከል ያስችላል፡

- ከዚህ የጊዜ ማዕቀፍ ርቀ ወደ ኋላ መጓዝ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ይሆናል፡ ምክንያታዊም አይደለም፡
- ይህ የጊዜ ማዕቀፍ ማስረጃና አጥፊዎችን በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል፡ ከጊዜ አንጻር ቀረብ ያለ መሆኑ ከ1987 ዓ.ም በኋላ የጀመሩ ብዙ ጥሰቶችን አጥርቶ ለመሸፈን ያስችላል፡ ተጠያቂነትን ለማስፈን ይረዳል፡
- የቆዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ ቀደም ባለው ዘመን የፈፀሙት ሰዎች በብዛት ስለሌሉ እና መረጃም ስለማይገኝ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከ1987 ዓ.ም እንዲጀምር ማድረግ ይመረጣል፡
- ያለጊዜ ገደብ ሁሉንም ጉዳዮች ወደኋላ ሄዶ በሽግግር ፍትህ ሂደት ማካተት እንደ ሀሳብ ጥሩ ቢሆንም ሊተገበር የሚችል አይደለም፡ ረጅም ጊዜና ሰፊ ሀብት ይጠይቃል፡ ኢኮኖሚው ይህን መሸከም አይችልም፡
- ከ1987 ዓ.ም በፊት ለተፈጸሙ ጥሰቶች አጥጋቢ ባይሆንም ምላሽ ተሰጥቷል፡
- የሽግግር ፍትህ እንደስሙ በሽግግር ላይ የሚያተኩር ነው፡ የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ነው፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉንም ጉዳይ በተጨባጭ ማዳረስ አይቻልም።

## ረ. (ሌላ) አማራጭ

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካካሄዱ 216 ቡድኖች ውስጥ 14.5 ቡድኖች የተለያየ ይዘት ያላቸው የራሳቸውን አማራጮች አቅርበዋል።


ሰንጠረዥ 67፡ 'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' - የአራቱም የትኩረት ቡድኖች ሀገር-አቀፋዊ ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | የቡድን ብዛት | አማራጭ 1 'ከ1983 በፊት' | አማራጭ 2 'ከ1983 ጀምሮ' | አማራጭ 3 'ከ1987 ጀምሮ' | አማራጭ 4 'ከ2010 ጀምሮ' | አማራጭ 5 'ለክስ ከ1987፡ ለሌላ መረጃ ከተገኘበት' | ሌላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | - | 1 | 1 | 1.5 | 3 | 1.5 |
| 2 | አፋር | 5 | 4 | 0.5 | - | 0.5 | - | - |
| 3 | አማራ | 32 | 3 | 14 | 4 | 4 | 3 | 4 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 0 | 1 | 0 | 2 | 6 | - |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 0 | | | 2 | 3 | |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 2 | 1 | - | 2 | - | - |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 1 | 0.5 | | | 2 | 0.5 |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 17 | 3.5 | 2.5 | 4.5 | 31 | 3.5 |
| 9 | ሲዳማ | 4 | | 1 | 1 | | 2 | |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 1.5 | 6.5 | 2 | | | 1 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 5.5 | 2 | 4.5 | 10 | 15 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | | 3 | 1 | 3 | 1 | |
| 13 | ትግራይ | 24 | 7.5 | | | 9 | 3.5 | 4 |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 216 | 41.5 | 35 | 16 | 37.5 | 69.5 | 15.5 |

ሰንጠረዥ 68፡ 'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ምልከታ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | የቡድን ብዛት | አማራጭ 1 'ከ1983 በፊት' | አማራጭ 2 'ከ1983 ጀምሮ' | አማራጭ 3 'ከ1987 ጀምሮ' | አማራጭ 4 'ከ2010 ጀምሮ' | አማራጭ 5 'ለክስ ከ1987፡ ለሌላ መረጃ ከተገኘበት' | ሌላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አገራዊ የሴት ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 49 | 4.5 | 10 | 1.5 | 15.5 | 15 | 2.5 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ማጠቃለያ | 47 | 9 | 10 | 3 | 12 | 12.5 | 0.5 |
| 3 | አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ | 96 | 23 | 13.5 | 10.5 | 9.5 | 32.5 | 6 |
| 4 | አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ | 24 | 5 | 1.5 | 1 | 0.5 | 9.5 | 6.5 |
| | **አገራዊ የአራቱም የትኩረት ቡድኖች ማጠቃለያ** | 216 | 41 | 35 | 16 | 37.5 | 69.5 | 15.5 |




ሰንጠረዥ 64፡ 'የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር' - ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ምልከታ

### 6.7.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

አብዛኛዎቹ የሕጻናት ቡድን ተሳታፊዎች፣ በህጻናት መብት ላይ የሚሰሩ ተሳታፊዎች፣ የሴቶች ብቻ መድረክ ተሳታፊዎችና የተፈናቃዮች የወንድ ተጎጂዎች ቡድን ተሳታፊዎች አማራጭ አምስትን ማለትም ለክስ ጉዳይ ከ1987 ጀምሮ ለሌሎች ጉዳዮች ደግሞ መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል፡፡ በምክንያትነትም የሚከተሉት ሃሳቦች ተነስተዋል፡፡

- የሽግግር ፍትህ አላማ ፍትህ ሰጥቶ ሰላም እንዲፈጠር ማድረግ ስለሆነ መረጃዎች እስካሉ ድረስ ረጅም ጊዜን ማየት፡ ለክስ ጉዳይ ደግሞ ከ1987 መጀመር ያስፈልጋል፡
- የተዛቡ የታሪክ አረዳዶችን ለማጥራት ከስር ከመሰረቱ ሁነቶችን እየመረመሩ መፍትሄ ለመስጠት ያግዛል፡
- እይታችንን እና አስተሳባችንን ለማስተካከል ትክክለኛውን እውነት ለማወቅ ያስችላል፡

- በእርቅ እና እውቅና በመስጠት ዘላቂ ሠላም የሚመጣበት ሁኔታ ለመፍጠር ይረዳል፡
- አሁን የምናያቸው ችግሮች መነሻቸው በ1966 የተነሳው የተማሪዎች ጥያቄ እና ተመሣሣይ ክስተቶች ናቸው፡ ይህ ማእቀፍ እነዚህን ጊዜያት ለመመልከት ያስችላል፡
- የታፈነው የቅሬታ ሁነት መተንፈስ አለበት፡ ይህ አማራጭ ከዘመናዊ ሀገር ምስረታ ጀምሮ ብዙ ጥያቄ ላለው ትውልድ ሰፊ እድል ይሰጣል፡ ነገሮችን ከምንጮቻቸው ለማድረቅ ያመቻል፡ በተለይም እውነትን ከማፈላለግ አንፃር ወደኋላ መመለሱ ተገቢ ነው።

በሌላ በኩል ሁሉም ከፆታዊ ጥቃት ያገገሙ ሴቶች መድረክ ተሳታፊዎች፣ ሁሉም ሴት ተፈናቃይ ተጎጂዎች አብዛኛው የተፈናቃዮች የቅልቅል ቡድን እንዲሁም የተወሰኑ የተፈናቃዮች ወንድ ተጎጂዎች ቡድን፡ የተወሰኑ ህጻናትና በህጻናት መብት ላይ የሚሰሩ ተሳታፊዎች ሂደቱ ከ2010 ዓ.ም ሊጀምር ይገባል ብለዋል። ከነዚህ አማራጮች በተጨማሪ ጥቂቶች ሌሎች አማራጮችን መርጠዋል።

### 6.7.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

በእነዚህ ባለድርሻ አካላት አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የጊዜ ማእቀፍን በተመለከተ በተለያዩ መመዘኛዎች ላይ በመመርኮዝ የተሰጠው ምክረ-ሃሳብ - ከ1983 በፊት በነበሩ ጉዳዮች ላይ እውነትን ማፈላለግ፣ ዕርቅ እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን ማከናወን፡ እንዲሁም ከ1983 ዓ.ም በኋላ ከተከሰቱ ግጭቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በወንጀል ክስ አማካኝነት ፍትህን ማረጋገጥ ይገባል የሚል ነው። ሆኖም በተወሰኑ ተሳታፊዎች ሌሎች የተለያዩ አማራጮች ቀርበዋል።

## 6.8. በሽግግር ፍትህ ሂደት የባህላዊ ፍትህ ሥርአቶች ሚና ምን ይሁን?

### 6.8.1. አካባቢያዊ ወይም ሀገራዊ ሚና መጫወት የሚችሉ ተለይተው ሊጠቀሱ የሚችሉ ባህላዊ አሰራሮች

ተሳታፊዎች በየክልሉ የሚገኙ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በዝርዝር በማንሳት በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ ተግባር ላይ የሚውሉበት ወይም የሚሳተፉበት ሁኔታ እንዲመቻች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በአጠቃላይ በተሳታፊዎች የተዘረዘሩ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ጥልቀት ባለው መልኩ እያንዳንዱ ስርዓት ለየትኛው የግጭት ዓይነት (ቤተሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የግል ግጭት ወይስ የተለያዩ ማህበረሶችን/ብሄሮችን ግንኙነት የሚመለከት፤ ለወንጀል ጉዳዮችን ብቻ ወይስ ለሌላም) ተግባር ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል በሚል ተለይተው የተገለጹ አይደሉም። በጠቅላላው 'ለግጭት መፍቻ ተግባር ላይ የዋሉ ናቸው' ተብለው የተቀመጡ ናቸው።

ስለሆነም የትኛው ባህላዊ ስርዓት ለሽግግር ፍትህ ሂደት ተግባር ስራ ላይ ሊውል ይችላል? የትኛው ባህላዊ ስርዓት ለየትኛው የግጭት ዓይነት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል? ስርዓቶቹ ጥቅም ላይ የሚውሉት ያለፉ ግጭቶችን ለመጠገን ነው ወይስ ወደፊት የሚከሰቱ ግጭቶችን በመደበኛነት ለማየት? የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ ያስፈልጋል። ሆኖም ይህን ማድረግ የሚቻለው ጠለቅ ባለ የምርምር ውጤት በመታገዝ ብቻ ነው።

### 6.8.2. ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች የትኞቹን ጉዳዮች ለመፍታት ሊተገበሩ ይችላሉ?

አብዛኛዎቹ የትኩረት ውይይት ቡድኖች እንደገለፁት ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ በማህበረሰብም ሆነ በግለሰብ ደረጃ የተከሰቱ ግጭቶችን የመፍታት፣ ስብራቶችን የመጠገን፣ በተለይም እርቅ፡ ምህረት እና ካሳ የመስጠት ስራዎችን የማከናወን ሚና ሊኖራቸው ይገባል የሚለው ሀሳብ አመዝኖ ታይቷል። ሽምግልናን በግለሰብ እና በቡድን ደረጃ ለተፈጸሙ በደሎች፡ ለእርቅ፡ ለካሳ፡ ለምህረት፡ እና ተጎጅዎችን ወደ ነበሩበት ሁኔታ ለመመለስ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል የሚል ምክረ-ሀሳብም ቀርቧል።

ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻለው ለሁሉም የሽግግር ፍትህ ዓላባዎች ወይስ ለተወሰኑ ብቻ የሚለውን በተመለከተ ሁለት የተለያዩ አስተያየቶች ጎልተው ተንጸባርቀዋል። የመጀመሪያውና በአብዛኛዎቹ ቡድኖች ተቀባይነት ያገኘው ሀሳብ - በሽግግር ፍትህ ሂደት ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በቀላል ጥፋቶች ላይ ብቻ ቢያተኩሩ የተሻለ ይሆናል የሚለው ነው። ከባድ ጥፋቶችን በተመለከተ ተጠያቂነት በመደበኛው የፍትህ ተቋማት አማካኝነት ቢከናወን የተሻለ ውጤት ይገኛል የሚል ሀሳብ ተነስቷል። ስለሆነም በባህላዊ ግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚሸፈን የሽግግር ፍትህ ሂደት የቀላል ወንጀሎች ተጠያቂነትን ጨምሮ - እርቅን፣ እውነትን ማፈላለግ እና የማካካሻ ስራዎችን ያካተተ ሊሆን ይገባል።

ሁለተኛው እና በአነስተኛ ቡድኖች የተደገፈው ሀሳብ ደግሞ ከላይ የተመለከቱ አላባዎችን ጨምሮ የከባድ ወንጀል ተጠያቂነትን በባህላዊ ግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ማስተናገድ ይቻላል የሚለው ነው።

ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በሽግግር ፍትህ ሂደት ሊጫወቱ የሚገባቸውን ዝርዝር ሚና በተመለከተ - የወንጀል ድርጊቶችን የመለየት፣ የሞኒተሪግ/ቁጥጥር ስራዎችን የመሥራት - ለምሳሌ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ወይም ምህረት እና ዕርቅ ከተከናወነ በኋላ ስምምነቱ ተፈጻሚ መሆኑ አለመሆኑን ወይም ድጋሚ ግጭት እንዳይቀሰቀስ በመከታተል ሥራዎች ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ የሚለው ሀሳብ ጎልቶ የወጣ ሆኗል።

በአጠቃላይ የሀገር ሽማግሌዎችና ባህላዊ እሴቶች ከሽግግር ፍትህ ሂደት ጋር ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ ሊተገበሩ ይችላሉ፤ እንዲሁም በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊኖራቸው የሚገባው ሚና ዋናውን የሽግግር ፍትህ ሂደት በማገዝ እና በመደገፍ ላይ ያተኮረ መሆን አለበት የሚለው አስተያየት ጠንካራ ሆኖ ወጥቷል። ከሌሎች የሽግግር ፍትህ ተቋማት ጋር ሆነው እውነትን በማፈላለግ፣ በካሳ እና በእርቅ ጉዳይ ደጋፊ ሊሆኑ ይችላሉ።

በሌላ በኩል የባህላዊ የግጭት መፍቻ ስነ-ሥርዓቶች የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ከማገዝ ባለፈ - የሽግግር ፍትህ ስራው የማይሸፍናቸው ጉዳዮችን በማስተናገድ ሰላም የማውረድ እና ግጭቶችን የመፍታት አቅማቸውን አጉልቶ መጠቀም እንደሚገባ ተሳታፊዎች አስተያየት ሰጥተዋል። በዚህ ረገድ በእርቅ፣ እውነትን በማፈላለግ እና በማካካሻ ስርዓት በመሳተፍ እንዲሁም በቀላል ወንጀሎች ላይ ብቻ በማተኮር እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል የሚለው ሀሳብ በአብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ተቀባይነት ያገኘ ሀሳብ ነው።

### 6.8.3. ባህላዊ ዘዴዎች እና እሴቶችን ለመጠቀም መደረግ የሚገባቸው ለውጦች/ማሻሻያዎች

#### I. ሀገራዊ የሴት ተጎጂዎች ቡድን

ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች እና እሴቶችን በተመለከተ መስተካከል አለባቸው ተብለው ከተነሱት ሀሳቦች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

- ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ መሆን አለባቸው፣
- መንግስት በባህላዊ አሰራሮች ላይ አመኔታን ከሚሸረሽር ድርጊት መቀጠብ አለበት፣
- የሽምግልና ስርዓቱ በደንብ እንዲጠናከር ከመንግስትና ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ማግኘት ይኖርበታል፣
- ለተቋማቱ በሕግ እውቅና መስጠት እና በሀገር-አቀፍ ደረጃ እንዲሰሩ ማደራጀት ተገቢ ነው፣
- ዝርዝር ተግባራቸው በየአካቢያቸው የሚወሰን መሆን አለበት፣ በዚህ ረገድ በኦሮሚያ ክልል የተሰራው ስራ ጥሩ ተሞክሮ ተፈትሾ በሌሎች ክልሎችም ሊደገም ይገባል፣
- ሽምግልና ትኩረቱ ማስታረቅ ላይ ብቻ ሳይሆን እውነትን የማውጣት እና የማሳወቅ ስራን በማካተት እርቅ መመስረት እንዲችል ሆኖ መደራጀት አለበት፣
- ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ሂደታቸው የሴቶችን መብት የሚጎዳ ወይም የሚጥስ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፣ ሂደቱ የሴቶችን ተሳትፎ የሚያበረታ እና እውቅና የሚሰጥ መሆን አለበት፣

- የውሳኔ አሰጣጥ እና አጠቃላይ የአሰራር ሥርዓቱን ማሻሻል፡ ለዚህም በመንግስት በኩል ድጋፍ ማድረግ ተገቢ ነው።

II. **አገራዊ የወንድ ተጎጂዎች ቡድን ሀሳብ**

**የአብዛኛው ሀገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ሀሳብ**

- ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ለፖለቲካ አላማ መጠቀሚያ እየሆኑ ነው የሚል ግንዛቤ በማህበረሰቡ ውስጥ ስለሰረፀ ይህን ግንዛቤ የሚለውጥ ስራ መሰራት አለበት፡
- ህዝቡ በሀይማኖት አባቶች እና በሀገር ሽማግሌዎች ላይ ያለውን እምነት እያጣ መጥቷል የሚለውን አስተሳሰብ ማስተካከል ያስፈልጋል፡
- በሌላ በኩል ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ገለልተኛነታቸውን ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡ ራሳቸውን ከፖለቲካ አርቀው ለእውነት እና ለህሊናቸው ብቻ የቆሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ስራዎችን ማከናወን አለባቸው፡
- ሽማግሌዎች ሂደትን ሳይጠብቁ ቶሎ እርቅ የመፈጸም ፍላጎት ስላላቸው ጊዜ ሰጥተው ተበዳይን በመስማት እና እውነቱን በማሳወቅ ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡
- ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በሕግ እውቅና እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡ ተቋማዊ ማድረግ እና የሚሰጡት ውሳኔ ተፈፃሚነትን የሚያጠናክሩ አሰራሮች ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡
- በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ላይ የእናቶች ተሳትፎን ማበረታታት ያስፈልጋል፡ የሚሰጡ ውሳኔዎች የሴቶችን መብት ያከበሩ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያችሉ ስራዎች መከናወን ይኖርባቸዋል፡
- በአንዳንድ ባህላዊ ስርአቶች የሚስተዋሉ ከሌላ ብሄር የመጡ ባለጉዳዮችን በአግባቡ ያለመስማት እና የማዳላት ሁኔታዎችን ለማስቀረት የሚያስችሉ ማሻሻያዎችን መተግበር አለባቸው፡
- መንግስትም በበኩሉ ባህላዊ ስርዓቶችን ሊጠብቅ እና ሊያጎለብት ይገባል፡
- በሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ላይ መሠረት ያደረገ ሥልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡

**የጥቂቶች ሀገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ሃሳብ**

የተወሰኑ ቡድኖች በየአካባቢው በርካታ ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ ስርአቶች ያሉ እንደመሆኑ መጠን በአግባቡ ታይተው እና በጥልቀት ተጠንተው በምን በምን ጉዳዮች ላይ የሽግግር ፍትህ ስራን ሊተገበሩ ይችላሉ የሚለው ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል፡ በደምሳሳው አስፈላጊ ናቸው በማለት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ በራሱ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡ አሁን ባለንበት ደረጃ ይህ ይሻሻል ያኛው ይቀጥል ማለት የሚቻልበት እድልም የለም ብለዋል።

III. **አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ሀሳብ**

**የአብዛኛው ሀገራዊ ቅልቅል ቡድኖች ሀሳብ**

አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ባህላዊ ዘዴዎች እና እሴቶችን በሽግግር ፍትህ ሂደት ጥቅም ላይ ማዋል እንዲቻል በሥርዓቶቹ ላይ መደረግ የሚገባቸውን ለውጦች አስመልክቶ ሰፊ አስተያየት ሰጥተዋል። እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ባህላዊና ሃይማኖታዊ ተቋማት ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ መሆን አለባቸው፡ ገለልተኛ ሆነው መሥራት ይኖርባቸዋል፡
- የተለያዩ የማሻሻያ ስራዎችን በመስራት የማህበረሰቡን አመኔታ እና ተቀባይነት ሊመልሱ ይገባል፡
- ስርዓቶቹ እሴታቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ መንግስት ተገቢውን ጥንቃቄ/ድጋፍ ማድረግ አለበት፡

- ባህላዊ ስርአቶች አዲስ በሚቋቋሙ መዋቅሮች ውስጥ መካተት አለባቸው፡ እርከን ተለይቶላቸው እና ስልጣን አግኝተው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ እንዲሰሩ ማድረግ ተገቢ ነው (ለምሳሌ እውነትን በማፈላለግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡ በማካካሻ ስራም በርካታ ባህላዊ አሰራሮች ሊተገበሩ ይችላሉ)፡
- አሰራራቸው እውቅና የተሰጣቸው መብቶችን የሚነካ ከሆነ ወደ መስመር በመመለስ ሚዛናዊ አድርጎ መጠቀም ያስፈልጋል፡
- የሽማግሌዎች የምርጫ ስርዓት ፍትሀዊ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡
- ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች ከአካባቢያዊነት እሳቤ ወጥተው አካታች እና አቃፊ መሆን አለባቸው፡ ከሌሎች ክልል ስርዓቶች ጋር መተዋወቅ እና አብሮ መስራት፡ ለዚህም ተገቢ ውስጣዊ ማስተካከያዎችን ማካሄድ ይኖርባቸዋል፡
- ለተቋማቱ እና አሰራራቸው በሕግ እውቅና በመስጠት በሀገር-አቀፍ ደረጃ እንዲሰሩ ማበረታታት ያስፈልጋል፡ ሆኖም በሀገራዊው የሽግግር ፍትህ ሂደት የሚኖራቸውን ዝርዝር ሚና ለማወቅ እንዲረዳ ስርዓት መዘርጋት ተገቢ ነው።

**የጥቂቶች ሀገራዊ ቅልቅል ቡድኖች ሃሳብ**

የተወሰኑ ተሳታፊዎች ደግሞ የባህላዊ የግጭት መፍቻ ሰርአቶች ውጤታማ የሚሆኑት ሳይሻሻሉ አሁን ባሉበት ሁኔታ ነው። ስለሆነም ማሻሻያ እንዲያካሂዱ ሊጠየቁ አይገባም የሚል ሀሳብ አንስተዋል።

IV. **የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድን**

ሁሉም ቡድኖች ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በእውነት ማፈላለግ፣ በእርቅ፣ ቀጣይነት ያለው አብሮነትን በማጠናከር እና እንደአስፈላጊነቱም በሌሎች የሽግግር ፍትህ አላባዎች ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይገባል ቢባልም - በቅድሚያ ሊሻሻሉ ይገባል ያሏቸውን ጉዳዮች አንስተዋል። እነዚህም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- የመንግስት ጣልቃ-ገብነትን ማስወገድ የሚያስችሉ ስራዎችን ማከናወን፡ ስራዎቻቸውን ሙሉ ለሙሉ "depoliticize" ማድረግ፡
- የሽማግሌዎች አመራረጥ እሴቱን ጠብቆ ህዝባዊ እንዲሆን መጣር፡
- ስርዓቶቹ የሴቶችን ሰብዓዊ መብቶችን በማክበርና እና በአሳታፊነት ረገድ ያሉባቸውን ውስንነቶች ማሻሻል፡ የጾታና የሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች (ለምሳሌ አካል ጉዳተኞች) ተሳትፎን ማሳደግ፡ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች እኩል ትኩረት እንዲሰጣቸው ማድረግ፡
- በካሳ አወሳሰን (ጉማ/ካሳ) በወንድና ሴት መካከል የሚከተሉት ልዩነታዊ አሰራር ማስቀረት፡
- ከሰብዓዊ መብት አኳያ የሚነሱ ችግሮችን መቅረፍ፡
- የብሔር አድልዎን በማስቀረት ገለልተኛ ሆነው እንዲሰሩ ማድረግ።

### 6.8.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

'በሽግግር ፍትህ ሂደት የባህላዊ ፍትህ ሥርአቶች ሚና ምን ይሁን'፡ 'አካባቢያዊ ወይም ሀገራዊ ሚና መጫወት የሚችሉ ተለይተው ሊጠቀሱ የሚችሉ ባህላዊ አሰራሮች የትኞቹ ናቸው'፡ 'ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች የትኞቹን ጉዳዮች ለመፍታት ሊተገበሩ ይችላሉ' እንዲሁም 'መደረግ የሚገባቸው ለውጦች ወይም ማሻሻያዎች ምን አይነቶች ናቸው' ለሚሉ ተያያዥ ጥያቄዎች ተሳታፊዎች አስተያየቶቻቸውን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

**ተለይተው ሊጠቀሱ የሚችሉ ባህላዊ አሰራሮችን በተመለከተ** - የሃገር ሽማግሌዎች፡ ሽምግልና፡ የደም አድርቅ ስርዓት፡ አባጋራ፡ አባ ገዳ፡ ቁመቴ፡ የጎሳ መሪዎች እና የሃይማኖት አባቶች ስርአቶች በዋናነት ተነስተዋል።

እነዚህ ባህላዊ ወይም እምነት-አከል አሠራሮች **ከሽግግር ፍትህ ጋር በተያያዘ የሚኖራቸውን ሚና** በተመለከተ ተሳታፊዎች አቋማቸውን እንደሚከተለው ገልፀዋል።

- ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ተቋማት ወይም አሰራሮች ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ አስተዋፅኦ ማበርከት እንጂ ሂደቱን ሊመሩ አይገባም፣
- እነዚህ ስርአቶች በወንጀል ክስ ጉዳይ ሚና ባይኖራቸው ይመረጣል፡ በዋናነት ትኩረቱ በእርቅ፣ በእውነት ማፈላለግና በማካካሻ የስራ ሂደቶች በሚኖራቸው ሚና ላይ መሆን አለበት፡
- ሆኖም ውስን ቡድኖች የባህል ግጭት አፈታት ስርአቶች በትናንሽ ወንጀሎች ላይ ጭምር ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል የሚል ሀሳብ አንስተዋል፡
- ስርአቶቹ ስራ ላይ ሲውሉ ወጥነት ባለው መንገድ ሊሆን ይገባል፡ በተለያዩ ባህላዊ ስርአቶች አሰራሮች መካከል ማበላለጥ ወይም ልዩነት እንዳይኖር መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡
- ጾታዊ ጥቃቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች ስለሚኖራቸው ሀላፊነት ከፍ ያለ ጥንቃቄ እና ገደብ ማበጀት ያስፈልጋል።

**በእነዚህ ባህላዊ አሠራሮች ላይ ሊደረጉ የሚገቡ ማሻሻያዎችን በተመለከተ፡-**

- ባህላዊ አሰራሮች ግጭቶችን በመፍጠር ረገድ ሚና ነበራቸው፣ የራሳቸውን በዳይ አሳልፈው አይሰጡም፣ ስለሆነም በቅድሚያ በአመራሮቻቸው መካካል ውይይቶችን ማካሄድ እና መግባባት መፍጠር ይገባል፡
- ለአመራር ሀላፊነት በፖለቲካ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌላቸው እና የተሻለ ቅቡልነት ያገኙትን ብቻ ማሳተፍ ያስፈልጋል፡ እንደአስፈላጊነቱ እነዚህን ከባለሙያዎች ጋር በማሰባጠር እና ሳይንሳዊ ዘዴዎችን በመጠቀም መስራት የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል፡
- ከህፃናት፣ ሴቶች፣ እና አካል ጉዳተኞች መብቶች አንፃር ያላቸውን አሉታዊ አሰራር ግምት ውስጥ በማስገባት ማሻሻያዎችን መተግበር ይኖርባቸዋል፡
- ስራዎቻቸውን እውቅና በተሰጣቸው የሴቶች መብቶች ላይ ተፅእኖ በማያሳድር (እንደአግባብነቱም ሴቶችን መሪ በሚያደርግ) መልኩ የሚያከናወኑበት አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ነው፣
- በመርህ ደረጃም ቢሆን አሰራራቸው ተጎጂ-ተኮር (victim-centered) ሊሆን ይገባል፡
- ከተደራሽነት፣ ተቀባይነት እና አሳታፊነት አንፃር የሚከወኑ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ባህላዊ የፍትህ ስርአቶች በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማእቀፍ በኦፊሴል እውቅና እንዲሰጣቸው ማድረግ ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆኑ እና ሰፊ ሚና እንዲኖራቸው ያደርጋል።

### 6.8.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

'የባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ምን ሚና ሊኖራቸው ይገባል' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ ተሳታፊዎች ሁለት አይነት ሃሳቦች አቅርበዋል።

አንደኛው - ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች አሁንም ሰፊ ህጋዊነት እና ተቀባይነት ስላላቸው ከሽግግር ፍትህ ሂደት ጋር በተያያዘ ማኅበራዊ ውህደትን በማሳለጥ እና ችግሮችን በመቅረፍ ረገድ ትልቅ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል የሚል ነው። መደበኛው የክስ ሂደት አሰራር በአመዛኙ ግጭት-ተኮር ስለሆነ - ለውይይት የተሻለ ቦታ የሚሰጡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶችን ይበልጥ ተመራጭ ያደርጋቸዋል።

በሌላ በኩል የተነሳው ሃሳብ - የባህል ግጭት አፈታት ዘዴዎች የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ከማገዝ ያለፈ ቀጥተኛ ሚና ሊኖራቸው አይገባም፣ በፖለቲካ አመለካከት የተበረዙና ተቀባይነት እያጡ የመጡ እንደመሆኑ መጠን ሚናቸው የገዘፈ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል የሚል ነው።

**የባህል ግጭት አፈታት ስርአቶችን ተሳትፎ** በተመለከተ በሚከተሉት ላይ እንዲተገበሩ ሃሳብ ተሰጥቷል።

- በጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰት ስር በማያርፉ ቀላል ወንጀሎች ጉዳይ ላይ፡
- በእውነት ማፈላልግ እና ይፋ ማውጣት ስራዎች፡

- ማስረጃ በማፈላለግ እና አጥፊዎችን በመለየት ስራዎች፣
- እርቅ በማስፈን፣ ዘላቂ ሰላም በመመስረት፣ በካሳ እና በምህረት መስጠት ዙሪያ በፖሊሲው መሰረት ከሚመሰረቱ ተቋማዊ አማራጮች ጋር አቀናጅቶ መጠቀም።

ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶችን እና እሴቶች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ለመጠቀም **በስርአቶቹ ላይ መደረግ የሚገባቸው ማሻሻያዎችን** በተመለከተ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርበዋል።

- ባህላዊ አሠራሮች ተጠያቂነት ከማረጋገጥ አኳያ በየትኛውም ደረጃ ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ ከሌሎች ዓለም-አቀፋዊ እና ሕገ-መንግሥታዊ የሰብዓዊ መብት እሴቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን በቅድሚያ ማረጋገጥ፣
- አንዳንድ ባህላዊ ዘዴዎች የሚከተሉት አሰራር እንደ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ካሉ ተጋላጭ ቡድኖች መብት እና ፍላጎት ጋር የሚቃረን ሊሆን ስለሚችል አሰራሮቻቸውን ከሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች እና አለማቀፋዊ እሴቶች ጋር ማጣጣም፣
- የተፈፃሚነት ወሰንን በተመለከተ ማናቸውም እውቅና/ህላፊነት የሚሰጠው ባህላዊ አሰራር ከሌላው ጋር የማይጣጣምበት እድል ሰላለ በዋናነት የእያንዳንዱ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርአት ተግባራዊነት አንድ አይነት ባህላዊ ዘዴ በሚከተል ማህበረሰብ ላይ ብቻ እንዲሆን ጥንቃቄ ማድረግ፣
- ጉዳዩ የተለያዩ ማህበረሰቦችን የሚመለከት ሲሆን ሂደቱ ለመደበኛው የሽግግር ፍትህ ስርዓት እና ተቋማት መተው የሚያስችል አሰራር መዘርጋት፣
- የባህላዊ ግጭት አፈታት ሥርዓት ዋና ተዋናዮች (ሽማግሌዎች) በጥንቃቄ የሚመረጡበትን አሰራር መዘርጋት፣ ኃላፊነት እና ግዴታቸውን በሚገባ እንዲያውቁ በተለይ የሽግግር ፍትህን በተመለከተ ተከታታይ ሥልጠና የሚሰጥበትን አሰራር መቀየስ።

## 6.9. በሽግግር ፍትህ ሂደት የክልሎች/ከተማ መስተዳደሮች ሚና ምን ይሁን?

### 6.9.1. መግቢያ

በሽግግር ፍትህ ሂደት የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ሚና ምን ሊሆን ይገባል የሚለው ጥያቄ ለውይይት ከቀረቡ እና የፖሊሲ ውሳኔ ከሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አንዱ ነው።

በሀገራችን ተግባራዊ የሚደረገው ፌዴራላዊ የመንግስት አስተዳደር ስርአትን እና የፌዴራል መንግስት እና የክልሎች ህገ-መንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል መርሆችን መነሻ በማድረግ፣ እንዲሁም ይህ ጉዳይ ከሽግግር ፍትህ ሂደቱ እና አላማ ጋር የሚኖረውን ቁርኝት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት - የክልሎች/ከተማ አስተዳደሮችን ሚና ለመወሰን ሁለት አማራጮች ቀርበዋል። የመጀመሪያው 'ከብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሃ-ግብሩ ጋር መተባበርና የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ' የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው 'የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር' የሚል አማራጭን የሚያቀርብ ነው። ተሳታፊዎች ሌላ አማራጭ ማቅረብ የሚችሉበት እድልም ክፍት እንደሆነ ተገልፆላቸዋል።

ከሁሉም መድረኮች ውይይት በመነሳት - ተሳታፊዎች በጥያቄው ላይ ያቀረቧቸው አማራጮች፣ አማራጮችን ለመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶች፣ በእያንዳንዱ የትኩረት ቡድን የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ክልል-አቀፍ እና ሀገር-አቀፍ ምልከታዎች በዚህ ክፍል ተካተው ቀርበዋል።

### 6.9.2. የተለያዩ የትኩረት ቡድኖች እይታ

I. **የሴት ተጎጂዎች ቡድን**

**ሀ. በአብዛኛዎቹ የሴት ተጎጂዎች ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፦ 'ከብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሃ-ግብሩ ጋር መተባበርና የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ'** (አማራጭ 1)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች ውስጥ 42 ቡድኖች (ወይም 85.71) የሚሆኑት ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሀ-ግብር በአንድ አካል በሀገር-አቀፍ ደረጃ መተግበር አለበት፡ ሁሉም ክልላዊ አስተዳደር የየራሱን የሽግግር ፍትህ ፕሮግራም መቅረፅ ወይም ማከናወን አይኖርበትም የሚል አቋም አንፀባርቀዋል።

የሽግግር ፍትህ መርሀ-ግብር ሀገራዊ ሀላፊነትን እና በሂደቱ ሁሉም የፌዴሬሽኑ መዋቅሮች ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና በተመለከተ ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን እንደሚከተለው ገልጸዋል።

- እንደ ሀገር አንድ ወጥ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሊኖር እና ሊተገበር ይገባል፡
- ሁሉም የክልል አስተዳደሮች በየፊናቸው የሽግግር ፍትህ ስርአትን ለማቀም ከሞከሩ ወጥ አተገባበር እንዳይኖር ያደርጋል፡ በሀገር ደረጃ የደረሰን ችግር በክልል ብቻ እንዲወሰን ያስገድዳል፡ ለውስን ቡድኖች ውግንና ያለው አካሄድን ይፈጥራል፡
- ለፖሊሲ አቀራረፅ ክልል፡ ዞን፡ ወረዳ እያሉ ማሰብ ሌላ ቁርሾ እና መከፋፈል ይፈጥራል፡ ሁሉም የራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ግጭት ውስጥ ሊገባ ይችላል፡
- ክልሎች ለብዙዎቹ የሽግግር ፍትህ ጉዳዮች ቅርብ እንደመሆናቸው መጠን ተሳትፏቸው ፍፁም አስፈላጊ ነው፡ ከብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሃ-ግብሩ ጋር በመተባበር እና በመደጋገፍ ሚናቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡
- የክልሎች ሚና የተለያዩ ድጋፎች ማድረግን (በገንዘብ፡ በሃሳብ፡ በቁሳቁስ)፡ በቅን ልቦና፡ በአንድነት እና በግልጸኝነት ላይ የተመሰረተ የምክክር መድረክ መፍጠር፡ ለሽግግር ፍትህ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ/በመስጠት ሂደት ባለሙያዎችን መመልመል፡ በጉዳዩ ላይ የአላማ አንድነትን ማጠናከር፡ እኛ የሚለውን ስሜት ማዳበር፡ እንደ ሀገር የጋራ ግብ እንዲኖር መሥራትን ያጠቃልላል፡
- ክልሎች እውነት ማፈላለግ እና እርቅን ማስፈጸም፡ በሕግ የሚሰጡ ሌሎች ሀላፊነቶችን በአግባቡ መወጣት፡ የተፈፀሙ ወንጀሎች ፍትህ እንዲያገኙ ማድረግ/ማገዝ፡ እና የተለያዩ ድጋፎችን በማከናወን ከብሄራዊ የሽግግር መርሀ-ግብሩ ጋር መተባበር አለባቸው፡
- ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ ስኬት መተባበር ሲባል በተቋማት ማሻሻያ ስራዎች እገዛ ማድረግን፡ ከጎጠኝነት ኣስተሳሰብ በመውጣት በአንድነት ላይ መስራትን፡ ህገ-መንግስታዊ ግዴታን መወጣትን፡ ያለውን ችግር በጋራ ለመፍታት መሞከርን፡ ከሌሎች ክልል አስተዳደሮች ጋር መሥራትን፡ እና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ማድረግን ያካትታል።

## ለ. በጥቂት ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ፡ የራሳቸውን ሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 49 የሴት ተጎጂ ቡድኖች መካከል 5 ቡድኖች (ወይም 10.2%) የሚሆኑት ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የራሳቸው የሽግግር ፍትህ ሂደት ሊተገብሩ እንደሚገባ በማመን የአማራጭ ሁለትን ሀሳብ ደግፈው ተከራክረዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- በሁሉም ክልል ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ የሚሆን ሕግ ማስቀመጥ አስቸጋሪ መሆኑ አይቀርም፡
- ይህ አማራጭ በክልሎች ለተፈጸሙ ጥሰቶች ተገቢ የሆነ፡ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የሽግግር ዓላባ/ስልት እንዲመርጡ እና ፍትህ እንዲሰፍን ያስችላል፡
- የሽግግር ፍትህ ሙሉ ለሙሉ ከማዕከል ወደታች ይውረድ ቢባል በደረሰው ጥፋት የተጎዳውና የጎዳው የማህበረሰብ ክፍል በተመሳሳይ የሚቀበለው አሰራር መመስረት የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጥራል፡
- እያንዳንዱ ክልል የችግሩን ስረ-መሰረት እና ስፋት የሚያውቀው ራሱ ነው፡ ስለሆነም እንደየችግሮቹ ስፋት እና ውስብስብነት የየራስ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል።

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ/አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 2 | 0 | 2 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 7 | 0 | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 2 | 0 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 13 | 0 | 1 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 0 | 3 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 9 | 0 | 0 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 2 | 0 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 4 | 0 | 1 |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 49 | 42 | 5 | 2 |

## II. የወንድ ተጎጂ ቡድኖች

### ሀ. በአብዛኛው የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ- 'ከብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሃ-ግብሩ ጋር መተባበርና የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ' (አማራጭ 1)

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረት 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 41 ቡድኖች (ወይም 87.23%) የሚሆኑት የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሚና ከብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሃ-ግብሩ ጋር በመተባበርና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል ብለዋል። ለዚህም የሚከተሉትን የማጠናከሪያ ሀሳቦች አቅርበዋል።

- በሀገራችን ብሄራዊ መግባባትን ለማምጣት፣ የህዝቦችን አንድነት ለመገንባት፣ ሰላም ለማፅናትና ለዘላቂ ፍትህ አንድ ወጥ ብሄራዊ የሽግግር ፍትሕ ሂደት መኖር አለበት፣
- የክልል መንግስታት የየራሳቸው የሽግግር ፍትሕ ስርአት ይተግብሩ ከተባለ ችግሮች ይባባሳሉ፣ መከፋፈሎች ይሰፋሉ፣ ወጥነት የሌለው አካሄድና አተገባበር ይጨምራል፣
- በየክልሎቹ ለደረሱ በደሎች (መፈናቀል፣ ሞት እና ግጭት) የክልል እና የአካባቢ መስተዳድሮች ተጠያቂ የሚሆኑበት እድል ስላለ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ሊያስተጓጉሉ፣ በሂደቱም ጣልቃ ሊገቡ ይችላሉ፣
- ሆኖም ክልሎች የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ዋና አጋሮች መሆናቸው መታወቅ ይኖርበታል፣ አብዛኛው ችግር በክልሎች ውስጥ የሚፈጠር እንደመሆኑ መጠን ክልሎች የችግሩ ባለቤት እንደሆኑ ሁሉ የመፍትሄውም አካል መሆን አለባቸው፣
- የሽግግር ፍትህ ስርአቱን እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ለማውረድ የግድ የክልሎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ ይኖርበታል፣
- ክልሎች በእርቅና እውነት ማፈላለግ እንዲሁም ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን በመካስ ሂደት ጉልህ ሚና ሊኖራቸው ይገባል፣
- ተዓማኒና ገለልተኛ መረጃና ማስረጃዎችን ለማሰሰብና ለማቅረብ የክልሎች ትብብር አስፈላጊ ነው፣
- በተለያየ ቦታ ላይ የሚገኙ የክልል ሀላፊዎች ጥሰቶችን ማን እና እንዴት እንደፈፀመ በቅርበት ስለሚያውቁ በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜት ሂደቱን ማገዝ ይኖርባቸዋል፣

- ክልሎች ለደረሰ የከፋ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሀላፊነት መውሰድና እንዳይደገም አስፈላጊ እና በቂ እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡ መተማመኛ ለመስጠትም መገደድ አለባቸው።

### ለ. በተወሰኑ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'የራሳቸው የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር'

በሀር አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 4 ቡድኖች (ወይም 8.51%) የሚሆኑት - ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በክልላቸው የተፈጸመውን ወንጀልና የሰብዓዊ መብት ጥሰት ጠንቅቀው ስለሚውያቁ የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ መርሀ-ግብር እንዲያካሂዱ ሙሉ ስልጣን ሊሰጣቸው ይገባል ብለዋል።

### ሐ. በጥቂት ወንድ ተጎጂ ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 47 የወንድ ተጎጂ ቡድኖች መካከል 2 ቡድኖች (ወይም 4.25%) የሚሆኑት ደግሞ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ምንም ሚና ሊኖራቸው አይገባም በማለት አዲስ አማራጭ አቅርበዋል።

ሰንጠረዥ 70፡ - አገራዊ የወንድ ተጎጂ ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ/አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 3 | አማራ | 7 | 7 | 0 | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 | 2 | 0 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 0 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 14 | 12 | 0 | 2 |
| 9 | ሲዳማ | 1 | 1 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 3 | 0 | 3 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 9 | 9 | 0 | 0 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 2 | 2 | 0 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 5 | 5 | 0 | 0 |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 47 | 41 | 4 | 2 |

## III. አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች

### ሀ. በአብዛኛው የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ ሂደትን ማገዝ'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች መካከል 87 ቡድኖች (ወይም 90.62%) የሚሆኑት - የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ሚና ከብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሃ-ግብሩ ጋር በመተባበር እና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ የተወሰነ ሊሆን ይገባል የሚል ሀሳብ አንፀባርቀዋል። ይህን አቋማቸውን ለመደገፍ የሚከተሉትን ሀሳቦች አንስተዋል።

- የሽግግር ፍትሕ ዜጋ-ተኮር አጀንዳ ነው፡ አገራዊ (ድንበር-ዘለል) እንደምታ ያለው እንደመሆኑ መጠን በተወሰነ የአስተዳደር ወሰን በተለየ መንገድ ሊተገበር አይችልም፡ በመሆኑም በተናጠል እንዲተገበር የሚያስችል ማናቸውንም ሀላፊነት ለክልሎች መስጠት ተገቢ አይደለም፡

- ክልሎች የራሳቸውን መርሀ-ግብር ያዘጋጁ ከተባለ ወደ መለያየት የሚያስኬዱ ጉዳዮች ይሰፋሉ፡ በየክልሉ ያለው የብሄር ክፍፍል ባህል እና የሙስና ሰንሰለት ሂደቱን ሊያደናቀፍ ይችላል፡ በብሔር በሃይማኖት ወይም በሌላ ማንነቶች ላይ በመመስረት ወንጀለኞችን የመሰወር እና የተጠያቂነት ስራን የማደናቀፍ እድልን ያሰፋል፡
- በክልል ደረጃ የሚወጣ ፖሊሲ በክልሉ የሚኖሩ ሁሉንም ብሔሮች የሚያካትት ወይም በእኩል የሚያይ ላይሆን ይችላል፡
- ስለሆነም የሽግግር ፍትሕ ስራ በየክልሉ ሳይሆን በሀገር-አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ መከናወን አለበት፡
- ሲጀመርም በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማእቀፍ ከሚሸፈኑ ጉዳዮች አንዱ እና ዋናው የሆነው የወንጀል ተጠያቂነት ስራ ስልጣን የፌዴራል መንግስት ነው፡
- በመሆኑም የክልሎች ሚና ከአገራዊ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ጋር በመተባበር ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል፡
- በዚህ ረገድ ሀገራዊ አንድነትን ለማረጋገጥ እና የህዝቦችን የጋራ ታሪካዊ እና ባህላዊ መስተጋብር ለማስቀጠል አጠቃላይ ሂደቱን በትብብር መምራት ተመራጭ ነው፡
- የክልል መንግስታት የሀገራዊ ችግሩ አካል እንደመሆናቸው መጠን የመፍትሄውም አካል መሆን ይጠበቅባቸዋል፡
- የክልሎች ተሳትፎ ዝርዝር ይዘትን በተመለከተ - ለሀገር ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶችን በመምረጥ፡ ተጎጂዎችን በመለየት፡ የማካካሻ ስራን በገንዘብ በመደገፍ፡ ተጎጂዎችን መልሶ በማቋቋም፡ ችግሩን ለማከም የሚረዱ ማስታወሻዎችን በማዘጋጀት፡ ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ መሳካት የሚፈለጉ ማስረጃዎችን በማቅረብ፡ የውይይት ጊዜና ቦታ በማዘጋጀት፡ ሎጂስቲክስ በማሳለጥ፡ ጥፋተኞችን ሪፖርት በማድረግ እና ለፍርድ በማቅረብ፡ የሚያስተዳድሩት ህዝብ በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ላይ አመኔታ እንዲኖረው በማድረግ፡ የህዝቦች አብሮነት እና ግንኙነት የሚያጠናክሩ ስራዎችን በመስራት፡ ሀሳቦችን በማመንጨት እና የክልሉን ህዝብ ተሳታፊነት በማረጋገጥ ተገቢ ትብብር ሊያደርጉ/ጉልህ ሚና ሊጫወቱ ይገባል።

### ለ. በተወሰኑ የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ፡ 'የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 የቅልቅል ቡድኖች መካከል 4 ቡድኖች (ወይም 4.16%) የሚሆኑት - ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር አለባቸው የሚለውን አማራጭ ደግፈው ተከራክረዋል። ምክንያታቸውንም እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- በየክልሉ የተፈጸመውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ከክልሎቹ የበለጠ የሚያውቅ አካል ሊኖር አይችልም፡
- በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ክልላዊ ልዩነቶችን ከግምት ለማስገባት እንዲቻል ክልሎች የመሪነት ሚና ሊኖራቸው ይገባል፡
- ሁሉም ክልሎች አንድ አይነት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ያስፈልጋቸዋል ተብሎ አይታሰብም፡
- የፌዴራል መንግስቱ ሃላፊነት ክልሎችን በማገዝ ላይ ያተኮረ መሆን አለበት፡

### ሐ. በጥቂት የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ- 'አዲስ አማራጭ'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 96 ቅልቅል ቡድኖች መካከል 2 ቡድኖች (ወይም 2.08%) የሚሆኑት የትግራይ ክልልን ልዩ ሁኔታ ያገናዘበ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር ያስፈልጋል፡ ክልሉ አሁን ላይ በፌዴራል ምክር ቤቶች ውክልና ስለሌለው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው በፌዴራል መንግስት ብቻ የሚመራ መሆኑ ቀርቶ ከክልሉ ልዩ ሁኔታ አንፃር የተለያዩ እሳቤዎችን ለማስተናገድ እንዲቻል የትግራይ ክልል የራሱን ፖሊሲ መቅረፅ ይኖርበታል ብለዋል።

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ/አዲስ አማራጭ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 6 | 6 | 0 | 0 | |
| 2 | አፋር | 2 | 2 | 0 | 0 | |
| 3 | አማራ | 13 | 13 | 0 | | |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 4 | 4 | 0 | 0 | |
| 5 | ድሬዳዋ | 2 | 1 | 1 | 0 | |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 2 | 0 | 0 | |
| 7 | ሀረሪ | 2 | 2 | 0 | 0 | |
| 8 | ኦሮሚያ | 27 | 25 | 0 | | 2 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 9 | ሲዳማ | 2 | 2 | 0 | 0 | |
| 10 | ሶማሌ | 4 | 1 | 3 | 0 | |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 18 | 17 | 0 | 0 | 1 ቡድን ሀሳብ አልሰጠም |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 4 | 4 | 0 | 0 | |
| 13 | ትግራይ | 10 | 8 | 0 | 2 | |
| ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ | | 96 | 87 | 4 | 2 | 3 |

## IV. ሀገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቡድኖች

### ሀ. በአብዛኛው የቅልቅል ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ ሂደትን ማገዝ'

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ውስጥ 22 ቡድኖች (ወይም 91.6%) የሚሆኑት - የክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ሚና ከብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሃ-ግብሩ ጋር መተባበር እና የተለያዩ ድጋፎችን መስጠት ሊሆን ይገባል ብለዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል።

- የሽግግር ፍትሕ ጉዳዮች ከአንድ ክልል በላይ የሚነካኩ በመሆኑ ሀገራዊ እይታ ያለው ፖሊሲ ማውጣትን የግድ ይላል፡ ይህም ሂደቱን በሚገባ ለማስተባበር እና ወጥነት ባለው መልኩ ለመተግበር ይረዳል፡
- በሂደቱ በህገ-መንግስቱ መሰረት በፌዴራል መንግስቱ ስልጣን ማእቀፍ የሚያርፉ ጉልህ የሰብዐዊ መብት ጥሰቶችን የሚመለከቱ አሰራሮች ይካተታሉ፡
- ክልሎች በራሳቸው የተፈፀሙ ጥሰቶችን ገለልተኛ ሆነው ያጣራሉ የሚል እምነት ስለማይኖር ፖሊሲውን ሀገራዊ መልክ ማስያዝ ያስፈልጋል፡
- አሁን ባለው የፖለቲካና የብሄር ጽንፈኝነት እና ጎጠኝነት በሰፈነበት ነባራዊ ሁኔታ ክልሎች እንዲህ አይነቱ ሀላፊነት ቢሰጣቸው ፍትሃዊና ገለልተኛ ሆነው ይወጡታል የሚል እምነት የለም፡ በመሆኑም በሀገር-ዓቀፍ ደረጃ የሚቋቋም ተቋም የሚመራው ብሄራዊ የሽግግር ፍትሕ ሂደት ማቀም ይገባል፡
- ሆኖም ብሄራዊው ሂደት ክልሎችን አሳታፊ ያደረገ መሆን አለበት፡ ክልሎች የማገዝ ሚና እንዲኖራቸው ሆኖ የሚቋቋም የሽግግር ፍትህ አሰራር ዓላማውን የማሳካት እድሉ ከፍ ያለ ነው፡
- ክልሎች ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን መቀበል እና መደገፍ አለባቸው ሲባል ይህ ሀላፊነት መድረኮችን ማመቻቸት፡ አስቻይ ሁኔታ መፍጠር፡ ለተቋማዊ ሪፎርም ዝግጁ መሆን፡ የጸጥታ እገዛ ማድረግ፡ በቅንነት ለተግባራዊነቱ መሥራት፡ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር ማጠናከር፡ የማህበረሰብ ተሳትፎን ማስተባበር፡ ተገቢው መረጃ መስጠት፡ የባህላዊው ስርአት አተገባበርን ማሳለጥ፡ እና የመሳሰሉ ድጋፎች ማድረግን ያካትታል፡

- ሆኖም ክልሎች ክልላዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውክልና ተሰጥቷቸው የሚሰሩበት እድል ሊኖር ይገባል፡ አንድን አካባቢ ብቻ የሚመለከት የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ስራ ሲኖር በዚህ ዙሪያ ሕግ እንዲያወጡ ወይም አሰራር እንዲዘረጉ ስልጣን ቢኖራቸው ይበልጥ ውጤታማ ያደርጋል፡ ይህ ካልሆነ ለሌላ ውጥረት ወይም ግጭት መነሻ ሊሆን ይችላል።

**ለ. በተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቡድን የተደገፈ አማራጭ፡ 'የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር'**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 24 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች መካከል 2 ቡድኖች (ወይም 8.33%) የሚሆኑት የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ በፌዴራል ይሁን በክልል ደረጃ እንደየሁኔታው ሊተገበር ይገባል፡ ክልሎች የራሳቸውን የሽግግር ፍትሕ እንዲተገብሩ እድል ሊሰጣቸው ይገባል የሚል ሀሳብ ሰጥተዋል።

ሰንጠረዥ 72፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 1 | 1 | 0 |
| 3 | አማራ | 5 | 5 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1 | 1 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 1 | 1 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 1 | 1 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 1 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 7 | 6.5 | 0.5 |
| 9 | ሲዳማ | 0 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 1 | 1 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 3 | 2 | 1 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 0 | 0 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 4 | 3.5 | 0.5 |
| | **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | 24 | 22 | 2 |

### 6.9.3. ሀገር-አቀፍ የቡድኖች ማጠቃለያ

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ 216 ቡድኖች መካከል 192 ቡድኖች (ወይም 88.89%) የሚሆኑት በሽግግር ፍትህ ሂደት የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ሚና በመተባበር እና ሂደቱን በመደገፍ ላይ የተገደበ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

በሌላ በኩል 15 ቡድኖች (ወይም 6.94%) የሚሆኑት - ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ሂደት ሊተገብሩ የሚችሉበት እድል ሊሰጣቸው እንደሚገባ አመልክተዋል።

ሌሎች 6 ቡድኖች (ወይም 2.78%) የሚሆኑት ደግሞ የተለያዩ አዲስ አማራጮችን ያቀረቡ ሲሆን፡ ተጨማሪ 3 ቡድኖች በዚህ ጥያቄ ላይ ሀሳብ አልሰጡም።

**ግኝቱ ከክልል እና ከተማ አስተዳደር አንጻር ሲተነተን**

ሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ሊባል በሚችል ደረጃ አማራጭ አንድን በመደገፍ በብሄራዊ ደረጃ በሚተገበረው የሽግግር ፍትህ ስራ የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ሚና ሂደቱን በመደገፍና በማስተባበር ሊወሰን ይገባል ብለዋል። በአንጻሩ የሱማሌ ክልል ሁሉም ቡድኖች ክልሎች የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ሂደት ሊተገበሩ እንደሚገባ ገልጸዋል።

***ግኝቱ ከቡድኖች አንጻር ሲተነተን***

*በሁሉም ሀገራዊ ቡድኖች በወጥነት በአብዛኛቹ ቡድኖች የተደገፈው የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ሚና የሽግግር ፍትህ ሂደቱን በመደገፍና ከሂደቱ ጋር በመተባበር ላይ ያተኮረ መሆን አለበት የሚለው ሀሳብ ነው።*

***ሀ. በሀገር-አቀፍ ደረጃ በአብዛኛቹ ቡድኖች የተደገፈ አማራጭ፡ 'ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ ሂደትን ማገዝ' - ምክንያቶች***

- *በሽግግር ፍትህ ሒደት የሚታዩ ጉዳዮች ከሀገራችን ታሪካዊ ኩነቶች፣ የግጭት አዙሪቶች እና ሰፋፊ/ከባድ ጥሰቶች ጋር ግንኙነት ስላላቸው በአንድ ክልል አሰራር ብቻ ሊታዩ የሚችሉ አይደሉም፡*
- *የሽግግር ፍትሕ መሰረታዊ አላማ ዜጎች ለደረሰባቸው ጉዳት ተገቢውን ፍትህ መስጠት እና ዘላቂ ሰላም እና መግባባትን መፍጠር እንደመሆኑ መጠን በይዘቱ ዜጋ-ተኮር እና ሀገራዊ ምልከታ ያለው ነው፣ በአንድ የአስተዳደር ወሰን የተከለለ አይደለም፡ በመሆኑም ክልሎች ሂደቱን በተናጠል የሚተገብሩበትን አሰራር መፍቀድ ከመነሻ ዓላማው ጋር ይቃረናል፡*
- *በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የሚታሰቡ ጉዳዮች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በስልጣን ክፍፍል መርህ መሰረት የሚታዩ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይ የሂደቱ አንኳር የሆነው ከባድ ወንጀሎችን ማየት በፌዴራል መንግስት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፣ በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የሚዳሰሱ ብዙዎቹ ጉዳዮች ከባድ ወንጀሎች/ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን የሚመለከቱ ናቸው፡*
- *በክልል ደረጃ የሚተገበር አሰራር በክልሉ የሚኖሩ ሁሉንም ብሔሮች የሚያካትት ላይሆን ይችላል፡ አሊያም በክልሉ ለሚገኙ ሌሎች ብሔሮች የማይመች ወይም የማይመረጥ ሊሆን ይችላል፡*
- *በተለይ የሚታየው ጉዳይ በሁለት ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦችን የሚመለከት ሲሆን በክልል የሚተገበር ሂደት ጠቃሚነት/ተገቢነት አይኖረውም፣ በፌዴራል ስልጣን ስር የሚወድቅም ይሆናል፡*
- *ክልሎች የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ መርሀ-ግብር ይተግብሩ ቢባል አሁን ላይ በሰፊው ከሚስተዋለው የፖለቲካ እና የብሄር ጽንፈኝነት እንዲሁም ጎጠኝነት ከሰፈነበት ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ፍትሃዊ እና ገለልተኛ ሆነው ሀላፊነቱን ይወጡታል የሚል እምነት አነስተኛ ነው፡*
- *በየክልሉ የሚስተዋለው የብሄር ክፍፍል ስራት እና የሙስና ሰንሰለት የትኛውንም የሽግግር ፍትህ ሂደት ሊያደናቅፍ ይችላል፡*
- *የሽግግር ፍትህ ሂደት በክልል ደረጃ ቢከናወን በብሔር፡ በሃይማኖት ወይም በሌላ ማንነት ላይ በመመስረት ወንጀሎኞችን የመሰወር እና ተጠያቂነትን የማዳከም ስራዎች የመሰራት እድላቸው የሰፋ ነው፡*
- *እንዲያም ሆኖ መርሀ-ግብሩ ሀገራዊ ይሁን ማለት ክልሎች ምንም ሚና አይኖራቸውም ማለት አይደለም፡ ክልሎች ጥሰቶች በማን፡ መቼ እና የት እንደተፈጠሩ፡ ምን አይነት ጉዳት እንደደረሰ በቅርበት ስለሚያውቁ በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜት ሂደቱን ማገዝ ይኖርባቸዋል፡ ጥፋተኛ የሆኑ የክልልና እና የከተማ አስተዳደር ሃላፊዎችን ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ለሕግ አሳልፈው ሊሰጡ ይገባል፡*
- *ክልሎች ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን መቀበል እና መደገፍ አለባቸው ሲባል ለደረሰው የከፋ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሀላፊነት መውሰድ፡ እንዳይደገም አስፈላጊ እና በቂ እርምጃ መውሰድ፡ መተማመኛ መስጠትን፡ መድረኮች ማመቻቸትን፡ አስቻይ ሁኔታ መፍጠርን፡ ለተቋማዊ ሪፎርም ዝግጁ መሆንን ያካትታል፡*
- *በተጨማሪም ክልሎች ተጎጂዎችን በመለየት ለተጎጂዎች ለሚሰጥ ማካካሻ ገንዘብ በማዋጣት አለባቸው፡ ተጎጂዎችን መልሶ በማቋቋም፡ የስራ እድል በመፍጠር፡ የማስታወሻ ስራዎችን በማከናወን፡ የሽግግር ፍትሕ ሂደቱን የሚያግዝ የአሰራር ማዕቀፍ በክልል ደረጃ በማዘጋጀት፡ እውነትን እና ማስረጃን በማፈላለግ፡ የማህበረሰብ ተሳትፎን በማስተባበር፡ እና ተጠያቂዎችን በመለየት መሳተፍ ይኖርባቸዋል፡*

- በሌላ በኩል አንድን አካባቢ ብቻ የሚመለከት የሽግግር ፍትህ ርእሰ-ጉዳይ ሲኖር በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ክልል-አቀፍ ስራ እንዲያከናውኑ አሊያም ክልላዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውክልና እንዲሰጣቸው ማድረግ በመጨረሻ አማራጭነት ሊታይ ይችላል፡ ይህን ማድረግ በክልሎችና በፌዴራል መንግስቱ መካከል ጤነኛ ግንኙነት እንዲኖር ያስችላል።

**ለ. በተወሰኑ ሀገራዊ ቡድኖች የተደገፈው አማራጭ፦ 'ክልሎች የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ መተግበር አለባቸው'**

- አንድ አይነት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የግድ ያስፈልጋል ማለት አይገባም፡ ክልሎች እንደየተጨባጭ ሁኔታቸው የየራሳቸው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡
- የተለያዩ ማንነቶች፡ የተለያዩ ችግሮች እና የተለያዩ መፍትሔዎች ስላሉ እንደየባህሪያቸው ክልሎች የራሳቸው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ቢተገበሩ ይመረጣል።

ሰንጠረዥ 73፡ ሀገራዊ የአራቱም ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ፡ በክልል

| | ክልል/ከተማ መስተዳድር | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ሌላ/አዲስ አማራጭ | ሌላ/አዲስ አማራጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | 8 | 6 | 2 | 0 | 0 |
| 2 | አፋር | 5 | 5 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | አማራ | 32 | 32 | 0 | 0 | 0 |
| 4 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 9 | 9 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | ድሬዳዋ | 5 | 4 | 1 | 0 | 0 |
| 6 | ጋምቤላ | 5 | 5 | 0 | 0 | 0 |
| 7 | ሀረሪ | 4 | 4 | 0 | 0 | 0 |
| 8 | ኦሮሚያ | 62 | 59.5 | 0.5 | | 2 |
| 9 | ሲዳማ | 4 | 4 | 0 | 0 | 0 |
| 10 | ሶማሌ | 11 | 2 | 9 | 1 | 0 |
| 11 | ደቡብ ህ/ብ/ብ | 39 | 37 | 1 | 0 | 2 |
| 12 | ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ | 8 | 8 | 0 | 0 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 24 | 21.5 | 0.5 | 2 | 1 |
| **ሀገር-አቀፍ ማጠቃለያ** | | 213 | 192 | 15 | 6 | 3 |

ሰንጠረዥ 74፡ ሀገራዊ የአራቱም ቡድኖች ሀሳብ ማጠቃለያ: በቡድን

| | | ጠቅላላ የቡድኖች ብዛት | አማራጭ 1 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አማራጭ 2 የደገፉ ቡድኖች ብዛት | አዲስ አማራጭ የደገፉ ቡድኖች ብዛት | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **አገራዊ የሴት ተሳኚ ቡድኖች ማጠቃለያ** | 49 | 42 | 5 | 2 | |
| 2 | **አገራዊ የወንድ ተሳኚ ቡድኖች ማጠቃለያ** | 47 | 41 | 4 | 2 | |
| 3 | **አገራዊ የቅልቅል ቡድኖች ማጠቃለያ** | 96 | 87 | 4 | 2 | 3 ቡድኖች ሀሳብ አልሰጡም |
| 4 | **አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቡድኖች ማጠቃለያ** | 24 | 22 | 2 | 0 | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አገራዊ የአራቱም የትኩረት ቡድኖች ማጠቃለያ | | 216 | 192 | 15 | 6 | 3 |
| | | | | | | |

### 6.9.4. ልዩ ትኩረት ከሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ማጠቃለያ

በዚህ የፖሊሲ ጥያቄ ላይ በሁሉም መድረኮች የተገኙ የተለያዩ ተሳታፊዎች የሽግግር ፍትህን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የክልሎች እና የከተማ አተዳደሮች ሚና ከፍተኛ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ክልሎች ሀገራዊ የሽግግር ፍትህ መርህ-ግብሩን ተቀብለው የማስፈፀም ቁርጠኝነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተነስቷል፡፡

በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተም በጥናት ላይ ተመስርቶ የሚለይ ድጋፍ የመስጠት፣ የማስተባበር፣ ህዝብን ከሚመለከታቸው የሂደቱ አካላት ጋር የማስተሳሰር፣ መረጃ የማዘጋጀት፣ ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት፣ እና ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ስራዎችን ሊያካትት እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ክልሎች በዘፈቀደ በሂደቱ ጣልቃ እንዳይገቡ ተገቢ መርሆች መቀረፅ እንደሚኖርባቸው ተመላክቷል፡፡

የተወሰኑ ተሳታፊ የቡድን አባላት ደግሞ የሽግግር ፍትህ ሂደት በማእከል እና በክልል አስተዳደሮች ተከፋፍሎ መተግበር አለበት የሚል ሀሳብ ይዘው ተከራክረዋል፡፡ ክልሎች በጉዳዩ ላይ እንዲያምኑበት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት እንደሚገባ፣ በፖሊሲ ቀረጻ ሂደትም ክልሎችን በሚገባ ማሳተፍ እንደሚያስፈልግ፣ በፌዴራልም ይሁን በክልል ደረጃ ያሉ ሃላፊዎች ለመተባበር እና ለተጠያቂነት ዝግጁ መሆን እንደሚኖርባቸው፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በክልሎች መካከል ያለውን መስተጋብር ወደ ሰላማዊ ሁነት ለመመለስ መዘጋጀት እንዳለባቸው ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

### 6.9.5. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የቀረቡ ግብዓቶች ማጠቃለያ

በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ክልሎች እና የከተማ መስተዳደሮች ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና በተመለከተ ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሰጡት አስተያየት የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሁሉንም ክልሎች እና የማህበረሰብ ክፍሎች የሚመለከት ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን የፌዴራል መንግስቱ ፖሊሲ የማውጣትና የማስፈጸም ሃላፊነት አለበት የሚል ሀሳብ አንፀባርቀዋል፡፡ ሆኖም የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት በፌዴራልና በክልሎች መካከል ሕገ-መንግስቱን መሠረት ያደረገ ግልጽና ውጤታማ ውይይት መካሄድ እንደሚኖርበት በአጽንኦት ተመላክቷል፡፡

የክልሎች ዝርዝር ሚናን አስመልክቶ በተሳታፊዎች በተሰጡ ምክረ-ሃሳቦች ላይ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያው - ሚናቸው ከብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሃ-ግብሩ ጋር በመተባበር፣ በመናበብ እና በመቀናጀት የተለያዩ ተግባራትን መፈፀም፣ ህገ-መንግስትን ጨምሮ ህጎችን በማሻሻል የተቋማዊ ማሻሻያ ስራዎችን ማከናወን፣ እና ባህላዊ የፍትህ እና እርቅ ስርአቶች ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ በማመቻቸት ላይ ያተኮረ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ በምክንያትነትም የሚከተሉት ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- የክልል አስተዳደሮች በሽግግር ፍትህ ሂደት ተግባራዊ ተሳትፎ የሚኖራቸው ከሆነ የሂደቱን ውጤት የመቀበል እድሉ የሰፋ ነው፣
- ክልላዊ መንግሥታት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያደረጉት ተሳትፎ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዳለው ከልምድ ይታወቃል፣
- ክልሎች በሂደቱ ካልተሳተፉ ስራውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ይቸግራል፣ በአፈጻጸም ደረጃ ፈተና ሊገጥም ይችላል፣ የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ሂደት ለመመስረት ሊገፋፉም ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል የቀረበው የልዩነት ሀሳብ ክልሎች ሂደቱን ከመደገፍ ባለፈ ቀጥተኛ ተሳትፎ/የመሪነት ሚና ሊኖራቸው አይገባም የሚል ነው፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የቀረበው - ክልሎች የሚወክሉትን ማህበረሰብ ብቻ የሚያገለግሉ መሆናቸው፣ በአሁኑ ጊዜ የክልል መንግሥታት እንደ ሉዓላዊ ሃገር እየሰሩ ያሉ መሆኑ፣ የስልጣን ወሰናቸውን የሚያልፉበት አጋጣሚ ብዙ መሆኑ፣ ለአድልዎ የተመቸ አሰራር ስላላቸው - በሽግግር ፍትህ ሂደት ማእቀፍ

ሀላፊነት ቢሰጣቸው ውስብስብ ችግርን ያስከትላል የሚል ነው። ይሁን እንጂ ክልሎች ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ የሎጂስቲክስ እና የአሰራር ድጋፍ ማቅረብ ያለባቸው መሆኑን የሚያመለክት ሀሳብም ተንፀባርቋል።

## ክፍል ሰባት

## ማጠቃለያ

በተለያዩ ጊዜያት በአፍሪካ ህብረት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከወጡ የሽግግር ፍትሕ ሰነዶች ለመረዳት እንደሚቻለው 'የሽግግር ፍትሕ' የሚለው ፅንሰ-ሀሳብ አገራት ያለፉ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ መከፋፈሎች፣ ቁርሾዎች፣ የእርስ በእርስ ግጭቶች ወይም ጦርነቶች፣ የእኩልነት ዕጦት፣ ኢ-ፍትሀዊነትን፣ የእርስ በእርስ አለመተማመን እና የተዛቡ ግንኙነቶችን በዘላቂነት በመፍታት - በቀጣይ ሰላም፣ አንድነት፣ ፍትሕ፣ እኩልነት፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ የሕግ የበላይነት፣ መተማመን እና ማህበራዊ እና ኢኮኖሚዊ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚጠቀሙበት ሥርዓት ነው።

ዛሬ ላይ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ሀገራት በሽግግር ፍትሕ ሂደት አልፈዋል። ሀገራቱ በጥንካሬም ሆነ በድክመት ሊነሱ የሚችሉ የአተገባበር ስልቶችን ተፈፃሚ አድርገዋል። ሁሉም ባይሆኑም በርካታ ሀገሮች ከሂደቱ መልካም ውጤት አግኝተዋል። ሀገርን ከመፍረስ፣ ህዝባቸውንም ከመበተን አድነዋል። ዘላቂ ሰላምን አፅንተዋል።

የሽግግር ፍትሕ ስራ የተሟላ እና ዘላቂ መፍትሔ እንዲሰጥ ተጎጂ-ተኮር፣ አሳታፊና አካታች የሆነ የምክክር እና የአተገባበር ሂደትን መከተል ይኖርበታል። ሂደቱ የተለያዩ የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን በተጣጣመና በተቀናጀ መልኩ የሚተገብር፣ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የፍትሕ ሥርዓቶችን እንደአስፈላጊነታቸው አቀናጅቶ የሚጠቀም፣ እንዲሁም የሀገርን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የሚከናወን መሆን እንዳለበት የሽግግር ፍትሕ ሂደትን መሰረታዊ መርሆዎች ከደነገጉ አህጉራዊና ዓለም-አቀፋዊ ሰነዶች እና ከሀገራት ተሞክሮዎች መገንዘብ ይቻላል።

በሀገራችን የሽግግር ፍትሕ ትግበራን የሚሹ የቆዩ እና የቀጠሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ ግጭቶች፣ ትርክቶች እና የአለመተማመን ሁነቶች አሉ። ከመንግስታት ለውጥ ጋር ተያይዞ - በተለይም በድህረ-ደርግ እና ድህረ-ኢህአዴግ የስልጣን ዘመናት የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን በተበጣጠሰና ባልተቀናጀ መልኩ ለመተግበር ውስን ሙከራዎች ተደርገዋል። ከነዚህ ሙከራዎች ውጭ ለሀገራዊ ችግሮቹ ዘላቂ መፍትሔ የሚሰጥ የተሟላ የሽግግር ፍትሕ ስርአት በኢትዮጵያ ተተግብሮ አያውቅም።

*በሀገራችን ለዘመናት ሲንከባለሉ ለመጡና እና ስር ለሰደዱ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ከመስጠት አንፃር - ዛሬ ላይ የሽግግር ፍትህ ስርአት የመዘርጋት አስፈላጊነትን ያጎሉ በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። በ2013 ዓ.ም የተዘጋጀ የገለልተኛ ቡድን ዝርዝር ጥናት ይህን እውነታ አረጋግጧል። በተጨማሪም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከነበረው ጦርነት ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት በጣምራ ያከናወኑት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ምርመራ ውጤት - ሀገሪቱ የሽግግር ፍትህን ተግባራዊ እንድታደርግ ምክረ-ሀሳብ አቅርቧል። በሌላ በኩል በፌዴራሉ መንግስት እና በህወሀት መካከል በፕሪቶሪያ የተፈረመው የሰላም ስምምነት ከጦርነቱ ጋር ተያይዘው የተፈፀሙ ወንጀሎችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በሽግግር ፍትሕ ማእቀፍ ሊፈቱ እንደሚገባ አስገዳጅ አንቀፅ አካቷል።*

*በመሆኑም በሀገራችን አሳታፊ፣ አካታች፣ ከዓለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብት መርሆዎች እና ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣመ፣ መሰረታዊ የሽግግር ፍትሕ መርሆዎችን የተከተለ እና የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ የሽግግር ፍትሕ ስርአት መተግበር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። የሽግግር ፍትሕ ሂደቱን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማካሄድ እንዲቻልም የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ መቅረፅና ወደ ሥራ መግባት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ በመንግስት ታምኖበታል።*

*በዚህ እሳቤ መሰረት የፍትሕ ሚኒስቴር 'በሀገር-አቀፍ ደረጃ ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ሕዝባዊ ምክክሮችን በማካሄድ የፖሊሲ ግብዓት የማሰባሰብ እና ረቂቅ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የማዘጋጀት' ሙሉ ኃላፊነት የተሰጠው የሽግግር ፍትሕ የባለሙያዎች ቡድን ህዳር 2015 ዓ.ም እንዲቋቋም አድርጓል። የባለሙያዎች ቡድኑ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በሽግግር ፍትሕና ሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር ከሚያደርጉ ምሁራን፣ ከሰብዓዊ መብት ተከላካይ ባለሙያዎች፣ ከጥብቅና እና ምክር አገልግሎት ዘርፍ፣ ከሲቪል ማህበረሰብ እና ከፖሊሲና ሕግ ማርቀቅ ባለሙያዎች የተውጣጡ 13 አባላትን ያካተተ ነፃ እና ገለልተኛ ስብስብ ነው።*

*የባለሙያዎች ቡድኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አጠቃላይ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱን በሶስት ምዕራፎች በመከፋፈል 'የቅድመ-ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ'፣ 'የረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ' እና 'የድህረ-ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ' ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።*

*የባለሙያዎች ቡድኑ የተጣሉበትን ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነቶች ማከናወን ከመጀመሩ በፊት - ለህዝባዊ ምክክሮች መነሻ የሚሆን የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮችን የሚያሳይ ሰነድ አዘጋጅቷል። በተጨማሪም የምክክር እና ግብአት ማሰባሰብ ሂደቱ እና የባለሙያዎች ቡድኑ የሚመሩባቸው የተለያዩ ሰነዶችን በማዘጋጀት ወደ ስራ ገብቷል።*

*ቡድኑ በቅድመ-ረቂቅ ፖሊሲ ዝግጅት ምዕራፍ ካከናወናቸው ሥራዎች መካከል አንዱና ዋናው ህዝባዊ ምክክሮችን በሀገር-አቀፍ ደረጃ በማከናወን የፖሊሲ ግብዓቶችን የማሰባሰብ ሥራ መስራት ነው። ይህ አካሄድ 'የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱ' እና ወደፊት የሚወጣውን 'የሽግግር ፍትሕ ሀገራዊ ፖሊሲ' ተአማኒነት፣ አሳታፊነት፣ አካታችነት፣ ፍትሐዊነት እና ህዝባዊ ተቀባይነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።*

*በመሆኑም የባለሙያዎች ቡድኑ ይህን ወሳኝ የሥራ ሂደት ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን በርካታ የቅድመ-ምክክር ሥራዎችን አከናውኗል። ከነዚህ ሥራዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።*

- *መሰረታዊ የሽግግር ፍትሕ መርሆዎችን ታሳቢ ባደረገ መንገድ የምክክር መድረክ ተሳታፊዎች የሚመለመሉበትን መስፈርት የማዘጋጀት፡*
- *በሀገር-አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎች በሚካሄዱ የምክክር መድረኮች ላይ የሚሳተፉ የማህበረሰብ ክፍሎችን እና ሰዎችን አስቀድመው የሚለዩ፣ ህዝባዊ ምክክር የሚደረግባቸውን ቦታዎች የሚያመቻቹ እና የምክክር መድረኮችን እለታዊ ኡደት የሚያስተባብሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን የመመልመል እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን የመስጠት፡*

- የተሳታፊዎችን ፅንሰ-ሀሳባዊ ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችል የሽግግር ፍትሕን ምንነትና ዓላማን የሚያስገነዝብ አጭር መግለጫ/ሲኖፕሲስ የማዘጋጀት፡
- ለምክክር ሂደት ተሳታፊዎች የሚቀርቡ የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦች ሰነድ የማዘጋጀት፡
- በየምክክር መድረኮቹ ላይ የተገኙ ተሳፊዎች ከሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጮች ጋር በተያያዘ የሚወያዩባቸውን ጥያቄዎች የማዘጋጀት፡
- የምክክር መርሀ-ግብሮችን በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ የሚያስችሉ የባለሙያዎች፣ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣ የትራንስፖርት እና የፋይናንስ ዝግጅቶችን የማመቻቸት፡
- እንዲሁም በአስተባባሪዎች የተመለመሉ ተሳታፊዎችን ከተቀመጡ መስፈርቶች አንፃር በትክክል የተመረጡ መሆናቸውን የማረጋገጥና የማስተካከያ እርምጃዎችን የመውሰድ።

የሽግግር ፍትሕ የቅድመ-ምክክር የዝግጅት ሥራዎች ከላይ በተገለፀው አግባብ ከተጠናቀቀ በኋላ የባለሙያዎች ቡድኑ ባወጣው ሀገር-አቀፍ መርሃ-ግብር መሰረት የፖሊሲ ግብዓት ማሰባሰቢያ ህዝባዊ የምክክር መድረኮችን ወደ ማካሄድ ሥራ ገብቷል። በዚህ አግባብ የፖሊሲ ግብዓት ማሰባሰቢያ ማስጀመሪያ መርሀ-ግብሩ - የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣ ሚኒስትሮች፣ አምባሳደሮች፣ የክልል ፕሬዝደንቶች፣ የፍትህ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች፣ የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ኮሚሽነሮች፣ የፀጥታና የደህንነት ተቋማት ኃላፊዎች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት የካቲት 27/2015 ዓ.ም በይፋ እንዲጀመር ተደርጓል።

ይህን ተከትሎም ከየካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ መስከረም 30/2016 ባለው የስምንት ወራት ጊዜ ውስጥ በድምሩ 80 የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የግብዓት ማሰባሰቢያ የምክክር መድረኮች በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋ እና በሁሉም ክልሎች ተከናውነዋል። በሂደቶቹም ከተሳታፊዎች እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ከፍተኛ መጠን ያለው ግብዓት ተሰብስቧል።

በምክክር መድረኮቹ ላይ የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጎጂዎች፣ ሴቶች እና የሴቶች ማህበራት ተወካዮች፣ ወጣቶች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ተፈናቃዮች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የሽግግር ፍትሕ ኤክስፐርቶች፣ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ተቋማት/ተወካዮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች እና አመራሮች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ የሚዲያ ባለሙያዎች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የህፃናት መብት አስጠባቂ ድርጅቶች፣ የሠራተኞች ማህበራት፣ የንግድ ማህበረሰብ ተወካዮች፣ የፍትህ አካላት ሀላፊዎች፣ የፀጥታ ዘርፍ ባለሙያዎች/ኃላፊዎች፣ የፌዴራል ተቋማት ኃላፊዎች፣ የክልል ተቋማት ኃላፊዎች እና ዓለም-አቀፍ የሽግግር ፍትሕ ባለሙያዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል።

ሀገር-አቀፍ የምክክር ሂደቱ የተመራበትንና ግብዓት የተሰበሰበበትን አግባብ በተመለከተ - በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ ላይ በአማካይ ስልሳ ሰው እንዲሳተፍ ተደርጓል። የፆታ ተዋጽኦን በተመለከተ ከአጠቃላይ ተሳታፊዎች ውስጥ ሀምሳ በመቶ የሚሆኑት ሴቶች እንዲሆኑ፡ እንዲሁም ከአጠቃላይ ተሳታፊዎች ስልሳ በመቶ የሚሆኑት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች እንዲሆኑ ግልፅ የአሰራር ፕሮቶል በማውጣት እንዲተገበር ተደርጓል።

ግብዓት የማሰባሰብ ሂደቱን በተመለከተ አይነታዊ የመረጃ አሰባሰብ ሥነ-ዘዴን በመጠቀም - በዋናነት የፕሌናሪ የውይይት መድረክ እና የትኩረት ቡድን ውይይቶችን በማመቻቸት ቀጥተኛ መረጃ እንዲሰበሰብ ተደርጓል። በተጨማሪም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦቹ ላይ የፅሁፍ አስተያየቶች ቀርበዋል።

የህዝባዊ ምክክሮች ሁሉ የህዝብን ተሳትፎ እና ወሳኝነት መብት ባስጠበቁ መልኩ እንዲካሄዱ ተደርገዋል። ከዚህ ባለፈም ሂደቶቹ የተሳታፊዎችን ማንነት እና ግላዊ ምልከታ ሚስጥራዊነትን በጠበቀ፣ እንዲሁም ለተጎጂዎችን እና ልዩ ትኩረት ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ሃሳብና አስተያየት ትኩረት በሚሰጥ መንገድ ተከናውነዋል።

ከውይይት መድረኮቹ የተገኙ ግብዓቶችን በአግባቡ አደራጅቶ ከመያዝ አንፃርም - በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ በተሳታፊዎች የተነሱ ሃሳቦች፣ አስተያየቶች እና በመወያያ ጥያቄዎቹ ላይ የተሰጡ ምላሾች፣ እንዲሁም በብዙሃኑ ተሳታፊዎች እና በጥቂት ተሳታፊዎች የተደገፉ ወይም በልዩነት የተነሱ ሃሳብ/አስተያየቶች - ዓለም-አቀፍ የሰብዓአዊ መብት እና የሽግግር ፍትህ መርሆዎችን በተከተለ መልኩ በቃለ-ጉባኤ እንዲያዙ ተደርገዋል። በተሳታፊዎች ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ በመመስረትም ሁሉም የትኩረት ቡድኖች ውይይቶች በመቅረፀ-ድምጽ ተይዘዋል። በመቅረፀ-ድምጽ የተያዙ ሃሳቦች ወደ ፅሁፍ እንዲቀየሩ በማድረግ - በተሳታፊዎች የተሰጡ ሀሳቦችና አስተያየቶች ሳይበረዙ በተሰጡበት አግባብ ለሪፖርት ትንተና እና ለፖሊሲ ቀረፃ ግብዓትነት በሚያመች አኳኋን ተለይተው እንዲደራጁ ተደርገዋል።

በዚህ አግባብ - በሀገራዊ የግብዓት ማሰባሰብ ምክክሮች ሂደት - ውይይት በተካሄደባቸው የፖሊሲ አማራጭ ጥያቄዎች ላይ በተሰበሰበው ግብዓት ላይ **የተንፀባረቁ ዋና ዋና ግኝቶች** እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።

በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ላይ በቀዳሚነት ለውይይት የቀረበው የፖሊሲ ጥያቄ **የወንጀል ተጠያቂነትን** የሚመለከት ነው። በዚህ የፖሊሲ አማራጭ ስር አራት ጥያቄዎች ውይይት ተካሄዶባቸዋል።

በወንጀል ተጠያቂነት ስር የመጀመሪያው ጥያቄ '**በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል**' የሚለው የፖሊሲ ጥያቄ ነው። በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ አብዛኛዎቹ 'የትኩረት ውይይት ቡድኖች'፣ እንዲሁም 'ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች' እና 'ሌሎች ባለድርሻ አካላት' የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ '**ጉልህ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል**' ብለዋል። ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የትኩረት ውይይት ቡድኖችም 'በሁሉም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር እንደሚገባ' የፖሊሲ ምርጫቸውን ገልጸዋል።

'ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' ያሉ ቡድኖች አቋማቸውን የሚያጠናክሩ በርካታ ምክንያቶችን አቅርበዋል። በዋናነትም ይህ አማራጭ ከዓለም-አቀፍ ስምምነቶች እና ተሞክሮዎች ጋር የሚጣጣም መሆኑን፣ ሁሉንም ወንጀሎች ያካተተ የክስ ሂደት ማካሄድ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽእኖ በማንሳት፣ የጥሰቶች መጠን፣ ስፋት እና የአጥፊዎች ብዛት የሚወስደውን ጊዜ እና ሀብት ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ እና አቅም ጋር በማመዛዘን፣ እንዲሁም ከተግባራዊነት እና ከሽግግር ፍትህ ዓላማ ጋር በማገናዘብ ዝርዝር መከራከሪያዎችን አንስተዋል።

በክስ ሂደቱ ሊታዩ የሚገባቸው ጉዳዮችን በተመለከተ - በጉልህ ጥሰቶች ላይ የሚመሰረት ክስ ሂደት የተጋላጭ የማህረሰብ ክፍሎችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ሊያስገባ እንደሚገባ፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ማካተት እንዳለበት፣ እንዲሁም ተያያዥ አካላዊ፣ ስነልቦናዊ እና ማህበራዊ ጥቃቶችን መሸፈን እንዳለበት ተመላክቷል።

በአንጻሩ 'በሁሉም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት' ሊኖር እንደሚገባ የደገፉ ተሳታፊዎች የወንጀል ትንሽና ትልቅ የሌለ መሆኑን፣ ተጠያቂነትን በሁሉም ጥሰቶች ላይ ሊሰፍን እንደሚገባ፣ በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ለቀጣይ ወንጀል መስፋፋት አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን፣ በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፣ ፍትህ ለማስፈን፣ የተጎጂዎችን ቁስል ለማከምና ማህበረሰባዊ ትስስርንና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የተሻለ ሚና ያለው መሆኑን በማንሳት ተከራክረዋል።

በወንጀል ተጠያቂነት ስር የቀረበው ሁለተኛው ጥያቄ '**በየትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል**' የሚል ነው። በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ አብዛኞቹ የትኩረት ውይይት ቡድኖች፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት '**ከፍተኛ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል**' ብለዋል። የተወሰኑ የትኩረት ውይይት ቡድኖች ደግሞ 'በማንኛውም ደረጃ የተሳተፉ አጥፊዎችን ያካተተ የክስ ሂደት' ሊኖር እንደሚገባ የፖሊሲ ምርጫቸውን ገልጸዋል።

'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' ሲሉ አቋማቸውን የገለፁ ቡድኖች ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች በተለያዩ መለኪያዎች ሊለዩ እንደሚገባ አመላክተዋል። ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ማተኮር ከጊዜ፣ ከገንዘብ፣ ከተፋጠነ ፍትህ እና ከተግባራዊነት አንጻር ተመራጭ መሆኑን፣ እንዲሁም ይህ አማራጭ ሌሎች የሽግግር ፍትህ አላባዎችን ለመተግበር እድል የሚሰጥ በመሆኑ ይበልጥ ተገቢ እንደሚያደርገው ገልፀዋል።

በአንጻሩ 'በሁሉም አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' ያሉ የትኩረት ውይይት ቡድኖች የሰብዓዊ መብት ጥሰት የማይከፋፈል እና የማይበላለጥ መሆኑን በመግለፅ ሁሉም አጥፊ እንደየተሳትፎ ደረጃው ተጠያቂ ሊሆን እንደሚገባ ተከራክረዋል።

የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ የቀረበው ሶስተኛው የፖሊሲ ጥያቄ '**ክስን መስማትና ውሳኔ መስጠት በየትኛው የፍርድ ቤት አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል**' የሚል ነው። በፖሊሲ ጥያቄው ላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ካደረጉ የትኩረት ውይይት ቡድኖች አብዛኞቹ፣ እንዲሁም ብዙዎቹ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች እና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳታፊዎች '**አዲስ ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም የተጠያቂነት ሂደቱን ማከናወን ያስፈልጋል**' የሚል አቋም አንፀባርቀዋል። የተወሰኑት የትኩረት ውይይት ቡድኖች ደግሞ ሂደቱ 'በፌደራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ልዩ ችሎት በማቋቋም፡ ብቁ የሆኑና ልምድ ያላቸውን ዳኞች በመመደብ፡ ነፃና ገለልተኛ ሆነው እንዲሰሩ ማድረግ' የተሻለ ይሆናል ሲሉ፣ ጥቂት ቡድኖች ደግሞ ሂደቱ 'አዲስና ገለልተኛ በሆነ ቅይጥ ፍርድ ቤት ወይም በዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤት' አማካኝነት መካሄድ አለበት በማለት አዲስ አማራጭ አቅርበዋል።

ይህን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ ተጨማሪ ምክረ ሃሳቦችም ተሰጥተዋል። ገለልተኛ ተቋም በመመስረት ሂደት አስፈጻሚው አካል ተሳትፎ ሊኖረው እንደማይገባ፣ በተለይም የዳኞች መረጣ ሂደት እና የአሰራር ሥርዓቱ አደረጃጀት ሙሉ ለሙሉ በገለልተኛ አካል መከናወን እንዳለበት፣ የዳኞች አቅም ግንባታና የፍትህ ተቋማት ማሻሻያ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ፣ በአደረጃጀት ሂደትም ቢያንስ ልምድ ያላቸው የውጭ ተቋማትን ማካተት እንደሚያስፈልግ ተመላክቷል።

በሌላ በኩል ተጠያቂነትን ከማስፈን አንጻር ባህላዊ የፍትህ ተቋማትን በጥንቃቄ መለየት እና ከሴቶች መብቶች ጋር ተጣጥሞ የሚተገበር ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሚገባ ተጨማሪ ምክረ-ሃሳቦች ተሰጥተዋል።

የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ ግብዓት የተሰበሰበበት የመጨረሻው የፖሊሲ ጥያቄ '**የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ሂደትን በማን ሊያከናወን ይገባል**' የሚለው ነው። በዚህ የፖሊሲ ጥያቄ ላይ አብዛኞቹ የትኩረት ውይይት ቡድኖች፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች እና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳታፊዎች '**የምርመራ እና ክስ ስራዎች አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋም ውጭ ሌላ የምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም፣ የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ ሊከናወን ይገባል**' ብለዋል። የተወሰኑ ቡድኖች ስራው 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ህግ ተቋማት ውስጥ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ የክስ ሂደት ምርመራ እና ክስ ላይ የሚሳተፉ የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር ሊተገበር' ይገባል በማለት ሀሳባቸውን ገልፀዋል። ጥቂት ቡድኖች ደግሞ አዲስ የፖሊሲ አማራጭ በማቅረብ የምርመራ እና ክስ ስራዎች 'በዓለም አቀፍ ተቋም አማካኝነት ሊከናወኑ ይገባል' የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።

በምክንያትነት የቀረቡ ግብዓቶች ሲታዩ - የምርመራ እና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር አዲስ የዓቃቤ ሕግ ተቋም እንዲቋቋም የጠየቁ ተሳታፊዎች አሁን ላይ ያሉት ተቋማት ተአማኒነት፣ ቅቡልነት፣ ነጻነት እና ገለልተኝነት የሌላቸው መሆኑን፣ በሰብዓዊ መብት ጥሰቶችም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሲሳተፉ የነበሩ መሆናቸውን፣ በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ የሚታዩ ዓለም-አቀፍ እና ውስብስብ ወንጀሎችን ለመመርመር የሚያስችል

*ቁመና የሌላቸው መሆኑን፣ እንዲሁም አዲስ ተቋም ማቋቋም የህዝብ አመኔታ ችግርን ለማስተካከል የሚረዳ መሆኑን በመግለፅ አቋማቸውን አብራርተዋል።*

*በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ላይ ተካቶ ውይይት የተደረገበት እና ግብዓት የተሰበሰበበት ሁለተኛው የሽግግር ፍትህ አምድ '**እውነት ማፈላለግ እና የእርቅ ተግባራትን**' የሚመለከት ነው። በዚህ የፖሊሲ አማራጭ ላይ ሁለት የፖሊሲ ጥያቄዎች በማንሳት ውይይት ተደርጓል።*

*የመጀመሪያው ጥያቄ '**እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል**' የሚል ነው። አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ሂደቱ '**ሁሉንም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መሸፈን ይገባዋል**' ያሉ ሲሆን የተወሰኑ ቡድኖች ደግሞ ሂደቱ '**በተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ሊያተኩር ይገባል**' የሚለውን ሀሳብ ደግፈዋል።*

*በአብዛኛዎቹ ቡድኖች እምነት ጉልህ የሆኑ እና ያልሆኑ ጥሰቶችን መለያየት በህብረተሰቡ ውስጥ ቅሬታ እንዲቀጥል የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ሰብዓዊ መብቶች አይነጣጠሉም፡ አይበላለጡም፡ አይተናነሱም የሚለውን መርህ ያጠናክራል፣ የአንዱ መብት መጣስ ለሌሎች መብቶች መጣስ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረው በመሆኑ ተገቢውን ጊዜ፡ ሀብት እና የሰው ሀይል በመመደብ በሁሉም ጥሰቶች ላይ እውነት የማፈላለግን ተግባር ማከናወን ይገባል ብለዋል።*

*እውነት ማፈላለግና የእርቅ ተግባርን በተመለከተ በሁለተኛነት የቀረበው ጥያቄ '**እውነትን የማፈላለግና እርቅ የማውጣት ሂደትን በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል**' የሚል ነው። ይህን ጥያቄ በተመለከተ አብዛኛው የትኩረት ውይይት ቡድኖች፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሂደቱ '**አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ሊተገበር ይገባል**' ብለዋል። የተወሰኑ ቡድኖች ስራው በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ሊከናወን ይገባል ሲሉ፡ ሌሎች ቡድኖች ደግሞ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት መከናወን አለበት ብለዋል።*

*አዲስ የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ማቋቋምን የደገፉ ተሳታፊዎች በስራ ላይ ያሉ ተቋማትን ከመጠቀም ይልቅ ገለልተኛ፣ ነጻ እና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ያካተተ አዲስ ኮሚሽን ቢደራጅ ውጤታማ እውነት የማፈላለግ ሥራ ይሰራል በማለት አብራርተዋል። ሆኖም የኮሚሽኑ አባላት አመራረጥ ግልጽና አሳታፊ መሆን እንዳለበት፣ ከአስፈጻሚው ጣልቃ ገብነት ነጻ በሆነ መንገድ ሊከናወን እንደሚገባ፣ የሴቶችን ጉዳይ በልዩ ሁኔታ የሚያስተናግድበት አሰራር እና አደረጃጀት መዘርጋት እንደሚኖርበት፣ እና የሀገር ሽማግሌዎችንና እና የእምነት አባቶችን ማካተተ እንዳለበት ቡድኖቹ ምክረ-ሀሳባቸውን አጋርተዋል።*

*ሌላው ውይይት የተደረገበት የፖሊሲ አማራጭ ጥያቄ '**በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ምህረትን**' የሚመለከት ነው። በዚህም '**ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ መስፈርቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ**'፡ እንዲሁም '**የምህረት መስጠቱ ሂደት በማን ሊከናወን ይገባል**' በሚሉ የፖሊሲ ጥያቄዎች ላይ ውይይቶች ተካሂደዋል።*

*'ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ መስፈርቶች ምን ሊሆኑ ይገባል' የሚለውን ጉዳይ አስመልክቶ ተሳታፊዎች ተመሳሳይ ሊባል በሚችል ደረጃ ምህረት ከህገ-መንግስቱን አንቀጽ 28 እና የዓለም-አቀፍ ግዴታዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ብቻ መሰጠት እንዳለበት፣ እንዲሁም በማህበረሰቡ ላይ ትልቅ ጉዳት አድርሰዋል በሚል የተለዩ የወንጀል ድርጊቶች ምህረት ሊሰጥባቸው እንደማይገባ አንስተዋል። ከእነዚህ ውጭ ያሉ የወንጀል ድርጊቶች ግን በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ አመላክተዋል። በመሆኑም የአጥፊዎችን የተሳትፎ ደረጃ፣ የወንጀሎቹን አይነት እና የአፈጻጸም ሁኔታን መሰረት በማድረግ - ጥፋትን ማመን፣ መጸጸት፣ ይፋዊ ይቅርታ መጠየቅ፣ ካሳ መክፈል፣ ተመሳሳይ ድርጊት ላለመፈፀም ቃል መግባት እና ሌሎች የቅደመ-ሁኔታ ተግባራት ሲሟሉ ምህረት ሊሰጥ እንደሚገባ ገልጸዋል።*

‘**የምህረት መስጠቱ ሂደት በየትኛው ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል**’ የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ አብዛኛዎቹ የትኩረት ውይይት ቡድኖች፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ ህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ይህ የስራ ሂደት ‘**አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ሊተገበር ይገባል**’ ብለዋል፡፡ የተወሰኑ ቡድኖች ‘አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀትን በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ መጠቀም ይገባል’ የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል፡፡ ጥቂት ቡድኖች ደግሞ የተለያዩ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን ለምህረት ጉዳይ አቅርበዋል።

አብዛኛዎቹ ቡድኖች የምህረት መስጠት ተግባር አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ይከናወን ሲሉ በምክንያትነት አሁን ያለው የምህረት ቦርድ የብቃት፣ የገለልተኝነት እና የአሳታፊነት ችግር ያለበት መሆኑ፣ እንዲሁም በእስካሁኑ ጉዞው ውጤታማ ስራ አለመስራቱን መነሻ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም ምህረት ሊሰጥ የሚገባው እውነቱን ባፈላለገው እና በቂ መረጃ በሚኖረው ነጻና ገልለተኛ አካል መሆን እንዳለበት አስቀምጠዋል፡፡

ሌላው ውይይት የተደረገበት እና ግብዓት የተሰበሰበበት የፖሊሲ አማራጭ ጉዳይ ‘**ማካካሻን**’ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ አማራጭ ስር ሶስት የፖሊሲ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

‘**የማካካሻ ሂደቱ በየትኞቹ ተጎጂዎች ላይ ሊያተኩር ይገባል**’ የሚለው የፖሊሲ ርእስን በተመለከተ - ጥያቄው አማራጮችን ሳይዘረዝር ተሳታፊዎች ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተጎጂዎችን በምክንያት አስደግፈው እንዲገልጹ ቀርቧል፡፡ ብዙዎቹ ተሳታፊዎች በመርህ ደረጃ ለሁሉም ተጎጂዎች እንደየጉዳታቸው መጠን ማካካሻ መስጠቱ ተገቢ መሆኑን ገልጸው - ሆኖም የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተጎጂዎችን ዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው ተጎጂዎች፣ ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች እና ህጻናት፣ የተፈናቀሉ ወገኖች፣ በጦርነት ምክንያት ወላጅ ያጡ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ናቸው፡፡

‘**የትኞቹ የማካካሻ አይነቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል**’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ - በተመሳሳይ አማራጮችን ሳይዘረዝር ለቀረበው ጥያቄ ተሳታፊዎች በመርህ ደረጃ የማካካሻ አይነቶች ሊወሰኑ የሚገባው የጉዳቱን አይነት እና መጠን መሰረት በማድረግ እንደሆነ ገልጸዋል። በዚህ ረገድ ‘መልሶ ማቋቋም’ የማካካሻ አይነት ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ጎልቶ የወጣ ሀሳብ ሲሆን፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ተፈናቃዮች የሚመለሱበት ቦታ ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ፡ እንዲሁም በዘላቂነት ማቋቋም አስፈላጊ መሆናቸው ተመላክቷል። በተጨማሪም የስነልቦና ድጋፍ መስጠት ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የማካካሻ አይነት መሆኑ፣ በተለይም የጾታ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች ልዩ ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ አጽንኦት ተሰጥቶበታል።

ከማካካሻ ጋር በተያያዘ ሌላው ግብዓት የተሰበሰበበት የፖሊሲ አማራጭ ጥያቄ ‘**የማካካሻ ሥርዓቱን ማን ይምራው**’ የሚለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ አብዛኞቹ የትኩረት ውይይት ቡድኖች፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ ህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ‘**የማካካሻ ሥርዓቱ አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ሊመራ**’ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ ሌላው አማራጭ ከነጻነት፣ ከገለልተኝነት እና ቅቡልነት አንጻር የሚነሳበትን ጥያቄ እና ተግዳሮት መሰረት በማድረግ፣ እንዲሁም በስራ ላይ ባሉ ተቋማት ላይ ተጨማሪ ጫናን የሚፈጥር መሆኑን በማንሳት - ስራው ለአዲስ ተቋም ቢሰጥ ውጤታማ አካሄድ እንደሚፈጥር አንስተዋል፡፡

ያለመደገም ዋስትናን ከማረጋገጥ አንጻር ግብዓት የተሰበሰበበት ሌላው የፖሊሲ አማራጭ ጥያቄ ‘**የተቋማት ማሻሻያን**’ የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ የፖሊሲ አማራጭ ተሳታፊዎች ግብዓት የሰጡባቸው ሶስት የፖሊሲ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

የመጀመሪያው እና ‘**የትኞቹን ተቋማት ቅድሚያ በመስጠት ማጥራት ያስፈልጋል**’ የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ - ተሳታፊዎች መጠነ-ሰፊ ተቋማትን በመዘርዘር ልየታ፣ ማጥራት እና ተገቢ ማሻሻያ ሊከናወንባቸው

ይገባል በማለት አንስተዋል። አብዛኞቹ ተሳታፊዎች በተመሳሳይ እና በተደጋጋሚ የፍትህ፣ የጸጥታ እና የደህንነት ተቋማት እና ሚዲያ በማሻሻያ ስራው ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ገልፀዋል።

'**ተመሳሳይ ወንጀሎች እና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ ምን እርምጃዎች መውሰድ ይገባል**' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ አስመልክቶ ተሳታፊዎች ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች በዝርዝር ጠቅሰዋል። ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ በፖለቲካዊ ምህዳር ዙሪያ አቃፊና አካታች ሥርዓት መዘርጋት፣ የህግ የበላይነትን በቁርጠኝነት ማስከበር፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ የህግና የተቋም ማሻሻያ ስራ ማካሄድ፣ በሕጎችና ፖሊሲዎች ላይ ከማሕበረሰቡ ጋር ውይይት እና መተማመን የሚፈጠርበትን አሰራር መዘርጋት፣ በከፍተኛ አመራሩ ላይ ጠንካራ ተጠያቂነትን ማስፈን፣ ወንጀል የፈፀሙትን ያለከለላ ተጠያቂ ማድረግ፣ ቀጣይነት ያለው ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ፣ የባለሙያዎችን አቅም መገንባት፣ ብዝሀነትን ያረጋገጠ በእውቀት እና በችሎታ ላይ የተመሰረተ የቅጥር እና የሹመት ሥርዓት መዘርጋት፣ እና የተቋም ሀላፊዎችን አሿሿም በጥንቃቄ ማከናወን የሚሉ ናቸው።

'**የተቋማት የልየታ እና የማጥራት ተግባር በየትኛው ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል**' የሚለውን የፖሊሲ ጉዳይ በተመለከተ - አብዛኞቹ የትኩረት ውይይት ቡድኖች፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት '**ገለልተኛ እና ነጻ የሆነ አዲስ ተቋም በማቋቋም የተቋማት ማሻሻያ ስራ ተግባር ሊከናወን**' እንደሚገባ ገልፀዋል። ለዚህም አሁን ባሉት ተቋማት አሠራር፣ ብቃት እና ገለልተኝነት ላይ እምነት የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ - በሽግግር ፍትህ ሂደት የተቋም ማሻሻያ ስራ የሚጠበቀውን ለውጥ እንዲያመጣ ከተፈለገ ተግባሩ ነጻና ገለልተኛ በሆነ አዲስ ተቋም አማካኝነት ሊተገበር ይገባል የሚል ጠንካራ አቋም አንፀባርቀዋል።

'በተቋማት ውስጥ ልዩ ቡድኖችን በማዋቀር የተቋማት ማሻሻያ ተግባራትን ማከናወን የተሻለ ነው' ያሉ ውስን ቡድኖች ደግሞ ጊዜ እና ሀብትን ከመቆጠብ፣ የሚቋቋሙት ቡድኖች የተቋሙን ውስጣዊ አሰራር የሚያውቁ ከመሆኑ አንፃር ውጤታማ ስራ ለመስራት ይህ አማራጭ ይበልጥ ተመራጭ መሆኑን አንስተዋል።

በመላ ሀገሪቱ ውይይት የተካሄደበት ሌላኛው መሰረታዊ ርእሰ-ጉዳይ '**የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን መነሻ ከመቼ ጀምሮ ሊሆን ይገባል**' የሚለው የፖሊሲ ጥያቄ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ አምስት አማራጮች ለውይይት ቀርበዋል።

አብዛኞቹ ሀገራዊ የትኩረት ውይይት ቡድኖች፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ ህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት - የሽግግር ፍትህን የጊዜ ወሰን በተመለከተ '**ለተጠያቂነት** ከ1987 **ዓ.ም ጀምሮ፣ ለሌሎች የሽግግር ፍትህ ስልቶች ደግሞ መረጃና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ**' የሚለውን አማራጭ ደግፈዋል። በዚህ አማራጭ መሰረት የክስ ጉዳይ ከ1987 ዓ.ም መጀመሩ የህግ ማእቀፍን መሰረት ያደረገ ተጠያቂነት እንዲኖር ያደርጋል፣ ከሌሎቹ ጊዜያት በተሻለ መረጃ እና አጥፊዎቹን ማግኘት የሚቻል መሆኑ፣ እንዲሁም ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስልቶችን በተመለከተ መረጃና ማስረጃ እስከ ተገኘ ድረስ ያለ ጊዜ ገደብ ወደኋላ በመሄድ የደረሱ በደሎች እና የታሪክ ዝንፈቶች የሚጠሩበት እና ይቅር በመባባል የወደፊት አብሮነት የሚጠናከርበትን እድል የሚሰጥ በመሆኑ የተሻለ አማራጭ ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል **በሁለተኛ** ደረጃ ድጋፍ ያገኘው አማራጭ የሽግግሩ ፍትህ ሂደቱ 'ከ1983 **ዓ.ም በፊት ጀምሮ የነበሩ ጉዳዮች ጥቅተተ መልኩ ሊተገበር ይገባል**' የሚለው ነው። ሌሎች ውስን ቡድኖች ደግሞ በቅደም-ተከተል የሽግግር ፍትህ ሂደቱ 'ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ'፣ 'ከ1987 ጀምሮ'፣ እና 'ከ2010 ጀምሮ' ያለውን ጊዜ የሚሸፍን መሆን አለበት በማለት የተለያዩ ደጋፊ ምክንያቶችን አቅርበዋል።

በመላ ሀገሪቱ በተደረጉ የምክክር መድረኮች ላይ ለውይይት የቀረበው ሌላው የፖሊሲ ጥያቄ '**በሽግግር ፍትህ ሂደት የባህላዊ ፍትህ ሥርአቶች ሚና ምን ሊሆን ይገባል**' የሚል ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ተሳታፊዎች ሀሳብ የሰጡባቸው ሶስት የፖሊሲ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

**'አካባቢያዊ ወይም ሀገራዊ ሚና መጫወት የሚችሉ ተለይተው ሊጠቀሱ የሚችሉ ባህላዊ የፍትሕ ስርአቶች የትኞቹ ናቸው'** ለሚለው ጥያቄ የትኩረት ውይይት ቡድኖች እንደአካባቢያቸው ሁኔታ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በማንሳት ተግባር ላይ እንዲውሉ አስተያየት ሰጥተዋል።

**'ባህላዊ የፍትሕ ስርአቶች የትኞቹን ጉዳዮች ለመፍታት ሊተገበሩ ይችላሉ'** በሚለው የፖሊሲ ጥያቄ ላይ አብዛኛዎቹ ሀገራዊ የትኩረት ውይይት ቡድኖች፣ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንደገለፁት - ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በማህበረሰብም ሆነ በግለሰብ ደረጃ የተከሰቱ ግጭቶችን የመፍታት፣ ስብራቶችን የመጠገን እና ማህበረሰባዊ ትስስርን የሚያጠናክሩ እንደመሆናቸው መጠን - ከሽግግር ፍትህ አምዶች ውስጥ **ከእርቅ፣ እውነትን ከማፈላለግ እና ከማካካሻ ስርአት አተገባበር ጋር በተያያዘ ሚና ሊኖራቸው ይገባል** ብለዋል። በተያያዘም ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በሽግግር ፍትህ ሂደት **በሚቋቋመው ኮሚሽን በማይሸፈኑ ቀላል ጥፋቶች ላይ ቢያተኩሩ** የተሻለ ይሆናል የሚል ሀሳብ ተነስቷል። በቁጥር ጥቂት የሆኑ የትኩረት ውይይት ቡድኖች ደግሞ ባህላዊ ስርአቶች በሁሉም የሽግግር ፍትህ ዓላባዎች ላይ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል የሚለውን ሀሳብ ደግፈው ተከራክረዋል።

ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች **በሽግግር ፍትህ ሂደት ሊጫወቱ የሚገባውን ሚና በተመለከተ** ስርአቶቹ ከሽግግር ፍትህ ሂደት ጋር ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ ስራዎችን ሊተገብሩ ይችላሉ የሚለው ሀሳብ ጎልቶ ወጥቷል። በመሆኑም ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች የሽግግር ፍትህ ሂደትን ማገዝ እና መደገፍ፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር ሆነው እውነትን በማፈላለግ፣ በካሳ እና በእርቅ ጉዳይ ደጋፊ ሚና ሊሸከሙ እንደሚችሉ ተመላክቷል። ሆኖም ጥቂት የትኩረት ውይይት ቡድኖች አሁን መሬት ላይ ያለው ሀቅ የማህበረሰብ ተቋማት ታማኝነት እና ለእውነት መቆም ጥያቄ ውስጥ የገባ በመሆኑ በሽግግር ፍትህ ተልዕኮ ውስጥ ሊሳተፉ አይገባም የሚል ጠንካራ አቋም አንፀባርቀዋል።

**'ባህላዊ የፍትሕ ስርአቶች እና እሴቶችን ለመጠቀም መደረግ የሚገባቸው ማሻሻያዎችን'** በተመለከተ ለቀረበው የፖሊሲ ጥያቄ ተደጋግሞ የተነሳው ሀሳብ ሥርዓቶቹን ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት በማስወጣት ገለልተኛነታቸውን ማረጋገጥን የሚመለከት ነው። ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል አስፈላጊው የህግ ማሻሻል እና ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡ ሕዝብም ባህላዊ ስርዓቶቹን ሊጠብቅ፣ ሊያጎለብትና ክብረዛ ሊከላከል ይገባል ብለዋል። በተጨማሪም የሴቶችን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ መልኩ አሰራራቸውን ሊያስተካክሉ እንደሚገባ ተገልጿል።

በመጨረሻም በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት የተደረገበት የፖሊሲ ጥያቄ **'በሽግግር ፍትህ ሂደት የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮችን ሚና ምን መሆን አለበት'** የሚለው ነው። ለዚህም በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት ያደረጉ አብዛኛዎቹ የትኩረት ውይይት ቡድኖች፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሽግግር ፍትህ ሂደት የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ዋና ሚና **በትብብር እና ድጋፍ ስራዎች ላይ የተገደበ ሊሆን ይገባል** ሲሉ፡ ጥቂቶች ደግሞ ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ሂደት ሊተገበሩ እንደሚገባ አመልክተዋል።

ብዙሀኑ ለደገፉት ሀሳብ በምክንያትነት - የሽግግር ፍትሕ ሀገራዊ ይዘት ያለው ጉዳይ እንጅ በተወሰነ የአስተዳደር ክልል ላይ ብቻ የሚያርፍ ባለመሆኑ በተናጠል እንዲተገበር ለክልሎች ሀላፊነት መስጠት ተገቢ አይደለም፡ በሽግግር ፍትህ የሚታቀፉት ብዙዎቹ ጉዳዮች በፌዴራል መንግስት ስልጣን ማእቀፍ ስር የሚወድቁ ናቸው፡ ስለሆነም ወጥነት ላለው ሀገራዊ አተገባበር - እንዲሁም ከፍትሃዊነት እና ገለልተኝነት አንጻር የአካባቢያዊ አስተዳደሮች ሚና ሂደቱን በመደገፍ ላይ የተገደበ ሊሆን ይገባል የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።

## ክፍል ስምንት

## የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ዋና ዋና ምልከታዎች እና ምክረ-ሀሳቦች

### 8.1. የወንጀል ተጠያቂነትን በሚመለከት

#### 8.1.1. የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?

ይህን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ ከተሳታፊዎች በተገኙ ግብአቶች ላይ የተመሰረተው ግኝት '**ጉልህ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል**' የሚለው አማራጭ የአብላጫውን ቡድን ድጋፍ ያገኘ መሆኑ ታይቷል። ሆኖም ቀላል በማይባል ቁጥር '**በሁሉም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል**' የሚለው የፖሊሲ አማራጭም ድጋፍ አግኝቷል። ከዚህ አንጻር በተሳታፊዎች የተነሳው አንዱ ምክንያት 'ጉልህ ያልሆኑ' የመብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ከተጎጂዎች አንፃር ትልቅ ጠባሳ የሚተዉ በመሆኑ በሁሉም ጥፋቶች ላይ ፍትህ ማስፈን ተገቢ ነው የሚል ነው።

ምንም እንኳ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ በሁሉም ጥፋቶች ላይ ክስ መመስረት አዳጋች ቢሆንም፣ ሁሉም ተጎጂዎች ተገቢ ፍትህ ይፈልጋሉ የሚለው ጥያቄ ወደ ጎን ሊባል የሚችል አይደለም።

በአጠቃላይ ሲታይ በሽግግር ፍትህ ሂደት 'ክስ' እንደ አንድ የፍትህ ማስፈኛ ሂደት እንጂ እንደ ብቸኛ መንገድ የሚታይ ባለመሆኑ፣ እንዲሁም በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ማተኮር ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስልቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ እድል የሚሰጥ በመሆኑ - በነዚህ ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ይኑር የሚለው አቋም ተቀባይነት ያለው ነው። ይህ አካሄድ ከሽግግር ፍትህ ዓላማ አኳያ፣ እንዲሁም ሀገራችን በህገ-መንግስቱ እና በዓለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች ከገባችው በጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ተጠያቂነትን የማስፈን ግዴታ ጋር የተጣጣመ ነው ማለት ይቻላል።

#### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

በፖሊሲው ላይ **የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የወንጀል ተጠያቂነት ሊኖር ይገባል** ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሊከናወን ይገባል።

- የሽግግር ፍትህ እና የወንጀል ተጠያቂነት ግብን ከማሳካት፣ ሀገራችን ካለባት የመክሰስ እና ተጠያቂነትን የማስፈን ግዴታ፣ እና ከሀገራችን ነባራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ አንጻር የወንጀል ተጠያቂነቱ የስረ ነገር ወሰን **በጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ብቻ ያተኮረ** ሊሆን ይገባል።

- የክስ ሂደቱ በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ላይ ማተኮሩ እንደተጠበቀ ሆኖ '**ጉልህ**' የሚለው ቃል ሲተረጎም የተወሰኑ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን (እንደ ዘር ማጥፋት፣ የጦር ወንጀል፣ በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች) ባካተተ መልኩ ብቻ ሳይሆን - ሰፋ ባለ መንገድ ሊታይ ይገባል። ምንም እንኳ ተሳታፊዎች 'ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' ወይም 'ከባድ ወንጀሎች' በሚለው ማዕቀፍ ውስጥ ሊካተቱ ይገባል ብለው ያነሷቸው ጥሰቶች (ለምሳሌ ጾታዊ ጥቃቶች፣ ማፈናቀል፣ ሰው መሰወር፣ ማሰቃየት እና የመሳሰሉት) በዓለም-አቀፍ ወንጀል ውስጥ ሊወድቁ የሚችሉ ቢሆንም - ይህ በማይሆንበት ሁኔታ ጥሰቶቹ ከሚያደርሱት ከባድ ጉዳት አንጻር በ'ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' ወይም 'ከባድ ወንጀሎች' ትርጓሜ ውስጥ ራሳቸውን ችለው ሊካተቱ ይገባል።

- በተጨማሪም የሀገራችን የወንጀል ህግ የተወሰኑ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን (ለምሳሌ በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ ሰው ማሰቃየት፣ ሰው መሰወር፣ ጾታዊ ጥቃት እና የተወሰኑ የጦር ወንጀሎችን) በተገቢ ሁኔታ ያላካተተ በመሆኑ - እነዚህን ወንጀሎች የሚያቅፍ የህግ ማዕቀፍ በማውጣት ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እና ሌሎች ዓለም-አቀፍ ወንጀሎች ተጠያቂነት እንዲያስከትሉ በማድረግ ፍትሕ ማስፈን ያስፈልጋል። ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን በማካተት የሚወጣው ህግ የእነዚህን ወንጀሎች ስረ-ነገር የሚያቋቁመው በዓለም-አቀፍ የልማድ ህግ ላይ በመመስረት ስለሚሆን የተፈፃሚነት ወሰኑ ህጉ ከሚጸናበት ቀን በፊት የተፈጸሙ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን በሚያቅፍ አግባብ ይሆናል።

- ነገር ግን  በተለያየ ምክንያት በዓለም-አቀፍ ወንጀሎች ዝርዝር ውስጥ ላይወድቁ ይችላሉ ተብለው በ'ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' ትርጓሜ ውስጥ እንዲካተቱ ከላይ የተመላከቱ ከባድ ወንጀሎችን በተመለከተ ተጠያቂነት ሲሰፍን የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑን የሚያትተውን መርህ በሚያከብር መልኩ ተግባራዊ ሊደረግ ስለሚገባ - እነዚህን ወንጀሎች በተመለከተ የተጠያቂነት ስራው በሀገሪቱ የወንጀል ህግ በተካተቱት ጉልህ ወንጀሎች (serious ordinary crimes) ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

- ከላይ የቀረቡት ምክረ-ሀሳቦች እንደተጠበቁ ሆኖ - በፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ተጠያቂነት የማስፈን ስራው በሁሉም ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ ሊያተኩር ይገባል የሚለውን የፖሊሲ አማራጭ የደገፉ ተሳታፊዎችን ፍላጎት እና የፍትህ ጥያቄ በሚቀርፍ አግባብ ሊከናወን ይገባል። ይህን ለማድረግ የሽግግር ፍትህ አላባዎች ሁለንተናዊነት እና ተደጋጋፊነት መርህን በመከተል - በወንጀል ተጠያቂነት የሚታዩትም ሆኑ የማይታቀፉት ወንጀሎች በሌሎቹ የሽግግር ፍትህ ስልቶች የሚታዩበትን መንገድ በመፍጠር የተነሱትን ስጋቶች መቅረፍ ይገባል። ይህ አካሄድ የተጎጂዎችን ፍትህ መሻት ለማሳካት እና ማህበረሰባዊ ስብራቶችን በመጠገን እርቅን ለማበረታታት ይረዳል።

### 8.1.2. የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል

በዚህ የፖሊሲ ጥያቄ ላይ ግኝቱ እንደሚያሳየው '**ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል**' የሚለው አማራጭ የአብላጫውን ተሳታፊ ድጋፍ አግኝቷል። ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የትኩረት ውይይት ቡድኖችም '**የክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ በተሳተፉ አጥፊዎች ላይ እንደየተሳትፎ ደረጃቸው ተጠያቂ ሊያደርግ ይገባል**' ብለዋል።

የተሳካ የተጠያቂነት ስራ ለማከናወን ሁለቱንም አማራጮች በደገፉ ቡድኖች የተነሱትን ስጋቶች፣ አማራጩን ከመደገፍ ጀርባ ያሉትን ምክንያቶች እና መነሻ ሀሳቦችን በአግባቡ መፈተሽ እና ተገቢ መፍትሄ መቀየስ ያስፈልጋል።

በዚህ ረገድ **ከፍተኛ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ ክስ ሂደት መተግበር ከሽግግር ፍትህ ዓላማ አንጻር ሲታይ የሚደገፍ አካሄድ** ነው። ብዙዎቹ የተኩረት ውይይት ቡድኖች እና ሌሎች ተሳታፊዎች እንዳመለከቱት ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ካላቸው ውጭ ያሉ አጥፊዎችን ጉዳይ እንደ እርቅ፣ ምህረት እና ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች ባሉ ሌሎች አማራጮች ማየት የሚቻልበት እድል አለ። ይህም 'በማንኛውም ደረጃ ያሉ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' ባሉ ተሳታፊዎች እንደ ዋና ጥያቄ የተነሳው እና 'ሁሉም ባጠፋው ልክ ካልተጠየቀ ነገ ወንጀሎች እንዲስፋፉ፣ ተጠያቂነት እንዳይኖር እና ፍትህ እንዳይሰፍን ያደርጋል' የሚለውን መሰረታዊ ስጋት የሚቀርፍ ነው።

'በማንኛውም ደረጃ ያሉ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት' በደገፉ ቡድኖች ጎልቶ የተነሳው ሌላው ስጋት ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት በተበዳዮች ላይ በቀጥታ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች ከተጠያቂነት የሚያመልጡበትን እድል ይፈጥራል፣ በማንኛውም ደረጃ ላይ ያሉ አጥፊዎችን ከተጠያቂነት ነጻ ያደርጋል የሚል ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ከትእዛዝ ውጭ ከባድ ወንጀልን የፈጸሙ ሰዎች ከወንጀል ተጠያቂነት የሚያመልጡበት መንገድ እንዳይሆንም ስጋታቸውን ገልፀዋል።

ስለሆነም 'የትኛዎቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል' በሚለው ጉዳይ ላይ የፖሊሲ ውሳኔ ሲወሰን በተለያዩ ተሳታፊዎች የተነሱት ስጋቶችን በተሻለ መንገድ ሊቀርፍ በሚችል መልኩ ሊቀረጽ ይገባል።

### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

ፖሊሲው **የትኞቹ አጥፊዎች ላይ ያተኮረ የወንጀል ተጠያቂነት ሂደት ሊኖር ይገባል** ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል።

- ከሽግግር ፍትህ ግብ፣ ከሽግግር ፍትህ የወንጀል ተጠያቂነት አምድ ዓላማ እና ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር **የወንጀል ተጠያቂነቱ የግል ወሰን** (personal jursidiction) **ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ያተኮረ** ሊሆን ይገባል።
- ከፍተኛ ደረጃ ተጠያቂነት ያላቸው ሲባል በህግ በግልጽ ወይም በተግባር የፖለቲካ ወይም ሌላ የስልጣን ተዋረድ መሰረት ደረጃ/ሀላፊነት ያላቸውን የሚያካትት ሆኖ በወንጀሎች አፈጻጸም ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ እና የሀላፊነት ወይም የመሪነት ደረጃ እንዲሁም በሌሎች የወንጀል ድርጊቶች ላይ የነበራቸው የተሳትፎ መጠንን መሰረት አድርጎ የሚለይ ሊሆን ይገባል።
- ከላይ ከተገለጸው ጋር በተያያዘ ወንጀሎችን በራሳቸው ፍላጎት ራሳቸው አቅደውና ውጤቱን ተቀብለው የፈጸሙ ሰዎች 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ' ባላቸው አጥፊዎች ማእቀፍ ውስጥ ሊካተቱ ይገባል። ስለሆነም ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው ሲባል በከፍተኛም ሆነ በመካከለኛ የእዝ ሰንሰለት ያላቸውን ደረጃ/ኃላፊነት፣ በወንጀል አፈጻጸም ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ፣ እንዲሁም ከዚህ ውጭ በራሳቸው ተነሳሽነት ወንጀል የፈጸሙትን የሚያካትት መሆን አለበት።
- የአጥፊዎችን የተሳትፎ ደረጃ በአግባቡ እና በግልጽ መወሰን አስፈላጊ ነው። ይህም ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ሲባል እስከየትኛው ደረጃ ያሉ አጥፊዎችን ያካትታል የሚለው ዓለም-አቀፍ የወንጀል ህግን እና የወንጀል ህግ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ በግልጽ በፖሊሲው ላይ ማመላከት እና በህግ መቀመጥ አለበት።

- በተጨማሪም 'የወንጀል ተሳትፎን' በተመለከተ በሀገራችን የወንጀል ህግ በአግባቡ የተካተተ ባለመሆኑ (indirect perpetration and command responsibility) - ተጠያቂነትን ከዓለም-አቀፍ ወንጀል ህግ መርሆዎች እና ግዴታዎች ጋር በተጣጣመ አግባብ፣ እንዲሁም የዓለም-አቀፍ ወንጀሎች የአፈጻጸም ሁኔታን በሚገልጽ መንገድ ለማከናወን ይረዳ ዘንድ እነዚህን የተሳትፎ አይነቶች በፖሊሲው ማመላከት እና በህግ ማዕቀፍ ማካተት ያስፈልጋል።
- የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ካላቸው አጥፊዎች ውጭ ያሉ አጥፊዎችን በተመለከተ ለተጎጂዎች እና ማህበረሰቡ የፍትህ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል - ከተጠያቂነት ጋር በተንሰላሰለ አግባብ ሌሎች የሽግግር ፍትህ አላባዎችን (ለምሳሌ እውነትን ማፈላለግ፣ ምህረት እና ማካካሻን) በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር በማህበረሰቡ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ባህላዊ የፍትህ ተቋማትን እና የማህበረሰቡን እሴቶች ጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችል አግባብ ፖሊሲውን መቅረጽ አካባቢያዊ ባለቤትነትን እና አውድን ያገናዘበ ምላሽ ለመስጠት ይረዳል።
- ከላይ የተመላከተው የወንጀል ተጠያቂነት ሂደት የአጥፊዎች ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ - ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ካላቸው አጥፊዎች ውጭ ያሉ ሌሎች አጥፊዎች በሌሎች የሽግግር ፍትህ ሂደት እና ለስኬታማ የወንጀል ተጠያቂነት ተግባር በተገቢው መልኩ የማይተባበሩ እና እንዳስፈላጊነቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ የማያደርጉ ከሆነ - ለፈጸሙት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጠያቂ የሚደረጉበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል።

### 8.1.3. ክሶችን የሚመለከቱ ፍርድ ቤቶችን በሚመለከት

የወንጀል ተጠያቂነት **በየትኛው ፍርድ ቤት ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል** የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ አብላጫ ድጋፍ ያገኘው አማራጭ '**ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም**' የሚለው ነው። ሌሎች ተሳታፊዎችም 'ልዩ ችሎትን'፣ ገለልተኛ 'ቅይጥ ፍርድ ቤት' እና 'ዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤት'ን ያካተቱ በተለያየ የድጋፍ ቁጥር የሚገለፁ አማራጮችን አቅርበዋል።

ብዙዎቹ ተሳታፊዎች የፖሊሲ ምርጫቸውን ሲወስኑ አሁን ያሉት ተቋማት ከተዐማኒነት፣ ገለልተኝነት፣ ቅቡልነት እና የአቅም ብቃት ማነስ ጋር በተያያዘ የሚነሳባቸውን ችግር፣ እንዲሁም ከህብት ውስንነት እና ከጊዜ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ዘርዝረዋል።

ለስኬታማ የሽግግር ፍትህ ስራ የወንጀል ተጠያቂነት ሂደትን በሚያከናውነው ተቋማዊ አደረጃጀት ላይ ያለው አመኔታ፣ የገለልተኝነት እና የብቃት ሁኔታ ፍፁም ወሳኝ ናቸው። ስለሆነም ብዙዎቹ ተሳታፊዎች በተደጋጋሚ ያነሷቸውን ስጋቶችን ሊቀርፍ የሚችል አደረጃጀት መቅረጽ መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ 'ሀገራዊ ሥርዓቶች የበላይነት ያላቸው በመሆኑ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የፍትሕ እና የተጠያቂነት አላባ ተፈጻሚ የሚሆነው ጉዳቱ በደረሰበት አባል ሀገር ውስጥ ፍርድ ቤቶች ካሉ እና በእነዚህ ፍርድ ቤቶች ላይ ማኀብረሰቡ አመኔታ ያለው እንደሆነ በገለልተኛ ሀገራዊ ፍርድ ቤቶች አማካኝነትና አግባብነት ባላቸው ሀገራዊ ህጎች መሠረት' ሊሆን እንደሚገባ በግልጽ ያትታል። ሆኖም 'ሀገራዊ ፍርድ ቤቶች አቅም የሌላቸው ከሆነ ወይም ህብረተሰቡ በእነርሱ ላይ አመኔታ የሌለው እንደሆነ ተፈላጊውን አቅም ለማስገኘትና ጉዳት በደረሰባቸው የማኀበረሰባቸው ክፍሎች ዘንድ ድጋፍና አመኔታን ለማግኘት ሲባል ልዩ ፍርድ ቤቶችን፣ ልዩ ሰሚ አካላትን ወይም ጥምር ፍርድ ቤቶችን የማቋቋም እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው'[64] ሲል ይደነግጋል።

---

[64] የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ (2011) 78

በተጨማሪም 'ስኬታማ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ማንጸሪያዎችና መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ' በማለት ፖሊሲው ሲያብራራ 'የፍርድ እና የምርመራ ሥራውን ለመሥራት ብቃት ያላቸውን ሰዎች የያዙና የሴቶች የፍርድ እና የምርመራ ባለሙያዎች ተዋጽዖ ተመጣጣኝ የሆነባቸው ገለልተኛ ፍርድ ቤቶች እና የምርመራ ተቋማትን ማቋቋም' እንደሚገባ ያትታል።

ስለሆነም የተሳካ የወንጀል ተጠያቂነት ስራ ለማከናወን እንዲቻል የተነሱትን መሰረታዊ ስጋቶች አጽንኦት ሰጥቶ በመፈተሽ በተሻለ መልኩ ለመቅረፍ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት መቀየስ ተገቢ ይሆናል። ከዚህ አንፃር በአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሰነድ ላይ የተገለጸውን ሀሳብ በመከተል፡ እንዲሁም ስኬታማ የወንጀል ፍትህ ሥርዓትን ከመዘርጋት አንፃር - የወንጀል ተጠያቂነት ተቋማዊ አደረጃጀት የህዝብ አመኔታ እና ቅቡልነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ማከናወን ይገባል።

### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

ፖሊሲው ***የተጠያቂነት ተግባር በየትኛው የፍርድ ቤት ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል*** ለሚለው ጥያቄ ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል።

- የተሳካ የተጠያቂነት ስራ ለማከናወን የተነሱትን መሰረታዊ ስጋቶች አጽንኦት ሰጥቶ በመፈተሽ ለመቅረፍ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል አካሄድ መከተል፡ በተለይም ከሽግግር ፍትህ ግቦች፡ ሂደቱ በሀገራችን ካስፈለገበት መሰረታዊ ምክንያት፡ እንዲሁም እንደ ሀገር ከመጣንበት እና ከተሞከሩ ያልተሳኩ ሂደቶች በመማር፡ የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ያስቀመጣቸውን ማንጸሪያዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተቋማዊ አደረጃጀቱን መቀየስ ተገቢ ነው።
- አሁን ባሉት ተቋማት ውስጥ ልዩ ችሎትም ሆነ አዲስ ፍርድ ቤት በማቋቋም ብቻ እነዚህን ስጋቶች ሙሉ ለሙሉ በመቅረፍ ስኬታማ የተጠያቂነት ስራ ማከናወን አዳጋች ስለሚሆን ክሶችን የመስማት፣ ውሳኔ የመስጠት እና የተጠያቂነት ተግባራትን ስራ የሚያከናውን አዲስ ነፃ እና ገለልተኛ ፍርድ ቤት እንዲቋቋም ማድረግ፡ ውጤታማነቱን ከማረጋገጥ አንፃርም በስራዎቹ ሂደት አግባብነት ያላቸው የውጭ ባለሙያዎችን ተጨባጭ እና ትርጉም ባለው መጠን እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።
- የዳኞች አመራረጥ የጾታ ስብጥርን ያረጋገጠ መሆን አለበት።
- የሚቋቋመው ልዩ ፍርድ ቤት ***የዓለም-አቀፍ ህግ እና መርሆዎችን እንዲሁም የሀገር ውስጥ ህጎችና አሰራሮችን የሚከተል መሆን አለበት።*** በውስጡም የተከላካይ ጠበቃ፡ የሬጅስትራር እና ደጋፊ የስራ ሂደቶችን አደረጃጀት ያካተተ መሆን ይኖርበታል።
- ከላይ በተዘረዘረው አግባብ የሚቋቋም ልዩ ፍርድ ቤትን ማደራጀት በተሳታፊዎች የተነሱ ስጋቶችን ለመቅረፍ፡ ተጎጂዎች እና ተከሳሾች በሂደቱ ላይ አመኔታ እንዲኖራቸው ለማድረግ፡ የተሻለ ቅቡልነት ለመፍጠር፡ ከችግሩ ግዝፈት ውስብስብነት እና አንገብጋቢነት አንጻር የሚያስፈልገውን ሰፊ ሀብት እና ድጋፍ ለማሰባሰብ፡ ከአቅም ከችሎታ እና ከብቃት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት፡ የሀገራችንን ባለሙያዎች ብቃት ለማጎልበት፡ እንዲሁም ሀገራችን ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ እና ከተነሱ ስጋቶች አንጻር የሽግግር ፍትህ ግብን ለማሳካት የተሻለው ተቋማዊ አደረጃጀት ነው።

### 8.1.4. የወንጀል ምርመራና የክስ ተግባር ተቋማዊ አደረጃጀት

በዚህ የፖሊሲ ጥያቄ ላይ ግኝቱ እንደሚያመለክተው ***አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጭ የምርመራ እና የክስ ሂደቶችን የሚያከናውን ልዩ ነጻና ገለልተኛ የዓቃቤ ሕግ ተቋም መቋቋም አለበት*** የሚለው አማራጭ ግልፅ የሆነ አብላጫ በማግኘት ተመራጭ ሆኗል።

የምርመራ እና ክስ ስራ 'በፖሊስ እና ዓቃቤ ህግ ተቋማት ውስጥ የተለዩ ቡድኖችን በማዋቀር ሊተገበሩ ይገባል' የሚለው አማራጭም በተወሰኑ ቡድኖች ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፣ የምርመራ እና ክስ ስራዎች በዓለም-አቀፍ ተቋም አማካኝነት ሊከናወኑ ይገባል የሚል ሌላ አማራጭም በጥቂት ተሳታፊዎች ቀርቧል፡፡

ተሳታፊዎች የፖሊሲ ምርጫቸውን ሲወስኑ ከተዐማኒነት፣ ገለልተኝነት፣ ቅቡልነት፣ የአቅም ብቃት ማነስ፣ የሀብት ውስንነት እና ከጊዜ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ስጋቶችን አንስተዋል፡፡

ስኬታማ የሽግግር ፍትህ ለማከናወን የምርመራና ክስ ተግባራትን የሚያከናውነው ተቋማዊ አደረጃጀት የሚኖረው የህዝብ አመኔታ፣ የገለልተኝነት እና ብቃት ሁኔታ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስለሆነም አደረጃጀቱ ተሳታፊዎች ያነሷቸውን ስጋቶችን ሊቀርፍ በሚችል መልኩ ማከናወን አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

**የምርመራ እና ክስ ስራዎችን የሚከያናውነው ተቋም ማን ሊሆን ይገባል** የሚለውን በተመለከተ በፖሊሲው ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል፡፡

- የተሳካ የተጠያቂነት ስራ ከማከናወን አንፃር የተነሱትን መሰረታዊ ስጋቶች በመፈተሽ በተሻለ መልኩ ለመቅረፍ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል፣ የህዝብ አመኔታን እና ቅቡልነትን እንዲሁም የባለሙያዎችን አቅም ሊያጎለብት የሚችል ተቋማዊ አደረጃጀት መቀየስ ይገባል፡፡

  ከዚህ አንፃር በህዝብ ዘንድ አመኔታ እና ቅቡልነትን ለማግኘት፣ ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መርምሮ ክስን ከመምራት አኳያ ሊያጋጥም የሚችልን የእውቀት እና ልምድ ክፍተቶችን በአግባቡ ለማስተካከል፣ እና ስኬታማ የምርመራ እና የክስ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል፣ ብቃትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን በተገቢ መንገድ የሚለይ **ልዩ የዓቃቤ ህግ ተቋም ማቋቋም** ይገባል፡፡ የተቋሙን ውጤታማነት ከማረጋገጥ አንፃርም በስራዎቹ ሂደት አግባብነት ያላቸው የውጭ ባለሙያዎችን ተጨባጭ እና ትርጉም ባለው መጠን እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

- የምርመራና የክስ ባለሙያዎች አመራረጥ የጸታ ስብጥርን ያረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

- የሚቋቋመው ልዩ የዓቃቤ ህግ ተቋም **የዓለም-አቀፍ ህግ እና መርሆዎችን እና የሀገር ውስጥ ህጎች እና አሰራሮችን** የሚከተል መሆን አለበት፡፡

- የሚቋቋመው ልዩ ዓቃቤ ህግ ተቋም ሌሎች ደጋፊ የስራ ሂደት አደረጃጀቶችን ማካተት ይኖርበታል፡፡

## 8.2. እውነት ማፈላለግ እና የእርቅ ተግባር

### 8.2.1. እውነትን የማፈላለግና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች/ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል?

በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ተካቶ ውይይት የተደረገበት እና ግብዓት የተሰበሰበበት ሁለተኛው የሽግግር ፍትህ አምድ **እውነት ማፈላለግ እና የእርቅ ተግባርን** የሚመለከት ነው፡፡ ግኝቱ በግልፅ እንደሚያሳየው በሁሉም ተሳታፊዎች ሊባል በሚቻል ደረጃ እውነት የማፈላለግ እና የእርቅ ተግባር ለሀገራችን አስፈላጊ መሆኑ ተንጸባርቋል፡፡

**'እውነትን የማፈላለግና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ጉዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል'** የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ አብዛኞቹ የትኩረት ውይይት ቡድኖች እና ተሳታፊዎች ትኩረቱ '**በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች**' ላይ ሊሆን ይገባል ሲሉ፣ ከዚህ አማራጭ ጋር ተቀራራቢ ቁጥር ያላቸው ሌሎች ተሳታፊዎች ደግሞ እውነት የማፈላለግና የእርቅ ተግባራት '**በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች**' ላይ ሊከናወን ይገባል ብለዋል፡፡

*በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ እውነት የማፈላለግ* ***ስራ-ነገር ወሰንን ጉልህ ባልሆኑ ጥሰቶች ላይ ጭምር ማድረግ*** *ከሽግግር ፍትህ ዓላማ፣ ከጥሰቶቹ መጠን፡ አይነት እና ብዛት፣ ከጊዜ፣ ከሀብት እንዲሁም ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የማይበረታታ ነው። የእውነት ማፈላለግ እና እርቅ ስራ ውጤታማነትን አዳጋች ያደርገዋል።*

*በተመሳሳይ ወሰኑን* ***በጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ላይ ብቻ*** *እንዲያተኩር ማድረግ የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታዎች የማያገናዝብ፣ የጥሰቶችን መሰረታዊ ምክንያት እና ሁነት በተሟላ መልኩ ለይቶ ይፋ ለማድረግ የማያስችል ያደርገዋል።*

*ከዚህ አንፃር የእውነት ማፈላለግ እና እርቅ ተግባር* ***የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ጥሰቶችን በሚያካትት መልኩ በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ እንዲሆን ማድረግ*** *ለታለመው ግብ ውጤታማነት ይረዳል። ሆኖም ከዚህ ጋር ተያይዞ ሂደቱ በሁሉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ሊተገበር ይገባል ያሉ ተሳታፊዎች ተመሳሳይ ፍላጎት እና ስጋትን ያንጸባረቁ እንደመሆኑ መጠን - የእውነት ማፈላለጉ የስረ-ነገር ስልጣን ሲወሰን ከተነሱት ፍላጎቶች፣ ስጋቶች እንዲሁም የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታን በማገናዘብ* ***በወንጀል ተጠያቂነት አምድ ለጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ከተሰጠው ትርጉም ሰፋ አድርጎ ማየት*** *ይገባል።*

### *የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች*

*በፖሊሲው* ***የእውነት ማፈላለግ እና እርቅ ተግባራት በየትኞቹ ጥሰቶች ላይ ሊያተኩር ይገባል*** *ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ነጥቦች እና መርሆዎች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል።*

- *የእውነት ማፈላለግ እና የእርቅ ተግባር ስረ-ነገር* ***በሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች፣ እና የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ በማተኮር - በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፡*** *የጥሰቶች መሰረታዊ ምክንያቶች፣ ሁነት፣ አይነት እና የጉዳት መጠንን በመመስረት* ***ይፋ የማውጣት ስራን*** *የሚያካሂድ መሆን አለበት። ይህን ማድረግ የጥሰቶችን ምክንያት በተሟላ መልኩ በመለየት እንዳይደገሙ ለማድረግ፣ የተጎጂዎችን እውነት የማወቅ መብት ለማረጋገጥ፣ ክብራቸውን ለመመለስ፣ ግላዊ፡ ግለሰባዊ፡ ማህበረሰባዊ እና ሀገራዊ እርቅን በማበረታታት በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ስብራቶች ለማከም፣ ቁስል እዲጠግ ለማድረግ እና በደሎችን በተመለከተ የጋራ ትርክት ለመፍጠር ይረዳል።*
- *ለእውነት ማፈላለግ እና እርቅ ተግባራት በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ብቻ ማተኮሩ የተሻለ ቢሆንም እውነት የማወቅ መብት እና ፍላጎትን በተሟላ መልኩ ለማረጋገጥ እንዲቻል* ***ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች*** *የሚለው አገላለፅ ለተጠያቂነት ከሚቀመጠው ትርጉም በተለየ መልኩ የእውነት ማፈላለግ እና እርቅ ተግባራትን አላማና ባህሪ ባገናዘበ አግባብ መመስረት ይኖርበታል። ውሳኔው በተፈፀመው ድርጊት ጉልህነት ወይም ክብደት ላይ ብቻ ሳይሆን -* ***ድርጊቶቹ ወይም ጥሰቶቹ ስልታዊ ወይም መጠነ-ሰፊ መሆን አለመሆናቸውን በማየት የሚመሰረት*** *መሆን አለበት።*
- *የእውነት ማፈላለግ እና እርቅ ተግባራት ስረ-ነገር ስልጣን አወሳሰን ተሳታፊዎች በተደጋጋሚ ያነሱትን ከትርክት እና ባለፉ ጊዜያት ከተፈጸሙ ወይም ተፈጽመዋል የሚባሉ በደሎችን በተመለከተ ያሉትን የአረዳድ ክፍተቶች፣ ተቃርኖዎች፣ ልዩነቶች፣ አንዳንዴም እውቅና ካለመስጠት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ማጥራት ወይም መቅረፍ በሚያስችል አግባብ ሊሆን ይገባል።*
- *የእውነት ማፈላለግ ስራው ለጾታዊ መብት ጥሰቶች፣ ከሀገር ውስጥ መፈናቀል ጋር ለተያያዙ በደሎች እና ለሌሎች ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ጉዳቶች እና ጥሰቶች ተገቢ አጽንኦት በሚሰጥ አግባብ መቅረጽ ይገባል።*

- የእውነት ማፈላለግ እና እርቅ ተግባራት የስረ-ነገር ስልጣን በጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ ቢሆንም **ሌሎች ጉልህ ያልሆኑ ጥሰቶችን በተመለከተ በማህበረሰባዊ (እና አካባቢያዊ) የግጭት አፈታት እና እርቅ ሥርዓት መፍትሄ የሚያገኙበትን** ሂደት ማመላከት ይገባል።

- የተወሰኑ ተሳታፊዎች ከእርቅ ጋር በተያያዘ ያነሱትን ስጋት ለመቅረፍ ከእውነት ማፈላለግ ጋር በተገናኘ የእርቅ ምንነት በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል። በዚህ ረገድ እርቅ ሲባል ሁሉን በይቅርታ ማለፍ ወይም ይቅር መባባል ብቻ እንዳልሆነ፣ ተጠያቂነት የሌለበት ሂደት እንደማይሆን፣ ይልቁንም እርቅ ሂደት እና ብዙ ስራት ያለው መሆኑን በግልጽ በማስቀመጥ የተለያዩ የእርቅ አይነቶች እና ደረጃዎችን ለማበረታታት እንዲቻል - **ሁሉም የሽግግር ፍትህ አላባዎች በተንሰላሰለ አግባብ ሊተገበሩ እንደሚገባ** ማመላከት ያስፈልጋል።

### 8.2.2. እውነት የማፈላለግ እና የእርቅ ተግባር ተቋማዊ አደረጃጀት

ይህን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በተሳታፊዎች እና ባለድርሻ አካላት ግብአት ላይ የተመሰረተው ግኝት እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ ተሳታፊዎች '**አዲስ ተቋም**' ሆኖ ገለልተኝነት፣ ተዓማኒነት እና ነጻነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ሊቋቋም ይገባል ብለዋል። የእውነት ማፈላለጉን ተግባር ሌላ ሀላፊነት ላላቸው ተቋማት - ለምሳሌ ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ወይም የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በተደራቢነት መስጠት የማይበረታታ ነው። ተቋማቱ ባሁናዊ ክስተቶች እና ሌሎች ሀላፊነቶች በመጠመድ ለእውነት ማፈላለጉ ስራ ተገቢ አትኩሮት ላይሰጡ ይችላሉ። የተቋቋሙበት የራሳቸው ትልቅ ሀገራዊ ዓላማ ከማሳካት አንጻርም ተግዳሮት የሚፈጥር ነው።

እንዲሁም ሀገራዊ አውዱ እንደሚያመለክተው በፍትህ፣ በእርቅ እና በእውነት ላይ የተመሰረተ ዘላቂ ሰላም ማምጣት ዘርፈ-ብዙ ምላሾችን የሚጠይቅ በመሆኑ **የእውነት ማፈላለግና እርቅ ተግባራትን ራሱን በቻለ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲሰጥ ማድረግ የሚመከር ነው።**

ከእውነት ማፈላለግና የእርቅ ተግባራት ጋር በተያያዘ ተሳታፊዎች ያነሱት ሌላው ሀሳብ በዚህ ሂደት የባህል ሥርዓቶች እና እሴቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል የሚል ነው።

ከተቋም አደረጃጀት ጋር በተመሳሳይ ቋንቋ የሚነሱትን የገለልተኝነት፣ ተዓማኒነት፣ ነጻነት፣ ቅቡልነት፣ እና የአቅምና የብቃት ችግሮችን በአግባቡ ምላሽ የሚሰጥ አደረጃጀትን ተግባራዊ ማድረግ መሰረታዊ ተግባር ሊሆን ይገባል።

#### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

በፖሊሲው **የእውነት ማፈላለግ እና የእርቅ ተግባራት ተቋማዊ አደረጃጀትን** በተመለከተ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ነጥቦች እና መርሆዎች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል።

- ይህን ሥራ የሚመራው ተቋም በተቻለ መጠን በሁሉም አካላት አመኔታ የሚጣልበት፣ ገለልተኛ እና ተቀባይነት ያለው ሊሆን ይገባል። አደረጃጀቱም ተቋማዊ እና የአሰራር ነጻነትን እና ገለልተኝነትን በሚያረጋግጥ አግባብ ሊከናወን ይገባል።

- በአብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች እንደተደገፈው ለእውነት ማፈላለግ እና እርቅ ተግባራት አሳታፊ እና አካታች በሆነ ግልጽ ሂደት **አዲስ የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ማቋቋም** ተገቢ ነው።

- ኮሚሽኑ ሙሉ በሙሉ ከመንግስት ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ፣ ማናቸውም ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ሊቋቋም ይገባል። ይህን ማድረግ በሀገር ውስጥ ተቋማት እምነት የለንም ያሉትን ጨምሮ በአጠቃላይ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ጥርጣሬ ያላቸውን ሰዎች **በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው እና የሂደቱም ባለቤት እንዲሆኑ፣ የህዝብ ቅቡልነት እንዲያድግ እና ስኬታማነቱ እንዲረጋገጥ** እድል ይፈጥራል።

- ኮሚሽኑ የጾታ፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ተወካዮች እና የሌሎች ማህበረሰብ ክፍሎች ውክልና ያለው እንዲሁም ብቁ እና ገለልተኛ ባለሙያዎችን የሚያካትት አደረጃጀት እንዲኖረው ማድረግ ይገባል።

- ከሀገር ውስጥ ተቋማት ጋር በተያያዘ የተነሱትን የቅቡልነት እና ተዓማኒነት ችግሮች ለመቅረፍ እንዲሁም የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽኑን ተቋማዊ ብቃት ለማጠናከር እና አመኔታን ለማጎልበት ይረዳ ዘንድ ከተለያዩ **ሀገሮች የሚውጣጡ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በአማካሪነት እና ድጋፍ ሰጪነት** በኮሚሽኑ ተቋማዊ አደረጃጀት ውስጥ ማካተት ይገባል።

- ለኮሚሽኑን ነጻነት እና ገለልተኛነት ከመሰረቱ ዋስትና ለመስጠት ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ እና የማያበቁ መስፈርቶችን በግልጽ መደንገግ፣ የኮሚሽነሮችን ጥቆማ፣ መረጣ እና ሹመት ግልጽ እና አሳታፊ በሆነ ሂደት እንዲከናወን ማድረግ፣ በበጀትም ሆነ በአሰራር የኮሚሽኑን ግልፀኝነትን ማጠናከር፣ እንዲሁም የሚሰጠውን አንኳር ተግባር እና ሀላፊነት በውጤታማነት ለመወጣት የሚያስችለው ስልጣን መስጠት ይገባል።

## 8.3. በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት

### 8.3.1. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ መስፈርቶች

በሽግግር ፍትህ ሂደት የተበዳይም ሆነ የበዳይ ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ስለሚሆን ሁሉንም ወንጀሎች በክስ ሂደት እንዲያልፉ ማድረግ ከባድ ይሆናል። በበርካታ ሰነዶች ላይ በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት እንደ አንድ የሽግግር ፍትህ አላባ ተመላክቷል። በዚህ አግባብ በቅደመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት ስርአት መዘርጋት ተዋጊዎች መሳሪያቸውን አስቀምጠው ወደ ሰላማዊ ኑሮ እንዲመለሱ፣ የሰብዓዊ  መብት ጥሰት የፈፀሙ የመከሰስ ስጋት ሳይኖርባቸው ከስልጣናቸው እንዲለቁና ቀጣይነት ያለው ጥሰት እንዳይፈፅሙ፣ በተዋጊ ሀይሎች መካከል መተማመን እንዲኖር፣ የተኩስ ማቆም እና የሰላም ስምምነቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ እና በሰላም ግንባታው አስተዋፅኦ እንዲኖራቸው ያደርጋል። እንዲሁም የእውነት ማፈላለግና ይፋ ማውጣት ተግባሩን በመርዳት ቁርሾ እና ቁስሎችን እንዲፈወሱ በማድረግ እርቅን ሙሉ ያደርጋል።

ውይይት ካደረጉ ተሳታፊዎች አብዛኞቹ በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ምህረት መስጠት ለእርቅ እና ለዘላቂ ሰላም አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል። ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ ቅድመ-ሁኔታዎችን በተመለከተም በምህረት ማዕቀፍ ሊታዩ የማይገባቸውን ወንጀሎች እና አጥፊዎችን አስቀምጠዋል። ለምህረት ብቁ ከማይሆኑት ውጭ ላሉ ወንጀሎች እና አጥፊዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ የተለያዩ ቅድመ-ሁኔታዎችን ዘርዝረዋል።

ተሳታፊዎች ለምህረት ብቁ የማይሆኑ ወንጀሎች እና አጥፊዎችን ሲያመላክቱ የአለም-አቀፍ ህግና እና የህገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ፣ የወንጀሎቹን ክብደት፣ በተለይም አጥፊዎች በተጎጂዎች ላይ ያደረሱትን ጉዳትና ጠባሳ በማየት በማህበረሰቡ ዘንድ ከባድ በሆኑ ወንጀሎች ተጠያቂ የሚሆኑ ሰዎች ከተጠያቂነት ለማምለጥ የሚጠቀሙበት መሳሪያ እንዳይሆን የተነሱትን ስጋቶች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይገባል።

በአንጻሩ የጥሰቶችን ሙሉ እውነት ለማወቅ፣ የማህበረሰቡን እና የተጎጂዎችን እውነት የማወቅ መብትን ለማረጋገጥ በቅደመ-ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ምህረት ትልቅ ሚና ስለሚጫወት ቅድመ-ሁኔታዎቹ ምህረት የመስጠትን ግብ የሚያሳኩ፣ ሂደቱም የአጥፊዎችን ተሳትፎ የሚያበረታታ እና የተበዳዮችን ተሳትፎ የሚያረጋግጥ ሆኖ መቀረጽ ይኖርበታል። በተጨማሪም በህገ-መንግስት እና በዓለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ማዕቀፎች የተቀመጡ መርሆችን በሚያከብር አግባብ መደንገግ ይገባል።

**የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች**

በፖሊሲው **በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ምህረትን** በተመለከተ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ሀሳቦች እና መርሆዎች ባገናዘበ አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡

- በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ምህረት ከሚኖረው ሰፊ ፋይዳ አንጻር ከሌሎች የሽግግር ፍትህ አምዶች ጋር በሚመጋገብ እና በሚደጋገፍ መልኩ በፖሊሲ ማዕቀፉ በማካተት ሊተገበር ይገባል፡፡
- ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ መስፈርቶችን በተመለከተ በተገቢ መንገድ በፖሊሲው ማማላከት እና በህግ መስፈርቶቹን መደንገግ ይገባል፡፡
- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀፅ 28 እና በዓለም-አቀፍ ህጎች ስር ስለ ምህረት አሰጣጥ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን በማክበር በቅድመ-ሁኔታ ላይ ብቻ የተመሰረተ ምህረት ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ለከባድ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎች ወይም ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በተለይም እንደ ዘር ማጥፋት፣ በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ የጦር ወንጀሎች፣ በሴቶች እና ህፃናት እንዲሁም በአዛውንቶች እና በአካል ጉዳተኞች ላይ ለተፈፀሙ የማሰቃየት ተግባራት፣ በአስገድዶ መድፈር፣ በአሰቃቂ ግድያ፣ ጠለፋ፣ ማፈናቀል፣ ሰው መሰወር፣ ሆነ ብሎ ለችግረኞች የምግብ እና የመሠረታዊ ሸቀጦችን ፍሰት መከላከል እና በሌሎች ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች (ጠንሳሾች፣ ትእዛዝ የሰጡ፣ ያቀዱ፣ የመሩ እና ከፍተኛ ሀላፊነት ኖሮባቸው ሀላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት ጉዳት እንዲደርስ ያደረጉ፡ እና ሌሎች ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎችን በተመለከተ) በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ምህረት የማይተገበር መሆኑን በፖሊሲው ላይ በግልጽ ማማላከት እና በህግ መደንገግ ይገባል፡፡
- ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እውነት የማፈላለግ ሂደቱን ለማገዝ እና እርቅን ለማበረታታት ከፍተኛ ተጠያቂነት ያለባቸው ተጠርጣሪዎች እንዳስፈላጊነቱ በእውነት ማፈላለግ ተቋም ፊት ቀርበው እንዲናገሩ ለማድረግ በተቋሙ ፊት ቀርበው ለሚሰጡት ቃል ህጋዊ ጥበቃ እና ከለላ ሊያገኙ የሚችሉበትን አግባብ (use immunity) ማስቀመጥ ይገባል፡፡
- በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት አሰጣጥ ሙሉ እውነቱን ማውጣት/መናገር እና በምርመራ ሂደት መተባበር፣ ጥፋትን ማመን፣ መጸጸት፣ በይፋ ህዝብን ይቅርታ መጠየቅ፣ እንዳስፈላጊነቱ ለተፈጸመ በደል በማካካሻ ሂደቱ ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆን፣ በበጎ ፈቃድ ስራ እና ህዝባዊ አገልግሎት ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆን፣ ወንጀል የተፈፀመበት ምክንያት (motive)፣ እንዳስፈላጊነቱ ከህዝባዊ ሀላፊነት ወይም ስልጣን ለመልቀቅ ፈቃደኛ መሆን፣ ተመሳሳይ የወንጀል ሪከርድ አለመኖር፣ ተመሳሳይ ጥሰቶችን ላላመፈጸም ቃል መግባት የሚሉት እና እንደየአግባብነቱ የሚወሰኑ ቅደመ-ሁኔታዎች ሊካተቱ ይገባል፡፡
- በተጨማሪም የምህረት ቅድመ-ሁኔታ እና የምህረት አሰጣጥ ሂደት እንደአግባብነቱ ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ሥርዓቶችን ባገናዘበ፣ የተበዳይ ፍላጎት ባማከለ፣ እና ተሳትፏቸውን ባረጋገጠ መልኩ ሊፈፀም ይገባል፡፡
- የምህረት መስጠት ሂደት በግጭት ውስጥ የነበሩ ማህበረሰቦችን ክብር እና የተጎጂዎችን ሞራል ግምት ውስጥ ባስገባ አግባብ ለመከወን እንዲቻል የሂደቱ ትግበራ ከመጀመሩ አስቀድሞ የተጎጂዎችን ፍላጎት እና ተሳትፎ ለማረጋገጥ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች በመውሰድ ግላዊ፣ ግለሰባዊ እና ማህበረሰባዊ እርቅን በሚያበረታታ አኳኋን ሊተገበር ይገባል፡፡

### 8.3.2. የምህረት መስጠቱ ሂደት ተቋማዊ አደረጃጀት

በዚህ የፖሊሲ ጥያቄ ላይ በተሳታፊዎች ግብአት ላይ የተመሰረተው ግኝት እንደሚያመላክተው ተሳታፊዎች በከፍተኛ ደረጃ የመረጡት አማራጭ **የምህረት መስጠቱ ሂደት አዲስ በሚቋቋም የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት ሊተገበር ይገባል** የሚለው ነው፡፡ የተወሰኑ ተሳታፊዎች ደግሞ አሁን ያለውን የምህረት አሰጣጥ አደረጃጀት

በማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ መጠቀም፣ ወይም በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ወይም በኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አማካኝነት ቢሰራ ይበልጥ ተመራጭ ነው ብለዋል።

የምህረት አሰጣጥ ተቋማዊ አደረጃጀትን በተመለከተ በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት የሚሰጥበት ዋና ምክንያት ሙሉ እውነትን ከማወቅ ጋር የሚያያዝ እንደመሆኑ መጠን ሂደቱን ከእውነት ማፈላለግ ተግባር ጋር በተንሰላሰለ መዋቅራዊ አደረጃጀት አማካኝነት መተግበር ተገቢ ነው። በተጨማሪም ከተቋማዊ አደረጃጀት ጋር የሚነሳውን የተዓማኒነት፡ የገለልተኝነት እና የቅቡልነት ስጋቶችን በሚቀርፍ እና የባህላዊ ሥርዓቶች ሚና ባገናዘበ አግባብ ሊደራጅ ይገባል።

### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

በፖሊሲው **የምህረት መስጠቱ ሂደት በየትኛው ተቋማዊ አደረጃጀት ሊከናወን ይገባል** ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ሀሳቦች እና መርሆዎች ባገናዘበ አግባብ ሊከናወን ይገባል።

- የምህረት መስጠት ተቋማዊ አደረጃጀት **ለእውነት ማፈላለግና እርቅ ተግባራት አላማ በሚቋቋመው የህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት** ሊሰጥ ይገባል።
- የኮሚሽኑ ሌሎች አደረጃጀቶች እና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ይህ ኮሚሽን በምህረት ጉዳይ የተነሱ ስጋቶችን በሚቀርፍ፡ ቅቡልነትን በሚያረጋግጥ፡ ለምህረት ስራ ተገቢውን ትኩረት በሚሰጥ አግባብ መቋቋም አለበት።
- እንዲሁም የምህረት አሰጣጥ ሂደትን በውጤታማነት ለማከናወን እንዲቻል ግልጽ፣ አሳታፊና አካታች በሆነ መንገድ የተመረጡ **የህገር ሽማግሌዎች እና በምህረት ተግባር በቂ ልምድና እውቀት ያላቸውን ዓለም-አቀፍ ባለሙያዎችን በአማካሪ እና በድጋፍ ሰጪነት ያካተተ አደረጃጀት ማዋቀር** ይገባል። ይህም ኮሚሽኑ የህዝብ ቅቡልነት ኖሮት ህጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሚዛናዊ የምህረት መስጠት ስራ እንዲፈፅም ያስችላል።
- የኮሚሽኑ ምህረት አሰጣጥ ሂደት ከተጠያቂነት፣ ከእውነት ማፈላለግ እና ሌሎች የሽግግር ፍትህ ስልቶች ጋር የተመጋገበ፣ የተበዳዮችና ፍላጎት ያማከለ እና ተሳትፏቸውን ያረጋገጠ እንዲሁም የአጥፊዎችን ተሳትፎ የሚያበረታታ ግልጽ የአሰራር ሂደትን የሚከተል መሆን አለበት።

## 8.4. ማካካሻ

### 8.4.1. ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተጎጂዎች እና የማካካሻ ዓይነቶች

በእነዚህ የፖሊሲ ጥያቄዎች ላይ ተሳታፊዎች በመርህ ደረጃ ማካካሻ ለሁሉም ተጎጂዎች እንደየጉዳታቸው መጠን መስጠት ተገቢ መሆኑን ገልጸዋል። የማካካሻ አይነቶችም ቢሆኑ ሊወሰኑ የሚገባው የጉዳቱን አይነት እና መጠን መሰረት ባደረገ መልኩ መሆን እንደሚገባው አመልክተዋል። ሆኖም የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተጎጂዎችን እና የማካካሻ አይነቶች በተሳታፊዎች ተዘርዝረዋል።

ሁሉን-አቀፍ የማካካሻ ስርአት መቀየስ እና መተግበር የተጎጂዎችን የካሳ ጥያቄ ለማርካት፣ እውቅና ለመስጠት፣ የተጎጂዎችን ክብር ለመመለስ እንዲሁም የማካካሻ ትግበራው በሀገር ላይ የሚፈጥረውን ኢኮኖሚያዊ ጫና ለመቀነስ ጠቀሜታ አለው። ሁሉን-አቀፍ የማካካሻ መርሀ-ግብር ሲባል ካሳ፣ ማገገሚያ፣ ወደ ነበሩበት መመለስ፣ እርካታ እና ያለመድገም ዋስትናን ያካተተ ነው።

የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ለተሳካ የማካካሻ ፕሮግራሞች ቀረጻ እና አተገባበር አመላካች ማንጸሪያዎች እና መለኪያዎችን ያስቀምጣል። የተጎጂዎች እና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ውጤታማ ተሳትፎ የሚያበረታታ፣ ግልጽነት፣ አለማግለል፣ አለማዳላት፣ ፍትሃዊነት እና ተገቢነትን የጠበቀ፣ ለተጎጂው ጉዳት መፍትሔ በመስጠት በኩል ፈጣን፣ በቂ እና ዘላቂነት ያለው፣ ጾታዊ እና ጾታ-ተኮር ጥሰቶችን በተገቢው ያካተተ፣ የተለያዩ

ተጎጂ ቡድኖችን ፍላጎት በተለይም የሕጻናትና የሴቶችን ፍላጎት ያገናዘበ እና ከልማት አጀንዳ ጋር የተቀራኘ መሆን አለበት የሚሉ ሀሳቦችን ያስቀምጣል።

የማካካሻ ሥርዓት እነዚህን መርሆዎች ባማከለ አግባብ ቢቀረጽ የታለመውን ግብ በማሳካት ረገድ ፋይዳው የጎላ ይሆናል። ከማካካሻ አይነቶች አንጻር በርካታ ተሳታፊዎች እንዳነሱት ለሁሉም የማካካሻ አይነቶች ተገቢ እውቅና እና ቦታ መስጠት አስፈላጊ ቢሆንም የማካካሻ ትግበራው ሊፈጥረው የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጫና ታሳቢ በማድረግ ለተወሰኑ የማካካሻ ሥርዓቶች ቅድሚያ እና ትኩረት በመስጠት መደንገግ አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም የማካካሻ ሥርዓት ሁለንተናዊነት እና ሁሉን-አቀፍነት እንደተጠበቀ ሆኖ የጥሰቶችን ሙሉ ሀቅ ማፈላለግ፡ ይፋ ማውጣት እና እውቅና መስጠትን፣ ለተፈጸሙት በደሎች እንደ መንግስት በተለያየ መንገድ በይፋ ይቅርታ መጠየቅን (ለምሳሌ ለተለዩት ተጎጂዎች የይቅርታ ደብዳቤ በመጻፍ)፣ የመታሰቢያ እና ማስታወሻ ክንዋኔዎችን፣ ሌሎች ምሳሌያዊ የማካካሻ ዘዴዎች፣ መልሶ ማቋቋም እና የማገገሚያ እርምጃዎች አካባቢያዊ አውድን ባገናዘበ አግባብ ቅድሚያ በመስጠት የሚተገበሩበትን ሁኔታ መደንገግ አስፈላጊ ነው።

በተጨማሪም ተጎጂዎች ያሉባቸውን አንገብጋቢ እና አስቸኳይ ችግሮች በተወሰነ መልኩ ለመቅረፍ ይረዳ ዘንድ የተሟላ የማካካሻ ሥርዓት እስኪተገበር ድረስ ጣልቃ-ገብ የማካካሻ ወይም የድጋፍ ተግባራትን መቀየስ ያስፈልጋል።

### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

ፖሊሲው ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተጎጂዎች እና የማካካሻ ዓይነቶችን በተመለከተ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ሀሳቦች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

- የማካካሻ ሥርዓትን እንደ ማገገሚያ፣ ወደ ነበሩበት ሁኔታ መመለስ፣ እርካታ፣ ካሳ እና ያለመድገም ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ ስራዎችን ባካተተ መልኩ መቅረጽ ይገባል።
- የማካካሻ መርሐ-ግብሮች የተጎጂዎችን ፍላጎት እና እርካታ ባማከለ፣ ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚመልስ፣ ፍትሐዊነትና ተገቢነትን በጠበቀ አግባብ ሊቀረጹ እና ሊተገበሩ ይገባል።
- የማካካሻ መርሐ-ግብሮች የተለያዩ ተጎጂ ቡድኖችን ፍላጎት በተለይም የሕጻናት፣ ሴቶች፣ ተፈናቃዮች፣ አካል ጉዳተኞች እና አዛውንቶችን ልዩ ሁኔታ ያገናዘቡ መሆን ይገባቸዋል።
- የማካካሻ መርሐ-ግብሮች የማህበረሰቡን እሴት ማእከል ያደረገ፣ በባህላዊ አሰራር መሰረት የሚሰጥ ካሳን ከሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ጋር ባጣጣመ አግባብ መተግበር የሚቻልበትን መንገድ ያገናዘቡ ሊሆን ይገባል።
- የተጎጂዎችን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ተደራሽ የማካካሻ ሥርዓት ለመተግበር የማካካሻ መርሐ-ግብሮች የመንግስትን ብቻ ሳይሆን የሁሉም ማህበረሰብ ክፍሎች አስተዋጽኦን የሚያበረታቱ ማዕቀፎች ሊኖሩት ይገባል።
- ማካካሻ ሊፈጥር የሚችለውን ኢኖሚያዊ ጫና በመቀነስ እና በውጤታማነት እንዲተገበር ለማስቻል የተለያዩ ምሳሌያዊ የማካካሻ አይነቶች (እውቅና መስጠት እና ይፋዊ ይቅርታ፣ የማስታወሻ ክዋኔዎች፣ መታሰቢያ እና ሲያሜዎች)፣ የማገገሚያ እርምጃዎች እና የጋራ ካሳ ሥርዓቶችን በቅድሚያ የሚከናወኑበትን አግባብ መቀየስ ይገባል።
- ጾታዊ ጥቃት የደረሳባቸው ተጎጂዎችን ጨምሮ ለሁሉም ተጎጂዎች አንገብጋቢ ችግሮች እና ጉዳቶች ጊዜያዊ መፍትሄ ከመስጠት አንጻር ጣልቃ-ገብ የማካካሻ ተግባራት ከወዲሁ የሚከናወኑበት ማዕቀፍ መቅረጽ ይገባል።

- የሚቀረጸውን የማካካሻ መርሀ-ግብር በምልዐት ለመተግበር እንዲቻል የተጎጂዎች መልሶ ማቋቋም እና ድጋፍ ፈንድ በህግ ማቋቋም ያስፈልጋል።

### 8.4.2. የማካካሻ ሥርዓት ተቋማዊ አደረጃጀት

አብዛኞቹ ተሳታፊዎች **የማካካሻ ሥርዓት አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ሊመራ ይገባል** የሚለውን አቋም አንፀባርቀዋል። የተወሰኑ ተሳታፊዎች ደግሞ ስራው በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ወይም የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እንዲከናወን ሀሳብ አቅርበዋል። ጥቂት ተሳታፊዎች አዲስ አማራጭ አቅርበዋል።

ተሳታፊዎች ተገቢ ነው ያሉትን አማራጭ ሲያቀርቡ በሁሉም የጋራ መነሻ የነበረው ምክንያት ተአማኒነት፣ ገለልተኝነት እና ውጤታማነትን የሚመለከት ነው።

በማካካሻ ሂደት የባህል ተቋማት የጎላ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል የሚለው አዲስ አማራጭም በብዙ ተሳታፊዎች የተንጸባረቀ ሀሳብ ነው። ማህበረሰቡ በባህላዊ ስርአት መሰረት በሚሰጥ ካሳ ምሉእነት አመኔታ ያለው እንደመሆኑ መጠን ይህን ከሚቋቋመው አዲስ ኮሚሽን ተግባራት ጋር አስተሳስሮ መተግበር የተጎጂዎች የማካካሻ ፍላጎት የተሟላ እንዲሆን፣ የግልም ሆነ የጋራ ካሳዎች የተጎጂዎችን እና የተለያዩ የህብረሰተሰብ ክፍሎችን ፍላጎት በሚያረካ መልኩ እንዲፈፀሙ ያስችላል።

#### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

ፖሊሲው የማካካሻ ተግባር በማን ይከናወን የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ሀሳቦች እና መርሆች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

- አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች የማካካሻ ተግባር ሊከናወን የሚገባው አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት ነው ሲሉ ከተዓማኒነት ከቅቡልነት እና ከገለልተኝነት አንጻር ያነሷቸው በርካታ ስጋቶች ያሉ እንደመሆኑ መጠን አዲስ የሚቋቋሙ ኮሚሽኖች ቁጥር ሲበዛ ሊከሰት የሚችለውን አላስፈላጊ የሀብት ሽሚያ እና የህዝብ ግርታ ለመቀነስ **የማካካሻ ትግበራው በህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን (እና በኮሚሽኑ) ምክረ-ሀሳብ አቅራቢነት** እንዲከናወን ቢደረግ የተሻለ ነው።
- የኮሚሽኑ ሌሎች አደረጃጀቶች እና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ ይህ ኮሚሽን በማካካሻ ጉዳይ የተነሱ ስጋቶችን የሚቀርፍ፣ የተጎጂዎችን ፍላጎቶችን ያማከለ፣ ቅቡልነት ያለውና ለማካካሻ ተግባር ተገቢ ትኩረት እና የዝግጅት ስራ ከጅምሩ እንዲሰራ ማድረግ ይገባል።
- የማካካሻ ሂደቱ አካባቢያዊ ባለቤትነትን በሚያረጋግጥ አግባብ እና አውድ-ተኮር እንዲሆን በማድረግ ውጤታማ ተግባራትን ለማከናወን እንዲያስችል የማካካሻ መዋቅራዊ አደረጃጀት ግልጽ፣ አሳታፊና አካታች በሆነ መንገድ የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች እና በቂ ልምድና እውቀት ያላቸው ዓለም-አቀፍ ባለሙያዎችን በአማካሪነት እና በድጋፍ ሰጪነት ያካተተ ሆኖ ሊዘጋጅ ይገባል።
- ኮሚሽኑ በሚዘረጋው ሁለንተናዊ የማካካሻ ሥርዓትና መርሀ-ግብር መሰረት የተጎጂዎች መልሶ ማቋቋምና ድጋፍ ፈንድ በህግ ማቋቋምን ጨምሮ - ከጅምሩ ለማካካሻው አስፈላጊ የሆነ ሀብት የሚያሰባስብበት፣ ጣልቃ-ገብ ማካካሻዎችን የሚተገብርበት፣ በረጅም ጊዜ የማካካሻ ትግበራ ላይም ምክረ-ሀሳብ የሚሰጥበት ስልጣን እንዲኖረው ሆኖ መደራጀት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ እንደነገሩ ሁኔታ የጉዳቱን አይነትና ክብደት መሰረት በማድረግ ለተጎጂዎች ግለሰባዊ ካሳን ጨምሮ ሌሎች የማካካሻ አይነቶች ሊሰጥ የሚችልበትን አግባብ አጥንቶ ምክረ-ሀሳብ የሚያቀርብበት ስልጣን ሊኖረው ይገባል።

## 8.5. ተቋማዊ ማሻሻያ

### 8.5.1. ቅድሚያ በመስጠት የመለየት እና ማጥራት ተግባራት የሚከናወንባቸው ተቋማት

ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ያስቻሉ የህግ ማዕቀፎች እና ተቋማትን በተገቢ መልክ መለወጥ እና ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ የሚረዱ ሌሎች አውድ-ተኮር ዘዴዎችን መተግበር - ተመሳሳይ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ሌሎች በደሎችን ለመከላከል እና እንዳይደገሙ ዋስትና ለመስጠት ይረዳል። ስለሆነም ተገቢ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በመቅረፅ ተቋማዊ ማሻሻያ ማድረግ ይጠበቃል።

የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ ማእቀፍ ዋና ትኩረት የተመረጡ ተቋማትን የስራ ክፍሎች/ግለሰቦች መለየት እና ማጥራት፣ ከስራ እና ከህላፊነት ማግለል፣ የህግ እና የአሰራር ለውጥ በማድረግ የዜጎችን መብት የሚያከብሩ፡ የሚያስከብሩ እና ያለፉትን አይነት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለመከላከል የሚያስችሉ ህጎች፣ አደረጃጀቶች እና አሰራሮች መፍጠር ነው። ይህን ማከናወን ተቋማቱን በተገቢ መልኩ ለመቀየርና የተቋማቱን ተዓማኒነት፣ ቅቡልነት እና አሰራር በመለወጥ ዘላቂ ማሻሻያ ለማኖር መሰረት ይጥላል። በሽግግር ፍትህ ሂደት የሚታሰብ የእርቅ እና የሰላም ሂደትንም የሚያሳልጥ ይሆናል።

ይህን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ ተሳታፊዎች የልየታ፣ ማጥራት እና ተገቢ ማሻሻያ ስራ ሊከናወንባቸው ይገባል ያሏቸውን ሰፊ የተቋማት ዝርዝር አቅርበዋል።

ተገቢውን ጥናት በማድረግ ማህበረሰቡ የጠቀማቸውን ተቋማት በማየት ገለልተኛ፣ ነጻ፣ እና ቅቡልነት ያላቸው ተቋማዊ አደረጃጀቶችን መገንባት ለሽግግር ፍትህ ስኬት መሰረታዊ ተግባር ነው። ይህም ሆኖ በሽግግር ፍትህ ሂደት በሁሉም ተቋማት ላይ የልየታ፣ የማጥራት እና የማሻሻል ተግባር ማከናወን አዳጋች ስለሚሆን - ያለመደገም ዋስትናን ከማረጋገጥ አንጻር ባለፉት ጊዜያት በሰብዓዊ መብት ጥሰት ላይ በተሳተፉ፣ የዜጎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በማስከበር ረገድ ባልተሳካላቸው፣ እንዲሁም ያለፉ ጥፋቶች እንዳይደገሙ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ በሚችሉ ተቋማት ላይ በማተኮር የማሻሻያ ተግባራት ማከናወን ከውጤታማነት አንጻር የተሻለ ነው።

በዚህ ረገድ ገለልተኝነት፣ ተዓማኒነት እና ቅቡልነት ያጡ ስለመሆናቸው በተሳታፊዎች በተደጋጋሚ በተነሱት የፍትህ፡ የደህንነት፡ የጸጥታ እና የሚዲያ ተቋማት፡ እንዲሁም በውስን የህግ ማሻሻያ ስራዎች ላይ የሚያተኩር የማሻሻያ ሂደት የተነሱትን ስጋቶች እና ቅሬታዎችን ለመቅረፍ የሚያስችል ይሆናል። ተግባሮቹም ግልጽ በሆነ የልየታ ሂደት እና የአለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት መስፈርቶችን ባከበረ መልኩ መከናወን ይኖርባቸዋል።

### 8.5.2. የማሻሻያ ተቋማዊ አደረጃጀት

ተሳታፊዎች በከፍተኛ መጠን የደገፉት አማራጭ 'ገለልተኛ እና ነጻ የሆነ አዲስ አካል በማቋቋም የተቋማት ማሻሻያ ተግባር ሊከናወን ይገባል' የሚለው ነው። 'በሁሉም ተቋማት ውስጥ የልየታ፡ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ሀላፊነት ያላቸው ቡድኖች በማዋቀር ተግባራቶቹን ማከናወን ይገባል' የሚለው አማራጭ በተወሰኑ ተሳታፊዎች ድጋፍ አግኝቷል።

የተቋም ማሻሻያ ስራ የሚከናወንበት ተቋማዊ አደረጃጀትን በተመለከተ በተደጋጋሚ በስጋትነት የተነሳው ዋና ሀሳብ ብዙዎቹ ተቋማት ሰብዓዊ መብት እንዲጣስ በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ተሳትፈዋል ወይም ሀላፊነት እያለባቸው ሀላፊነታቸውን ባለመወጣት አስቻይ ሁኔታን ፈጥረዋል፡ ስለሆነም ትርጉም ያለው ማሻሻያን ለማድረግ አዲስ ነጻና ገለልተኛ ተቋም መመስረት ያስፈልጋል የሚል ነው።

#### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

ፖሊሲው ተቋማዊ ማሻሻያን በተመለከት ለቀረቡት የፖሊሲ ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ባገናዘበ አግባብ ሊሆን ይገባል።

- የማጥራት ስራ የሚካሄድባቸው ተቋማት እና ትኩረት የሚሰጣቸው ተቋማት የስራ ክፍሎች እና ግለሰቦች የሚለዩበት ግልጽ ማንጸሪያ በፖሊሲው ማመላከት እና በህግ መደንገግ ይገባል።

- በዚህ ረገድ የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባር ትኩረት በሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ከፍተኛ ሚና በነበራቸው ተቋማት፡ የዜጎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በማስከበር ረገድ ሀላፊነት በተሰጣቸው ተቋማት፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ ሰብዓዊ መብትን የማስከበር ሀላፊነት እያለባቸው ይህን ባላደረጉ ተቋማት፤ እንዲሁም ያለፉ ጥፋቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ በሚገባቸው ተቋማት ላይ ሊሆን ይገባል። በዚህ ረገድ በተለይ በተሳታፊዎች በተደጋጋሚ የተለዩ ተቋማት (የፍትህ፡ የጸጥታ፡ የደህንነት እና የሚዲያ ተቋማት) ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል።
- ለሰብዓዊ መብት ጥሰት አስቻይ ሁኔታን የፈጠሩ ፖሊሲዎች፡ ህጎችና አሰራሮችን ማሻሻል ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል ሊካተት ይገባል።
- የማጥራት ሂደቱን በነፃነት እና በገለልተኝነት ለመተግበር፡ ቅቡልነቱንም ለመጨመር፡ እንዲሁም ከሌሎች የሽግግር ፍትህ መንገዶች ጋር ያለውን መስተጋብር የበለጠ ጠንካራ ለማድረግ እንዲቻል የማጥራትና የተቋማት ማሻሻያ ስራ ገለልተኛ እና ነጻ በሆነ አዲስ አካል ሊከናወን ይገባል።
- የሚቋቋመው አዲስ ተቋም የመለየት፡ የማጥራት እና የማሻሻል ስራዎች ሲሰራ የሚያጋጥመውን የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ለመድፈን በዘርፉ በቂ ልምድ እና እውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን በአማካሪነት ማካተት ይኖርበታል።
- የዳኝነት ዘርፍን በተመለከተ የሚቋቋመው ተቋም የልየታ እና ማጥራት ተግባራትን ካከናወነ በኋላ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክረ-ሀሳብ ማቅረብ ይገባል።
- የሚቋቋመው ተቋም የመለየትና የማጥራት ስራ በሚሰራበት ወቅት የሚሻሻለውን ተቋም መሰረታዊ ችግር በቅጡ ለመረዳት እንዲችል ከተቋሙ ራሱ ተገቢ ልምድና እውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ማሳተፍ ይገባል።
- በፖሊሲ ማእቀፍ በሚቀመጡ የልየታ እና የማጥራት ማንጸሪያዎች እና የማጥራት ሂደቱ በሚመራበት ሥነ-ሥርዓት መሰረት ክልሎች በክልል ተቋማት ላይ የመለየትና የማጥራት ተግባራትን ማከናወን ይኖርባቸዋል።

## 8.6. የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ውይይት የተካሄደበት ሌላው መሰረታዊ ጉዳይ '**የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን መነሻ ከየት ሊሆን ይገባል**' የሚለው የፖሊሲ አማራጭ ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ ከሁሉም የሽግግር ፍትህ አላባዎች ጋር በተያያዘ የተነሳ ቢሆንም - ከእውነት ማፈላለግ እና ከተጠያቂነት ጋር በተያያዘ የጊዜ ወሰኑን በግልጽ ማስቀመጥ ተገቢ ነው።

ሀገራዊና አካባቢያዊ አውዶችን መሰረት በማድረግ፡ ያለፉ በደሎችን መጠን እና አይነት በማንሳት፣ ህዝብ ያልተግባባቸውን የታሪክ አረዳዶች ከመሰረቱ ለማጥራት፡ ተጠያቂነትን ለማስፈን እና የተጎጂዎችን የፍትህ ጥማት ከማርካት አንጻር - ተሳታፊዎች ተገቢ ነው ያሉትን የጊዜ ወሰን በርካታ ማንጸሪያዎችን በማገናዘብ አስቀምጠዋል።

ይህን ርእስ በተመለከተ የፖሊሲ ማርቀቅ ሂደቱ ሁሉም የሽግግር ፍትህ አምዶች በሚደጋገፍ አግባብ፡ የሀገራችን አውድ እና ሁኔታን ታሳቢ ባደረገ መልኩ፡ እንዲሁም የተነሱ ተስፋዎችን በሚያጠናክር እና ስጋቶችን በሚቀርፍ መንገድ መቅረጽ ይገባል።

### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

ፖሊሲው የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰንን በሚመለከት የፖሊሲ ጥያቄ ላይ ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ጉዳዮች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

- የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን የተከሰቱ በደሎችን እና ጥሰቶች በተገቢ መልኩ በሚያካትት፣ የወገንተኝነት እና አድሎአዊነት ስሜትን በማህበረሰብ ደረጃ በማያስከትል አግባብ መወሰን ተገቢ ነው።
- የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን በመርህ ደረጃ ለወንጀል ተጠያቂነት ከ1987 ጀምሮ፣ ለእውነት ማፈላለግ፣ ለእርቅ እና ለማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ/ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ ቢሆን የተሻለ ነው። ይህ አማራጭ የታለመውን ግብ ከማሳካት አንጻር፣ በተለይም ከወንጀል ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ ወደኋላ መሄድ የሚያስከተለውን ጫና እና ከህግ ማዕቀፍ ክፍተቶች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ተጠባቂ ውዝግቦችን ለማስወገድ ይረዳል።
- ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ እና ሌሎች አምዶች እንዳስፈላጊነቱ ወደኋላ በመሄድ የጥሰቶችን መሰረታዊ ምክንያት እና ሁነት በማጥራት ቁስሎቹ እንዲሽሩ፣ የተለያዩ ማህበረሰባዊ ስብራቶች እንዲጠገኑ፣ እርቅን በማበረታታት ባለፉ ጊዜያት በተፈጸሙ በደሎች አንፃር የጋራ ምልከታ እና አረዳድ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል። ሆኖም በዚህ ረገድ የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎች ከኢትዮጵያ ሀገራዊ ኮሚሽን ስልጣን እና ሀላፊነቶች ጋር በተናበበ እና በማይጣረስ መልክ መከናወን ይኖርባቸዋል።
- የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን ወደኋላ በተለጠጠ ቁጥር በቅርብ ጊዜያት የተፈጸሙ ጥሰቶች ተገቢ አትኩሮት እንዳይሰጣቸው ሊያደርግ ይችላል በሚል በተወሰኑ ቡድኖች የተነሳውን ስጋት ለመቅረፍ በሽግግር ፍትህ አምዶች የስረ-ነገር ስልጣን ስር የሚካተቱ ጉዳዮችን በተገቢ መልኩ በመደንገግ አስፈላጊው ትኩረት እንዲሰጣቸው ማመላከት ይገባል።

## 8.7. ባህላዊ የፍትህ አፈታት ስርዓቶች ሚና

ኢትዮጵያ በርካታ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ያሏቸው የተለያዩ ማህረሰቦች ሀገር ናት። በተቻለ መጠን እነዚህን ባህላዊ ሥርዓቶች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ተገቢ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል።

ግኝቱ እንደሚያሳየው '**ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች የትኞቹን ጉዳዮች ለመፍታት ራሳቸውን ችለው ወይም ከየትኞቹ የሽግግር ፍትህ ዓላማዎች ጋር ሊተገበሩ ይገባል**' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች በእውነት ማፈላለግ፡ በእርቅ፡ በማካካሻ እና በምህረት ስራዎች ላይ ሊተገበሩ እንደሚገባ አንስተዋል።

ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊኖራቸው የሚገባ ዋና ሚና ሀገራዊ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ማገዝ እና መደገፍ ነው። ከሌሎች ተቋማት ጋር በመሆን እውነትን በማፈላለግ፡ ተጠያቂዎች ለፍትህ እንዲቀርቡ በመርዳት፡ በእርቅ ጉዳይ፡ በማካካሻ ሥርዓት እና የህዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር የሚያስችሉ ስራዎችን በመስራት ደጋፊ ሊሆኑ ይችላሉ።

በተጨማሪም በህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን የስረ-ነገር ስልጣን ስር የማይሸፈኑ ወይም በተግባር በማይከናወኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ግጭቶችን ለመፍታት በኮሚሽኑ በሚቀመጡ መርሆዎች መሰረት እውነት በማፈላለግ፡ በእርቅ ተግባራት እና ተያያዥ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ሀላፊነት ተሰጥቷቸው መሳተፍ ይኖርባቸዋል።

ክልሎች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊሳተፉ የሚገባቸውን ባህላዊ የፍትህ ሥርአቶችን በመለየት እውቅና እንዲሰጡ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

'**ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች እና እሴቶችን በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ለመጠቀም በስርዓቶቹ ላይ መደረግ የሚገባቸው ለውጦች ወይም ማሻሻያዎችን በተመለከተ**' ግኝቱ እንደሚያሳየው - ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርአቶች ሚና እንዲኖራቸው የሚጠበቀው አሁን ባሉበት አግባብ ሳይሆን ከሽግግር ፍትህ አምዶች ጋር በተመጋገበ መንገድ በቅድሚያ ማሻሻያዎችን እንዲያከናውኑ በማድረግ ነው። ከዚህ አኳያ ትኩረት ተሰጥቶ መሻሻል ሊደረግባቸው ይገባል የተባሉት ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች ባህላዊ ሥርዓቶችን ከመንግስት ፖለቲካዊ ተፅእኖ ማላቀቅ፡ እንዲሁም

ህዝቡ በሀይማኖት አባቶች እና ሀገር ሽማግሌዎች ላይ ያለውን እምነት መመለስን የሚመለከቱ ናቸው። ተቋማቱ በሽግግር ፍትህ ሚና እንዲኖራቸው ከተፈለገ ገለልተኛነታቸው፣ ነጻነታቸው እና ተዓማኒነታቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

ሊደረጉ ከሚገቡ ማሻሻያዎች ጋር ተያይዞ የባህል ፍትህ ሥርዓቶች ተዓማኒነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ውስጣዊ ማሻሻያዎችንም መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። ይህም በተለይ የሀገር ሽማግሌዎች የምርጫ ሥርዓት ፍትህዊ እንዲሆን ማድረግ፣ የጾታ፣ የአካል ጉዳተኞች እና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎን ማሳደግ፣ የባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ከአካባቢነት እሳቤ ወጥተው አካታች እና አቃፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የጾታ እኩልነት ለማረጋገጥ የሥርዓት ማሻሻያ ማካሄድ፣ ብሄርን መሠረት ካደረገ አድሎአዊ አሰራር ነጻ ሆኖ መስራት፣ ሃቀኛ እና ከሙስና የጸዱ መሆን፣ እንዲሁም በሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ላይ ትኩረት መስጠትን የሚመለከት ነው።

የማሻሻል ተግባሩ በባህላዊ ፍትህ ሥርዓቶቹ ላይ ብቻ የሚጣል ሳይሆን የሁሉንም እገዛ የሚጠይቅ ነው። እነዚህን ስርዓቶች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ጥቅም ላይ ማዋል እንዲቻል በህግ እውቅና መስጠት ያፈልጋል። ሕዝብም ባህላዊ ስርዓቶቹን ሊጠብቃቸው፣ ሊያጎለብታቸው እና ከብረዛ ሊከላከላቸው ይገባል።

### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

ፖሊሲው ከባህል የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ሚና ጋር በተያያዘ ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጥ የሚከተሉትን ሀሳቦች ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል።

- ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች በተቻለ መጠን በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ተገቢ ሚና ሊኖራቸው ይገባል።
- የባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ዋና ሚና የሽግግር ፍትህ ሂደትን ማገዝ እና መደገፍ ነው። ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት እውነትን በማፈላለግ፣ ተጠያቂዎች ለፍትህ እንዲቀርቡ በመርዳት፣ በእርቅ ጉዳይ፣ በማካካሻ ሥርዓት እና የማህበረሰብ ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችሉ ስራዎችን በመስራት ደጋፊ ስራ እንዲያከናውኑ ማድረግ ያስፈልጋል።
- በህቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ስረ-ነገር ስልጣን ማእቀፍ የማይሸፈኑ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች በኮሚሽኑ የማይታዩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ግጭቶችን በተመለከተ - ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች በሀገር-አቀፍ ደረጃ በሚዘረጋ አሰራር እና መርሆዎች መሰረት እውነት በማፈላለግ፣ በእርቅ ተግባራት እና ተያያዥ በሆኑ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ሀላፊነት ተሰጥቷቸው እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።
- ክልሎች በሚቀመጠው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት በሽግግር ፍትህ ሂደት ሊሳተፉ የሚችሉ የባህል ፍትህ ሥርአቶችን የሚመለከት ህግ ማውጣትና እውቅና መስጠት ይኖርባቸዋል።
- በሽግግር ፍትህ ሂደት ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ተገቢ ሚና እንዲጫወቱ ለማስቻል ገለልተኛነታቸውን፣ ነጻነታቸው እና ተዓማኒነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመተግበር ከማንኛውም የፖለቲካ ጣልቃ-ገብነት መጠበቅ ያስፈልጋል።
- ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች ያሉባቸውን ውስጣዊ እና ውጫዊ ክፍተቶች ለመሙላት ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል አስተዋጽኦ ማድረግ በሚችልበት አግባብ መደራጀት ይኖርባቸዋል። በተለይም የጾታ እና የዜጎችን እኩልነት፣ የፖለቲካ ተጽዕኖ ነፃነት፣ የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ማሻሻያዎችን ለማከናወን ተገቢ ድጋፍ የሚደረግበት ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

## 8.8. የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ሚና

በሽግግር ፍትህ ሂደቱ '**ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ምን ሚና ሊኖራቸው ይገባል**' የሚለውን የፖሊሲ ጥያቄ በተመለከተ በከፍተኛ ደረጃ ድጋፍ ያገኘው እሳቤ ከገለልተኝነት፣ ከጉዳዩ ይዘት እና በሀገራችን ከሚታዩት ግጭቶች አይነት እና ውስብስብነት በመነሳት፡ እንዲሁም የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊያሳካው ከሚሻው ዓላማ አንፃር በሀገር-አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሊኖር ይገባል የሚል ነው። በመሆኑም የህዝቡ እይታ በዚህ ሂደት ክልሎች እንደ ሀገር ለሚሳለጠው ትግበራ አስፈላጊውን ድጋፍ እና ትብብር ከማድረግ ባለፈ የራሳቸውን የሽግግር ፍትሕ ሂደት መተግበር የለባቸውም የሚል ነው።

ሀገር-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር በበርካታ ምክንያቶች የሚመከር አማራጭ ነው። የመጀመሪያው ከሽግግር ፍትሕ ሂደት አስፈላጊነት አንፃር የሚታይ ነው። የሽግግር ፍትሕ የሚተገበረው መደበኛውን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር በዘላቂነት ለመተካት ወይም በየእለቱ የሚከናወን የግጭት መከላከል እና አስተዳደር ስርአትን ለማስወገድ አይደለም። መሰረቱ የዘላቂ ሠላም አስፈላጊነት ነው። በመሆኑም ሀገራዊ ይዘት እና እንደምታ ባለው ጉዳይ ላይ በተናጠል እንዲተገበር ለክልሎች ስልጣን መስጠት የሚመከር አይደለም።

በሁለተኛ ደረጃ መታየት ያለበት ጉዳይ ከሽግግር ፍትሕ ሂደት ዓላባዎች እና ከሚሸፍናቸው ጉዳዮች አንጻር የህግ መሡረቱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ነው። በመሰረቱ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 55(5) ላይ የወንጀል ህግ የማውጣት ስልጣን በዋናነት ለፌዴራል መንግስቱ የተሰጠ ነው። በዚህ ረገድ የክልሎች ስልጣን በፌዴራል መንግስቱ የወንጀል ህግ ላይ በግልፅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የተወሰነ ነው። ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን አስመልክቶ የወጡት ሕጎች በፌዴራል የወንጀል ህጉ ላይ የተመለከቱ ናቸው። ከህገ-መንግስቱ አንቀፅ 74(3)፣ 77(1) እና 94(1) ንባብ መረዳት እንደሚቻለው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣቸው ሕጎች ተግባራዊ መሆናቸውን የመከታተል፣ በስራ መተርጎማቸውን የማረጋገጥ እና በሕግ የተሰጡ ኃላፊነቶችን በተመለከተ ወጪ የመሸፈን ግዴታው የሚያርፈው በፌዴራል መንግስቱ ላይ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፍርድ ቤት ስልጣንን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 4(3) ላይ ዓለም-አቀፍ ሕጎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስለመሆናቸው ተመላክቷል።

በሌላ በኩል በክልል የሚወጣ ህግም ሆነ ባህላዊ አሰራር አገራዊ እንድምታ ባለው ግጭት ላይ ተፈጻሚ ማድረግ ከፌዴራል መርህ ጋር የሚቃረን ይሆናል። የሽግግር ፍትሕ ጉዳይ በአመዛኙ ከአንድ ክልል በላይ ያሉ ጉዳዮችን ወይም ዜጎችን የሚነኩ ጉዳዮችን የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን ለዚህ ስራ ሀገራዊ ፖሊሲ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል። ይህም የፌዴራላዊ አደረጃጀት መርህ የሚደግፈው ነው።

ሶስተኛው ጉዳይ በተግባር የታዩ አንዳንድ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው። ክልሎች የራሳቸውን የሽግግር ፍትህ ሂደት ይተግብሩ ቢባል አሁን ባለው ሁነት ፍትሃዊ እና ገለልተኛ ሆነው ያስፈፅሙታል የሚል እምነት በህዝቡ ዘንድ እንደሌለ በምክክሮቹ ሂደት በግልፅ ተንፀባርቋል።

በመጨረሻም በሽግግር ፍትህ ሂደት ማእቀፍ የሚታዩ ጉዳዮች ከሀገራችን ታሪካዊ ሁነቶችና የግጭት አዙሪቶች ጋር ግንኙነት ስላላቸው በአንድ ክልል ብቻ የሚታዩበት አሰራር ተገቢ አይሆንም።

ሆኖም በክልሎች ደረጃ በተናጠል የሚዋቀር እና የሚከናወን የሽግግር ፍትሕ ሂደት መኖር የለበትም ማለት ክልሎች በብሄራዊው ሂደት ላይ ተሳታፊ ወይም ባለቤት ሊሆኑ አይገባም ማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል። ክልሎች የሀገራዊ ችግሩ አካል እንደመሆናቸው መጠን የመፍትሄውም ዋና ተዋናይ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ክልሎች የባህላዊ ግጭት አፈታት ሥርዓቶችን በመለየት፡ እንዲሁም እያንዳንዱን የሽግግር ፍትህ ዓላማ ለማሳካት በሚደረጉ ልዩ ልዩ ስራዎች ጉልህ ሚና ሊጫወቱ ይገባል። ለአብነትም ክልሎች የሚያስተዳድሩት ህዝብ በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ላይ አመኔታ እንዲኖረው ማድረግ፡ ተሳታፊነት ማረጋገጥ፡ የህዝቦችን አብሮነት እና ግንኙነት የሚያጠናክሩ ስራዎች በመስራት ወዘተ የበኩላቸውን አበርክቶ ሊፈጽሙ ይችላሉ። ሂደቱን መደገፍ እና ከአዳናቃፊ ድርጊቶች በመቆጠብ የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን መተባበር አለባቸው ነው። በፌዴራል

ሥርዓት ውስጥ በፌዴራልና ክልል መንግስታት መካከል መተባበር፣ መተጋገዝና የጋራ ግብ መተለም የሚጠበቅ አሰራር ነው። በተጨማሪም በፌዴራል (ሀገር-አቀፍ) ደረጃ በሚከናወኑ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች በማይሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ሀላፊነት ተሰጥቷቸው ከሀገር-አቀፉ የሽግግር ፍትህ መሰረታዊ መርሆች ጋር በተናበበ አግባብ ስራዎችን መስራት መቻል ይኖርባቸዋል።

### የባለሙያዎች ቡድኑ ምክረ-ሀሳቦች

ፖሊሲው የክልሎችን ሚና ሲወስን የሚከተሉትን ጉዳዮች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

- በሀገር-አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሽግግር ፍትህ የትግበራ ሂደት ሊኖር ይገባል።
- በሽግግር ፍትህ ሂደት ክልሎች እንደ ሀገር ለሚደረገው የትግበራ ስራ አስፈላጊውን ድጋፍ እና ትብብር ማድረግ አለባቸው።
- ሀገራዊ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከቀረጻው እስከ ትግበራ የክልሎችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማረጋገጥ አለበት።
- በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ክልሎች የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል የሕግ እና የአሰራር ስርአት መዘርጋት እንዲሁም ተገቢ ማሻሻያዎችን ማካሄድ ያስፈልጋል።
- በሚደራጁት የፌዴራል (ሀገር-አቀፍ) ተቋማት የስረ-ነገር ስልጣን ማእቀፍ ስራ የማይወድቁ ወይም የፌዴራል ተቋማት ስልጣን ቢኖራቸውም በተለያዩ ምክንያቶች የማይተገብሯቸው የሽግግር ፍትህ ጉዳዮችን በተመለከተ ክልሎች ራሳቸውን ችለው ነገር ግን በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሚመሰረቱ መርሆችን በመከተል የእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ እና ማካካሻ ሥርዓት መመስረት እና መተግበር ይኖርባቸዋል።
- በዚህ ረገድ ክልሎች እነዚህን ተግባራት ሲያከናውኑ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶችን በሚያሳትፍ እና ከሽግግር ፍትህ መሰረታዊ መርሆዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ሊሆን ይገባል።
- በክልሎች እና በፌዴራል መንግስት፣ በክልሎች መካከል፡ እንዲሁም ከሌሎች አካላት ጋር የሚኖረው ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት በፖሊሲው በግልጽ እንዲመላከት ማድረግ ያስፈልጋል።

### 8.9. የፖሊሲ አፀዳደቅ እና የመንግስትና የባለድርሻ አካላት ሚናን በተመለከተ የቀረቡ ተጨማሪ ምክረ-ሀሳቦች

#### ሀ. የፖሊሲ አወጣጥ ሂደቱን በተመለከተ

- ረቂቅ ፖሊሲው ከተዘጋጀ በኋላ ተገቢ የሆነ የምክክር እና ተጨማሪ ግብዓት የማሰባሰብ ሥራ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ማካሄድ ይገባል። ይህ አካሄድ ረቂቅ ፖሊሲውን ለማጎልበት ከሚኖረው ፋይዳ በተጨማሪ በሽግግር ፍትህ ሁሉም ምዕራፎች ላይ ሊኖር የሚገባውን አሳታፊነት እና የሂደቱን ግልጸኝነት ለማረጋገጥ ይረዳል። ህዝብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሂደቱ ላይ ያላቸውን ባለቤትነት እንዲሁም የሂደቱን ቅቡልነት ከማጠናከር አንጻርም ጠቀሜታው የጎላ ነው።
- የፖሊሲ ማጽደቅ ሂደትን በተመለከተ ፖሊሲው ዓለም-አቀፍ ባህሪ ያላቸውን ጉዳዮች ያካተተ እና ትልቅ አገራዊ ፋይዳ ያለው በመሆኑ፣ የፖሊሲው ብዙ ክፍልም ከሰብዓዊ መብቶች ጋር በጥብቅ የተገናኘ በመሆኑ፣ መንግስት ለፖሊሲው የሰጠውን ትኩረት እና ክብደት ለማሳየት እና ቅቡልነቱን ለማጉላት፣ እንዲሁም ፖሊሲው አገራዊ የተፈጻሚነት ወሰን ያለው ቢሆንም በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ከፌዴራል መንግስቱ ባለፈ ክልሎችም የራሳቸውን የፖሊሲው ማስፈፀሚያ አሰራር የሚያወጡበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ - በዚህ አግባብ ሊፈፀም የሚችልን ፖሊሲ - በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 (10) ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲያፀድቀው ቢደረግ የተሻለ ይሆናል።

**ለ. የሽግግር ፍትህ ስልቶች ሁለንተናዊነት እና የተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር**

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ሁለንተናዊ እና ሁሉን-አቀፍ እንዲሆን ለማስቻል የሚከተሉትን ጉዳዮች በማገናዘብ ሊቀረጽ ይገባል።

- የሽግግር ፍትህ ስልቶች ሲቀረፁና ሲተገበሩ በሁለንተናዊነት እና ተመጋጋቢነት መርህ ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው።
- ሂደቱ የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስልቶች እና መንገዶችን በማቀናጀት በተናበበ መልኩ ለመተግበር እና ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል ሊሆን ይገባል። አንዱን የሽግግር ፍትህ ስልት ብቻ ተግባር ላይ ማዋል ወይም የተለያዩ ስልቶችን ሳያቀናጁ መፈፀም የተሳካ ውጤት እንዳይገኝ ያደርጋል። ስለሆነም በሀገራችን የተሳካ የሽግግር ፍትህ ሂደት እንዲኖረ ከተፈለገ አንዱ የሽግግር ጊዜ ፍትህ መንገድ ሌላውን የሚተካ ሳይሆን ሁሉም የሚደጋገፉ እና የሚመጋገቡ መሳሪያዎች እንደሆኑ በመገንዘብ በዚህ አግባብ እንዲተገበሩ ማድረግ ያስፈልጋል።
- የሽግግር ፍትሕ አላባዎችን ቅደም ተከተል እና ሚዛን መጠበቅ ያስፈልጋል።
- አጠቃላይ አሰራሩ በሽግግር ፍትህ ሂደትና አተገባበር ላይ ተሳታፊ በሆኑ አካላት መካከል መተማመንን መገንባት የሚያስችል፣ ወገንተኛ ያልሆነ፣ እና በአላማና በመርህ ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል።
- የሽግግር ፍትህ ሂደት ተግባራት ከአንድ በላይ በሆኑ ተቋማት መከናወንን የሚጠይቁ ናቸው። ስለሆነም እነዚህን ተግባራት የማቀናጀት እና የማስተባበር ሥራ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል።
- የተለያዩ የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን የሚያስፈፅሙ ተቋማትን ስልጣንና ተግባራት በግልፅ ማስቀመጥ፣ እንዲሁም በእነዚህ ተቋማት መካከል ተመጋጋቢ እና ተደጋጋፊ (complementary and mutually supportive) የስራ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ የሽግግር ፍትህ አላማን በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት ያስችላል። ስለሆነም በተቋማቶቹ መካከል ተገቢ ትብብር (cooperation) እና ቅንጅት (coordination) መኖሩ የግድ ነው። በተለይም ከጅምሩ በእነዚህ ተቋማት መካከል አላስፈላጊ የሆነ ፉክክር (competition) እንዳይኖር ማድረግ ያስፈልጋል።
- ስለሆነም ስኬታማ እና የተሟላ ሂደት እንዲኖር ለማስቻል የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን በሀገር-አቀፍ ደረጃ በባለቤትነት የሚያስፈፅም እና በአተገባበሩ ሂደት ላይ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግ፡ ኃላፊነት ያለባቸውን ተቋማት ሁሉ የሚያስተባብር አካል/አደረጃጀት መመስረት ያስፈልጋል።

**ሐ. ለመንግስት የቀረቡ ምክረ-ሃሳቦች**

በሀገር-አቀፍ ደረጃ ግብዓት በማሰባሰብ ሂደት ተሳታፊዎች በተደጋጋሚ ያነሷቸውን ስጋቶች ለመቅረፍ እና ለሚዘጋጀው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ገቢራዊነት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር የሚከተሉት ምክረ-ሀሳቦች ቀርበዋል።

- በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚስተዋሉ ግጭቶች ለማርገብ እና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማስቆም መንግስት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለበት። ለሰላም፣ ለሽግግር ፍትህ ትግበራ እና ለሌሎች የሰላም ግንባታ ሂደቶች ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ ተገቢ ነው።
- የሽግግር ፍትህ ትግበራውን ውጤታማ ለማድረግ ለማህበረሰቡ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ቀጣይነት ባለው መልኩ ማከናወን ያስፈልጋል።
- የሽግግር ፍትህ ትግበራ ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅ ሂደት በመሆኑ ከወዲሁ አስፈላጊ የዝግጅት ስራ የሚጀመርበትን ሁኔታ መቀየስ ያስፈልጋል።

- በምክክር ሂደቱ የተሳተፉ ተጎጂዎች በተለይም ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው ያልተመለሱ እና መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው ባልተሟሉበት ከባድ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ እንደመሆኑ መጠን ችግራቸው በዘላቂነት መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ለመሰረታዊ ፍላጎቶች እና የደህንነት ሁኔታዎቻቸው አቅም በፈቀደ መጠን አስቸኳይ መፍትሔ እንዲሰጥ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የዜጎች ደህንነት፣ ከቦታ ቦታ በነጻነት ተዘዋውሮ የመስራትና የመኖር ህገ-መንግስታዊ መብት ለአደጋ የተጋለጠበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ በተቻለ መጠን መንግስትም ሆነ ሌሎች ሀይሎች ለዜጎች ደህንነት እና ሰብዓዊ መብት መከበር ቅድሚያ በመስጠት አስፈላጊውን ስራ መስራት ይገባቸዋል፡፡

**ሐ. ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለመገናኛ ብዙሃን የቀረቡ ምክረ-ሃሳቦች**

ለፖሊሲው ተግባራዊነት ምቹ መደላደል ለመፍጠር እንዲቻል የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

- ለሽግግር ፍትህ ትግበራ ስኬት ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የሽግግር ፍትህ ጽንሰ-ሃሳቦችን እና ያልተገቡ ተስፋዎችን ወይም ግምትን ለማጥራት እንዲቻል ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ያለማቋረጥ ሊሰራ ይገባል፡፡
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደቱ ለተጎጂዎች እና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ድምጽ ሊሆኑ ይገባል፡፡
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተለያዩ የሽግግር ፍትህ ምዕራፎች ዝርዝር ስራዎች ትግበራ በንቃት መሳተፍ፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ቀጣይ ስራዎች በመከታተል የእርምት ሀሳቦችን መስጠት፣ እንዲሁም ለሽግግር ፍትህ ውጤታማ ተግባራዊነት ቀጣይነት ያለው የውትወታ ስራ ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

## አባሪዎች

-
-